

# በባቢሎን ወንዞች

ኔልሰን ደሚል

ትርጉም

ባሕሩ ዘርጋው ግዛው

CITY - HALL LIBRARY of ADDIS ABABA

ጥቅምት ፲፱፻፸፬ ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ለብወለድ
ግጥሚዎ
ፋ-7
24-2-92

ማስታወሻነቱ
ለውድ ባለቤቴ ለወይዘሮ የግሸንወርቅ አየሁ
ይሁንልኝ።

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።

ከአሁን በፊት የታተሙ
* የምሥጢሩ ቁልፍ
* ስምየለሽ

በንግድ ማተሚያ ቤት ታተመ

# ማስታወሻ

የሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎች ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ መተር ጐም ለጸሐፊዎችና ለአንባቢዎቻቸው ፣ ለቋንቋና ለሥነ ጽሑፍ ዕድ ገቶች በጣም አስፈላጊ ናቸው ። ላለፉት ምዕተ ዓመታት ሰዎች የጽ ሑፍ ችሎታቸው እንዲሻሻልና የሃሳብ አድማሳቸው እንዲሰፋ የትር ርጉም ሥራ በጣም ረድቷቸዋል ። በመሆኑም አንድ ሥነ ጽሑፋዊ ሥ ራን ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ መተርጐም ጠቃሚነቱ ስለታመነ በት በብዛት ተቀባይነትን እያገኘ መጥቷል ።

ዛሬ በዓለም ላይ በስፋት የሚነገሩ እንደ እንግሊዝኛ ፣ ፈረንሳይኛ ………የመሳሰሉት ቋንቋዎች አሁን ላሉበት ዕድገት የበቁት ከላቲን ፣ ከግሪክና ከሌሎችም ቋንቋዎች እየተተረጐሙ በሥራ ላይ በመዋላ ቸው ነው ። የእነሆመር ፣ ሼክስፒየር ፣ ቶሎስቶይ ፣ ድስቶቭስኪ … ሥራዎች ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች በመተርጐማቸው የዓለም አንባቢያን ውበታቸውንና ምሥጢራቸውን እያደነቁ ተምረውባቸዋል ፣ እየተ ማሩባቸውም ነው ።

የመጀመሪያው የትርጉም ሥራ የተካሔደው በ250 ዓመተ ዓለም አካባቢ ሊቪዩስ አንድሮኒከስ የተባለው ግሪካዊ የሆመርን ኦዲሴ ተርጉሞ ለአንባቢዎች በአቀረበበት ጊዜ ነበር ። ከዚያ ዘመን ጀምሮ ሥነ ጽሑ ፋዊ ሥራዎች በተባ የአጻጻፍ ዘዴ እየተተረጐሙ በሥራ ላይ ውለዋል ።

በአገራችን ውስጥ የማንበብ ባሕል ከጊዜ ወደ ጊዜ በብዛት እያ ደገ ስለመጣ የንባብ ጥማት ለአደረበት ሕዝብ ምርጥ ጽሑፎችን በፈ ጠራም ሆነ በትርጉም ለማቅረብ አለመሞከርና አለመጣር የተለሰነ ግድግዳ መሆን ነው ።

ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎችን ማቅረብ ተፈላጊና ተገቢ ከመሆኑም በላይ ወቅታዊ ስለሆነ በማንበብ ፍቅር የተማረከውን ሕዝብ በመጠ ኑም ቢሆን በማርካት ችሎታ ፣ ዕውቀትና ጥበብ ያስጨብጠዋል ብዬ

ያመንኩበትን በኔልሰን ደ ሚል “ ባይ ዘ ሪቨርስ ኦፍ ባቢሎን” ተብሎ የተጻፈውን መጽሐፍ “ በባቢሎን ወንዞች ” በሚል ስያሜ ተርጉሚ ጀባ ብያለሁ ። ይህ መጽሐፍ ብዙ የሕይወት ውጣ ውረዶች ያሉበትና በልብ ሰቃይነቱ ጨብጦ ይዞ የሚያውል ከመሆኑም ባሻገር በተፋላሚ ዎቹ ገጸ ባሕርያት መካከል ስለ ሀገር ፍቅር ያለውን ጀግንነትና በቆራጥነት የሚከፈለውን መስዋዕትነት ስለሚያሳይ ትምህርት ይሰጣል ብዬ አምናለሁ ።

ትርጉም ሳይንስ ስለሆነ በሚቻል መጠን የደራሲው ኪነ ጥበባዊ ሕይወት እንዳይጐድፍ በመጨነቅና በመጠበብ ደራሲውን ሆኜ ይህን መጽሐፍ ወደ አማርኛ ተርጉሜ ለአንባቢያን አቅርቤአለሁ ።

በዚህ አጋጣሚ ደራሲ ኔልሰን ደ ሚልን ሳላመሰግን አላልፍም ።

ባሕሩ ዘርጋው ግዛው

ትግላችን በመጠኑ ጀምሯል ። እጅግ በጣም አስከፊው ግን መምጣት አለበት ። ሰላም ሊኖር እንደማይችል ለአውሮፓና ለአሜሪካ መነገር ያለበት ወቅቱ አሁን ነው . . . ሦስተኛው የዓለም ጦርነት መነሻና ምላጭ መሳቢያ መሆኑ አያስጨን ቀንም ። ዓለም ሲጠቀምብን ቆይቷል ፣ እናም ረስቶናል ። የእኛን መኖር ማሳወቂ ያው ጊዜ አሁን ነው ። የሚከፈለው መስዋዕትነት ምንም ይሁን ምን ትግላችንን እን ቀጥላለን ። ያለ እኛ ፈቃድ ሌሎች አረቦች ስለ እኛ ሊያደርጉት የሚችሉት ጉዳይ የላቸውም ። ለሰላም ድርድር ፈጽሞ አንቀርብም ። አረቦች ለማድረግ ለሚያቀዱት ሁሉ የእኛ መካፈል ወሳኝ ነው ።

ዶክተር ጆርጅ ሀባሽ

የፍልስጥኤም ነፃ አውጭ

ሕዝባዊ ግንባር መሪ

እኛ ይሁዳውያን ከገጸ—መሬት ላይ ለመጥፋት አሻፈረኝ አልን ። የደረሰብን አሰቃቂና ኢሰብአዊ ድርጊት የፈለገውን ያህል አስከፊ ቢሆንም አሁን ባለንበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን ። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰውነቶች ተሰባብረዋል ፣በሕ ይወት ተቀብረዋል ፣በእሳት ተቃጥለዋል ።ይሁን እንጂ የይሁዳውያንን አላማ ለመ ስበር የቻለ አንድም የለም ።

ጉልዳ ሜየር

ጥር 19 ቀን 1976

# ፈረንሳይ - ቅዱስ ናዛየር

ኑሪ ሳላሜ ለማጅ የኤሌክትሪክ ሠራተኛ ነው ። የለበሰውን ነጭ ካፖርቱን ኪስ እንደገና ደባበሰ ። በትልቁ አኤሮስፔሻል ተቋም ውስጥ በሚቀጥለው ስለሚወስደው እርምጃ እርግጠኛ ባለመሆን ጐብደድ ብሎ ቆመ ። በአካባቢው የነበሩ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ አልጀሪያውያን የሥራ መውጫቸው ጊዜ ስለደረሰ ለመሔድ እያዘገሙ የሰዓቱን መደ ወል ይጠባበቃሉ ።

በመሰናበት ላይ የነበረችው የፀሐይ ብርሃን ከአቧራው ጋር በመ ዋሀድ ባለስድስት ፎቆች በሆነው ሕንጻ የመስታወት መስኮቶች ላይ በመንፀባረቅ በተፈጠረው ሙቀት ምክንያት ከሳላሜ የሚወጣው ትን ፋሽ በመስታወቱ ላይ ጉም ጥሎአል ።

ከተቋሙ ውጭ የአየር ማረፊያው መብራቶች ደምቀው ይታያሉ ። ሰማያዊ ቀለም ያሏቸው ሚራዦች በአየር ማረፊያው ሜዳ ላይ ተሰል ፈው ቆመዋል ። እንደዚሁም የአኤሮስፔሻል ተቋም ሠራተኞችን የመ ኖሪያ ሠፈራቸው ወደሆነው ወደ ቅዱስ ናዛየር ከተማ የሚያጓጉዙ አው ቶቡሶች ቦታቸውን መያዝ ጀምረዋል ።

በተቋሙ ውስጥ በተጨማሪ የተሠሩት የፍሎሬሰንት መብራቶች ደብዘዝ ያለ ብርሃን አልጀሪያዊው ሳላሜን ፍርሃት አሳድሮበታል ። ሳላሜ ዙሪያውን ለመቃኘት በፍጥነት ዘወር ብሎ ሲመለከት አንድ የአ ገሩ ተወላጅ ሲያልፍ በውልብታ ታየው ። ሳላሜ እንዳይታይ ተጠንቅቆ በፍጥነት ወለሉን አቋርጦ አለፈ ።

በፊት ለፊቱ አንድ ትልቅ ኮንኮርድ በብረት ተሸካሚው ላይ ተቀ ምጧል ። ሠራተኞች የሚተላለፉባቸውና ቆመው የሚገጣጥሙባቸው ርብራቦች በአውሮፕላኑ ጐኖችና ክንፎች ሥር ተሠርተዋል ። በከፊል ያልተጠናቀቁትን የአውሮፕላኑን ክፍሎች ለመጨረስ ጉንዳኖች በሞተ ተርብ ላይ ተሰብስበው እንደሚሽሙ ዓይነት ሠራተኞች ከወዲያ ወዲህ ይሯሯጡ ነበር ።

ሳላሜ በመሰላሉ ላይ ከወጣ በኋላ በርብራቦቹ ላይ አጐንብሶ 12 ሜትር እርዝመት ወዳለው የጅራቱ ክፍል ሔደ ። ቀለም ባልተቀባው የአውሮፕላን ጅራት ላይ የፋብሪካው ቁጥር ታትሞበታል ።

ሰውየው ሰዓቱን ሲመለከት ተረኛ ሠራተኞች በሚቀጥሉት 10 ደቂቃዎች ውስጥ መሔድ እንደነበረባቸው ተገነዘበ ። ተተኪ ሠራተኞች መጥተው የአውሮፕላኑን ጅራት ክፍል ገጣጥመው ከማሸጋቸው በፊት አሁኑኑ ተልዕኮውን መፈፀም አለበት ። በዚያ ተሰቅሎ የነበረ የሥራ ሒደቶች የሚመዘገቡበት ወረቀቶች የተለጠፉበትን ሠሌዳ አውርዶ በፍጥነት ተመለከተ ። ከትከሻው ዘወር ብሎ አቆልቁሎ ሲመለከት አንድ አልጀሪያዊ ቀና ብሎ ካየ በኋላ ብረታ ብረቶች አንስቶ ሲሔድ አየው ።

ሳላሜ በድንጋጤ በፊቱ ላይ ችፍ ያለበትን ላብ በእጅጌው ከጠረገ በኋላ በሁለቱ መወጣሪያዎች መካከል ሥራው ተገጣጥሞ ወዳላለቀው የአውሮፕላን የኋላ ክፍል አጐንብሶ ሔደ ። የአውሮፕላኑ ጅራት ክፍል የተገጣጠሙው ብረቱ እየቀለጠ ነበር ። ከአንዱ መወጣሪያ ወደሌላው እየተንጠለጠለ በመሔድ ቁጥሩ 11 በሆነው የነዳጅ መያዣ አጠገብ በከፊል ወደ አላለቀው ክፍል አመራ ። ተሳፋሪዎች በሚቀመጡበት ክፍል ውስጥ የፍሎሬሰንት መብራት መስመር ተዘርግቷል ። እንደዚሁም ወደ ጅራቱ ክፍል የተዘረጋ የኤሌክትሪክ ሽቦ ቢኖርም ሳላሜ አላበራውም ። ጥቂት ደቂቃዎች በጨለማው ውስጥ ከተንፏቀቀ በኋላ በከፊል ወዳላለቀው የጅራቱ ክፍል ደረሰ ።

ራቅ ብሎ በተሳፋሪዎች ክፍል ውስጥ የነበረ አንድ ሰው ስላየ ጉሮሮውን ካፍታታ በኋላ "ተቆጣጣሪ ላቫሌ" ብሎ ጠራው ።

የተሠሩ ሥራዎችን በመቆጣጠር ላይ የነበረው ረጅም ፈረንሣዊ በአደጋ ጊዜ ከሚወጣበት በር አጠገብ ተመልሶ ወደ ሰውየው ሔደ ። አልጀሪያዊውን የሚያውቀው መሆኑን ለማስገንዘብ ፈገግ ካለ በኋላ "ሳላሜ ፣ አይጥ ይመስል ራስህን ለምን በጨለማ ውስጥ ትሸሽጋለህ ?" ብሎ ጠየቀው ።

አልጀሪያዊው ራሱን አስገድዶ ፈገግታ በማሳየትና የያዘውን ወረቀት የተሰፋበትን ሠሌዳ እየተመለከተ " ሥራው ስላለቀ ለመዘጋት ተዘጋጅቷል ፤ አይመስልህም ? " ብሎ ጠየቀው ።

ሔንሪ ላቫሌ ጐንበስ ብሎ ኃይለኛ ብርሃን ባለው የእጅ መብራት የጅራቱን ክፍል በዐይኑ ገረፍ አድርጐ አየ ። ቀጥሎም ከሳላሜ ላይ ወረቀት የተለጠፈበትን ሠሌዳ ወስዶ ወረቀቶቹን በፍጥነት ገልበጥ ፣ ገልበጥ እያደረገ ተመለከታቸው ። እነዚህ አልጀሪያውያንን በትክክል የምርመራ ሥራ ያካሒዳሉ ብሎ ማመን አይቻልም የሚል ሐሳብ ስለ አደረበት ተቆጣጣሪ ላቫሌ እያንዳንዱን ገጽ እንደገና ተመለከተ ። እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ ስለኤሌክትሪኩ ፣ ስለኃይድሮሊኩና ስለነዳጅ መያ

ዦው የሰጠው አስተያየት ትክክል እንደነበረ አረጋገጠ ። የራሱንም አስተያየት በመጨመር "የምርመራ ሥራዎች በትክክል ተከናውነ ዋል " ብሎ መልሶ ሰጠው ።

" እኔንስ የሚመለከተው የኤሌክትሪክ ሥራ ? " ብሎ ሳላሚ ጠየ ቀው ።

" አዎን ፡ አዎን ፤ አንተም በጣም ጥሩ ሠርተሀል ። መገጠም ይች ላል " ብሎ የወረቀቱን ሠሌዳ ለአልጀሪያዊው መልሶ መልካም ምሽት እንዲሆንለት በመመኘት ትቶት ሔደ ።

ሳላሚ " አመሰግናለሁ ፡ ተቆጣጣሪ" ካለው በኋላ ወረቀት የተ ሰፋበትን ሠሌዳ እንደገና በመታጠቂያው ላይ አንጠለጠለው ። ከዚያ ዞሮ እያደባ በጥንቃቄ በተሽካሚው ላይ በሚሔድበት ጊዜ በስውር በት ከሻው ላይ ተመልክቶ ተቆጣጣሪ ላቫሌ መሔዱን አረጋገጠ ። ሳላሚ የኤሌክትሪክ ሠራተኞቹ እቃዎቻቸውን ሰብስበው ከአውሮፕላኑ ክፍል ወጥተው በመሰላሉ ላይ ሲወርዱ ድምጻቸውን ሰማ ። አንድ ሰው በተ ሳፋሪዎች ክፍል ውስጥ ያለውን መብራት አብዛኛውን ስላጠፋው ወገ ግታ የነበረው የጅራቱ ክፍል በበለጠ ጨለመ ።

ሳላሚ የእጅ መብራቱን አብርቶ ክፍት ወደሆነው ወደ ጅራቱ ክፍል ተመለከተ ። ቀጥሎም ባጥንቃቄ እየተራመደ ሁለቱ የአውሮፕ ላኑ ጅራቶች ወደተጋጠሙበት ደረሰ ። ከኪሱ ውስጥ የራሱ ቁጥር ያል ሆነ የተጻፈበት ከክብሪት መያዣ ያነሰ አንድ ጥቁር የኤሌክትሪክ ሳጥን አወጣ ።

ከላይኛው ኪሱ ፈሳሽነት ያለው ማጣበቂያ አውጥቶ በማፍረጥ በአሉሚኒየሙ ላይ ከቀባ በኋላ ሳጥኑን በአውሮፕላኑ ጐን ላይ አጣብቆ ለትንሽ ሴኮንዶች ያዘው ። ከኤሌክትሪክ ሳጥኑ ውስጥ የቴሌስኮፕ አን ቴና በማውጣትና በማሽከርከር ከጅራቱ ጐን ካለው ብረት ጋር በግልጽ ትይዩ እስኪሆን ድረስ አስተካከለው ።

በጠባቡ ክፍል ውስጥ ይሠራ የነበረው ተጨንቆና ተኮረማምቶ በመሆኑ በክፍሉ ውስጥ ሙቀት ባይኖርም በፊቱ ላይ ላቡ ተንጠባ ጠበ ።

ብርሃን በመስጠት ለበረራ እንዲያገለግል ወደ ጅራቱ የተዘረጋ ውን በአረንጓዴ ቀለም የተሸፈነውን ሽቦ በኤሌክትሪክ ሴንጢ በመ ሰንበጥ ተመሳሳይ ሽቦ ከኪሱ አወጣ ። ካወጣው ሽቦ በአንደኛው ጫፍ ላይ ከብረት የተሠራ አንድ ትንሽ ክብ ነገር ነበረው ። ሌላው ጫፍ ደግሞ ያልተሸፈነ የመዳብ ሽቦ ነበር ። የመዳቡን ሽቦ ወደጅራቱ ከተ ዘረጋው ሽቦ ጋር ቀጥሎ በጥንቃቄ ፈተለው ።

ከዚህ በኋላ ሳላሚ ብዙ ቀለማት ካላቸው ሽቦዎች ጋር ቀላቅሎ ቁጥሩ 11 እሆነው ነዳጅ መያዣ ድረስ ዘረጋው ። ይህን በሚያደር ግበት ጊዜ አልፎ አልፎ ባልተዘጉ ቀዳዳዎች ውስጥ ሠራተኞች ለመ ሔድ ሲንቀሳቀሱ ራሳቸውን ስላየ ያሰመጠው ላብ ተንጠባጥቦ በእነ ርሱ ላይ ያረፈ መስሎት ፍርሃት ወረረው ። እርሱን ግን ቀና ብሎ የተ መለከተው አልነበረም ።

ሳላሚ ግማሽ ኪሎ ክብደት ያለው ቀለሙ ነጭ የሆነ እንደሙጫ የሚያጣብቅ ነገር ከሌላው ኪሱ አውጥቶ በቁጥር 11 የነዳጅ መያዣ ላይ ካጣበቀው በኋላ ስቦ ያመጣውን በጫፉ ላይ ድቡልቡል ብረት ያለ በትን ሽቦ በላቆጠው ነጭ ማጣበቂያ ላይ ገፍቶ አያያዘው ። ወደዚያው ሠራተኞች የመቀያየሪያ ጊዜያቸው መድረሱን የሚያመለክተው ደወል በኃይል ስለጮኸ አስደነገጠው ።

ሳላሚ በፊቱና በአንገቱ ላይ የነበረውን ላብ በፍጥነት ጠርጐ ከጨለማው የአውሮፕላን ክፍል ወጥቶ በተሽካሚው ብረት ላይ ወደነ በሩት ርብራቦች ዘሎ ሲወርድ ሰውነቱ ይንቀጠቀጥ ነበር ። ይህን ሁሉ ሥራ ለመጨረስ የፈጀበት ጊዜ ከአራት ደቂቃዎች ያነሰ ነበር ።

ተቀይረው ለሥራ ከመጡት ሁለት ሠራተኞች እርሱ እነበረበት ቦታ እስኪደርሱ ድረስ ሰውነቱ መንቀጥቀጡን አላቆመም ነበር ። እነ ርሱም በጉጉት ተመለከቱት ። ከሁለቱ ሠራተኞች አንዱ ፈረንሳዊ ፡ ሌላው ደግሞ አልጀሪያዊ ነበሩ ። የአልጀሪያው ተወላጅ በፈረንሳይኛ “ዝግጁ ነው ?” ብሎ በመጠየቅ እጁን ዘረጋ ። ሳላሚ ሁለቱም ሰዎች በቀበቶው ላይ ባንጠለጠለው ወረቀት በተሰፋበት ሰሌዳ ላይ ዓይኖ ቻቸውን ተክለው እስኪያያቸው ድረስ ተደናግሮት ነበር ። አስተያየ ታቸውን ከተመለከተ በኋላ በፍጥነት ከቀበቶው ላይ አውልቆ በመስ ጠት “አዎን ፡ አዎን ፡ ኤሌክትሪኩም ሆነ ሌሎቹ በሙሉ ስለተመረ መሩ መዘጋት ይችላሉ” አለው ።

ሁለቱ ሰዎች የምርመራውን ውጤት በወረቀቱ ላይ ካዩ በኋላ የአ ዎንታ ንቅናቄ አሳዩት ። ቀጥለውም የቀሩት ሥራዎች የሚገጣጠሙ በትን መሣሪያ አዘጋጁ ። ሳላሚ የሚብረከረከው ጉልበቱ እስኪበረታ ድረስ ከተመለከታቸው በኋላ በመሰላሉ ላይ ወርዶ በሰዓት መፈረሚ ያው መዝገብ ላይ ፈረመ ።

ኑሪ ሳላሚ ከሠራተኞቹ ጋር ተሳፍሮ ወደቅዱስ ናዛየር በሚሔድ በት ጊዜ ሌሎቹ የሥራ ባልደረቦቹ የወይን ጠጅ ጠርሙሶቻቸውን እየ ከፈቱ ሲጠጡ ትንፋሽ ሳያሰማ በጽሞና ተመለከታቸው ። መሐል ከተ ማ ሲደርሱ ከአውቶቡሱ ወርዶ ወደመኖሪያ ቤቱ ሔደ ። እቤቱ እንደ

ደረስ ለሚስቱና ለአራት ልጆቹ በአረብኛ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ ብርቱ መልዕክት አድርሶ እስኪመጣ ድረስ ራት የሚበሉበት ጊዜ እን ዲዘገይ ነገራቸው ።

ብስክሌቱን ካቆመበት ከጨለማ ክፍል ውስጥ እየገፋ ወደ መንገዱ ካወጣ በኋላ የሎይር ወንዝ ወደሚገናኝበት የቢስኬይ ባሕር ወሽመጥ እየነዳ ሔደ ። ከድካሙ የተነሳ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ከአፉ የሚወጣው ትንፋሽ ቀዝቃዛ ነበር ። በተጨማሪም የብስክሌቱ ጐማ በቂ ነፋስ ስላልነበረው በኮረኮንቻው መንገድ ላይ ሲሔድ ብስክሌቱ ይንገጫቀጭ ስለነበረ ተማረረ ።

ጀርመኖች በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ከአንድ በኩል የባ ሕሩን ድምበር በማድረግ ቦምብ እንኳን ሊያፈነዳው የማይችል ትል ቅና ረጅም ዋሻ ሠርተውበት ወደነበረው ቦታ ብስክሌቱን እየነዳ ሲደ ርስ ጨልሞ ነበር ። ዋሻው ሠርዶና ሌላም ሳር በቅሎበት ስለነበረ በው ስጡ እንደልብ ለመሔድ አይቻልም ነበር ። ሳላሜ ብስክሌቱን እየገፋ በዋሻው ደረጃዎች ላይ ወርዶ ብስክሌቱን አስጠግቶ በማቆም ሲመለ ከት የናፍታና የረግረግ ሳር ብስባሽ ሽታ አፍንጫውን ሰነፈጠው ። እዚያው ቆሞ ትኩር አድርጐ ሲመለከት በሸበተው ግድግዳ ላይ በጀ ርመንኛ የተጻፉ ቃላትና ቁጥር 8 የሚል አየ ። ሳላሜ ቀስ ብሎ በመቅ ረብ የውስጠኛውን ዋሻ መዝጊያ ከፍቶ ገባ ።

በዋሻው ውስጥ ውሀው ከግድግዳው ጋር ሲላተም የሚሰጠውን ድምጽ ሰማ ። ከባሕሩ በኩል ካለው ፋኳ ከውሀው እየተንጸባረቀ ከሚ መጣው ብርሃን በስተቀር ሌላ አልነበረም ። ሳላሜ የብርሃን ብልጭታ ወደአለበት በሚሔድበት ጊዜ በእርጥብ አዘሉ አየር ምክንያት ኃይ ለኛ ብርድ ስለተሰማው ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ ። ሊያስለው የነበረውን ለብዙ ጊዜ አምቆ አስቀረው ።

በድንገት የእጅ መብራት ብርሃን በዓይኖቹ ላይ ብልጭ ስለተደ ረገበት "ሪሽ" ብሎ ካንሾካሾከ በኋላ በድጋሚ "ሪሽ ነህ ? " ብሎ ጠየ ቀው ።

አህመድ ሪሽ የእጅ መብራቱን አጥፍቶ " የታዘዝከውን ፈጸምክ፤ ሳላሜ ? " ብሎ በአረብኛ ጠየቀው ።

ኑሪ ሳላሜ በዚያ ዋሻ ውስጥ ሪሽ ብቻውን እንዳልነበረና ሌሎች ሰዎችም እንደነበሩ ስለተሰማው ተጨነቀ ። "አዎን " ብሎ መለሰለት ።

"አዎን ነው የምትለው?" ብሎ አህመድ ሪሽ እንደገና ሲጠይቀው ከድምጹ አጣጣል የብቀላ ደስታ ያለበት ይመስል ነበር ።

ሳላሚ ቀኑን ሙሉ ሲመለከቱት የዋሉት የአልጀሪያዊው ጥቁር ዓይኖች የፈረንሣዊውና የሌሎቹም አስተያየቶች በድንገት በፊቱ ላይ ድቅን ያለበት በዚህ ጊዜ ነበር ።

" ምርመራዎቹ አልቀዋል ፡ የአውሮፕላኑ ጅራት ክፍልም ተፈትሾ ስላበቃ ዛሬ ማታ ተገጣጥሞ ይዘጋል ? " ብሎ ሪሽ ሲጠይቀው መልሱን እንደሚያውቀው ሰው ሆኖ ነበር ።

" አዎን " አለው ሳላሚ ።

" ራዲዮኑን በትክክል መቀመጥ በሚገባው በአውሮፕላኑ ጅራት ውስጥ አስቀምጠኸዋል ? "

" በትክክል አስቀምጬዋለሁ ፡ አህመድ ። "

" ጥሩ ፡ አንቴናውስ ? "

" አንቴናውንም በሚገባ ስቤና አስተካክየ አስቀምጬዋለሁ ። "

" አያይዘኸዋል ? ራዲዮኑ ከአውሮፕላኑ ባትሪዎች ያለማቋረጥ እንዲሞላ አስተካክለኸዋል ? "

ሳላሚ በአዕምሮው ውስጥ የሚከተለውን ለብዙ ጊዜ ደጋግሞ አብላላ — " ክሩ የተያያዘው በአውሮፕላኑ ጅራት ላይ ኤሌክትሪክ ከሚያስተላልፈው ሽቦ ጋር ነው ። የተዘረጋውን ሽቦ በምርምር ለይቶ ለማወቅ አይቻልም ። የሽቦው ቀለም ሳይቀር አመሳስየዋለሁ ። ማንም ሰው ራዲዮኑን ማየት አይችልም ። ድንገት እንኳን ቢሞክር የፋብሪካውን ዕቃ የሚያሳይ ቁጥር በራዲዮኑ ላይ ለጥፌበታለሁ ። የኤሌክትሪክ መሐንዲስ ብቻ በዚህ ሥራ ሊታለል አይችልም ። ሌሎች ጠጋኝ ሠራተኞች ሊያዩት አይችሉም ። ቢያዩትም የአውሮፕላኑ አካል ነው ብለው ያልፉታል ። "

ሪሽ " እጅግ በጣም ጥሩ — እጅግ በጣም ጥሩ " በማለት ራሱን በአዎንታ የሚያነቃንቅ መሰለ ። ሪሽ ለጊዜው ንግግሩን አቀብ ቢያደርግም ሳላሚ የሰውየውን አተነፋፈስ ከመስማቱም በላይ ከአፉ ቡልቅ እያለ ይወጣ የነበረው እርጥበት አዘል ትንፋሽ ወደ አፍንጫው ደረሰ። ሪሽ እንደገና " በኤሌክትሪክ አማካኝነት የሚፈነዳው ከሌላው ጫፍ ጋር በትክክል ተያይዟል ነው የምትለኝ ? " ብሎ ጠየቀው ።

" በሚገባ" ብሎ ሳላሚ መለሰለት ።

" ፕላስቲኩስ ? " በማለት ፈረንሣዮች ለፈንጂ የሚጠቀሙ በትን ቃል ተናገረ ።

ሳላሜ ያደረገውን በሐሳቡ አወጣ አወረደ — "በነዳጅ መያዣው ጫፍ ላይ እንዳይላቀቅ አድርጌ አጣብቄዋለሁ ። የነዳጅ መያዣው በዚያ ባደረኩበት ላይ ትንሽ ክብ አለው ። ፈንጂው በነዳጅ መያዣው ክብ ውስጥ 10 ሴንቲ ሜትር ጥልቀት ያለው ሲሆን በትክክል በባትሪው እንዲሞላ አድርጌዋለሁ — " እያለ የሠራውን ሁሉ ካስታወሰ በኋላ የቀዘቀዘ ከንፈሩን በምላሱ ላሰ ። ሳላሜ ለእነዚህ ሰዎችም ሆነ ለምክ ንያታቸው ርኅራኄ የለውም ። ነገር ግን ትልቅ ወንጀል እንደፈጸመ አወቀ ። ከመጀመሪያው በዚህ ዓይነት ነገር ውስጥ ራሱን የማስገባት ምኞት አልነበረውም ። ነገር ግን እንደ ሪሽ አባባል ማንኛውም አረብ የደፈጣ ተዋጊ ነው ። ከሞሮኮ ፥ ካዛብላንካ 5 ሺ ኪሎ ሜትር አቋርጦ እስከ ባግዳድ ድረስ ባለው እንደረሞጫ እሳት በሚያቃጥለው ምድረ— በዳ ውስጥ የሚኖሩ ሁሉ የደፈጣ ተዋጊዎችና ወንድማማቾች ናቸው ። ቁጥራቸውም ከ100 ሚሊዮን በላይ ይሆናል ። ሳላሜ ግን በዚህ አባ ባል አንድ ቃል እንኳን አያምንም ። ይሁን እንጂ ወላጆቹና እህቶቹ አሁንም በአልጄርስ ውስጥ ስለሚኖሩ ይህን ሥራ እንዲሠራ ተገደደ። "የተሰጠኝን ሥራ በሚገባ በማከናወኔ ኩራት ይሰማኛል " አለ ሳላሜ የቆመውን ንግግር እንደገና ለመጀመር ። ሆኖም ይህ ንግግሩ ፋይዳ ቢስ እንደነበረ ተገንዝቧል ። እነዚህ ሰዎች ይህንን ነገር እንዲያደርግ የጠየቁት ዕለት የመኖር ዕድሉ እንዳከተመ በድንገት በአዕምሮው ውስጥ ብልጭ አለበት ።

ሪሽ በአዕምሮው ውስጥ ያውጠነጥን የነበረው ስለሌላ ጉዳይ ስለ ነበረ የሳላሜን ንግግር የሰማው አልመሰለም ። " ፈንጂው ፥ በትክ ክል ከነዳጅ መያዣው በርሜል ቅርጽ ጋር በሚገባ ተስተካክሎ ተጣብ ቋል ብለህ ታምናለህ ? ምናልባትም በአሉሚኒየም ቀለም እንድትቀ ባው መንገር ነበረብን " ብሎ በሐሳብ እየዋለለ ጠየቀው ።

ሳላሜ የሰውየውን ጥርጣሬ ለማስወገድ ከፍተኛ ስሜት ስላደረ በት"ማንም ሰው ወደዚያ እንደገና ለሥራ አይሔድም ። ፍጹም እንደ ማይታወቅ ተደርጐ ተለትሟል ። ችግር ሲያጋጥም ብቻ ነው ያንን የተ ለጠፈውን ማንሳት አስፈላጊ የሚሆነው ። ይህ ካልሆነ በስተቀር ያ የነዳጅ መያዣ ያለበት ክፍል በምንም ዓይነት ከአሁን በኋላ ተከፍቶ አይታይም" በማለት አረጋገጠለት ። ሳላሜ በሪሽ በስተጀርባ ባለው ጨለማ ውስጥ ቢያንስ ሦስት ሌሎች ሰዎች መኖራቸውን ትዕግሥት በሌለው አተነፋፈሳቸው ለማወቅ ቻለ ። የዋሻው መጨረሻ ሙሉ በሙ ሉ ጨለማ ሆኖአል ። አልፎ አልፎ የመርከብ ጥሩምባና የውሀው ግፊት ከዋሻው ግድግዳ ጋር የሚያደርገው ድምጽ ይሰማ ነበር ።

ሪሽ አንድ ነገር አጉተመተመ ። በዚህ ጊዜ ሳላሜ መቅሰፍት እንደ ሚደርስበት ተረዳ ። በእኔ ላይ መጥፎ ነገር ባያስቡ ኖሮ በጥሩ ቤቶች

ውስጥ ወይም በሌላ ቦታ ሊያነጋግሩኝ ሲችሉ ለምን ወደዚህ ጨለማ ወደሰፈነበትና ምንም ነገር ዝር ወደማይልበት እንድመጣ ተደረገ? ይህ የገመተው ጽዋ እንዳይደርስበት ሰውየውን ለማግባባትና ለማ ባበል “ አንተ እንደተመኘኸው ወደ ቱሉስ ከተማ ለመዛወር ጥያቄ አቅርቤአለሁ ። እንደሚፈቀድልኝም እርግጠኛ ነኝ ። በዚያም በሌላው አውሮፕላን ላይ የዚሁ ዓይነት ድርጊት እንድፈጽም ቢፈቀድልኝ ክብር ይሰማኛል ” ብሎ ነገረው ።

ሪሽ ያሰማው የፌዝ ሳቅ በሳላሜ ጀርባ ላይ ላብ ኮለል ብሎ እንዲ ወርድ አደረገው ። የነበረው የመኖር ተስፋም ሲንጠፈጠፍ ተሰማው ። “ መሔድ አያስፈልግህም ወዳጄ ፤ በዚያም የሚደረገው ቅንብር ተጠ ናቋል ። ብጤህም በዚህ ቦታ ላይ ሰውነቱ በሰላም እንዲያርፍ ተደር ጓል ። ሌላውም ይህንኑ ዕጣ አሁን ያገኛል ” የሚል ድምጽ ከጨለማው ውስጥ ተሰማ ።

ሳላሜ ምላሱ ተሳስሮ “በእርግጥ . . ” ብሎ ለመናገር ሲሞክር የሪሽን ጭብጨባ ሰማ ።

ከመቅጽበት ሳላሜ በብዙ እጆች ተይዞ ከግድግዳው ጋር ከተጣጋ በኋላ ቀዝቃዛ ስለት በጉሮሮው ላይ ሲያርፍ ተሰማው ። አፉን ጭምር አፍነው ይዘውት ስለነበር መጮህም ሆነ መንፈራገጥ አልቻለም ። ደጋግመው ስለቱን በጉሮሮውና በልቡ ላይ ስለሻጡበት ትኩስ ደም በቀዘቀዘው ሰውነቱ ላይ እየተንደቀደቀ ሲፈስ ተሰማው ። እንደገናም በአከርካሪው ላይ ተወጋ ። ሳላሜ ደመነፍሱን ለመንፈራፈር ቢሞከ ርም አልሆነለትም ። በሐሳቡ ለራት የሚጠብቁትን ሚስቱንና ልጆ ቹን አስታወሰ ። በመጨረሻም ልቡን ደጋግመው ስላረሱት ከስቃዩ ተገ ላገለ ።

ቦርሳውንና ሰዓቱን ከወሰዱ በኋላ የሥራ ጫማውንና ልብሱን አውልቀው ኪሱን ጭምር በረበሩ ። በድኑን በዋሻው ፉካ አጠገብ ወዳ ለው ጥቁርና የረጋ ውሀ ሲወስዱት ድምጽ ሰምተው ለመመገብ የሚ ሯሯጡ የውሀ ውስጥ አውሬዎች ወዳሉበት አካባቢ ስለጣሉት ተሻ ምተው ተቀራመቱት ።

ፊታቸውን የሸፈኑ ሰዎች ለመጨረሻ ጊዜ የቀረውን ሥራ ለማ ጠናቀቅ አውቶማቲክ የቀለም መርጫ ይዘው ወደ ኮንኮርዱ ውስጥ ገቡ ። ሥራቸውን እንደጨረሱ እስ የሚል ድምጽ የሚሰጠው የመ ርጫ መሣሪያ አቆመ ። ትልቁና ጨለማው ክፍል የተቀባውን ቀለም ለማድረቅ በኤሌክትሪክ ኃይል እንዲግል ስለተደረገ ከተቀባው ቀለም የሚወጣው እንፋሎት እንደጉም ሆኖ ክፍሉን ሸፈነው ። ከጥቂት ጊዜ

በኋላ ግን አየር በሚመጥ መሣሪያ ጉሙ ከክፍሉ ውስጥ እንዲጠፋ ተደረገ ። ቀደም ብሎ በእንቅስቃሴና በድምጽ ተሞልቶ የነበረው ክፍል አሁን ጸጥታ ሰፍኖበታል ። እንደዚሁም በግለት ፍም መስሎ የነበረው ክፍል የኤሌክትሪኩ ኃይል ሲጠፋ ቀስ በቀስ እየጨለመ መጣ ። ቀጥሎም በመቶ የሚቆጠሩ የፍሎሬሰንት መብራቶች ስለበሩ ክፍሉ በብርሃን ተሞላ ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ነጭ ቱታ የለበሱ ሁለገብ ሠራተኞች ወደ ቅዱስ ቦታ እንደሚገቡ ሆነው በጸጥታ በመሰለፍ ግርማ ሞገስ ያለውን ሸንጠ ረጅም ወፍ አሸቅበው ለጥቂት ሴኮንዶች ተመለከቱት ። ኮንኮርዱ በረጅም ጉማ አቃፊዎች ላይ በኩራት ቆሞ ሰውን ናቂ እንደነበረው የጥንት ብርቃማ ወፍ አቀልቁሎ የሚመለከታቸውና በአባይ ወንዝ ላይ የሚመለክበት የተከበረ ቦታ መስሎ ታያቸው ።

ሰዎቹ ማተሚያዎችና የቀለም መርጫ መሣሪያዎች ተሸክመውና 200 ሊትር ክፍት ሰማያዊ ቀለም ይዘው በሞተር በሚንቀሳቀስ መሰ ላል ላይ ሆነው ወጡ ። አንድ ሰዓሊ ደብዝዞ የነበረውን የፋብሪካውን ቁጥር የበለጠ ጉልቶ እንዲታይ አስተካክሎ አተመው ። ከአሁን በኋላ የፋብሪካው ቁጥር ቋሚ ዓለም አቀፋዊ የምዝገባ ቁጥር ይሆናል ። የብ ሔራዊ ባለቤትነትና የተጠቃሚነት ዓለም አቀፋዊ ስያሜ ለመስጠት የሚያስችለውን ቁጥር በተጨማሪ አተመ ። ከዚያም የአውሮፕላኑ መለያ የሆኑ ፊደላትን ጻፈ ።

ሁለት ሰዓሊዎች ከፍ ብለው በመሰላሉ በመውጣት ነጭ ቀለም በተቀባው ጅራቱ ላይ በክፍት ሰማያዊ ቀለም በስሩ ኤል አል የሚል ያለበት ስድስት ጫፎች ያሉት የዳዊት ኮከብ አተሙበት ።

# ክፍል አንድ

## እስራኤል — የሻሮን ሜዳ

የወገኔንም ልጅ መቀጥቀጥ በሐሰት ይፈውሳሉ እንዲህ ሲሉ
ሰላም ሰላም ። ሰላምም አልሆነም ።

ኤርምያስ 6፡14

ሕዝቤን አስተዋልና እንዲህ ሲሉ ። ሰላም ሰላምም ፤
የለም . . .

ሕዝቅኤል 13፡10

## — 1 —

ጐህ ከመቅደዱ ቀደም ብሎ አራት ሰዎች በሰማሪያ ተራራ ላይ ቆመው አቆልቁለው የሻሮንን ሜዳ ይመለከታሉ ። ዘጠኝ ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ የተንጣለለው የሎድ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ መብራቶች በግልጽ ይታዩአቸዋል ። ከሎድ ባሻገር የቴል አቪቭና የሔርዝላ መብራቶች ደብዝዘው ይታያሉ ። ከዚያም ባሻገር የሜዲትራኒያን ባሕር በመጥለቅ ላይ የነበረችውን የጨረቃ ብርሃን ያንጸባርቃል ።

የቆሙበት ቦታ እስከ ስድስቱ ቀን ጦርነት ድረስ የዮርዳኖስ ግዛት ነበር ። በ1948 ጦርነቱን ለማቆም በተደረገው ስምምነት መሠረት ወሰኑ ከሻሮን ሜዳ ግማሽ ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ስለነበረ በ1967 በተደረገው ጦርነት የሰማሪያ ተራራ መያዝ ለእስራኤል አማራጭ የሌለው ጉዳይ ሆነ ። ከ1967 ጦርነት ወዲህ በሎድ አየር ማረፊያ አቅራቢያ የዮርዳኖስ ግዛት የለም ። ቀድሞ የእሥራኤል የጦር አውሮፕላኖች ጸጥ እስኪያሰኙአቸው ድረስ የዮርዳኖስ የጦር ሠራዊት በዚያ ተራራ ላይ ሆኖ ይተኩስባቸው ነበር ። የአረብ የጦር ኃይል እንዲለቅ የተገደደው ይህን ቦታ ብቻ ሳይሆን የዮርዳኖስን ምዕራብ ክፍልንም ነበር ። አሁን በእስራኤል ግዛት ሥር ስለሆነ የሰማሪያ ተራራ ቁልፍነቱ ይህን ያህል አስፈላጊ አልሆነም ።

በ1967 የአረብ የጦር ኃይል በለቀቀበት ጊዜ አንድ ወቅት የፍልስጥኤም ነጻ አውጭ አባል የነበሩና ከጦሩ ጋር ግንኙነት የነበራቸው አራት ፍልስጥኤማውያን ሦስት ባለ 120 ሚሊ ሜትር አዳፍኔዎች

ከነጥይቶቻቸው በድብቅ እንዲቆዩ አደረጓቸው ። እነዚያ ወጣት ሰዎች ትዕዛዝ እስኪደርሳቸው ድረስ ቦታውን ለቀው እንዲሔዱ አልተፈቀደላቸውም ። ሰዎችንና መሣሪያዎችን ወደኋላ ትቶ መሔድ የጥንት የጦር ስልት ነበር ። በዘመናዊ ሥርዓትም በማፈግፈግ ጊዜ የራስን ሰዎች ትቶ የሚኬደው ለመልሶ ማጥቃት ከፍተኛ ድጋፍ ያስገኛል በሚል እምነት ነው ።

አራቱ ፍልስጥኤማውያን በእስራኤል በተያዘው የቡርዲስ መንደር ተወላጆች ሲሆኑ ከ12 ዓመቶች በላይ በሰላም ኖረዋል ። እውነቱን ለመናገር ያህል መልዕክቱ እስኪደርሳቸው ድረስ አዳፍኔዎቹና ጥይቶቹ የት እንደነበሩ እንኳን ረስተዋቸዋል ። የሰላሙ ስብሰባ ሊደረግ በታሰበበት ዋዜማ መልዕክቱ በመምጣቱ ቢያስገርማቸውም ዋና ምክንያቱ የሰላሙ ድርድር እንደነበረ ገብቷቸዋል ። ከሩቅ ቦታ ሆነው ኑሮአቸውን የሚቆጣጠሩአቸው ሰዎች የሰላሙ ስብሰባ እንዲካሔድ አይፈልጉም ። ትዕዛዙን ላለመፈጸም መንገድ ስላልነበራቸው ሊያስፈትልክ በማይችል ወጥመድ ውስጥ ገብተዋል ። ሰዎቹ በዛፉ ሥር ተንበርክከው አንድ ትልቅ የፕላስቲክ ከረጢት እስኪያገኙ ድረስ በእጃቸው የላመውን አቧራማ አፈር ዛቁ ፣ በከረጢቱ ውስጥ 12 ባለ 120 ሚሊሜትር የአዳፍኔ ጥይቶች ነበሩ ። ጥቂት አሸዋና ቅጠላ ቅጠል በጉድጓዱ ውስጥ መልሰው ዛፎቹን ተደግፈው ተቀመጡ ። ወደዚያው ጉሆ እየቀደደ ስለመጣ ወፎቹ መዘመር ጀመሩ ።

ከፍልስጥኤሞቹ አንዱ ሳባህ ካባኒ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ተራራው ጫፍ ሔዶ አቀልቁሎ ወደ ሜዳው ተመለከተ ። ምናልባት አላህ ቢረዳቸውና ምሥራቃዊ ነፋስ ቢመጣ እንደምንም ብለው ወደ አየር ማረፊያው በመቅረብ ዋናውን የአየር ማረፊያና አውሮፕላኑ የሚቆምበትን ሜዳ በእነዚያ ሲያርፉ በሚፈነዱ ጥይቶች ተኩሰው ለማፈራረስ ይችላሉ ።

ለዚህ ሐሳቡ መልስ ይመስል በጀርባው ላይ ሙቅ አየር እንደተሰማው የካባኒ ጥምጣም በድንገት በነፋሱ ኃይል ተፈትቶ ፊቱን ሸፈነው ። ዛፎች ተወዛወዙ ። ሀማሲን የተባለው ሙቀት አዘል ነፋስ ጀመረ ።

* * *

ቴዲ ላስኮቭ በሔርዝላ ከተማ ውስጥ ባለ አንድ አፓርትማ በ3ኛው ፎቅ ላይ በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ ተኝቷል ። በኃይል የነፈሰው ነፋስ መጋረጃዎቹን ከመጠቅለሉም በላይ አንደኛውን መስኮት በኃይል ሲያላትመው ድምጽ አሰማ። ቴዲ ላስኮቭ ባለ.45 አውቶማቲክ ሽጉጡን ከጠረጴዛው ኪስ አውጥቶ በደብዛዛው ብርሃን ውስጥ ሲመለከት የመስኮቱ መጋረጃ ሲወዛወዝ ስላየው ሽጉጡን እንደያዘ ተጋደ

መ ። ሞቃቱ አየር ጠባቡን ክፍል ሞላው ። አጠገቡ የነበሩት አንሶላ ዎች ተነቃንቀው አንድ ራስ ብቅ በማለት "የተፈጠረ ችግር አለ ?" የሚል ጥያቄ አቀረበ ።

ላስኮቭ ጉሮሮውን አፍታቶ " ሞቃታማው አየር መንፈስ ጀመረ። ጸደይ ገባ ። ሰላም እየመጣ ነው ። ስለዚህ የተፈጠረ ችግር የለም " ብሎ ሽጉጡን በማስቀመጥ ሲጋራ ከጠረጴዛው ኪስ ውስጥ አውጥቶ አቀ ጣጠለ ።

ሚሪያም በርንስቴይን የትራንስፖርት ምክትል ሚኒስትር የሆነ ችው አንሶላውን ከራስዋ ላይ አንስታ የተቀጣጠለውን የላስኮቭን ሲጋራ ጫፍ ስለአየች " ደህናም አይደለህ ? " ብላ ጠየቀችው ።

" ደህና ነኝ " ብሎ ክንዱን ካንተራሳት በኋላ አቆልቁሎ ተመ ለከታት ። ፊትዋ በከፊል በትራሱ ተሸፍኖ ነበር ። መብራቱን አብርቶ አንሶላውን ከእርስዋ ላይ አነሳው ።

" ቴዲ " በምትልበት ጊዜ ድምጽዋ የቁጣ ምልክት ነበረው ። ላስኮቭ ፈገግ ብሎ " ላይሽ ፈልጌ ነው " አላት ።

" በብቃት አይተኸኛል ። ብርድ ነው " ብላ አንሶላውን አፈፍ ስታደርግ መልሶ ስለገፋባት ሰውነትዋን ኲርትምትም አደረገች ።

" ሙቀት ነው ። አይሰማሽም ? "

የብስጭት ድምጽ አሰምታ ክንዶቿንና እግሮቿን ዘርግታ ተንጋላ ተኛች ።

ላስኮቭ እርቃነ ገላዋን እየተመለከተ በእጁ ጭንዋንና ዳሌዋን ዳሰሰ ። እጁን ከጡቶቿ በአንዱ ላይ አስቀምጦ " በማን ነው የምትስ ቂው ? " ብሎ ጠየቃት ።

ዓይኖችዋን አሻሽታ " ሕልም ነው ብየ አስቤ ነበር ። ግን አይደለም " አለችው ።

" ስለስብሰባው ነው ? " ብሎ በሚጠይቃት ጊዜ የድምጹ አጣ ጣል ትዕግሥት ማጣቱን ያሳይ ነበር ።

" አዎን " ብላ እጅዋን በእርሱ እጅ ላይ አሳረፈች ። መአዛ ያለ ውን አየር ወደ ውስጥ በአፍንጫዋ እየሳበች ዓይኖችዋን ዘጋች ። " ነገሩ እኮ እንደተአምር ነው ። ሁኔታው በ1970ዎቹ እንደነበረው አይደለም ። አዲስ ዘመን ፣ አዲስ ሕይወት ነው የጀመርነው ። በአሁኑ ጊዜ እስራኤ ሎችና አረቦች በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ስለሰላም ሊወያዩ ነው " ብላ ከልብ በመነጨ ስሜት ነገረችው ።

" ስለሰላም ውይይት " አላት መጠንኛ ፌዝ ባለበት አነጋገር ።

" ተጠራጣሪ አትሁን፤ከመጀመሪያው መጠራጠር መጥፎ ነው። "

" ተጠራጥሮ መጀመር የተሻለ ነው ፤ ምክንያቱም ውጤቱ የሆነውን ቢሆን ብስጭትን አያስከትልም "

" ዕድል መስጠት አስፈላጊ ነው ። "

ሴትየዋን በጉምዥት እየተመለከተ " በእርግጥ ያስፈልጋል " አላት ።

አስደሳች ፈገግታ ካሳየችው በኋላ " መነሳት አለብኝ " ብላ ከአፋሸገችና ከተንጠራራች በኋላ " የቁርስ ቀጠሮ አለብኝ " አለችው ።

እጁን ከእርስዋ ላይ ሰብስቦ " ከማን ጋር ? " ብሎ ጠየቃት ።

" ከአንድ አረብ ጋር ፤ ቀናህ እንዴ ? "

" አልቀናሁም ፤ እንዳው ለደህንነት ጭምር ለማወቅ ነው ። "

ከሳቀች በኋላ " አብደል ማጂድ ጃባሪ ነው ። ታውቀዋለህ ? " አለችው ።

ላስኮቭ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። ጃባሪ ከሁለቱ እስራኤላውያን አረብ የምክር ቤት አባልና ስለሰላሙ ንግግር ከሚሔዱት አንዱ ነው ።

" ቀጠሮአችሁ የት ነው ? "

" ሎድ በሚቸል ቡና ቤት ነው ። ሰዓቱ እንዳያልፍብኝ ልብሴን መልበስ አለብኝ ፤ ጄኔራል " ብላ ፈገግታ አሳየችው ።

ፈገግታዋ በአፍዋ ላይ ብቻ እንደነበረ ላስኮቭ አጢኗል ። ጥቁር ዐይኖቿ ግን ትኩር አድርገው ከሚመለከቱ በስተቀር ንቅናቄ አልነበራቸውም ። ያ የሚያስጐመዠ አፍዋ የሰውን ስሜት የሚቀሰቅስ መስሎ ሲታይ ዐይኖቿ ግን ከማተኮር በስተቀር ምንም ዓይነት መልዕክት አያስተላልፉም ነበር ። በዐይነ ሕሊናዋ የምታየውን ማንም እንዲያውቅ አትፈልግም ብሎ ላስኮቭ ገመተ ።

ረጅምና ጥቁር ጸጉርዋን ዳሰሰው ። የተለየ ውበት ነበራት ። ይህም ቅንጣት ያህል እንኳን አጠራጣሪ አልነበረም ። እነዚያ ዐይኖችዋ . . . በድስሻው ከንፈሮችዋ ሲነቃነቁ አያቸው ። " ዳግመኛ ፈገግ አትይም ? " ብሎ ጠየቃት ።

ምን ማለቱ እንደሆነ ገብቷታል ። ፊትዋን በትራስዋ ላይ ደፍታ "ምናልባት ከኒውዮርክ ስመለስ ፤ ምናልባት ከዚያ በኋላ " ብላ አጉመተመተች ።

ላስኮቭ ጸጉርዋን መዳሰሱን አቆመ ፡፡ የሰላሙ ውይይት ውጤታማ ቢሆን ማለትዋ ይሆን ? ወይስ ከሦስት ዓመት በፊት ከሶሪያ ጋር ጦርነት በተደረገ ጊዜ ስለጠፋው የአየር ኃይል መኰንን ስለነበረው ባልዋ ስለዮሴፍ ጥሩ ወሬ ካገኘሁ ማለትዋ ይሆን ? ባለቤትዋ ከላስኮቭ እዝ ሥር ነበር ፡፡ ላስኮቭ በራዳር ሲወርድ አይቶታል ፡፡ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ዮሴፍ እንደሞተ እርግጠኛ ነበር ፡፡ ሊያጽናናትና ሊያስደስታት ስለወ ... ወደ ኒውዮርክ ከመሔድዋ በፊት ስለእርሱ ያላትን ስሜት ማወቅ ፈልጓል ፡፡ እንደገና ሳያያት ለብዙ ወሮች ይቆይ ይሆናል ፡፡ "ሚሪያም . . . " ብሎ ሳይጨርስ መዝጊያው በኃይል ስለተቆረቆረ ከአልጋው ውስጥ ተስፈንጥሮ በመውረድ ቆመ ፡፡

" ቴዲ ሽጉጥህን ያዝ ፡፡ "

" ሽብር ፈጣሪ ፍልስጥኤማውያን አብዛኛውን ጊዜ አይቆረቁሩም " ብሎአት ሳቀ ፡፡

" ምናልባት እኔን ለሥራ ጉዳይ የሚፈልግ ሰው ስለሚሆን ልብስህን እንኳን ልበስ ፡፡ "

ላስኮቭ ሱሪውን ለብሶ የኮልት ሽጉጡን ከታጠቀ በኋላ " ሌሊቱን የት እንደምታሳልፊ ለሥራ ባልደቦረችሽ ባትነግሪአቸው እደሰት ነበር " አላት ፡፡

መዝጊያው እንደገና በኃይል ስለተቆረቆረ ላስኮቭ በሳሎን አቋርጦ ባዶ እግሩን በሥጋጃ ምንጣፉ ላይ ወደ በሩ ተጠግቶ " ማን ነው ? " ብሎ እየጠየቀ ወደ መኝታ ቤቱ ሲመለከት መዝጊያውን ያልዘጋው መሆኑን አየ ፡፡ ሚሪያም ራቁትዋን ተኝታ ከበሩ ትታያለች ፡፡

* * *

አብደል ማጂድ ጃባሪ በሎድ በሚቸል ቡና ቤት በአንድ ጨለማ በሆነ ጓዳ ውስጥ ቆሞአል፡፡ ቡና ቤቱ የአንድ የክርስትና ሃይማኖትን የተቀበለ አረብ ሲሆን የሚገኘውም በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ነበር ፡፡ ጃባሪ ሰዓቱን ተመልክቶ ቡና ቤቱ በዚያ ሰዓት መከፈት እንደነበረበት ቢያምንም የሚንቀሳቀስ ሰው አልነበረም ፡፡ እርሱም በጨለማው ውስጥ ወደግድግዳው ተጠግቶ ቆመ ፡፡

ጃባሪ መልኩ ጥቁር ከመሆኑም በላይ አፍንጫው ቀጥ ብሎ እጫፉ ላይ ጐበጥ ያለ ነበር ፡፡ ልኩ ያልሆነ ቦርቃቃና ጥቁር የሆነ የሥራ ልብስ የለበሰ ሲሆን መልኩ ነጭና ጥቁር የሆነና ጥቁር ቁጢት ያለው ባሕላዊ ጨርቅ በራሱ ላይ ጠምጥሟል ፡፡

ጃባሪ ላለፉት 30 ዓመቶች በጨለማ ሰዓቶች ብቻውን የወጣባቸው ቀኖች በጣም ጥቂት ነበሩ ። በአዲሲቱ እስራኤል ከአይሁዳውያን ጋር በግሉ ተስማምቶ ለመኖር ከወሰነበት ጊዜ ጀምሮ ስሙ በሚገደሉ ፍልስጥኤማውያን መዝገብ ውስጥ ገብቷል ። በተጨማሪም ከሁለት ዓመት በፊት የእስራኤል ምክር ቤት አባል ሆኖ እንዲሠራ በመመረጡ ከሚገደሉት ሰዎች ውስጥ የመጀመሪያው እንዲሆን ተወስኖበታል ። አንድ ወቅት ሊገድሉት ተቃርበው ነበር ። በደብዳቤ አማካይነት በተላከ ፈንጂ የግራ እጁ ተቆርጧል ።

አንድ በሞተር ብስክሌት የሚዘዋወር እስራኤላዊ የፀጥታ ሠራተኛ በጥርጣሬ ዐይን ቢመለከተውም የሞተር ብስክሌቱን አቁሞ አልጠየቀውም ። እንደገና ሰዓቱን ሲመለከት ከሚሪያም በርንስቴይን ጋር ከተቃጠረበት ሰዓት ቀድሞ ደርሷል ። ሌላ ግለሰብ ፣ ወንድ ወይም ሴት ወደ ዚያ ብቸኛ ወደሆነ ቦታ ሊያመጣው የሚችል ይኖራል ብሎ አላሰበም ። አፍቅሯታል ። ፍቅሩ ግን የውስጥ እረመጥ እንጂ በግንኙነት ዕውን እንደማይሆን አውቋል ። ይህ በምዕራባውያን ዘንድ ያልተለመደ ቢሆንም ለእርሱ ግን ጥሩ ሆኖ አግኝቶታል ። በ1948 ሚስቱ ፣ ልጆቹና የሥጋ ዘመዶቹ ወደ ምዕራብ ዮርዳኖስ ከኮበለሉበት ጊዜ ጀምሮ ይህ ምኞት በውስጡ ሰርጾ እንዲገባ አደረገችው ። በ1967 ምዕራብ ዮርዳኖስ በእስራኤል ቁጥጥር ሥር በዋለ ጊዜ ለብዙ ቀኖች ሲያስብ የነበረው ከቤተሰቦቹ ጋር እንደገና ስለመገናኘቱ እንጂ ሌላ ትዝ የሚለው አልነበረም።

የእስራኤል ወታደሮች እስከ ያዙት የመጨረሻ ቦታ ድረስ ተከትሎ ሔደ ። ምርኮኞች ተይዘው ወደ ታሰሩበትና ዘመዶቹ ወደ ነበሩበት ቦታ በደረሰ ጊዜ ፤ እህቱ መሞትዋንና ሌሎቹ ወደ ዮርዳኖስ መሰደዳቸውን ተረዳ ። ልጆቹም ከፍልስጥኤም ደፈጣ ተዋጊዎች ጋር አብረው መግባታቸውን ሰማ ። አንዲት የቆሰለች ዘመዱ ብቻ በእስራኤል ተንቀሳቃሽ ሐኪም ቤት ተኝታ ነበር ። ይህች በሞት አፋፍ ላይ የነበረች የአክስቱ ልጅ ከእስራኤሎች የሕክምና እርዳታ ለመቀበል አሻፈረኝ ባይነቷ በፍልስጥኤም ሕዝብና በወንዙ ሰዎች ዘንድ ያደረውን ከፍተኛ ጥላቻ ለመገንዘብ ቻለ ።

ጃባሪ ቀድሞም ሆነ አሁን እንደዚህ ያለ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር አጋጥሞት አያውቅም ። በ1948 ከቤተሰቦቹ ከተለየበት ቀን ይልቅ በሰኔ ወር 1967 ያጋጠመው በጣም መራራና የከፋ ነበር ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሰላም ሊሰፍን የሚችልበትን ዘዴ በመሻት ብዙ ተጉዟል ። አሁንም ኒውዮርክ በተባበሩት መንግሥታት ስለሰላም ስብሰባ ለማድረግ ከምትሄደው ሴት ጋር በቁርስ ሰዓት ለመወያየትና ሐሳብ ለሐሳብ ለመለዋወጥ እዚህ ቆሟል ።

በመንገዱ ላይ የጥላ እንቅስቃሴ ስላየና የመጣውም ለብርቱ ጉዳይ እልባት ለመስጠት ስለነበረ የበለጠ ጥንቃቄ ማድረግ እንደነበረበት አውቋል ።

ሞቃታማው ነፋስ ቆሻሻዎችን እየጠራረገና እያንኮሻኮሸ አደባ ባዩን አቋርጦ ነፈሰ ። ቀጥ ብሎ በረጅም ወንዝ እንደሚሔድ ውሀ ሆኖ ይነፍስ ስለነበረ እየሰባበረ ከሚወስዳቸው ዕቃዎች ጋር ድምጹ በመደ መሩ በኃይል ይሰማ ነበር ። የዚህ ዓይነቱ ነፋስ በመጣ ቁጥር ምንጊዜም ቢሆን ሰዎችን በጭንቀት ላይ ይጥላቸው ነበር ።

ሦስት ሰዎች ከመንገዱ ማዶ ከነበረው ሕንጻ ጥላ ስር መንገዱን አቋርጠው ወደ እርሱ አቅጣጫ መጡ ። ጃባሪ የንጋት ውጋጋን መስ ጠት በጀመረው ብርሃን ሲመለከት በትከሻዎቻቸው ጠመንጃዎች አዘ ቅዝቀው መሸከማቸውን አየ ። ተዘዋዋሪ የፀጥታ ጠባቂዎች ከሆኑ ለጥ ቂት ጊዜ ከእርሱ ጋር እንዲቆዩ ለመጠየቅ ፈልጓል ። ካልሆኑ ግን . . . በኪሱ ውስጥ የያዛትን ትንሽ የበሬታ ሽጉጥ በእጁ ጨበጠ ። ቢያንስ ቢያንስ ከፊት የነበረውን እንደሚገነጥለው እርግጠኛ ነበር ።

* * *

ሳባህ ካባኒ ሦስቱን ፍልስጥኤማውያን ትልቁን ቋጥኝ እንዲያንከ ባልሉ ረዳቸው ። ድንጋዩን ሲያንቃንቁት በስሩ የነበሩ እንሽላሊቶች እየወጡ ሔዱ ። ድንጋዩ በነበረበት ቦታ ላይ 120 ሚሊ ሜትር ስፋት ያለው ቀዳዳ ነበር ። ካባኒ ቀዳዳው የተዘጋበትን በዘይት የጨቀየ ድቡ ልቡል ጨርቅ ስቦ በሚያወጣበት ጊዜ አንድ የአምሳ እግር (የትል ዓይ ነት) በእጁ ላይ ሲሔድበት ተሰማው ። ቀዳዳውን ዳብሶ እጁን ካወጣ በኋላ "በጥሩ ሁኔታ ላይ ነው ፤ አልዛገም እንኳን" አላቸው ። ቀጥሎም ዘይት የነካውን እጁን በሱሪው ላይ እየጠረገ ቀዳዳውን ትኩር አድርጎ ተመለከተው ።

ቬየትናሞች ሌትና ቀን እየተቀያየሩ ይጠቀሙበት የነበረ የቀድሞ የደፈጣ ውጊያ ዘዴ ነበር ። አዳፍኔው በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ከተቀ መጠ በኋላ ጥይቱ በየተራ እንዲገባ ይደረጋል ። አዳፍኔው ኢላማውን እንዳይስት ተቀኝቶ ይስተካከላል ። ከተኮሱ በኋላ ድንጋዮች ሸፍነው ትተውት ይሔዳሉ ። ከአንድ ቀን ወይም ከአንድ ሣምንት ወይም ከአ ሥር ዓመቶች በኋላ በመሣሪያው ለመጠቀም ከፈለጉ ከ100 ኪሎ ግራም በላይ ክብደት ያለውን አዳፍኔ ይዘው ወዲያና ወዲህ በማለት ፋንታ የሸ ፈኑበትን ድንጋዮች ከአፈሙዙ ላይ አንስተው ጥይቱን በመጨመር መተኮስ ይችላሉ ።

የካባኒ ተኳሾች እያንዳንዳቸው አራት ጥይቶች ከተኮሱ በኋላ የተ ቀበረውን አዳፍኔ አፍ በድንጋዮች ሸፍነው መሔድ ይችላሉ ።

ካባኒ ጨርቅ በአልኮል ነክሮ ጥይት የሚገባበትን ቀዳዳ ወለወለ ው ። አዳፍኔው በ1967 በተቀበረበት ጊዜ ኢላማውን እንዲመታ ተስ ተካክሎ ይሆን ? ጥይቶቹስ አልተበላሹም ይሆን ? መሬቱ ከፍና ዝቅ ብሎ ወይም የዛፍ ማደግ ያስከተለበት ችግር ይኖር ይሆን ? የሚሉት ጥ ቄዎች አስጨንቀውታል ።

* * *

" ሪቻርድሰን ነኝ " ስላለ ላስኮቭ የመዝጊያውን ቁልፍ ፈለቀቀ ።

ሚሪያም በርንስቴይን ከአልጋው ውስጥ ራቁትዋን ወጥታ ጉን በስ ብላ ፈገግታ ስታሳይ የምታባብል ትመስል ነበር ። ላስኮቭ በሁኔ ታዋ አልተደሰተም ። መዝጊያውን ቀስ አድርጐ ስለከፈተለት የአሜ ሪካ አየር ኃይል አታሼ ቶም ሪቻርድሰን ወደውስጥ ሲራመድ የመኝታ ቤቱ መዝጊያ ሲዘጋ ላስኮቭ ሰማ ። አይቷት እንደሆነ ለማረጋገጥ የሪ ቻርድሰንን ፊት ተመለከተ ። ሰዓቱ የውጥረት ጊዜ ስለነበረ ሐሳብን አጠ ቃሎ በአንድ ነገር ላይ ትኩረት የሚሰጥበት ስላልነበረ ለማየቱም ሆነ ላለማየቱ እርግጠኛ ሊሆን አልቻለም ። " የመጣኸው ለሥራ ወይስ ለግል ጉዳይ ? "

ሪቻርድሰን እጆቹን ወደላይ ዘርግቶ " እንደምታየኝ ገና ፀሐይ ሳትወጣ ሙሉ ዩኒፎርም ለብሻለሁ " አለው ።

ላስኮቭ ወጣቱን መኰንን ከላይ እስከታች ተመለከተው ። ሪቻር ድሰን ረጅምና አብረቅራቂ ፀጉር የነበረው ሰው ሲሆን ለዚህ ሥራ የተ መረጠው ለአብራሪነት ካለው ችሎታ ይልቅ ሰውን ለመሳብና ለማግ ባባት የበለጠ ችሎታ ስላለው ነበር — ዩኒፎርም የለበሰ ዲፕሎማት— " የተናገርከው ለጥያቄዬ መልስ አይሆንም " አለው ላስኮቭ ።

" ለምንድነው ሽጉጥ የታጠቅኸው ? እኛ እንኳን በዋሽንግተን መዝጊያ ስንከፍት እንደዚህ አናደርግም ።"

" ብታደርግ ይሻልሃል ። እባክህ ተቀመጥ ። ቡና ላምጣልህ ? "

" እሺ ። "

ላስኮቭ ወደ ጓዳው እየተራመደ " የቱርክ ፥ የጣሊያን ፥ የአሜሪካ ወይስ የእስራኤል ፤ የትኛው ይሻልሃል ? "

" ከሆነ የአሜሪካን ይሻለኛል ።"

" ያለኝ የእስራኤል ብቻ ነው ። "

ሪቻርድሰን በወንበሩ ላይ ተቀምጦ “ ከቀድሞዎቹ ቀኖች አንዱ እንኳን ይኖረን ይሆን ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ ዘወትር አለን አይደለም ? ”

“ ላስኮቭ ሁኔታዎችን በደህና ተመልከታቸው ፤ ሰላም ሊወርድ ነው ። ”

“ ምናልባት ይሆን ይሆናል ” ብሎ በጋዝ ምድጃው ላይ ጀበና ሲጥድ በገላ መታጠቢያው ውስጥ ውሃ በኃይል ሲፈስ ሰማ ።

ሪቻርድሰን ወደተዘጋው መኝታ ቤት በር እየተመለከተ “ ችግር እየፈጠርኩ ነው እንዴ ? አገር ውስጥ ካለች የአረብ ልጅ ጋር ለብቻህ የሰላም ድርድር እያካሔድህ ነው እንዴ ? ” ብሎ ከሳቀ በኋላ “ ምን ድን ነው ያለው ፤ በግልጽ ለመነጋገር እንችላለን ? ” በማለት ጠየቀው ።

ላስኮቭ ከጓዳ ወጥቶ “ አዎን ፤ ግን ይህን ጉዳይ ለጊዜው እናቆየው ። ስለዚህ ነገር ለመወያየት ሙሉ ቀን አለኝ ” አለው ።

“ እኔም አለኝ ” ብሎ ሪቻርድሰን ሲጋራውን ካቀጣጠለ በኋላ “ስለኮንኮርዶቹ ደህንነት ያዘጋጀኸውን ማወቅ እፈልጋለሁ ” አለው ።

ላስኮቭ ወደ መስኮቱ ሔዶ መጋረጃውን ከፍቶ ወደውጭ ተመለከተ ። በሚኖርበት ሕንጻ ሥር የሐይፉ — ቴል አቪቭ ዋና መንገድ አለ ። በሜድትራንያን ባሕር አጠገብ ካሉ የግል መኖሪያ ቤቶች የኤሌክትሪክ ብርሃን ይታያል ። ሔርዝሊያ የአየር ኃይል አታሼ መናኸሪያ የሚል ስም አግኝቷል ። እንደዚሁም የእስራኤል ሆሊውድና የዕረፍት ማሳለፊያ ነበር ። ሔርዝሊያ የኤል አልና የአየር ኃይል ሠራተኞች ለመክፈል ከቻሉ የሚኖሩበት ቦታ ነበር ።

ከምዕራባዊ ባሕር ወደ ላስኮቭ መኖሪያ የሚመጣው የነፋስ ሽውታ ከሰማርያ ተራራዎች በኩል የብርቱካንና የለውዝ አበቦች ሽታ ይዞ የሚመጣው በምሥራቅ ደረቅ ነፋስ ተተካ ። የፀሐይ ፍንጣቂ በጀመረበት በመንገዱ ባሻገር ባለ በአንድ ሱቅ ታዛ ሥር ሁለት ሰዎች ቆመዋል ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ወደ ጨለማው ውስጥ አፈግፍገው ገቡ ። ላስኮቭ ከመስኮቱ አጠገብ ተመልሶ በአንድ ረጅም ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ከተቀመጠ በኋላ “ እንደማስበው አንተ ከሾፌርና ከአጃቢ ጋር ካልመጣህ በስተቀር ይህን ቤት በዐይነ ቁራኛ የሚከታተል አለ ” አለው ።

ሪቻርድሰን በግዴለሽነት ትከሻውን ነቅንቆ “ ማንም ይሁን ማን የራሳቸው ሥራ ነው ፤ እኛም የራሳችን አለን ” ብሎ ጉብደድ በማለት “ ስለዛሬው ቀን ሥራ ሙሉ ሪፖርት ማግኘት እፈልጋለሁ ” አለው ።

ላስኮቭ በወንበሩ ላይ ወደ ጣሪያው አንጋጦ ተቀመጠ ። እንደገና በዋርሶው ላይ የተልዕኮ ቡድን ይዞ ሲበር በሐሳቡ ታየው ። የቀዬ አየር ኃይል ካፒቴን ቴዲ ላስኮቭ ነበር ። በዚያ ጊዜ ነገሮች ቀላል ነበሩ ወይም ይመስሉ ነበር ። በጦርነቱ የመጨረሻ ቀኖች ለሦስተኛ ጊዜ ተመትቶ የወደቀው ላስኮቭ የማገገሚያ ፈቃድ ተሰጥቶት ከሚንስክ ወጣ ብሎ ወደሚገኘው የዛስላቭል መንደር ተ[illegible]ሰ ። በዚያም የናዚ ሰዎች በስ በብ በአስባቡ ከጨፈጨፏቸው ቤተሰቦቹ ውስጥ የተረፉትን ጥቂት ዘመ ዶቹን አገኘ ። ላስኮቭ ድርጊቱን ንጹህና ረዳት የሌላቸውን ሰዎች በግፍ መጨረስ ነው ብሎ ጠራው ።

ሩስያ ፈጽሞ አይለወጥም ፤ የትም ይሁን የትም አይሁዳዊ ፣ አይሁ ዳዊ ነው በሚል ውሳኔ ላይ ደረሰ ።

ካፒቴን ላስኮቭ በቀዩ አየር ኃይል ከፍተኛ ሽልማት ያገኘ መኰ ንን ነበር ። በጀርመን ውስጥ ወደ ነበረው ምድብ ቦታው ተመልሶ ሔደ። ከደረሰ 10 ደቂቃዎች ቆይታ በኋላ አንድ ተዋጊ አውሮፕላን አስነስቶ ከበርሊን ወጣ ብሎ የሚገኘውን የራሱን የጦር ሠፈር በቦምብ ካጋየ በኋላ በአሜሪካን ሁለተኛ ብረት ለበስ ዲቪዚዮን ተይዞ በነበረው በኤ ልብ ምዕራባዊ ዳርቻ አየር ማረፊያ አረፈ ።

በምዕራብ አውሮፓ የነበሩ አይሁዶች የደረሰባቸውን አሰቃቂ እል ቂት ካየ በኋላ ከነበረበት የአሜሪካ የጦር ሠፈር በመጨረሻ ወደ ኢየ ሩሳሌም መጣ ። አየር ኃይሉ የነበሩት ጥቂት የተሰባበሩ የእንግሊዝ የጦር አውሮፕላኖችና ጥቂት የአሜሪካን የሕዝብ ማመላለሻ ቀላል አው ሮፕላኖች ሲሆኑ በተምር ጫካዎች ውስጥ ሸሽገው ይጠቀሙባቸው ነበር ።

የቀድሞው የቀዩ አየር ኃይል ካፒቴን ላስኮቭ የዳዊት ኮከብ ያለበ ትን የመጀመሪያውን ተዋጊ አውሮፕላን ባየ ጊዜ ዓይኖቹ በእንባ ጭጋግ ተጋረዱ ።

ከ1946 ጀምሮ በ1948 የነፃነት ጦርነት ፣ በ1956 የስዊዝ ጦር ነት ፤ በ1967 የስድስቱ ቀን ጦርነትና በ1973 የዮም ኪፑር ጦርነት ላይ በመሠማራት አኩሪ ሥራ ፈጽሟል።5,136 ጊዜ የስለላ በረራዎች አድር ጓል ። በጦርነቱ ወቅት 5 ጊዜ ተመቷል ። ሁለት ጊዜ የሚያበረው አው ሮፕላን ተመቶ ወድቋል ። በልዩ ልዩ ጊዜ በአጋጠመው አደጋ ምክን ያት በሰውነቱ ላይ ብዙ ጠባሳዎች አሉ ። በ1973 አንድ ፋንቶም ተዋጊ ጄት ሲቃጠል በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ሲሔድ ጉብደድ ብሎ ነው ። እርጅና እየተጫጫነው መጥቷል ፤ ድካምም ተሰምቶታል። አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር የጦር አውሮፕላኖች አይነዳም ። ለወ

ያፈቱም ከዚህ ስብሰባ በኋላ ዳግመኛ ላለማብረር ተስፋ ከማድረጉም በላይ አምኗል ። እንዲያውም ፈጽሞ አላደርገውም የሚል ስሜት አድርበታል ።

የተጣደው ጀበና በኃይል ቢፈላም ላስኮቭ ከመመልከት በስተቀር ምንም አላደረገም ። ሪቻርድሰን ከተቀመጠበት ተነስቶ የጋዙን ምድጃ ካጠፋ በኋላ " ምን ሆነሀል ፤ ደህና አይደለህም እንዴ ? " ብሎ ጠየቀው ።

ላስኮቭ ትከሻውን ከፍ አድርጐ " የዚያ ዓይነት መረጃ ለማን እንደምናስተላልፍ በጥንቃቄ ማወቅ አለብን " አለው ።

ሪቻርድሰን በፍጥነት ወደላስኮቭ ተራመደ ። ፊቱ አሸሸ ከመምሰሉም በላይ መንቀጥቀጥም ሞከረው ። " ምን ? ለመሆኑ ምን ማለትህ ነው ? ስማ የማቀርባቸው ሪፖርቶች አሉኝ ። በሜድትራንያን ባሕር ላይ ካለው የጦር መርከባችን ጋር ሁኔታዎችን ማዛመድ አለብኝ ። ይህ መሆኑ እየታወቀ አንተ ከእኛ የምትደብቀው አለ ? የወጣ ወይም ያፈተለከ መረጃ አለ የምትል . . . " አለው በቁጣና በንዴት ስሜት ።

ላስኮቭ የሪቻርድሰንን በቁጣ መቅለብለብ ከቁም ነገር አልቆጠረውም ። ለቁም ነገሩ ሥራ ቀደምትነት ይሰጣል ። ይህም ዋና አላማው ነው ። ላስኮቭ በሰጠው ማሳሰቢያ ላይ የተደረገው መቅበጥበጥና ቁጣ ትክክል አይደለም ። ምናልባት ሌሎቹ ሁሉ በዛሬው ቀን እንደሚያሳዩት ያልተረጋጋ ሁኔታ ዓይነት በሪቻርድሰንም ላይ ተጽዕኖ አሳድሮ ይሆናል ።

" አትበሳጭ ኰሎኔል " ብሎ ላስኮቭ ወጣቱን ሰው ትኩር አድርጐ ተመለከተው ።

ሪቻርድሰን ፈገግታ አሳይቶ እየተቀመጠ " አዝናለሁ ጄኔራል" አለው ።

ላስኮቭ " ምንም አይደል" ብሎ ወደ እስራኤል አየር ኃይል ዋና መሥሪያ ቤት ስልክ ደውሎ "ኢ—2 ዲን አገናኘን " አለው ። ኢ—2 ዲ ኾኪ እጅግ በጣም ዘመናዊ የበረራ መቆጣጠሪያ ሲሆን ለጠብም ሆነ ለወዳጅነት በመሬት ፣ በባሕርና በአየር የሚደረገውን እንቅስቃሴ ያለምንም ስህተት እስከ አሁን ድረስ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የሚጠቁም ፣ አጉልቶ የሚያሳይና የሚከታተል የኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ነው ። ይህም መረጃ በኮምፒዩተር ከተቀነባበረ በኋላ ለሚመለከታቸው ክፍሎች በዳታ ትራንስሚሽን ይሰራጫል ። እስራኤል የዚህ ዓይነት መሣሪያ ሦስት ነበራት ። ላስኮቭ በሚነጋገርበት ጊዜ ሪቻርድሰን ያዳምጥ ነበር ።

ላስኮቭ ንግግሩን እንደጨረሰ ስልኩን አስቀመጠ ።

" ማንኛውንም ነገር ማየት ይችላሉ ? " ብሎ ሪቻርድሰን ጠየቀው ።

" ምናልባት የግብጽ ንብረት የሆኑ አራት ተዋጊ አውሮፕላኖች — ለልምምድ የወጡ ናቸው ብየ የምገምታቸው — እንዲሁም ምናልባትም የሩስያ የስለላ በራሪ እጅግ በጣም በከፍተኛ እርቀት ላይ ታይተዋል ። "

ሪቻርድሰን ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ።

ላስኮቭ ቡናውን በሁለት ስኒዎች ውስጥ እየቀዳ ስለአንዳንድ ቴክኒካዊ ስለሆኑ ጉዳዮች በሚነጋገሩበት ጊዜ በመታጠቢያ ክፍሉ ውስጥ ይፈስ የነበረው ውሀ ቆመ ።

ሪቻርድሰን ከቡናው የሚወጣውን እንፋሎት እፍ እያለ "ለመሆኑ ኤፍ—14 አውሮፕላኖቻችሁን በአጃቢነት ትጠቀሙባቸዋላችሁ ? " ብሎ ጠየቀው ።

" ያለጥርጥር" አለው ላስኮቭ ። ኤፍ—14 ተዋጊ አውሮፕላኖች በዓለም ውስጥ እጅግ በጣም ዘመናዊ ነበሩ ። ሚግ 25ም እንደዚሁ ነበር ። የሁለቱም አስተማማኝነት የተመሠረተው በአብራሪዎቹ ላይ ነበር ። በላስኮቭ አመራር ሥር የእነዚህ ዓይነት 12 እንደነበሩና የእያንዳንዳቸው ዋጋም 18 ሚሊዮን የአሜሪካ ብር እንደነበረ ታውቋል ። ለጊዜው በሎድ አየር ማረፊያ አጠገብ ባለው የጦር ሠፈር ነበሩ ።

" አንተ ታበራለህ ? "

" ያለጥርጥር ።"

" ለምን የዚህ ዓይነቱን ሥራ በጣም ወጣት ለሆኑት አትተውም ?"

" አንተ ለምን ራስህን አትገድልም ? "

ሪቻርድሰን ስቆ " አንተ ጥሩ የአሜሪካን አገላለጽ ችሎታ አለህ " አለው ።

"አመሰግናለሁ ። "

" ይህን ሥራ እስከ መቼ ድረስ ትቀጥላለህ ? "

" ችግራችን እስኪቃለል ድረስ እቀጥላለሁ " ብሎ ወደመስኮቱ በመራመድ ጉሀ መቅደዱን ተመለከተ ። " አውሮፕላኖቻችን በእንደዚህ ዓይነቱ ቀን ቦምብ አልባ በመሆን ከድንበራችን ውጭ ደጋግ

መው እንዲበሩ ማድረግ ይገባናል ። ድርጊቱ ጠላቶቻችን በዛሬው ቀን አንድ ነገር ለማድረግ የጠነሰሱት ሴራ ቢኖር በፍርሃት ከአካባቢው ለቀው እንዲሔዱ ያደርጋቸዋል ” አለው ።

“ በዚህ አካባቢ የሚደረገው የማስደንገጫ በረራ በሊቢያ ፣ በሞሮኮ ፣ በቱኒሲያና በአልጀሪያ ያሉትን ሊያስፈራቸው አይችልም ። ከእነዚህ አካባቢዎች ለመራቅ ካስፈለገህ ሲሲሊ ባለው በእኛ የጦር ሠፈር ማረፍ ይቻላል ። ካስፈለገም አውሮፕላኖቻችሁ በአየር ላይ እንዳሉ ነዳጅ እንዲሞሉ ለዚሁ የተዘጋጀውን አውሮፕላናችንን መላክ እንችላለን ” ብሎ ሪቻርድሰን ነገረው ።

ላስኮቭ ዐይኖቹን ከሪቻርድሰን ላይ አንስቶ ወደሌላ እየተመለከተ ፈገግ አለ ። “ አሜሪካኖች የተፈለገው ተከፍሎ ሰላም እንዲወርድ በሚያደርጉት ጥረት መረበሽ ከሚሰማቸው በስተቀር ተባባሪዎች ነበሩ ። ችግሩ ግን በሜድትራንያን ባሕር ላይ ዳር እስከ ዳር ሊፈጽሙት የሚችሉት ነገር አልነበረም ። ኮንኮርዶቹ በኢጣሊያን ድንበር የሚያደርሳቸውን የበረራ ፕሮግራም እንደአስፈላጊነቱ በመጨረሻው ደቂቃ መለወጥ ይችላሉ ። በፈረንሳይና በኢጣሊያን አየር ላይ እንዲበሩ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገናል ። ካስፈለገም አቋርጠን ወደ ምሥራቅ ሲሲሊ እንገባለን ። የዝግጅታችንን ቅንብር ስለምስጥህ የእናንተም ሰዎች ከጦር ሠፈራቸው ሆነው ሊከታተሉ ይችላሉ ። ግን ይህ ሁሉ አስፈላጊ መስሎ አይታየኝም ። መርሳት የሌለብህ ኮንኮርዶቹ19ሺህ ሜትር ከፍ ብለው ስለሚበሩ ከአረቦቹም ሆነ ከሩስያ የጦር ሠፈሮች ውጭ ይሆናሉ ። ”

ሪቻርድሰን ተንጠራርቶ “ ከጸጥታ ክፍላችን ባለን መረጃ መሠረት ማንኛውም ነገር ደህና ነው ። አንተ በበኩልህ አደጋ ይኖራል ብለህ ታስባለህ እንዴ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ በዚህ አገር ውስጥ ሁልጊዜም ችግር ሊኖር ይችላል ብለን ማሰብ አለብን ። እውነቱን ለመናገር ግን እስከ አሁን የማውቀው አንድም ነገር የለም ። የምንወስደው እርምጃ ሁሉ ለጥንቃቄ ያህል ነው ። በኮንኮርዶቹ ላይ ከሚሳፈሩት ሰዎች ብዙዎቹ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ናቸው ። እያንዳንዱ ነገር አስጊ ነው ። ለማጥፋት አንድ እብድ አንድ ነገር ለማድረግ ይችላል ። ”

ሪቻርድሰን አሁንም ራሱን በአዎንታ እየነቀነቀ “ የምድር ጸጥታው እንዴት ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ ይህ የጸጥታ ሹሙ ሐላፊነት ነው ። እኔ አብራሪ እንጂ የደፈጣ ተዋጊ አይደለሁም ። ኮንኮርዶቹን አየር ላይ እንዳሉ አስገድዶ ለማ

ውረድ ቢሞከር ድምጥማጡን አጥፍቼ ኮንኮርዶቹ ጭረት እንኳን ሳይ ደርስባቸው እንዲመለሱ አደርጋለሁ ። ከምድር ስለሚደረገው ግን አላውቅም ። ”

ሪቻርድሰን ስቆ “ ልክነህ ፤ እኔም አላውቅም ። በነገራችን ላይ ከ.45 ኮልት ሽጉጥህ ሌላ ምን ይኖርሃል ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ ሰውንም ሆነ ሌላ ነገር ሊያጠፉ የሚችሉ ሁለት ሳይድዊንደ ርስ ፣ ሁለት ስፓሮውስና ስድስት ፎኒክስ ይኖሩናል ። ”

ሳይድዊንደሮቹ ከ5—8 ኪሎ ሜትር ፣ ስፓሮዎቹ ከ16—56 ኪሎ ሜትር ፣ ፎኒክሶቹ ደግሞ ከ56—160 ኪሎ ሜትር ለመምታት የሚችሉ ስለነበሩ ሪቻርድሰን በጥሩነታቸው አምኗል ።

“ ላስኮቭ ለዓይነት ካልሆነ በስተቀር መውሰድ የለብህም ። በ19ሺህ ሜትር እርቀት ላይ ሊፈጠር የሚችል ነገር አይኖርም።ባለ20 ሚሊ ሜትር የመድፍ ጥይቶችህን እቤት አስቀምጣቸው ። 950 ያሉ ሲሆን ክብደታቸውም ከፍተኛ ነው ። ቀርቦ ለሚመጣው ሁሉ ሳይ ድዊንደሩ በቂ ነው ። ”

ላስኮቭ በጣቶቹ ጸጉሩን እየደባበሰ “ ምናልባት ፤ ምናልባት ክፉ ነገር ቢያጋጥመን—ለስለላ የሚበር አውሮፕላን እንኳን ቢመጣ ድምጥማጡን ለማጥፋት መሣሪያዎቼን እወስዳቸዋለሁ ። ”

ሪቻርድሰን ፈገግታ እያሳየና ሌላ የሚሰማ ሰው ያለ ይመስል ድም ጹን ዝቅ አድርጎ “ ማንም እንዲዘዋወርበት በተፈቀደ ሕዋው ውስጥ ለስለላ ሥራ የተሰማራ ትጥቅ የሌለው አውሮፕላን ትደመስሳለህን ?” ብሎ ከጠየቀው በኋላ “ ለመሆኑ ዛሬ የምትጠቀምበት የራዲዮ መስመ ርና ምልክትህ ምንድን ነው ? ” አለው ።

“ የምንጠቀመው በጣም ከፍተኛ ሞገድ በሆነው በ31 ባንድ ወይም 134.725 ሜጋኸርትዝ ይሆናል ። ተለዋጭ መስመራችን ግን በመጨረሻው ደቂቃ ከደህንነት ሠራተኞች ጋር በሚደረገው ስምምነት ይወሰናል ። ይህንንም በኋላ እነግርሃለሁ ። የዛሬው ስሜ መልአኩ ገብ ርኤል ተብሎ ይሰየማል ። የመለያ ቁጥሬም 32 ነው ። የቀሩት 11 ሰዎች ከመለያ ቁጥራቸው ጋር ገብርኤል ይባላሉ ። የዚህንም ዝርዝር በኋላ እልክልሀለሁ ። ”

“ የኮንኮርዶቹስ ? ”

የተፈበረከበት ቁጥር 4X—LPN የሆነው ኤል አል 01 ፣ 4X—LPO የሆነው ደግሞ ኤል አል 02 ነው ። እነዚህ ቁጥሮች በአየር

ትራፊክ መቆጣጠሪያና በኤል አል መስመሮች የምንጠቀምባቸው ና ቸው ። በእርግጥ የግላችን የሆኑ ምሥጢራዊ ስሞች ይኖሩናል ።

" ምንድን ናቸው ? "

ላስኮቭ ፈገግ ካለ በኋላ " የ01 አብራሪ ወጣት ሃይማኖተኛ ሰው ስለሆነ ኮሸር ክሊፐር ፣ የ02 አብራሪ ደግሞ ቀድሞ አሜሪካዊ ስለነበረ ለአሜሪካን አየር መንገድ ክብር ሲባል የአማኑኤል ክንፎች ተብለው ይጠራሉ ። "

" መጥፎ ነገር " ብላ ሚሪያም በርንስቴይን ተኳኩላ፣ ቢጫ ልብስ ተጐናጽፋና የማታ ቦርሳ ይዛ እነርሱ ወደነበሩበት ሳሎን መጣች ።

ሪቻርድሰን ከተቀመጠበት ተነሳ ። የትራንስፖርት ምክትል ሚኒ ስትር መሆንዋን ቢያውቅም ለመናገር አልፈለገም ።

በርንስቴይን ወደ ሪቻርድሰን እየተመለከተች " ችግር የለም ኰሎኔል ፤ ተራ ሴት አይደለሁም ። በራሴ ላይ ከፍተኛ እምነት ያለኝ ነኝ ። ጄኔራልም ቁጥብ ሰው ነው " ብላ ረጋ ባለ መንፈስ ነገረችው ።

ሪቻርድሰን ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ።

ላስኮቭ ለማስተዋወቅ ሲያቅማማ ሚሪያም ለመውጣት እበሩ ላይ ደርሳ ዘወር በማለት " ሰዎቹን በመንገዱ ላይ አይቻቸዋለሁ ፤ ታክ ሲ እንዲመጣልኝ ጠርቻለሁ ፤ ጃባሪ እየጠበቀኝ ስለሆነ በአፋጣኝ መ ሔድ አለብኝ ። የመጨረሻው ውይይት በሚደረግበት ጊዜ እንገናኛ ለን " ብላ በላስኮቭ ትከሻ ላይ በመመልከት " መልካም ቀን ኰሎ ኔል " አለችው ።

ሪቻርድሰን ስለጉዳዩ ምንም እንደማያውቅ አድርገው እንዳያስቡ ለማድረግ " ሰላም ይሁንላችሁ ፤ በኒውዮርክ መልካም ዕድል ይግጠ ማችሁ " አላት ።

ሪቻርድሰን የቡና ሲኒውን እየተመለከተ " የዚህ ዓይነት ቡና ዳግመኛ አልጠጣም ። ቁርስ አብረን ሔደን ከበላን በኋላ ወደ ኤምባ ሲዬ ስሔድ እግረመንገዴን ወደ ጦር ምሽግህ አደርስሀለሁ " አለው ።

ላስኮቭ ግብዣውን በመቀበል ወደ መኝታ ቤቱ ገብቶ ማዕረጉን የሚያሳይ ሁለት የወይራ ቅጠሎች ያሉበት ካኪ ሸሚዙን ለበሰ ። አው ቶማቲክ ሽጉጡን በአንድ እጁ ይዞ ሸሚዙን በሱሪው ውስጥ አስገ ብቶ እየታጠቀ በመስኮቱ ሲመለከት ማንነታቸው የማይታወቅ ሁለት ሰዎች ራሳቸውን ደፍተው ጫማዎቻቸውን ይመለከቱ ነበር ። ሚሪያም ሲጠብቃት በነበረው ታክሲ ውስጥ ገብታ ሔደች ።

ላስኮቭ በነፋሱ ምክንያት የመቁነጥነጥ ሁኔታ ተሰምቶታል ። ይህ መጥፎ ነፋስ በየአገሩ ልዩ ልዩ ስሞች ተሰጥተዉታል ። በእስራ ኤል ሀማሲን ወይም ሻራቭ (ሞቃታማ ነፋስ) ተብሎ ይጠራል ። ላስኮቭና ሌሎችም ሰዎች በዚህ ነፋስ የሚታመሙ ወይም የሚታወኩ ፣ በስነልቦናም በኩል ችግር የሚፈጠርባቸው ነበሩ ። የሆነ ሆኖ በ19 ሺህ ሜትር ከፍታ ላይ ይህ ነፋስ ስለማይኖር ላስኮቭ ችግር እንደማይኖርበት አምኗል ። በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ የፀደይ ሞቃታማ ነፋስ መምጣቱ ጥሩ ነበር ። ወደ ሰማዩ አንጋጦ ሲመለከት ሰማዩ ፍጹም ጥራት ስለነበረው ለበረራ አመቺ ቀን ነበር ።

## — 2 —

አብደል ማጂድ ጃባሪ ተቀምጦ በስኒው ውስጥ የነበረውን ጥቁር ቡና ትኩር አድርጐ እየተመለከተ “ በጣም ፍርሀት ተሰምቶኝ እንደ ነበረ ስነግርሽ ያለአንዳች ማፈር ነው ። አንድ የጸጥታ ሠራተኛ በእጄ ሊያልፍ ምንም ያህል አልቀረውም ነበር ” አላት ።

ሚሪያም በርንስቴይን ፣ ጃባሪ ባለው በመስማማት ራስዋን ነቀነቀች ። ወቅቱ የበዓል ማክበሪያ ጊዜ ስለነበር ሁሉም በየፊናቸው ይሯሯጡ ነበር ። በሌላ በኩል ደግሞ የመጨነቅ ሁኔታም ይታይ ነበር ።

ሚሪያም “ ስህተቱ የእኔ ነው ፤ ይህ እንደሚሆን ማወቅ ነበረብኝ ” አለችው ።

ጃባሪ እጁን ወደላይ አንስቶ “ ግድየለም ፤ ሽብር ፈጣሪዎች የሆኑ ፍልስጥኤማውያን በያለበት እናያለን ። በእውነት ከሆነ ግን በአሁኑ ጊዜ ብዙ የሉም ” አላት ።

“ ይህ እስከመቼ ይሆን የሚቀጥለው ? አንተን በተለይ ስለሚከታተሉህ መጠንቀቅ አለብህ ። ለእንግዳ ሰው ባልተለመደ አገር ሁኔታው ከባድ መሆን አለበት ” አለችው ።

“ እኔ የተወለድኩት እዚህ አገር ስለሆነ እንግዳ አይደለሁም ። አንቺ ግን እዚህ አልተወለድሽም — ” ካላት በኋላ በተናገረው ፀፀት ስለተሰማው አስታራቂ የሚሆን ፈገግታ እያሳየ “ የአንተ ጉዳዮች የእነርሱም ጭምር መሆናቸውንና መፍትሔአቸውም የጋራ መሆን እንዳለበት እንዲያውቁት ብታደርግ ወንድሞችህ ይሆናሉ ” የሚለውን የአረቦች ምሳሌ ነገራት ።

ሚሪያምም በበኩልዋ ሌላ የአረቦች አባባል አስታወሰች ። “ወደ ተወለድኩበት ቦታ መጥቼ የወጣትነት ወዳጆቼ የት ናቸው ብየ ጮ

ኩ ” ብላ ንግግርዋን ለትንሽ ጊዜ ቆም ካደረገች በኋላ “ እንደምገም ተው አባባሉ ለሁለታችንም ይሆናል ። በአሁኑ ጊዜ ይህ መሬት የአ ንተ አይደለም አብደል ፤ ይህን ዳርቻ እግሬ ከነካበት ጊዜ ጀምሮ የእኔ መሬት ነው ። — ራሳቸው ተፈናቅለው ሌሎች ጭቁኖችን የሚያፈ ናቅሉ ። ድርጊቱ . . . ከጭካኔም በላይ የሚቆጠር ነው ። ”

ጃባሪ የሴትዮዋ አስተሳሰብ ወደ መጥፎ እያዘነበለ መምጣቱን ስላ ስተዋለ “ ሚሪያም ፡ የፖለቲካውንና የጂኦግራፊውን ወደጐን እንተ ወውና ሌላውን ስንመለከት በአረቦችና በአይሁዶች ባሕል መካከል ብዙ ተመሣሣይ ነገሮች አሉ ። እኔ እንደማስበው ከሆነ በመጨረሻ ሁሉም ወገኖች ይህን አምነዋል ” ካላት በኋላ በብርጭቆው ውስጥ ቀመም ያለው ሻይ ቀድቶ በማንሳት “ በእብራይስጥ እናንተ — እኛ— ሻሎም አልክሄም — ሰላም ለእናንተ ይሁን — የሚል ሲሆን በአረ ብኛ ደግሞ — ሰላም አሌይኩም — እንላለን ። ሁለቱም ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ” አላት ።

ሚሪያም በርንስቴይን የሞላችውን ብርጭቆ ከፍ አድርጋ በመ ያዝ “ ሰላም ይሁንልህ ” ብላ ከጠጣች በኋላ ጨዋታዋን ተሰማት ።

ቁርሳቸውን እየበሉ በኒውዮርክ ስለሚደረገው ስብሰባ ተጫወቱ ። ሁለቱም በንግግር ይግባባሉ ። በተባበሩት መንግሥታት በአንድ ጠረ ጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ከአረቦች ጋር ስለሚያደርጉት የሰላም ድርድር ሚሪያም ሥጋት አድሮባታል ። ጃባሪ ላለፉት 30 ዓመቶች ከአረቦች ጋር ተለያይቶ ስለኖረና ለእስራኤልም ያለው አስተሳሰብ ጥሩ ስለነበረ ከእርሱ ጋር የምታደርገው ውይይት ያለአንዳች መቆጠብና በግልጽ ነበር ። የዘር ጉዳይ በሚነሳበት ጊዜ ግን የተለየ ስሜት ያሳይ ነበር ።

በርንስቴይን በዚያ በወፍራም ድምጽዋ ታወራ በነበረበት ጊዜ በጽሞና ያዳምጣትና ይመለከታት ነበር ። ጃባሪ ባለፉት ዓመቶች ቀስ በቀስ ታሪኳን ለማወቅ ችሏል ። እርሷም ስለእርሱ ታሪክ ማወቅ ችላ ለች ። ሁለቱም የዓለምን ውጣ ውረድ ተረድተዋል ። ሁለቱም የሕዝ ቦቻቸው ቁንጮ በመሆን የታሪክን ሒደት በጥሩ ወይም በመጥፎ ለመ ለወጥ በሚያስችላቸው ሁኔታ ላይ ደርሰዋል ።

ሚሪያም በርንስቴይን ከአውሮፓ እልቂት የተረፈች ነበረች ። የተ ገኘችው እያጠቃ ወደፊት በሔደው በቀዩ ጦር ሰዎች እየተያዙ እንዲ ቆዩ በሚደረግበት በአንድ መከማቻ ሠፈር ነበር ። ወላጆች ፡ ቤተሰቦ ች ፡ አንዲት ሕጻን እህት እንደነበሩዋትና እርስዋም አይሁዳዊት እንደ ነበረች አስታውሳለች ። ከዚህ ሌላ የምታውቀው ጥቂት ነበር ። ምና ልባት የእስር ቤቱን ከሚጠብቁ ዘበኞች ይሆናል የተማረችው ፤ ጀር

መንኛ በመጠኑ ትናገራለች ። እንዲሁም የፖላንድ ቋንቋ በመጠኑ ትና ገራለች ። ይህንንም ምናልባት የተማረችው አብረዋት ታስረው ከነ በሩ የፖላንድ ልጆች ሳይሆን አይቀርም ። በተጨማሪም ጥቂት የሁን ጋርያ ቃላት ትችል ስለነበረ ዜግነትዋ ሁንጋሪያዊ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ እንዲታመን አድርጓታል ። አብዛኛውን ጊዜ ዝምተኛ ልጅ ስለ ነበረች የጀርመን፣ የፖላንድ ወይም የሁንጋሪ አይሁዳዊት ትሁን ወይም አትሁን ከቁም ነገር አትቆጥረውም ነበር ። አንድ ነገር ብቻ በእርግጥና ያለመጠራጠር ያመነችው አይሁዳዊት መሆንዋን ነበር ።

ቀዩ ጦር እርስዋንና ሌሎች ልጆችን የመንገድ ጥገና ወደሚካሔ ድበት ሰፈር ወሰዳቸው ። በቀዝቃዛው ክረምት ምክንያት ብዙዎቹ ሞቱ ። የቀሩት ልጆች በፀደይ ጊዜ ወደመስክ እየተወሰዱ ይሠሩ ነበር። ከሆስፒታል ድናና አገግማ ከወጣች በኋላ ባልና ሚስት የሆኑ አይሁዳ ውያን በአሳዳጊነት ተረከቧት ።

አንድ ቀን ከአይሁዳውያን ድርጅት ጥቂት ሰዎች መጡ ። እር ሷና አሳዳጊዎቿ ከሌሎች ጋር ሆነው ጦርነት ያጠቃትን አውሮፓን በባቡር አቋርጠው ለብዙ ሳምንቶች ተጓዙ ። ሁኔታው ለእርስዋ የቀን ቅዠት ሆነባት ። ቀጥለውም በመርከብ ተሳፍረው የባሕር ጉዞ ጀ መሩ ። ሀይፋ እንደደረሱ መርከባቸው በዚያ እንዳያርፍ በእንግሊዝ ወታደሮች ተገዶ ተመለሰ ። መርከቡ ጨለማውን ተገን በማድረግ ወደ ሌላ ዳርቻ ሔዶ ተሳፋሪዎቹን ለማራገፍ ሞከረ ። ይሁን እንጂ የባሕ ሩን ዳርቻ ለመያዝ በሚፈልጉ አይሁዳውያንና ከመርከቡ እንዳይወ ርዱ በሚፈልጉ አረቦች መካከል በተነሳው ጠብ ምክንያት አስከፊ ጦርነት ተከፈተ ። ሆኖም የእንግሊዝ ወታደሮች ጦርነቱን አስቁ መው መርከቡ ከዚያ ግድም እንዲሔድ አደረጉ ። እርስዋ ጦርነቱ ከመ ከፈቱ በፊት ከመርከቡ ከወረዱት አንዷ ስለነበረች መርከቡ ወዴት እንደሔደ አላወቀችም ። ስማቸውን የማታስታ ውሳቸው አሳዳጊዎችዋ ጠፉባት ። በባሕር ዳርቻው በተደረገው ጦርነት ይሙቱ ወይም በመር ከቡ ተመልሰው ይሔዱ የምታውቀው ነገር የላትም ።

ሌሎች አይሁዳውያን የሆኑ ባልና ሚስት ከባሕር ዳርቻው ወስ ደው ልጃቸው እንደሆነችና ስምዋም ሚሪያም በርንስቴይን እንደሆነ ለእንግሊዝ ወታደሮች አስረዱ ። በተጨማሪም ከቤታቸው አምልጣ በመሔድ አሁን በጦርነቱ መካከል ያገኟት መሆናቸውንና የተወ ለደችውም በዚሁ በፍልስጥኤም ውስጥ መሆኑን ለወታደሮቹ ነገሩ ። ሁለቱ ወጣት ባልና ሚስት ለመዋሸት ብዙ ልምድ እንዳል ነበራቸውና የእንግሊዝ ወታደሮችም ልጅቱን ከተመለከትዋት በኋላ ትተዋቸው እንደሔዱ ታስታውሳለች ።

[illegible] HAILE - ALIF

ቤተሰቦችዋ ከቴል አቪቭ ወጣ ብሎ ወደሚገኝ ወደ አንድ የሕብረት ልማት መንደር ይዘዋት ሔዱ ። እንግሊዞች ፍልስጥኤምን ለቀው እንደወጡ አረቦቹ መንደሩን ወረሩ ። አዲሱ አባትዋ አረቦቹን ለመከላከል እንደወጣ አልተመለሰም ። ብዙ ዓመቶች ካለፉ በኋላ ታላቅዋ የሆነው የእንጀራ አባትዋ ልጅ ዮሴፍ እንደ እርስዋ ጉዲፈቻ እንደነበረ ለማወቅ ቻለች ። ይህ ለእርስዋ አዲስ ነገር አልነበረም ። ምክንያቱም በዓለም ላይ — በእርሷ ዓለም — አብዛኞቹ ልጆች በአውሮፓ ውስጥ ከነበሩ እስር ቤቶች ከሞት ተርፈው የመጡ መሆናቸውን ለማወቅ በመቻልዋ ነበር ። ዮሴፍ በርንስቴይን እርስዋ የደረሰባትን — ምናልባትም በበለጠ — ደርሶበታል ። እርሱም እንደ እርስዋ እውነተኛ አባትና እናቱን ፤ ትክክለኛ ስሙን ፤ ዜግነቱንና ዕድሜውን አያውቅም ። በመጨረሻም ሁለቱ ወጣቶች በፍቅር ስለተሳሰሩ ተጋቡ ።

ሚሪያም በርንስቴይን በአይሁዳውያንና በአረቦች መካከል ሰላም ሊወርድ ስለሚችልበት ጉዳይ ቀደም ብላ በመጀመር ታደርገውና ታሳየው በነበረው አስተሳሰብ በአካባቢዋ በሚኖሩ አረቦች ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነትንና ጥሩ አስተያየትን አግኝታለች ። በመንደሩ ውስጥ የሚኖሩ የእርስዋ ወገኖች ግን በጥርጣሬ ዐይን ይመለከትዋት ስለነበረ ከወዳጆችዋና ከጐረቤቶችዋ ጋር የመራራቅ ሁኔታዋ እየጨመረ መምጣቱ ተሰምቷታል ። አላማዋ በደንብ የገባው ግን ዮሴፍ ብቻ ነበር ። ለእርሱም ቢሆን ተዋጊ አውሮፕላን አብራሪ ሆኖ የሰላም መልዕክት ዘንባባ ካቀፈች ሚስት ጋር መኖሩ ቀላል አልነበረም ።

ከ1973 ጦርነት በኋላ ከእስራኤላዊ አረቦችና ከሰላም ንቅናቄ ሴቶች ማህበር ጋር የነበራትን ከፍተኛ አድናቆት በመመልከት ፓርቲው የእስራኤል ምክር ቤት አባል እንድትሆን መረጣት ።

በጠቅላይ ሚኒስትር ሜየር ዘንድ ወደዚያው በበለጠ ስለታወቀች ሁለቱ የቅርብ ወዳጆች ሆኑ ። በ1974 ወይዘሮ ሜየር የሥራ ሙልቀቂያ ባቀረበች ጊዜ ሚሪያም በርንስቴይን በምክር ቤቱ ውስጥ የሜየር ጆሮ ፣ ዐይንና አንደበት ነበረች ። ሚሪያም በሜየር ድጋፍ የፖስታ ምክትል ሚኒስትር ሆነች ። በየጊዜው በምክር ቤቱ ውስጥ የመንግሥት መለዋወጥ ሲደረግ ሚሪያም መቀመጫዋንና ሥራዋን ሳታጣ ለብዙ ጊዜ ቆይታለች። በየጊዜው በተደረገው ሹምሽር ሥራዋን እንደያዘች የቆየችው በምታደርገው ሁሉ ተወዳጅነት ስለነበራት የማይወዱት እንኳን ስለመልካም አስተሳሰብዋ በሥራዋ ላይ እንድትቆይ ይፈልጉ ነበር ።

ስለሜየር ርዳታና ድጋፍ በምታስታውስበት ጊዜ በቀደምትነት ቀላሎቹ ነገሮች በፊትዋ ላይ ይደቀኑባታል ። ከእነዚህም ጥቂቶቹ የሚ

ከተሉት ነበሩ ። ሌሊቱን ሙሉ የካቢኔ ስብሰባ ሲያደርጉ አድረው ሲጨርሱ ጠቅላይ ሚኒስትሪቷ ወደ ሚሪያም አፓርትሜንት አብራ በመሔድ ቡና እፍልታ ሚሪያምን ታጠጣት ነበር ። እንደዚሁም በመንግሥት ፖሊሲ መሠረት የካቢኔ ስምዋን በእብራይስጥ ስም እንድትለውጥ በተጠየቀችበት ጊዜ ሜየር — የቀድሞ ስሟ ሜየርሰን — ለመለወጥ የማትፈልግ መሆንዋን በማወቅዋ አቋሟን ደግፋላታለች ።

የሜየርን ሥራ አንድ ቀን ትወስዳለች የሚሉ ሰዎች ቢኖሩም ሚሪያም በርንስቴይን ግን ምንም ዓይነት ፍላጐት አድሮባት እንደማያውቅ ገልጻለች ። ሜየር ጠቅላይ ሚኒስትሪት ሆና የተሾመችው ሥራውን ስለማትፈልገው ነው እየተባለ ይወራ ነበር ። እስራኤሎች ሥልጣን የማይፈልጉትን ሰዎች በሥልጣን ላይ ማስቀመጥ የተሻለ ነው ብለው ያምናሉ ።

አሁን ግን ሚሪያም በርንስቴይን ከጠቅላይ ሚኒስትሪትነት የበለጠ የምትወደው ሥራ አግኝታለች ። ይኸውም የሰላም ድርድር ተወካይ ሆና እንድትሠራ መደረግዋ ነው ። ከጥቂት ወሮች በፊት ያልነበረ ሥራ ቢሆንም አንድ ቀን የዚያ ዓይነት ሥራ እንደሚኖር አውቃለች ።

በኒው ዮርክ በግልዋ ጭምር የምታከናውናቸው ብዙ ተግባሮች ነበሩዋት ። በዮም ኪፑር ጦርነት ጊዜ በውጊያ ላይ እንዳለ ብቸኛ ልጃቸው ኤሊያሁ ተገድሏል ። ዮሴፍም ከጠፋ ሦስት ዓመቶች አልፈውታል ። በኒው ዮርክ ስብሰባ በምታደርግበት ጊዜ ምናልባት ከአረቦቹ ስለባልዋ ፍንጭ የምታገኝበት ዘዴ ይኖር ይሆናል የሚል አስተሳሰብ አድሮባታል ።

ጃባሪ ከውጭ መጠነኛ ጩኸት ስለሰማ ሳያውቀው እጁን በኪሱ ውስጥ አስገብቶ ሽጉጡን ጨበጠ ።

ሚሪያም በርንስቴይን ግን የምትናገረው ተመስጣ ስለነበረ በውጭ ስለላው እንቅስቃሴ አላጤነችም ። “ ሕዝቡ ዘላቂ ሰላም እንዲኖረው በማሰብ የመረጠው መንግሥት ስለሰላሙ ድርድር አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ፈቃድ ሰጥቷል፥አብደል። በቀላሉ እንደማንበረከክ ለዓለም አሳይተናል ። ሳዳት ይህን ለማወቅ ከቻሉት ዘመናዊ የአረብ መሪዎች አንዱ ነው ። ሰላምን ለመፈለግ ወደ ኢየሩሳሌም የመጡትን የብዙ ሰዎች ፈለግ ተከትሎ በመምጣቱ ለ30 ዓመቶች የነበረው ችግር እንዲሰባበር አድርጎታል ” ካለችው በኋላ ከትከሻዋ ወደፊት ሰግደድ ብላ “ በኃይል በመዋጋታችን የብዙ አገሮችን ከበሬታ አግኝተናል ። በአሁኑ ጊዜ ጠላቶቻችን በበራችን ላይ አይደሉም ። ለረጅም ጊዜ የነበረው ከበባ ተወግዷል ። አሁን ሕዝቡ ተቀራርቦ ለመወያየት በሚችልበት ደረጃ ላይ ነው ” በማለት በሰፊው ተረከችለት ።

ጃባሪ በአዎንታ ራሱን እየነቀነቀ “ ተስፋ አለኝ ” አላት ። ሚሪ ያም ንግግርዋን እንደቀጠለች በትከሻዋ ላይ አሻግሮ በመንገዱ ላይ የተሰበሰበውን ሕዝብ ሲመለከት እጅዋን በእጁ ላይ ጣል ስታደርግ ተሰማው ። “ አንተስ አብይል ? አዲስ የፍልስጥኤም ግዛት ቢመሠረት ትሔዳለህ ? ” ብላ ጠየቀችው ።

ጃባሪ ለጥቂት ጊዜ በሐሳብ ተዋጠ ። “ የምክር ቤት አባል እንድ ሆን የተመረጥኩ ነኝ ። በዚህ የተነሳ በአዲሱ የፍልስጥኤም ግዛት ውስጥ ተቀባይነት አገኛለሁ ብየ አላስብም ” ብሎ ከነገራት በኋላ የእጅ ጣቶቹን አሰባጥሮ “ ማን ያውቃል ፤ ያን ዕድል እጠቀምበት ይሆናል ። በዚያም እንደገና ከቤተሰቦቼ ጋር እዋሀድ ይሆናል ” አላት።

ሚሪያም በርንስቴይን ባቀረበችለት ጥያቄ አዝና “ መልካም፡ለወ ደፊቱ ሁላችንም የየራሳችን ውሳኔ ይኖረናል ። በአሁኑ ጊዜ ዋናው ቁም ነገር ስለዘላቂው ሰላም ለመወያየት ወደ ኒውዮርክ መሔዳችን ነው ” አለችው ።

ጃባሪ ራሱን በአዎንታ በማነቃነቅ “ አዎን ፤ በአሁኑ ጊዜ የሰላም አዝማሚያ ስላለ ሳንውል ሳናድር ማድረግ አለብን ። በዘገየን ቁጥር የሚ ያደናቅፍ እንቅፋት እንዳያጋጥመን እፈራለሁ ። አንድ ድርጊት ወይም አለመግባባት እንዳይፈጠር ማለቴ ነው ” ብሎ ካጫወታት በኋላ አሁ ንም ወደፊት ጐብደድ ብሎ “ ኮከቦቹ ሁሉ — ማህበራዊ ፣ ታሪካዊ ፣ ኤኮኖሚያዊ ፣ ወታደራዊና ፖለቲካዊ — እነዚህ ሁሉ ለብዙ ሺህ ዓመ ቶች ያልነበራቸውን በቅድስት አገር ውስጥ ሰላም እንዲኖር ተስማም ተዋል ። ጊዜው ጸደይ ነው ። ስለዚህ ለመነጋገር የሚያስቸግር ነገር የለም ። ትክክል አይደለንምን ? ” ብሎ ጥያቄ ካቀረበላት በኋላ ከተቀ መጠበት ተነስቶ “ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ኒውዮርክ ደርሰን ስብሰባ ውን ጀምረን ቢሆን ኖሮ ምን ያህል ጥሩ ነበር ” በማለት ከልብ የመ ነጨ ምኞቱን ገልጾላት ወደ ጐዳናው እየተመለከተ “ አንደማስበው አውሮፕላኖቻችን እየመጡ ነው ። እስቲ እንያቸው ” አላት ።

ሕዝቡ ከቡና ቤቱ እየወጣ በሩጫ ወደ ጐዳናው ሔደ ። ከሰሜን በኩል ሁለት ኮንኮርዶች ወደ ሎድ አየር ማረፊያ እየተቃረቡ ነበሩ። አንደኛው ኮንኮርድ ለማረፍ ዝቅ እያለ በመጣ ጊዜ ነጭ ቀለም በተቀ ባው ጅራቱ ላይ ሰማያዊ ቀለም ያለውን የዳዊትን ኮከብ ሕዝቡ ማየት ቻለ ። አልፎ አልፎም ከአረቦቹና ከአይሁዳውያን ጭብጨባ ተሰማ ።

ሚሪያም በርንስቴይን እንዳያብረቀርቃት እጅዋን በዐይኖቿ ቅን ድቦች ላይ አድርጋ ኮንኮርዶቹ ለማረፍ ዝቅ እያሉ ሲመጡ አየቻቸው ። ከአየር ማረፊያው ባሻገር የሰማሪያ ተራሮች ከሜዳው በላይ ጉብ ብለ

ው ይታያሉ ። ሌሊቱን ከተራራዎቹ ላይ በነፋስ ኃይል መጥቶ የነበ ረው የለውዝ አበባ ሽታ ትውስ አላት ። ተራሮቹ በሐምራዊና በነጭ ደመና ተሸፍነዋል ። በተራራው ግርጌ ያለው ድንጋያማ ቦታ በለመ ለሙ አረንጓዴ ቅጠላቅጠሎች ከመሸፈኑም በላይ በሚያብረቀርቁ ልዩ ልዩ አበቦች ተውቧል ። በሞቃቱ አየር (ሀማሲን) መምጣት ምክ ንያት በየዓመቱ ከሚያብቡት አበቦች ጋር በቅድስት አገር የሰላም ጮራ እየፈነጠቀ ነበር ። ወይም የሚፈነጥቅ መስሏል ።

* * *

ቶም ሪቻርድሰንና ቴዲ ላስኮቭ በሔርዝልያ ከቡና ቤቱ ወጥተው በሪቻርድሰን ቢጫ መኪና ተሳፍረው የቴል አቪቭን የዓርብ ቀን ከባድ ትራፊክ ተያያዙት ። አየር ኃይል ዋና መሥሪያ ቤት በምሽጉ አጠገብ እንደደረሱ መኪናው በትራፊክ መብራት ምክንያት ስለቆመ ላስ ኮቭ የመኪናውን መዝጊያ እየከፈተ “ ከዚህ በእግሬ እሔዳለሁ ፤ አመ ሰግናለሁ ፤ ቶም ” አለው ።

ሪቻርድሰን ተመልክቶት “እሺ ፤ ከመብረርህ በፊት እንገናኛለን” አለው ።

ላስኮቭ የመኪናውን መዝጊያ ከፍቶ አንድ እግሩን እንዳወጣ የሪ ቻርድሰን እጅ በትከሻው ላይ ሲያርፍ ስለተሰማው ዞሮ ተመለከተው ።

ሪቻርድሰን ለጥቂት ሴኮንዶች አተኩሮ ከተመለከተው በኋላ “ ስማ ፤ በሰማይ ላይ ምላጭ እንዳትስብ ። እዚያ ምንም ነገር እንዲፈ ጠር አንፈልግም ” አለው ።

ላስኮቭ በጥቁር ዓይኖቹ እንደመተከዝ ብሎ ተመለከተው ። ግን ባሩም ተጨማደደ ።

የቴል አቪቭ መኪናዎች ድምጽ ኃይለኛ ስለነበረ ላስኮቭ ጮኾ “እኛም አንፈልግም ። የእኛ ፍላጐት ኮንኮርዶቹ በሰላም እንዲደርሱ ማድረግ ነው ። ነገር ግን ሊያደናቅፈን የሚችል ምንም ዓይነት ነገር ቢመጣ ወይም ቢታይ ያለማወላወል እንመታዋለን ” ካለው በኋላ ላስ ኮቭ ሻንጣውን አንጠልጥሎ ሔደ ።

አረንጓዴው የትራፊክ መብራት ስለበራ ሪቻርድሰን ጉዞውን ቀጠለ። በላይኛው ከንፈሩ ላይ የተጠራቀመውን የላብ ጭፍታ ጠርጐ በንጉሥ ሳኦል ጐዳና በኩል ወደቀኝ ዞሮ ሔደ ። ላስኮቭ እስከ አሁን ድረስ በአዕምሮው ውስጥ ይታየው ነበር ። በላስኮቭ ትልቅ ትከሻ ላይ ያረፈውን ትልቅ ኃላፊነት ለመገንዘብ ችሏል ። አስቸኳይና ፈጣን ውሳ ኔዎች የሚፈልጉ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ላስኮቭ በትክክልና በቆራጥነት እርምጃ እንደሚወስድ ሪቻርድሰን አረጋግጧል ።

ሪቻርድሰን ወደ ሒያርኪን ጐዳና ዞሮ በመሔድ አሚሪካን ኤም ባሲ ፊት ለፊት ሲደርስ አቁሞ በመኪናው መስታወት እየተመለከተ ጸጉሩን በጣቶቹ አበጠረ ። ቀኑ በመጥፎ ሁኔታ ጀመረ ።

ሁለቱ ነጭ ኮንኮርዶች እያንዣበቡ በሎድ አየር ማረፊያ ላይ ለማረፍ ዝቅ እያሉ ሲወርዱ ሪቻርድሰን አያቸው ።

* * *

ሳባህ ካባኒ ቆም አንድ የዳቦ ቁራጭ እያኘከ በትልቅ መነጽር ወደ ሎድ አየር ማረፊያ ተመለከተ ። በአካባቢው የነበሩት የኢየሩሳሌም ዛፎች በሞቃቱ ነፋስ ተወዛወዙ ። የኪስ ሰዓቱን አውጥቶ ከተመለከተ በኋላ አንድ ሰዓት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ በአውሮፕላን ማረፊያ ያለው የእንግዳ መቀበያ ክፍል በታዋቂ ሰዎች እንደሚሞላ ገመተ ። በተሰጠው መመሪያ መሠረት ኮንኮርዶቹ ከመነሳታቸው በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ እርምጃ ሊወሰድ ይቻላል ። የሚተኮሰው ጥይት ሰዎቹ በተሰበሰቡበት ክፍል ደርሶ ሙሉ ውጤት ለማግኘት ትንሽ የሚያስቸግር ይመስላል ብሎ ካባኒ አሰላሰለ ። ነገር ግን ነፋሱ ካቆመ ለመምታት ይቻላል ። ይህም ባይሆን ኮንኮርዶቹ የሚበሩበትን አስፋልት ማፍረስ ይቻላል ። ዋናው ቁም ነገር አንድ አደጋ ፈጥሮ በረራው ሊቀር የሚችልበትን ዘዴ መፈለግ ነበር ።

ከሰዎቹ አንዱ ዝቅ ባለ ድምጽ ተጣራ ። ካባኒ ሰውየው ወደሚያመለክትበት ቦታ ሲያይ ሁለት ኮንኮርዶች ከሰሜን በኩል ወደ ሎድ አየር ማረፊያ ሲመጡ አየ ። ካባኒ በመነጽሩ አማካይነት እነዚያን የ ሚያማምሩ አውሮፕላኖች አያቸው ። እያንዳንዳቸው 113 ሺህ ኪሎ ግራም ነዳጅ እንደሚይዙ አረጋገጠ ። ሁለቱ በአንድነት ሩብ ሚሊዮን ነዳጅ ስለሚይዙ አደጋ ቢደርስባቸው የፍንዳታቸው ጩኸት እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ ሊሰማ እንደሚችል ገመተ ።

## — 3 —

የሎድ ከተማ — የጥንቷ ሊዳ — በፀደይ መግቢያ ላይ በሚነፍ ሰው ደረቅና ሞቃታማ ነፋስ አራለች ። ሀማሲን የተባለው የዓመቱ ሞቃታማ ነፋስ ያለወትሮው ቀደም ብሎ በመጀመር ከወደ ምሥራቅ በመምጣት ከተማውን አቋርጦ ሀይል እየጨመረ ነፈሰ ። የሀማሲን ነፋስ የሚቆየው ለጥቂት ቀኖች መሆኑ ታውቋል ። ነገር ግን ቀስ በቀስ እየለሰለሰ ስለሚመጣ ለጤንነት ተስማሚ ይሆናል ። በአረቦች ባሕል መሠረት የዚህ ዓይነቱ ነፋስ የሚቆየው እስከ 50 ቀኖች ይሆናል — በአረብኛ ሀማሲን ማለት 50 ነው ። የመጀመሪያው ነፋስ ከጁዲያና

ከሰማሪያ ተራሮች ላይ የልዩ ልዩ አበቦች መዐዛ ስለሚያመጣ ሕዝቡ በደስታ ይቀበለዋል ።

የሎድ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ አንጸባርቋል ። አውሮፕላኖቹ በሩሙብት አካባቢ ብዙ የእስራኤል ወታደሮች ያለወትሮአቸው ጠመንጃዎቻቸውን አንግተው ቆመዋል ። መንገደኞች በሚሳፈሩበት ሜዳ አጠገብ የጸጥታ ሰዎች መነጽሮች አድርገውና ከፊታቸው ጋዜጦች ይዘው ቆመዋል ። ከአውሮፕላኑ ሜዳ መጨረሻ አልፎ በነበሩ የወታደሮች መኖሪያ ጐጆዎች አካባቢ ልዩ ጓዶች በተጠንቀቅ ቆመዋል ። እንደዚሁም በጐጆዎቹ በስተጀርባ ባለው የአስፋልት ሜዳ ላይ በአሜሪካ የተሠሩ 12 ኤፍ — 14 ተዋጊ አውሮፕላኖች (ቶምካትስ) ቆመዋል ። በተዋጊ አውሮፕላኖቹ ላይ የሚሠሩ መካኒኮችና በያጆች ከአብራሪዎችና ከበረራ መኰንኖች ጋር ይነጋገሩ ነበር ።

በሎድ ውስጥ የሚገኘው የቅዱስ ጊዮርጊስ ኦርቶዶክስ ቤተ መቅደስ ክርስቲያን በሆኑ አረቦችና በሌሎች የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ተሞልቷል ። ምንም እንኳን ለእያንዳንዳቸው የሚፈልጉት የተለየ ነገር ባይደረግላቸውም በዚህ ዓይነት ልዩ ቦታ ከሌሎች ጋር መገናኘቱ የመንፈስ እርካታ ይሰጣቸው ነበር ።

ፀሐይ ከመጥለቅዋ በፊት መደረግ ስለሚገባው ጸሎተ ሥርዓት በከተማው ውስጥ በነበሩ ምኩራቦች ሰዎች በቡድን በቡድን ተቀምጠው ለብዙ ሰዓቶች ዝቅ ባለ ድምጽ ይወያዩ ነበር ። በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አካባቢ በነበሩ የገበያ ቦታዎች አይሁዳዊ ሴቶች ለሰንበት ቀን የሚሆኑአቸውን ዕቃዎች ለመግዛት ይሸቀዳደሙ ነበር ። ሁልጊዜ አርብ ከሰዓት በኋላ ለሰንበት ቀን የሚሆኑአቸውን ሸቀጦችና የቤት ባልትናዎች ለመግዛት ያደርጉት የነበረው ሽሚያ አንዱ ለሌላው ደንታ እንዳልነበረው ያሳይ ነበር ። በሥነ ሥርዓት ባለመገበ ያየታቸው ጊዜአቸው በከንቱ ባክኗል ።

በራምላ በታላቁ የጀሚኤል ከቢር መስጊድ ፊት ለፊት ባለው አደባባይ ላይ ሙኤዚኑ ጸሎት ከመጀመሩ በፊት ሕዝቡ ተሰብስቧል ።

አረቦቹ የሚገበያዩበት ቦታ እንደ ሎዱ ብዙ ሕዝብ ቢኖርም በዚህኛው የነበረው ጫጫታና ጩኸት ከፍተኛ ነበር ። አረቦቹ በላንድሮቨሮች፣በመኪናዎች፣በፈረሶችና በግመሎች ላይ ሆነው የሚያውቁትን ሲያገኙ እየቆሙ ስለሚያወሩ ትርምሱ ከፍተኛ ሆኖ ታይቷል ።

በራምላ የወታደር እስር ቤት ውስጥ ከነበሩ ፍልስጥኤማውያን ሽብር ፈጣሪዎች ውስጥ ጥቂቶቹ በቅርብ ቀን በነፃ እንለቀቃለን የሚል ተስፋ ነበራቸው ።

የሎድና የራምላ ሁኔታ እንደቀረው እስራኤልና እንደመካከለኛው ምሥራቅ ዓይነት ነበር ። እያንዳንዱ ገናና ታሪካዊ ኃይል አንድ

ወቅት ይህን የዓለም ክፍል የጦር ሜዳ አድርጎ ተጠቅሞበታል ። ብዙ ሺህ ወታደሮችና ብዙ ሚሊዮን ወንዶች በዓለም ካርታ ላይ እንደ አንድ ነቁጥ በምትታየው በዚች ቅድስት አገር ተብላ በምትጠራው ላይ ተሰልፈዋል ። የልዩ ልዩ ርዕዮተ ዓለም ተከታዮችና አማኞች በዚች ቦታ ተገናኝተዋል ፤ ተጋጭተዋል ፤ ደምም ተቃብተዋል ። ፍርስራሾች ፥ በመቃብሮች ላይ ተጠርበው የቆሙ ድንጋዮች ወይም በመሬት ውስጥ ተቀብረው የተገኙ ቅርሶች በምሥራቅም ሆነ በምዕራብ ያሉትን የእያንዳንዱን ባሕል ሁኔታ ይገልጻሉ ።

ራምላና ሎድ የጥንታዊቱ አገር ታሪክ ምን እንደነበረና የአዲሲቱን እስራኤል መከፋፈልና አንድነት አጉልተው ያሳያሉ ። የብዙ ሃይማኖቶች የግዛት ሁኔታንም አንጸባርቀዋል — ተስፋ ያለፈንጠዝያ— ለቅሶ ያለእንባ — ።

* * *

የኤል አል የጸጥታ ሹም ያዕቆብ ሆስነር ስልኩን መልሶ ከዘጋ በኋላ ረዳቱ ወደሆነው ወደ ማቲ ያዲን ዞሮ “ እነዚህ ሰዎች ጤና የሚሰጡን መቼ ይሆን ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ እነእርሱ እነማን ናቸው ? ” ብሎ ማቲ ያዲን ጥያቄውን በጥያቄ መለሰለት ።

ሆስነር በጠረጴዛው ላይ የተንጠባጠበውን ቆሻሻ ጠረገ ። ብዙ ጊዜ ከራሱ ገንዘብ እያወጣ ያጸዳ ስለነበረ የጽሕፈት ቤቱ ንጽሕና ግሩም ነበር ። አየር ማረፊያውን ወለል አድርጎ ለማየት ወደሚችልበት መስኮት ሔዶ መጋረጃውን ሲከፍተው የብርሃን ፍንጣቂ ገባ ። “ሁሉም” ብሎ ሆስነር እጁን ካራገበ በኋላ “ ያ ምሽጋችን ነው ። ሰዎቹ ብዙ የተጨነቁበት አይመስሉም ” አለው ።

“ አልፈርድባቸውም ። ”

ሆስነር በቀዘቀዘ መንፈስ ያዲንን ለጥቂት ሴኮንዶች ተመለከተው።

ያዲን ፈገግታ እያሳየ አለቃውን ርኅራኄ ባለው ሁኔታ ተመለከተው ። ያለፉት ጥቂት ሳምንቶች በጸጥታ ክፍል ውስጥ ለነበሩት ሠራተኞች በሥራቸው አስከፊነት ምክንያት ያሳለፉት ጊዜ እጅግ ከባድ ነበር ። ሆስነር በመስኮቱ መካከል ሲመለከት ፍጹም በሃሳብ ተውጦ ያለፈውን የሕይወት ዘመኑን የሚዳስስ መስሎ ለያዲን ታየው ።

ያዕቆብ ሆስነር በልጅነቱ ወራት በ5ኛው ረድፍ ተሰደው ወደ ፍልስጥኤም ከገቡት ውስጥ አንዱ ነበር ። እነዚህ 5ኛው የጀርመን አይሁዳውያን ስደተኞች በ1933 ሂትለር ሥልጣን በያዘበት ጊዜ የቀድሞ ቤታቸውን ትተው ወደ ጥንታዊ አገራቸው የተመለሱ ነበሩ ። እነዚህ

ዕድለኞች ወይም እርቆ አስተዋዮች የአውሮፓ ዕልቂት ከመጀመሩ ቀደም ብሎ እንደልባቸው ለመንቀሳቀስ በሚችሉበት ወቅት ከአውሮፓ ውስጥ አምልጠው የወጡ ነበሩ ። ባለጸጐችና የተማሩ ስለነበሩ ሀብት ፣ ዕውቀትና ሙያ ይዘው ኮበለሉ ። ብዙዎቹ ኑሮአቸውን የመሠረቱት ቀድሞ የጀርመን ግዛት በነበረችው በሀይፋ ወደብ አካባቢ በመሆኑ በልጽገዋል ።

የሁለተኛው ዓለም ጦርነት በፈነዳ ጊዜ ሆስነር በ17 ዓመቱ በእንግሊዝ የጸጥታ ክፍል ውስጥ የምስጢር ሠራተኛ ሆኖ ተቀጠረ ። የሰለጠነው በእንግሊዞች በመሆኑ የአሠራር ዘዴው እንደ እንግሊዞች ነበር ። ሆስነር ቁጥብ ከመሆኑም በላይ የረጋ ጠባይ ነበረው ። አስተያየቱ እንደብዙዎቹ እንግሊዛውያን ቢሆንም በሥራው እጅግ በጣም ዋሩና ጥንቁቅ ነበር ። አስፈላጊ መሆኑን ካመነ ችሎታውን ሁሉ በመጠቀም ይሠራል ። ሆስነር ወጣትና ሀብታም ከመሆኑም በላይ የስለላ ሥራውን በፈለገው ዓይነት እየተለዋወጠ ሠርቷል ። የሥራው ተፈጥሮ ከአንዱ አገር ወደሌላው በመዘዋወርና በልዩ ልዩ ግብዣዎችና የመዝናኛ ሥፍራዎች እንዲገኝ ያስገድደው ስለነበረ እንደጀርመን ዜጋ ሆኖ ከሀይፋ ውጭ የጀርመን ቅኝ ግዛቶች ወደ ነበሩት ወደ ካይሮና እስታንቡል ተመላልሷል ። ሆስነር በዚሁ ሥራ ልዩ ችሎታ ስለነበረው በጣም ረቂቅና ውስብስብ ስለሆኑት ጉዳዮች ጭምር በማሰብና በመተንተን በተፈለገው ዓይነት ሕይወቱን ለዋውጦ መሥራት የሚችል ሰው ነበር ። ሆስነር ይህን ሥራውን ሾፒንን ፣ ሞዛርትንና ሳሸርቶርትን እንደሚያፈቅር ያህል አፍቅሮታል ።

ሆስነር ከጦርነቱ በፊት በአንድ የእንግሊዝ የግል በረራ ክፍል ተቀጥሮ የሲቪል አውሮፕላን በፍልስጥኤም ውስጥ ለማብረር ፈቃድ ካገኙት ከጥቂቶቹ አንዱ ነበር ። በጸጥታ ሥራው ላይ በተጨማሪ በዚህኛው ሥራውም ከፍተኛ ልምድ አግኝቷል ። ችሎታውን በበለጠ ለማሻሻል እንዲችል ተዋጊ አውሮፕላኖችና ሁሪኬይንስ በብዛት እንዲያበር እንግሊዞችን ጨቀጨቃቸው ።

ከጦርነቱ በኋላ ወደ አውሮፓ ተሻግሮ አሮጌ የጦር አውሮፕላኖች ሕጋዊ ላልሆነው ለሀጋናህ አየር ኃይል ጄኔራል ላስኮቭ ያበረረውን የመጀመሪያውን የእንግሊዝ ተዋጊ አውሮፕላን ገዛ ።

ከ1948 ጦርነት በኋላ ሆስነር በጸጥታና በበረራ ሥራዎች በቂ ችሎታ ስለነበረው የኤል አል የጸጥታ ሠራተኞች ከሆኑት የመጀመሪያው ነበር ። በዚያ ዘመን በእርሱ ዕድሜ ክልል ከነበሩ አይሁዳውያን ጋር ሲተያይ እርሱ የተሻለ ኑሮ ነበረው ። አሁን በሜዲትራንያን ባሕር አጠገብ በሔርዝሊያ በአንድ ትንሽ ቪላ ውስጥ ይኖራል ። ብዙ ቅም

ጦችና ውሽሞች የነበሩት ከመሆኑም በላይ በዚያ አካባቢ ከብዙ ሰዎች ጋር ለመተዋወቅ ችሎአል ። በሀይፋ የሚኖሩ ቤተሰቦቹን በሃይማኖት በዓል ቀኖች ጊዜ እየሔደ ይጠይቃቸዋል ። በአቋሙና በመልኩ ምክንያት ብዙ ሰዎች የአውሮፓን ባላባቶች እንዲያስታውሱ አድርጓቸዋል ። ቀጭንና ጉባጣ አፍንጫ ፤ ረጅም የጉንጭ አጥንትና ጥቅጥቅ ያለ ነጭ ጸጉር ነበረው ።

ሆስነር ወደ ያዲን እየተመለከተ “ በዚህ አውሮፕላን አንድ ሔድ እንደሚፈቅዱልኝ ተስፋ አለኝ ” አለው ።

ያዲን ራሱን ነቅንቆና ፈገግታ አሳይቶ “ አውሮፕላኖቹ ድንገተኛ አደጋ ቢደርስባቸው በኃላፊነት ማን ሊወነጀል ነው ” ብሎ ጠየቀው ።

“ አደጋ የሚለውን ቃል ልንጠቀምበት አይገባንም ማቲ ” ብሎ እርሱም ፈገግ አለ ። ሁሉም ነገር በሰላም እየተካሄደ ነው ። በሕይወቱ ዘመን ሁሉ እጹብ ድንቅ የሆነ የሥራ ውጤት ስላለው 01 እና 02 ኮንኮርዶች ይህንን ለብዙ ጊዜ የተመሰገነበትን ሥራውን ሊያጎድፉ አይችሉም ።

ማቲ ያዲን ተነስቶ ከተንጠራራ በኋላ “ ከጸጥታ ሰዎቻችን የተሰማ ነገር አለ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ሆስነር አሁንም በመስኮቱ መካከል አተኩሮ መመልከቱን ሳያቋርጥ “ የተሰማ ነገር የለም ። ፍልስጥኤማውያን ወዳጆቻችን የሚያስቡትን ባናውቅም እስከ አሁን ድረስ ምንም ዓይነት ኮሽታ አላሰሙም ” አለው ።

“ ጸጥታ ሰፍኗል ? ”

ሆስነር ትከሻውን ከፍና ዝቅ አደረገ ። መሠረት በሌለውና ባልሰማው ነገር ላይ አስተያየት ለመስጠት የማይፈልግ ሰው ነው ። ጭምጭምታ ከሌለ ወሬ የለም ። አንድ ቀንም አሳፍረውት ባለማወቁ በአገሩ የደህንነት ሠራተኞች ላይ ይተማመናል ። አንድ ቀጭን የእሥራኤል የጸጥታ ድር በአንድ ቦታ ላይ ብትነካ ድሩ ስለሚነቃነቅ በመሃል የተቀመጠችው ሸረሪት እንደምትሰማው ዓይነት የጸጥታ ክፍሉም የማያውቀው ነገር የለም ። ከድሩ ውጭ ያለው በጣም እሩቅ ስለሆነ የሚያሰጋ አይሆንም ።

ሆስነር መስኮቱን በመጋረጃው መልሶ አልብሶ ከተመለሰ በኋላ በግድግዳው ላይ በነበረው መስታወት ክረቫቱንና ኮቱን አስተካክሎ በጽሕፈት ቤቱ አቋርጦ በማለፍ ወደ መሰብሰቢያው አዳራሽ ገባ ። ያዲ

ንም ተከትሎ በመግባት በአዳራሹ ውስጥ ወንበር ሊያገኝ ወደሚች ልበት ወደ ኋላ ሔደ ።

በአዳራሹ ውስጥ የተሰበሰቡት ሰዎች ንግግራቸውን አቋርጠው ወደ ሆስነር ዞረው ተመለከቱ ። በትልቁ ክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ከተ ሰበሰቡት ውስጥ በእስራኤል ውስጥ እጅግ በጣም ታዋቂ ከሆኑት ጥቂቶቹ ነበሩበት ። ከእነዚህም ውስጥ ቼይም ማዛር ፣ የሺን ቤትዝ (የእስራኤል የአገር ውስጥ የሕዝብ ደህንነት አገልግሎት ) ኃላፊ ፣ ብርጋዲየር ጄኔራል ኢዝሀቅ ታልማን ፣ የአየር ኃይል የኦፕሬሽን ኃላፊ ፤ ጄኔራል ቤንጃሚን ዶብኪን ፣ የመከላከያ ቺፍ ኦፍ ስታፍን በመ ወከል ፤ ሚሪያም በርንስቴይን ፣ የትራንስፖርት ምክትል ሚኒስትሪ ትና ይስሐቅ በርግ ፣ የሚሽትዛን ኤሎሂም (የሽብር ፈጣሪዎች አጥቂ ቡድን) ኃላፊ ነበሩ ።

እንደዚሁም ከበርንስቴይን ሌላ አምስት የምክር ቤት አባሎች በስብሰባው ላይ ተገኝተዋል ። በግድግዳው ጥግ የበታች ረዳት መኰን ኖች ተቀምጠዋል ። እንደዚሁም አንድ ጸሐፊ ቃለ ጉባኤ ለመውሰድ በመዘጋጀት ላይ ነበር ። ሆስነር ወደ ክቡ ጠረጴዛ መጣ ።

ይህ ጊዜያዊ ኮሚቴ የተሰበሰበው የኮንኮርዶቹ በረራ ምንም ዓይ ነት እንከን እንዳያገኘው ለመወያየትና ስለዚሁ ጉዳይ ለሆስነር አንዳ ንድ ጥያቄዎችን በማቅረብ ስላለው ሁኔታ በጥልቀት ለመነጋገርና መፍትሔም ለመስጠት ነበር ።

ሆስነር ሁልጊዜም እንደሚያደርገው ሱፍ የለበሰው እርሱ ብቻ እንደነበረ አጢኗል ። ወደ ሚሪያም በርንስቴይን ፊት ለፊት ሲመለ ከት በዐይኖቿ ላይ ለውጥ አልነበረም ። ታዲያ ለምንድን ነበር ሁል ጊዜ ግምት ወይም አስተያየት የምትሰጥበት መስሎ የሚሰማው ? የፍ ትወተ ሥጋ ስሜት አድሮባታል እንዳይል አዘውትራ ስለማታደርግ ይህን ሐሳብ አምኖ ሊቀበለው አልቻለም ። ይሁን እንጂ አንድ ሐቅ ነበር ። ይኸውም በርንስቴይን ስሜትን የምትቀሰቅስ ነበረች ። ከእር ስዋ ላይ ዐይኖቹን አንስቶ ወደ ሌሎቹ ተመለከተ ። የትራንስፖርት ሚኒስቴር አለቃው ስለነበር ፣ ምናልባትም ይህን ጭንቀት የፈጠረበት ይኸው መስሎ ታሰበው ። እዚያው እንደቆመ ጉሮሮውን አፍታቶ “በዚህ ስብሰባ ላይ ለመገኘት የተስማማሁት አውሮፕላን ለማብረር እንደምችል በማንኛችንም ላይ ጥርጣሬ እንዳይኖሩ ለማድረግ ነው ” አላቸው ።

ሆስነር ወደመስኮቱ ተራምዶ ሲመለከት ከማኰብኰቢያው ሜዳ መጨረሻ ላይ ከሌሎቹ አውሮፕላኖች ራቅ ብለው በጅራቶቻቸው ላይ

የዳዊት ኮከብ የተሳለባቸው ሁለት ኮንኮርዶች ከፀሐዩ ብርሃን ጋር እያንጸባረቁ ቆመዋል ። በአውሮፕላኖቹ ዙሪያ የሆስነር የጸጥታ ሰዎች የኡዚ መሣሪያዎች ይዘው ይጠብቃሉ ። የጦር ክፍሉም አስር ወታደሮች ያለው አንድ ቡድን የላከ ቢሆንም የሆስነርን ሁኔታ አላ ረካውም ። እያንዳንዱ ተሰብሳቢ በአዳራሹ ውስጥ ስለነበረው ጸጥታ አጢኗል ።

ሆስነር በእጁ እያመለከተ “ የጦር መርከቦቻችን መኩሪያ እነዚ ያውና እዚያ ማዶ ። የእያንዳንዳቸው ዋጋ 80 ሚሊዮን የአሜሪካን ብር ነው ። ተሳፋሪዎቹን የአንደኛ ደረጃና በተጨማሪም 20 በመቶ እናስከፍላለን ። ሁላችሁም እንደምታውቁት ከአውሮፕላኖቹ እስከ አሁን ድረስ ምንም ገቢ አላገኘንም ” ብሎ ከነገራቸው በኋላ በምክር ቤቱ ውስጥ ከፍተኛ ተቃውሞ ወደምታቀርብበት ወደ ሚሪያም በር ንስቴይን እየተመለከተ “ እስከ አሁን ድረስ የኤል አል አየር መንገድ ለምን ትርፍ እንደማያስገኝ ታውቃላችሁ ? ምክንያቱም በሰው ሊደ ረግ የሚችል እጅግ በጣም ጠንካራ የጸጥታ ሥራ ስለሚያካሂድ ነው ። እንደሚታወቀው ጥሩ ጸጥታ ለማስፈን ከፍተኛ መስዋዕትነትን ያስከ ፍላል ” ብሎ ከመስኮቱ ትንሽ ፈቀቅ ሲል የሰዎቹ ዐይኖች ይከተሉት ነበር ። ንግግሩን በመቀጠል “ ከእናንተ ውስጥ ከጥቂት ወሮች በፊት ስለትርፍ ትጨነቁ ነበር ። በዚህም ምክንያት የጸጥታው ጉዳይ ላላ እንዲል ፈቃደኞች ነበራችሁ ። አሁንም እነዚያው ሰዎች ” ብሎ ወደ ሚሪያም በርንስ ቴይን እየተመለከተ “በቂ እንዳልሠራሁ አድርገው ያስ ባሉ ” አላቸው ። ሆስነር ተመልሶ ከተቀመጠ በኋላ “ ግድ የለም ፤ ይህን እንተወው ” ብሎ የጠረጴዛውን ዙሪያ ተመለከተ ። “አውሮፕ ላኖቹን በሜዳው ላይ ላለፉት 13 ወሮች አቁመናል ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የጸጥታ ሰዎች ዐይኖች ለአንድ አፍታ እንኳን አልተለዩአቸውም ። በቅዱስ ናዛየርና በቱሉስ ፋብሪካዎች የዕቃና ሌሎች ክፍሎችም ብረት እንዲለብሱ ተደርገዋል ። በዚህ በሎድ ውስጥም ማንኛውም የለ ውጥ ጥገና ሥራ የተከናወነው በኤል አል መካኒኮች ብቻ ነው ። በዛ ሬው ቀን ለአውሮፕላኖቹ የሚሞላውን ራሴ በቁጥጥር መልክ አይቼ አንደኛ ደረጃ ነዳጅ መሆኑን አረጋግጫለሁ ። ለኮንኮርዶቹ እያንዳን ዳቸው ተጨማሪ አንድ ረዳት የኃይል መስጫ በውስጣቸው እንዲቋ ቋም አድርጌአለሁ ። የዓለም ኮንኮርዶች ለመነሳት የሚጠቀሙት በመሬት ላይ ባለ የኃይል መስጫ ነው ። እኛ ግን እነዚህን እያንዳንዳ ቸው 900 ኪሎ ግራም ክብደት ያላቸውን ረዳት የኃይል መስጫዎች በመ ሥራታችን ኮንኮርዶቻችን በውጭ አገር አየር ማረፊያዎች በሌላ ኃይል ሳይጠቀሙ ራሳቸውን ችለው ለመነሳት የሚያስችላቸው ነው ። ለዚ ህም እኔም ሆንኩ እናንተ ሌላ ምርጫ የለንም ። ”

ስለተናገረው አስተያየት እንዳለ በማለት ሆስነር ዙሪያውን ቢመ ለከትም አንድም አልነበረም ። ንግግሩን በማራዘም “ ማንኛውንም አስፈላጊ ነገር የምናዘጋጀው በዚህ በሎድ አየር ማረፊያ ነው ። የምን ጠቀምበትን ውህ የምንይዘው ከዚህ ይሆናል ። የሸንት ቤት ጽዳት ሳይቀር የሚሠራው በእኔ የጸጥታ ሰዎች ነው ። አንድ በአንድ ምርመ ራና ፍተሻ ያደርጋሉ ። እቃዎቹን ሁሉ እንፈትሻለን ። ምግብ ሳይቀር ተቆጣጥሬአለሁ ። ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆኑን አረጋግጣለ ሁ ” ብሎ ወደ ኋላው ጋለል በማለት ሲጋራውን አቀጣጠለ ። ቀጥሎም “ ይህ አውሮፕላን ከሌሎቹ ሁሉ የበለጠ የማያሰጋ ስለሆነ ስለተሳፋ ሪዎቹ ምንም የሚያስፈራ ወይም የሚያሳስብ ነገር አይኖርም ” አላቸው ።

ሆስነር ወደ ማቲ ያዲን ዞሮ “ ረዳቴ ማቲ ያዲን በኮንኮርድ 01 ውስጥ የሚሳፈሩትን ሰባት የፀጥታ ሰዎች ለመምራት ፈቃደኛ ሆኗል ። ራሴ ደግሞ በኮንኮርድ 02 ውስጥ የሚሳፈሩትን የጸጥታ ሰዎች ለመ ምራት ፈቃደኛ ነኝ ። ይሁን እንጂ ከዚህ የመልዕክት ቡድን ጋር አብሬ ለመሔድ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ እስከ አሁን ድረስ አልተነገረኝም ” ብሎ እንደገና ዙሪያውን ከቃኘ በኋላ “ የኤል አል ደህንነትን በሚመ ለከት ጥያቄዎች አሉ ? የሉም ? በጣም ጥሩ ” አላቸው ።

በስብሰባው አዳራሽ ውስጥ ጸጥታ ሰፈነ ። ስብሰባው የተካሔ ደው በሆስነር የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ በመሆኑ ሊቀመንበሩ ራሱ ነበር ። ወደ ቼይም ማዛር ፡ የሺን ቤትዝ—የአገር ውስጥ የደህንነት— ኃላፊ ዞሮ “ የምታቀርበው ሪፖርት አለህ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ማዛር ከተቀመጠበት ቀስ ብሎ ተነሳ ። ረጅምና ቀጭን ሰው ነበር። ለብዙ ጊዜ በአገር ውስጥ የጸጥታ ክፍል የሠራ ሲሆን ጠባዩ ተለዋ ዋጭ ነበር።ባለጌ ነው የሚሉም አልታጡም ። ያላንዳች መግቢያ ንግግ ሩን በመጀመር“አንዳንድ ልክፍተኞች አንድ ሰው ሊሸከመው በሚችል መሣሪያ በዚህና በባሕር አካባቢ ባሉ የሮቅ ቤቶች ላይ በመሆን ተኩ ሰው አደጋ እንዳይጥሉ የሚል ጭንቀት ነበረን ። ይህ ሁኔታ እንዳይ ደርስ በማሰብ በዚህና በባሕር ዳርቻው መካከል ባሉ የሮቅ ቤቶች አን ድምሰው ቆሞ እንዳይታይ ከማድረጊም በላይ በተጨማሪ አውሮፕ ላኖቹ ለመነሳት በሚያኮበኩቡበት አካባቢ ማንም ሰው ዝር እንዳይል አዝዣለሁ ። ለዚህም የመከላከያ ሚኒስቴር በአየር ላይ ሆነው ሜዳውን የሚቆጣጠሩ ሔሊኮፕተሮች እንዲያሰማራ ጠይቄአለሁ ። በአ ሁኑ ሰዓት በእስራኤል ውስጥ ምንም ዓይነት የደፈጣ ተዋጊ እንቅስ ቃሴ ምልክት አልታየም ። ችግር እንደማያጋጥመን እርግጠኛ ነኝ ፤ አመሰግናለሁ ” ብሎ ተቀመጠ ።

የማዛር ንግግር አጭርና ቁም ነገር የተመላበት በመሆኑ ሆስኒር ፈገግታ ካሳየ በኋላ ወደ ይስሃቅ በርግ የሚሸትዛን ኤሎሂም — ሽብር ፈጣሪዎችን የሚከታተል — ኃላፊ ተመለከተ ።

በርግ እንደተቀመጠ ወደፊት ሰግደድ አለ ። በርግ አጭር፡ጨዋ ፣ ሽቢታምና የሚያስፈሩ ሰማያዊ ዓይኖች ነበሩት ። ሲመለከቱት ጭንቀት የሌለበት ይመስላል ። ሰውነቱ ከዕድሜው የበለጠ የበሰለ ይመስላል።በሥራው የማይበገርና አርበድባጅ ስለነበረ በዓለም ትቀፍ የነበሩት የፍልስጥኤም ደፈጣ ተዋጊ ድርጅቶች በብዛት እንዲጠፉ ያደረገ እርሱ መሆኑን ማንም ሰው አላመነም።የእርሱ ሰዎች እያሳደዱ የወሰዱት እርምጃ አስከፊ ስለነበረ በውጭም ሆነ በአገር ውስጥ ሽብር ፈጣሪዎች እንዲጠፉ አድርጓል ። “ በፓሪስ ውስጥ አንድ የጥቁሩ መስከረም የፍልስጥኤም የደፈጣ ቀንደኛ አባል የሆነ ሰው ከትናንትና በስቲያ አሳደን ይዘናል ። አንዳንድ ጥያቄዎች በጉጉት አቅርበንለት ስለነበረ የሰላሙን ድርድር ለማደናቀፍ የሚያስብ ቡድን መኖሩን የማያውቅ መሆኑን አረጋግጠልናል ። በአሁኑ ጊዜ የደፈጣ ተዋጊዎቹ የተበታተኑ በመሆናቸው ተገናኝተው እርስ በእርሳቸው ይወያያሉ ብሎ በእርግጠኝነት ለመናገር አይቻልም ። ከሰዎቹ አንዱ በፍልስጥኤም ድርጅት ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ያለው የጸጥታ ተከታታያችን ስለሆነ የሚተናኮል እቅድ እንደሌላቸው አረጋግጠልናል ” ብሎ በዝርዝር ነገራቸው ።

በርግ ፒፓውን በዳሰሳ ፈልጐ ካነሳ በኋላ ለብዙ ሴኮንዶች ትኩር አድርጐ ተመለከተው ። “ እንደተረዳነው የአረብ መንግሥታት የአሁኑ የሰላም ውይይት እንዲካሔድ እኛ የምንፈልገውን ያህል እነርሱም ይፈልጋሉ ። ከብዙ አቅጣጫዎች በደረሰን መረጃ መሠረት የታወቁትንም ሆነ የተጠረጠሩትን የደፈጣ ተዋጊዎች እንደሚከታተሉ ደርሰንበታል ። ምናልባት ትንሽ ግዴለሽነት ቢያሳዩም እኛ እንከታተላለን ” ብሎ በፒፓው ውስጥ ትምባሆ ጠቀጠቀ ። “ ጆን መክለር የአሜሪካ የማዕከላዊ ደህንነት ድርጅት አባል ከእኛ ጋር ግንኙነት ያለው ስለሆነ ወኪሎቹ ከአረቦች በኩል በየትኛውም ዓለም ጭምጭምታ እንኳን ያልሰሙ መሆናቸውን ያረጋገጡለት መሆኑን አስረድቶናል ። መክለር እንደ አጋጣሚ ከነገ ጀምሮ የዓመት እረፍቱን ስለሚጀምርና ወደ አገሩ ስለሚመለስ ለእኛ ክብር ሲል አብሮን እንደሚሔድ ነግሮኛል ” በማለት ፒፓውን እያቀጣጠለ ደስ የሚል ፈገግታ አሳያቸው ። ጣፋጩ የትንባሆ ጢስ በጠረጴዛው ላይ እየተጥመለመለ ወጣ ። ቀጥሎም ወደ ጄኔራል ዶብኪን ተመልክቶ “ በአገር ውስጥ ያሉት'አረቦች እንዴት ናቸው ? ” ብሎ ጠየቀው ። ቤንጃሚን ዶብኪን ተነስቶ የክፍሉን ዙሪያ ተመለከተ ። ጠንካራ ሰውነት ፣ ወፍራም አንገትና ዞማ ጸጉር አለው ። እንደ አብዛኞቹ የእስራኤል ጄኔራሎች የሸሚዙን

እጅጌ ጠቅልሎ ለብሷል ። ሰፊ ክንዶችና እጆች አሉት ። አማተር የአርኬኦሎጂስትነት ሙያ አለው ። የምድር ጦር ብርጌድ አዛዥ በነ በረበት ጊዜ ወታደሮቹ በፍላጐታቸውም ሆነ ሳይፈልጉ ለምሽግ ይሁን ለሽንት ቤት ወይም ለሌላ ጉዳይ ሳይመርጡ ይቆፍሩ ነበር ። ዶብኪን በተጨማሪ የሃይማኖት ሰው ስለሆነ የልብ እምነቱን በግልጽ ያሳያል ። ቆራጥ ፣ ጥብቅና በራሱ ላይ ሙሉ እምነት ያለው መሆኑን መኰንኖቹ በሰጡት ግምገማ ተረጋግጧል ።

ንግግሩን በማራዘም "ችግሩ ሁልጊዜም እንደነበረ አሁንም አለ። ሽብር ፈጣሪዎች በአለሙ አገሮች ውስጥ እየገቡና እየተዘዋወሩ ይቦርቁ ይሆናል ። ይሁን እንጂ የእስራኤል ወታደራዊ ኃይል ብዙዎቹን ለማ ጥቃት ችሏል።የአረብ መንግሥታትም በከፊል እያስገደዷቸው ነው" ብሎ ዙሪያውን ከተመለከተ በኋላ " ነገር ግን ከእናንተም ጥቂ ቶቻችሁ እንደምታውቁት በአረብ ገጠር የሚኖሩ የፍልስጥኤማውያን ወይም የሌሎች አረቦች ሽብር ፈጣሪዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ወታደ ራዊ ኃይላችን ሳያስገነዝብ አያልፍም ። የጦር ሠራዊታችን በእያንዳ ንዱ ቦታ እየገባ ለማጥቃት የሚችልበት መንገድ ውስን ነው ። ይሁን እንጂ በቂ የጸጥታ ሰዎች እንደ አረብ ሆነው በመዘዋወር ሁኔታውን እየተከታተሉ የሚያመጡ አሰማርተናል " ብሎ ካቅማማ በኋላ "ሁል ጊዜ እንደምናደርገው ሁሉ መሬታቸውን እንሰልላለን ። ይህንም ከሦ ስት ሺህ ዓመት በፊት ጀምረን አድርገነዋል ። "" እና ሙሴ የከነዓን መሬት እንዲሰልሉ ላካቸው ። አላቸውም ወደ ደቡብ ከሔዳችሁ በኋላ ወደ ተራራው ጫፍ ላይ ውጡ ፤ ከዚያም መሬቱን እዩ ፤ ምን እን ደሆነ ፤ እንደዚሁም በዚያ የሚኖሩት ሰዎች ጠንካሮች ወይም ደካሞች ጥቂቶቹ ወይም ብዙዎች መሆናቸውን እዩ ''' አላቸው ። "

ያአኮቭ ሳፒር የምክር ቤት ግራ ክንፍ አባል የሆነ " በበኩሌ በት ክክል የማስታውሰው ከሆነ እነዚህ የሙሴ ሰላዮች ወተትና ማር የሚ ፈስበት አገር ነው የሚል ሪፖርት አቀረቡለት ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በወ ታደራዊ ስለላ የሚቀርበውን ሪፖርት የሚያምን አንድም ሰው ይኖ ራል ብየ አላስብም " የሚል አነጋገር ወረወረ ።

በጠረጴዛው ዙሪያና በአዳራሹ ውስጥ ያሉ የሳቅ ድምጽ አሰሙ ።

ጄኔራል ዶብኪን፤ ያአኮቭ ሳፒርን ለብዙ ጊዜ ከተመለከተው በኋላ " የፖስታ መሥሪያ ቤትን በመወከል የምክር ቤት አባል እንደመሆ ሆንህ ሁሉ ፤ የቆረንቶስ ሰዎች ለጳውሎስ ደብዳቤዎች የሰጧቸው መል ሶች በኢየሩሳሌም ፖስታ ቤት ውስጥ እስከ አሁን ድረስ መቀመጣቸ ውን ለማወቅ ጉጉት አለህ ብየ እገምታለሁ " ብሎ ሲመልስለት በስ ብሰባው አዳራሽ ውስጥ የበለጠ ሳቅ ፈነዳ ።

ሆስንር ቆጣ ብሎ “ ጄኔራል ስለመጽሐፍ ቅዱስ የምታወራውን እንተወውና ቁም ነገሩን እንቀጥል ” አለው ።

ዶብኪን ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ እሺ ፤ በአጠቃላይ ሁሉም ነገር ደህና ይመስላል ። በአረብ አገር የሚገኙት ተባባሪዎቼ አልፎ አልፎ የሚከሰቱትን የደፈጣ ተዋጊዎች እንደሚበታትኑአቸው መል ዕክት አስተላልፈውልኛል ” በማለት ለስብሰባው አስረዳ ።

ቼይም ማዛር ወደፊት ጐብደድ ብሎ “ ጄኔራል ፤ ለመሆኑ እን ዚህ የደፈጣ ተዋጊዎች እንዲበታተኑ ባይደረጉ ኖሮ የሰላም ተልዕኮ ውን በመቃወም ምን ማድረግ ይችሉ ነበር ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ በባሕርና በአየር — አሁንም በባሕርና በአየር ስለሚደረገው ችላ የማይባልና የሚያሳስብ ጉዳይ ነው ። ኮንኮርዶቹ የሚበሩት የሜ ዲትራንያን ባሕር በእኛ አየር ኃይልና በአሜሪካ 6ኛ የጦር መርከብ ብቻ ታጅበው አይደለም። በአሁኑ ጊዜ የሰሜን አትላንቲክ ቃል ኪዳን አባሎች የሆኑት የግሪክ ፣ የጣሊያንና የቱርክ የጦር መርከቦች ልም ምድ በማድረግ ላይ ስለሚገኙ ሙሉ ቁጥጥር እየተደረገበት ነው ። በተጨማሪም ኮንኮርዶቹ በሚበሩበት እርቀት ለመድረስ የሚችል ከባሕር ወደ አየር የሚተኮስ ሚሳይል በአረቦቹ እጅ የለም ። ድንገት ቢኖራቸውና ከባሕር መተኮስ ቢችሉ የሚያጅባቸው የአየር ኃይላ ችን በቀላሉ ሊያውቀውና መትቶ ሊጥለው እንደሚችል አረጋግ ጦልኛል ። የተናገርኩት ትክክል ነው ፤ ጄኔራል ? ” ብሎ ወደ ኢዝ ሃቅ ታልማን የአየር ኃይል ኦፕሬሽን ኃላፊ ሲመለከት ሌሎቹም ፊታቸውን ወደ ታልማን አዞሩ ።

ኢዝሃቅ ታልማን ተነስቶ ወደ መስኮቱ በመራመድ አሻግሮ በሩቅ ተመለከተ ። ኢዝሃቅ ረጅም ፣ መልከ መልካም ሰውና እንደ እንግሊዝ ወታደር የተከረከመ ሪዝ የነበረውና የቀድሞ የእንግሊዝ ሮያል አየር ኃይል አባል ነበር ። የእብራይስጥ ቋንቋ ችሎታው ዝቅተኛ ቢሆንም የእንግሊዘኛ ድምጽ አጣጣሉ እንደ እንግሊዝ ገዥ መደብ ዓይነት ነበር ። ታልማን በተፈጥሮው ቁጡና ስሜታዊ ቢሆንም ራሱን መቆጣጠር ስለሚችል ሁሉንም አምቆ ይይዘው ነበር ።

ታልማን ከመስኮቱ ወደ ተሰበሰቡት ሰዎች ዞሮ በረጋ መንፈስ “እጅግ በጣም ድንቅ የሆነው አብራሪ መኰንን ቴዲ ላስኮቭ በዓለም ውስጥ እጅግ በጣም ዘመናዊ የሆነውን ተዋጊ አውሮፕላን ማብረር የሚ ችሉ የጥቂት አብራሪዎች መሪ ይሆናል ። በአሁኑ ጊዜ በዚያ ሜዳ ላይ ያሉትን 12 ተዋጊ አውሮፕላኖች ሁኔታ ይቆጣጠራሉ ። በሰማይ ላይ የሚያጋጥመውን ሁሉ ለመቆጣጠር እንደሚችልና በራዳሩ ከታየው

ሰይጣን ሳይቀር ተኩሶ እንደሚያወርደው አረጋግጦልኛል ” ብሎ ነገራቸው ። በክፍሉ ውስጥ የተሰበሰቡትን የወንዶችና የሴቶች ራሶች ከተመለከተ በኋላ “ የአየር ኃይል የጸጥታ ክፍል ፣ ደፈጣ ተዋጊዎች በአየር ላይ ለመዋጋት ምንም ዓይነት ችሎታ የሌላቸው ከመሆናቸ ውም በላይ በአሁኑ ጊዜ ምንም እንደ ሌሉና ምናልባትም ማንም ቡድን ቢሆን ኮንኮርዶቹን ለማጥቃት ቢሞክር በሜድትራንያን ባሕር ላይ ያሉት እጅግ ዘመናዊ ተዋጊ አውሮፕላኖች ድምጥማጡን እንደሚያ ጠፉት ተነግሮኛል ” ብሎ ሪዙን ከደባበሰ በኋላ “ ላስኮቭ እጅግ የም ንተማመንበት ሰው ነው ። ኮንኮርዶቹ የባሕር ዳርቻውን እንዳለፉ በእኔ ቁጥጥርና ኃላፊነት ሥር ናቸው ። ያንንም ኃላፊነት ያለምንም መጠራጠርና ማወላወል በደስታ እቀበላለሁ ” ብሎ ወደ መቀመ ጫው ተመለሰ ።

ቴዲ ላስኮቭ በመተላለፊያው አጠገብ ተቀምጦ ያዳምጥ ስለነበረ መዝጊያውን ቀስ አድርጎ ከፍቶ እርሱን ለማየት ለዞሩት ሰዎች ፈገ ግታ በማሳየት እጁን አወዛውዞ ተቀመጠ ።

ሚሪያም በርንስቴይን የሆስነርን ሁኔታ ለመመልከት ብትሞክ ርም እርሱ ከምንም አልጣፋትም ። ሰዎቹን አንድ በአንድ ተመልክቶ አስተያየት ለመስጠትም ሆነ ለመጠየቅ ምልክት የሰጠ ባለመኖሩ “ እሺ ፣ ከዚህ በኋላ ” ሲል ሚሪያም በርንስቴይን ተነስታ “ ሆስነር” አለች ።

“ አቤት ። ”

“ ትንሽ ለመጨመር እፈልጋለሁ ። ”

“ አሀ ! እሺ ። ”

“ አመሰግናለሁ ” ብላ ሆስነር ልብ ያላደረገውን ፈገግታ አሳ የች ። በፊቷ የተቀመጡትን ወረቀቶች አገላብጣ ከተመለከተች በኋላ “ እስከ አሁን የተባሉትን ሁሉ በጥንቃቄ አዳምጫለሁ ። ስለተወሰዱት እርምጃዎች ብረካም የተሰማኝን በግልጽ ለመናገር እወዳለሁ ። ይሁን እንጂ ሊወሰዱ የቻሉበት መንፈስና በተለይም የተወሰዱትን ጥንቃ ቄዎች ለመግለጽ የተጠቀሙበት ቋንቋ አሳስቦኛል ። የተከበራችሁ የስብሰባው ተካፋዮች ፣ የምንሔደው ሰላምን ለመፍጠር የሚያስችል ስብሰባ ለማድረግ ነው ” አለች ።

ሚሪያም በርንስቴይን ንግግርዋን ቆም አድርጋ የያንዳንዱን ሰው ሁኔታ ከተመለከተች በኋላ “ ከሰማይ ላይ ተኩሶ ስለማውረድ ፣ በወ ዳጅ አገሮች የሚኖሩ የተጠረጠሩ አረቦችን ስለመጠየቅና ስለመከታ ተል እንደዚሁም የወታደር ሰላዮች ወደ አረብ አገር ስለመላክ የተደ

ረገው ውይይት በአስፈላጊው ቦታ ተቀባይነት ይኖረው ይሆናል ፡፡
ነገር ግን ይህ ሲደረግ የታሰበውን ታሪካዊ ስብሰባ ነገሩን ሌላ አድርጐ
በመመልከት ተቃዋሚ መስሎ አለመታየት የሚመረጥ ነው ፡፡ ወ፡
ተባበሩት መንግሥታት እንደማንም ወሬ አድናቂ ሆነንና በልዩ ልዩ
መግሪያዎች ታጅበን መሔድ አንፈልግም ፡፡ ወደዚያ የምንሔደው
ስለሰላም ለመወያየትና ዘላቂ ሰላም ለመፍጠር ነው ’’ ብላ ከንፈር
ዋን ግጥማ ልትናገራቸው ስለምትፈልጋቸው ቃላት አሰበች ፡፡ በፓር
ቲው ውስጥ የሰላም ውይይት እንዲደረግ ለብዙ ዓመቶች የታገሉ
ስለነበሩ የሰላም እውነነት እየተቃረበ በሚመጣበት በአሁኑ ጊዜ ሌላ
አጨናጋፊ ነገር እንዳይፈጠር አቋም የመውሰድ ግዴታ ነበረባት ፡፡
ሕይወትዋን ሙሉ ለአንድ ቀን እንኳን ሰላም ባለበት ቦታ ኖራ አታ
ውቅም ፡፡ የእጆችዋን መዳፎች ወደላይ ገልብጣ ወደፊት በመዘርጋት
የሰላም ምልክትነቱን አሳየች ፡፡ ‘‘ ችግር ሳይኖር ችግር እንዲፈጠር
አልሞክርም ፡፡ የወታደርና የጸጥታ ኦፕሬሽን ለሚቀጥሉት ሳምንቶች
አብዛኛው እንዲቆሙ ያስፈልጋል ፡፡ ይህም በኛ በኩል ያለውን እም
ነት በሥራ ያሳያል ፡፡ አንድ ወገን በመጀመሪያ የጠመንጃውን አፈሙዝ
ወደ መሬት ማዘቅዘቅ አለበት ፡፡ ጄኔራል ታልማን ፣ በራዳርህ ውስጥ
ሰይጣንን ብታየው እንኳን ከሚሳይሎችህ አንዱን በመተኮስ አትግደ
ለው ፡፡ ለሰላም ውይይት በመጓዝ ላይ መሆንህንና ለተልዕኮህ እንቅፋት
እንዳይሆን አስረዳው ፡፡ እርሱም ለሰላም ብለህ የምታደርገውን ያስ
ተውላል ፡፡ አምላክም እንዲገለል ያደርገዋል ’’ ብላ በዓይኖቿ ስት
ቃኝ ዓይኖችዋ ለጥቂት ሴኮንዶች በቴዲ ላስኮቭ ላይ አረፉ ፡፡

እርሱም ሲመለከታት ጥቂት ሰዎች ብቻ ለሚየት የታደሉትንና
ለመግለጽ የሚያቅተውን ነገር በዐይኖቿ ላይ አየ ፡፡

ሚሪያም በርስቴይን እንደገና አካባቢዋን ከተመለከተች በኋላ
‘‘በደማቸው ያገኙትን በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ለሚደረገው የሰላም ውይ
ይት አሳልፈው ለመስጠት የማይፈልጉ ከእኛም መካከል አሉ ፡፡ ይህ
ም በትክክል ይገባኛል ፡፡ የሰላሙን ድርድር ለማደፍረስ የሚያጋጥሙ
ችግሮች ቢመጡም እስከ መጨረሻው እንቋቋማቸዋለን ፡፡ አሁን
ግን የምለምናችሁ ለሚቀጥሉት ጥቂት ቀኖች ስለተናገርኩት እንድ
ታስቡበት ነው ፡፡ አመሰግናለሁ ’’ በማለት ሐሳብዋን ገታች ፡፡

አንድም ሰው መልስ ወይም አስተያየት አልሰጠም ፡፡ ክፍሉ
እረጭ አለ ፡፡

ጄኔራል ታልማን ተነስቶ ወደ ቴዲ ላስኮቭ ሔዶ ክንዱን ከያዘው
በኋላ አብረው ወደ መተላለፊያው ወጡ ፡፡

ሰዎቹ አጠገባቸው ከተቀመጡት ጋር ቀስ ብለው ማውራት ጀመሩ ። ቀጥሎም የመጨረሻ ዕቅዶችን ለማውጣት በቡድን ተከፋፈሉ ።

ያዕቆብ ሆስነር በአካባቢው የነበረውን ዝቅተኛ ድምጽ ካዳመጠ በኋላ ወደ ሚሪያም በርንስቴይን ለረጅም ጊዜ ተመለከተ ። በመካከላቸው ረቂቅ የሆነ የተዳፈነ ነገር አለ ። ይህም ተሰምቶታል ። ምናልባት ባልታሰበ ወቅት ይገለጽ ይሆናል ። በመኖሪያ ቤቱ የሳምንቱን መጨረሻ አብራው እንድታሳልፍ ጠይቋት እምቢታዋ በድንገት ትዝ አለው ። አሁን ተቀምጦ ጣሪያውን ተመለከተ ። ገደል ልትገባ ትችላለች ። በዚህች ደቂቃ ውስጥ ከሚሪያም በርንስቴይን የበለጡ ብዙ የሚያሳስቡ ጉዳዮች አሉት ።

በአሁኑ ጊዜ ለብዙ ዓመቶች ያካበተውን ልምድ በሥራ ላይ የሚያውልበት ከባድ ሥራ አጋጥሞታል ። በ1948 ኤል አል ሥራ ከጀመረበት ቀን አንስቶ ፍልስጥኤማውያን ኤል አል የወታደር ሥራ ባሕሪ አለው ብለው ስላመኑ እስከ አሁን ድረስ የሚያናፍሱት ይህንኑ ቢሆንም የበለጠ ጥፋት ያደረሱት ግን በ1960 እና በ1970 ነበር ።

የመጨረሻው ሙከራ ሎንዶን ከሔዝሮው አየር ማረፊያ ኤል አል 747 የሕዝብ ማመላለሻ አውሮፕላን ለመጥለፍ የተደረገው ነበር። የዚያ ሙከራ ዋናው ጠንሳሽ አህመድ ሪሽ የሚባል ነበር ። ይህን ስም ሲያስታውሰው የሆስነር ፊት ቅጭም አለ ። ሪሽ — ከመጨረሻዎቹ አንዱ — ምናልባትም እጅግ አስጊ ከሆኑት አንዱ — ሪሽ ባልታወቀ ምክንያት በሎድ አየር መንገድ አካባቢ በመገኘቱ አንድ ወቅት በራምላ የወታደር እስር ቤት እንዲቆይ ተደርጐ ነበር ። እስራኤል ከሽብር ፈጣሪዎች ጋር በምንም ዓይነት ለመደራደር የማትፈልግ መሆንዋን የሚገልጽ ፖሊሲ ከማውጣትዋ በፊት በ1968 ጄኔራል ሻሮንን ለመማረክ የተሳፈረበትን የኤል አል አውሮፕላን ለመጥለፍ በሞከሩበት ጊዜ ከሌሎች አስራ አምስት ሽብር ፈጣሪዎች ጋር ሪሽም ተፈትቶ ልውውጡ ተፈጽሚል ። ሆስነር ድርጊቱ ስህተት እንደነበረ አውቋል ። ቀስ በቀስ እየተከሰተ በመጣው ድርጊት አባባሉ ልክ እንደነበረ ተረጋግጧል ።

ባለፉት ዓመቶች በየጊዜው በተደረጉት የሚሽትዘን (ሽብር ፈጣሪዎችን የሚከታተል ክፍል) ባደረጋቸው ድንገተኛ ወረራዎች በአንዱ አህመድ ሪሽ ተገድሎ ቢሆን ኖሮ ሆስነር ምንኛ በተደሰተ ነበር ። ሪሽ ያላንድ መጸጸት በቆራጥነት ለማጥቃት የሚፈልገው አውሮፕላኖችን ስለነበር የሆስነር ናላው ተበጠበጠ ። በራምላ እስር ቤት ታስሮ ጥያቄዎች ያቀርቡለት ከነበሩት ዋናው ሆስነር ነበር ። ሆስነር

ራሱን መቆጣጠር እስኪአቅተው ድረስ ብው ከሚያደርጉት ጥቂት ሽብር ፈጣሪዎች ውስጥ አንዱ ሪሽ ነበር ። ሆስነር በሪፖርቱ ማጠቃለያ ላይ ሪሽ በጣም አደገኛ ሰው ስለሆነ በእስር ቤት ተቆልፎበት እስከ መጨረሻው መቆየት እንደሚገባው ጽፎአል ። ግን ምን ያደርጋል ተለቆ ሔዷል ።

ሪሽ የኤል አል አውሮፕላኖች በሚሔዱባቸው አገሮች በድብቅ እየተዘዋወረ ለማጥቃት በብዛት አልሟል ። በእንተቤ በተደረገዉ ድንገተኛ ወረራ ጊዜ ካመለጡት ጥቂት ሽብር ፈጣሪዎች ውስጥ አንዱ ሪሽ ነበር የሚል ጭምጭምታ አለ ። ይህ አባባል ምናልባትም እውነትነት ሊኖረው ይችላል ብሎ ሆስነር ገምቷል ።

ይስሐቅ በርግ አንድ የደፈጣ ተዋጊ በፈረንሳይ ውስጥ ተያዘ ብሎ በተናገረ ጊዜ ሆስነር በሐሳብ ተወጠረ ። በሔዝሮው አየር ማረፊያ ለመጥለፍ ሙከራ ከተደረገ ወዲህ ከአንድ ዓመት በፊት ሪሽ በፈረንሳይ ውስጥ ታይቷል የሚል ወሬ ተሰምቷል ። ሪሽ ወደ ፈረንሳይ ለምን ሔደ ? ሆስነር ይህን በሰማበት ጊዜ ጭንቀት ተሰምቶት እንደነበረ አስታወሰ ። ምክንያቱ ምን ይሆን ? በፈረንሳይ — ሪሽ — ሪሽ የሚከተለው የማጥቃት ዘዴ — የሆስነርን አዕምሮ የበጠበጠው ይኸው የሪሽ በዚያ መታየትና ዘዴው ነበር ። ሪሽ ሕጻኖች እንደሚያደርጉት በጠመንጃ አይጫወትም ። በሕይወቱ ብዙ አስጊ ወይም ጀብደኛ የሆኑ ድርጊቶች አልሠራም ። ሪሽ የሚፈልገውን በጥንቃቄ ያደርጋል ።

ሪሽ በተለይ በፈረንሳይ ለምን ታየ ? በብዛት አረቦች ባሉበት በጀርመን ለምን አልታየም ? በፈረንሳይ ውስጥ ያሉ የአረብ ወገኖች የአልጀሪያ ሰዎች ብቻ ነበሩ ። ሪሽ ምንም እንኳን ለፍልስጥኤም ነጻነት ቢዋጋም ኢራቃዊ ነበር ። ለሌላው ዓለም አረቦች አንድ ዓይነት ነበሩ ። ለየራሳቸው ግን አልነበሩም ። አልጀሪያውያኖች ለፈረንሳይ ፖሊሶች እንግዳ ስላልነበሩ ኢራቃዊ በቀላሉ ሊታወቅ ይችል ይሆናል ።

አዎን ፤ ሪሽ በቅርብ ቀን የእስራኤልን የጸጥታ መረብ የነካና እንዲነቃነቅ ያደረገ ትንኝ ነው ። በፓሪስ ውስጥ ሳይሆን በገጠር እንደሚኖር ደርሰውበታል ። ሁኔታው የሚያስገርም ነገር ነው ። አንድ ጊዜ በብሪታኒ በሌላ ጊዜ ደግሞ በደቡብ ፈረንሳይ በእስፓኝ ድንበር አካባቢ ታይቷል ። የዚህ ሁሉ ምክንያት ምን ይሆን ? በጸጥታ ሥራቸው ውስጥ የት እንደሆነ ያልታወቀ አንድ ደካማ ወይም ልል የሆነ ጐን እንዳለ ለሆስነር ተሰምቶታል ። ባደረበት ጭንቀት ምክንያት በጀርባው ላይ ቀዝቃዛ ላብ ኵለል ሲል ተሰማው ። ስለ ሪሽ ገጽታ ለማወቅ የሚያስችል የተቀመጠ ጽሑፍ ስላለ ማኅደሩን ፈልጐ ካጠና በኋላ

ከፈረንሳይ ወኪል ጋር ለመነጋገር ፈለገ ። ሆስነር ከሀሳቡ እንደ መባ ነን ብሎ ዙሪያውን ሲመለከት የስብሰባው ተካፋዮች በትንንሽ ቡድን በመከፋፈል መወያየት ጀምረዋል ። ሆስነር ከተቀመጠበት ተነስቶ “ ከእናንተ ውስጥ የሚፈልገኝ ከሌለ ወደ ሥራዬ መሔድ እፈልጋ ለሁ ” አላቸው ።

መልስ የሰጠ የለም ።

“ ምክትል ሚኒስትሪት ? ”

“ እናስቸግርህም ” አለችው ሚሪያም በርንስቴይን ። አሁንም ክፍሉን እንደገና ቃኝቶ “ ክፍሉን የምትፈልጉትን ጊዜ ያህል ልት ጠቀሙበት ትችላላችሁ ። ለእኔ ይቅርታ አድርጉልኝ ” አላቸው ። አሁንም ወደ በሩ ከሔደ በኋላ እንደገና ዞሮ በመመልከት “ ሰላም ለእ ናንተ ይሁን ” አላቸው ፍቅር በተመላበት አነጋገር ።

## — 4 —

ካፒቴን ዴቪድ ቤከር የኤል አል ኮንኮርድ 02 አብራሪ በበረራ ዝግጅቱ ክፍል ውስጥ ከረዳት አብራሪ ሙሴ ሐስ አጠገብ ተቀምጧል ። ከሔስ ባሻገር ባለው ጠረጴዛ አጠገብ አሜሪካዊ አይሁድ የሆነው የበ ረራ መሐንዲስ ፒተር ካን አብሮ ተቀምጧል ። በግድግዳው ላይ ማፖ ች ፣ ካርታዎችና መግለጫዎች ነበሩ ። በአንድ በኩል ባለው ትልቅ መስ ኮት አውሮፕላኖች የሚቆሙበት ሜዳ ወለል ብሎ ይታያል ። ሁለቱ ኮንኮርዶች በከፊል ጥላ በነበረው ሜዳ ላይ ቆመዋል ። በመስታወት በተከፈለው ክፍል ውስጥ ሙሉ የመልዕክት ማስተላለፊያ መሣሪያ ዎችና የአየር ሁኔታን የሚያሳዩ ካርታዎች አሉ ።

በበረራ ዝግጅት ክፍል ውስጥ በነበረው ረጅም ጠረጴዛ ዙሪያ የኤል አል ኮንኮርድ 01 የበረራ ሠራተኞች ተቀምጠዋል ። አብራሪው አሸር አቪዳር ፣ ረዳት አብራሪው ዜቪ ሔሪሽና የበረራ መሐንዲሱ ሊዮ ሺሬት ነበሩ ።

አቪዳር ለሠራተኞቹ ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ቤከር በችኮላ የሚነገረው የዕብራይስጥ ቋንቋ እንዲገባው ተጨንቆ አደመጠ ። ይህ በረራ በከፍተኛ ጥንቃቄ የተዘጋጀ ከመሆኑም በላይ በዚህ ረጅም ጉዞ ቤከር ከአቪዳር ጋር አብሮ ይሔዳል ። አቪዳር ለሠራተኞቹ አጠር ያለ ገለጻ በሚያደርግበት ጊዜ ቤከር በተጨማሪ በካርታው ላይ የነበረውን የመጨረሻ የአየር ሁኔታ ያጠና ነበር ።

ቤከር እጅግ በጣም ረጅም በመሆኑ ምክንያት የኮሪያ ጦርነት በተጀመረበት ጊዜ የተዋጊ አውሮፕላን ሥልጠና እንዳይሰጠው ተነፍጎት ነበር ። በኋላ ግን ረጅምነቱን ሳያጤኑ በሲ—54 የማመላለሻ አውሮፕላን ከቦታ ቦታ እንዲያመላልስ ተፈቀደለት ። ውሎ አድሮ በስትራጂክ ኤይር ኮማንድ ውስጥ በመቀጠሩ በከፊልም ቢሆን የውጊያ አውሮፕላኖች ለማብረር የነበረው ፍላጐት ተሟላለት ። በ1950ዎቹ በሩስያ ውስጥ አንድ ከተማ እንዲደመስስ ተመድቦ ስለነበር ተራውን በትዕግሥት ጠብቋል ።

ዕድሜው እየገፋ በመጣ ቁጥር ግን የተዋጊነት ዝንባሌው እየቀነሰ መጣ ። ዓለም አቀፍ ባለስቲክ ሚሳይል በሥራ ላይ በዋለበት ጊዜ በዕቃ ማመላለሻ አውሮፕላን ሥራ ላይ እንደገና ተመደበ ። ቀጥሎም የቪየትናም ጦርነት ስለተቀሰቀሰ ቢ — 52 አውሮፕላን እንዲነዳ ተመድቦ ከፍተኛ ጀብዱ ሠራ ።

በ1967 ጦርነት ጊዜ በራሱ ፈቃድ በእስራኤል በረራ ክፍል ገባ ። ዕጣ የደረሰው በሎድ አየር መንገድ እንዲሠራ ነበር ። በእዚያው ስለቆየ በእስራኤል አየር ኃይል ውስጥ የምትሠራ አንዲት ሴት አገባ ።

የእስራኤል አየር ኃይል ቤከር አቀላጥፎ የሚያውቃቸው ትላልቅ ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች አልነበሩትም ። በወቅቱ አስፈላጊም አልነበሩም ። በዚያ ጊዜ አየር ኃይሉ በሔል አቪር የነበሩ ጥቂት ሲ — 130 የወታደር ማጓጓዣዎች ነበሩት ። ይሁን እንጂ ወደ ውትድርና ተመልሶ ለመሥራት ፈቃደኛ አልነበረም ። በመጨረሻም በኤል አል ዲሲ — 4 የዕቃ ማመላለሻ አውሮፕላኖች አብራሪ ሆነ ።

በአሜሪካ አየር ኃይል ውስጥ ለብዙ ሺህ ሰዓቶች ጀቶች አብርሯል ። እንዲሁም የአሜሪካ ኤፍ — 111 ሱፐር ሶኒክ ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች በማብረር ሠርቶ ስለነበር የሱፐርሶኒክ ፍጥነት ያላቸው ትላልቅ አውሮፕላኖች በእስራኤል ውስጥ ለማብረር ከሚችሉት ጥቂት አብራሪዎች አንዱ ነበር ። ኤል አል አየር መንገድ ኮንኮርዶቹን በገዛ ጊዜ ቤከር ለሥልጠና ወደ ቱሉስ ተልኮ ስለሰለጠነ አሁን ይህን እጅግ አስፈላጊ የሆነ አውሮፕላን ሊያበር ተዘጋጅቷል ። ሁሉም ነገር ያለ እንከን እንደሚካሔድ ከፍተኛ እምነት አድሮበታል ።

ቤከር ወደ መልዕክት ማስተላለፊያው ክፍል ዘወር ሲል ጄኔራል ታልማንና ጄኔራል ላስኮቭ ሲገቡ አያቸው ። ለጥቂት ደቂቃዎች ሠራተኞቹን ካነጋገሩ በኋላ እርሱ ወዳለበት ክፍል መጡ ።

ሁለቱ ጄኔራሎች ሲገቡ በበረራ ዝግጅት ክፍል ውስጥ የነበሩት ሁሉ ተነስተው ተቀበሏቸው ።

ታልማንና ላስኮቭ ፈገግታ በማሳየት እንዲቀመጡ አዘዟቸው ። “ እንደምን ዋላችሁ ። አሁን የመጣነው ከጸጥታ ስብሰባ ላይ ነው ። ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል ። ይሁን እንጂ ለበለጠ ደህንነት የመነሻ ጊዜአችሁን በማራዘም ከቀኑ በ9 ፡ 30 ሰዓት እንዲሆን አድርገናል ። በተጨማሪም በሜዲትራንያን ባሕር ላይ ወደ ማድሪድ አት በሩም ። በዚህ ፋንታ በኢጣሊያን ድንበር አድርጋችሁ ነዳጅ ለመሙላት ወደ ኦርሊ ትሔዳላችሁ ። ሱፐርሶኒክ አውሮፕላኖች በኢጣሊያንና በፈረንሳይ ምድር ላይ ለማብረር ፈቃድ አግኝተናል ። ለዚህም የሚያገለግሉ የበረራ ፕላኖች ፣ ማፖችና የአየር ሁኔታን የሚያሳዩ ቻርቶች ተዘጋጅተዋል ። በኦርሊ አየር ማረፊያ ከእናንተ ውስጥ አንደም ሰው ከአውሮፕላኑ ውስጥ አይወርድም ። ይህ ትዕዛዝ እንደ ማድሪድ አየር ማረፊያ የተጠበቀ ይሆናል ” ብሎ ታልማን ከነገራቸው በኋላ እያንዳንዱን ሰው ተመለከተ ። ቀጥሎም “ የተወደዳችሁ ፤ ” ብሎ የሚናገረውን ትክክለኛ ቃል ለመምረጥ ሪዙን እየነካካ ንግግሩን ለትንሽ ጊዜ ቆም ካደረገ በኋላ “ መልካም በረራ ይሁንላችሁ ፤ ሰላም ለእናንተ ይሁን ” ብሏቸው ወደ መልዕክት ማስተላለፊያው ክፍል ተመለሰ ።

ቴዲ ላስኮቭ በጠረጴዛው ላይ ተቀመጠ ። “ ሁሉንም ነገር ለማጠናቀቅ በመጨረሻው ደቂቃ ላይ እንገኛለን ። በአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ አማካኝነት ከመሥሪያ ቤታችን ጋር እንገናኛለን ። ሐሳብ ለመለዋወጥ በምንፈልግበት ጊዜ የእኔ የሞገድ መስመር 31 ሲሆን የእናንተ ደግሞ 134.725 ይሆናል ። ይህ መስመር አጠራጣሪ መስሎ በሚታይበት ጊዜ ግን የቁጥር ሦስት ነዳጅ መያዣ ምልክት አይሠራም ብላችሁ እንደተናገራችሁ የእኔ ሞገድ 27 ሲሆን የእናንተ 129.475 ስለሚሆን በዚህ እንገናኛለን ማለት ነው ። ግልጽ ነው ? 19 ሺህ ሜትር ከፍታ ላይ እስክትደርሱ ድረስ በዚህ ዓይነት አልለያችሁም ። ምናልባትም በቂ ነዳጅ ካለኝ እኔም በአካባቢያችሁ እበራለሁ ። ከዚያ በኋላ ምንም የሚያሰጋ ነገር አይኖርም ። ጥያቄ አላችሁ ? ” አላቸው ።

አቪዳር ተነስቶ “ ጄኔራል ፣ ማን ነው የቁጥጥር ስልቱን የሚከታተለው ? ማለት እኔ የእነዚህ ሁለት ኮንኮርዶች በረራ መሪ ነኝ ። አንተ ደግሞ የአንተን ሰዎች ትቆጣጠራለህ ። በሔል አቪር ውስጥ በሹመት ትበልጠኛለህ ። ግን ይህ የሲቪል አውሮፕላን ነውና ለምሳሌ በአንድ በውጭ አካል አደጋ ቢቃጣብንና እኔም ለመከላከል ስልእርምጃ ለመውሰድ ብፈልግ ፤ አንተም በዚህ ጉዳይ ላይ ጥብቅ ክትትል ስለምታደርግ ፤ ይህን ትዕዛዝ ለመስጠት ኃላፊው ማን ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ላስኮቭ ወደ አቪዳር አስተዋለ ። ስለወጣቱ ፓይለት ሰዎች የተ ሰማቸውን ቢናገሩም እርሱ ግን የሆነ ያልሆነውን በመቀባጠር ጊዜ አላባከነም ። አቪዳር ይሆናል ብሎ ያሰበውን በመናገሩ የኋላ ኋላ ጸጸት አያድርበትም ። ላስኮቭ ራሱን ነቅንቆ " መልካም ፣ ጥሩ ጥያቄ ነው ፣ አሸር ። ችግር ይገጥመናል የሚል ግምት ባይኖረንም ከአሁን በፊት የተነገርከውን ደግሜ ልንገርህ ። ግን . . . ብንወጋ የከባድ ቦምብ ጣይ ሕጐችን ትከተላለህ ። እስራኤል ከባድ ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች ስለሌሏት ከደንቦቹ ጋር ላስተዋውቅህ ። ደንቦቹ ቀላል ናቸው ። በመ ጀመሪያ ከአጃቢ አውሮፕላኖች መሪ ማለትም ከእኔ ትዕዛዝ እስከታ ገኝ ድረስ መንገድህን ትቀጥላለህ ። ይህም እያንዳንዱ የመከላከያ እር ምጃ እንዲወሰድ ወይም መስመሩን፣ፍጥነቱን ወይም ከፍታውን ለመ ለወጥ ይሆናል ። ለሁለተኛው ደንብ የመጀመሪያውን ደንብ ተመል ከት ። ይህ ጥያቄህን ይመልስልሀል ? " በማለት አብራራለት ።

" አይመስለኝም " ብሎ አሸር በመቀመጥ በሐሳብ ባዘነ ።

ላስኮቭ በሚያግባባ ድምጽ " እየው አሸር ፣ አጃቢ በራሪ ሁልጊ ዜም ቢሆን ለእያንዳንዱ የቂጥ ቁስል ነው ። በእስራኤል ውስጥ ቀደም ብሎ ሁኔታው ስላልፈቀደ የረጅም ጉዞ አጃቢዎች ስላልነበሩ ላንተ ነገሩ አዲስ ነው ። እኔ ግን በጦርነት ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ ልምድ ስላለኝ እንደምሳሌ አድርጌ የምነግርህ ጊዜም ትክክለኛነቱን ያረጋ ገጠለትን አባባል ነው — በጐች በመንጋቸው ውስጥ በመቆየት ጠባቂ ውሻቸው የሚነግራቸውን መስማት አለባቸው ። ይህን ካላደ ረጉ ግን ተኲላዎቹ ያገኟቸዋል ። በመንጋው ውስጥ ያሉት በጐች የፈ ለገውን ያህል ይሁን በተኲላዎቹ የሚለቀሙ ቢመስሉም ፣ በተናጠል ለመሔድ መሞከሩ በጣም አደገኛ መሆኑን አረጋግጥልሀለሁ ። አሁን አመሳስየ ለመንገር የሞከርኩት ትክክለኛ አግባብ ባይኖረውም የአ ነጋገሬ መልዕክት ምን እንደሆነ የገባህ ይመስለኛል " ብሎ ነገረው ። ላስኮቭ የአባታዊ አመለካከት ሊያሳየው ቢሞክርም አባባሉ በአቪዳር አንጀት ውስጥ ጠብ አላለም ። ላስኮቭ ትከሻውን ከፍና ዝቅ አድርጐ ወደ ቤከር በመዞር " ዴቪድ በአዕምሮህ ውስጥ የተጠነሰሰ ነገር አለ ? " ብሎ ጠየቀው ።

" ለመነጋገሪያ ልንጠቀምባቸው ካሰብናቸው ዘዴዎች በስተ ቀር ከላይ በአጭሩ በተነገረው ስለተጠቃለለ የምናገረው የለኝም ፣ ጀኔራል ። "

ላስኮቭ ከመቀመጫው ተነስቶ " እኔ መላኩ ገብርኤል ተብየ የምጠራ ሲሆን የመለያ ቁጥሬ 32 ነው ። የእኔ ረዳቶች ከመታወቂያ ቁጥራቸው ጋር ገብርኤል ተብለው ይጠራሉ ። አንተ ዴቪድ የአማ

ኑኤል ከንፎች ተብለህ ትጠራለህ ። አሸር ደግሞ ኮሽር ከሊፐር ነህ ። ለማንኛውም በአየር ላይ የሚሆኑት አማኑኤልና ከሊፐር ናቸው ። ” ላስኮቭ ሰዓቱን ሲመለከት ከቀኑ 8 ሰዓት ሆኗል ። “ ከመለያየታችን በፊት አንድ ነገር በተጨማሪ የምነግራችሁ አለኝ ። ይኸውም ለሰ ላሙ ውይይት እንዲሔዱ ከተመረጡት ሰዎች ውጭ በተሳፋሪዎች የስም ዝርዝር ውስጥ ያልገቡ ጥቂት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ይኖራሉ ። ከእነዚህም ውስጥ በአሜሪካ ኤምባሲ ውስጥ የሚሠራ ጀን መከለር የሚባል በዕረፍት ምክንያት አብሮ ይሔዳል ። ስለዚህ ከተሰጣችሁ የስም ዝርዝር በተጨማሪ ሌሎች ሰዎች እንደሚኖሩ ለአስተናጋጆቹ አለቃ እንዲነገረው ያስፈልጋል ። ”

ቤከር የስም ዝርዝር የያዘውን መዝገብ እያገላበጠ “ ቶም ሪቻር ድሰን የአየር ኃይል አታሼ ለሥራ ጉዳይ ወደ ኒውዮርክ አብሮ ስለሚ ሔድ ልታውቀው የሚገባህ ሰው ነው ፤ ጄኔራል ” አለው ። ላስኮቭ ንግግሩን ለትንሽ ጊዜ ቆም አደረገ ። ይህ በመጨረሻው ደቂቃ የተወ ሰደ እርምጃ መሆን አለበት ። ላስኮቭ ነገሩን በትክክል ባያውቀውም ታስቦ የተደረገ መሆኑ ገብቶታል ። ምናልባትም የወዳጅነት ምልክት ለማሳየት ይሆናል ። ራሱን አነቃንቶ “ አንድ ወዳጅ ሥራችንን ለመ ንገር የማይሞክር ቢሆንም በሥራ ምክንያት እንተዋወቃለን ። የሚቀርብለት ምግብ የማይዋጥለት ከሆነ ችላ በለው ። አቪዳር ሰው የው ከአንተ ጋር ከተሳፈረ ስለፖለቲካም ሆነ ስለሃይማኖት ከእርሱ ጋር እንዳትከራከር ፤ ከሁለቱም የለበትምና ። ”

ቤከር ፈገግታ በማሳየት “ ከእኔ ጋር እንዲሔድ ስለጠየቀ ጥሩ ጥንቃቄ አደርግለታለሁ ” አለው ።

“ አድርግለት ” አለው ላስኮቭ በአዕምሮው ውስጥ ሌላ ነገር እየዳሰሰ ። ታልማን ከመልዕክት ክፍል ኃላፊው ጋር ይነጋገር ስለነ በረ ወደ እርሱ ሔደ ። ላስኮቭ እንደደረሰ ሁሉም ቆሙ ። “ ዴቪድ ፣ ከአንተ ጋር እንዲሔድ መርጧል አልክ ? ” አለው ።

“ አዎን” ብሎ ቤከር የስም ዝርዝር የተጻፈበትን ወረቀት ለላስ ኮቭ ሰጠው ።

ላስኮቭ ሲመለከት ከሪቻርድሰን ስም አጠገብ “ 02 ” ተጽፏል ። በስም ዝርዝሩ ውስጥ በየትኛው አውሮፕላን እንደሚሔዱና የመቀ መጫ ቁጥራቸው አልተገለጸም ። ይህም ለጸጥታ ተብሎ ስለሆነ በመ ጨረሻ የመቀመጫ ምርጫ በየግለሰቦቹ ፍላጐት መሠረት ይሆናል ። ምናልባት በምድብ ሆነው ለመሥራት ለሚፈልጉ የመቀመጫ ምርጫ ይሰጣል ። ሪቻርድሰን ወዳጆቹ ወይም የሚያውቃቸው ሰዎች በየት

ኛው አውሮፕላን እንደሚሔዱ ሳያውቅ ቁጥር 02ን ለምን ለመምረጥ እንደቻለ ላስኮቭን አስጨንቆታል ። መልዕክተኞቹ ተከፋፍለው በየትኛው አውሮፕላን እንደሚሔዱ እስኪታወቅ ድረስ ለምን አልታገሰም ? ሁለቱም ኮንኮርዶች ይዘው የሚበሩት እያንዳንዳቸው መያዝ ከሚገባቸው በግማሽ ያነሰ ነው ። ምናልባት ከቤከር ጋር መጓዝ ፈልጐ ይሆናል ። ቀና ብሎ እየተመለከተ " አንተ ኮንኮርድ 02ን እንደምታበር አውቋል ? " ብሎ ጠየቀው ።

" ይመስለኛል ። እንደምገምተው በቅርብ ተቀምጦ እያወራ ለመሔድ የፈለገ ይመስላል ። የዕብራይስጥ ቋንቋ ይህንንም ያህል አይናገርም " አለው ።

" እኔም ያሰብኩት እንደ አንተው ነው ። መልካም መንገድ ይሁንላችሁ ። በ5 ሺህ ሜትር ከፍታ ላይ አያችኋለሁ ። ሰላም ለእናንተ ይሁን " አላቸው ።

* * *

የአየር መንገዱን የእንግዳ መቀበያ ክፍል ከአንድ መቶ የማያንሱ ሰዎች ሞልተውታል ። የአየር ማቀዝቀዣውን እንዲረዱ በማለት መስኮቶች መጋረጃዎች ቢለብሱም ክፍሉ እንደሞቀ ነበር ። ሆኖም ጥላ እየወረደ ስለነበረ አየሩም እየቀዘቀዘ እንደሚመጣ ይታመናል ። በየደቂቃው ሰዎች መጋረጃውን በየተራ ገለጥ እያደረጉ በወታደሮች የተከበቡትን ሁለት ኮንኮርዶች ይመለከቱ ነበር ።

ያአኮቭ ሌይበር የቤከር አውሮፕላን የአስተናጋጆች ኃላፊ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ወደ ተቀመጡበት አዳራሽ ሲገባ ሁሉም ትንሹ ያአኮቭ ብለው ስለጠሩት ድንጋጤ ተሰማው ። መንገደኞቹን ስለበረራው ጉዞ ሌላ ሰው ገለጻ ቢያደርግላቸው ኖሮ ደስ ባለው ነበር ። እስከ ዛሬ ድረስ ስለበረራው አጭር መግለጫ የሚሰጠው እርሱ ቢሆንም የዛሬዎቹ ከልዩ ልዩ የተውጣጡ ከፍተኛ ሰዎች ከመሆናቸውም በላይ የብዙዎቹን ፊትና ስማቸውን ያውቅ ነበር ።

ከሃያዎቹ የሰላም መልዕክተኞች በተጨማሪ ብዙ ረዳቶች ፣ ጸሐፊዎች ፡ አስተርጓሚዎችና የጸጥታ ሰዎች ነበሩ ። ክፍሉ በጭስ እንደ ታፈነና ቡና ቤቱም ባዶ እንደነበረ ሌይበር አጢኗል ።

ያአኮቭ ጉሮሮውን አፍታቶ " ክቡራትና ክቡራን ፤ ክቡራትና ክቡራን " በማለት እጁን አነሳ ።

በክፍሉ ውስጥ ጸጥታ ሰፈነ ። ብዙ ራሶች ወደ እርሱ ዞረው ልኩ ያልሆነ ሰፊና ነጭ ዩኒፎርም የለበሰውንና ጥቁር መነጽር ያደረገውን ትንሽ ሰው አስተዋሉት ።

ሌይበር ጀርባውን ወደ ቡና ቤቱ በማድረግ “ እንደምን ዋላች ሁ ፤ ያእኮብ ሌይበር ፣ የኤል አል ኮንኮርድ 02 የአስተናጋጆች አለቃ ነኝ ” አላቸው ።

ከኋላ ከተቀመጡት አንዱ “ የአውሮፕላናችን ነጂ ባለመሆኑ ተደስቻለሁ ” ብሎ ስለተናገረ ጥቂት ሰዎች ሳቁ ።

ሌይበር ፈገግ ብሎ “ አንድ ወቅት አብራሪ ነበርኩ ። ግን አንድ ቀን ወፍራም የስልክ ማውጫ በመቀመጫዬ ላይ ሳላደርግ በመቅረቴ ከአውሮፕላን ጋራዥ ጋር ተጋጭቻለሁ ” አላቸው ። ሰዎቹ ይህን ሲሰሙ ከመሳቅ አልፈው ጥቂቶቹ አጨበጨቡለት ።

ሌይበር ወደ ሰዎቹ ጠጋ በማለት “ ከአንዳንድ ነገሮች ጋር ላስ ተዋውቃችሁ እፈልጋለሁ ” አላቸው ። ስለመቀመጫውና ስለመሳ ፈሪያው ሰዓት ለብዙ ደቂቃዎች ከተናገረ በኋላ “ ጥያቄዎች አሏች ሁ ? ” አላቸው ።

የኦርቶዶክስ ቄስ የሆነው ሔይም ሌቪን ቆሞ “ አንተ ወጣት ፣ ዛሬ ዓርብ መሆኑን ታውቃለህ ። እንደ ነገርከን ከሆነ በቀጥታ ወደ ኒው ዮርክ እንደምንሔድና የቅዳሜ ሰንበት ሳይጀምር እዚያ እንደምናርፍ ነው ። ይህ ትክክል ነው?” አለው ። ሌይበር የመጣበትን ሳቅ አምቆ ያዘ ። በኤል አል አየር መንገድ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ቄስ እንኳን ተሳፍሮ ነበር ለማለት አያስደፍርም ። የኤል አል ሠራተኞች የሰንበ ትን ቀን ስለማያከብሩ ጥቂት ቄሶች በዓለም አቀፍ በረራ እንኳን አይ ሳፈሩም ። በሌሎች አገሮች አየር መንገዶች ግን ሠራተኞች የአይ ሁዶቹንም ሆነ የራሳቸውን የሰንበት ቀን ባያከብሩም ተሳፍረው ይሔ ዳሉ ። ሁለቱ ቄሶች — አንዱ የኦርቶዶክስ ሌላው ደግሞ የወግ አጥ ባቂ የመልዕክተኞቹ አባሎች — የአገር አንድነት የሚሆን የሰላም ውይይት ለማድረግ ስለሆነ በኤል አል አየር መንገድ ተሳፍረው ለመ ሔድ ተስማምተዋል ።

ሌይበር “ በኒውዮርክ ፀሐይ የምትጠልቀው በኒውዮርክ ሰዓት በ12 ፣ 08 ሲሆን እኛ ግን ከፀሐይዋ ፈጥነን ከቀኑ በ8 ሰዓት እንደርሳ ለን ” አላቸው ።

ቄስ ሌቪን ለብዙ ጊዜ ወደ ሌይበር ተመለከተ ።

“ በሌላ አነጋገር ከተነሳንበት ሰዓት 1 ፣ 30 ሰዓት ቀድመን እን ገባለን ማለት ነው ” አላቸው ሌይበር ።

“ እሺ ይገባኛል ። ከአሁን በፊትም ሔጃለሁ ። ነገር ግን ፀሐይ ከጠለቀች ከአንድ ሴኮንድ በኋላ ብናርፍ ከእኔ የምትሰማው ይኖርሀ ል ” አለው ቄስ ሌቪን ።

ጥቂት ሰዎች ሳቁ ። ሌይበርም ፈገግታ ካሳየ በኋላ "እሺ ጌታዬ" ብሎ ዙሪያውን ተመልክቶ " ምግባችን ሥጋና ድንች ጥብስ ነው ። ለማየት ፍላጐት ላላቸው ልዩ ልዩ ፊልሞች አሉ ። ከእኔ በጣም ውብ የሆነችው ሚስቴ ማርሻ በ01 ኮንኮርድ ከአስተናጋጆቹ አንዷ ናት " አላቸው ። ብዙ ባልና ሚስቶች አብረው ቢበሩም የሌይበር ፖሊሲ ግን በምንም ዓይነት አብሮ አለመብረር ነው ። ልጆች አሉአቸው ። ይህን እስተሳሰብ የማይረዳ እንደማይኖር ተስፋው የደነደነ ነው ። " ጥያቄ ዎች አሏችሁ ? በኤል አል አየር መንገድ በመጓዛችሁ አመሰግናለሁ" ብሎ ሁለቱንም እጆቹን ወደላይ በማንሳት ጨብጦ " እንግዲያውስ ሰላም ለእናንተ ይሁን " አላቸው ።

* * *

ካፒቴን ዴቪድ ቤከር በኮንኮርድ 02 ውስጥ የሚሳፈሩትን የሰዎ ች ስም ዝርዝር አንድ በአንድ ካየ በኋላ በአውሮፕላኑ ጥላ ሥር ቆመ ። ኮንኮርዱን ከበው ቆመው የነበሩት የምድር ጦር ወታደሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ እርሱ ይመለከቱ ነበር ። የኤል አል የጸጥታ ሠራተኛ የሆ ነው ናታን ብሪን ወደ እርሱ ቀርቦ "እንዴት ነው ፤ ካፒቴን ? " አለው ።

" ጥሩ ነው ። "

" በበኩላችን ደስ ብሎናል ፤ አንተስ ? "

ቤከር ወደ አውሮፕላኑ እየተመለከተ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። " በአውሮፕላኑ ውስጥ እንገናኛለን " ብሎት ብሪን ሔደ ።

" እሺ " ብሎ ቤከር አንጋጦ ወደ አውሮፕላኑ ተመለከተ ። ይህ የሰላም ነጭ ወፍ የሚመስለው ሌላ ሳይሆን እርግብ ነው ። ቤከር የባሕር ወፍ ይመስላል የሚል ስሜት አደረበት — እርሱም — ምና ልባትም የባሕር ጭላት ። በረጅም እግር ላይ ቆሟል ። ይህም ረጅም ክንፎቹን ወደ ላይ ሰቅሎ መያዝ ስላለበት ነው ። እነዚህ ረጅም የመ ቆሚያ እግሮች ባይኖሩት ኖሮ ለመብረር በሚሽከረከርበት ወይም በሚ ያርፍበት ጊዜ ሰውነቱ ከመሬት ጋር ይፋተግ ነበር ። እግዚአብሔር የባሕር ወፎችን እረጅም እግሮች እንዲኖራቸው አድርጐ የፈጠራቸው ለዚያ ምክንያት ነው ። የእንግሊዝ አውሮፕላን ኮርፖሬሽንና የአኤሮ ስፔሻል የቴክኒክ ሠራተኞች እንደዚያ አድርገው የሠሯቸው ይህን ምክንያት በመከተል ነበር ። እንደዚሁም ሩስያውያን ሱፐርሶኒክ ቲዩ 144 የሠሩት ይህንኑ በመከተል ነበር ። ትልቅ አዋቂነትና ብልህነት ነው ። አዋቂዎች — ባለሙያዎች — የእግዚአብሔር ሥራ ልክ እንደ ሆነ ሲያረጋግጡ ማየት ጥሩ ነገር ነው ብሎ ቤከር አሰበ ።

የሰው ልጆች በየጊዜው በሚያደርጉት ፍልስፍናና ያልተቆጠበ ማሻሻል በአሁኑ ጊዜ እጅግ ድንቅና አስገራሚ የሆኑ አውሮፕላኖች

ከልዩ ልዩ መሣሪያዎቻቸው ጋር ተሠርተው በአገልግሎት ላይ ውለ ዋል ።

ቤአር የአውሮፕላኑን እርዝመት ሲመለከተው ይህንን ያህል ትል ቅ አልነበረም ። የዋና ሰውነቱ እርዝመት 52 ሜትር ሲሆን ክንፉ ደግሞ 27 ሜትር ነበር ። ጠቅላላ ክብደቱ ከመንገደኞችና ከነዳጅ ጋር 181 ሺህ ኪሎ ግራም ወይም የ747 አውሮፕላን ክብደት ግማሽ ነበር ።

ለመጨረሻ ጊዜ በአውሮፕላኑ ዙሪያ ዞረ ። በክንፉ ስር ቆሞ አሻቅቦ ተመለከተው ። ሁለት መቶ ተሳፋሪዎችን ለማሳፈር ሳይሆን ሰባ ከፍተኛ ባለሥልጣኖችን ይዞ በሰዓት 2300 ኪሎ ሜትር እየበረረ ወደኒውዮርክ እንዲሔድ ነበር ።

ቤከር ኮንኮርዱን ወደ 19 ሺህ ሜትር ከፍ አድርጐ በሚያበርበት ጊዜ ችግር ይኖር ይሆን የሚል ሃሳብ በአንጐሉ ውስጥ ስለተደነቀረበት ተጨነቀ ። ይኸውም አውሮፕላኑ በሚሳይል ቢመታ ፤ ወይም አንድ አነስተኛ ፈንጂ ከውስጥ ቢፈነዳ ፡ ወይም አንድ ሰው መስኮቱን በጥ ይት ቢሰብረው ከፍተኛ ችግር ያጋጥመዋል ። የንግድ አውሮፕላን አብዛኛውን ጊዜ የሚበረው በ9ሺህ ሜትር እርቀት ላይ ስለሆነ ይህ ዓይነቱ ችግር ቢያጋጥመው በሰዎቹ መቀመጫ ክፍል የሚፈጠረው የአየር ሁኔታ ይህን ያህል አስጊ አይሆንም ። ምክንያቱም ሠራተኞ ቹም ሆኑ መንገደኞቹ የኦክስጂን መሳቢያ በመጠቀም ትክክለኛውን አየር እስኪያገኙ ድረስ አውሮፕላኑ ዝቅ እያለ ይመጣል ። በ19 ሺህ ሜትር ከፍታ ላይ ግን ለመተንፈስ የሚያስችል ሌላ መሣሪያ ከሌለ በስተቀር በኦክስጂን መሳቢያ ብቻ ቢጠቀሙም እንኳን ችግር ይፈጠ ራል ። ምክንያቱም በኦክስጂን መሣሪያ ለመጠቀም የሚኖረው ዕድል ለጥቂት ሴኮንዶች ብቻ በመሆኑ ነው ። በ19ሺህ ሜትር ከፍታ ላይ ለመጠቀም የሚያስችል መንገድ ባለመኖሩ በአውሮፕላኑ ውስጥ ያለ ው የኮምፒዩተር መሣሪያ ችግሩን በራሱ ተረድቶ አውሮፕላኑ ወደ ታች እንዲወርድ ያደርገዋል ። ይሁን እንጂ በዚያ ሰዓት የአዕምሮ መታ ወክ በእያንዳንዱ ተሳፋሪ ላይ ይደርሳል ።

ቤከር በዚህ ጭንቀት ውስጥ እንዳለ በቅዠት ባሕር ውስጥ ስለ ማሰኑ በሐሳቡ የሚከተለው ታየው ። አዕምሮአቸው የቀወሰ የአውሮ ፕላኑ ሠራተኞች ከችግራቸው ለመውጣት በመፍጨርጨር የኦክስጂን ጡጦ ሲስቡ — ይህንም ለማድረግ ምናልባት ለማስታወስ የሚያስ ችል ዕውቀት ካላቸው ነው — የሚያዩት ብርሃን በፊታቸው ላይ እየ ተብለጨለጨ ነገሩ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ዓይኖቻቸው እየተንከዋ ረሩና ምራቃቸው ከአፋቸው እየተንጠባጠበ ሰማይ መሬቱ የተቀላቀለ መስሎ ይታያቸዋል ።

ኮንኮርዱ በኮምፒዩተር አዛዥነት ቆሞ በሰው እንዲመራ የሚ ጠብቅ መስሎ ታየው ። ሰባ መንገደኞች ሁሉም ነገር ተመሰቃቅሎ ባቸውና ራሳቸውን ስተው ፤ ኮንኮርዶቹ አርፈው ሰዎቹ እጆቻቸውን እያውለበለቡ ወዳጆቻቸውንና ፍቅረኞቻቸውን ሲቀበሉ በአዕምሮዉ ውስጥ ታየው ። ቤከር ዓይኖቹን ጨፈነ ። ኮንኮርዱ ከዚያ ከፍታ ተመ ልሶ እንደማይመጣ ገበው ። ሆኖም ይህ ምክንያት የሌለው የእውን ቅዠት እንደሆነ ስለገባው ራሱን አጽናና ።

ቤከር በዚህ ጭንቀት ምክንያት ያጠለቀውን ላብ ከፊቱ ላይ ጠርጐ ወደ ሜዳው ተመለከተ ። ሃምሳ ሜትር ርቀት ላይ ቆሞ የነበረ ውን ኮንኮርድ 01 አቪዳር እየተዘዋወረ ሲመለከት አየው ። በእርሱ ላይ የደረሰው የቀን ቅዠት በአቪዳር ላይም እንዳላደረ ተስፋ አደረገ ።

## — 5 —

በእንግዳ ማረፊያው አዳራሽ ውስጥ ሚሪያም በርንስቴይን ከአ ብዱል ጃባሪ ጋር ቡና እየጠጣች ተቀምጣለች ። ጃባሪ ሌላው የአረብ መልዕክተኛ የሆነው ኢብራሂም አሊ ሲመጣ ስላየው ይቅርታ ጠይ ቋት ለመነጋገር ተነስቶ ሔደ ።

ሚሪያም በቡና ቤቱ ውስጥ ያዕቆብ ሆስነር ተቀምጦ ስላየችው ተነስታ ካቅማማች በኋላ ወደ እርሱ ሔደች ። ሆስነር ግን ዞሮ ባይመለ ከታትም " ሀሎ " አለችው ።

ከትከሻው ዘወር ብሎ ከተመለከታት በኋላ " አሀ ፣ ሀሎ " አላት።

" ስማ ፣ ቀደም ብየ በሰዎች ላይ ችግር ፈጥሬ እንደሆን አዝና ለሁ ። "

በብርጭቆው ውስጥ የነበረውን መጠጥ እየነቀነቀ " ግዴለም ፣ ችግር አይኖርም " አላት ።

" ጥሩ " ብላ ለጥቂት ጊዜ ከቆመች በኋላ " ታዲያስ ፣ ከኛ ጋር ነው የምትሔደው ? " ብላ ጠየቀችው ።

" አዎን ፤ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በኮንኮርድ 02 ተሳፍሬ እንድ ሔድ አሁን ተነገረኝ ። "

ይህን ዜና በመስማትዋ ምክንያቱን ልትገልጸው ባትችልም ከእ ርሱ ጋር አብራ መሔድዋ ለደህንነትዋ ጥሩ የሚመስል ድንገተኛ ስሜ ት አደረባት ። " እኔም የምሔደው በኮንኮርድ 02 ነው " አለችው ።

ለጊዜው በመካከላቸው ጸጥታ ሰፈነ ።

ራስዋን አስገድዳ ፈገግታ ካሳየችው በኋላ " የተመደብክበትን

አውሮፕላን መለወጥ ትፈልጋለህ — ወይስ እኔ እንድለውጥ ትፈልጋለህ ? ’’ ብላ ጠየቀችው ።

አነጋገርዋ እንዲቆጣ የምትገፋፋው መስሎ በኃይል ለምን ተሰማው ? ሆስነር አምቃ በውስጥዋ የያዘችው ጠንካራ ስሜት እንዳላትና ያም ስሜት ከእርሱ ጋር የተያያዘ መስሎ ታየው ። ሆኖም ይህን ስሜቷን ለማጠናከር የሚገፋፋበት ምክንያት ባይኖረውም ነገሩ ከነከነው ። ሆስነር ወደ ሚሪያም እየተመለከተ “ መለወጡ አስፈላጊ መስሎ አይታየኝም ’’ አላት ።

በሁለቱ መካከል የነበረውን የገጽታ ሁኔታ ያየ እንዳለ በማለት የሆስነርን ሁኔታ ጭምር በመስታወቱ ውስጥ ተመለከተች ። በእርሷ ፊት ላይ ይታይ የነበረው የስሜት አስተያየት ደህና ቢመስልም ውስጠ ስሜትዋ ግን ተረብሿል ። እንዲያውም በእግር ጣቶቿ የቆመች መስሎ ተሰማት ። ይህ ሆስነርን ባገኘች ቁጥር የሚፈጠርባት ስሜት ነበር ። እርሷ ግን ተዝናንታ ፈገግ በማለት “ ከእኛ ጋር መሔድ መልካም ነው ። እንድትቀር ያደርጉህ ይሆን ? ’’ ብላ ጠየቀችው ።

ሆስነር መጠጡን ግልብጥ አድርጐ ከጨለጠ በኋላ “ ለስቅላት እዚህ ለማቆየት ወይም እንድሔድ ፈቅደውልኝ በኮንኮርዱ ላይ አንዳች ነገር ቢደርስ አብሬ እንድጠፋ የሚደረገው ምርጫ የእነሱ ነው ’’ አላት ።

ራስዋን ነቅንቃ “ ስለዚህ አደጋ ቢደርስበት አብረህ ለመጥፋት መርጠሀል ’’ አለችው ። “ እንደማስበው የእነሱ ምርጫ በአውሮፕላኑ ላይ አደጋ ሳይደርስ በኔ ላይ አደጋ ደርሶ ለማየት ነበር ። ነገር ግን ሁለቱም ሊሆን አይችልም ። መጠጥ ትፈልጊያለሽ ? ’’

“ አልጠጣም — ግን ። ’’

“በዚህ በተረገመ አገር ውስጥ ማንም መጠጣት አይፈልግም። በሮያል አየር ኃይል ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ ካልጠጡ አያበሩም ነበር ’’ ብሎ ብርጭቆውን ወደ አሳላፊው ከገፋ በኋላ መልካም በአውሮፕላኑ ውስጥ አይሻለሁ ’’ አላት ።

ወደ እርሱ ተመልክታ “ እሺ ’’ ካለች በኋላ ሔደች ።

ማቲ ያዲን የሴትዮዋን ከቡና ቤቱ ወጥታ መሔድ ካየ በኋላ መጥቶ “ ይህች ሴት እንደገና ችግር ፈጠረችብህ ይሆን ? ’’ አለው ።

ሆስነር ለትንሽ ጊዜ ካሰበ በኋላ “ እርግጠኛ አይደለሁም ’’ አለው ።

* * *

ቴዲ ላስኮቭ ቶም ሪቻርድሰንን ለመጠየቅ የሚፈልጋቸው ነገሮች ስለነበሩትና በዚያውም ከታልማን ጋር ሆነው ስለመረጧቸው

የመገናኛ መስመሮች ለሪቻርድሰን ለመንገር ወደ እንግዳ ማረፊያው ክፍል ሔደ ። ወደ አሜሪካ አየር ኃይል አታሼ ጽሕፈት ቤት እንደተ ጠራ በመቁጠር ነገሩን በሚገባ አብላላው ። ይሁን እንጂ ለራሱ እን ኳን ሊገልጸው ባልቻለው ምክንያት ሊነግረው የነበረውን ከሪቻርድ ሰን ለመደበቅ ወሰነ ። ነገር ግን እርሱ የደበቀውን አሜሪካኖች የሚ ያስፈልጋቸው ሆኖ ካገኙት ያለጥርጥር ከታልማን ያገኙታል ።

ሆስነርና ሚሪያም በቡና ቤቱ ውስጥ ሆነው ሲያወሩ ላስኮቭ አይቷቸዋል ። በመጨረሻም ስትሔድ ተመልክቷታል ። ሁለቱ እንደ ማይግባቡ ባያውቅም ሆስነር በተናገራት የተቀየመች ትመስላለች ለማ ለት ይችል ነበር ። ላስኮቭ በድንገት በተሰማው ቅናት ተገረመ ። እርሷ ልብ ብላ ባታየውም ላስኮቭ ተመልክቷታል ። ሆኖም ቀደም ብለው ተሰነባብተው ስለነበረ ወደ ኋላው ዞሮ በደረጃዎቹ ላይ በመውረድ ሊወስደው ወደ መጣው ጂፕ ሔደ ።

ጄኔራል ቤንጃሚን ዶብኪን ከይስሐቅ በርግ ጋር እየተነጋገረ በቡና ቤቱ አጠገብ ቆሟል ።

ዶብኪን ትኩር አድርጎ ወደ በርግ እየተመለከተ “ ከእኛ ጋር ወደ ኒውዮርክ ልትሔድ ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

በርግ ራሱን በአዎንታ እየነቀነቀ “ ኒውዮርክ ካሉት ወኪሎቼ ጋር አስቀድሜ አንዳንድ ነገሮች መነጋገር አለብኝ ። እንደዚሁም እን ዲት ውሽማ አለችኝ ። እርስዋም ከሰባት ሰዓት በኋላ የሰንበት በዓል ትጀምራለች ” ብሎ ሲስቅ ዓይኖቹ ተርገበገቡ ።

ዶብኪን አስቀድሞ ስኒውን ቀጥሎም ወደ በርግ እየተመለከተ “ ይህ የመጨረሻ ዕድላቸው ነው አይደለም ? ማለቴ አንዳንድ ነገር ለማድረግ ቢፈልጉ መሆን ያለበት አሁን ነው ። ካላደረጉ ግን በደጋ ፊዎቻቸው ዓይኖች ፊት ይናቃሉ ። ይህ እጅግ በጣም ትልቅና አስፈ ላጊ አላማቸው አድርገው የሚመለከቱት ነው ። አሁን ካላደረጉት ምን ጊዜም አይሆንላቸውም ፤ አይደለም እንዴ ? ” አለው ።

በርግ ራሱን በመጠኑ ነቅነቅ በማድረግ “ አዎን ” ብሎ ወደ ዶብኪን ተመለከተ ። “ ታስታውስ እንደሆነ ከዚያ ስብሰባ ስወጣ ከፍ ተኛ የውስጥ እምነት ነበረኝ ። ነገር ግን የሰው ልጆች ሐሳብንና ዘዴን ለማፍለቅ የሚችሉ ብልህ ፍጥረቶች ናቸው ። ፍላጎት ካላቸው ፍላ ጐታቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ልዩ ልዩ መንገዶች አሏቸው ። ይህን ከአረቦች ጋር ለብዙ ዓመቶች አብሬ በመቆየቴ ለማወቅ ችያለሁ ። አንተም ሆንክ እኔ እንደምናውቀው እነርሱ በጋዜጦች ላይ እንደሚ ጻፍ አስቂኝ ወይም ቂላቂል ነገሮች አይደሉም ” ብሎ እንደገና ራሱን

ከነቀነቀ በኋላ “ አዎን ፤ ተጨንቄአለሁ ፤ ሥጋትም አድሮብኛል ”
አለው ።

ኮንኮርድ 01 እና ኮንኮርድ 02 ደጃፋቸው ተከፍቶ በፀሐይ ላይ
ቆመዋል ። በእያንዳንዳቸው ውስጥ ከሆስነር የጸጥታ ጓድ የተውጣጡ
ስ፦ስት ሰዎች ተሳፍረዋል ። በኮንኮርድ 01 ውስጥ ማቲ ያዲን ከስ
ድ፦ቱ ሰዎች ጋር ተቀምጦ አጭር መግለጫ ሰጠ ። እያንዳንዳቸው ስሚ
ዝና ዌሰን . 22 ካሊበር አውቶማቲክ ሽጉጥ ይዘዋል ። ጥይቶቹ ሲተ
ኮሱ ከአውሮፕላኑ ይልቅ ሰዎችን እንዲጐዱ ተደርገው የተሠሩ ነበሩ ።
በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ጥሩ ቢመስልም በእንደዚህ ያለ የአየር ግፊቱ ዝቅ
ተኛ በሆነበት አውሮፕላን ውስጥ ጥይት መተኮስ ፈጽሞ ትክክለኛ
ሐሳብ አይደለም ።

* * *

በአውሮፕላኑ ውስጥ ኤም—14 አርጌ የአሜሪካ ጠመንጃ በሌ
ሊት ሊያስተኩስ የሚያስችል በኮከብ ብርሃን የሚሠራ መነጽር የተ
ገጠመበትና በቀን ብርሃን ደግሞ ለመተሬ ተኳሽ የሚጠቅም አስር
ጊዜ አጉልቶ የሚያሳይ መነጽር ያለውና አንድ ኡዚ ድግን መትረየስ
ነበሩ ። የኡዚው እርዝመት 46 ሴንቲ ሜትር ሲሆን ክብደቱ ደግሞ
አራት ኪሎ ግራም ነበር ። መሣሪያው ትንሽ ቢሆንም 25 ባለ 9 ሚሊ
ሜትር ጥይቶች በአንድ ካርታ ውስጥ በአንድ ጊዜ መጉረስ ይችላል ።
በኤም - 14 እና በኡዚው ሊጠቀሙባቸው የሚችሉት ከአውሮፕላኑ
ውጭ ነው ።

በአውሮፕላኑ ውስጥ የተሳፈሩት ሰዎች አንደኛቸውም የማያው
ቁት ሌላ አደገኛ መሣሪያ ነበር ። በሁለቱም ኮንኮርዶች ጅራት ውስጥ
ከነዳጅ መያዣው ጋር የተጣበቀ ግማሽ ኪሎ የሚመዝን የፕላስቲክ
ፈንጅ ተቀምጧል ። ፈንጂዎቹን በቅዱስ ናዛየርና በቱሉስ በኮንኮር
ዶቹ ውስጥ ያስቀመጡአቸው ሁለት አልጀሪያኖች በአሁኑ ጊዜ በሕ
ይወት የሉም ።

ቴዲ ላስኮቭ በኤፍ—14 ነጂ ክፍል ተቀምጦ በኪስ በሚያዝ
ትንሽ የሐሳብ ማስሊያ ስለነዳጅ ፍጆታ ፣ ስለክብደት ፣ ስለእንቅስቃሴና
ስለአየር ሁኔታ ይሠራ ነበር ። ላስኮቭ — የቀድሞው ኃይለኛ ተዋጊ—
ባለ 20 ሚሊ ሜትር የሆኑ የመድፍ ጥይቶች ይዞ ለመሔድ በጣም ፈል
ጓል ። ነገር ግን በሚሳይል መጠቀም ሲቻል እነዚህን ከባድ ክብደት
ያላቸውን መውሰዱ ተገቢ እንዳልሆነ ማወቅ አለበት ። ምናልባትም
ሪቻርድሰን መዝጊያውን አስከፍቶ ባለ20 ሚሊ ሜትር የሆኑት ጥይ
ቶች እንዲወርዱ ማዘዙ ልክ ነበር ።

የመድፍ ጥይቶች ከሁለቱም ኮንኮርዶች ውስጥ እንደተራገፉ ግራና ቀኝ ተመልክቶ በአውሮፕላኑ ውስጥ በነበረው የመገናኛ መጣ ሪያ “ ሞተሮቹን ቀስቅሱ ” አላቸው ።

ሞተሮቹ በኃይል ሲያጓሩ ጩኸታቸው ጆሮ የሚበጥስ ይመስል ነበር ። ከአንድ ደቂቃ በኋላ ላስኮቭ አውራ ጣቱን ወደ ላይ አንስቶ በድ ምጽ ማጉሊያው “ ተንቀሳቀሱ ” አለ ።

አስራ ሁለት ተዋጊ አውሮፕላኖች ወደ ማኮብኮቢያው ሜዳ መጡ ።

ቶም ሪቻርድሰን ከላስኮቭ ጋር የሚነጋገርበትን የምሥጢር መለ ዋወጫ መስመር ቁጥር ለማግኘት በጣም የዘገየ መሆኑን አወቀ ። ስልክ በመደወል ሊጠይቀውና ሊነገረው የማይገባ ጉዳይ ነበር ። በተጨማ ሪም የበረራው ጊዜ እንደሚለወጥ ቢጠራጠርም መለወጡ በመጠኑም ቢሆን ሥጋት ፈጥሮበታል ። የመድፉ ጥይቶች እንዲቀሩ የቀረበውን ሐሳብ ላስኮቭ ተቀብሎት ይሆን ብሎ አሰበ ።

የሰላም መልዕክተኞቹ ከእንግዳ ማረፊያው አዳራሽ እየወጡ ቆሞ ወደሚጠብቃቸው አውቶቡስ መሔድ ጀምረዋል ። ሪቻርድሰን በቡና ቤቱ አጠገብ የነበረ ስልክ አንስቶ በእስራኤል ቁጥጥር ስር ወደ ሆነው ወደ ጃሪኮ ደወለ ። በስልክ መነጋገሩን ባይወደውም ጊዜም ሆነ ሌላ ምርጫ አልነበረውም ።

ያዕቆብ ሆስነር የጽሕፈት ቤቱን ግድግዳ በመደገፍ “ ከፈረንሳይ የደህንነት ጥበቃ እስከ አሁን ድረስ የመልስ ጥሪ የለም ? ” ብሎ ጸሐ ፊውን ጠየቃት ።

ጸሐፊው ቀና ብላ “ የለም ” አለችው ።

“ያሳዝናል ” ብሎ በእርስዋ ላይ አሻግሮ በመስኮቱ መካከል ሲመለከት አውቶቡሶቹ በመሙላት ላይ ስለነበሩ “ መሔድ አለብኝ ። ነገ በአንደኛው ኮንኮርድ ተመልሼ እመጣ ይሆናል ። ምናልባት እኔ በአየር ላይ እንዳለሁ አስፈላጊ ነገር ከመጣ ለጦር ምሽጋችን እንደ ተነገረ መልዕክቱን ያስተላልፉልኛል ። የምሔደው በኮንኮርድ 02 ነው ” አላት ።

“ መልካም መንገድ ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን ” በማለት ምኞት ዋን ገለጸችለት ።

“ ይህ ሁሉ ጥረት እዚህ ለመድረስ ነው ። ሰላም ለአንቺም ይ ሁን ” ብሏት በፍጥነት ወጥቶ በደረጃዎች ላይ እየተንደረደረ ወረደ ።

ማቲ ያዲን ወደ ኮንኮርድ 01 በሚወስደው አውቶቡስ ውስጥ ሆኖ በመስኮቱ መካከል ሲመለከት ሆስነር ተቻኩሎ በአውቶቡሱ አጠገብ ሲያልፍ ስላየው " አለቃዬ " ብሎ ሲጠራው ሆስነር ዘወር በማለት አሻቅቦ ተመለከተው ።

ያዲን ራሱን በመስኮቱ ብቅ አድርጎ " ከፈለግህ እኔ ካንተ ጋር መሔድ እችላለሁ " አለው ።

ሆስነር ራሱን በአሉታ በማወዛወዝ " ግድ የለም ፤ አጭር ጉዞ ስለሆነ አያስፈልግም ። በተጨማሪም የበረራ ዕቅድን መለወጥ የመ ጥፎ ዕድል ምልክት ነው " አለው ። ሆስነር አንድ ነገር ለማለት አቅ ማማ ። በትክክል ስለማያውቀው ስለአንድ ነገር ተጨነቀ ። ስለበረራ ቸውም ድንገተኛ የሆነ መጥፎ ስሜት አደረበት ። ይህን ለእርሱ የተ ሰማውን ስሜት ከያዲን ዓይኖች ላይም ማንበብ ችሏል ። " አህመድ ሪሽን ታስታውሰዋለህ ? "

" እንዴት አድርጌ ልረሳው እችላለሁ " አለው ያዲን ።

" እንዴት ፣ በእርግጥ ፤ ስለእርሱ አስበህ በአዕምሮህ ውስጥ ትንሽ ነገር እንኳን ብልጭ ቢልብህ በራዲዮ ንገረኝ። ኒውዮርክ እንገናኛለ ን" አለው ።

ያዲን ራሱን በማስገደድ ፈገግታ ካሳየው በኋላ " ሰላም ለአንተ ይሁን " አለው ።

ሆስነር ቀድሞ አድርጎት የማያውቀውን ተንጠራርቶ የያዲንን እጅ በኃይል ይዞ ጨበጠው ።

* * *

ቹይም ማዛር በዓይኖቹ ላይ የመስክ መነጽር አድርጎ በሎድ አየር መንገድ መቆጣጠሪያ ማማ ላይ ቆሞ ሲመለከት አውቶቡሶቹ ወደ ኮን ኮርዶቹ ሲቃረቡ አያቸው ። በሎድ ውስጥ በአንድ ፎቅ ቤት ላይ ቅጽ በታዊ የብርሃን ብልጭታ ስለአየ መነጽሩን ወደዚያ አዞሮ ተመለከተ። መነጽሩን እዚያው ላይ እንደተከለ የመስክ ራዲዮኑን አንስቶ ወደ አፉ በፍጥነት በማስጠጋት "የሄልኮፕተር ተቆጣጣሪ ፤ ይህ ከማማ ቁጥ ጥር ነው ። በፒንክ ስቱኮ ፎቅ ጣሪያ ላይ የብርሃን ብልጭታ ስለአየሁ በአስቸኳይ ወደዚያ ሰው ላክ " ብሎ አዘዘ ። በተወሰኑ ሴኮንዶች ውስጥ ሒዩ ሄሊኮፕተር በጣሪያው ላይ ለማረፍ ዝቅ እያለ ሲወርድ አየው ። ሄሊኮፕተሩ ከማረፉ በፊት አራት ሰዎች ኡዚ ድግን መት ረየስ ይዘው ዘለው ወጡ ። ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ " የአየር ማማ መቆ ጣጠሪያ ፤ ይህ ሒዩ 7—6 ነው " አለው ።

" ሮጀር ፣ 7—6 ፣ ቀጥል " አለው ።

" ማማ ተቆጣጣሪ ፣ ምንም ችግር የለም ። እንዲት ወጣት ወይ ዘሮ የፀሐይ ማንጸባረቂያ ይዛ አግኝተናታል ። " ለትንሽ ጊዜ ጸጥታ ሆነ፤ድምጹ ያስገርም ነበር ። " እርቃንዋን ሆና ፀሐይ ትሞቃለች ። "

ማዛር በግንባሩ ላይ እንደጤዛ የተቋጠረውን ላቡን ጠርጐ በብ ርጭቆው ውስጥ ከነበረው ውሃ ተጐነጨ ። " ሮጀር ፤ የአየር ወረራ የሚደረግ ይመስላል ። ሴትየዋን አንድ ነገር አልብሰህ በቁጥጥር ሥር አውላት ። ለፖሊስ እስክታስረክባት ድረስ በሄሊኮፕተሩ ውስጥ አስ ቀምጣት " አለው ።

የረጅም ጊዜ ዝምታ ሆነ ። " ሮጀር ፣ ማማ ። "

" ማማ ፣ ጨርሰናል ። " ማዛር ከአየር ተቆጣጣሪዎቹ ቀጥሎ በወ ንበሩ ላይ ወደ ኋላው ተለጥጦ ተቀመጠ ። ቀጥሎም ወደ አንደኛው ተቆጣጣሪ ዞሮ " ሁኔታው አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ቀኑም ረጅም ሆነ " አለው ።

* * *

ሳባሕ ካባኒ በተራራው ጫፍ ላይ ተጋድሞ በመስከ መነጽር አቶ ልቁሎ ይመለከት ነበር ። ምንም እንኳን ቀኑ ፀሐያማና ግልጽ ቢሆ ንም ዘጠኝ ኪሎ ሜትር በጣም እሩቅ እርዝመት በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ሊታየው አልቻለም ። ኮንኮርዶቹ በመጫን ላይ የነበሩ መስሎ ታየ ው ። ቀኑ እንደሌላው ጊዜ ሁሉ ጥሩ ነበር ። እጁን ወደላይ ከፍ አድ ርጐ ሄሊኮፕተሩ እስኪያልፍ ድረስ ጠበቀ ።

በኋላው በኩል በነበሩት የጥድ ዛፎች ሥር ሦስት ሰዎች በጥቂት ሜትሮች በመራራቅ ተንበርክከዋል ። እያንዳንዳቸው በመሬቱ ላይ ከነበሩት ጉድጓዶች ብቅ ብቅ ያሉ የአዳፍኔ ጥይቶች ይዘዋል ። በተጨ ማሪም ሌሎች ሦስት የአዳፍኔ ጥይቶች በእያንዳንዳቸው አጠገብ ተቀ ምጠዋል ። በጥይቶቹ ጫፍ ላይ ከነጭ ፎስፈረስ የተሠሩ ከፍተኛ ፈን ጂዎች ነበሩ ። በአጠቃላይ በነበሯቸው አስራ ሁለት የአዳፍኔ ጥይ ቶች ኮንኮርዶቹ የቆሙበትንና በአካባቢያቸው ያለውን የአውሮፕላን ማረፊያ ጭምር እንዳልነበረ ለማድረግ ተዘጋጅተዋል ። አንድ ነዳጅ የያዘ ዕቃ ቢፈነዳና በእሳት ቢያያዝ — የማይሆንበትም ምክንያት የለም — አንድም በሕይወት ሊተርፍ የሚችል አይገኝም ።

ካባኒን ትኩር አድርገው ሲመለከቱት ክንዱ አይንቀሳቀስም ። እያንዳንዳቸው ይንቀጠቀጥ ከነበረው እጃቸው የያዟቸው ጥይቶች እየ ተንሸራተቱ ወደ ጉድጓዱ ሲገቡ ተሰማቸው ። የሚፈነዱ መስሏቸው ጩኸቱ እንዳያደነቁራቸው ጆሮቻቸውን በጣቶቻቸው ደፍነው ያዙ ።

ካፒቴን ኤፍሬም ዲኒትዝ ተጠምደው የነበሩት አዳፍኔዎች እስከ መጨረሻው መደምሰሳቸውን እስኪያረጋግጥ ድረስ ጠበቀ ። ከዚያ በኋላ እርሱና የእርሱ ሰዎች ከተደበቁባቸው ዛፎችና ድንጋዮች ስር እየሮጡ ወጡ ። ቀጥሎም ዲኒትዝ “ በወታደር ሕግ መሠረት በቁጥጥር ሥር አውያችኋለሁ ፤ እጆቻችሁን በራሶቻችሁ ላይ አድርጉ ” ብሎ በአረብኛ ጮኾ ነገራቸው ።

ሦስቱ ፍልስጥኤማውያን ወደ ከበቡአቸው የእስራኤል ወታደሮች አፍጥጠው ተመለከቱ ። ቀጥለውም ጩኸት ወዳላሰሙት አዳፍኔዎች አዩ ። ቀስ ብለው በመነሳትና በመቆም እጆቻቸውን በራሶቻቸው ላይ አስቀመጡ ።

ካባኒ ከትከሻው ወደኋላው ዞሮ ዘጠና ጫማ ዕርቀት ላይ የነበረ ውን ትዕይንት ተመለከተ ። በጉሮሮው ውስጥ አንድ እንደ አንኳር ያለ ነገር ተሰማው ። ራሱንም እሾህ ባለው ሽቦ በታጠረው በራምላ ወህኒ ቤት ውስጥ ሕይወቱን ሙሉ እንደሚያሳልፍ ታየው ። ሚስቱ ንና ልጆቹን በሽቦው አጥር ቀዳዳ በስተቀር ዳግመኛ እንደማይዳስሳ ቸው ታወቀው ። ተነስቶ ከተራራው ጫፍ ላይ ዘሎ ወረደ ። አንድ ወታ ደር ጮኾ ተናገረ ። ካባኒ የወታደሩን ትዕዛዝ ከምንም ባለመቁጠር በድንጋዮቹና በቁጥቋጦዎቹ ላይ እየተወላከፈ መሮጥ ጀመረ ። ሌላ ጩኸት ሰማ ። የአሁኑ ግን የአውቶማቲክ ጠመንጃ ነበር ። ጥይቶቹ ዙሪያውን ሲዘንቡ አያቸው ። ካባኒ በመሬቱ ላይ ተጋድሞ ወደ ሞት የሚያደርሰውን ኃይለኛ የደም መፍሰስ እንጂ መሮጥ እንዳልቻለ ለማ መን ብዙ ሴኮንዶች ፈጀበት ።

ቼይም ማዛር የመስከ ራዲዮኑን አነሳ ። በመቆጣጠሪያ ማማው ላይ ሆኖ በተራራው ላይ የሆነውን ሁሉ ተመልክቷል ። ራሱን ከነቀ ነቀ በኋላ “ እሺ ፣ ዲኒትዝ ፤ በአስቸኳይ ጥያቄዎች ካቀረብክላቸው በኋላ እንደገና አነጋግረኝ ” ብሎት በወንበሩ ላይ ተመልሶ ተቀመጠ። እነዚያ የሚያሳዝኑ ፍልስጥኤማውያን ይህ የሚያሳዝን ድርጊት እንዲ ፈጸምባቸው ስላደረጉአቸው ሰዎች እርሱ የሚያውቀውን ያህል እንደ ማያውቁ ተገነዘበ ።

በዚያ ቦታ በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ እንዲቀመጡ የተደረ ጉት አዳፍኔዎች ከአሥር ዓመቶቹ በፊት ተደርሶባቸዋል ። ሳይነሱ እንዲቆዩ የተደረገው ግን በዚያ ማን እንዳስቀመጣቸውና ማን ሊጠ ቀምባቸው እንደከጀለ ለማወቅ ነበር ። በእርግጥ የጥይቶች ባሩዶች እንዲወጡ ተደርገዋል ። በተለይ ባለፈው ሳምንት በዚያ አካባቢ ልዩ ቁጥጥር ሲደረግ ሰንብቷል ። በተጨማሪም ጧት ስለሁኔታው ከልዩ ወኪል ጥቆማ ደርሷአል ።

የዚህ ዓይነት የቂላቂል ሙከራ ውጤታማ ይሆናል ብለው ማመ ናቸው ለማዛር ሊዋጥለት አልቻለም ። በበኩሉ የእዚህን ዓይነት ድር ጊት እንግሊዞች ለመበላት የተዘጋጀ ልዩ የአሳ ጥብስ ሲሉት በእብራ ራይስጥ ደግሞ ለመስዋዕትነት የቀረበ የበግ ጠቦት የሚሉት ዓይነት ሆኖ ተሰማው ። ለእነዚያ ዕድለ ቢስ ፍልስጥኤማውያን የደረሳቸው ዕጣ ይኸ ነው ። ይህ ታላቅ የውንብድና ሴራ በመከሸፉ እያንዳንዳቸው ከጥበቃ ሥራቸው ዘና እንዲሉ አደፋፍሮአቸዋል ። ማዛር ግን ነገሩን በዚህ ብቻ አልተመለከተውም ። ለመስዋዕትነት የቀረበ በግ ለመሆን ከሆነ ፤ ድርጊቱ የሚያሳየው በዚህ የሚያበቃ ሳይሆን የሰላም ተልዕ ኮው እንዳይሳካ ለማድረግ የሚጥሩ ገና ያልተደረሰባቸው አድማዎች እንዳሉ ያስገነዝባል ።

በራሱ ሕይወት ላይ ጭምር ምን ሊደርስበት እንደሚችል መገመት አልቻለም ። ለሕይወቱ ግድ እንደሌለው ዓይነት ሆኖ ትከሻውን ነቀነቀ።

* * *

የአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪው ከራዲዮኑ ላይ ቀና ብሎ “ ኮንኮር ዶቹ ለመንቀሳቀስ ተዘጋጅተዋል ” አለው ።

ማዛር ራሱን ነቅንቆ “ ሌላ ጣልቃ እንዳይገባባቸው አድርግ ። ቶሎ ከዚህ ቦታ ይሂዱ ” አለው ።

የኤል አል ኮንኮርድ 01 ሠራተኞች የተሳፈሩትን ሰዎች የስም ዝርዝር አንድ በአንድ አዩ ። ኮንኮርዶቹ አራት ሺህ ሜትር እርዝመት ባለው ሜዳ ላይ አሽኮብኩቦ ለመነሳት ተዘጋጅተዋል ። ራዲዮኑ ቅቅ አለ ። “ ኤል አል 01 እና 02 ለመብረር እንድትችሉ ሜዳው ዝግጁ ነው ። ስትነሱ በመካከላችሁ የሁለት ደቂቃ ልዩነት አድርጉ ። መልካም በረራ ይሁንላችሁ ። ”

“ ሮጀር ። ” አቢዳር የነዳጅ መስጫውን ስለገፋው ኮንኮርዱ እያጓራ በሜዳው ላይ መሮጥ ጀመረ ።

ዴቪድ ቤከር በግራ በኩል ባለው መቀመጫ ላይ ተቀምጦ ኮን ኮርድ 01 መሬት ለቆ ሲነሳ በመስታወቱ መሀል ተመለከተው ። ወደ ሙሴ ሔስ ዞሮ “ እባክህ ሁለት ደቂቃ እስኪሆን ድረስ ሰዓትህን እይ ልኝ ” አለው ።

ሔስ ራሱን በእሽታ ነቅንቆ ሰዓቱን መመልከት ጀመረ ። ፒተር ካን በስተጀርባቸው ተቀምጦ የመቆጣጠሪያ መሣሪያዎቹ በትክክል የሚሠሩ መሆናቸውን ስለተመለከተ ወደ ቤከር ዞሮ “ ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ ላይ ነው ” አለው ። ቤከር በአነጋገሩ ተደስቶ ፈገግታ በመስጠት “ ጥሩ ነው ” አለው ።

“ አንድ ደቂቃ ። ”

በተሳፋሪዎች ክፍል ውስጥ መንገደኞችና ሠራተኞቹ በዝቅተኛ ድምጽ ሲነጋገሩ ይሰሙ ነበር ። በስም ዝርዝሩ ውስጥ አሥር መልክተኞች ፣ ሃያ አምስት ረዳቶች ፣ ሁለት ወንዶችና ሁለት ሴቶች አስተናጋጆች እንደዚሁም አንድ የአስተናጋጆች አለቃ የሆነው ሴይበር ነበሩ ። በያዕቆብ ሆስነር ቁጥጥር ስር የነበሩ ስድስት የጸጥታ ሠራተኞች ከተሣፋሪዎቹ ጋር ተሰባጥረው ተቀምጠዋል ። ቶም ሪቻርድሰን ከጆን መክለር አጠገብ ተቀምጦ አንድ መልስ የማይሰጥ ሰው ያነጋግራል ። ጄኔራል ዶብኪን ያዘጋጀውን ማስታወሻ ይመለከታል ። ይስሐቅ በርግ ለብቻው ተቀምጦ ያልተቀጣጠለ ፒፓ በአፉ ይዞ እየሳበ ጋዜጣ ያነባል ። ቄስ ሌቪን ከመልዕክተኞቹ አንዱ ጋር ስለሃይማኖት ይከራከራል ። የስም ዝርዝሩ እንደሚያሳየው በጠቅላላው በኮንኮርዱ ውስጥ አምሳ አምስት ሰዎች ነበሩ ። ኮንኮርዱ ከመነሳቱ በፊት ሊይዝ የሚገባውን ክብደት ተጨማሪ ዕቃዎች በመጫን እንዲሟላ ተደርጓል ።

በኮንኮርድ 02 ውስጥ ሚሪያም በርንስቴይን ከአብደል ጀባሪና ከሌላው የአረብ መለዕክተኛ ከሆነው ከኢብራሂም አሪፍ ኋላ ተቀምጣለች ። ቁጡና ወጣት የነበረው የጸጥታ ሠራተኛ ሞሼ ካፕላን ጥቁርና ነጭ ጥምጣም ያደረጉትን ሁለት ሰዎች ትኩር አድርጐ ተመለከታቸው ።

ክፍሉ ጠባብ ቢሆንም መቀመጫዎቹ በአንድ በኩል ሁለት በሌላ በኩል ደግሞ ሁለት ነበሩ ። 180 ሴንቲ ሜትር ቁመት ለነበረው ሰው እንደልብ ለመቆም አያስችልም ነበር ። ፈረንሳዮቹ ውስጡን የሠሩት ለእንደዚያ ያለ ነገር እንዲስማማ አድርገው ሲሆን መልኩ ደግሞ ጥሩ መስሎ እንዲታይ ነበር ። የክፍሉ መጥበብ የሚያመጣው ችግር አል ነበረም ።

ተሳፋሪዎቹ አውሮፕላኑ ሲበር ፍጥነቱን ለማየት የሚያስችል መሣሪያ ከግድግዳው ጋር ተያይዟል ። ኮንኮርዱ ከመነሳቱ በፊት የመሣሪያው መብራት የሚያሳየው 0.00 ነበር ። ”

ሔስ በነጂው ክፍል ውስጥ ሆኖ ሰዓቱን ተመልክቶ “ ጀምር ” አለው ።

ቤከር ፍሬኑን ለቆ የነዳጅ መስጫውን ሲጫነው አውሮፕላኑ መንቀሳቀስ ጀመረ ። በሚያብረቀርቀው ሜዳ ላይ ፍጥነቱን እየጨመረ አኮበኮበ ።

“ ፍጥነቱ በሰዓት 60 ማይል ደርሷል ” በማለት ሔስ አስታወቀ ።

ካን በበኩሉ ፍጥነት መለኪያውን መሣሪያ እየተመለከተ "ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ ላይ ነው" አለ ።

ቤከር ነዳጅ አቀባይ መሣሪያዎች እንዲከፈቱ በጠየቀው መሠረት የበረራ መሃንዲሱ የተጠየቀውን ከፈጸመ በኋላ ሁሉም በትክክል በመሥራት ላይ መሆናቸውን ገለጸለት ።

ሔስ "ፍጥነቱ በሰዓት 100 ማይል ደርሷል" አለው ። ኮንኮርዱ እየሮጠ ሲሔድ የሚወጣው ጭስ ሜዳውን ወጣ ገባ አስመስሎት እንደ ነበረና ከሜዳውም ግማሹን የሔዱ ይመስል እንደነበረ ሔስ በመስታዋቱ ተመለከተ ። ፍጥነቱን በማየት ቤከር ዓይኖቹን ብልጭ ድርግም አደረገ ። ወደ ውጭ ማየቱን ትቶ በመሣሪያዎቹ ላይ እንዲያተኩር ራሱን ለማስገደድ ቢሞክርም በሚያየው ተመሰጠ ። በግንባሩ ላይ ላብ እንደተንቆረዘዘ ቢሰማውም ሔስ ልብ እንዳላደረገው ተስፋ አደረገ ። ዓይኖቹን የፀሐይ ብርሃን ከሚያንጸባርቅበት መስታዎት ላይ መልሶ ልዩ ምልክት ወደሚሰጠው መሣሪያ ጐንበስ ብሎ ተመለከተ ። ምልክት የሚሰጡት አመልካች መርፌዎች መወዛወዝ ጀምረዋል ። መሪውን ደዞ ወደላይ ወደላይ እያለ ከተቀመጠበት ሳያውቀው ብድግ ብድግ አለ ። ፍጥነቱ በሰዓት 165 ማይል ደረሰ ።

ቤከር የመቆጣጠሪያውን መሣሪያ እየሳበ ሲነካካው የፊት ጎማዎቹ መሬት ለቀቁ ። ክንፎቹም እየተንሳፈፉ ወደ ሰማይ አመሩ ። ቤከር ለትንሽ ጊዜ ተደናግጦ ስለነበረ የበረራ ትምህርት ይማር በነበረበት ጊዜ የነበረው የመጠራጠር ትዝታ በአዕምሮው ውስጥ ስለመጣ እንደ መበርገግ እያለ በውስጡ ሲነጋገር ለራሱ ተሰማው — ለምንድነው የሚበረው ? ቤከር አንድ ስህተት የሆነ ነገር አለ ፤ ይህንም ለመናገር የሚችል የለም ፤ በመለኪያው ውስጥ ደብዛዛ መስሎ የሚታየው ምንድን ነው ? ይህን አውሮፕላን የሠራው ማነው ? ይህን ለማብረር እችላለሁ ብለህ ለምን አሰብክ ? ቤከር! ከሽፏል! ከሽፏል! ልትሞት ነው ፤ ቤከር ! — የሚል ጫጫታ በአዕምሮው ውስጥ ስለተሰማው የአንገቱ ጡንቻ የተሳሰረ መሰለው ። እጆቹና እግሮቹ ተብረከረኩ ። ከሃሣብ ቅዠቱም ነቃ ።

ቤከር መሪውን አጥብቆ አለመያዙ ተሰማው ። አሁንም እንደገና የመቆጣጠሪያ መሣሪያውን ተመለከተ ። የበረራው ፍጥነት በሰዓት 220 ማይል ሲሆን አሻቅቦ አወጣጡም ጥሩ ነበር ። ሁሉም ነገር ደህና መሆኑን ስለተረዳ ፈገግ ብሎ ጉሮሮውን አፍታታ ። ቀጥሎም ከሌላው አውሮፕላን ጋር አስተካክሎ መብረር ጀመረ ። ፒተር ቡና እንዲያስመጣለት ጠየቀው ። ጡንቻዎቹም ተዝናኑ ። በአርሊ ማሪፍና መነሳት ከዚያም ወደ ኒውዮርክ መብረር ነበረበት ። በ24 ሰዓት

ውስጥ ወደ ሎድ መመለስ ይኖርበታል ። ተመልሶ እንደመጣም ሥራ ውን ለመልቀቅ ወስኗል ። አውሮፕላኑ በሚነሳበትና በሚያርፍበት ጊዜ ወገቡ ጥንካሬ የሚያጣ ይመስለዋል ። ነጐድጓድ ባለበት መስመር በሚበርበት ጊዜ እጁን ላብ ጥምቅ ጥምቅ ያደርገዋል ። ይህ ሁሉ ከእ ርሱ በተሻሉ አብራሪዎች ላይም ይደርስ ስለነበረ አስቸጋሪ አልነበ ረም ። ለዚህ ሁሉ መፍትሔው " መተው ነው " አለ በመጠኑ ድም ጹን ከፍ አድርጐ ።

" ምኑን ነው የምትተወው ? " አለው ሔስ ።

ቤከር ከራሱ ዘወር ብሎ በመመልከት " ምን ? " አለው ።

" የምትተወው ምኑን ነው ? ለመተው የምትፈልገው ምንድን ነው?" ብሎ ሔስ እየጠየቀው የተሳፋሪዎቹን የስም ዝርዝር ይመለከት ነበር ።

" መተው . . . ቡና መጠጣት ፤ ቡና ። እረሳሁት ። ምንም አልፈ ልግም ። "

ሔስ የስም ዝርዝሩን ማየቱን ትቶ ቀና ብሎ ሲመለከተው ዓይኖ ቻቸው ግጥምጥም አሉ ። ሔስ " ሁለት ስኒ ቡና አምጣልን ፒተር " አለው ።

ቤከር መዳፎቹን አብሶ ፊት ለፊት አየ ። አሁን ሁሉም ነገር ደህና ነበር ። ሔስ ለማወቅ መብት ነበረው ። ሲጋራ አቀጣጥሉ በኃይል ወደ ውስጥ ሳበው ።

— 6 —

ኮንኮርድ 02 መሰስ እያለ በጥሩ ሁኔታ ወደ ሰማይ መውጣቱን ቀጥሎአል ። ሔስ በመሣሪያዎቹ አማካኝነት ኮንኮርዱ የተስተካከለ መስመሩን እንዲይዝ አድርጓል ። የኤሌክትሮኒክሱ መሣሪያ ከወደ ውስጥ ከሚያሰማው ድምጽ በስተቀር የነጂዎቹ ክፍል ጸጥታ ሰፍኖበ ታል ። ቤከር ኮንኮርዱን ወደ ምዕራብ በ30 ዲግሪ አቅጣጫውን በማ ስተካከል በቴል አቪቭ ላይ እንዲበር አደረገው ። የሁለቱ የከፍታ መለ ኪያ 6 ሺህ ጫማና 1800 ሜትር ያመለከተ ሲሆን የአየር ፍጥነቱ 300 ማይል ነበር ። ቤከር ተቀምጦ ልዩ ልዩ የመቆጣጠሪያ መሣሪያዎቹን ተመለከተ ። ኮንኮርዱ ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ቁጥጥር እንዲሠራ የተደረገ ነበር ።

በቴል አቪቭ ዳርቻ ሲበሩ በዓይኖቹ ላይ የማጉሊያ መነጽር አድ ርጐ ወደ መሬት ተመለከተ ። በአዘቦቱ ቀን በባሕር ዳርቻው በሺህ የሚቆጠሩ ዋናተኞችና ፀሐይ የሚሞቁ ሰዎች ይታዩ ነበር ። አሁን በአጃቢ አውሮፕላኖች በረራ ምክንያት በተፈጠረው ጥርጣሬ ሁሉም ከየቤቶቻቸው አልወጡም ። ቤከር በሔርዝሊያ ቤቱን ተመልክቶ

ግቢው ባዶ እንደነበረ አየ ። በዛሬው ቀን እያንዳንዱ ሰው የመጀመሪያውን የፀደይ ፀሐይ እንዳይሞቅ ከአቋረጡት ምክንያቶች አንዱ እርሱ መሆኑን ባለቤቱ ታውቅ ይሆን የሚል አስተሳሰብ አደረበት ። በፊት ለፊቱ ሰማያዊው የሜዲትራንያን ባሕርና ጥራት ያለው ሰማይ ወለል ብለው ታዩት ። ቤከር መሪውን በማስተካከል ፍጥነቱና ከፍታው እንዲጨምር አደረገ ።

ኮንኮርድ 01 በሩቅ ታየው ። ኮንኮርዱ በመሬት ላይ በነበረበት ጊዜ ጥቅም የሌለው ወፍ ይመስል ነበር ። በሚበርበት ጊዜ ግን የባለሙያዎች የአዕምሮ ጭማቂ ውጤት በመሆኑ ዕጹብ ድንቅነትን ያተረፈና ሊበሩበት የሚገባ ውብ አውሮፕላን ነው ። ቤከር ግን ኮምፒዩተሮቹ አንድ ቀን በአደጋ ላይ የሚጥሉት መስለው ስለተሰማው የአዕምሮ መቁነጥንጥ አደረበት ። በእርግጥ ይህ አስተሳሰቡ ተጨባጭ ያልሆነ ነበር ። ሦስት ሰዎች ያላቸውን ኃይል ሁሉ በመጠቀም ሊያከናውኗቸው የማይችሉትን ሥራዎች እነዚህ አስደናቂ የሆኑ ኮምፒዮተሮች በአንድ ጊዜ በሺህ የሚቆጠሩ ሥራዎችን ይሠራሉ ። ኮምፒዩተሮቹ እስከ 60 ሺህ ጫማ — 19 ሺህ ሜትር — ከፍታና የድምጽ ፍጥነቱም 2.2 እስኪያመለክት ድረስ አንድ ቀን ወደላይ አውጥተው ሥራቸውን ሊያቆሙ ይችላሉ ። በዚህ ጊዜ ነበር ቂል አትሁን ራስህ ንዳው የሚል ሐሳብ የተጸነሰበት ። ቤከር ፈገግ ብሎ ከአሁን በኋላ ሁለት ጊዜ ኮንኮርዱን አስነስቶ እንደሚነዳና ሦስት ጊዜ እንደሚያሳርፍ አስታወሰ ።

የድምጽ ማስተላለፊያውን መስመር በጣቱ ጫን አድርጎ "የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ ፤ ይህ የኤል አል ኮንኮርድ 02 ነው ፤ ትሰማኛለህ ? ' አለው ።

" ቀጥል 02 "

" ሮጀር ፤ አውሮፕላኑ ይታየኛል፤ 380 ማይል በሰዓት እየበረርኩ ነው ። "

" ሮጀር ፤ በ5ሺህ ሜትር ከፍታ አስተካክል ። "

" ሮጀር ፤ 02—በ8 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ነኝ ። 5 ኪሎ ሜትር ድረስ በመጠጋት ከአንተ በመጠኑ ዝቅ ብየ እበራለሁ ። አንተ ግን ቀጥል ። "

አቪዳር የሰማ መሆኑን አረጋገጠ ። ሁለቱም በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት ፍጥነታቸውን አስተካከሉ ።

ቤከር ከፍታውን በ5 ሺህ ሜትር ከአስተካከለ በኋላ ወደ አቪዳር ተቃረበ ። ቀጥሎም " ኤል አል 01 እና 02 በትይዩ እየበረርን ስለሆነ

የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ ወደ 19 ሺህ ሜትር ከፍ ብለን እንድንበር መመሪያ ይስጠን ” አለ ቤከር ።

“ ሮጀር ፤ የኢራን 747 አውሮፕላን ከእናንተ በላይ በመብረር ላይ ስለሆነ ከ5 ሺህ ሜትር ከፍታ ሳትወጣ በረራህን ቀጥል ። ”

አቪዳር ወደዚያው ለቤከር “ ኤልአል 02 ፤ ይህ 01 ነው ። ለአንተ ይታይህ እንደሆን ተመልከት ፤ ለእኔ አይታየኝም ” አለው ።

ቤከር መስመሩን ወደ 134.725 ለወጠ ። “ ገብርኤል 32 ፤ ይህ አማኑኤል ነው ። ”

ቴዶ ላስኮቭ መስመር እየፈለገ ስለነበረ የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያው 31 የሞገድ መስመሩን ከቤከር ጋር ለመነጋገር ከፈተ ። “ አማኑኤል ፤ ይህ ገብርኤል 32 ነው ። በጥሩ ሁኔታ እሰማሃለሁ ። በዚህ ሞገድ ላይ እንድንገናኝ መስመሩን ከፍት ተውልኝ ። ”

“ ሮጀር ፣ ገብርኤል ፤ ከአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ ሲፈቀድልን በ280 ዲግሪ በማመልከት ወደ 19 ሺህ ሜትር ከፍታ እንወጣለን ።”

“ ሮጀር ፤ እስከ አሁን ድረስ ሁሉም ነገር ደህና ነው ። ግንኙነት እናደርጋለን ። ”

“ በእኔም በኩል ደህና ነው ። ወደ አየር መንገዱ ራድዮ ስለም መለስ ረዳት ነጂው ይጠብቅሃል ። ”

“ሮጀር ፤ ኾኬ—ይህ ገብርኤል 32 ነው ። ራዳርህ እንዴት ነው ?”

ኢ — 2 ዲ ኾኬ ከኮንኮርዶቹና ከኤፍ— 14 ተዋጊ አውሮፕላኖች በ5 ኪሎ ሜትር ከፍታ ላይ ነበሩ ። በሦስቱም ሞገዶች በተመሣሣይ ጊዜ እየተጠቀመባቸው ነበር ። በውስጥ የነበረው የአየር ተቆጣጣሪ መኰንን የሚናገርበትን ራዲዮ አንስቶ “ ሁላችሁንም ተከታትየአችኋለሁ ፤ ገብርኤል ፣ ከተወሰነለት መስመር ውጭ በ183 ዲግሪ ከአንተ በ180 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ወደ አንተ የሚበር አውሮፕላን ይታይሀል ? ” አለው ።

ላስኮቭ በድምጽ ማጉሊያው ለበረራ መኰንኑ “ የሚታይህ ነገር አለ ፤ ዳን ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ዳንኤል ላቮን ከቴሌቪዥን ጋር የተያያዘውን የመመልከቻ መሣሪያ ጐንበስ ብሎ እየተመለከተ “ ያለ ይመስላል ፤ በራዳራችን ደቡብ ምዕራብ ጫፍ አንድ ነገር ይታያል ። አሁን ያለበት እርቀት ከ160 ኪሎ ሜትር በላይ ሲሆን እኛ ወደምንበርበት መስመር እየተቃረበ ነው ” አለው ።

ኢ—2 ዲ ኾኬ በውስጡ አምስት ሰዎችና ዘመናዊ የሆኑ የኤሌ ክትሮኒክስ መሣሪያዎች ይዟል ። በዚህም የተነሳ ከኤፍ—14 በተ ሻለ ነገሮችን ለመመርመርና ዓይነታቸውንም ለይቶ ለማወቅ ይች ላል ። የኾኬ የቴክኒክ ሠራተኛ ለላስኮቭ “ ይህን አውሮፕላን ለመ ናኘት እየሞከርን ነው ። ለማወቅ ግን አልቻልንም ” አለው ።

የኢ — 2 ዲ የዜና ተቆጣጣሪ አዛዥ ስልኩን አንስቶ “ ገብርኤል ይህ ያልታወቀ አውሮፕላን በሰዓት 960 ኪሎ ሜትር እየበረረ ነው ። ፍጥነቱ በእናንተ መስመር ውስጥ ሊያስገባው ይችላል ። አንተ ፣ አማ ኑኤልና ክሊፐር 1800 ሜትር ከፍታ ላይ ዝቅ በሉ ” አላቸው ።

“ ሮጀር ፣ ኾኬ ይህን እብድ መስመሩንም ሆነ ፍጥነቱን እንዲ ለውጥ ንገረው ። ”

“ ሮጀር ፣ ገብርኤል ፣ እየሞከርን ነው ። ”

ይህ የማንነቱ ያልታወቀ አውሮፕላን በደቂቃ ውስጥ እንደሚ ቀርባቸው ላስኮቭ አወቀ ። ይህ አውሮፕላን የሩስያ አክሪድ ሚሳይል የያዘ ከሆነ 130 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ካልደረሰ በስተቀር ኮንኮር ዱን ተኩሶ መምታት አይቻልም ። በሩስያው አክሪድና በአሜሪካው ፎኒክስ መካከል የሚኖረው ልዩነት 30 ኪሎ ሜትር ብቻ ነው ። ለዚህ ነው ኤፍ—14 የሰማይ ንጉሥ ነው የሚባለው ። ላስኮቭ በትንሽ ደቂ ቃዎች ውስጥ ምንም ውጤት ስለማያገኝ “ኾኬ ፣ ይህ አውሮፕላን 130 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ከመድረሱ በፊት ፣ አንተ ካላወከው ወይም የራሱን ማንነት ካላሳወቀ በስተቀር ልመታው ነው ” አለው ።

ጄኔራል ታልማን በምሽግ ቢሮው ውስጥ ሆኖ ከተቀመጠበት ተነስቶ የራዲዮ ስልኩን በማንሳት ገብርኤል ፣ ይህ ከሥራ መመሪያ መቆጣጠሪያ ክፍል ነው ፣ ስማ ፣ ኢላማው አንተ ነህ ፣ ውሳኔ የምት ሰጠውም አንተ ነህ ። ነገር ግን ለእግዚአብሔር ብለህ ነገሩን ከሁሉም አቅጣጫ ተመልከተው ። ምንም ይሁን ምን ከአንተ ጋር ነኝ ” ብሎ ከነገረው በኋላ ሪዙን እየነካካ ራዳሩን መመልከቱን ቀጠለ ።

ላስኮቭ ከታልማን ይጠብቅ የነበረው እንዲመታ ቁርጥ ያለ ትዕ ዛዝ እንዲሰጠው ነበር ። ግን ታልማን የተሻለ ያውቃል የሚል ስሜት አደረበት ።

“ ገብርኤል ፣ ይህ ኾኬ ነው ፣ ስማ ፣ የጦር አውሮፕላን አይደ ለም ” አለው ።

“ ታዲያ ለምንድን ነው 960 ኪሎ ሜትር በሰዓት የሚበረው ? ”

" ምናልባት የሕዝብ ማመላለሻ ጄት ሊሆን ይችላል ፤ ገብርኤል እስኪ አንድ ጊዜ — በራዲዮኔ ድምጽ እየተሰማኝ ነው ። "

" የሕዝብ ማመላለሻ ጄት ቢሆንም እኔ ግድ የለኝም ። ምክንያቱም በዚያ ተመስሎ ሚሳይል ለመተኮስ የሚችል ይሆናል ። ይህ አውሮፕላን ማንነቱን በአስቸኳይ ካላስታወቀ በስተቀር ላጠዘው ነው " ብሎ ላስኮቭ ጮኾ ተናገረ ።

መልስ አልነበረም ።

ዳኒ ላቮን " ይህ ሁሉ ጣጣ ማብዛት ነው ። ኃላፊነቱን እወስዳለሁ ። አንተ ደንግጨ ያደረከት ይመስልሀ ይሆናል ። እኔ ግን አነጣጥሬ ልመታው ነው " ብሎ ነገረው ።

ራዲዮናቸው በድንገት ተቋረጠ ።

" ስማ አንተ ልጅ ፤ ትዕዛዞችን እየተቀበልክ መፈጸም አለብህ ። ከአሁን በኋላ ሌላ ውጣ ውረድ እያስፈልግም " የሚል ንግግር በራዲዮኑ ሰማ ።

የኢ — 2 ዲ አየር ተቆጣጣሪ መኰንን እንደገና በመስመሩ ላይ በመምጣት " ገብርኤል ፤ ይህ ኾኬ ነው ። አድምጠኝ ፤ በሳይፕረስ ውስጥ ከሚገኘው የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ ጋር ስለዚህ ማንነቱ ስላልታወቀ አውሮፕላን ተነጋግረን ነበር ። የሕዝብ ማመላለሻ ሌየር ጄት ሞዴል 23 በፈረንሳይ ስም የተመዘገበ ሲሆን ከካይሮ በሳይፕረስና በኢስታንቡል በኩል አድርጐ ወደ አቴንስ ለመብረር ያስመዘገበ መሆኑ ተነግሮናል ፤ ተሳፋሪዎቹም የፈረንሳይ ፓስፖርት ያላቸው ስድስት ነጋዴዎች መሆናቸው ተነግሮናል ። የራዲዮ መስመራቸውና ምልክታቸው ስለተነገረን ለመገናኘት እየሞከርን ነን " አለው ።

ላስኮቭ የሰማው ስለአልጣመውና ስላላጠገበው " እየሞከርን ? የማይመስል ነገር ፤ አሁን 130 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ደርሰዋል ። የራዲዮ መስመራቸውን አግኝተሃል ። አንተም እጅግ በጣም ዘመናዊ ራዲዮ ይዘሃል ። ታዲያ ኾኬ ችግሩ ምንድን ነው ? " ብሎ ጠየቀው ።

" ችግሩ የእነርሱ ሊሆን ይችላል ፤ ገብርኤል ። "

" ሮጀር " ብሎ ላስኮቭ በረጅሙ ተነፈሰ ። በመስኮቱ መካከል በመነጽር ተመለከተ ። ሁለቱ ኮንኮርዶች ከወረቀት እንደተሠሩ አውሮፕላኖች ዓይነት ሆነው ከበታቹ ተንሳፈዋል ።

" ክሊፐርና አማኑኤል ፤ ይህ ገብርኤል ነው ። ይህን ሁሉ ነገር እየተከታተላችሁ ናችሁ ? " ብሎ ጠየቃቸው ።

ቢከርና አቪዳር በአዎንታ መለሱለት ።

" እንግዲያውስ የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያን ወደ ሰሜን በመ ዞር ወደ 19 ሺህ ሜትር ከፍታ እንድትበሩ ፈቃድ ጠይቁ "

ቢከርና አቪዳር ትዕዛዙን ተቀበሉ ። አቪዳር ለአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያው ክፍል ይህንኑ ስለአስታወቀ ትራንስወርልድ አሜ ሪካ — 747 እና ሉፍታንዛ — 707 ከላይ ስላሉ ወደ ጠየቁበት ከፍታ ለመብረር አምስት ደቂቃ እንዲጠብቁ መልዕክት ደረሳቸው ።

ላስኮቭ ግን አምስት ሴኮንዶች እንኳን መቆየት አልፈለገም ። በውስጥ መነጋገሪያው ከላቮን ጋር ተነጋገረ ። ታልማን ወይም ሌሎች ሰዎች እንዲሰሙት ስላልፈለገ በራዲዮኑ አልተጠቀመም ። " ፎኒ ክሱን አነጣጥር ዳንኤል ፤ ኢላማህን ለማግኘት ተዘጋጅ " አለው ። በዚህ ጊዜ ነበር ሚሪያም በርንስቴይን " በራዳርህ ሰይጣንን ራሱን ብታየው በሚሳይልህ እንዳትመታው ። " እንደዚሁም ሪቻርድሰን " ስማ ፤ በሰማይ ላይ ምላጭ በመሳብ እንዳትደሰት ፤ ምንም ዓይነት ግጭት እንዲደርስ አንፈልግም " ያሉትን ያስታወሰው ። ቀጥሎም በሕ ይወት ዘመኑ ሁሉ ምን ዓይነት አስቀያሚ ሥራ እንደነበረው አስ ታወሰ ። " ኾኬ ፤ ይህ ሰው ካልተናገረና ራሱን ካላሳወቀ በስተቀር የመኖር ዕድሜው ስልሳ ሴኮንዶች ብቻ ይሆናል " አለው ።

በዚህ ጊዜ መልስ የሰጠው የኾኬ አብራሪ ነበር ።

" ሮጀር ፤ ገብርኤል ፤ ልናነጋግረው ባለመቻላችን አዝናለሁ ። ምንም ማድረግ አልችልም ። ያለህበት ሁኔታ ይገባኛል ። ያዋጣል ብለህ የምታምንበትን ፈጽም " አለው ።

" አመሰግናለሁ ። "

ታልማን አቋርጦ በመስመሩ በመግባት " ገብርኤል ፤ እኔም ከአ ንተ ጋር ነኝ " አለው ።

ታልማን አንድ ችግር እንደተፈጠረ እየገባው መጣ ። የዚህ ያል ታወቀ አውሮፕላን ራዲዮ የማይሠራ ቢሆን ኖሮ ተመልሶ እስክንድ ሪያ ያርፍ ነበር ። ታዲያ ካልተበላሸ ለምን መልስ አይሰጡም ? የኾ ኬውን ጥሪ በሌየሩ መስመር ላይ ሰምቶታል ። ኾኬው የበረራ ዓለም አቀፍ ቋንቋዎች በሆኑት በእንግሊዘኛና በፈረንሳይኛ በመጨረሻም በአረብኛ ሳይቀር ለሌየሩ ተናግሯል ። ታልማን በራዲዮ " ገብርኤል ፤ ነገሩ በጣም አሳሳቢ ነው " አለው ።

" ልክነህ " ካለ በኋላ ላስኮቭ በውስጥ የድምጽ ማጉሊያው "የት ደርሷል ? " ብሎ ጠየቀው ።

ላቮን ራዳሩን ተመልክቶ " በአሁኑ ጊዜ 60 ኪሎ ሜትር እር ቀት ላይ የደረሰ ሲሆን ወደ ላይ እየወጣ ነው " ብሎ መለሰለት ። በፎ ኒክሱ አንጣጥረውና ግብ አግብተው ሊ.ሙቱት የሚችሉበት ጊዜ የዘ ገየ ቢሆንም " የእስፖርውን መሣሪያ አቀባብለህ በኢላማህ ውስጥ ለስገባው " ብሎ አዘዘው ።

" እሺ ጄኔራል " ብሎ ላቮን መሣሪያውን ካቀባበለ በኋላ ጣቱን በኤሌክትሪኩ መስመር ላይ ባለው ቀይ ቁልፍ ላይ አስቀመጠ ።

" ገብርኤል ፤ ይህ አማኑኤል ነው " ብሎ ቤከር ሲናገር ድምጹ የጐረና መሰለ ።

ላቮን እንዳይተኩስ ላስኮቭ እጁን ከያዘው በኋላ የሚሰማው መሆ ኑን ለቤከር ገለጸለት ።

" ሌየሩ በእኛ መስመር እየጠራን ነው ። "

"ሮጀር" ፡ ላስኮቭ በፍጥንት የኤል አልን ራዲዮ መስመር አስተ ካከለ ። ላቮን ሌሎቹም መስመራቸውን ከፍተው እንዲያደምጡ ትዕዛዝ ሰጣቸው ።

" ኤል አል 01 እና 02 ፤ ይህ ሌየር ቁጥር 5—4 ነው ፤ ይሰማች ኋል ? "

በዚህ ጊዜ ላስኮቭ ቀዝቃዛ ላብ በጀርባው ላይ ኩለል ብሎ ሲወ ርድ ተሰማው ። የድምጽ አጣጣሉ ያለጥርጥር አረብኛ ነበር ።

ቤከርና አቪዳር እንደሚሰሙት አስታወቁ ።

ሌየሩ እንደገና ተናገረ ። ድምጹ የረጋና አጭር ነበር ። " በጣም በጥንቃቄ አድምጡኝ ። ለእናንተ በጣም አስፈላጊ የሆነ መልዕክት አለን ። "

ቤከርና አቪዳር የሚሰሙት መሆናቸውን ሲገልጹለት በድምጻ ቸው ላይ የፍርሃት ምልክት ነበረበት ።

ሌየሩ ጊዜ ለማጥፋት ነው ብሎ ላስኮቭ ስለአመነ ለላቮን "እጁን ሳነሳ " ተኩስ አለው ።

ታልማን በሥራ መምሪያው ክፍል እንደ በድን ሆኖ ቆመ ። እም ነት በሚያሳጣ ዓይነት ወደ ራዲዮኑ ተናጋሪዎች ትኩር አድርጐ ተመ ለከተ ። ለራሱ " ምን ዓይነት አጋጣሚ ነው " ብሎ ተናገረ ።

ሌየሩ በድጋሚ በጣም በችኮላ " በእያንዳንዱ ኮንኮርድ ጅራት ውስጥ በራዲዮ መቆጣጠሪያ የተጠመደ ቦምብ አለ ። ይህ ምንም የሚ

ያጠራጥር ነገር አይደለም ። ቦምቦቹ እንዲጠመዱ የተደረጉት በ01 ውስጥ በቅዱስ ናዛየር ሲሆን በ02 ውስጥ ደግሞ በቱሉስ ከተማ ነው ። እያንዳንዳቸው ከቁጥር አሥራ አንድ ነዳጅ መያዣ ጋር እንዲገናኙ ተደርገዋል ። በአሥራ ሁለት ኤፍ—14 ተዋጊ አውሮፕላኖች እንደ ታጀባችሁ አውቃለሁ ። የሚሳይሎቻቸውን ጢስ ወይም የመድፎቻ ቸውን ብልጭታ ባይ ከመቅጽበት የራዲዮኔን መዘውር ስለምነካው ሁለቱም ኮንኮርዶች አመድ ይሆናሉ ። የምናገረው ይገባችኋል ? የኤፍ—14 ነጂዎች ትሰማላችሁ ? ይገባችኋል ? ” አላቸው ።

ላስኮቭ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆን ተቀምጦ ተመለ ከተ ።

አቪዳር በንዴት ድምጹ እየተንቀጠቀጠ “ዲቃላ” ብሎ ጮኸ ።

ቢከር በራዲዮኑ “ ሮጀር” ብሎ ተናገረ ። በድምጽ ማጉሊያው ረጋ ብሎ “ ሆስነር ፣ ጄኔራል ዶብኪንና በርግ ወደ ነጂው ክፍል ኑ ልኝ ” አላቸው ።

ላስኮቭ በትካዜ ሰመመን ውስጥ ዋዠቀ ። ባጭሩ የደረሰውን ነገር ሊያምን አልቻለም . . . ጥንድ የመስክ መነጽሮች በእግሩ አጠ ገብ ካስቀመጠው የቆዳ ቦርሳ ውስጥ አውጥቶ በጭኑ ላይ በማስቀመጥ አጉንብሶ ተመለከታቸው ። ከዩኒፎርሙ ሌላ ከሩስያ ያመጣቸው መነጽሮቹ ነበሩ ። ወደ ንጹሁ ሰማይ አንስቶ ተመለከተባቸው ። አረ ንጓዴና ነጭ ቀለም ያለው ሌየር 23 ከሁለት ሞተሮቹ የሚወጣው ጢስ እንደመቀነት በቀጭኑ እየተጥመለመለ ወደ እነርሱ በመቃ ረብ ላይ መሆኑን ተመለከተ ። በጣም በመቅረቡ ምክንያት በያዙት መሣሪያ አነጣጥሮ ለመምታት እማይቻልበት አካባቢ ደርሷል ። በስ ፓሮው ተኩሶ ለመምታት እርቀቱ ቢያንስ ከ16 ኪሎ ሜትር ማነስ የማይኖርበት ሲሆን በሳይድዊንደሩ ከ8 ኪሎ ሜትር መርዘም የለበ ትም ። ሌየሩ 90 ዲግሪ ዞሮ በኮንኮርድ 02 በኩል በረረ ። ሌየሩ የመ ቆጣጠሪያ መሣሪያ እንዳለውና በመስክ መነጽርም አንድ ሰው እንደ ሚመለከታቸው ገባው ። መነጽሮቹን ከዓይኖቹ ላይ አነሳ ። ላስኮቭ ሚሳይሉን ለማነጣጠር እንዲችል አውሮፕላኑን በድንገት ከፍ ለማ ድረግ አስቦ ነበር ። ነገር ግን የሌየሩ መመልከቻ የሚያደርገውን ለማ የት እንደሚችል ስለተረዳ ወደ ላይ ወይም ወደጐን ድንገተኛ በረራ ለማድረግ ፈራ ። ስለዚህ በረራውን እንደ ነበረ ቀጠለ ። ቀስ ብሎ ሰላቮን “ ከዚህ የበለጠ ከተጠጉን ለመምታት እንድንችል ሳይድዊ ንደርህን አስተካክል ” አለው ። ይሁን እንጂ ጥሩ ውጤት እንደማያ ስገኝ አውቋል ። ሌየሩ ከኮንኮርድ 02 ስር በመካከላቸው 150 ሜትር የከፍታ ልዩነት ብቻ የነበረው ሲሆን አልፎ አልፎ ወደ ኮንኮርድ 02

አፍንጫ እየተጠጋ ይመጣ ነበር ። አሁን ሌየሩ በኮንኮርዱ ስር ስለሆነ ላስኮቭ ሊያየው አልቻለም ።

ታልማን ተዝለፍልፎ በወንበሩ ላይ ተቀመጠ ። የሥራ አመራር ሠራተኞች ፍጹም በሆነ ጸጥታ ላይ ሆኑ ። ታልማን ሌየሩና ኮንኮርድ 02 ተቀራርበው ሲሔዱ በራዳር ተመለከታቸው ። ላስኮቭ በሚሳይሉ ምንም ማድረግ እንደማይችል ታልማን አወቀ ። ይህ ሁሉ የሆነው ላስኮቭ ሌየሩን ካየበት ጊዜ ጀምሮ ከአስር ደቂቃ ባነሰ ጊዜ ነበር ። የዚህ ዓይነት ነገር ሊያጋጥም እንደሚችል ምንጊዜም ያውቅ ነበር ። በአንድ ወይም በሁለት እብድ ሰዎች ብዙ ነገሮች ሊደርሱ ይችላሉ ። በዘመናዊ የጥበብ ዕድገት ምክንያት የማይቻል ነገር የለም ። እዚህ ይግባ በማይባል ግለሰብ የአንድ ሕዝብ የወደ ፊት ዕድል ሊገታ አይ ችልም ። በከተማ ውስጥ የተጠመደ አውቶሚክ ቦምብ ፣ ዕልቂት የሚ ያስከትል በውሃ ውስጥ የተደረገ መርዝ ፣ በኮንኮርድ ውስጥ የተጠመደ ቦምብ — እንደዚህ ዓይነቱን አስቸጋሪ ሁኔታ እንዴት አድርጐ መቆ ጣጠር ይቻላል ?

ሆስነር ፡ ዱብኪንና በርግ መጥተው እንደቆሙ ስላጋጠማቸው ሁኔታ ቤከር ገለጸላቸው ። ቶም ሪቻርድሰንና ጆን መክለር ሳይጠሩ ወደ እነቤከር መጡ ። ሌየሩ እየቀረበ በመምጣቱ አንድ ነገር እንዳጋ ጠመ ገብቶአቸዋል ።

መክለር የክብሪት እንጨት እያኘከ እንደ መዝለፍለፍ ብሎ ግድ ግዳውን ተደግፎ ቆመ ። ፍጹም ረጅምና ቀጭን በመሆኑ የተነሳ አን ዳንድ ሰዎች መክለርን ሲያዩ ጂም አልባው ሊኮንን ያስታውሱ ነበር ። ቤከር የተጠለፉ መሆናቸውን በነገራቸው ጊዜ መክለር “ በፓን አሜ ሪካ አየር መንገድ መሔድ ነበረብኝ ? ” አለ ።

በርግ ወደ ቤከር ዞሮ “ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ወደዚህ እንዲ መጣ እንድነግረው ትፈልጋለህ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ቤከር ራሱን በአሉታ ነቅንቆ “ አንድም የፖለቲካ ሰው ምክር እንዲሰጠኝ አልፈልግም ። ስለዚህ ትንሽ ብትታገሰኝ ውሳኔውን እኛው ራሳችን እዚሁ እንሰጣለን ” አለው ።

ቤከር ሌየሩ በየጊዜው በኮንኮርዱ አፍንጫ ስር ብቅ ጥልቅ ሲል አይቶታል ። ቬትናሞች በተኩስ ልውውጥ ጊዜ በጣም መጠጋቱን ይወዱት ከነበሩአቸው ምክንያትቶች አንዱ፣ አሜሪካኖች “ከባድ መሣ ሪያቸውን የራሳቸውን ሰዎች ካልገደሉ ሊጠቀሙበት አይችሉም ” ብሎ አንድ ወቅት በቬትናም ውስጥ የነበረ አንድ የእግረኛ ጦር ወታ ደር የነገረውን አስታወሰ ። ላስኮቭ በዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ እንደ ወደቀቤከር አወቀ ። ሁሉም በዚህ ችግር ውስጥ ነበሩ ።

ሆስነር በነገሩ ያልተቆረቆረ በመምሰል አርቆ ያስብ ነበር ። በፊቱ ላይ የትዝታ ፈገግታ ታየ ። ቀድሞ ሊያስታውሰው ያልቻለው ነገር አሁን ትዝ አለው ። ሪሽ በእነዚያ የፈረንሳይ መንደሮች ታይቶ ነበር ። የመንደሮቹ ስም በዚያ ጊዜ ትርጉም አልሰጠውም ነበር ። በዚያ ጊዜ እስራኤል ኮንኮርዶች አልነበሩአትም ። አሁን ግን እነዚያ ለእርሱ ግልጽ ያልነበሩ መንደሮች ለቅዱስ ናዛየርና ለቱሉስ ከተሞች ቅርብ ነበሩ ። ስለጸጥታ ጉዳይ ስብሰባ ባደረገበት ጊዜ የተናገራቸውን ቃሎች አስታወሰ — እነዚህ ኮንኮርዶች በአውሮፕላን ሜዳችን ላይ ባለፉት አሥራ ሦስት ወሮች ቆመዋል ። እጃችን ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የጸጥታ ሠራተኞቻችን ለአንድ አፍታ እንኳን አልተለዩአቸውም — ያ ነበር ደካማ ጐኑ — በእጃችን ከገቡ ጀምሮ . . . ቅዱስ ናዛየር ፥ ቱሉስ ምን ዓይነት ደደብ ነበር ።

ቤከር ከትከሻው ጭምር ወደ ሆስነር ዞሮ “ በቦምብ ለመምታት ይቻል ይሆን ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ሆስነር በአሉታ ራሱን በመነቅነቅ “ አዝናለሁ ” አለው ።

ቤከር ለራሱ እጉተምትሞ በሩቅ ማሰብ ጀመረ ።

ራዲዮኑ ቅቅ አለ ። ወደዚያው የማቲ ያዲን ድምጽ ተሰማ ። ሆስነር በአውሮፕላኑ አብራሪዎች ክፍል ውስጥ እንደነበረ አውቋል ።

“ አለቃዬ ፥ ልክ ነበርክ ። ”

ሆስነር መልስ አልሰጠውም ።

ቤከር በልዩ የመስመር ሞገዳቸው በመጠቀም ለላስኮቭ “ ምን እናድርግ ገብርኤል ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ በተጠንቀቅ ቆይ ። ” ላስኮቭ የሌየሩ አፍንጫ በኮንኮርድ 02 አፍንጫ ስር አልፎ አልፎ ብቅ ሲል ይታየው ነበር ። ወደ መድፉ ቃታ ተመለከተ ። በሐሳቡ ስልሳ ባለሃያ ሚሊ ሜትር የመድፍ ጥይቶች ተኩሶ የኮንኮርዱን መስታዎት አልፈው የሌየሩን ነጂ ክፍል ሲበታትኑት ታየው ። ነገር ግን ባለሃያ ሚሊ ሜትር የመድፍ ጥይቶች አልነበሩትም ። ቢኖረውም እንኳን ያን የመሰለ አደገኛ ሁኔታ ለመውሰድ ይደፍር ይሆን ? ቀደም ብሎ ዕድሉ ነበረው ፤ አሁን ግን አይችልም ። ስለሪቻርድሰንና በርንስቴይን አሰበ ። የተከዳ መስሎም ተሰማው ። የተከዳውም ጉዳዩን በደንብ በሚያውቁ ሰዎች መሰለው ። በማንም ይሁን በማን ክህደቱ ተፈጽሟል ።

በኮንኮርዶቹ ራዲዮኖች የሌየሩ ድምጽ እንደገና መጣ ። “እንደሚመስለኝ አጃቢዎቻችሁ የኤል አል ሞገዶችን እየነካኩ ናቸ

ው ። የአጀቢ አውሮፕላኖች አብራሪዎች ተጠንቅቃችሁ አድምጡኝ ። የምታደርጉትን የሚቆጣጠር መሣሪያ አለኝ ። ከእናንተ አንድ የተ ኩስ ብልጭታ ባይ በአንድ ጊዜ ኮንኮርዶቹን ድምጥማጣቸውን አጠ ፋቸዋለሁ ። ሞትን አልፈራም ። አሁን የምነግራችሁን መስማት አለ ባችሁ ። አጀባችሁን ትታችሁ ወደ ጣቢያችሁ መመለስ አለባችሁ ። እዚህ ምንም ማድረግ አትችሉም ። በስድሳ ሴኮንዶች ውስጥ ተመል ሳችሁ ባትሔዱ ምን ያህል ቆራጥ እንደሆንኩ ለማሳየት ከፊት የሚ ሔደውን ኮንኮርድ አመድ አደርገዋለሁ ። ”

አቪዳር “ ምን እናድርግ ገብርኤል ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ሌየሩ በኤል አል ሞገድ በመጠቀም “ ኮንኮርዶች ፣ እንደምገ ምተው ከአጃቢዎቻችሁ ጋር እየተነጋገራችሁ ናችሁ ። ምንም የሚ ጠቅሙአችሁ ነገር የለም ። ተመልሶ ለመሔድ የሚቀሯቸው አሥራ አምስት ሴኮንዶች ብቻ ናቸው ” አላቸው ።

ላስኮቭ ኤፍ—14 ተዋጊ አውሮፕላኖች ትተው እንደሔዱ ሌየሩ ኮንኮርዶቹን ያቃጥላቸዋል የሚል ፍርሃት አደረበት ። ሌየሩ- ወይም የፈለገው ይሁን-ጂሆ (መያዣ) ይፈልግ ይሆን ? ለመጀመሪያ ጊዜ የኢል አልን ሞገድ በመጠቀም ለሌየሩ ተናገረ ። “ ሌየር ፤ ይህ ተዋጊ አጃቢ ነው ። እንሔድም ፤ በድጋሚ እነግርሃለሁ ፤ እንሔድም—አን ተንም ጭምር ወደ ሎድ ይዘንህ እንሔዳለን ። እኛን ተከትለህ በመ ሔድ ማረፍ አለብህ ። ባታደርግ ግን እበታትንሃለሁ ” አለው ለስለስ ባለ ድምፅ ።

ከሌየሩ የመጣው ድምፅ ሳቅ ነበር ። “ የተሰጠህ ጊዜ አልቋል ። ወደዚያ ሒድ ። አለበለዚያ ግን ሞት በአንተ ላይ ይሆናል ” አለው።

ሆስነር ከእነርሱ ጋር የሚነጋገረው ማን እንደሆነ አወቀው ። እጁን በቤከር ትከሻ ላይ አስቀምጦ “ ያን ሰው አውቄዋለሁ ። ለላስ ኮቭ የሰውየው ስም አህመድ ሪሽ መሆኑን ንገረው ። የሚናገረውን ሁሉ የሚያደርግ ሰው ነው ። ለላስኮቭ ትቶ እንዲሔድ ንገረው ” አለ ው ።

ሪቻርድሰን “ አደጋ አናደርስባችሁም ማለታቸው አይደለም ። አስቀድመው ቦምቡን አጥምደው ይሆናል ። ባጭሩ ይህ ድርጊት ጠለፋ ነው ። ምን እንደሚፈልጉ ጠይቃቸው ” ብሎ ንግግሩን ለት ንሽ ጊዜ ቆም ካደረገ በኋላ “ ስለባለ ሃያ ሚሊ ሜትሩ የማዝን መሆ ኔን ለቴዲ ላስኮቭ ንገረው ” አለው ።

ቤከር ወደ ዶብኪንና በርግ ዞረ ። የሆስነርንና የሪቻርድሰንን መል ዕክት ለላስኮቭ ካስተላለፈ በኋላ ሌየሩን “ እናንተ ሰዎች እነማን ናች ሁ ፤ የምትፈልጉትስ ምንድን ነው ? ” ብሎ ጠየቃቸው ።

ሪሽ ጮክ ባለና ግልጽ በሆነ ድምፅ " እነማን እንደሆን ማወቁ ዋጋ የለውም ። ዋናው አላማችን እናንተን ወደ አንድ አልታወቀ ቦታ በመውሰድ የምንፈልገው እስኪፈጸም ድረስ በጁሆነት ለማቆየት ነው ። የምንላችሁን ካደረጋችሁ በማንም ላይ ጉዳት አይደርስም ። ይሁን እንጂ አጃቢዎቻችሁ በአንድ ሴኮንድ ውስጥ ትተው ባይሔዱ ከፊት ያለውን ኮንኮርድ አቃጥለዋለሁ " አለው ።

ዳኒ ላቮን በውስጥ መነጋገሪያው " በአውሮፕላኑ ውስጥ ቦምብ ካለው እዚህ ከአሁን በኋላ ምንም ማድረግ አንችልም ፤ ጄኔራል ። ምናልባት ከዚህ ኢላማ በመውጣት ከ160 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ልን ቋቋመው እንችል ይሆናል " አለው ።

ላስኮቭ ለታልማን " ተቆጣጣሪ ፤ ተመልሼ ወደ ማረፊያዬ እየ መጣሁ ነው " ብሎ ነገረው ።

ታልማን በራዲዮ ረጋ ባለ አነጋገር " የእኔ ስህተት ነው ፤ ገብር ኤል " አለው ።

ላስኮቭ የማንም ስህተት እንዳልሆነ አውቋል ። ነገር ግን ብዙ ሰዎች ለሚቀጥሉት ቀኖች እንደዚህ የሚሉ እንደሚኖሩ ጥርጥር የለውም ።

እንደገና ከሴየሩ ድምፅ ተሰማ ። ያው የቀድሞው ድምፅ እንደ ነበረ ላስኮቭ አስታውሷል ። ሪሽ ወደ ኋላው ተመልሶ እንዲሔድ እየ ጮኸ ነበር ። ላስኮቭ በበኩሉ የሰማውን ድምፅ ለጥቂት ሴኮንዶች ከምንም ባለመቁጠር ሁኔታውን ማመቻቸት ጀመረ ። ሴየሩ በኮንኮርዱ ላይ እንደዚህ አድርጎ ሊያጠምድ እንደቻለ ፤ በትክክል በተወሰነው ጊዜ ተነስቶ እንደዚህ ሊያደርግ ስለመቻሉ አወጣ አወረደ ። በተለይም ኮንኮርዶቹ በተነሱ በ30 ደቂቃ ውስጥ እንደዚህ ሊሆን መቻሉና በተጨማሪም በምሥጢር የሚነጋገሩበትን መስመር እንዴት ሊያገኝ እንደቻለና የሚናገሩትንም ሪሽ ሊሰማ መቻሉ አስገርሞታል። " ሦስተኛው የነዳጅ ታንክ አመልካች አይሠራም " ብሎ ተናገረ። ኤፍ—14 ፣ ኢ—2 ዲ ፣ ታልማንና ኮንኮርዶቹ ልዩ የሞገድ መስመራቸውን ከፈቱ ። ላስኮቭ በራዲዮ ክሊፐርንና አማኑኤልን ጠርቶ በችኮላ " ስሙና ማንነቱ የማይታወቅ ሰው በምሥጢር የምንጠቀምበትን የሞገድ መስመር እንዴት እንዳገኘው ባላውቅም እየተጠቀመበት ነው ። ይህንንም ሊያገኘው ይችላል ። ቢሆንም ላነጋግራችሁ እፈልጋለሁ ። ትተናችሁ አንሸሽም ። ኢ—2 ዲ የት እንዳላችሁ ይከታተላሉ። እኛም በ100 ማይል እርቀት ላይ እንሆናለን ። አሁን በምንነጋገርበት መስመር ላይ የሚያጋጥማችሁን እየተከታተላችሁ ንገሩኝ ። አስፈላጊ መስሎ የሚታያችሁን እርምጃ ለመውሰድ ስትወስኑ በ100 ኪሎ

ሜትር እርቀት ላይ በሚገኘው ፎኒክስ በተባለው መሣሪያ እንጠቀ ማለን ። በዚያ እርቀት ላይ ከአውሮፕላኑ የሚወጣውን ጭስ ጭምር ልዩ ክትትል ካላደረጉ በስተቀር ለማየት ጥሩ ዕድል አይኖራቸውም ። የምናገረው ይገባችኋል ? ” አላቸው ።

ሁሉም የአዎንታ መልስ ሰጡት ።

አህመድ ሪሽ በኤል አል ሞገድ ጮኾ በራዲዮኑ ተናገረ ።

“ እየተነጋገራችሁ እንደሆነ አውቃለሁ ። ይህን የማይጠቅም ሆያሆያችሁን አቁሙ ። ከአሁን በኋላ ያላችሁ አምስት ሴኮንድ ብቻ ነው ” ካላቸው በኋላ በኮንኮርድ 01 ላይ ተስተካክሎ የተቀመጠ ውን የራዲዮ መስመር ለመጫን ጣቱን በላዩ ላይ አድርጎ አንድ ፣ ሁለት ፣ ሦስት — ” አለ ።

ላስኮቨ በኤል አል መስመር “ መልካም ዕድል ” አላቸው። ኤፍ-14 አውሮፕላኖች ትዕዛዝ ስለተሰጣቸው 180 ዲግሪ ዞረው በሴኮንድ ውስጥ ከዓይን ተሰወሩ ። ቤከር ሲሔዱ ሊያያቸው ባይችልም ብቸኝነት ብድንገት ተሰማው ።

— 7 —

አቪዳር በተወሰደው እርምጃ አልተደሰተም ። ቀስ አድርጎ ፍጥ ነቱን ጨመረ ። እንደገመተው ከሌየሩና ከኮንኮርድ 02 መካከል ቢያ ንስ 10 ኪሎ ሜትር እርቀት አለ ። በራዲዮ አማካይነት ሊፈነዳ የሚ ችል ደማሚት ወይም ሌላ ንጥረ ነገር እስከ ምን ያህል እርቀት ድረስ ሊሠራ ይችላል ? በእርግጥ ከ10—12 ኪሎ ሜትር የበለጠ ሊሆን አይ ችልም ። ከፍታ የሚያሳየውን መሣሪያ ሲመለከት የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ ካዘዘው ከ5ሺህ ሜትር ትንሽ ላቅ ብሏል ።

የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያው ሌየሩ ከኮንኮርድ 02 ጋር በአ ንድ አቅጣጫ ሆኖ በጣም መቀራረቡንና ኤፍ — 14 አውሮፕላኖች ትተው መሔዳቸውን አውቋል ። ይሁን እንጂ በኤል አል የመስመር ሞገድ ላይ የተደረጉትን ውይይቶች ባይሰማም ተቆጣጣሪው አንድ ችግር እንዳጋጠመ ተገንዝቧል ። ተቆጣጣሪው “ በእናንተ በኩል ሁሉም ነገር ደህና ከሆነ በቀጥታ ወደ 19 ሺህ ሜትር ከፍታ መብረር ትችላላችሁ ። ስለመዘግየቴ አዝናለሁ ” አላቸው ።

ሪሽ የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያውን መስመር ጠልፎ ያዳምጥ ስለነበረ መልስ እንዲሰጡት ነገራቸው ።

አቪዳርና ቤከር መልስ ሰጡት ። አቪዳር ፍጥነት የሚያሳየውን ሲመለከት አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር በሰዓት የአየር ፍጥነት እየበረረ እንደነበረ አየ ። ስለዚህ በኃይል ከነዳ ከአሥራ አምስት ሴኮንዶች ባነሰ ጊዜ ውስጥ በተጨማሪ 3 ኪሎ ሜትር እንደሚርቅ ገመተ ።

የሬሽ ድምፅ እንደገና በራዲዮው ተሰማ ። " በጣም ጥሩ ፣ በጣም የሚስማማ — አሁን እንግዲህ የበረራ መስመራችሁን ለውጣችሁ እኔን ትከተላላችሁ። የምበረው በ160 ዲግሪ በ300 ማይል የአየር ፍጥነት ነው ። ኮንኮርድ 02 እኔን በቀጥታ ይከተላል ፤ 01 ደግሞ በቀጥታ 02ን ይከተላል ። ወደ 150 ሜትር ዝቅ ብለን እንበራለን ። ገባችሁ ?" አላቸው ።

ቤከርና አቪዳር የሰሙ መሆናቸውን አስታወቁ ።

ሌየሩ በረራውን ወደ ግራ ማዞር ሲጀምር ቤከር ለመከተል ተዘጋጀ ።

አሸር አቪዳር ኃይሉን ሁሉ በመጠቀም የአውሮፕላኑን ሞተሮች ሙሉ በሙሉ ቤንዚን አቅሞ በፍጥነት ስለበረረ ከፊት ለፊቱ በነበረው ንድፍ በመሰለው ደመና ውስጥ ገባ ።

ዜቪ ሂሬሽ በመደናገጥ " የምን እብደት ነው " ብሎ በአቪዳር ላይ ጮኸበት ።

ሊዮ ሻሬት ፊቱን ወደ እርሱ አዙሮ " አሸር ተው— " አለው ።

ማቲ ያዲን አብሮት ስለነበረ የአቪዳርን ክንድ አፈፍ ቢያደርግም በአቪዳር ተገፋ ። ያዲን በጣም ከመደናገጡ የተነሳ የስሚዝና ዌስን . 22 ሽጉጡን መዥርጦ አፈሙዙን በአቪዳር ራስ ላይ አደረገው ። አቪዳር ግን አንዲት የምታናድድ ትንኝ እንደሚያበር ዓይነት ሽጉጡን ከራሱ ላይ በፍጥነት ገፋው ።

በኮንኮርድ 02 ውስጥ ሙሴ ሔስ የቤከርን ክንድ ይዞ በኮንኮርዱ መስታወት ውስጥ ወደ ኮንኮርድ 01 ተመለከተ ። ቤከር የአቪዳር አውሮፕላን በዳመናው ውስጥ ገብቶ ሲሰወር አየው ።

የ02 ተሳፋሪዎች ባሁኑ ጊዜ እያንዳንዳቸው ያጋጠመ እክል መኖሩን አውቀዋል ። ያአኮቭ ሌይበር በአንድ ባዶ መቀመጫ ላይ ጉብደድ ብሎ በመስታወቱ ውስጥ ሚስቱን የያዘው ኮንኮርድ 01 በደመናው ውስጥ ገብቶ ከተሰወረ በኋላ እንደገና ከዳመናው ሲወጣ ተመለከተው።

በሌየሩ ውስጥ ከነበሩት ስድስት አረቦች አንዱ በአህመድ ሪሽ ላይ ጮኸበት ። ሪሽ ኮንኮርዱ ወደ ላይ ሲተኮስ ተመልክቷል ። በመ

ቀመጫው አጠገብ የነበረውን ኮንኮርዱን ሊያፈነዳ የሚችለውን የራ ዲዮ መስመር ማብሪያና ማጥፊያ የሚመስለውን በእጁ ያዘ ። ሁለት ቀለማቸው ቀይ የሆነ ማብሪያና ማጥፊያ የመሰሉ ነበሩ ። በስህተት ጣቱን 02ን ሊያፈነዳ በሚችለው ላይ ቢያስቀምጥም በፍጥነት ስህተ ቱን አርሞ ጣቱን ወደሌላው ላይ አዛወረ ።

ኮንኮርድ 01 ወደ ላይ መውጣቱን ቀጥሏል ። በአውሮፕላኑ ውስጥ ያሉት የከፍታና የፍጥነት መለኪያዎች እንደዚሁም የመቀመጫ መብ ራቶች ምልክት ሰጡ ።

አህመድ ሪሽ ከራዲዮኑ ክር ጋር የተያያዘውን ተጫነው ። በኤል አል 01 የነበረው የራዲዮ ተቀባይ ምልክት በሰማዩ ላይ ብልጭታ ሰጠ። ከአህመድ ሪሽ ጋር ያለው ራዲዮ መስመሩ ሲነካ በአውሮፕላኑ ውስጥ እንዲቀመጥ ያደረገው ፈንጂ በፍጥነት እንዲፈነዳ ተደርጐ የተሠራ ነበር ። በአውሮፕላኑ ጅራት ውስጥ የነበረው አራት ሺህ ሊትር ነዳጅ ፈነዳ ። የእሳቱ ምላስ ተውዘግዝጐ ወደ ተሳፋሪዎቹ ክፍል ተወረወረ። በክፍሉ ውስጥ የነበሩ ዕቃዎች በተሳፋሪዎቹ ላይ አረገፉ ። ኮንኮርዱ ሚዛኑን መጠበቅ አልቻለም ።

አሸር አቪዳር ፍንዳታውን ከመስማቱ በፊት የወሰደው እርምጃ እንዳልተሳካለት አወቀ ። ኮንኮርዱን ሊቆጣጠረው አልቻለም ። መብ ራቶቹ አንድ በአንድ ብልጭ ድርግም ማለት ጀመሩ ። በነጂዎቹና በተ ሳፋሪዎቹ መካከል የነበረው መዝጊያ ተበረገደ ። ሠራተኞቹ የተሳፋ ሪዎቹን ጩኸት ሰሙ ። ሂሪሽ ወደኋላው ዞሮ ሲመለከት በተጐመ ደው የአውሮፕላን አካል መካከል የፀሐይ ብርሀን ባየ ጊዜ ሊል የቻ ለው " አ አምላኬ ! " የሚል ብቻ ነበር ። በስተኋላው በኩል ማቲ ያዲን በወለሉ ላይ ወድቆ ደሙ መፍሰስ ጀምሯል ። አቪዳር ወደ ዜቪ ሂሪሽ ዞሮ " ለእነዚህ መጥፎዎች እጅን ከመስጠት በዚህ ዓይነቱ መሞት ይሻላል" ብሎ ወደ ውስጥ በገባው ሀይለኛ አየር ውስጥ ጮኾ ነገረው ። ሂሪሽ ትኩር አድርጐ ተመለከተው ።

ኮንኮርድ 01 ሚዛኑን ለመቆጣጠር የሚያደርገውን መፍጨርጨር ቤከር በኮንኮርድ 02 መስታወት መካከል ተመለከተ ። ከሚወጣው የብርቱካን ዓይነት የእሳት ነበልባል ፈንጂው የተጠመደው ማንም ሰው ሊደርስበት በማይችለው በቁጥር 11 የነዳጅ መያዣ ላይ እንደነ በረ ለማወቅ ቻለ ። ቦምቡ ትንሽ እንደነበረና ከፍተኛ አደጋ ሊደርስ የቻለው ግን በነዳጁ ፍንዳታ እንደነበረ ተገነዘበ ። እረጋ ባለ አነጋገ ለፒተር ካን " በኮምፒዩተር አማካይነት በቁጥር 11 ውስጥ ያለውን ነዳጅ አንድም ሳይቀር ለማውጣት ሞክር " ካለው በኋላ ወደ ሒስ

ዞሮ “ ተሳፋሪዎቹ ወደፊት እንዲመጡ በድምፅ ማጉሊያው ንገራ ቸው ” አለው ።

ቤከር በመስታወቱ መካከል ሁኔታውን ፈዞ ተመለከተ ። ሆስ ነር ፣ ዶብኪን ፣ በርግ ፣ ሪቻርድሰንና መክለር በሚያዩት ተደናግጠ ውና ፈዘው ይመለከቱ ነበር ።

ኤል አል 01 እየተፈረካከሰ ተገለባበጠ ። ክንፎቹ እየተገለባበጡ ተበታተኑ ። አቪዳር ከአደጋው ለመዳን የአውሮፕላኑን የመቆጣጠ ሪያ መሣሪያዎች በየተራ ሲነካካ ቤከር በሃሣቡ ታየው ። የድል መመቻ ጦርነት ነበር ።

ኮንኮርድ 02 በመሞት ላይ ወደ አለችው እሀቱ እየተቃረበ መጣ ። ቤከር የመስክ መነጽሩን አድርጎ ሁኔታውን ተመለከተ ። የአውሮፕ ላኑ አካላት እየተሰባበሩ ሲበታተኑ አያቸው ። አጉልቶ በሚያሳየው መነጽሩ ያየው ሁሉ እጅግ በከፋ ሀዘን ላይ ስለጣለው መነጽሩን አስ ቀምጠ ዓይኖቹንና ቅንጠቹን አሻሸ ።

እየተሰባበረ በመበታተን ላይ በነበረው አውሮፕላን ውስጥ አቪዳርና ሂሪሽ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ልዩ ልዩ መሣሪያዎች እንዲሠሩ ለማድረግ እየነካኩ ይታገሉ ነበር ። ሊዮ ሻሬት በትዕግሥት ሆኖ አንዳንድ መሣሪያዎች ለማስተካከል ቢሞክርም ሁሉም ስለተበ ታተኑ ውጤት አልባ ሆነ ። መሣሪያዎቹ አንድ በአንድ ብልጭ ድር ግም እያሉ ሥራቸውን አቆሙ ። ኮንኮርዱ በነፋስ ኃይል እየተገለባ በጠ እንደሚውለበለብ ብራማ ቅጠል ዓይነት ከጅራቱ በአፍንጫው ተደፋ ። ቀጥሎም ተቀጣጥሎ ተበታተነ ።

ቤከር ከተሳፋሪዎቹ የጭንቀትና የሀዘን ጩኸት ሰማ ። ያኮቭ ሌይበር ስለሚስቱ ያደርገው የነበረው ጩኸት በመጠኑ ይሰማው ነበር ።

ቤከር ስብርባሪው ወደ እነእርሱ ሲመጣ ስለአየ አደጋ እንዳይጥ ልበት በማሰብ ድንገተኛ እንቅስቃሴ ስለአደረገ በአጠገቡ ቆመው የነበሩ አምስት ሰዎች በወለሉ ላይ ወደቁ ። ተሳፋሪዎቹም ከመቀመ ጫቸው ላይ ተፈነጠሩ ። ፒተር ካን የመቀመጫ ቀበቶአቸውን እንዲ ታጠቁ ምልክት የሚሰጠውን መብራት ካበራ በኋላ በድምፅ ማጉ ሊያው “ እያንዳንዳችሁ በመቀመጫችሁ ላይ ቆዩ ። ሁሉም ነገር ይስተካከላል ” በማለት ሁኔታውን ገለጸላቸው ።

በነጂው ክፍል የነበሩት ሁሉ ከወደቁበት ወለል ላይ ከተነሱ በኋላ ሆስነር ወደ ዶብኪንና በርግ ተመለከተ ። እነርሱ ግን ፊታቸውን አዞሩበት ።

ከሌየሩ ጂት እንደገና በራዲዮ ድምፅ ተሰማ ። አሁንም የሪሽ ድምጽ ነበር ። ድምፁ ጩብራራና ቀጭን ሆኗል ። " ያን እንዳደርግ አስገደዱኝ ። አሁንም እናንተ ተጠንቅቃችሁ ስሙኝ ። ተከተሉኝ ፤ የምነግራችሁን አድርጉ ፤ ካልሆነ ግን የእነርሱ ዕድል ይገጥማችኋል " ብሎ ነገራቸው ።

ሆስነር የድምጽ ማጉሊያውን አንስቶ " ሪሽ ፤ አንተ ዲቃላ ፤ ይህ ያዕቆብ ሆስነር ነው ። አንተ የተረገምህ ነፍሰ ገዳይ ነህ ። ወርደን እንደተገናኘን እገድልሃለሁ ። አንተ የውሻ ልጅ " ብሎ ጮኸ በአረብኛ ነገረው ።

ሆስነር እንደጨረሰ የሪሽ ድምፅ እንደገና በራዲዮኑ ውስጥ መጣ። ሪሽ ራሱን ለመቆጣጠር ይሞክር እንደነበረ ከአነጋገሩ ያስታውቃል ። ረጋ ባለ አነጋገር " እንደወረድን የመጀመሪያ ሥራዬ አንተን መግደል ነው " አለው ።

ሆስነር በአረብኛ መልስ ለመስጠት ሲሞክር ቤከር መናገሪያውን ቀምቶ በልዩ መስመሩ ከላስኮቭ ጋር ለመነጋገር ሞከረ ። የሚሰማው ግን የተንጨባረረና ጫጫታ የሞላበት ቀጭን ድምጽ ብቻ ሆነ ። የሪሽ ድምፅ እንደገና ቢመጣም ከጫጫታው የተነሳ በግልጽ አይሰማም ነበር ። " ከአሁን በኋላ ከአጃቢዎቻችሁም ሆነ ከእኔ ጋር መልዕክት መለዋወጥ አትችሉም ። ማድረግ የምትችሉት እኔን መከተል ብቻ ነው " እንዳላቸው የራዲዮኑ መንጫጫት እየጨመረ መጣ ።

ቤከር የራዲዮኑን መስመሮች በሙሉ ካጠፋ በኋላ " ንግግራችን እንዳይሰማ አደረገ ። ምናልባትም ለመነጋገር እንዳንችል የሚያደርግ መሣሪያ ይዞ ይሆናል " ብሎ ወደ በርግ ተመለከተ ።

በርግ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። ፊቱም አመድ መሰለ ። ሌሎቹም እንደዚሁ ። የኤል አል ኮንኮርድ 01 ሁኔታ ጭንቅላታቸውን በጠበጠው ። በርግ እንደገና ራሱን በማነቃነቅ " ልሒድና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩና ለተሳፋሪዎች ልንገር ። በምን ሁኔታ ላይ እንዳለን ሁሉም ማወቅ አለባቸው " ብሎ ሲናገር ጉሮሮውን አንድ ነገር ፈጥርቆ እንደ ያዘው ዓይነት ዕንቅ ዕንቅ ያደርገው ነበር ። ቀጥሎም "ይቅርታ " ብሎ ከአውሮፕላኑ ነጂዎች ክፍል ወጣ ።

ቶም ሪቻርድሰን ጉሮሮውን ካፍታታ በኋላ " የአጃቢ አውሮፕላኖች ነጂዎች እንዲሔዱ መንገር አለብን " አለ ።

ዶብኪን በአዎንታ ራሱን ከነቀነቀ በኋላ " ጥሩ ነው ፤ እኛም እያንዳንዱ ተሳፋሪ ስናርፍ ምን ማድረግ እንደምንፈልግ መነጋገር አለብን ። በመያዣነት ስንወሰድ የአዕምሮ ውድቀት እንዳያስከትል

ባቸው ከአሁኑ የሥነልቦና ትምህርት በመስጠት የተስተካከለ አቋምና ወኔ እንዲኖራቸው ማዘጋጀት አለብን ። ይህ ደግሞ በጣም አስፈላጊ ነው ” አላቸው ።

ሆስነር “ አዎን ፤ ጥሩ ሃሣብ ነው ፤ የረጅም ጊዜ ምርኮኛነት ሊሆን ይችላል — በተለይም ላንተ ” አለው ።

ሪቻርድሰን “ ስለዚያ አትጨነቅ ሆስነር ፤ ያ የጠንቋይ ልጅ ሊያስፈራራህ እየሞከረ ነው ” አለው ።

መከለር በፓን አሜሪካ አየር መንገድ ቢሔድ የሚሻለው መሆኑን ከተናገረበት ጊዜ ጀምሮ ምንም ሳይተነፍስ ከቆየ በኋላ “ ራስህን አታታል ፣ ሪቻርድሰን ፤ ያ ሰው አምሳ ሰዎች ገድሏል ። ሆስነርን እገድለዋለሁ ብሎ ተናግሮ እንደሆን ቃሉን ተግባራዊ በማድረግ ይገድለዋል ” ብሎ ነገረው ።

“ አመሰግናለሁ ” አለው ሆስነር ።

“ እቅጩን መናገር አለብኝ ” ብሎ መከለር የክብሪት እንጨት ከኪሱ አውጥቶ በከንፈሮቹ መካከል ያዘ ።

ኮንከርዱ ሌየሩን ተከትሎ ወደ ደቡብ በረረ ። ሌሎቹ ወደ ተሳፋሪዎቹ ክፍል ሲሔዱ ሆስነር ግን በአውሮፕላኑ ነጂ ክፍል ቆየ ። ሆስነር የማንንም ፊት ሊቋቋም አልቻለም ። ምንም እንኳን ታልማን ስለ ጥንቃቄ የተናገረው ቃል ቢኖርም ፤ የላስኮቭ ፈጣን ውሳኔ አለመስጠት ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆን ቢያደርገውም ፤ ሆስነር ለደረሰው ችግር ሙሉ ኃላፊነት ተሰማው ። ላስኮቭ በዕድሜው ያካበተው የሥራ ልምድና የወታደርነት ችሎታው በሰላም ቃል ኪዳን ስም እንዲደበዝዝ ከመሆኑም በላይ በተጨማሪም ሌየሩ የንግድ ሰዎች የተሳፈሩበት ነው ተብሎ ከኮኪው የተሰማው ድምጽ እርምጃ እንዳይወስድ አደረገው ። አውሮፕላኖቹ በተሠሩበት ቦታ የፈረንሳይ የፀጥታ ክፍል ጥንቃቄ የጐደለውና ደካማ ነበር ። ከዚህ በስተቀር ላለፉት ብዙ ሺህ ዓመቶች ከጠራው ሰማይ በታች ከሜድትራንያን ባሕር በሺህ ከሚቆጠር ጫማ በላይ ሲፈጸም የቆየ ነበር ። ሆስነር አውሮፕላን ከማቲ ያዲን ጋር ተለዋውጠን ቢሆን ኖሮ የሚል ምኞት በአእምሮው ውስጥ ሠፈረበት ።

— 8 —

ጀኔራል ታልማን በምሽጉ የሥራ አመራር ክፍል ውስጥ ሆኖ የሥራ ባልደረቦቹንና የቴክኒክ ክፍል ሠራተኞቹን ዓይን ላለማየት እየጣረ ነበር ። ኮንኮርድ 01 ተበታትኖ ሲወድቅ በራዳሩ አይቶታል ።

ታልማን ሌየሩና ኮንኮርድ 02 ወደ ሲናይ ዳርቻ እየተቃረቡ በመሔድ ላይ እንደነበሩ ተመልክቷል ። በአሁኑ ዓይነት በረራቸውን ከቀጠሉና ካልተሰወሩ በስተቀር የት ቦታ እንደሚሔዱ ለማየት ይችላል ። ቀስ በቀስ ግን ሌየሩ ኮንኮርዱን ዝቅ ብሎ እንዲበር ስለሚያስገድደውና ይህም በራዳር ለማየት ችግር ስለሚፈጥር ወዴት እንደሚሔዱ ላይ ታወቅ ይችላል ።

የቴዲ ላስኮቭ የበረራ መኰንን የሆነው ዳኒ ላቮን በራዳሩ እየተ መለከተ በታልማን አባባል በመስማማት " ዝቅ እያሉ ስለሚሔዱ ሚዛናቸውን በትክክል ለመጠበቅ እማይችሉበት ደረጃ ላይ ሊደርሱ ይችላሉ ፤ ጄኔራል ። እኛም በሲናይ ላይ ሲበሩ ለማየት አንችልም" አለው ።

ላስኮቭ አባባሉን በዝምታ አለፈው ።

ታልማን ስልኩን አንስቶ በቁጥጥር ሥር የሆኑትንና ያሰማራቸ ውን አውሮፕላኖች አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት የግብጽን አየር ክልል በመ ጣስ በራዳራቸው በመጠቀም ኮንኮርዱ የት እንዳለ እንዲጠቁሙ አዘ ዛቸው ። ከታልማን ረዳቶች አንዱ ከካይሮ ጋር የስልክ ግንኙነት ቢያ ደርግ ግብጾች እንደሚተባበሩ ይታወቃል ። ችግሩ ግን ጥሪው ደርሶ እስኪነጋገሩ ድረስ የተወሰነ ጊዜ ይባክናል ።

ዴቪድ ቤከር ከውሃው በላይ 100 ሜትር ከፍታ እስኪደርስ ድረስ ተከተለው ። የሲናይን ዳርቻ እንዳለፉ ቤከር ለማየት እንዲያመቸው የአውሮፕላኑን አፍንጫ ዝቅ አደረገው ። በረሃው አልፈው አልፈው ጉች ጉች ብለው በበቀሉ አበቦች ተብረቅርቋል ። አውሮፕላኑም ዝቅ ከማለቱ የተነሳ ተንገጫገጨ ። በሪሽ አዕምሮ ውስጥ ምን እንዳለ ቤከር አላወቀም ። ይሁን እንጂ ሰውየው እብድ እንደነበረ ቅንጣት ያህል እንኳን ጥርጣሬ አልነበረውም ። ሌየሩን ከፍና ዝቅ እያደረጉ ማብረር ይችላሉ ። ለቤከር ግን ይህን ትልቅ ኮንኮርድ በዚያ ዓይነት ዝቅታ አስ ተካክሎ ለመንዳት እጅግ በጣም ከባድ ነው። የአየር ፍጥነቱ 250 ማይል ነበር። ከዚህ ባነሰ ፍጥነት ለመብረር ቢሞክር ግን አደጋ ላይ ይወድ ቃል ። ሌየሩ ግን ይህን ችግር የሚያውቅ አይመስልም ። ሌየሩ መጠ ነኛ እርማት ቢያደርግም ቤከር በዚያ ዓይነት እየበረረ ለመከተል ተቸ ግሮ ነበር ። የሌየሩ አብራሪ ብዙ የበረራ ልምድ እንደሌለው ቤከር ከሁ ኔታው ለመገንዘብ ችሏል ። ቤከር ኮንኮርዱ ወድቆ እንዳይከሰከስ ያለ ማቋረጥ ሚዛኑንና ኃይሉን ያስተካክል ነበር ። ካን በበኩሉ ኮንኮርዱ ሚዛኑን ለመጠበቅ እንዲችል ነዳጁን ወደ ቁጥር አሥር መያዣ እንዲ ተላለፍ አደረገ ።

ቤከር መቆጣጠሪያዎቹን ሲይዝ አፉ ደረቀ ፤ ልቡም መታ ። በቀኙ በኩል የስዊዝ ቦይ ፤ ከስሩ ደግሞ የሚትላ መተላለፊያ ነበሩ ። በፊት ለፊቱ ቦታው አቀበት እየሆነ መጣ ። ከባሕር በላይ የነበረው ከፍታ 330 ሜትር ወይም 1,100 ጫማ እንደነበረ በመሣሪያው ላይ ይነበብ ነበር ። ለቤከር ግን ከ100 ሜትር በላይ ከፍታ እንደሌለው ሆኖ ተሰማው ። በሩቅ የደቡባዊ ሲናይ ተራራዎች ሲያብረቀርቁ ታዩት ። ቀደም ብሎ እንደ ሚያውቀው የእነዚያ ተራራዎች ከፍታ 800 ሜትር ያህል ነበር ። የሌየሩ አብራሪ ከአሁን ጀምሮ ከፍታውን ካልጨመረ በስተቀር ከተራራዎቹ ጋር እንላተማለን የሚል ሃሣብ በቤከር አዕምሮ ውስጥ አደረበት ።

ሔስ ወደ ቤከር እየተመለከተ “ ዴቪ ይህ ሰው ሊገድለን ነው ” አለው ።

ቤከር እንደገና የራዲዮኑን ድምፅ ከፍ አደረገው ። ነገር ግን ሊ ሰማ የቻለው የድምፅ ጓጓታ ብቻ ነበር ። “ የውሻ ልጅ ! ሪሽ ! ሌየር ! በዚህ ከፍታ መብረር አንችልም ። የሌየሩ ነጂ ማንም ይሁን ማን እጅግ በጣም መጥፎና ማሰብ የማትችል ሰው ነህ ” ብሎ ጮኸ ። የራዲዮኑ ጫጫታ ስለቀጠለ “ የውሻ ልጅ ” ብሎ የራዲዮኑን ድምፅ ዝቅ አደ ረገው ።

ፒተር ካን ከበረራ መሃንዲሶች ክፍል “ ካፒቴን ፤ 585 ኪሎ ግራ ም ነዳጅ በደቂቃ እየተጠቀምን ነው ” አለው ።

“ ምን ያህል የበረራ ጊዜ ይቀረናል ? ”

“ ከሁለት ሰዓት ሠላሳ ደቂቃ ያነሰ ። ”

ቤከር ሰዓቱን ተመልክቶ አሥር ሰዓት ሊሆን ትንሽ እንደሚቀ ረው አየ ።

ሪሽ ሌላ ኢንቴቤ ለመፍጠር ዕቅድ ካለው በምንም ዓይነት አይ ሳካለትም ።

ቤከር “ መልካም ፤ ይህ ከንቱ ወዴት እንደሚወስደን ባውቅ የም ወስደው እርምጃ አዋጭ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ማወቅ እችል ነበር ። ቤከር ያጋጠመውን መጥፎ ዕድል እረገመ ። ከአሁን በኋላ የሚቀረው ሁለት ጊዜ መነሳትና ሦስት ጊዜ ማረፍ ነበር። ያ ሁሉ ሐሳብ ከንቱ ሆነና አሁን ግን ያለው ዕድል ኮንኮርዱን አንድ ጊዜ ብቻ ካሳ ረፈ በኋላ ተመልሶ ሊነሳ እንደማይችል በሐሳቡ ታየው ።

ሌየሩ ወደ ግራ በኃይል ተጠምዝዞ ስለበረረ ቤከር ተከተለው ። የቤከር አስተጣጠፍ ግን እንደ ሌየሩ ሳይሆን ወደ ቀኝ ከፍ ብሎ ስለነ

በረ ወደዚያው አስተካክሎ ሌየሩን ተከተለ ። ካን መነጽሩን እንዲሰ ጠው ቤከር ጠየቀው ። ቤከር በአሁኑ ጊዜ አንድ ሺህ ሜትር ያህል ወደሚርቀው ሌየር ተመለከተ ። ሌየሩ ወደ ኮንኮርዱ የሚመለከትበ ትን ልዩ መሣሪያ ለማየት ቻለ ። አንድ ሰው በመስክ መነጽር በሌየሩ ውስጥ ወደ ኋላ ዞሮ ወደ ኮንኮርዱ ሲመለከት ስላየ "የውሻ ልጆች" ብሎ ቤከር የመስክ መነጽሩን አስቀመጠ ። ለብዙ ጊዜ ያልተሰማ ውን አሁን እርግጠኛ በመሆን ድርጊቱ ሁሉ እንደ አዲስ ሆኖ ተሰ ማው ። "ሁሉም ነገር በትክክል ተከናውኗል ብለን ያመንበት ሁሉ መሆን የሚገባው እንደዚህ ነበር ?"

ሆስነር ፀጥ ብሎ ተቀምጦ ከቆየ በኋላ ቀና ብሎ በመመልከት "በራዳር እየተከታተሉ የሚመለከቱን ሰዎቻችን ዕድል ምን ይሆን ?" ብሎ ጠየቀ ።

ሔስ በትከሻው ላይ ተመልክቶ " በዚህ ከመሬት በላይ ዜሮ ሊደርስ በተቃረበ ከፍታ ላይ ለማየት ችግር ነው ። ይሁን እንጂ ኢ—2ዲ ከመሬት ላይ ያለውን ለመለየት የሚያስችል ኮምፒዩተር አለው ። ሆኖም በግብጽ መሬት ላይ ለጥቂት ጊዜ ስለበረርን ፈለጋችንን ተከ ትሎ ያያል ብየ አልገምትም " አለው ።

" ግብጾችስ ? "

ሔስ ራሱን ነቀነቀ ። " የግብጽ ራዳር አነጣጥሮ እንዲያይ የተደ ረገው በምሥራቅ በኩል ወደ እስራኤል ነው ። ምናልባትም ወደ መሬት ዝቅ ብለን በምንበርበት ጊዜ ሊያዩን ይችሉ ይሆናል ። ነገር ግን ግብ ጾች ምን እየተካሔደ እንደሆነ ለማጣራት በሚሞክሩበት ጊዜ አሁን ባለን አቅጣጫና ፍጥነት መሠረት በቀይ ባሕር ላይ እንሆናለን ። ለማ ንኛውም ፍላጐት ቢኖራቸውም እንኳን ሊረዱን አይችሉም ፤ ልክ ነኝ ? "

" ላስኮቭ በሚሳይል ለመምታት አቅርቦት ስለነበረው ጥያቄ እ ያሰብኩ ነበር ። ምናልባት እስከ አሁን በራዳር እየተከታተለን እንደ ሆን በጥያቄው እኛስ እንስማማለን ? " አለው ሆስነር ።

" አሁንም በራዳሩ እየተከታተለን ከሆነና ጀንበር ከጠለቀችም በኋላ እንደዚሁ የምንቀጥል ከሆነ እርምጃ እንዲወሰድ እኔም እስማማ ይሆናል ። በአሁኑ ሰዓት ፀሐይ እያለች ግን ሚሳይል ቢተኮስ ጭሱን ለማየት የሚያግድ ነገር አይኖርም ። ከሚሳይሉ ይልቅ በኤሌክትሮኒ ክስ አማካይነት እንዲፈነዳ የተጠመደው የበለጠ ፍጥነት ስላለው አደጋ ያስከትልብናል " ብሎ ቤከር ነገረው ። ቀጥሎም ወደ ግራና ወደ ቀኝ እያዘነበለ የነበረውን የኮንኮርዱን ጅራት ለማስተካከል እየሞ

ከረ " ግን ሌየሩ በጣም ቀርቦናል ። በራዳሩም የሚያየን በጣም ፣ በጣም ቀርበን ነው ። በዚህ ምክንያት ቢተኩስም ለይቶ ለመምታት እጅግ አስቸጋሪ ነው " ብሎ በተጨማሪ ነገረው ።

ሆስነር ከተቀመጠበት ተነስቶ " ድራቱንና ሌላውን የሚለየውን የብረት ግድግዳ ማየት አለብኝ " አለው ።

" ጥሩ ነው ፤ እኔም ስለእዚያ ሳወጣና ሳወርድ ነበርኩ ። እንደምታውቀው ከዚህ ወደ እዚያ ለመግባት አይቻልም ። ነገር ግን አንተ ከፈለግህ በድራቱ ለመውጣት ተፈቅዶልሃል ። " ቤከር በሰጠው አስተያየት ወደዚያው አዘነ ። በነበረው የበረራ ሁኔታ በየደቂቃው አስተሳሰቡ እየተለዋወጠ መጣ ።

ሆስነር ከአብራሪው ክፍል ወጥቶ በተሳፋሪዎቹ መካከል ሲያልፍ አንድም ሰው አልተናገረውም ። ትንሹ ያአኮቭ ሌይበር እንባ በተሞሉ ዓይኖቹ ትኩር አድርጐ ተመለከተው ። ስለጸጥታ በተደረገው ስብሰባ ላይ የነበሩት ሰዎች ፊታቸውን ከእርሱ አዞሩ ። በሚያልፍበት ጊዜ ሚሪያም በርንስቴይን ክንዱን ብትነካውም ዞሮ አላያትም ። የእርሱ የሆኑትን ሁለት ሰዎች በሚያልፍበት ጊዜ በትከሻቸው ላይ መታ ስለአደረጋቸው ተነስተው ተከተሉት ።

ሆስነር የአውሮፕላኑ ነጂዎችና አስተናጋጆች ልብሳቸውን ወደ አስቀመጡበት ወደ አንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ ገባ።በውስጡ የተሰቀሉ የመንገደኞች ኮቶችና ካፖርቶች እንደዚሁም የሠራተኞች ሻንጣዎች ነበሩ ። ልብሶቹን ገለል በማድረግ የብረቱን ግድግዳ ትኩር አድርጐ ተመለከተ ።

* * *

ታልማን አስር አውሮፕላኖቹ በሲናይ ላይ እየተከታተሉ ለሥራ መምሪያው ክፍል ያስተላለፉትን ሪፖርት አዳምጧል ። በራዳርም ሆነ በዓይን በመመልከት ምንም ዓይነት ዕይታ ያላገኙ መሆናቸውን ተረድቷል ። በመጨረሻም ላስኮቮ " ነዳጅ ለመሙላት ወደ ኢላት እየመጣሁ ስለሆነ ነዳጅ የሚሞሉልን ተዘጋጅተው ይጠብቁን ። እንደገና ከተነሳሁ በኋላ እነእርሱን እስካገኛቸው ድረስ ተመልሼ አልመጣም ፡ ስለዚህ በአየር ላይ የአሜሪካ ነዳጅ ጫኝ አውሮፕላን ሲያስፈልገን እንዲሞላልን አዘጋጁልን ። እስከ ማገኛቸው ድረስ በአካባቢው ባለው በእያንዳንዱ ቦታ ላይ እበራለሁ ። አብራሪዎቹና የአብራሪ መኰንኖች አንዱ ሲያንቀላፋው ሌላው በፈረቃ ያበራል " የሚል ሪፖርት አስተላለፈ ።

ታልማን ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ " እስኪ አንድ ጊዜ ገብርኤል" ብሎ የቦታዎችን ሁኔታ የሚያሳየውን የሚያብረቀርቅ ማፕ ተመለከተ ። ኮንኮርዱ ከተሰወረበት ጊዜ ጀምሮ 30 ደቂቃዎች ያለፉ ሲሆን

ፍጥነቱም በሰዓት 500 ኪሎ ሜትር ነበር ። ከዚያ በኋላ በማንኛውም አቅጣጫ ሊበሩ ይችላሉ።በዚያ ዓይነት የአየር በረራ ፍጥነት ከቀጠሉ ክትትል ሊደረግበት የሚገባው ክልል እስከ አሁን ድረስ 196,350 ካሬ ኪሎ ሜትር ይሆናል ። ይህም ከ150 ሜትር እስከ 8 ኪሎ ሜትር ያለው ከፍታ በስሌት ውስጥ ሳይገባ ነው ። እያንዳንዱ የበረራ ደቂቃ የካሬ ኪሎ ሜትሩንና የኪዩቢክ ኪሎ ሜትሩን ብዛት ሳይጨ ምር ነው ። የራዲዮኑን መስመር ነክቶ “ ገብርኤል ፤ ምናልባት ወደ ሎድ አምርተው ይሆናል የሚል ግምት ስለአለን አንተ ተመልሰህ ና ። የት እንዳሉ በቅርብ ጊዜ እናውቃለን ። የውጭ አገር ክልል ለአ ንድ ቀን በድፍረት ተላልፈናል ። ግብጾች እስከ አሁን ድረስ ቢታገ ሱንም ከአሁን በኋላ በዝምታ ሳያልፉ እንድንወጣ ይፈልጋሉ ። ክት ትል የሚያደርግ አየር እንደሚልኩ ቃል ገብተውልናል። ስለዚህ ገብ ርኤል ፤ ከሕግ ውጭ ለመሥራት አትሞክር። ጠላፊዎቹ የሚፈልጉት በሕገ ወጥ የሰው አየር ክልል ጥሰን እንድንገባ ነው ። እኛ ደግሞ የዚህ ዓይነቱ ድርጊት እንዳይፈጸም ማድረግ አለብን ። ስለዚህ ወደ ምሽግህ ተመልሰህ ና ” ብሎት ንግግሩን ለትንሽ ጊዜ ቆም ካደረገ በኋላ “ይህ ትዕዛዝ ነው ” አለው ።

ላስኮቭ ትዕዛዙን መቀበሉን አስታወቀ ።

ታልማን በኃይል ከተነፈሰ በኋላ ሌሎቹም እንዲመለሱ ትዕዛዝ አስተላለፈ ። በአሜሪካ ሳተላይት አማካይነት ኮንኮርዱ የት እንዳለ በመደረግ ላይ የነበረውን ጥረትና የአሜሪካ የስለላ መሣሪያዎች ጠቅ ላላ የሲናይ ምድርን ፎቶግራፍ ለማንሳት በአየር ላይ መሰማራታቸውን በዚህ አስተማማኝ ባልሆነ የራዲዮ መስመር ማስተላለፍ አልፈለገም። ምንም እንኳን በሳተላይትም ሆነ በሌላ መሣሪያ የሚወሰዱት ዘገባዎች እስኪመረመሩ ድረስ ጊዜ ቢወስዱም ባዶ ከመቅረት የተሻለ ነበር ።

ታልማን እስከ አሁን መሥራት የነበረበትን በማድረጉ ለጊዜው ደስ ብሎታል ። ቀጥሎም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለደረሰው ሁኔታና ሥራውንም የለቀቀ መሆኑን በስልክ ከነገረ በኋላ መልስ ሳይሰጠው ቴሌፎኑን ዘግቶና ከመቀመጫው ተነስቶ ምክትሉ ወደ ነበረው ወደ ጄኔራል ሁር ሔዶ ለትንሽ ጊዜ ተነጋገረ ።

ከዚህ በኋላ ባርኔጣውን አንስቶ ከሥራ መምሪያው ክፍል ሲወጣ እያንዳንዱ ሠራተኛ በፀጥታ ተመለከተው ።

* * *

ኮንኮርዱ ቀስ ብሎ እየበረረ በሲናይ ተራሮች ላይ ወጣ ። ቤከር በ150 ሜትር ከፍታ እንዲበር ሌየሩ እንደሚፈልግ አውቋል ። ነገር ግን በመሬቱ ወጣ ገባነት ምክንያት ኮንኮርዱ ወደ ላይና ወደታች

እያለ በሚያደርገው በረራ ተሳፋሪዎቹ ተሰቃይተዋል ። በዚህም ምክ ንያት ብዙዎቹ ታመዋል ። በፊት ለፊታቸው የሲናይ ተራራ ከፍታው ታያቸው ። ሴየሩ በተራራው ላይ በ50 ሜትር ከፍታ በረረ ። ቤከርም ትልቁን ኮንኮርድ በ50 እና በ100 ሜትር ከፍታ ላይ በከፍተኛ ችግር እንዲበር አደረገ ። ከችግሩ የተነሳ ከሴየሩ ከፍ ብሎ ለመብረር ስለ ሞከረ ሴየሩ በፍጥነት ከፍታውን አስተካክሎ ከፊት ለፊቱ ሆነ ። በተለይም አንድ ጊዜ ከጉብታ ጋር ሊላተም እጅግ ተቃርቦ ነበር ። ቤከር ባደረገው ጥረትና መፍጨርጨር ከአደጋ ድነዋል ።

" ወደ መሬት በጣም ተጠግተን ነበር " ብሎ ሔስ ሲናገር ድ ምፁ የመንቀጥቀጥ ምልክት ነበረበት ። " እንደምገምተው የፈለ ገው ዓይነት አስቸጋሪ ቢሆንም እየተሰቃየን እንድንከተለው ይፈል ጋል ። ምን ዓይነት ጠንካራና አስደናቂ አብራሪ እንደሆንክ ማወቅ አለበት ፤ ዴቪ " አለው ።

ቤከር ከግንባሩ ላይ ቀዝቃዛውን ላብ ጠረገ ። ሴየሩ የበረራ ከፍ ታውን እንደቀድሞው ካስተካከለ በኋላ ፍጥነቱን ቀነሰ። ቤከርም ከኋ ላው ተከተለው ። ሥራውን በትክክል ያላከናወነ አንድ መኰንን ለቅ ጣት ወዳልታወቀ ቦታ ሲወሰድ አንድ ታዛዥ የሆነ ልጅ ባልፈጸመ ውና በማያውቀው ወንጀል አብሮ እንዲሔድ የተደረገ ዓይነት ሆኖ ለሆስነር ተሰማው ። ውርደትም ሆኖ ታየው ። ሪሽ ያሰበው ካልተሳ ካለት በአየር ላይ እንዳለ ለመጋጨት ዝግጁ መሆኑን አውቋል ። በዚህ ምክንያት የቤከር እጆች ከፍርሃት ይልቅ በንዴት ኃይል ተን ቀጠቀጡ ።

* * *

የሆስነር ሰዎች የኮንኮርዱን የኋላ ክፍል እንዲለይ ብረት እየቀ ለጠ በተሠራው ግድግዳ ላይ ተለጥፎ የነበረውን ልባስ በሰንጢ መላጥ ጀመሩ ። ቀስ በቀስ በብረት የተሠራው ግድግዳ መታየት መጀመሩን ሆስነር ተመለከተ ። ሁኔታውን አጢኖ ሲመለከተው በዚያ በኩል ወደኋላ ክፍሉ ለመግባት የሚያስችል አንድም ፍንጭ አልነበረም ።

" የተሻለ ሃሣብ አላችሁ ?" ብሎ ሆስነር ጠየቃቸው ።

ናታን ብሪን የተባለው ወጣት በወለሉ ላይ ተጋድሞ ከሚሠራ በት ቀና በማለት "አደጋ የሚያስከትል የሚመስል ሃሣብ ቢኖርስ!" አለው ።

" እስቲ እንስማው ! "

" ከጥይቶቻችን ውስጥ ባሩድ አውጥተንና በብረቱ ግድግዳ ላይ ሠርስረን ቅርጽ በመሥራት በውስጡ ባሩዱን ካስቀመጥን በኋላ በኤ ሌክትሪክ በመጠቀም ብናፈነዳው በብረት የተሠራውን ግድግዳ መሻ

ንቆር እንችላለን ። በእጅ ባትሪ ብርሃን እየተጠቀምን በዚህ ቀዳዳ ውስጥ አንድ ለመሳብ የሚያስችል የልብስ መስቀያ በመስደድ ወደ ተጠመደው ቦምብ የተዘረጋውን ሽቦ መንጭቀን ማውጣት እንችላ ለን ” ብሎ ወጣቱ ሰው ነገራቸው ።

ሆስነር ወደ ሞሼ ካፕላን ዞሮ “ ካፕላን በእነዚህ ቀኖች እየቀጠ ርኩ ያለሁት የእዚህን ዓይነት ሰው ነው ? ” አለው ።

ብሪን ፊቱ ፍም መሰለ ። ቀጥሎም “ የዚህ ሃሣብ ስህተት ምን ድን ነው ? ” ብሎ ጠየቀ ።

“ ይህ አደገኛ ነው ። ለመሆኑ ባትሪ በመሆን ፈንታ ሽቦ ሊሆን ይችላል ሊያሰኝህ የቻለው ምንድን ነው ? ”

ብሪን ካሰበ በኋላ “ ለራዲዮኑ የሚያቀባብል በአውሮፕላኑ ውስጥ አንድ የኃይል ምንጭ መኖር አለበት ። በ01 ውስጥ የተጠመደውን ቦምብ ያፈነዳው ከአንድ ዓመት በፊት የተቀመጠ ባትሪ ሊሆን አይ ችልም ” አለው ።

ሆስነር በአዎንታ ራሱን በመነቅነቅ “ ሊሆን ይችላል ። ሽቦ ከሆነ ከማያቋርጥ ቮልቴጅ ጋር መገናኘት አለበት — ምናልባትም በጅራቱ ላይ ካለው የበረራ መብራት — ” አለው ። ለትንሽ ጊዜ ካሰበ በኋላ ወደ አውሮፕላኑ የበረራ ክፍል በፍጥነት ተመልሶ ሔደ ።

ሆስነር ሲገባ ቤከር ስለሰማ “ የመፍትሔ ሃሣብ ተገኘ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ ስማ የእዚህ የራዲዮ የኃይል ምንጭ በጅራቱ ላይ ያለው የበ ረራ መብራት ሊሆን ስለሚችል አጥፋው ” አለው ።

አባባሉ ቤከርን ከነከነው ። ሪሽ በጅራቱ ላይ ያለውን የበረራ መብራት እንዳለ እንዲተወው የነገረውን አስታወሰ ። ሁሉም አውሮ ፕላኖች አላቸው ። ግን ሪሽ ለምንድን ነው አጠንክሮ የነገረው ? “በ ዚያ ክፍል ውስጥ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚንቀሳቀሱ ሌሎች መሣሪ ያዎች አሉ ። ለመብረር የሚያገለግለኝን ብቻ በመተው የጅራቱን የበረራ ምልክት ሰጭ የሆነውን ኃይልም ሆነ ሌሎቹን ማቋረጥ እችላ ለሁ ” አለው ።

ካን “ እኔም ያሰብኩት እንደዚያው ዓይነት ነው ። የኃይሉ ምንጭ በጅራቱ ላይ ለበረራ ምልክት እንዲሆን የተሠራው መብራት መሆን አለበት ። በራዲዮ ተቆጣጣሪነት የሚፈነዳ ቦምብ በባትሪ የሚረዳ ሊ ሆን ይችላል — ባትሪውም የማያቋርጥ ኃይል በጅራቱ ውስጥ ካለው

ኃይል ስለሚያገኝ ይሞላል ። ባትሪው ለብዙ ዓመቶች እንኳን ቢቆመጥ ሞተር ባስነሳን ቁጥር ሙሉ በሙሉ ይሞላል ። እኔ መቼም ልሳሳት እችላለሁ ። በበኩሌ የድራቱን መብራት ማቋረጥ እችላለሁ ። እንፈነዳ ወይም እንፈነዳም ይሆናል ። ለመሞከር የሚፈልግ አለ ?" አላቸው ።

መልስ የሰጠ አንድም ሰው አልነበረም ።

ሆስነር ተቀምጦ ሲጋራውን አቀጣጠለ ። ለአፍታ ተሰምቶት የነበረው ደስታ እንደ ጉም በነነ ። "ምናልባት በወለሉ ላይ የተነጠፈውንና በጣሪያው ላይ ያለውን ብረት ማንሳት እንችላለን። በዕቃ ማስቀመጫው ክፍል ወደ ጅራቱ ለመሔድ በብረት የተዘጋውን ክፍል በመንደል ወደ ጅራቱ ለመግባት ይቀል ይሆናል" ብሎ ለቤከር ነገረው ።

ቤከር ይህን ሲሰማ ራሱን በአሉታ ነቀነቀ ። ማንም ሰው ቢሆን በአውሮፕላኑ ውስጥ እየቆፈረም ሆነ እየቆራረጠ ቀዳዳ እንዲሠራ አልፈለገም ። "እንደምታውቀው የጉዞ ዕቃ መያዣው ክፍል ከብደቱ ጭምር ተመዛዝኖ እጅግ በጣም በጥንቃቄ የተሠራ ነው ። የኤሌክትሪኩም ሽቦዎች ብዙና ውስብስብ ናቸው ። ስለዚህ የሚባለው ሁሉ አደጋ የሚያስከትል ስለሆነ ማንም ሰው ቢሆን በዚህ ዓይነት አውሮፕላኑን እንዲነካካ አልፈልግም ። በድፍረት አደጋ ሊያስከትል የሚችል ነገር እንዲሞከርም አልሻም" አለው ።

ሆስነር ራሱን አስገድዶ ፈገግታ ካሳየው በኋላ "እንደምገምተው የጥይት ባሩድ አጠራቅመን ጅራቱን ከሌላው ጋር የሚከፍለውን የብረት ግድግዳ አፈንድተን ቀዳዳ መሥራት ያለንን ሃሣብ አትቀበለውም ማለት ነው ?" አለው ።

ብዙ ጭንቀት ቢኖርበትም ነገሩ ቤከርን አሳቀው ።

"አዝናለሁ" አለው ቤከር ። ሆስነር የእዚህን ዓይነት ውርደት ከሚደርስበት ሞትን እንደሚመርጥና የራሱን ዘዴ ፈጥሮ ከዚህ ችግር ካልወጣ የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት አድርጎ ራሱን እንደሚቆጥር ቤከር ቢያውቅም አውሮፕላኑን እየነዳደሉ በግምት ሊሠራ የታቀደውን ሊያምንበት አልቻለም ።

"ሆስነር ለመሥራት እየሞከርክ ስለአለኸው አመሰግናለሁ ። ነገር ግን የአውሮፕላኑ ካፒቴን እኔ ስለሆንኩ የአውሮፕላኑንም ሆነ በውስጡ ያሉትን ተሳፋሪዎች ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል መስሎ የሚታየኝን ሃሣብ ሁሉ ድምጽን በድምጽ በመሻር ጭምር የመከል

ከል መብት አለኝ ። በአየር ላይ እስከ አለን ድረስ አዛዡ እኔ ነኝ ። አንተ ወይም በርግ ወይም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አይደላችሁም ፤ እኔ እንጂ — ” ከአለው በኋላ በትከሻው ላይ ራሱን ዘወር አድርጐ በመመልከት “ ስማ ያዕቆብ ፤ ምን እያሰብክ እንደሆን አውቃለሁ ። ነገር ግን ነገሩን በእርጋታ ያዘው ። አሁን የሚቀረን ሁለት ሰዓት የበረራ ጊዜ ነው ። እስከዚያ የሚሆነውን እንይ ” አለው ።

ሆስነር ራሱን ነቅንቆ “ እሺ ፤ እንዳልክ ” ብሎት ከአብራሪው ክፍል ወጥቶ ሔደ ።

— 9 —

ኮንኮርዱ በሲናይ ተራራ ላይ አልፎ ወደ ቀይ ባሕር በማምራት ሌየሩ ወደ ግራ ታጥፎ ወደ ሳውዲ አረቢያ ሲሔድ ተከትሎ በረረ ። ቤከር ወዴት እንደሚሔድ ለማወቅ ጉጉት ይዞታል ። የጉዞአቸው እርቀት ምን ያህል እንደሆነ ማወቁ አስፈላጊነቱ እየቀነሰ መጥቷል ።

ኮንኮርዱ አፍንጫው ዝቅ ብሎ ፣ ጅራቱና ክንፎቹ ወደታች ቀንገርብበው ሲመለከቱት ፈለጉ ጠፍቶበት በሥሩ ባለው ባሕር ላይ ለማረፍ የሚፈልግ የባዘነ ወፍ መሰሏል ። ነገር ግን በነበረው በቂ ምክንያት የተነሳ ለማረፍ አልቻለም። ቤከር በቀይ ባሕር ላይ የነበረው ነጭ አረፋ ተመልክቶ በሃሣብ ተመሰጠ ።

“ ወደ የብስ እየመጣን ነው ዴቪ ። ”

በሳውዲ አረቢያ የባሕር ዳርቻ ደረሱ ። መሬቱ እስከሚታየው ድረስ ሜዳ ስለነበረ የደህንነት ትንፋሽ ተነፈሰ ። “ ከአሁን በኋላ መጥፎ አይሆንም ። ”

ሔስ ወደ እርሱ ዞሮ “ በዚያ ዓይነት ልንመለከተው የሚገባን አንዱ መንገድ ነው ። ለትንሽ ጊዜ በማብረር እንዳግዝህ ትፈልጋለህ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ቤከር ተመለከተው ። ኮንኮርዱን በዚህ ዓይነት ቦታና ሁኔታ ላይ ሔስ ሊያበረው ይችላል ወይ የሚል ሃሣብ አደረበት ። በግልጽ “ልታበረው ትችላለህ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ እንኳን ይህን የመሰለውን ኮንኮርድ ይቅርና አሮጌውም ቢመጣ አበረዋለሁ ። ”

ቤከር ፈገግታ አሳይቶት ከመቆጣጠሪያ መሣሪያዎቹ ላይ እጁን አንስቶ ከኪሱ ውስጥ ሲጋራ በረበረ ። ጥሩም ነገር ተሰማው ። አንድ አብራሪ መንፈሱ እንዲረበሽ የሚያደርገው ምክንያት ካለ በሲናይ

ተራራ ላይ የተደረገው በረራ መሆን አለበት ። ከአሁን በኋላ የፈለገዉ ቢሆንም ይህ የአደረገው በረራ የመጨረሻው ይሆናል ብሎ ያሰበውና እጅግ በጣም ጥሩ ነው ብሎ የተቀበለውም በመሆኑ ደስታ ተሰምቶ ታል ።

ሌየሩ ፍጥነቱን በመጨመር 800 ኪሎ ሜትር በሰዓት መብረር ጀምሯል ። ሔስ በ150 ሜትር ከፍታ ሌየሩን ተከትሎ ለመሔድ ብዙ ጥረት እያደረገ ነበር ። ቤከር በፊት ለፊቱ የምድረ በዳ ዘላን አረቦች ግመሎች ጋልበው ሲሔዱ አያቸው ። በመጥለቅ ላይ ያለችው ጀን በር የትልቁ ኮንኮርድ ጥላ በአረቦቹ ላይ እንዲያርፍ አድርጋዋለች ። አውሮፕላኖቹ ሲያልፉ ግመሎቹ ደንብረው እንደመዝለልና እንደመ ሯሯጥ አሉ ። ቤከር ሲጋራውን አነሳ ። አሁን በመብረር ላይ ያሉበት ሜዳ ስለሆነ ችግር የሚያጋጥመው አልመሰለውም ። ይሁን እንጂ በ150 ሜትር ከፍታ ላይ ሲበሩ ምንም ዓይነት ጉብታ ቢያጋጥም ለዕር ምት የሚሆን ዕድል እንኳን ሳይኖራቸው ከፍተኛ አደጋ ላይ ሊወድቁ ይችላሉ ።

ፒተር የነዳጁን መለኪያ ተመልክቶ አንድ ሰዓት ከአምሳ ደቂ ቃዎች ለማብረር የሚያስችል ነዳጅ እንደሚኖራቸው ተረዳ ።

ዶብኪን መጥቶ እጁን በቤከር ትከሻ ላይ በማስቀመጥ “ እን ዴት ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ ደህና ነው ፤ የተሻለ ውጥን አላችሁ ? ”

ዶብኪን ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ በዚያኛው ክፍል ትንሽ ስብ ሰባ አድርገናል ” አለው ።

“ እና ? ”

“ መልካም — ብልህ ሰዎች ናቸው ወደሚለው ውሳኔ ደርሰናል። በመጀመሪያ ሌሎች አረቦች እንደሚያደርጉት የፖለቲካ ጉራ አልነ ዙም ። ምናልባት ፍልስጥኤማውያን ይሆናሉ ከማለት በስተቀር በት ክክል እነማን እንደሆኑ እንኳን ለማወቅ አልቻልንም ። ሆስነር የሪ ሽን ድምጽ ባያውቀው ኖሮ ማንነታቸውን ለማወቅ ችግር ነበር ። የጸ ጥታ ሰዎቻችን ሥራቸውን እንዳይጀምሩ ያገዳቸው ይህ ሁሉ ችግር ተሰባስቦ ነው ። ”

“ ጥሩ አይደለም ” አለው ቤከር ።

“ ፈጽሞ ጥሩ አይደለም ” በማለት ዶብኪን ከተስማማ በኋላ “ በተጨማሪም ራዲዮናችን መልዕክት እንዳያስተላልፍ በድምጽ ማዕበል ስለመቱት የምንሰማው ኳኳታና ጫጫታ ብቻ ሆነ ። ይህም

ማለት ወደ አልታወቀ ቦታ ለመውሰድ ነው ። በአሁኑ ጊዜ በአ ንድ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ በሺህ የሚቆጠሩ ጋዜጠኞች አይሰበ ሰቡም ። በኢንቴቤ እንደተደረገው ከጠላት ለማዳን ኃይል አይኖርም። ምክንያቱም የት እንዳለን አንድም የሚያውቅ ሰው የለም ። ከማንም ሰው ጋር ግንኙነት ሳናደርግ በመያዣ ልንቆይ ነው ። ”

ቤከር ተመሳሳይ ሃሳብ አድርቦታል ። በበረሃ ውስጥ አውሮፕ ላኑን ለማሳረፍ ጥርጣሬ አድርቦበት ነበር ። አሁን ግን እርግጠኛ ሆነ ።

ዶብኪን የቤከርን ሃሳብ የሚያነብ መሰለ ። ኮንኮርዱን በበረሃ ውስጥ ያሳርፈዋል የሚል ጥርጣሬ አደረበት ። “ በየትኛውም ቦታ ልታሳርፈው ትችላለህ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ በየትኛውም ቦታ ላሳርፈው እችላለሁ ። ችግር አይኖርም ፤ አይዞህ ፤ ስለዚህ ብዙ አትጨነቅ ” አለው ።

“ ላለመጨነቅ እሞክራለሁ ። ”

* * *

ሆስነር በሚሪያም በርንስቴይን አጠገብ ተቀመጠ ። ለትንሽ ጊዜ በእርጋታ ተነጋገሩ ። የአሳላፊዎቹ አለቃ ዳንኤል ጃኮቢ ተሳፋሪ ዎቹ ቢፈልጉም ባይፈልጉም ምግብና መጠጥ እንዲቀርብላቸው አዘዘ። ሆስነር ጥንድ ውስኪ አዘዘ ። በብርጭቆ የመጣለትን ውስኪ እየነቀ ነቀ “ ነገሩ ሁሉ እንደዚህ ይሆናል ብየ አላሰብኩም ነበር ” አላት ።

ሚሪያም በርንስቴይን ከእርሱ ውስኪ ፉት ብላ “ ይህን ለማድ ረግ ሌላ መንገድ መፈለግ ነበረባቸው ” አለችው ።

“ በየትኛውም መንገድ ቢጠቀሙ ኃላፊነት ነበረብኝ ። ”

“ ስለቴዲ . . . ጄኔራል ላስኮቭ አስባለሁ ። በዚህ ዓይነት ወጥ መድ ውስጥ እነእርሱም ገብተዋል ። እኔ ባልናገር ኖሮ እነእርሱ በተ ለየ መንገድ ተቃውሞአቸውን ይናገሩ እንደነበረ አውቃለሁ . . . ”

“እነዚህ የባለጌ ልጆች ለምን እንደዚህ እንዳደረጉ ላምን አልቻ ልኩም ” ብሎ ነገራት ።

“ ያዕቆብ ፤ ሪሽ አንተን እንደሚያውቅህና እንደ አስፈራራህም ሰማሁ ። ”

“ ያን የውሻ ልጅ ሳገኝ እገድለዋለሁ ። ”

“ አንተን እንደሚገድልህ በራዲዮ ተናገረ እንዴ ? ”

“ ወሬ አትስሚ ፤ ሁሉም ነገር ወደፊት ይታያል ። ”

እጅዋን በክንዱ ላይ አድርጋ “ ወደ አንተ ጋር እንድመጣ . . . አንድ ጊዜ የጠየከኝን ታስታውሳለህ . . . ”

ሆስነር ስቆ “ አሁን አንዳንድ ነገሮች ባትናገሪ ይሻላል ፤ ቴል አቪቭ በምንደርስበት ጊዜ እንዳይቆጭሽ ። በኋላ ልጠይቅሽ እችላለሁ ” አላት ።

ፈገግ ብላ “ በትክክል አላውቅህም ነበር ። ሁልጊዜም አደንቅሃለሁ . . . ግን ሰዎችን ታስፈራለህ ” አለችው ።

“ አሁን ምንም አይነት ኑዛዜ መስማት አልፈልግም ። ለዚህ ዓይነቱ ውይይት ጊዜ የለኝም ” አላት ።

ሚሪያም “ እሺ ” አለችው ።

ስለሌሎች ጉዳዮች ሲነጋገሩ ራት ቀረበላቸው ። ነገር ግን ሁለቱም መብላት አልቻሉም ።

* * *

አብደል ማጂድ ጃባሪ በአረብኛ ለኢብራሂም አሊ አሪፍ “ ይህ እጅግ በጣም አስከፊና አሳዛኝ የሆነ ድርጊት ነው ” አለው ።

አሪፍ እየበላ ቸኮል ባለ አነጋገር “ በአሁኑ ወቅት ሀፍረት ይሰማኛል ። የእኔ ሁኔታ በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ እንደተጣለው ዳንኤል ዓይነት ሆኖ ተሰማኝ ” አለው ።

ጃባሪ “ ወዳጄ ፣ ስለራስህ ችግር ብቻ ሁልጊዜ አታስብ ። ከአረቦች ጋር ስምምነት ለመፍጠር ሲሉ ክብራቸውንና ሥራቸውን አደጋ ላይ ለጣሉት አይሁዶች በጣም አዝናለሁ ” አለው ሲጋራውን እያቀጣጠለ ።

“ አሁንም በግሌ ጥሩ ሁኔታ አይታየኝም ። ደም ለማፍሰስ በሚደረገው ውንጀላ አላምንም ። ውንጀላ የአይሁዶች ስሜታዊ አመለካከት ነው ” ብሎ ወደ ጃባሪ ከተመለከተ በኋላ አንድ ጉርሻ እንኳን ወደ አልተነሳለት የጃባሪ ምግብ ተመልክቶ “ ብበላው ቅር ይልሃል ? ” ካለ በኋላ አንስቶ በራሱ ሣህን ላይ አስቀመጠው ።

ጃባሪ ከቀረበለት አረቄ ፉት አለ ። ቀጥሎም ወደ ሴየሩ እያመለከተ “ ለማንኛውም የአንበሶቹ ጉድጓድ ያ ነው ። እነዚህ የአገራችን ሰዎች ናቸው ። በተንኮል ዓይን ማየት የለብህም ። እነዚህ አብረን ያለናቸው ሰዎች የሚያጋጥማቸውን ጥሩም ሆነ መጥፎ ዕድል እኛም እንደምንካፈል አትጠራጠር ” አለው ።

አሪፍ በአፉ ውስጥ ያለውን ምግብ እያላመጠ “ በጣም ዕድለኛ መሆን አለብን ወዳጄ ፤ በመጨረሻ ላይ ቢለቀቁም ለራሳቸው ጉዳይ

ሲ.ት እንደሚንከባከቡን ጥሩ አድርገህ ታውቃለህ ። ይህም የአንበሳ መኖሪያ ጉድጓድ ፤ ያም የአንበሳ መኖሪያ ጉድጓድ ነው ። እኛ አገር ፡ ሕዝብና መጠለያ የሌለን ሰዎች ነን ። እኛ ዕድለቢሶችና ለማንኛውም አደጋ የተጋለጥን ነን ። ተጨማሪ ምግብ እፈልጋለሁ ፤ አሳላፊ ” በማለት በሆዱ ውስጥ ደብቆ የያዘውን ዘከዝኮ ነገረው ።

ሌየሩ ወደ ሰሜን አቀጣጫ ስለዞረ ኮንኮርዱም ተከተለው ። ሳው ዲ አረቢያን ለቀው ወደ ኢራቅ በረሩ ። ጀንበርዋ እያሽቆለቆለች ስለ ነበረች ተራሮች ጥላቸውን መጣል ጀምረዋል ።

ቤከር ምሽቱ እየተቃረበ በመምጣቱ በጣም ተደናግጦ “ ከበ ረራ ሰዓታችን ምን ያህል ይቀረናል ? ” ብሎ ጠየቀ ።

ካን “ ሠላሳ ደቂቃ አለን ” ብሎ ነገረው ።

ቤከርን ካሳሰቡት ነገሮች ውስጥ አንዱ በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ትክክለኛው የፀሐይ መጥለቅ አለመታወቁ ነበር። ከአንድ ደቂቃ በፊት ፀሐይ የነበረው በሚቀጥለው ደቂቃ በድንገት ይጨልማል ። የተስተካከለ የአየር ማረፊያ በሌለበት ሜዳ ላይ በጨለማ ይቅርና በቀን እንኳን ለማረፍ ችግር ነው ። ጨለማ ከሆነ ደግሞ የባሰ አደገኛ ሊሆን ይችላል ። “ ለመሆኑ የትኛው የሚቀድም ይመስልሃል ፤ ፒተር ? ”

ምን ማለቱ እንደሆነ ካን ገብቶታል ። ጊዜ የሚያሳየውን ካርታ ዘርግቶ እየተመለከተ “ በዚህ አካባቢ ፀሐይ የምትጠልቀው 12 ሰዓት ከ16 ደቂቃ ሲሆን ፤ ከዚያ በኋላ የብርሃኑ ውጋጋን ሳይጠፋ ለ5 ደቂቃ ይቆያል ። አሁን 12 ሰዓት ከ01 ደቂቃ ነው ። በአሁኑ ጊዜ 20 ደቂቃ የብርሃን ጊዜና 29 ደቂቃ ያህል የሚያበር ነዳጅ አለን ” ብሎ ነገረው ።

ቤከር ከፊት ለፊቱ ጨለማ እየወረሰው ባለው አድማስ አናት ላይ ጨረቃዋን አየ ። ጨለማው እየጨመረ በመምጣቱ ኮከቦች አልፈው አልፈው መታየት ጀምረዋል ። በሰሜን በኩል በመስታወቱ መካከል ሲመለከት የሰሜን ኮከብ በመውጣት ላይ እንደነበረ አየ። ከአድማሶቹ በታች ያለው መሬት የወይን ጠጅ ከሚመስለው ብርሃን ወደ ጨለማ ነት እየተዛወረ ነበር ።

ሔስ “ ተመልከት ” አለው ።

በፊት መስታወቱ ሲመለከት ቦታው ተዳፋት ሆኖ አረንጓዴ የለ በሰ መሬት አየ ። ብዙ የተምር ዛፎች ባሉበት መካከል የሚያልፍ ወንዝ አየ ። እንደዚሁም ከዚህኛው ወንዝ ባሻገር ሌላ ወንዝ አየ ። የጤግሮ ስና የኤፍራጥስ ወንዞች ናቸው ። በጤግሮስ ወንዝ ባሻገር ከአንድ ሺህ ሜትር በላይ ከፍታ ያላቸው የኢራን ተራሮች ታዩት ። የከፍታ ማሳያ

መለኪያውን ሲመለከት ከባሕር በላይ ከፍታው 180 ሜትር ነበር ። ሌየሩ እንደቀድሞው ወደ 150 ሜትር ዝቅ ብሎ ለመብረር ምንም ምልክት አላሳየም

" ይህ የመጨረሻ በረራችን መሆን አለበት " አለ ሔስ ።

ቤከር በወንዞቹ መካከል የነበረውን መሬት አቆልቁሎ ተመለከተ ። ለምለምዋና የሥልጣኔ ምንጭ የሆነችው ሜሶፖታሚያ ነበረች። ያን ሁሉ በረሃና አሸዋማ መሬት አልፎ ይህን በማየቱ እፎይታ ተሰማው ። ምናልባትም በሰሜን በኩል ወደ ባግዳድ እንበር ይሆናል ብሎ አሰበ ። በሃሳቡ ላስኮቭ የተኮሰው ሚሳይል ጭስ ሲጥመለመል ታየው። ሲጋራውን አጥፍቶና ወደ ሔስ ዞሮ " ከዚህ አወጣዋለሁ " አለው ።

ሌየሩ በስፋት ክብ መዞር ጀመረ ። ቤከርም ተከተለው ። ሌየሩ ዝቅ እያለ በመሔዱ ሚዛኑን መጠበቅ አልቻለም ። በዚህ ጊዜ ቤከር ወደ ባግዳድ እንደማይሔዱ ለማወቅ ቻለ ።

ሔስ የመታጠቂያና የማጨስ መብራት ምልክት የሚሰጠውን መሣሪያ ነካ ። የድምጽ ማጉሊያውን አንስቶ " የምናርፍበት ቦታ እየተቃረበ ስለሆነ በያላችሁበት ተቀመጡ ፤ ቀበቶአችሁን እሰሩ ፤ ሲጋራ ማጤስ አቁሙ " አላቸው ።

" በኤል አል አየር መንገድ በመጓዛችሁ እናመሰግናለን ብለህ ንገራቸው " አለው ቤከር ።

" አባባልህ ቀልድ ሳይሆን ትክክለኛ ነው " አለው ካን ።

" ነዳጃችን እንዴት ነው ? " ብሎ ቤከር ጠየቀው ።

" ካን " ምንም ያህል አልቀረንም " ብሎ ካቅማማ በኋላ "ሁለት ሺህ ኪሎ ግራም ሊኖረን ይችላል " አለው ።

ቤከር ራሱን ነቅንቆ " ምንም ነገር ሳያጋጥመን ከበረርን አምስት ደቂቃ የበረራ ጊዜ ይኖረናል ማለት ነው ።" ከአሁን ጀምሮ ለማረፍ ዝቅ እያለ ከሔደ በአምስት ደቂቃ ውስጥ ያለአንዳች ችግር በደህና ለማረፍ አቅዷል ። ለማረፍ ሞተሮቹ አንድ በአንድ ብልጭታ እየሰጡ ዝቅ እያሉ ሲወርዱና መሬት ሲነኩ አስፈሪ ድምጻቸውን ለመስማት ይጠብቃል ።

ሌየሩ መስመሩን ቀይሮ ወደ ሰሜን በመዞር አቆልቁሎ መሔድ ጀመረ ። ራቅ ብሎ ወደ ሰሜንና ደቡብ የተዘረጋ ቀጥ ያለ መንገድ ቤከር አየ ። " እንደማስበው ያ የምናርፍበት ሜዳ ነው " አለው ። እርሱም ዞሮ ሌየሩን ተከተለ ።

ሕስ ለማረፍ የሚያስችለውን ማርሽ አስገብቶ “ ለእኔ በተሻለ ይታየኛል ” አለው ።

ፀሐይዋ በመጥለቅዋ ምክንያት ጊዜው ድንግዝግዝ ስላለ በግ ልጽ አይታይም ነበር ። ቤከር ያልተስተካከለ ሜዳና ቁጥቋጦዎች አየ ። አሁን ለማረፍ እየተቃረቡ መጡ ።

ዶብኪንና ሆስነር ሮጠው ወደ ቤከር ክፍል ገቡ ። ዶብኪን ጮኾ አንድ ነገር ተናገረው ።

ቤከር በቁጣ “ ወደ መቀመጫችሁ ተመለሱ ፤ ለማረፍ እየሞከ ርኩ ነው ” አላቸው ።

እነእርሱ ግን ከቆሙበት አልተላወሱም ። “ የድምጽ ምርጫ አካሒደናል ” አለው ሆስነር ።

“ ይህ የእስራኤል ምክር ቤት አይደለም ፤ ዝም በል ” አለው ቤከር ።

አቆልቁሎ ሲመለከት በሜዳው ግራና ቀኝ መጠነኛ ብርሃን የሚ ሰጡ አራት ጥንድ መብራቶች ነበሩ። አንድ ሰው በማረፊያ መጀመሪያ ው ላይ ቆሞ ኃይለኛ መብራት ወደ ላይ ይዞ ያወዛውዛል ። ሌየሩ በሜ ዳው ላይ ለማረፍ በጣም ዝቅ ብሎ ክንፉን እያርገበገበ ሲሔድ ቤከር ተመለከተው ። ቤከር ጥንካሬውን ለመጨመር ራሱን ወዲያና ወዲህ አነቃነቀ ። መሣሪያዎቹንም በችኮላ ተመለከተ ። በመስታወቱ መካ ከል ወደ ውጭ ሲያይ መብራቶቹ ዓይኖቹን ስለወጉት ዓይኖቹን አሻሸ።

ሆስነር በቤከር ኋላ ቆሞ “ ድምጽ አሰጣጡ ተቀባይነት ያገኘው ሙሉ በሙሉ ነው ። ይህ ባይሆን ግን እኛም አንቀበለውም ነበር ” አለው ።

ቤከር አንድ እጁን በመሪው ላይ ሌላውን እጁን ደግሞ በሌላው መሣሪያ ላይ አድርጎ በመብራቶቹ መካከል ለማረፍ ያስተካክላል ። ዓይኖቹን በሌየሩ ጅራት ላይ በነበሩት መብራቶች ላይ ተክሏል ። “የ ምን ድምጽ መስጠት ነው ? ምን መአት እያወራህ ነው ? በዚህ አር ፌበት በማላውቅ መጥፎ ሜዳ ላይ ለማረፍ እየሞከርኩ ነው ። ምንድን ነው የምትፈልገው ? ” አለው ።

ሆስነር ፈጠን ባለ አነጋገር “ በዚህ ማረፉ ለእኛ ጥሩ አይሆንም ። ቦምቡም በመሬት ላይ ጥሩ አይደለም ፤ ቤከር ። እጅግ ቢበዛ ሊያደ ርግ የሚችለው ጅራቱን መቀርጠፍ ነው ” ብሎ ነገረው ። ቤከር ሌየሩ መሬቱን እየነካ ብድግ ቁጭ ሲል አየው ። ኮንኮርዱን ለማሳረፍ እየተ ቃረበ መጥቷል ።

" በመሬት ላይ ለመዋጋት በምርጫ ወስነናል ። የእኔ ሰዎች ጥቂት መሣሪያዎች አሏቸው ። ስለዚህ ከዚህ እልፍ ብለህ በሌላ ቦታ ልታሳርፈን ትችላለህ ? " ብሎ ሆስነር እየጮኸ ነገረው ።

" ታዲያ ለምን ከሁለት ደቂቃ በፊት አልነገርከኝም ፤ አይ አምላኬ ! " በማለት መልሶ ጮኸበት ። የኮንኮርዱ ጐማዎች መሬት ሲነኩ ተሰማው ። መብራት ያበሩ መኪናዎችና መብራት በእጃቸው የያዙ ሰዎች በዳርና በዳር ቆመዋል ። ሜዳው በጣም መጥፎ በመሆኑ አውሮፕላኑ በአደገኛ ሁኔታ ይነጥር ነበር ። አኮብኩቦ ለመቆም ሁለት ኪሎ ሜትር ይቀረዋል ። በዚያም የፊት መብራቶች ያበሩ መኪናዎች ነበሩ። በግራው በኩል ትልቅ ተራራ አለ ። ይህ ተራራ የኤፍራጥስን ወንዝ አቀልቁሎ ለማየት የሚያስችል ነው ። ሆስነር አንድ ነገር ጮኾ ነገረው ። በዚህ ጊዜ ቤከር ያለማወላወል ፈጣን ውሳኔ ወሰደ ። የአውሮፕላኑ ፍጥነት እንዲጨምር አድርጐ እንደገና አስነሳው ። የመቆጣጠሪያ መሣሪያዎቹ ሁሉ እንዲሠሩ ስላደረጋቸው ኮንኮርዱ አጓርቶ ወደግራ በመዞር ወደ ሌየሩ አመራ ።

ሌየሩ በመንገዱ በስተግራ በኩል መኪናዎች ባሉበት አጠገብ ቆሟል ። አህመድ ሪሽ በሌየሩ ክንፍ አጠገብ ሆኖ ይመለከት ስለነበረ በመጀመሪያ ኮንኮርዱ በኃይል ስለናረ ከመንገዱ ወጥቶ የሚሔድ መስሎ ታየው ። ቀጥሎም የአውሮፕላኑ ተርገብጋቢዎች አቀማመጣቸውን አስታወሰ ። ሮጦ ወደ ሌየሩ በመግባት ራዲዮኑን ከፍቶ "ቁም! በረራህን አቁም ! " ብሎ ጮኸ ። ኮንኮርዱ ከመሬት ትንሽ ከፍ ብሎ ወደ እርሱ በሚመጣበት ጊዜ ሊያፈነዳ የሚችለውን የራዲዮ ማስተላለፊያ በእጁ ያዘ ። የኮንኮርዱ የማረፊያ ጐማ መሬቱን ሊነካ የሚቀረው ትንሽ ነበር ። የኮንኮርዱ የአየር ፍጥነት 180 ማይል ደርሷል ።

ቤከር ለመብረር ያነጣጠረው በግራው በኩል ከፍ እያለ ወደ ሚሔደው ተራራ ነው ። የራዲዮኑ ጫጫታ ስለቆመ የሪሽ ጩኸት ይሰማው ነበር ። በእርግጥ ሌየሩ በፊት ለፊቱ 50 ሜትር እርቀት ላይ ታይቶታል ። ከመቅጽበት ባደረበት ንዴት በሌየሩ ላይ ሊነዳበት አሰበ ። ግን ሪሽን መግደሉ ለችግሩ መፍትሔ እንደሌለውና በዚያ ፍጥነቱ ሌየሩን ቢመታው እነእርሱም ጭምር እንደሚያልቁ ተገነዘበ ። ስለዚህ የሪሽን ሌየር መግጨት አልፈለገም ።

በአሁኑ ጊዜ ሞተሩን ማቀዝቀዙም ሆነ በኃይል እንዲበር ማድረጉ አስቸጋሪ ነበር ። ኮንኮርዱ ከፍ ብሎ እንዲበር ከተደረገ በጅራቱ ውስጥ ያለው ፈንጂ ስለሚፈነዳ ሁሉም ይሞታሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ በዚያ ደረጃ ላይ እያለ በኃይል ነዳጅ ቢሰጥ በሞተሮቹ ላይ የእሳት ቃጠሎ ስለሚነሳ ሁሉም ያልቃሉ ። ስለዚህ ሌየሩን በማይነካ ከፍታ ላይ

ሆኖ ዝቅ ብሎ መብረር ነበረበት ። ኮንኮርዱ በሌየሩ ላይ ሲበር ቤከር ትንፋሹን አምቆ ያዘ ። የኮንኮርዱ ጐማ ሌየሩን ለትንሽ ሳተው ። ከፍ ያለ አሮጌ ግድግዳ ከፊት ለፊቱ ስለታየው መሪውን ቀስ በቀስ በማስ ተካከል ኮንኮርዱ ከፊቱ ትንሽ ቀና እንዲል አደረገው ። በትልቁ አሮጌ ግድግዳ ላይ ሲያልፍ ጐማው የነካው መሆኑን በመንገጫገጩ ቤከር ለማወቅ ችሏል ። አሁንም ባደረገው ጥረት የኮንኮርዱ አፍንጫ ከፍ እያለ በመምጣት ወደ ተራራው አመራ ። ቤከር ወደ ወንዙ ቢሔድ በተደሰተ ነበር ። ግን ሪሽ ለማፈንዳት የቀረው ጊዜ ሁለት ሴኮንዶች ብቻ ስለነበረ ወደዚያ መሔድ አልፈለገም ።

ኮንኮርዱ በላዩ ላይ ሲበር ሌየሩ በኃይል ነጥሮ ተንገጫገጨ ። ፍን ጣሪዎቹ ሌየሩን ፣ መኪናዎቹንና ሰዎቹን መታቸው ። የተነሳው ኃይ ለኛ አቧራም ዓይኖቻቸውን ሸፈናቸው ። ሪሽ እንደምንም ተንደፋድፎ በዳበሳ ማፈንዳት የሚችለውን የራዲዮኑን ክር ያዘ ። ቤከር አሁንም ከኮንኮርዱ ጋር በመታገል ላይ እንዳለ የሪሽ ጩኸት ተሰማው ። የአው ሮፕላኑ አፍንጫ ቀና ሲል የማረፊያ ጐማው ተራራውን ሲነካ ተሰ ማው ። መናርም ጀመረ ። ከፊቱም ዝቅ ስላለ የፊት ጐማው መሬ ቱን ሲነካ በኃይል ስለናረ በቤከር በስተጀርባ የቆሙት ሰዎች በወለሉ ላይ ተነጠፉ ። ከጐማዎቹ አብዛኞቹ እየተቀነጠሱ ተሽከረከሩ ። ቀጥ ሎም የአውሮፕላኑ ጅራት ፈነዳ ።

ቤከር አራቱንም ሞተሮች አጠፋ ። ሔስ በበኩሉ የእሳት ማጥ ፊያ መሣሪያውን በሥራ ላይ አዋለ ። ካን ማናቸውንም የአውሮፕላኑን መገናኛዎች ዘጋ ። አውሮፕላኑ በወደቀበት ጊዜ አስደንጋጭ ድምጽ ነበረው ። የሞተሮቹ ድምጽ ስለቆመ የሚሰማው እየተሽከረከሩ የሚ ንከባለሉት ጐማዎች ድምጽ ነበር ።

ቤከር የአውሮፕላኑ ጅራት ከመፈንዳቱ በፊት ብዙ ዕቃዎች እርስ በእርሳቸው ሲላተሙ ሰምቷል ። በቁጥር 11 የነዳጅ መያዣ ውስጥ የነ ዳጅ መቀጣጠል እንዳለ ስለአወቀ ከፍተኛ ጥፋት እንደሚያስከትል ገም ቷል ። በዚህ ምክንያት ሌላ የነዳጅ መያዣ ቢፈነዳ ኮንኮርዱን ጨርሶ ድምጥማጡን ያጠፋዋል ።

በድንገት የአውሮፕላኑ የፊት ጐማ ስለታጠፈ እያንዳንዱ ሰው ወደፊት ተገፈተረ ። አፍንጫው መሬቱን ስለአረሰው ሰፊ ቦይ ተፈ ጠረ ። ስብርባሪዎቹ እየተፈናጠሩ መስታዎቱን ሰነጣጠቁት ። የመስ ታወቱ ስብርባሪዎች የቤከርን እጆችና ፊት ገሸለጧቸው ። በመጨረ ሻም ኮንኮርዱ ተረጋግቶ ቆመ ።

ቤከር ቀና ብሎ እየተመለከተ "ሁላችሁም ደህና ናችሁ ?" ብሎ ጠየቃቸው ። በግራው በኩል ሲመለከት ሙሴ ሔስ ተጋድሞ ደም ከጭንቅላቱ ላይ ሲፈስ እየው ። ሔስ በተጋደመበት ፊት ለፊት ትልቅ ቀዳዳ አየ ።

" መዋጋት ትፈልጉ እንደሆን ከአውሮፕላኑ ውጡ " ብሎ ቤከር ጮኾ ነገራቸው ።

ፒተር ካን ተነስቶ " ውጡ ፤ የአውሮፕላኑ ሠራተኞች በአስቸኳይ የመውጫ በሮቹን ከፈቱ " በማለት ጮኾ ነገራቸው ።

ያአኮቭ ሌይበር ቀደም አድርጐ ቀበቶውን ፈቶ ስለነበረ ወደ በሩ ሮጦ የመዝጊያውን እጀታ ጠምዝዞ ከፈተው። የሆስነር ስድስት ሰዎች በመጀመሪያ ወጡ ። ሁለት አስተናጋጆች ተሳፋሪዎቹን እየመሩ እንዲወጡ አደረጉ ። የሴት አስተናጋጆች ደግሞ በክንፎቹ አጠገብ ያሉትን ሁለት መዝጊያዎች ከፍተው እንዲወጡ አደረጉ ። ሌሎችም እየዘለሉ ወረዱ ።

ሆስነር ከበረራ ክፍሉ ዘሎ ከወጣ በኋላ " ወደ ቁልቁለቱ ውረዱ፤ አሳዳጆቻችን ከታች መንገዱን ተከትለው ይመጣሉ ። በየአለበት ተበታትናችሁ በየመቶ ሜትሩ በመሆን ጠብቁ " ብሎ አዘዛቸው ።

ሆስነርን ተከትሎ ዶብኪን በመውጣት አካባቢያቸውን በፍጥነት ቃኝቶ ገመገመ ። በከፍታ ቦታ ላይ በማረፋቸው ለደህንነታቸው ጥሩ ነበር ። ኮንኮርዱ ያረፈበት ደልዳላ ቦታ ሲሆን በምሥራቅ በኩል ወደ መንገዱ የሚያስወርድ ቁልቁለትና በምዕራብ በኩል ደግሞ ወደ ወንዙ መለስ ያለው ቀጥ ያለ ዘቅዛቃ ነበር ። በጨለማው ምክንያት በሰሜንና በደቡብ በኩል ያለውን ማየት አልቻለም ። ባለ . 22 የሆኑ ስድስት ሽጉጦች ፣ አንድ ኡዚ ድግን መትረየስና አንድ ጠመንጃ ነበሯቸው ። አረቦቹ ግን ከዚህ የበለጡ መሣሪያዎች እንዳሏቸው የታወቀ ነበር ። ወደ አውሮፕላኑ ጅራት ቀና ብሎ ሲመለከት ተገንጣጥሎ አየው ። ይሁን እንጂ ከአሁን በኋላ የሚሰጠው ጥቅም ብዙ ስላልነበረ ከምንም አልቆጠረውም ።

ዕቃዎቹ ተበታትነው ስለነበረ የዕቃ መያዣውን ከኋላው ክፍል ጋር የሚለየው የብረት ግድግዳ መገንጣጠሉን ተረዳ ። ጫማዎችና ልብሶች ኮንኮርዱ በቀደደው ቦይ ውስጥ እንደ እህል ዘር ተበታትነው አያቸው ። ጀንበርዋ ስለጠለቀች ሰማዩ ሙቀት በማይሰጡ ኮከቦች ተሞልቷል ። ዶብኪን በድንገት ስለቀዘቀዘው ሃማሲን የተባለው ሞቃት አየር በዚያ መንፈስ እንዳልጀመረ አወቀ ። ሌሊቱ ረጅምና ቀዝቃዛ ይሆናል ። አንደኛችን እንኳን ጧት ፀሐይ ስትወጣ ለማየት ዕድል ይኖረን ይሆን ብሎ አሰበ ።

ሌሎቹ መንገደኞች እየዘለሉ ሲወርዱ ይስሐቅ በርግ በክንፉ ላይ ወጥቶ ከተመለከተ በኋላ ወደ ተሰባበረው የአውሮፕላን ጅራት ሔደ ። ከግማሽ ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ወዳለው መንገድ አቅልቁሎ ሲመለከት ቀስ ብለው በሚሔዱ መኪናዎች መብራት ፊት የሰዎች ጥላ ሲንቀሳቀስ አየ ። የአሜሪካ ኮልት . 45 ሽጉጡን አውጥቶ ቆመ ።

ጃባሪና አሪፍ ከአውሮፕላኑ ወርደው ሲሔዱ አሪፍ ተደናቅፎ ሊወድቅ ሲቃጣው ጃባሪ ረዳው ። ሁለቱም እየወደቁና እየተነሱ በአንድ ከፍ ያለ ቦታ በስተጀርባው ደረሱ ። ጃባሪ በጉብታው ላይ እንጋጠ ተመልክቶ “ ይፈነዳል ብየ አላስብም ” አለው ።

አሪፍ ቁና ቁና እየተነፈሰ ፊቱን ከጠረገ በኋላ “ እንዋጋለን ብየ ድምጽ መስጠቴን ማመን አልችልም ” አለው ።

ጃባሪ በመሬቱ ላይ ጋደም ብሎ “ አንተ ራስህ እንደተናገርከው ምንም ይሁን ምን እንደ ያዕቆብ ሆስነር ተፈርዶብሃል ። ቀደም ብሎ ምን እንደተባለ ሰምተሃል ? ሪሽ በራምላ ወህኒ ቤት በነበረበት ጊዜ ሆስነር በጥፊ ወልውሎታል አሉ ” አለው ።

“ ነገሩ ለሆስነር መጥፎ አጋጣሚ ነው ። የፈለገው ይሁን ለእምነቱ ይሞታል ። እኔ ግን ከሚስቴ በስተቀር አንድም ሰው በጥፊ አልመታሁም ። ሪሽ ግን የሆስነርን አንገት እንደሚቆርጠው ሁሉ የእኔንም ያጭደዋል ። ”

“ ራስህን ወዳድ ሰው ነህ፤ኢብራሂም ” አለው ጃባሪ ሲጋራውን እያቀጣጠለ ።

“ በራሴ ላይ ሲመጣ ፤ ልክ ነህ ። ”

ጃባሪ ከተቀመጠበት ተነስቶ “ የትና በምን ዓይነት ለመዋጋት የሚያወጡትን ዕቅድ ሔደን እንይ ። ምናልባት ልንረዳቸው እንችል ይሆናል ” አለው ።

አሪፍ ከተቀመጠበት አልተንቀሳቀሰም ። “ እኔ እዚሁ እቆያለሁ ። አንተ ግን ሒድ ” ካለው በኋላ በራሱ ላይ የጠመጠመውን ጨርቅ አንስቶ “ አሁን አይሁዶችን እመስላለሁ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ጃባሪ በነገሩ ስቆ “ የዕብራይስጥ ቋንቋህስ እንዴት ነው?” አለው።

“ የምክር ቤት አባሎች ከሆኑት ከግማሾቹ እሻላለሁ ። ”

“ እንግዲያውስ ኢብራሂም ፤ ጊዜው የሚመጣ ከሆነ ሙከራው መልካም ነው ” አለው ጃባሪ ።

ቶም ሪቻርድሰን ወደወንዙ በሚወስደው ተዳፋት አጠገብ ቆሞ አቅልቁሎ ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ ተመለከተ ። ጆን መክለር እርሱን ተከትሎ በመሔድ አንድ እግሩን በአንድ ትንሽ ጉብታ ላይ አድርጐ ቆመ ። መክለር አንድ ሽጉጥ ይዞ እንደነበረ ሪቻርድሰን አየ ። ሪቻርድሰን ሁለቱን ቀዝቃዛ እጆቹን አፋትጐ " ይህ መጥፎ እንቅስቃሴ ነው " አለው ።

መክለር በከንፈሮቹ መካከል ይዞት የነበረውን የከብሪት እንጨት ጥሎ ሌላ ከኪሱ በማውጣት " ምናልባት ይሆን ይሆናል " አለው ።

" ስማ ፤ በዚህ አካባቢ እንድንቆይ የሚያስገድድ ነገር ያለ አይመስለኝም ። በወንዙ ዳርቻ አንድም ሰው ያለ አይመስልም ። ስለዚህ ብንሔድ ይሻላል ። ነገ በዚህ ሰዓት ባግዳድ እንገባ ይሆናል " አለው ።

መክለር ወደ እርሱ እየተመለከተ " የት እንዳለን እንዴት ታውቃለህ ? " ብሎ ጠየቀው ።

ሪቻርድሰን ሳይንቀሳቀስ ጸጥ ብሎ ቆመ ።

" ጥያቄ ነው ያቀረብኩልህ ኰሎኔል ። "

ሪቻርድሰን ራሱን አስገድዶ የመክለርን ዓይኖች ትኩር አድርጐ ተመለከታቸው ። የተናገረው አንድም ነገር አልነበረም ።

መክለር ከትንሽ ሴኮንዶች ጸጥታ በኋላ በጭኑ ላይ አጋድሞ ይዞት የነበረውን ሽጉጡን አነሳ ። የሪቻርድሰንን ፍንከች አለማለት አጤነ ። ቀጥሎም በለሰለሰ አንደበት " እኔ በዚህ አካባቢ እቆያለሁ " አለው ።

ሪቻርድሰን ትልቁን ሽጉጥ ተመልክቶ " መልካም ፤ እኔ መሔዴ ነው " አለው በለሰለሰ አነጋገር ።

መክለር በወንዙ ዳርቻ ብዙ መብራቶች ወዲያና ወዲህ ሲሉ ተመለከተ ። ከመብራቶቹ 270 ሜትር ራቅ ብሎ ሦስት የጓስ ሜዳዎች አሉ ።

" ሙሉ በሙሉ ከበውናል " ብሎ ወደ እነርሱ አመለከተው ።

ሪቻርድሰን ምንም የመጨነቅ መልክ ሳያሳይ " ሲቪሎች ሊሆኑ ይችላሉ " አለው ።

"ይሆኑ ይሆናል" ብሎ መክለር ሪቮልቨሩን በሁለት እጁ ይዞ ሁለት ጥይቶች መብራቱ ወዳለበት ተኰሰ። የአውቶማቲክ መሣሪያዎች የእሩምታ ተኩስ ምላሽ ሰጡ ። መክለር ሽጉጡን አቀባብሎ " ቦታ እንያዝ ፤ በእዚህ አካባቢ ለብዙ ጊዜ እንቆይ ይሆናል " አለው ።

ናታን ብሪን ኤም-14 ጠመንጃውን በቋጥኙ ላይ አስደግፎ አስ ቀመጠው ። በባትሪ የሚሠራውን በሌሊት ሊያስተኩስ የሚያስችል በኮከብ ብርሃን አጉልቶ የሚያሳየውንና በጠመንጃው ላይ ሊገጠም የሚችለውን መነጽር አንስቶ የመሬቱን አቀማመጥ ተመለከተ ። ያ መነጽር በአረንጓዴ ቀለም ሁሉን ነገር አጉልቶ ለማሳየት ይችላል ። መነጽሩን በጠመንጃው ላይ ገጥሞ እየነካካ ሁሉ ነገር ግልጽ እስኪ ሆንለት ድረስ አስተካከለው ። አካባቢውም የጥንት ከተማ ፍርስራሽ እንደነበረ ለመረዳት ቻለ ። ለብሪን ሁሉም ነገር ብርቅ ሆነበት ። ከመ ንገዱ አካባቢ 20 ያህል ከሚሆኑት በስተቀር ሌሎች አረቦች ጥንቃቄ በሌለው ሁኔታ ወደ ተራራው ሲመጡ አያቸው ። ከእነርሱ ወደኋላ ዳገቱ ከመጀመሩ በፊት 100 ሜትር ያህል እርቀት ላይ መኪናዎች ቆመ ዋል ። በአሁኑ ጊዜ አረቦቹ ከብሪን 200 ሜትር ርቀት ላይ ናቸው ። ከፊት ሆኖ የሚመራውን ሰው ተመለከተው ። ሰውየው አህመድ ሪሽ ነበር ። ብሪን ግን አላወቀውም ። ጣቱን በምላጩ ላይ አድርጎ ጫን ማለት ሲጀምር የተሰጠውን ስልጠና በማስታወስ በመጨረሻ ወደ ተሰለፈው ሰው ጠመንጃውን አነጣጥሮ ምላጩን ሲስበው ድምጽ የሌሹ ጥይት ሰውየውን እረብ አደረገው ። ሌሎቹ የሰውየውን መመ ታት ሳያጤኑ አቀበቱን መውጣታቸውን ቀጠሉ ።

ብሪን እንደገና አሁንም በመጨረሻ ላይ ያለውን ሰው አነጣጥሮ ዘረረው ። ይኸኛውም ምንም ድምጽ ሳያሰማ ለሽ አለ ። ብሪን ባደረ ገው ተደስቶ ለራሱ ፈገግ አለ ። ለሦስቱኛ ጊዜ አሁንም ከኋላ ወዳለው ሰው አነጣጥሮ ሲቆነድደው ሰውየው ድምጽ አሰማ ። አረቦቹ በዚህ ጊዜ በርግገው በየቋጥኙ ሥር ተበታተኑ ። ብሪን ተነስቶ ወደ ቋጥኙ ኋላ አፈግፍጎ ሲጋራውን አቀጣጠለ ። ለጥሩም ሆነ ለመጥፎ ለመዋ ጋት ተገደዋል ። ባደረገው ደስታ ተሰምቶታል ። ከኋላው በኩል ድምጽ ስለሰማ ጠመንጃውን አዙሮ ደገነ ። ሆስነር ወደ እርሱ እየተመለከተ ነበር ።

ብሪን ፈገግ ብሎ “ አማን ናችሁ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ሆስነር በአዎንታ ራሱን ነቅንቆ “ አዎን ፤ ደህና ነን ” አለው ።

ቤከር ወደ ጨለማው እየተመለከተ “ ያለነው የት ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ፒተር ካን አስቸኳይ ምልክት በሚሰጠው መብራት የአየር ካር ታውን እያነበበ “ ጥሩ ጥያቄ ነው ” አለው ።

ቤከር የወንበር መቀመጫ ቀበቶውን ፈትቶ በመቆም የሔስን ራስ ቀና አድርጎ ተመለከተው ። ተፈናጥሮ በገባ ድንጋይ ራሱ ተበ

ርቅሷል ። የሕይወት መኖር ምልክት አልነበረውም ። ራሱን ቀስ አድ ርጐ መልሶ በማስቀመጥ እጁ ላይ የነካውን ደም በነጭ ሸሚዙ ጠረ ገው ። ወደ ካን ዞሮ " ሕይወቱ አልፏል ፤ ፒተር " አለው ።

ካን ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ።

ቤከር ላቡን ከፊቱ ላይ ጠርጐ " ወደ የሥራችን እንመለስ ። ያለ ነው የት ነው ? " ብሎ በድጋሚ ጠየቀው ።

ካን ካርታውን እንደገና ተመልክቶ በእርሳስ ምልክት ካደረገ በኋላ ቀና በማለት " በባቢሎን ፤ በባቢሎን ወንዞች ነው የምንገኘው " ብሎ ነገረው ።

ቤከር እጁን በካን ትከሻ ላይ ጣል አድርጐና ጐንበስ ብሎ ካር ታውን እየተመለከተ በሃሳብ ተውጦ ራሱን ነቀነቀ ። ቀጥሎም " ጽዮ ንን ባሰብናት ጊዜ አለቀስን " የሚለውን ጥቅስ አስታውሶ ነገረው ።

# ምዕራፍ ሁለት

## ባቢሎን ፡ መመልከቻ ማማዎች

ከዚያ በባቢሎን ወንዞች ተቀምጠን ጽዮንን ባሰብናት ጊዜ አለቀስን ።
መሰንቆቻችንን በውስጥዋ ባለው ህያ ዛፍ ሰቀልን ።
ከዚያም የማረኩን ከፅዮን ቅኔ አንዲቱን ተቀኙልን አሉን ።
ያስለቀሱንም ደስታ አድርጉ ብለው ከእኛ ፈልገው ነበሩና ።
እንደት የእግዚአብሔርን ቅኔ በንግዳ ምድር እንቀኛለን ።
የሩሳሌም ሆይ ረስቼሽ እንደሆን ቀኜ ትርሳኝ ።
ያላሰብሁሽም እንደሆን መላሴ በትናጋዬ ይጣበቅ ። ከደስታዬ ሁሉ
በላይ የሩሳሊምን ከፍ ከፍ ባላደርጋት ።

መዝሙር 137 ፡ 1 - 6

በባቢሎንም የመንግሥታት ጌጽ የከልዳውያንም ሽልምና ትምክህት ፤
እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን እንዳፈረሰ ተሆናለች ።
ለዘላለም የሚቀመጥባት የለም ። ለልጅ ልጅም አትለማም ።
አረቧም ከዚያ ድንኳኑን አይተክልም ። በግ ጠባቆችም
መንጋቸውን አያሳድሩበትም ።
ነገር ግን ከዚያ አራዊት ያርፉበታል ፤ ጉጉትም በቤተቻቸው
ይመላባቸዋል ። ሰጐንም ከዚያ ትቀመጣለች ። ጅኖችም
ከዚያ ይዘፍናሉ ።
ቀበሮችም በቤተ ንጉሣቸው ይጮሃሉ ፤ የሚያስፈሩ እንስሶችም
በተድላ ግምብ ይኖራሉ ። ጊዜዋም ለመምጣት ቀርበዋል ።
ቀንዋም አይዘገይም ።

ኢሳይያስ 13 ፡ 19 - 22

# — 10 —

እየቀዘቀዙ በመሔድ ላይ የነበሩት ከአራቱ የኮንኮርድ ሞተሮች ቅጭ ፣ ቅጭ የሚል ድምጽ ከሚሰማ በስተቀር በተራራው ላይ ጸጥታ ሰፍኗል ። ትልቁ ነጭ አውሮፕላን ጉማዎቹ ረግፈው ፣ አፍንጫው ወደ መሬት ተተክሎና ተጋድሞ ሲያዩት አንድ ኩሩ ፍጥረት ተገዶ የተቀመጠ ይመስል ነበር ። ለጊዜው ሁሉም ነገር ጸጥ ያለ መሰለ ። ትንሽ ቆይቶ ግን የሌሊት ወፎችና የሌሎች ልዩ ልዩ ፍጥረቶች ድምጽ መሰማት ጀመረ ።

ያዕቆብ ሆስነር ማንኛውም ነገር — ሕይወታቸው ፣ የወደፊት ሕልውናቸው ምናልባትም የሕዝባቸው የወደፊት ዕድል — በሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች ላይ የተመረኮዘ እንደሚሆን አወቀ ። በፍል ስጥኤማውያኖች በሚደረገው ወሳኝ ውጊያ ተራራው ከተያዘ ሁሉም ነገር ያከትማል ። ግልጽ ባልሆነው ብርሃን ዙሪያውን ሲመለከት ሰዎች ያለአንድ አላማ በኮንኮርዱ ዙሪያ ሲንቀሳቀሱ አያቸው ። እንደ ተጠራጠረው ከሆነ ጥቂቶቹ በአውሮፕላኑ መውደቅ ከደረሰባቸው ድንጋጤ ገና አልተላቀቁም ። ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ባያውቅም ጊዜው ግን መጥቷል ። ተዋናዮቹ ፈቃደኞች ናቸው ፤ ግን ትርዕይቱን ለማቅረብ ዝግጁ አልነበሩም ። ሆስነር ግጥሙን በዚያ ወቅት በቦታው ላይ ለመጻፍ ወሰነ ። ግን ዶብኪንና በርግ በአቅራቢያው ሆነው የጽሑፉ ተካፋይ እንዲሆኑ ተመኘ ።

ሆስነር ኤም - 14 ጠመንጃውን ከብሪን ወስዶ በመሳሪያው መነጽር አቆልቁሎ ተመለከተ ። ሦስቱ አረቦች በወደቁበት ድንጋይ አጠገብ ተጋድመዋል ። ሆስነር በተጨማሪም ሁለት ኤኬ—47 አውቶማቲክ ጠመንጃዎች በመሬቱ ላይ ወድቀው አየ ። እነዚህን ቢያገኝ ጠላቶቹን መልሶ ለመጠራረግ ያመቸው ነበር ።

ወደ ብሪን ዞሮ “ እነዚያን መሳሪያዎች ለማምጣት መውረዴ ስለሆነ መከላከል እንድታደርግልኝ ” ብሎት ኤም—14 ጠመንጃውን መልሶ ከሰጠው በኋላ የራሱን ስሚዝና ዌሰን . 22 ሽጉጡን አውጥቶ በእጁ ያዘ ።

ከሆስነር የጸጥታ ሰዎች አንዱ ሙሼ ካፕላን ወደታች ለመውረድ ሆስነር ሲዘጋጅ ስላየው “ ቀድመህ ልትሔድ ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ ከእኔ ጋር ለመሔድ ፈልገህ እንደሆነ ጉንበስና ጸጥ ማለት አለብህ ” ብሎ ሹክ አለው ። ሆስነር የካፕላን ሽጉጥ . 22 ድምጽ የሌለው መሆኑን አስታውሶአል ። ከአንዱ ድንጋይ ወደሌላው ቀስ እያሉ

በመራመድ መንገዳቸውን ቀጠሉ ። አንዱ ከጠላት ሲጠብቅ ሌላው ይራመድ ነበር ። ሆስነር ድንጋዮች የመሰሉት ጡቦችና የአፈር ናዳ ዎች መሆናቸውን ተገነዘበ ። አንዱን ሲረግጠው ሌላው እየተፈረፈረ -ይንከባለል ነበር ። የሸክላ አፈርና አሸዋ እየተንሸራተተ ባለበት ቦታ አሻቅቦ ለመውጋት ለጠላት በጣም አስቸጋሪ ነው ።

ብሪን በተራራው ቋይ ሆኖ በኮከብ ብርሃን የሚሠራ መነጽር በተ ገጠመበት በኤም - 14 አቀልቁሎ ሲመለከት ከተራራው በታች 1500 ሜትር ርቀት ላይ ባለው ቦታ በመኪናዎቹ አጠገብ ፍልስጥኤማውያ ኖቹ እንደገና ሲዘጋጁ አያቸው ። ሁኔታቸውን ሲመለከታቸው በቁጣ የሚንቀሳቀሱ ይመስላሉ ። ብሪን ዘዴአቸውን ያውቀዋል ። እነዚህ የአሁኖቹ ቀደም ብሎ ባጋጠማቸው የሚደነቁ ከሆነ የእነእር ሱም ዕጣ ፋንታ ሲደርስ አብዛኛውን ጊዜ ይበታተናሉ ። በሚደርሰው ሀፍረትም አንዱ በአንዱ ያመካኛል ። አሁን ብሪን እንደሚመለከታ ቸው በቁጣና በድፍረት በመነሳሳት ላይ ነበሩ ። መመልከቱን እንደ ቀጠለ ሃያ የሚሆኑ እንደገና ወደ ተራራው ለመውጣት መምጣት ጀመሩ ። አንድ ሰው ከመኪናው ላይ አንድ ነገር ሲያወርድ አየው ። ቀጥለውም ሦስት ቃሬዛዎች ይዘው ወደ ተጐዱት ሰዎች መጡ ።

ሆስነር በጨለማ ውስጥ በሚገባ ማየት አልቻለም ። ከተነሳበት ቦታ ጀምሮ መስመሩን ሳያሳብር ቀጥ ብሎ ለመሔድ ሞከረ ። የሞ ቱት ሰዎች በአንድ ጉብ ባለ ነገር አጠገብ ነበሩ ። ቁልቁለቱን በሚ ወርድበት ጊዜ በኮንኮርዱ አጠገብ የቀሩት ሰዎች ምን እየሰሩ ይሆን የሚል ሃሳብ አደረበት ። ብሪን ለእያንዳንዳቸው ጠመንጃ እንደሚሰ ጧቸው ተስፋ አድርጓል። የእርሱ አምስት ሰዎች አሁንም በተራራው ላይ ነበሩ ። እያንዳንዳቸው ስሚዝና ዌሰን . 22 አላቸው ። በተጨማ ሪም ብሪን ኤም - 14 ሲኖረው ሌላ ግለሰብ ደግሞ ምናልባትም ጀ ሹዋ ሩቢን ባለ 9 ሚሊ ሜትር ድግን መትረየስ አለው ። እንደዚሁም ሌሎች የእጅ ጠመንጃዎች በኮንኮርዱ ውስጥ ይኖራሉ ብሎ አምኗል። ይሁን እንጂ የእጅ ጠመንጃዎች ከ20 ሜትር ርቀት በኋላ ኢላማቸ ውን አይመቱም ። በመሆኑም ኡዚ ውና ኤም-14 ዋነኛ ተስፋ የተጣለባ ቸው መሣሪያዎች ናቸው ። ነገር ግን ጥይቶቻቸው ካለቁ ከፍተኛ ችግር ይገጥማቸዋል ። ኤኬ—47 ጠመንጃዎች ከበቂ ጥይቶች ጋር ከሞቱት አረቦች ከተገኙ ተራራውን ሳያስነኩ ለአንድ ወይም ከዚያ ለበለጠ ቀን እንደሚቆዩ አምኗል ። ሆስነር በዚያ ብዙ እንቅፋት ባለበት ቦታ ላይ ሔዶ የሰዎቹን አስከሬን የማግኘቱን ነገር ተጠራጠረ ።

ሆስነር ድምጽ ስለሰማ ሰወር ብሎ ቆመ ። ካፕላን ደግሞ ከቋጥኙ ጋር ተለጠፈ ። ድምጹን እንደገና ሰሙ ። እያቃሰተ ደጋግሞ በአረብኛ “ እዚህ ነው ያለሁት ” የሚል ድምጽ ነበር ።

ሆስነር በአረብኛ ቀስ ብሎ “ እየመጣሁ ነው ” አለው ። የድ ምጽ አጣጣሉ ማንነቱን እንዳያሳውቅበት ሆስነር ፈራ ።

“ እዚህ ነኝ ። ተጐድቻለሁ ” አለ ሰውየው እንደገና ።

“ እየመጣሁ ነው ” አለው ሆስነር በድጋሚ ።

በአንድ ጠባብ ቦይ ውስጥ እየዳኸ ከሔደ በኋላ በአንድ ገላጣ ቦታ ደርሶ አዲስ በወጣችው የጨረቃ ብርሃን ሲመለከት ሦስት ሰዎች ተዘርረው አየ ። ከሦስቱ አንዱ ኤኬ—47 ጠመንጃውን አንግቶ ከተ ኛበት ሲንቀሳቀስ ስለአየው በልቡ ተራገመ ።

ካፕላን በጐኑ በኩል ተጠግቶ “ በማይጮኽ መሣሪያ ልጨር ሰው ” ብሎ በጆሮው ሹክ አለው ።

ሆስነር በአሉታ ራሱን እየነቀነቀ “ እሩቅ ስለሆነ አይሆንም ” አለው ። ምናልባት የሚተኩሰው ጥይት ሰውየውን ቢስትና በሌላ ቦታ ላይ ሲያርፍ ድምጽ ቢያሰማ ኤኬ—47 ጠመንጃዎች ከየአቅጣ ጫው ስለሚተኮሱ ከፍተኛ አደጋ ያስከትላል ። “ እኔእይዘዋለሁ።”

ሆስነር ከረባቱንና ኮቱን አወለቀ ። ሰማያዊ ሸሚዙን ከሱሪው ጐትቶ አውጥቶ ከላይ ያሉትን ጥቂት አዝራሮች ፈታ ። በኮቱ ላይ ያለውን ነጭ ሀር ተልትሎ አረቦቹን ለመምሰል በራሱ ላይ ጠመጠመ። ቀጥሎም ወደ ቆሰለው አረብ እየዳኸ መሔድ ጀመረ ።

ካፕላን ሽጉጡን አቀባብሎ የጨረቃ ብርሃን በሌለበት ቁጢጥ ብሎ አደፈጠ ።

ብሪን ፍልስጥኤማውያኖቹ ወደ ተራራው ሲወጡ አያቸው ። ሆስ ነርንና ካፒላንን በመጨረሻ ካየበት ሥፍራ በግምት ከ100 ሜትር ባነሰ እርቀት ላይ ደርሰዋል ። በአሁኑ ጊዜ እንደ እግረኛ ጦር ወታ ደሮች የሰለጠኑ ይመስል ተበታትነው አንዱ ሌላውን እየጠበቀና እየ ተከላከለ ስለነበረ የሚሔዱት ለኢላማ ምቹ አልነበሩም ። ብሪን ጠመንጃውን አዙሮ ሆስነርን በዓይኑ ቃኘ ። በወጣ ገባው መሬት ላይ አንድ በራሱ ላይ ጨርቅ የጠመጠመ ሰው ሲድኽ ተመለከተ ።

ሆስነር “ እዚህ ነኝ ፤ እዚህ ነኝ ” ብሎ አንሾካሾከ ።

የቆሰለው አረብ ወደ ጨለማው ተመለከተ ።

ሆስነር በፍጥነት ወደ እርሱ ተራመደ ።

ብሪን ለየት ያለ ጥምጣም አድርጐ እንደ እንሽላሊት እየተሳበ በፍጥነት የሚሔደውን በጠመንጃው መነጽር ተከታተለው ፡፡ የቆሰለው አረብ አሁን ማን እንደሆነ አስታወሰው ፡፡ ሰውየው ቀደም ብሎ በጥይት የመታውና ድምጽ በማሰማቱ ሌሎቹ እንዲበረግጉ ያደረገው ነበር ፡፡ ጠመንጃውን እየዳኸ በሚሔደው ሰው ላይ አነጣጠረ ፡፡ ምላጩን መሳብ ከጀመረ በኋላ እንደገና አቅማማ ፡፡ የቆሰለ ጓዱን ለማዳን ሲል ሕይወቱን በመሰዋት ላይ ያለውን ሰው መግደል ከብረ ቢስ መሆኑን ቢያውቅም ሌላ ምርጫ እንደሌለው አሰላሰለ ፡፡ ለራሱ አስታራቂ ሃሣብ በመፈለግ እየዳኸ የሚሔደውን ለመግደልና የቆሰለውን በድጋሚ ላለመንካት ወሰነ ፡፡ ይህ ውሳኔ የጦር አማልክትን ለምን እንደሚያስደስታቸው ራሱም አላወቀውም ፡፡ በበኩሉ ሁኔታውን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መመልከቱ አስፈላጊ መሆኑን ተረድቷል ፡፡ ቁልቁለቱን እንደ ገና በፍጥነት ቃኘ ፡፡ አሁንም ሆስነርንም ሆነ ካፕላንን ማየት አልቻለም ፡፡ አረቦቹ ከቆሰለውና እየዳኸ ከሚሔደው ጓድ ለመድረስ ከ50 ሜትር ያነሰ እርቀት ላይ ደርሰዋል ፡፡ ይሁን እንጂ የሚሔዱበት የመሬት አቀማመጥ ጥሩ ስላልነበረ ኢላማ ውስጥ ለማስገባት አስቸጋሪ ሆነበት ፡፡ ብሪን በግልጽ ቦታ ላይ እየዳኸ በሚሔደው ሰው ላይ አነጣጠረ ፡፡

“ አይዞህ ፤ ደርሼልሃለሁ ” ብሎ ሆስነር ቀስ ብሎ ሲናገር በዳገቱ ላይ የሚወጡትን ሰዎች ድምጽ ሰማ ፡፡

የቆሰለው አረብ በክንዱ ተንተርሶ ቀና በማለት ራሱን አስገድዶ ለሆስነር ፈገግታ አሳየው ፡፡ ከአንድ ሜትር ያነሰ እርቀት ላይ ሲደርስ ሆስነርን ትኩር አድርጐ ከተመለከተው በኋላ የሚያስደንቅ ድምጽ አሰምቶ ጠመንጃውን ሲያዞርበት ሆስነር ዘሎ አንቆ ያዘው ፡፡

ብሪን በምላጩ ላይ የነበረውን ጣቱን አላላ ፡፡

አረቡ እንደገና ጮኸ ፡፡

ሆስነር በአቧራው ውስጥ አንድ ድንጋይ ስላገኘ አንስቶ ከመረገበት በኋላ የአረቡን ፊት ጨምዶ በመያዝ አፉን አፍኖ ያዘው ፡፡

ካፕላን ገስግሶ ከሞቱት አረቦች ላይ አውቶማቲክ ጠመንጃዎቻቸውንና በጥይቶች የተሞሉ ዝናሮቻቸውን አፈፍ አደረገ ፡፡ ሆስነርም ከቆሰለው አረብ ላይ ጠመንጃውንና ጥይቱን ገፈፈው ፡፡

ብሪን አረቦቹን የሚመራው ወደ ግልጽ ቦታ እስኪመጣ ድረስ ጠብቆና አነጣጥሮ በድምጽ የለሹ ጠመንጃው ተኩሶ በጀርባው ዘረረው ፡፡

ሆስነርና ካፕላን ሰውየው ሲወድቅ ድምጽ ወደ ሰሙበት ዞረዉ ሲመለከቱ በ20 ሜትር ዕርቀት ላይ አረቦቹን አዩአቸው ። ብሪን እንደ ገና ተኩሶ ሌላውን ሲያደብነው አረቦቹ ተበታተኑ ።

ሆስነር የቆሰለውን አረብ በጀርባው ላይ ካዘለ በኋላ ጠመንጃ ውንና ጥይቱን ለካፕላን ሰጠው ። ከከባድ ሸክም ጋር ዳገቱን መዉ ጣት ጀመሩ ። ጉርፍ በቀደደው ቦይና በወጣ ገባው መሬት አጉንብ ሰው እየተሹለከለኩ ጉድቢያውን መከታ እያደረጉ በሚሔዱበት ጊዜ ድንገተኛ የተኩስ እሩምታ ከኋላቸው ሰሙ ። የአፈር ናዳ ፣ የጡብ ሸክላና ድንጋዮች በአካባቢያቸው እየተፈናጠሩ አረፉ ።

ካፕላን በተለይ ያን የኤኬ—47 ተኩስ ድምጽ ፈጽሞ አይረሳ ውም ። ጥይቱ እያፏጨ በጆሮው አጠገብ ሲያልፍ ልቡ የቆመ መሰ ሎት ነበር ። እንደዚሁም በብዙ ቦታ የተመታ መሰለው ። ሲያጠዙት የነበሩት ግን የአፈሩና የጥይቱ ፍንጣሪዎች ነበሩ ።

“ አጋድመው ” ብሎ በሆስነር ላይ ጮኸበት ። ምክንያቱም ያን ሰው ተሸክመው ለማምለጥ አስቸጋሪ ነበር ።

“ አይሆንም ፤ ያስፈልገናል—ይልቅስ ወደፊት ቀጥል ። ”

“ ምናባቱንስ ” ብሎ ካፕላን ጠመንጃውን አቀባብሎ ሰላሳ ጥይቶች ተኮሰ ። ከተራራውም ላይ የስሚዝና ዌሰን .22 ሽጉጦች የተ ኩስ ድምጽ አስተጋቡ ። እንደዚሁም የኡዚ ድግን መትረየስ ተኩስ ሰሙ ። ብሪን ወደ ሆስነር ዞሮ ተመለከተ ። አሰፈራቸው ሊደርሱ 50 ሜትር ያህል ቀርቷቸዋል ። ከተራራው ላይ ሰዎች እየሮጡ መጥተው አንዱ ከሆስነር ላይ አረቡን ተቀበለው ። ካፕላን ደክሞትና አልቦት ስለነበረ ተንገዳግዶ በመሬቱ ላይ ወደቀ ። እርሱንም አንድ ሰው ተነ ስቶ እንዲሔድ እረዳው ። ከጠላት የሚተኮሰው ጥይት እንዳይመታ ቸው ወዲያና ወዲህ እየተጥመዘመዙ ሲሔዱ የመሬቱ ፍንጣሪ በዙሪ ያቸው ያርፍ ነበር ። ብሪን በተራራው ጫፍ ተዳፋት አጠገብ ሆኖ እያ ነጣጠረ ድምጽ በሌለው ጠመንጃ ጠላትን ሲያዋክብ ካፕላን ተመለ ከተው ። ካፕላን አንድ ነገር እንደመታው አይነት ሆኖ ተሰማው ። በአሁኑ ጊዜ የመታው እንደፊተኛው የአፈር ወይም የድንጋይ ፍንጣሪ አልነበረም ። የአሁኑ የሚያምና የሚያቃጥል ነበር ። ራሱንም ሳተ ።

* * *

ሆስነር በጀርባው ተንጋሎ በመተኛት ሁለት እጆቹን ግራና ቀኝ ዘርግቶ አየር እየሳበ ከዚያ ሁሉ ችግር አልፎ የፈለገውን ፈጽሞ በደ ህና በመመለሱ ተደስቷል ። ዶብኪን ቀስ ብሎ ሦስቱን ኤኬ—47 ጠመንጃዎች እነ ማን እንደሚይዟቸው ትዕዛዝ ሲሰጥ ሰማው ። ከሁ ለቱም ወገኖች የሚደረገውን የተኩስ ልውውጥ አዳመጠ ። የኤኬ—

47 ተኩስ እንደተጀመረ አረቦቹ በድንገት አቆሙ ። ከሁለቱም ወገን ያለው ተኩስ ስላቆመ በተራራው ላይ ጸጥታ ሆነ ።

ዶብኪን ወደ ሆስነር ጐንበስ ብሎ " በጣም አስከፊና መጥፎ ነበር ። ያዕቆብ ፣ ለጊዜው የዚህ ዓይነቱን እንደገና አይሞክሩም " አለው ።

" ካፕላንስ ? " አለው ሆስነር ።

ዶብኪን በሆስነር ጐን ቁጢጥ ብሎ በመቀመጥ " ተመቷል ፤ ግን አደገኛ አይመስልም " አለው ።

ሆስነር ቀና ብሎ በመቀመጥ " የት ነው ያለው ? " ብሎ ጠየቀው ።

ዶብኪን አርፎ እንዲጋደም ወደታች እየገፋው " በመጀመሪያ በድካም የወጠረህ አየር ይውጣልህ ። የልብ ድካም እንዲይዝህ አንሻም " አለው ።

ትልቁ ሰው ሆስነርን በጀርባው እንዲተኛ አደረገው ። እርሱ ግን በመሬቱ ላይ መጋደሙን አልፈቀደውም ።

" ለመሆኑ ጥቃት አድርሰናል ? የማረክናቸው መሣሪያዎችስ አሉ ? "

" ጥቂቶች ገድለናል ። ግን ድጋሚ ስህተት አልሠሩም ። ቁስለኞቻቸውንና መሣሪያዎቻቸውን ይዘው አፈትልከዋል ። ቢሆንም ጥቂት የሞቱ ሰዎች ቀርተዋል ። "

" የእኔስ እስረኛ ? "

" በሕይወት አለ ።"

" መናገር ይችላል ? "

" ይመስለኛል ። "

ሆስነር ራሱን ከነቀነቀ በኋላ " ተነስቼ ሰዎቼን ማየት እፈልጋለሁ " አለው ።

" እሺ ትሔዳለህ ። አሁን ግን ትንሽ እረፍ ። "

ሆስነር " ግድየለም " ብሎ ቀስ ብሎ ከተነሳ በኋላ አካባቢውን ቃኝቶ " ሌላስ የተጐዳ አለ ? " ብሎ ጠየቀው ።

" ሙሴ ሔስ አርፏል ። "

ሆስነር የመስኮቱን መሰባበር በማስታወስ " ሌላስ ? " ብሎ ጠየቀው ።

" ጥቂት ሰዎች እውሮፕላኑ ሲያርፍ በመጋጨታቸው መጠነኛ ቁስለት ደርሶባቸዋል ። ቤከርና ሔስ ሊታመን የማይችል ከፍተኛ ሥራ ሠርተዋል ። "

" አዎን " ብሎ ሆስነር ወደ ብሪን ጥቂት እርምጃዎች ተራመደ። ብሪን አሁንም በመንጽሩ ይመለከት ነበር ። ብሪን የሚጠቀምበት ጉብታ በምዕራብ በኩል ቁልፍ የሆነ የመከላከያ ሥፍራ ነበር ። ከፍና ዝቅ ያሉ ጉድጓዶች በአካባቢው ነበሩ ። ሆስነር አንድ እግሩን ከፍ ባለው መሬት ላይ አድርጐ በጨለማው ውስጥ የአገሩን አካባቢ ከተመለከተ በኋላ ወደ ዶብኪን በመዞር " ያለነው የት ነው ? " ብሎ ጠየቀው ።

" ባቢሎን ። "

" ከአንጀትህ ነው ? "

" ባቢሎን ። "

ሆስነር ለጥቂት ጊዜ ጸጥ ብሎ ከቆየ በኋላ " የባቢሎን መውደቅ ወይስ በባቢሎን ወንዞች ማለትህ ነው ? " ብሎ ጠየቀው ።
" ቦታው ይህ ነው ። "

ሆስነር ሃሣቡ ተመሰቃቀለበት ። ከጥቂት ሰዓቶች በፊት ምቾት ባለው አዲስ ኮንኮርድ ወደ ኒውዮርክ ይበር ነበር ። አሁን ደግሞ በባቢሎን አካባቢ ባለ አቧራ ውስጥ እየዳኸ ነው ። ነገሩ ግራ የሚያጋባ ነበር ። ዶብኪን በተጨማሪም " ማርስ " ነው ብሎ መናገር ይችል ነበር ።

ሆስነር ድምጹን ከፍ አድርጎ " ባቢሎን " አለ ። በጂኦግራፊ መዝገበ ቃላት ውስጥ እንደ ድንቅ ከሚቆጠሩት ስሞች አንዱ ነበር ። ስም ሆኖ ከስምነቱ የበለጠ ትርጉም ያለው — ቦታ ሆኖ ከቦታ የተለየ ትርጉም ያለው — እንደ ሒሮሽማ ወይም ኖርማንዲ ፤ ካሜሎት ወይም ሻንግሪላ ። " ለምን ? "

ዶብኪን ትከሻውን ነቅንቆ " ማን ያውቃል ? በሪሽ በኩል እንደ ቀልድ የተቀጠረ ይሆናል ብየ እገምታለሁ ። የባቢሎን ምርኮኛና የመሳሰሉት " አለው ።

" የዱሮ ጨዋታ ። "

" ቀልድ ላይሆን ይችላል—ታሪክ ቀመስነት ያለው እንጂ—"

" ይገባኛል " ብሎ ሆስነር ወደ ብሪን ዞረ ። " የተባለውን ሰማህ አይደል ፤ ናታን ? አንተ እንግዲህ የባቢሎን ምርኮኛ ነህ ። ስለዚህ ጉዳይ ምን ታስባለህ ? "

ብሪን በእጁ ይዞት የነበረውን ሲጋራ እቀጣጥሎ " ምርኮኛ ፤ ገሃ ነመሳት ይግቡ ። ጕሀ እንደቀደደ ወርጂ እነዚህን የውሻ ልጆች እጃቸ ውን እንዲሰጡ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እሰጣቸዋለሁ " አለው ።

ሆስነር ስቶ ጀርባውን ቸብ አደረገው ። ወደ ዶብኪን ዞሮ "አየህ አይደለም ፤ የእኔ ሰዎች በእነዚህ እመጸኞች ላይ እርምጃ ለመውሰድ ተዘጋጅተዋል ፤ ጀኔራል ።" አለው ።

ዶብኪን ምንም መልስ ሳይሰጥ ትከሻውን ነቀነቀ ።

" አቋማችን ምንድን ነው ? ማለትም የምንጠቀምበት ዘዴ " ብሎ ሆስነር ጠየቀው ።

" በትክክል ለመናገር እምንችልበት ደረጃ ላይ ባንደርስም አንተ ጠመንጃ ለመማረክ በሔድክበት ጊዜ የዚህን ተራራ አካባቢ መጠነኛ ጥናት አድርጌአለሁ ።

" እና ። "

የዚህ ቦታ ከፍታው ሰባ ሜትር ያህል ሲሆን እንደማስበው የተ ፈጥሮ ተራራ አይደለም ። አንድ ነገር የተመሠረተበት ወይም የተደ ራጀበት ቦታ ይመስላል ። ስመለከተው በላዩ ላይ ልክ እንደጠረ ጴዛ ሆኖ የተደለደለ ይመስላል ። ይህ የሰሜኑ ከተማ ምሽግ ሆኖ ሲያ ገለግል የቆየ ነው ብየ አስባለሁ ። ነፋስ ባመጣው አቧራ ተሸፍኗል ። ቢቆፈር ግድግዳዎችና ለጠላት መመልከቻ እንዲያገለግሉ ከግንብ የተሠሩ ትላልቅ ማማዎች እንደሚገኙ አያጠራጥርም ። በዚያ የሚ ታየው ጉብታ ምናልባት የማማው ጫፍ ሊሆን ይችላል ። ይህ ብሪን የቆመበት ከፍታ ቦታ ከግድግዳዎቹ የወጣ የመጠበቂያ ማማ ነው ።

ሆስነር " ይህን ቦታ ታውቀዋለህ ? " ብሎ ሲመለከተው አነጋ ገሩ ከጥያቄ ይልቅ ትዕዛዝ የሚሰጥ ይመስል ነበር ። " እንዴት ልታ ውቀው ቻልክ ? "

" ከማፖችና ከልዩ ልዩ ሞዴሎች ነው ። ይህን በሕይወቴ አየዋ ለሁ ብየ ፈጽሞ አላሰብኩም ነበር ። የአይሁዳዊ በመሬት ውስጥ የተ ቀበሩ የታሪክ ቅርሶች አጥኚ ሕልም ነው " ብሎት ፈገግ አለ ።

ሆስነር በጨለማው ውስጥ ትኩር አድርጎ ተመለከተው። "በእ ውነት ጀኔራል ስለአንተ ደስ ብሎኛል ። ኤል አል ወደ አልተጠበ ቀና አልታሰበ ቦታ ለሽርሽር ወስዶ ይህን ስላሳየኝ የምሥራች ማለት አለብኝ ። ለወደፊቱም በፕሮግራማችን ውስጥ እናስገባው ይሆናል ። "

" አትጨነቅ ፤ ያዕቆብ ። "

ሆስነር በረጅሙ ተንፍሶ " እሺ እንግዲህ ፤ ይህን ቦታ ላለማስ ያዝ መከላከል እንችላለን ? " ብሎ ጠየቀው ።

ዶብኪን የራሱን ጸጉር በጣቶቹ እርሶ " እኔ . . . ይመስለኛል" ብሎ ንግግሩን ቆም አደረገ ። ቀጥሎም " ጉብታው ሞላላ ሲሆን ስፋቱም በጣም ትልቅ አይደለም ። በሰሜንና በደቡብ የኤፍራጥስ ወንዝ ያዋስነዋል ። በአሁኑ ጊዜ ወንዙ ጢም ብሎ የሚሞላበት ወቅት ስለሆነ የጐርፉ ውሃ በምዕራብ በኩል የዚህ ጉብታ ዳገት መነሻ ይደርሳል ። አረቦቹ በሞላው ውሃ ዳርቻ ጥቂት ሰዎች አሰልፈዋል ። አሜሪካዊው መከለር ቀደም ብሎ ተኩሶባቸዋል ። እርሱ ትልቅ ሽጉጥ የያዘ ሲሆን ኰሎኔል ሪቻርድሰን አብሮት አለ ። "

" በዚያ ያሉት እነእርሱ ብቻ ናቸው ? "

" በአፋፉ ላይ ብዙ ሰዎች እንዲጠብቁ አድርጌአለሁ ። ነገር ግን ጠመንጃ ያለው መከለር ብቻ ነው ። ቁልቁለቱ ግልጽ ፣ ክፍትና በጣም ቀጥ ያለ አቀበት በመሆኑ በዚያ በኩል ጥቃት የሚደርስብን አይመስለኝም ። ምክንያቱም እንደምንጠባበቃቸውና ከመጡም እንደምንወጋቸው ቀደም አድርገን አሳይተናቸዋል ። "

" በዚህኛው ኮረብታ በኩል እንዴት ነው ? "

" በዚህ በኩል ችግር አለ።ከሰሜን እስከ ደቡብ 500 ሜትር ያህል ይሆናል ። ኮረብታው ጋደል ያለ አግድመት እስከ መንገዱ ድረስ ያለው ሲሆን ከዚያ በኋላ ሜዳ ነው ። እንዳየኸው በጥቂት ቦታዎች ላይ ጐርፍ የቀደዳቸው ቦዮችና የተቆለሉ አፈሮች አሉ ። ሊያጠቁን የሚሞክሩት እነዚህን መከታ በማድረግ ይሆናል ። ሌላው ግን ግልጽና በሩቅ ለማየት ችግር ስለሌለ ጠላትን በቀላሉ ለማጥቃት ይቻላል ። በዚህ በኩል ያለውን ሦስት ኤኬ—47 ጠመንጃዎች የአንተ ሦስት ሰዎች ተረክበው ይጠብቃሉ ። ሌላው የአንተ ሰው ጀሹዋ ሩቢን ኡዚ ያለው ሲሆን እዚህ ደግሞ ብሪን ኤም—14 ይዟል ። ሰዎችህ እስሚዝና ዌሰን .22 ሽጉጣቸውን ለተሳፋሪዎቹ እንዲሰጡ ስለተደረገ ጥበቃውን ያጠናክራሉ። እስከታች ድረስ የሚቆጣጠሩና የሚያዳምጡ ሰዎች አሰማራለሁ " ብሎ ወደ ውስጥ አየር ስቦ " ይህም ሆኖ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል ፣ ኤኬ ጠመንጃዎች ባይኖሩን ኖሮ ለመደራደር ሃሣብ አቀርብ ነበር " አለው ።

ሆስነር የብሪንን ሲጋራ ወስዶ በኃይል ከማገ በኋላ መለሰለት ፣ " በዚህ ሌሊት እንደገና ይወጉን ይመስልሃል ? " ብሎ ዶብኪንን ጠየቀው ።

" ይህ በጦር አዛዡ አስተሳሰብ የሚወሰን ነው ። አጥቂው ወገን አከታትሎ ካልገፋ ተከላካዩ ጊዜ ስለሚያገኝ የበለጠ እየተጠናከረ

ይመጣል ። ከግማሽ ሰዓት በፊት ያጋጠሙን ሁሉ ድንገተኛ ስለነበሩ አስደንጋጭ ነበሩ ። አሁን ግን ጨለማውን ተገን አድርገን ልንቋቋማ ቸው እንችላለን ። ”

“ በቀን ውጊያ አይገጥሙንም ፤ ይገጥሙን ይሆን ? ”

“ አይመስለኝም ። ”

“ ቤከር መልዕክት አያስተላልፍ ይሆን ? ”

“ ራዲዮኖቹ በባትሪ እንዲሠሩ እየሞከረ ነው ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በስብሰባው ላይ አንተም እንድትገኝ ስለሚፈልግ ወደ ኮን ኮርዱ እንሒድ ” አለው ዶብኪን ።

“ እዚህም ? ” ብሎ ሆስነር እንደመንገሽገሽ አደረገው ።

ብሪን ባትሪው እንዳያልቅበትና ዓይኑን እንዳይደክመው በየደቂ ቃው እያጠፋ በጠመንጃው የኮከብ ብርሃን መነጽር ጠላት ያለበትንና አካባቢውን ይመለከታል ። ሆስነር በትከሻው ላይ ቸብ ካደረገው በኋላ “ አንድ የሚረዳህ ሰው እመድብልሃለሁ ” አለው ።

“ የእኔን መሣሪያ ለመውሰድ በጣም ትልቅ መሆን አለበት ።”
ሆስነር ስቆ “ እንግዲያውስ አንተ በፈለግኸው መንገድ አድር ገው ” ብሎት ዶብኪንን ተከትሎ ሔደ ።

## — 11 —

ኮንኮርዱ ጋደም ብሎ ደልደል ባለው ጉብታ አጠገብ ቆሟል ። በጉብታው ሰሜንና ደቡብ መጨረሻዎች ወንዙ የሸረሸራቸው ሸር ተቴዎች ይታያሉ ። ኮንኮርዱ ወደ ላይ ያመራው በጉብታው ደቡባዊ ክፍል ነበር።ሆስነርና ዶብኪን የኮንኮርዱ አፍንጫ የአረሰውን ቦይ አቋ ርጠው አውሮፕላኑ ወደ ቆመበት ሔዱ ። ሆስነር ትልቁን ሰው ተከ ትሎ ሲሔድ ሊደርስበት ባለመቻሉ ተቸግሮ ነበር ።

“ የበላይ ኃላፊ የሚሆነው ማን ነው ? ”

ዶብኪን መልስ አልሰጠውም ።

“ እንወያይበት ጄኔራል ፤ የእዝ ሰንሰለት ፤ ምን ማለቱ እንደሆን ይገባሃል ። አንድ አዛዥ ብቻ መኖር አለበት ። ”

ዶብኪን እርምጃውን ቀንሶ “ በእርግጥ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በክብር ይበልጣል ” አለው ።

“ ሌላስ ? ”

“ ይስሐቅ በርግ ይመስለኛል ። ”

“ ሌላስ ? ”

ዶብኪን በኃይል ተንፍሶ “ መልካም ፤ የሚቀጥለው የፖለቲካ ሰው ይሆናል ” አለው ።

“ ማን ? ”

“ በርንስቴይን ፤ የካቢኔ አባል ናት ። ”

“ ያን አውቃለሁ ። ግን አባል መሆንዋ ለዚህ ሥራ ብቁ አያደርጋትም ። ”

ዶብኪን ትከሻውን ከፍና ዝቅ ካደረገ በኋላ “ እኔ በዚህ ውስጥ እንድገባ አታድርገኝ ” አለው ።

“ ሌላስ ? ”

“ አንተ ወይም እኔ ብየ እገምታለሁ ። ”

“ ስድስት የታጠቁ ሰዎች አሉኝ ። ሁሉም ለእኔ ታማኞች ናቸው። በዚህ ተራራ ላይ ለሚካሔደው ጦርነት ብቃት ያላቸው ተዋጊዎች ናቸው ። ”

ዶብኪን ቆም ብሎ “ አንዱ እቂጡ ላይ በጥይት ተመትቷል ። የሌሎቹም ብቃትና ውጤታማነት ወደፊት ይታያል ። ዛሬ ማታ የተካሔዱት ሁለት ውጊያዎች እንደቅምሻ የሚቆጠሩ ናቸው ። የሚቀጥለው ጦርነት መራራ ይሆናል ” አለው ።

ሆስነር ዞሮ እንደገና መራመዱን ቀጠለ ።

ዶብኪን ወደ ጐኑ መጥቶ በጀርባው ላይ ቸብ አደረገው ። “እሺ ፤ አባባልህ ይገባኛል ። ነገር ግን ሥራውን አስቀድመህ ጀምረኸዋል ያዕቆብ ። ከሞት ያመለጥከው ለጥቂት ነበር ። አሁን ትንሽ እፎይታ አድርግ ። ከፊታችን ብዙ ሰዓቶች የሚፈጁ ከባድ ውጥረቶችና ሥራዎች ይጠብቁናል ። ”

“ ምናልባትም ለቀናት ይሆናሉ ብየ እገምታለሁ ። ”

“ አይሆንም ፤ ቢበዛ መቆየት የምንችለው እስከ ነገ ማታ ድረስ ይሆናል ። ”

“ ከዚያ በፊት እርዳታ ልናገኝ አንችልም ይሆናል ። ”

ዶብኪን ራሱን ነቅንቆ " ልክ ነህ ። ይህ የዓመቱ እጅግ በጣም መጥፎው ወር ስለሆነ እዚህ የሚቆይበት አይደለም ። የጸደይ ወር ውሃ ሙላት የሚበገር አይደለም ። ቱሪስቶች ወደዚህ መምጣት የሚጀምሩት ከአንድ ወር በኋላ ነው ። ቤከር በራዲዮ ከሰው ጋር ተገናኝቶ መነጋገር ካልቻለ እዚህ መሆናችንን ማንም ሳያውቅ ለብዙ ቀኖች እንከርማለን ። "

" የኢራቅ ሰዎች እርዳታ ያደርጉልናል ብለህ ታስባለህ ? "

" ማን ያውቃል ? አረቦች እጅግ በጣም ርኅራኄ ያላቸው ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ እጅግ በጣም ከዳተኞች ናቸው ። ይህን ሁሉ የሚያደርጉት በዚያው ቀን ውስጥ ነው ።

ሆስነር ራሱን ነቅንቆ እኔ እንደማስበው ይህ የሰላም ተልዕኮ ግቡን እንዲመታ እነርሱም ይፈልጉታል ። ባግዳድ እዚህ መሆናችንን ካወቀ እርዳታ እንደሚሰጠን ተስፋ አለኝ " አለው ።

ዶብኪን እጁን በማራገብ እንደማያምን ከገለጸ በኋላ " ይህን ማለት እንዴት ይቻላል ? የሰላሙ ውይይት አስቀድሞ አከትሟል ። ይሁን እንጂ እኔ የፖለቲካ ሰው አይደለሁም ። በወታደርነቴ ስመለከተው በዚህ ቦታ እያለን እርዳታ ለመስጠት ለእነእርሱ በጣም ችግር ነው ። ይህን ያለጥርጥር አውቃለሁ " አለው ።

ሆስነር ቆመ ። በአውሮፕላኑ አቅራቢያ ደርሰዋል ። ሰዎች ቆመው በቡድን በቡድን ሆነው ይነጋገራሉ ። ድምጹን ዝቅ አድርጐ "ለምን ? " ብሎ ጠየቀው ።

ዶብኪን ለስለስ ባለ አንደበት " መልካም አሁን በመጨረሻ ባገኘነው መረጃ መሠረት ኢራቆች ብዙ የሄሊኮፕተር በረራ አያደርጉም ። የአየር ወለድ ወታደሮቻቸው ችሎታም ዝቅተኛ ነው ። በአሁኑ ወራት ወታደሮች የሚያመላልሱ በየብስና በባሕር ላይ የሚያርፉ አውሮፕላኖች የላቸውም ። ለበረሃ ጦርነት በሚገባ የታጠቁ ናቸው። ሆኖም በዚህ የጐርፍ ወቅት በጤግሮስና በኤፍራጥስ ወንዞች መካከል እረግረግ ፤ ጭቃና ምንጭ ስለሚበዛ እንደልባቸው መንቀሳቀስ አይችሉም ። በዚህ በጸደይ ወራት በሜሶፖታሚያ ውስጥ ብዙ ወታደሮች በሥራቸው ላይ ችግር ይፈጠርባቸዋል " ብሎ በዝርዝር ነገረው ።

" ተዘዋዋሪ የሆነ እግረኛ ወታደርስ ? እነእርሱም አይሠሩም ይሆን ? "

ዶብኪን ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። " አዎን ፣ ተዘዋዋሪ እግረኛ ጦር ሊያገኘን ይችላል ። ግን ብዙ ጊዜ ይፈጃል ። ከዚህ በደቡብ በኩል አንድ ትንሽ ሂላ / የምትባል ከተማ አለች ። ግን በዚያ የወታደሮች

የጦር ሠፈር እንዳላቸው አላውቅም ። ወደዚህም መጥተው ሊያገኙን ቢችሉ ለፍልስጥኤማውያኖቹ ይረዱ ይሆን ? ”

“ ይህ የምንነጋገረው ከራሳችን ውጭ ለሌላ አይነገርም ። ”

“ ወታደራዊ ምሥጢር ቁጥር አንድ ነው ። አሁን ደግሞ ስለወታደራዊ ምሥጢር ቁጥር ሁለት እነግርሃለሁ ። የተፈናቀሉ ፍልስጥኤማውያን ሙሉ በሙሉ ያሉበት የኢራቅ ክፍለ ጦሮች አሉ ። ታማኝነታቸውን ለመግለጽ ሲሉ የአገራቸውን ልጆች እንዲወጉ የሚያዘውን የኢራቅ ወታደራዊ የጦር አዛዥ መሆንን እጠላለሁ ። ነገር ግን የሁሉም ሞራል እንዲወድቅ አንፈልግም ። ለሕዝብ የሚነገር አይደለም ።”

ዶብኪንና ሆስነር ወደ ኮንኮርዱ ሔደው አፍንጫው አጠገብ ቆሙ ። ከዚያ ጥቂት ሜትሮች እልፍ ብሎ ሊመቱት የነበር አንድ ጉች ያለ ነገር ነበር ። የፈረሰ የበግ እረኛ መጠለያ ይመስላል ። ቀርበው ባዩት ጊዜ ሆስነር እንደመሰለው ድንጋይ ወይም ሌላ ነገር አልነበረም። የተቃጠለ ሸክላ — የሜሶፖታሚያ የተቃጠለ ሸክላ — ነበር ። ጣሪያው በአንድ በኩል ከተምር ዛፍ የተሠራ ነበር ። ሆስነር ወደ ውስጥ ሲመለከት በከፊል የፈረሰውን ግድግዳ አየ ። ወንዶችና ሴቶች በውስጡ ቆመው ያወራሉ ። ይህ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ስብሰባ ነበር ።

ሆስነር በጨለማው ውስጥ ወደሰማው ድምጽ ዞረ ። አብዛኞቹ ተሳፋሪዎች በአውሮፕላኑ ክንፍ ሥር ቆመው አያቸው ። ቄሱ የሰንበት ሥርዓት የጀመረው ዘግየት ብሎ ነው ። ያአኮቭንና አብረው የነበሩትን ሁለት አስተናጋጆች ሆስነር በጥላቸው አወቃቸው ።

ሆስነር በአውሮፕላኑ ሥር አንድ ነገር ሲንቀሳቀስ ተመለከተ ። ፒተር ካን በድንገት ዘሎ ከተጨራመተው አውሮፕላን አፍንጫ ውስጥ ወጥቶ ይዞት የነበረውን የእጅ መብራት በፍጥነት አጠፋው ።

ዶብኪን ወደ እርሱ ተጠግቶ “ እንዴት ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ መጥፎ ። ”

“ መጥፎው ምንድን ነው ? ” ብሎ ሆስነር ጠየቀው ።

ካን ወደእርሱ ተመልክቶ ፈገግ ካለ በኋላ “ አንተ ያመጣኸው ጣጣ ነው ፤ ሆስነር ” አለው ።

“ እኮ መጥፎው ምንድን ነው ? ”

“ ረዳት የኤሌክትሪክ መስጫው ኮንኮርዱ በሚያርፍበት ጊዜ በደረሰበት መጨረማመት አብሮ ተጐድቷል ። ”

“ ታዲያ ምን ይሁን ፤ ከአሁን በኋላ ልንጥለው ነው ? ”

ካን ራሱን አስገድዶ ፈገግታ በማሳየት “ ከመቶ ሊትር በላይ የሚ ሆን ያልፈሰሰ ነዳጅ ስለአለ የኤሌክትሪኩ ኃይል እንዲሠራ ካደረግ ነው በራዲዮ መልዕክት ማስተላለፍ እንችላለን ። ባትሪዎቹ ለብዙ ጊዜ ሊሠሩልን አይችሉም ” አለው ።

ሆስነር በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ ። ለእነርሱ ለብዙ ጊዜ ማለት በሰዓታት የሚቆጠረውን ነው ። ለማንኛውም ባትሪዎቹ በቂ ናቸው ።

“ ካፒቴኑ የት ነው ? ”

“ በአብራሪዎቹ ክፍል ውስጥ ነው ። ”

ሆስነር አንጋጦ በመስኮቱ መካከል ሲመለከት አረንጓዴ ብርሃን አየ ። የቤከርን ሃሣብ ለማወቅ ስለፈለገ “ ላነጋግረው እፈልጋለሁ ፤ ” አለው ለዶብኪን ።

ዶብኪን ወደ እረኛው ጐጆ እያመለከተ “ የውጭ ጉዳይ ሚኒስ ትሩ ሊያነጋግርህ ይፈልጋል ” አለው ።

“ አሁን አይሆንም ። ”

“ መሔድ ይኖርብናል ብየ እኔም አምናለሁ ። ”

በመካከላቸው ረዘም ያለ ጸጥታ ከሰፈነ በኋላ ሆስነር አሽቅቦ ወደ በረራ ክፍሉ ቀጥሎም ወደ ጐጆው ተመለከተ ። ካን ሁኔታቸው ደስ ስላላለው ትኳቸው ዘወር አለ ። “ በእጅ ሻንጣዬ ውስጥ የአህመድ ሪሽ ፎቶ ግራፍና ስለእርሱም ሁኔታ የጻፍኩት ማስታወሻ ስለአለኝ አሁን ማግኘት እፈልጋለሁ ። ”

ዶብኪን ካቅማማ በኋላ “ ደህና እንደምገምተው . . . ” ካለው በኋላ በድንገት በመደነቅ “ ለምን ብለህ ይዘኸው መጣህ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ ያጋጣሚ ጉዳይ ነው ። ”

“ በእውነት ያዕቆብ ፤ በጣም ነገሩ አስደስቶኛል ፤ አስገርሞኛ ልም ። በጠየከው መሠረት ፈልገው ያመጡልሃል ። ”

ሆስነር በክንፉ በኩል ዘሎ ገብቶ ወደ ድንገተኛ መውጫው በር ሔደ ።

ተሳፋሪዎች የሚቀመጡበት ክፍል ጨለማ ነበር ። ወደ አብራሪ ዎቹ ክፍል በሚያስገባው በር መካከል ግን አረንጓዴ ብርሃን ታየው ። የመቀመጫ ቀበቶና የማጤስ ምልክት የሚሰጠው መብራት አል ጠፋም ። ክፍሉ ጋዝ እንደፈሰሰበት አይነት ይሸታል ። የእጅ

ቦርሳዎች ፣ ብርድልብሶችና ትራሶች በያለበት ተበታትነዋል ። በስተኋላ በኩል የቁስ ሌቪን ድምጽ በግልጽ ይሰማ ነበር ።

ወደ ውስጥ ሲገባ ቤከር አረንጓዴ መብራት የሚያሳየውን ራድዮ ሲያስተካክል አገኘው ። የሚንጫጫ ድምጽ ያሰማል ። ሙሴ ሔስ በዚያው በሞተበት ቦታ ላይ አለ ። ቤከር ዝቅ ባለ ድምጽ ይነጋገር የነበረው ወደ ራዲዮኑ ሳይሆን ለሔስ መሆኑ ሆስነር የገባው በመጨረሻ ነበር ። ሆስነር ጉሮሮውን አፍታቶ "ዴቪድ" አለው ።

ቤከር ከራሱ ዘወር ቢልም አልተናገረም ። ተመልሶ ወደ ራዲዮኑ ተመለከተ ።

ሆስነር በወንበሩ ላይ ተቀመጠ ። ሆኖም የሔስ በድን በዚያ ተጋድሞ መቀመጡ ሰላም ነሳው ። "የማይረሳ ሥራ አከናውነሃል ሔስ" አለ ሆስነር ነፍስና ሥጋው ለተለያየው በድን ። ቤከር እንደገና ራዲዮኑ የሚሠራ ወይም የማይሠራ መሆኑን ለማረጋገጥ ድግግሞሹን መነካካት ጀመረ ። ሆስነር በመቀመጫዎቹ መካከል ሲያልፍ እግሩን የሔስ ሰውነት ስለነካው ወደኋላ ተመልሶ ተራመደ ። እርሱ እንደሚያስበው ከሆነ በአሥር ደቂቃ ውስጥ መቀበር አለበት ። ችግሩ ግን ቁሱ በሰንበት እንዲቀበር አይፈቅድም ። መቆየቱ ለጤንነት ጠንቅ እንደሚሆን ሆስነር ወይም ሌላ ሰው በቂ ምክንያት ሰጥቶ ካላሳመነ በስተቀር እስከ ነገ ማታ ድረስ የሔስ አሬሳ አይቀበርም ።

በመጨረሻም ሆስነር "ከዚህ አወጣዋለሁ ፤ ዴቪድ" አለው ።

"እንደፈለግህ ።"

የራዲዮኑ የጫጫታ ጩኸት ክፍሉን ሞላው ።

ቤከር ተራግሞ ራዲዮኑን ዘግቶ አስቸኳይ የኃይል መስጫውን ሲያጠፋው ደካማው ብርሃን ስላቆመ ክፍሉ በጨረቃ ብርሃን ተሞላ ።

"ያ ጀብደኛ አሁንም ለመነጋገር እንዳንችል መስመሩን የማዕበል ሞገድ እየሰደደበት ነው ። አሁን ካለበት ቦታ ሆኖ ምንም ዓይነት ጥሩ ሥራ ሊሠራ አይችልም ። እርሱ ግን እየሞከረ ነው ።"

"ከሰዎች ጋር ለመገናኘት ምን ዓይነት ዕድል ይኖረናል ?"

"ማን ያውቃል ?" ብሎ ቤከር ወደኋላው ተለጥጦ ሲጋራውን አቀጣጠለ ። "የራዲዮኑ ከፍተኛ ሞገድ ፍጹም ጸጥ አለ ። እንዲሠራ ካደረግነው እንደ አየሩ ሁኔታ ከየትኛውም ዓለም ጋር መገናኘት እንችላለን ። በጣም ከፍተኛው የራዲዮ ሞገድ ደህና እየሠራ ስለሆነ በዓ

ለም አቀፍ በድንገተኛ ጥሪ ማስተላለፊያ በሆነው 121.5 እያሰራጨሁ ነው ። እንደዚሁም በመጨረሻው የኤል አል ሞገድ ላይም እያሰራ ጨሁ ብሆንም የአንድ ሰው ድምጽ እንኳን መስማት አልቻልኩም ። መልስም አላገኘሁም ። ”

“ ምክንያቱ ምንድን ነው ? ”

“ መልካም ፤ በጣም ከፍተኛ የራዲዮ ሞገድ የሚሠራው ትይዩ በሆነ መስመር ብቻ ነው ። እዚህ ሆነን ባይታየንም እኛ ካለንበት ቦታ ከፍ ያሉ ተራራዎች አሉ ብየ እገምታለሁ ። ”

“ አሉ ። ”

“ በተጨማሪም የባትሪዎቹ ኃይል ከጄኔሬተር እንደሚገኘው ኃይለኛ አይደለም ። ሌላው ደግሞ መርሳት የሌለብን ሬሽ ያለማቋረጥ በሁሉም መስመሮች ላይ ኃይል ባለው ማስተላለፊያ እያሰራጨ መሆ ኑንና ሞተሩና ጄኔሬተሩም ያለማቋረጥ እንዲሠራ ሊያደርግ ይችላል።” ቤከር ወደ ውጭ የተነፈሰው የሲጋራ ጢስ እንደ አመልማሎ እየ ተጥመለመለ ወጣ ። “ እንግዲህ ለምን አይሆንም ለተባለው ጥያቄ መልሱ ይህ ነው ። ”

“ ደህና ” ካለው በኋላ ሆስነር በመስታወቱ መካከል ትኩር አድርጐ ሲመለከት ከበታቹ ባለው ጉጆ ውስጥ ሰዎች ሲርመሰመሱ አየ ። “ ምናልባት ከበላያችን የሚበር አውሮፕላን በድንገት ቢመጣ ያለምንም ችግር ግንኙነት ማድረግ እንችላለን ፤ ልክ ነኝ ? ”

“ ልክ ነህ ፤ የምንመኘው አንድ አውሮፕላን በእኛ ላይ ሲበር ማግኘት ብቻ ነው ። ”

ሔስን መትቶ የገደለው የሸክላ ድንጋይ በደም ተበክሎ በወለሉ ላይ ሆስነር አየው ። በመስመሩ ላይ በነበረው አረንጓዴ መብራት በቀ ድሞ ዘመን በሸክላው ላይ የተቀረጸውን ተመለከተ ። ጽሑፉን ሊያነ ው ባይችልም የሚለው በአብዛኞቹ የባቢሎን ሸክላዎች ላይ የተጻ ፈው እንደሚሆን እርግጠኛ ነበር — ናቡከደነጾር ፤ የባቢሎን ንጉሥ ፤ የናቦፖላሰር ልጅ የባቢሉን ንጉሥ —

ሆስነር ሸክላውን መመልከቱን አቁሞ “ በዚህ ኮንኮርድ ላይ አንድ ሰው ቆሞ አውሮፕላን ሲመጣ እንዲያይ አደርጋለሁ ። ሰውየው እንደ አየ አንተ እንድታውቀው የሚያደርግ ምልክት እንዲሰጥህ ዘዴ እንፈጥራለን ” አለው ።

“ ድምጽ ማሰማቱ ጥሩ ነው ። ”

የበረራ እረዳቱ የነበረውን የሔስን ሬሳ ለብዙ ጊዜ ከተመለከተ በኋላ ወደ ሆስነር ዞሮ “ ካን አሁንም የኃይል መስጫውን ለማስተካ ከል እየሞከረ ነው ” አለው ።

“ አይቸዋለሁ ፤ እርሱ እንደሚለው መጥፎ ይመስላል ። ባትሪ ዎቹ ለምን ያህል ጊዜ ይቆያሉ ? ”

“ በእውነቱ ከሆነ ለመናገር አስቸጋሪ ነው ። ለመቆጣጠር ብጥ ርም ለማስተላለፍ በምሞክርበት ጊዜ ሁሉ የባትሪው ውሀ አብሮ ይመ ጠጣል ። ባትሪዎቹ የነሐስ ማሠሪያ ስላላቸው ጥሩ ናቸው ። ችግሩ ግን ማለቃቸውን የሚያሳይ ማስጠንቀቂያ አይሰጡም ። እስኪአቋርጡ ድረስ ጥሩ አገልግሎት ይሰጣሉ ።

ሆስነር ስለገባው ራሱን ነቀነቀ ። ነገሩ አስጨንቆታል ። ብሪን በሚጠቀምበት ጠመንጃ ላይ የገጠመው የኮከብ ብርሃን መነጽር ባት ሪዎቹ የነሐስ ማሠሪያ አላቸው ። “ ካን የጀመረው የኃይል ማስተካ ከል ቢያልቅ በኤሌክትሪኩ በመጠቀም ባትሪዎቹ እንዳይሞቱ ማድ ረግ ጥሩ አይመስልህም ? ”

ቤከር እጁን በጸጉሩ ላይ አፋትጉ “ እንጃ ፤ ከአሁን በኋላ የምን ሠራው ሁሉ ችግር እያስከተለ ሊመጣ ይችላል ። ስለዚህ አንተ ያል ከውን አሁን በትክክል ስለማላውቀው አስብበታለሁ ” አለው ።

“ እሺ ” ብሎ ወንበሩን ይዞ በመነሳት ወደፊት ተራምዶ “ በኋላ አይሃለሁ ” አለው ።

ቤከር እንደተቀመጠ ዞሮ “ ልትሠራው ነው ? ” አለው ።

“ ያለጥርጥር” ብሎት ሻንጣው ወደተቀመጠበት ሔደ ። ሆስነር በክንፉ በኩል ዘሎ ከወጣ በኋላ የሰንበት ጸሎት እንደተፈጸመ አየ ። አብዛኞቹ ወንዶችና ሴቶች ወደየሥራቸው ሔዱ ። ወደእረኛው ጉጆ ከሔዱት ጥቂት ሰዎች ውስጥ ቄስ ሌቪን ነበረበት ። ሆስነር ወደ እርሱ ራመድ ብሎ “ ሙሴ ሔስን መቅበር እንችላለን ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ አይሆንም ። ”

“ ለመከላከያ የሚሆነንን ምሽግ መሥራት እንፈልጋለን ። በሰ ንበት ቀን በመሥራታችን ትቃወማለህ ? ”

“ አዎን ። ”

በእረኛው ጉጆ አጠገብ ቆሙ ። ጥቂቶቹ ከሰንበት ጸሎት ተመ ልሰው በአጠገባቸው ወደ ጉጆው አለፉ ። ሆስነር ወደ ቄሱ ተመል

ክቶ “ በአንድነት አብረን እንሠራለን ወይስ እንለያያለን መምህር ? ” አለው ።

የጸሎት መጽሐፉንና ቆቡን በካፖርቱ ኪስ ውስጥ አስገብቶ “አንተ ወጣት ሰው ፤ ሃይማኖቶች በተፈጥሮአቸው ከሥጋዊ ጥቅሞች ጋር ግጭት ያደርጋሉ ። በእርግጥ ሙሴ ሔስ ዛሬ ማታ መቀበር ይገባዋል ። የመከላከያ ምሽጐች ሥራም መጀመር ይኖርበታል ። ይህ አስታራቂ ሃሣብ ነው ብየ አምናለሁ ። የእኔ ተቃውሞ እንዳለ ሆኖ እያንዳንዱ እንዲሠራ እዘዝ ። የሙሴ ሔስ ሬሳ በእኔ ቁጥጥር ሥር ሆኖ እንዳይቀበር እከለክላለሁ ። እስራኤል ከ1948 ጀምሮ የተቀበለቻቸው እነዚህን ዓይነቶች አስታራቂ ሃሣብ ነው ” አለው ።

“ መጥፎዎች ናቸው ። ይህ ሁሉ ግብዝነት ነው ። ለአሁኑ በራስህ መንገድ ተጠቀም ” ብሎት ሆስነር ወደ ጐጆው በር ተራመደ ።

ቄስ ሌቪን የሆስነርን ክንድ ይዞ ወደኋላ በመሳብ “ አንድ ጊዜ ስማኝ ፤ መኖር ሁልጊዜም የጅልነት ፥ የግብዝነትና የመቻቻል ቅልቅል ነው ” አለው ።

“ ለዚህ ነገር ጊዜ የለኝም ። ”

“ ቆይ ፤ አንተ እንግሊዞችን አድናቂ ነህ ፥ ሆስነር ። እንግሊዞች በጦርነት መካከል ውጊያ አቁመው በአሥር ሰዓት ሻ... አንደሚጠጡ አስደንቆህ ያውቃል ? ወይም በምቃት... ለራት ግብዣ የሚሆን ልብስ ለምን እንደሚለብሱ ? ”

“ ባህላቸው ነው ። ”

“ ለሞራላቸው ... ነው ፤ ለሞራላቸው ጥሩ ነው ” ብሎ በመ... ...ረት መታ አደረገው ። “ በማይወዱን አረቦች ተከድገም የሆስ... ...ሮን ተራራ ላይ በመቀመጣችን ምክንያት ሰዎቻችን ያለቁ በን...ተር እንደፈለጉ እንዲያደርጉ አንፈልግም ። ስለዚህ የየቀኑን ሥራ በየቀኑ እንሠራለን ። የሰንበት ጸሎት እናደርጋለን ። በሰንበት ቀን ሙታኖችንን አንቀብርም ። በሰንበት ቀን አንሠራም ። እንሽላሊቶች ወይም መሰሎቻቸውን እንድንበላ አንገደድም ። ምክንያቱም በሕጋችን መሠረት እንሽላሊቶች የሚበሉ አይደሉም ፤ ያዕቆብ ሆስነር ” በማለት እንደገና ከበፊቱ ጠንከር አድርጐ በልቡ ላይ መታ ካደረገው በኋላ “የሌሎች ሃይማኖት ሕጐችን አንቃወም ” አለው ። ከሆስነር ሸሚዝ ላይ አቧራውን አራግፎ “ወታደሮች በጦርነት ጊዜ በየቀኑ ጢማቸውን ለምን እንደሚላጩ ጄኔራል ዶብኪንን ጠይቀው-ለሞራል ነው ፤ ያዕቆብ ሆስነር ። ቅርጽ ፥ ባሕል ፥ ሥልጣኔ — ይህም ቡድኑ ሥራውን

በንቃት እንዲከታተል ይገፋፋዋል ። ወንዶቹ ጢማቸውን እንዲላጩ ፣ ሴቶቹ ጸጉራቸውን እንዲያበጥሩና ከንፈሮቻቸውን ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ ይገባሃል ። ሁሉም ነገር የሚመነጨው ከዚያ ነው ። የወታደር ቄስ ሆኜ ሠርቻለሁ ። ይህን ሁሉ አውቃለሁ ” አለው ።

ሆስነር ፈገግ ብሎ “ የሚያስደስት ንድፈ ሃሣብ ነው ። እኔ የጠየኩህ ለሥራ መሠማራት እንችል እንደሆነ ነው ” አለው ።

“ እኔ ስለሃይማኖት ሕግ አንተ ደግሞ ስለወታደራዊ ጥቅም አውራ ፣ አድንቅም ። ሰዎች የየራሳቸውን ምርጫ ይወስዳሉ ። የእርስ በእርስ ጭቅጭቅ ሁልጊዜ መጥፎ አይደለም ። ምክንያቱም በተስፋ መቁረጥ ላይ ያሉት ሰዎች ስለጥቃቅን ነገሮች ሲወያዩ ችግራቸውን ያስረሳቸዋል ። እኔና አንተ በተራ ነገር ላይ እንንዛንዛለን ። በግላችንም እንስማማለን ። በሰንበት ቀን ስብሰባውን እካፈላለሁ ። የማሰብ ችሎታ ያለኝ ሰው ነኝ ። ገባህ ? ” ብሎት ወደ ጐጆው ሔደ ።

ሆስነር ቆሞ ቄሱን በአንክሮ ተመለከተው ። የቄሱን የአስተሳሰብ ዘይቤ ሊከተለው አልቻለም ። ምክንያቱም ያቀረባቸው ሃሣቦች ድብልቅ ይዘት ኖሯቸው የተጣመመ አስተሳሰብን ያቀፉና ለመልካም ዕርምጃ በግልጽ የሚደረጉ የአይሁዳዊ አመለካከትን የቀላቀሉ ዓይነት ስለነበሩ ቄሱ የሚናገረው ለራሱ እንኳን የገባው አይመስልም ። ቄሱ ከሴቶች ትክክለኛ አመለካከት ካላቸው ሰዎች ውጭ መሆኑ በግልጽ ቢያስታውቅም ያለው ግን ስሜትን ሊነካ የሚችል ነገር ነበር ።

ሆስነር ወደ ጐጆው ውስጥ በገባ ጊዜ አሥራ አምስት ያህል ሰዎች ቆመው ዝቅ ባለ ድምጽ ይነጋገሩ ነበር ። እርሱ እንደገባ ሁሉም ንግግራቸውን አቁመው ወደ እርሱ ዞረው ተመለከቱ ። እበሩ ላይ ለትንሽ ጊዜ ቆም አለ ። በተምር ዛፉ መካከል የ[illegible] የጨረቃ ብርሃን ቆሞበት በነበረው ቦታ ላይ አበራ ። አሪኤል ዌይዝማን [illegible] ጉዳይ ሚኒስትሩ ትንሹን ክፍል አቋርጦ በመምጣት እጁን ይዞ “ አበ[illegible] ሥራ ሠርተሃል ፣ ሆስነር” አለው ።

“ ቦምቦቹ በአውሮፕላኑ ውስጥ እንዲጫኑ በመፈቀዱ ማለትህ ነው ፣ ሚኒስትር ? ”

ዌይዝማን በጨረቃው ብርሃን ተጠግቶ ካየው በኋላ በለሰለስ አንደበት “ ያዕቆብ፣ ይበቃል ፣ ስለዚያ ማንሳት አያስፈልግም ” ካለው በኋላ ዙሪያውን ተመልክቶ “ ስብሰባችንን እንጀምር ፣ አሁን እዚህ ያለነው ሥራችንን በትክክል እንድናውቅና ተግባራዊ ለማድረግ ያለንን ዕድል ለመነጋገር ነው ” አላቸው ።

ሆስነር ያንጠለጠለውን የእጅ ሻንጣ አስቀምጦ ለምክር ቤቱ ‘‘ጎላት እንደሚሰጥ ዓይነት ንግግር ወደሚያደርገው ሚኒስትር ተመለከተ ።

ካፕላን በግድግዳው አጠገብ በላቡ ተጋድሟል ። ከወገቡ በታች የኤል አል ሰማያዊ ብርድ ልብስ ለብሷል ። በደም የተነከረው ሱሪው በአጠገቡ ተቀምጧል ። ሁለት አስተናጋጆች ቤተ አብራምስና ራሄል ባሉም ካፕላንን እየተንከባከቡ ነበሩ ። የኤል አል የወንዶችና የሴቶች አስተናጋጆች መጠነኛ የሕክምና ሙያ ስላላቸው ሆስነር ደስ ብሎታል ።

አስሩ የሰላም ተልዕኮ አባላት በስብሰባው ላይ ነበሩ ። ከእነእርሱ ውስጥ ሁለቱ አረቦች ማለትም አብደል ጃባሪና ኢብራሂም ይገኙበታል ። ሚሪያም በርንስቴይን በተሰነጠቀው ግድግዳ አጠገብ ቆማ ስለነበር በጨረቃዋ ብርሃን ጥሩ ሆና ስለታየችው ሳያውቀው ትኩር አድርጎ ተመለከታት ።

ምርኮኛው አረብ እጅና እግሩን ተጠፍሮ በግድግዳው ማዕዘን አጠገብ ተቀምጧል ። ሆስነር በመታው ፊቱ ላይ ደሙ ደርቆ ተጉረብርቧል ። በትከሻው ላይ ከተመታው ቁስሉ የፈሰሰው ደም ሸሚዙን በክሎታል ። አንድ ሰው ሸሚዙን ቀዶ ሕክምና አድርጎለታል ። በከፊል የተኛ ወይም ያንጐላጀ ይመስላል ።

እያንዳንዱ ሰው እየተነሳ ያደረገውን ንግግር ሆስነር አደመጠ ። ስብሰባው ልክ የእስራኤል ምክር ቤት የዘወትር ስብሰባ ዓይነት ክርክር ፣ የሥነ—ሥርዓት አከባበር ፣ ድምጽ አሰጣጥ የመሳሰሉት ይካሔዱ ነበር ። እዚያ ለምን እንዳሉ ፣ ለመዋጋት ለምን እንዳስፈለገ ወይም ምን መደረግ እንደሚገባው ተወያይተው መወሰን እንኳን አልቻሉም ። ለጊዜው የሆስነር አምስት ሰዎች ከጥቂት ፈቃደኞች ጋር በጣም ረጅም የሆነውን ክልል በመጠበቅ ላይ ናቸው ። ዲሞክራሲ ለሥራ ወይስ ላለመሥራት የሚለውን ጥያቄ ያስከትላል ። ቸርችል አንድ ወቅት ዲሞክራሲ ለብዙሃኑ ሊሆን ካልቻለ እጅግ በጣም መጥፎ ዓይነት የመንግሥት ቅርጽ ነው ያለው ትዝ አለው ።

ዶብኪን ትዕግሥቱ በአፋፍ ላይ እንደደረሰ ሆስነር ተመልክቶ ስለነበረ አቋርጦ ‘‘ ለእስረኛው ጥያቄ ያቀረበለት አለ ? ’’ አላቸው ።

በአንድ ጊዜ ጸጥታ እረጭ አለ ። ይህ ሰው ለምንድን ነው ተራውን ሳይጠብቅ የተናገረው ? እስረኛው ከዚህ ጋር ምን ግንኙነት አለው ? የምክር ቤት አባል የሆነው ቼይም ታሚር ተዝናንቶ እንቅልፍ

የወሰደውን እስረኛ አቆልቁሎ እየተመለከተ “ ሞክረናል ። ግን ለመ ናገር ፈቃደኛ አይደለም ። በተጨማሪም ክፉኛ ቆስሏል ” አለው ።

ሆስነር ወደተኛው እስረኛ ሔዶ በእርግጫ ሊመታው ላይ ሲያቀም ሰው ከአንዱ አረብና ከጥቂት ሰዎች የ—ደነቅ ድምጽ ተሰማ ። ሆስነር ዙሪያውን ተመልክቶ “ እያችሁ ሴቶችና ወንዶች ፤ በዚህ ክፍል ውስጥ ዋና ተናጋሪ መሆን ያለበት ይህ ወጣት ሰው ነው ። በሌላ በኩል ስለአ ላቸው ወታደራዊ ኃይል የሚሰጠው አስተያየት የዕድላችን ወሳኝ ነው ። ይህን ሰው ወደ እናንተ ለማምጣት ሕይወቴን ሰውቻለሁ ። እናንተ ግን እርስ በእርሳችሁ ትጨቃጨቃላችሁ ” አላቸው ።

በርግና ዶብኪን እንደተደሰቱና ጉጉትም እንዳደረባቸው ሆስ ነር አጢኗል ። ማንም የተናገረ ስላልነበረ ንግግሩን በመቀጠል “ ይህ ወጣት የሚነግረን መጥፎ ዜና ከሆነ ለሁሉም መዳረስ የለበትም ። ስለዚህ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ፤ ከዶብኪንና ከበርግ በስተቀር ሌሎቹ ከዚህ ክፍል እንዲወጡ ሃሣብ አቀርባለሁ ” አላቸው ።

ክፍሉ በቁጣ ጩኸት ተሞላ ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጸጥታ እንዲሰፍን ካዘዘ በኋላ ወደ ጄኔ ራል ዶብኪን ሲዞር የጥያቄ መልክ ነበረው ።

ዶብኪን ራሱን በአወንታ ነቅንቆ “ በእውነት ቀደምትነት የሚ ሰጠው ሥራ ነው ። እስረኛው በምንም ዓይነት ሁኔታ ላይ ቢገኝ መጠ የቅ አለብን ። ይህንንም ያለምንም መዘግየት ማድረግ አለብን ” አላ ቸው ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በንግግሩ ተደንቆ “ ታዲያ እስከ አሁን ለምን አልተናገርክም ጄኔራል ? ” አለው ።

“ እስረኛው ተጐድቶ ነበር ፤ አስተናጋጅዋም የሚያደነዝዝ የሕ መም ማስታገሻ ሰጠችው ። በመሃከል አንተ ደግሞ ይህን ስብሰባ ጠራህ ። ”

ሆስነር ወደ በርግ ዞሮ “ ትጠይቀዋለህ ? ” አለው ።

በርግ ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ የሰለጠንኩበት ሥራ ነው ” ብሎ ፒፓውን አቀጣጠለ ።

እስረኛው አረብ ውይይቱ ስለእርሱ እንደነበረ ስለገባው አልተ ደሰተም ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ራሱን ነቅንቆ “ እኛ ስብሰባችንን በሌላ ቦታ እንቀጥላለን ። እናንተን እዚህ ከእስረኛው ጋር ትተናችሁ እንሔዳለን በርግ ” አለው ።

በርግ የተባለውን ተቀበለ ።

የቀሩት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ተከትለው ሲወጡ ቁጣ በፊታቸው ላይ ይታይ ነበር ።

ሚሪያም በርንስቴይን በያዕቆብ ሆስነር ፊት ቆማ ቀና ብላ ስትመለከተው ጀርባውን ስለሰጣት እጁን አፈፍ አድርጋ ከግማሽ ጐኑ ወደ እርስዋ እንዲዞር በማድረግ “ አንተ ማነኝ ብለህ ታስባለህ ? ” ብላ ጠየቀችው ።

“ አንቺ እኔ ማንና ምን እንደሆንኩ በሚገባ ታውቂያለሽ ። ”

ቁጣዋን ለመቆጣጠር እየሞከረች “ ሆስነር ፤ የመጨረሻዎቹ ግብ የማድረስ መብት የላቸውም ” አለችው ።

“ ዛሬ ማታ ያደርጋሉ ። ”

እረጋ ብላና በአጭሩ “ ስማ ፥ ከዚህ በሕይወት ከወጣን ርጎራጌና የራስ ክብር ምን እንደሆነ ታያለህ ። በአጭር ጊዜ ውስጥ የተደረገውን ዲሞክራሲያዊ ስብሰባ በትነሃል ። ቁስለኛውንም ሰው ለማሰቃየት ፈቃድ ተሰጥቶሃል ” አለችው ።

“ እኔን ያስገረመኝ ብዙ ጊዜ ስለወሰደብኝ ብቻ ነው ” ብሏት ሲጋራውን ካቀጣጠለ በኋላ ንግግሩን በመቀጠል “ ስሚ ሚሪያም ፥ በዙሪያችን ከፍተኛ አደጋ እያንዣበበብን ነው ። ምናልባትም ከአሁን ጀምሮ ጥቃት ሊደርስብን ይችላል ። ከወታደሮቹ በስተቀር እናንተ በአዕምሮአችሁ ውስጥ የምታዩት ላይ ላዩን ነው ። ይህን ተራራ ወደ እስር ቤት የምለውጠው ቢሆንም ሕዝባችንን ከአደጋ ማዳን አለብኝ ” አላት ።

በጥፊ እፊቱ ላይ በኃይል ስትመታው በአፉ የያዘው ሲጋራ እረገፈ ።

በክፍሉ ውስጥ ቀርተው የነበሩት ሰዎች ጥፊውን እንዳላዩ ሆነው ጸጥ አሉ ።

ሆስነር ጉሮሮውን አፍታቶ “ በርግ የሚሠራው ሥራ ስለአሏው እያስተጓጐልሽው ስለሆነ እባክሽ ክፍሉን ለቀሽ ሒጂ ” ስላላት ወጥታ ሔደች ።

ሆስነር ወደ ዶብኪን ዞሮ “ አካባቢያችንን ከፈተሸን በኋላ እን ዴት እንደምንሰለፍ እናያለን ” ብሎ ክፍሉን አቋርጦ በመሔድ “ ይስሐቅ አንድ ተጨባጭ ነገር እንዳገኘህ አንድ ሰው በሩ ጋ መጥቶ እንዲነግረን “ አለው ። ቀጥሎም በወለሉ ላይ ወዳስቀመጠው የበረራ ሻንጣ እያመለከተ ” ስለሪሽ ገጽታዎች አንዳንድ የጻፍኳቸው ነገሮ ችና ፎቶግራፉ በማስታወሻዬ ውስጥ ስለአሉ በጥንቃቄ ያዛቸው ” አለው ።

በርግ ትኩር አድርጎ የበረራ ሻንጣውን ከተመለከተ በኋላ ቀና ብሎ “ በእግዚአብሔር ስም ብለህ እንዴት — ” ብሎ ሳይጨርስ ሆስ ነር አቋርጦት “ እንዲያው በአጋጣሚ ነው ፤ ሌላ ነገር የለውም ” ብሎ ከነገረው በኋላ በካፕላን ጐን ተንበረከከ ። ምናልባትም በማደን ዘዣው ምክንያት ሊሆን ይችላል የተኛ ይመስላል ። ጥያቄም ቢቀርብ ለት የሚሰማ አይመስልም ። “ ሞሼ ፤ ደህና ነህ ? እንድንወስድህ ትፈልጋለህ ? ” ብሎ ሆስነር ጠየቀው ።

ካፕላን ራሱን በአሉታ ነቅንቆ “ ቀደም ብየ አይቸዋለሁ ፤ ወደ ክልላችን ድንበር ሔዳችሁ ካያችሁ በኋላ ከጥሩ የመከላከያ ዘዴ ጋር ተመለሱ ” ብሎ በደከመ ድምጽ ነገራቸው ።

“ ምን ዓይነት ሌላ መከላከያ ያለ ይመስልሃል ፤ ሞሼ ? ”

“ ሌላ ዓይነት የለም ። ”

ሆስነርና ዶብኪን እንደወጡ ከጐጆው ውስጥ አየር የሚሰነጥቅ ኃይለኛ ጩኸት ተሰማ ። የብሪን የመጀመሪያ ተኩስ ከሆነ እንዲዋጉ ያደረጋቸው ፤ አረቡን ማሰቃየት ሁለተኛ እጃቸውን እንዳይሰጡ ቃል እንዲገቡ ያደርጋቸው ይሆን ? ብሎ ሆስነር አሰበ ። እነእርሱ ከአደ ረጉት የበለጠ እንክብካቤ ከሌላው ሊጠብቁ አይችሉም ። ወደኋላ ለመ መለስ የሚያስችል መንገድ የለም ።

በወንዙ በኩል ወዳለው ተራራ ሔደው ክልላቸውን እየተዘዋወሩ አንድ በአንድ ተመለከቱ ። በየአምሳ ሜትር ዕርቀት ላይ ወንዶችና ሴቶች በጥንድ ወይም በነጠላ ሆነው በመቆምና በመቀመጥ አቆልቁ ለው በኤፍራጥስ ወንዝ በኩል የሚመጣውን ይመለከታሉ ። ብዙዎቹ ረዳቶች ፣ ጸሐፊዎችና አነጋጋሪዎች ነበሩ ። ወደ ኒውዮርክ ለመሔድ ጓጉተዋል ። ምናልባትም ጥቂቶቹ ይሳካላቸው ይሆናል ። ሆስነር ለዶ ብኪን አስሩ መልዕክተኞች ከሌሎቹ ጋር በመቀላቀል እንዲጠብቁ ማድረግ ተገቢ ይሆናል በማለት አስታወሰው ። “ ይህ ለስብሰባ የሚ ያውሉትን ጊዜ ያሳጥርላቸዋል ” ብሎ ሲነግረው ዶብኪን ፈገግ አለ ።

መክለርና ሪቻርድሰን በአንድ በአሸዋ ክምር ላይ ተቀምጠው ሲጠብቁ አገኟቸው ። ሆስነር ወደ እነእርሱ ተጠግቶ “ ለእናንተም መጥፎ ዕድል ሆነባችሁ ” አላቸው ።

መክለር ቀስ ብሎ ቀና በማለት ካየው በኋላ “ በጣም መጥፎ ሊሆን ይችል ነበር ” አለው ።

ሪቻርድሰን ተነስቶ “ ሁኔታው እንዴት ነው ? ” ብሎ ጠየቃቸው።

“ ድፍንፍን ያለ ነው ” ብሎ ሆስነር መለሰለት።ነገሩን በአጭር ከነገራቸው በኋላ“ እናንተ ሁለታችሁ ነጭ ባንዲራ ይዛችሁ መሔድ ትፈልጋላችሁ ? ኰሎኔል የአሜሪካ አየር ኃይል ዩኒፎርም ለብሰሃል ። መክለርም እኔ ፡ እርግጠኛ ነኝ ፤ የአሜሪካ ኤምባሲ ሠራተኛ መሆንህን የሚያሳይ ትክክለኛ የመታወቂያ ወረቀት አለህ ። ሁለታችሁንም አደጋ እንደማይጥሉባችሁ በመጠኑም ቢሆን እርግጠኛ ነኝ ። በአሁኑ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን የአሜሪካን መንግሥት ማስኮረፍ አይፈልጉም ” በማለት ዘርዘር አድርጐ ነገራቸው ።

መክለር ራሱን በአሉታ ነቅንቆ “ የሚገርም አጋጣሚ ነው ። በአላሞ ጦርነት ላይ የተገደለ አንድ ትልቅ አጐት ነበረኝ ። በቁጥጥር ሥር በመዋል ምን አይነት ስሜት እንዳስከተለበት በመገረም ይናገር ነበር ። ለመማረክ የተሰጠውን ዕድል አለመቀበልና የሜክሲኮ ወታደሮች በዕድሞው ላይ እየዘለሉ እንደጐርፍ በሚተሙበት ጊዜ የነበረውን ሁኔታ ታውቅ የለም ? ያ ድብልቅልቁ የወጣ የውጊያ ወቅት ነበር ” አለው ።

ዶብኪን አነጋገሩ ምን ማለቱ እንደሆነ ገብቶታል ።“ የጥያቄው መልስ ይኸው መሆኑ ነው ? ”

ሆስነር ስቆ “ የምታስገርም ሰው ነህ ፤ መክለር ። ከእኛ ጋር ለመቆየት ምንም ችግር የለብህም ። በነገራችን ላይ በዚህ አካባቢ መሣሪያ ያለህ አንተ ብቻ ነህ ” አለው ።

“ አዎን ። ”

“ ጥሩ፤በዚህ አካባቢ አንድ ሰው የጩኸት ድምጽ ካሰማ ጥቂት የአውቶማቲክ መሣሪያ የያዙ ሰዎች እስክልክልህ ድረስ በዚያ በኩል ሆነህ ጥቂት ጥይቶች ተኩስ ” አለው ሆስነር ።

“ አደርጋለሁ ። ”

ሆስነር በመከለር ላይ እምነት አደረበት ። "በመሠረቱ በዚህ በኩል ጥቃት ያደርሳሉ ብየ አላስብም ።"

"ምናልባት ላይሞክሩ ይችላሉ"ብሎ መከለር ወደሰማይ በኋላም ወደ ሆስነር ተመልክቶ "ጨረቃዋ ከመጥለቅዋ በፊት ለመከላከያ የሚያስፈልገውን ሁሉ ብታደርግ በጣም የተሻለ ነው" አለው ።

"አውቃለሁ፤ ስለ አሳብህ አመሰግናለሁ ፤ መከለር" ካለው በኋላ ሆስነር ወደ ሪቻርድ ሰን ዞሮ "አንተም ኰሎኔል" አለው ።

"ቶም ብለህ ጥራኝ" አለው ሪቻርድሰን። "ስሙ፤እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ ። ግን ስምምነት ለመፍጠር መሞከሩ መልካም ይመስለኛል"ብሎ በእብራይስጥ ሲናገራቸው ሁለቱም በጣም ተደነቁ ።

ዶብኪን ወደ ሪቻርድሰን ተጠግቶ "ስምምነቱ ለምንድን ነው ? ጉዞአችን የሰላም ስምምነት ውይይት ለመክፈት ነበር ። በአሁኑ ጊዜ ግማሾቻችን አልቀናል ። ታዲያ ምን ዓይነት ስምምነት ማድረግ እንችላለን ?" ብሎ በዕብራይስጥ ነገረው ።

"ለማንኛውም ምክርህን ሰምተናል፤ ኰሎኔል ። እናመሰግናለን" አለው ሆስነር ።

መከለር በማያውቀው ቋንቋ በመነጋገራቸው ስሜት የሰጠው አል መሰለም ። በሁለቱ አሜሪካኖች መካከል አለመግባባት እንደነበረ ለሆስነር ተሰምቶታል ። ስህተቱም ያ ነበር ።

# — 12 —

ሆስነርና ዶብኪን የክልሉን ዙሪያ ጉበኙ ። ቦታው ሙሉ በሙሉ ሽሙልሙል ወይም የእንቁላል ቅርጽ ነበረው ። ዶብኪን እንዳለው ስፋቱና ቅርጹ ለእሽቅድምድም ሜዳ የተሠራ ይመስላል ። ዶብኪን የመሬቱ አቀማመጥ ምናልባት በተፈጥሮ ላይሆን ይችላል ባለው ሆስነርም ተስማማ ። የተራራው ጫፍ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ሜዳ ነው ። ምናልባትም ሰው ሠራሽ የሆኑ ነገሮች በመሬቱ ውስጥ ይኖራሉ ። በነፋስ ከመጣ የአሸዋ ክምርና በጉርፍ በተቀደዱ ቦዮች ሜዳው በመጠኑ ወጣ ገባ ሆኗል ። ከሜዳው ከፍ ተደርገው የተሠሩ ነበሩ ። ዶብኪን እንደገመተው እነዚህ ግዙፍ መመልከቻ ማማዎች ከምሽጉ ግድግዳ በላይ ከፍ ተደርገው ለጥበቃ እንዲያመቹ ተደርገው የተሠሩ ነበሩ ።ዶብኪን ባእያንዳንዳቸው ላይ ጠባቂዎች እንዲቀመጡ አደረገ ።

ሠላሳ ወንዶችና ሴቶች ቦታቸውን ይዘዋል ። ዶብኪን አማራጭ ለመውሰድ አንዳንድ ነገሮች እንዲስተካከሉ አደረገ ።በተገን ፣ በመሸሸጊያና በመታኮሻ ቦታ በኩል ስላለው ችግር ሲያሰላስል ሆስነር ቆሞ ይመለከተው ነበር ። ለመከላከያ ድንጋይና አፈር እንዲቆልሉና በሚቻልበት ቦታ ሁሉ የቀበሮ ጉድጓዶች እንዲቆፍሩ ዶብኪን ትዕዛዝ ሰጣቸው ።

በርግ ለዶብኪን ኮልት .45 አውቶማቲክ ሰጠው ። ዶብኪን ደግሞ ካስተናጋጆቹ አንዱ ለሆነውና በአስፈላጊ ቦታ ላይ ለተቀመጠው ለአቤል ጊለር ሰጠው ። ሆስነር በበኩሉ አንዲት ወጣት ጸሐፊ ለሆነችው ለሩት ማንዴል ስሚዝና ዌሰን. 22 ሽጉጡን ሰጣት ።

“ እንዴት እንደምትጠቀሚበት ታውቂያለሽ ? ”

በትንሽ እጅዋ ይዛ እያየች “ጊዜዬን ያጠፋሁት በውትድርና ነው” አለችው ።

ሆስነር ሦስት የእጅ ጠመንጃዎች ፣ የእርሱ ሰዎች የያዟቸው ስድስት ስሚዝና ዌሰን . 22 እና ሌሎች አሥር መሣሪያዎች ፣ የጀሹዮ ሩቢን ኡዚ ፣ የብሪን ኤም —14 ፣ የእርሱ የጸጥታ ሰዎች ጃፍ ፣ ማርከስና አልበርን እያንዳንዳቸው ኤኬ—47 ተሰጥቷቸዋል ። በኤኬ—47 የምሥራቁን ተራራ ክፍል እንዲጠብቁ ተደርጓል ። እንደዚሁም በሰላሳ ሜትር እርቀት ላይ አንድ ሰው ተመድቧል ። አሰላለፉ ጥሩም ተስፋ የሚያስቆርጥም አልነበረም ።

ዶብኪን አስተናጋጅ ዳንኤል ጃኮቢን ስላገኘው በጥበቃ ላይ ላሉት ቡና ለማዘጋጀት የሚቻልበትን መንገድ እንዲፈልግ ጠየቀው ።

ሆስነርና ዶብኪን ፡ ብሪን በሚጠብቅበት ቦታ ሲደርሱ ቆሙ ። ሰማያዊ ልብስ የለበሰች አንዲት ወጣት ልጅ በብሪን አቅራቢያ ዲብ ተንተርሳ ተኝታለች ። ሆስነር “ እርስዋ ማን ናት ? ” ብሎ ጠየቀ ።

ብሪን ከጠመንጃው መነጽር ላይ ዓይኑን አንስቶ ቀና በማለት “ ናኦሚ ሀበር ትባላለች ፣ ጸሐፊ ናት።አንድ ነገር ባይ የሚላከኝ ሰው ስለሚያስፈልገኝ ለዚሁ ሥራ በፈቃደኝነት የመጣች ናት” አለው ።

ሆስነር በአዎንታ ራሱን ነቅንቆ “ያየኸው ነገር አለ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ የለም ። ”

“ ከጨረቃ ጥልቀት በኋላ ታያለህ ። ”

“ አውቃለሁ ። ”

ሆስነርና ዶብኪን ከብሪንና ከተኛችው ሴት እልፍ ብለው ቆሙ ።
ሁለቱም በጸጥታ አቅልቁለው ወደ ባቢሎን ተመለከቱ ።

ሆስነር ሲጋራውን አቀጣጥሎ “ ደህና ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ዶብኪን ራሱን ነቅንቆ “እንጃ ፤ ወሳኙ አሰላለፉ ነው ። በጥሩ
ሁኔታ የተሰለፈ አንድ የምድር ጦር ክፍል ይህን ተራራ አሸንፎ ሊወ
ስድ ይችላል ። በሌላ በኩል ደግሞ 500 ወታደሮች ያለው አንድ ባታ
ሊዮን ጦር አሰላለፉ መጥፎ ከሆነ አሸንፎ ይህን ተራራ ሊይዝ አይ
ችልም ። ለመከላከል ቦታ የያዘውን ወገን በጦርነት ለማስለቀቅ በጣም
ከባድ ነው ” ብሎ ዘርዘር ባለ ሁኔታ ነገረው ።

“ እነእርሱ የዚያ ዓይነት ጥበብና ዘዴ አላቸው ብለህ ታስባለህ ?”
“ ማን ያውቃል ? ሪሽ እንዴት ያለ መሪ እንደሆነ ይታወቃል ?
“ ማን ያውቃል ? ሪሽ እንዴት ያለ መሪ እንደሆነ ይታወቃል ? ለምክንያታቸው ? ስንት እንደሆኑ እን
ሰዎች ለእርሱ ሲሉ ይሞታሉ ? ለምክንያታቸው ? ስንት እንደሆኑ እን
ኳን አናውቅም ። ስለዚህ የበርግን ሪፖርት መጠበቅ ይኖርብናል ።”

ሆስነር “ እሺ ” ብሎ አቅልቁሎ ወደ ምሥራቅ ተመለከተ ። በው
ሃው ላይ እንደመቀነት እየሆነ በጨረቃው ብርሃን የሚያበራውንና
የሚያብረቀርቀውን ረግረግ አየ ። ከአሸዋና ከጡብ በስተቀር ሌላ
ነገር አልነበረም ። በቀድሞ ዘመን ሜሶፖታሚያ በብዙ ሚሊዮን የሚ
ቆጠሩ ሕዝቦች እየመገበ ያስቀምጥ ነበር የሚለውን ለማመን አስቸ
ጋሪ ሆነበት ። በአንድ ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ግምብ ከዚያም ባሻ
ገር ሰዎች መስፈር የጀመሩበት ሰፊ መንገድ ይታያል ።

“ በእውነት ይህን ቦታ ታውቀዋለህ ፤ ቤን ? ”
“ በአዕምሮዬ ውስጥ ከማስታውሰው አንድ ማፕ መሳል እችላ
ለሁ ። ሲነጋ አንድ ጥሩ የወታደር ማፕ ስዬ አሳይሃለሁ ። ”
“እነዚህ ፍልስጥኤማውያን እዚህ ሊመጡ እንዴት ቻሉ?”
“ የደፈጣ ተዋጊዎች በየቦታው እንዴት ሊገቡ ይችላሉ ?”
“ ጥቂት ከባድ መኪናዎች አሏቸው ። ”
“ አይቻቸዋለሁ ። ”
“ ከባድ መሣሪያዎች ? አዳፍኔዎች ? ”
“ እንደማይሆኑ በእግዚአብሔር ተስፋ አለኝ ። ”
“እኛን በባቢሎን ውስጥ መያዣ — ምርኮኛ—አድርገው ሊያ
ቀምጡን ይፈልጋሉ ። ሁኔታው የሚያስገርም ነው ። ’
‘ ሪሽ እንደፈለገው በዚያ ሰፊ መንገድ ላይ ብናርፍ ኖሮ ችግር
ያ ጋጥመን ነበር ። አሁን ሳስበው እርሱን ተከትለን ብናርፍ ኖሮ ም
እንደምንሆን ለማወቅ ከባድ ነበር ” አለው ዶብኪን ።

"ለማወቅ አንችልም" ብሎ ሆስነር ሲጋራውን አቀጣጥሎ የቀዘቀዙ እጆቹን በኪሱ ውስጥ አስገባቸው ። "ምናልባትም አሸር አቢዳር ትክክለኛ እርምጃ ወስዷል ።"

" ሊሆንም ላይሆንም ይችላል ። "

ሆስነር ወደ ሰሜን ሲመለከት 750 ሜትር እርቀት ላይ ከሜዳው ላይ ቀጥ ብሎ የወጣ ተራራ አየ ። ምሽግም መስሎ ታየው ። " ያ ምንድን ነው ? " ብሎ ጠየቀው ።

ዶብኪን የእርሱን አመለካከት ተከትሎ "ያ የባቤል ተራራ ነው ። ጥቂት በመሬት ውስጥ የተቀበሩ የታሪክ ቅርሶች አጥኚዎች የባቤል ግዙፍ የመጠበቂያ ማማ ነው ብለው ያምናሉ " አለው ።

ሆስነር ትኩር አድርጎ እየተመለከተ " አንተስ ታምናለህ ?" ብሎ ጠየቀው ።

' ማን ያውቃል ? '

" ከዚህ ሆነን በዓለም በአስደናቂነታቸው ከሚታወቁት አንዱ የሆነውን የባቢሎን የአትክልት ሥፍራ ተብሎ የሚጠራውን (ዘሀንጊንግ ጋርደን እፍ ባቢሎን) ማየት እንችላለን ? "

ዶብኪን ስቆ " በሰንበት ቀን አላስጎበኝህም " ከአለው በኋላ ትልቅ እጁን በሆስነር ትከሻ ላይ አስቀምጦ "ዋና ፍራሹ ከዚያ በደቡብ በኩል ነው " አለው ።

" በዚህ አካባቢ የሚኖር አለ? "

" አረቦቹ በእርኩስ መንፈስ የተያዘ ነው ብለው ስለሚያምኑ አይወዱትም ። "

" ሆኖም እዚህ የእረኛ ጎጆ አለ ። "

ዶብኪን በአዎንታ ራሱን ነቅንቆ "በፍራሹ መካከል ትንሽ መንደር አለ " አለው ።

ሆስነር ሲጋራውን አጥፍቶ "መንደሩ ለኛ የሚያስገኘው እርዳታ ይኖር ይሆን ? " ብሎ ጠየቀው ።

" አይመስለኝም ። ቀደም ብየ ከኢራቅ የተመለሱ ወታደራዊ የደህንነት ሰዎች አነጋግሬአለሁ ። ብዙ የኢራቅ መንደሮች ከሚታመን ውጭ ኋላ ቀር ናቸው ። ከሕዝቡ ጥቂቱ ዜግነቱ ኢራቃዊ መሆኑን እንኳን አያውቅም ። ከአምስት ሺህ ዓመት በፊት ሥልጣኔ እንደጀመሩት የመጀመሪያዎቹ የሜሶፖታሚያ ገበሬዎች ዓይነት ይኖራሉ ።"

"ስለዚህ በየትኛውም ዓይነት ዘመናዊ የመጓጓዣና የመገናኛ አካባቢ አይደለንም ? "

"በደቡብ በኩል ሂላ አለ ። ግን በዚህ እንዳለን ያውቃሉ የሚል እምነት የለኝም " ብሎ ንግግሩን ቆም በማድረግ አንድ ነገር ለማስ ታወስ የሚያሰላስል መሰለ ። " በፍራሹ ደቡባዊ ክፍል በኢሽታር መግቢያ አንድ ትንሽ ቤተ መዘክርና አንድ የእንግዳ ማረፊያ ቤት አለ ።"

ሆስነር በፍጥነት ራሱን ወደ ዶብኪን አዞሮ "ቀጥል" አለው ።

" የኢራቅ የጥንት ቅርሳቅሶች ክፍል ሁለቱንም ቤቶች ከሃያ ዓመት በፊት አሠርቷቸዋል ። የሙዚየም ኃላፊ የሆነውን ዶክተር አል—ታኒን ከስድስት ወሮች በፊት በአቴንስ ውስጥ ተገናኝተን ተዋውቀናል ። በቆጵሮስ ውስጥ በሚኖር በጋራ ወዳጃችን በኩል እንጻጻፋለን ። "

" የምትናገረው ሁሉ ከእንጀትህ ነው ? " ብሎ ሆስነር እየተራመደ " ለመሆኑ እዚያ መድረስ ትችላለህ ? " ብሎ ጠየቀው ።

"ያዕቆብ እዚህ ያለነው ተከበን ነው ። እዚህ ለመተኮስ የሚያመቸንን ቦታ መርጠንና ተዘጋጅተን እንዳለን ሁሉ በእነርሱም በኩል ይህን ተራራ ከበው እንደሚጠብቁን እርግጠኛ መሆን አለብህ ።"

" ግን እኮ ሾልከህ ብትሔድ — "

" ዶክተር አልታኒ የጐብዎች ወራት እስከሚጀምርበት እስከ ሚያዝያ መጨረሻ ድረስ በዚያ አይገኝም ። ስለዚህ እርሱን የማግኘቱ ዕድል የለንም ። "

" ስልክ መኖር አለበት ። "

" ምናልባት ይኖር ይሆናል — የሚወርድ ውሃ — የሪሽ ዋና የእዝ ጽሕፈት ቤት የት እንደሆነ በግምት ልነግርህ እችላለሁ ። "

ሆስነር መራመዱን ቆም አድርጎ "ቢሆንም እዚያ መድረስ ብት ችል—እንግዳ ማረፊያው ቤት ወይም ሙዚየሙ — አል - ታኒ በዚያ ሊኖር ይችላል ። ጂፕ መኪናም ማግኘት ትችል ይሆናል ። ወይም ስልክ ለማግኘት ችግር አይኖርም ይሆናል ። ምን ይመስልሃል ፤ ቤን ?" ብሎ ጠየቀው ።

ዶብኪን አሻግሮ ወጣ ገባውን ደቡባዊ ክፍል በእንክሮ ተመለከተ። ፍርስራሾቹን መከታ እያደረገ መሔድ ይችላል ። ኢሽታር መግቢያ ለመድረስ እርቀቱ ቢያንስ ሁለት ኪሎ ሜትር ያህል ነው ። በተራራው

ዙሪያ ያለውን ቀጭን መንገድ የሚጠብቅ ተረኛ ወታደር ይኖርበታል ። " ታዳኙ እኔ ነኝ ። ከተያዝኩ እዚህ ያዘጋጀነውንና የማውቀውን ሁሉ እንድናገር ያስገድዱኛል ። ማንም ቢሆን ይናገራል ፤ ያዕቆብ ፤ ይህን አንተም ታውቀዋለህ ። "

" በእርግጥ ያን አውቃለሁ ። "

" በእጃቸው ላለመውደቅ እርግጠኛ ለመሆን ሽጉጥ ያስፈልገኛል። በአሁኑስ ጊዜ ሽጉጡን ማጣት እንችላለን ? "

" አይመስለኝም ። "

" እኔም እንዳንተ ። "

" አንድ ጩቤ " አለው ሆስነር ።

ዶብኪን ስቆ " ስማ ፤ ቅድመ አያቶቻችን በገዛ ጕራዴዎቻቸው ላይ የሚጥሏቸውን ኳሶች ከየት ያገኙአቸው እንደነበር ፈፅሞ አይገባኝም ። ያ መቼም ድፍረትን ይጠይቃል ድርጊቱ በጣም ፤ በጣም የሚያሰቃይ መሆን አለበት " ብሎት በሩቅ ከተመለከተ በኋላ " ያን ማድረግ የምችል መሆኔን አላውቅም " አለው ።

" እሺ እንግዳው ፤ በብዛት ቢወሰድ አደገኛ የሚሆን የመድኃኒት ዓይነት ያለው ሰው በአካባቢያችን እንዳለ እንፈልግ" አለው ሆስነር ።

" ሕይወቴን በራሴ ላጠፋ የምችልበትን መንገድ ለማግኘት ስለ ምታደርገው ጥረት አደንቅሃለሁ ። "

" ከሃምሳ የበለጡ ሰዎች አሉ — "

"አውቃለሁ ፤ እሺ እሔዳለሁ ። የምሔደው ግን ቀን በፀሐይ ብርሃን ካየሁት በኋላ ነው ። ነገ ማታ ጉዞዬን እጀምራለሁ ። "

" እስከዚያ በሕይወት ላንኖር እንችላለን ። "

"ቆይቶ መሔዱ ይጠቅመኛል ። ውጤት ለማግኘት የተሻለ ዕድል ይኖረኛል ። ዛሬ ማታ ብሔድ ሕይወቴን በገዛ እጄ አሳልፌ እንደመስጠት ይቆጠራል ። ያን ማድረግ ደግሞ አልፈልግም ። ውጤት ማግኘት እፈልጋለሁ ። "

" በእርግጥ ። "

* * *

ይስሐቅ በርግ ፒፓውን ቡልቅ ቡልቅ እያደረገ ቀረበ ። አረማመዱ ተስማሚ ያልሆነ ሥራ እንደፈጸመ ዓይነት ሰው ነበር ።

ሆስነርና ዶብኪን ሊያገኙት ሔዱ ። ወደዚያው " ተናገረ ? ". ብሎ ሆስነር ጠየቀው ።

" እያንዳንዱ ሰው ይናገራል ። "

ሆስነር ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ " እርሱ — ? " አለው ።

"አሆ ! አይደለም ፤ በሕይወት አለ ፤ ለመናገር ስለአልፈለገ በጣም አልተጫንኩትም ። '

" ለምን ? "

" እነእርሱ ሁሉም እንደዚያ ናቸው ። ዶብኪን ይነግርሃል ። አንተም ራስህ በራምላ እስር ቤት አይተሃቸዋል ። የመፎከር ፤ የመደንገጥ ፣ የመርበድበድና የመፍራት ባሕርያት የተቀላቀለባቸው ናቸው ። ወደ ወዳጆቹ መልሼ እንደምልከው ቃል ገብቼለታለሁ ። "

ዶብኪን ራሱን በአሉታ ነቅንቆ "እንደዚያ ማድረግ አንችልም ። በወታደራዊ ሕግ መሰረት የመከላከያ አካባቢዎችን ያየ የጠላት ወገን ጠቡ እስኪበርድ ድረስ አይለቀቅም ። እዚህም ሆነ በሌላ ቦታ ሕጉ አንድ ዓይነት ነው " አላቸው ።

"ደህና" አለ በርግ " በእኔ ዓለም ውስጥ — ሰላዮችና የምሥጢር ወኪሎች — ነገሮችን በተለያዩ ሁኔታዎች እንጠቀምባቸዋለን ። ወይም እናደርጋቸዋለን ። ለሰውየው ቃል ገብቸለታለሁ ። ስለዚህ በሕክምና ምክንያት ልዩ አስተያየት ማድረግ እንችላለን ። በተጨማሪም ሰውየው ሕክምና ባለማግኘቱ እንዲሞት ማድረግ ትክክል አይደለም ።"

" ስለዚህ ጉዳይ አስብበታለሁ " አለ ዶብኪን ።

ሆስነር ሲጨቃጨቁ አዳምጧቸዋል ። ውይይቱ ይህን ያህል አመርቂ አልነበረም ። በሕጉ ላይ የተለያዩ ትርጉሞች በመስጠት የተደረገ አለመግባባት ነበር ። በርግ ግራ የተጋባ መስሎ ለሆስነር ታየው ። ለአንድ ደቂቃ ሰውየው እስኪሞት ድረስ ለማስቃየት ተዘጋጅቶ ነበር ። ቀጥሎ ደግሞ የሰውየውን ሕይወት ለማዳን ሞከረ ። " ከፈለገ አረቡ ይሒድ ። አረቦቹ ተመልሰው መጥተው ተራራውን በመያዝ ?ርግን በሕይወቱ ይማርኩት ። አረቦቹ በርግን ቀስ በቀስ እንዲሞት ?ድርጉት ። እርሱ በርግን ቢሆን ኖሮ ሰውየውን ገድሎ አርቆ ይቀብረ ?ው ነበር " ብሎ ሆስነር አሰበ ። ዶብኪን ትክክለኛ ወታደር ፤ ታማኝ፤ ?ዋቂና ተመራማሪ ነበር ። ነገር ግን የደንቦቹን መጽሐፍ አይወደውም። ?ስነር የእነርሱ ጭቅጭቅ ትዕግሥቱን ስላስጨረሰው "ይህን ተውት ፤ ?ልቅስ እስረኛው ምን ተናገረ ?" አለው ።

በርግ ፒፓውን በጫማው ላይ ቀርቅሮ እያራገፈ " ምን ተናገረ ? ?ብዙ ነገሮች ተናግሮአል ። ስሙ ሙሐመድ አሳድ መሆኑንና እርሱም

አሸባል መሆኑን ተናግሯል ። ቃሉ ምን ማለት እንደሆነ ታውቀዋ ለህ ። የነብር ግልገል — ከእስራኤል ጋር በሚደረጉ ጦርነቶች ምክን ያት ፍልስጥኤማዊ የቲም (እናት አባት የሌለው) — በዚህ ምክንያት ብዙ አሸባሎች አሉ ። ሁሉም ያደጉት በፍልስጥኤም የደፈጣ ተዋጊ ድርጅት ነው።በአሁኑ ጊዜ ሁሉም አድገዋል። እኛንም አይወዱንም ።”

ዶብኪን በአዎንታ ራሱን ነቅንቆ “ ጦርነቱ ብዙ የጠባሳ ቅርሶች ትቷል ። ይህ ግን እጅግ በጣም አስከፊው ነው ” አላቸው ። ስለአሸ ባሎቹ አሰላሰለ ። ስንቶቹ ዓይኖቻቸው ጠፉ ፤ አካለ ስንኩሎች ሆኑ ፤ ስንስቶቹ በሚያሳዝን ሁኔታዎች ላይ ወደቁ? ጦርነት—አሁን ሁሉም: አድገዋል ። እነዚህ ወጣቶች የመከራውን ገፈት ቀማሾች ። የማታ ቅዥ ት ቀን ተመልሶ የሚመጣ — “ ፈጽሞ አይወዱንም ” ብሎ ዶብኪን ተስማማ ።

“ ፍጹም ትክክል ነህ ” አለው በርግ ። በጣም አደገኞች ናቸው ። በሕጻንነታቸው ወራት አንድ ነገር ምን እንደሆነ መለየት ከጀመሩበት ቀን አንስተው በእኛ ላይ ጥላቻ እንዲያድርባቸው መርዘዋቸዋል ። ትክክለኛ አስተሳሰብን አይቀበሉም ። እስራኤልን መጥላት ሃይማኖታ ቸው አድርገውታል ። ቆመው መሔድ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምረው የው ትድርና ትምህርት ስለአስተማሩአቸው በሚገባ ሰልጥነዋል ።

“ ስንት ናቸው አለህ ? ” ብሎ ዶብኪን ጠየቀው ።

“ አንድ መቶ ሃምሳ ። ”

ሁሉም ጸጥ አሉ ።

“ እርግጠኛ ነህ ? ” ብሎ ሆስነር ጠየቀው ።

በርግ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ ።

“ እርግጠኛ ለመሆን እንዴት ቻልክ ? ”

በርግ ፈገግ አለ “ አባባሉ ወታደሮች ከሚዋሹበት ነገሮች አንዱ ነው ። አይደለም እንዴ ፤ ቤን ? በመጀመሪያ አምስት መቶ ናቸው አለ። ይህን አባባል ልቀበለው ስላልቻልኩ በመጨረሻ በአንድ መቶ አም ሳዎቹ ተስማማን ። ”

ዶብኪን ራሱን ነቅንቆ “ከባድ መሣሪያዎችስ?” ብሎ ጠየቀው ። በርግ በአሉታ ራሱን ነቀነቀ ። “ ይቋቋሙናል ብለው አልተጠራጠ ሩም ነበር ። ቢሆንም አብዛኞቹ ኤኬ—47 ጠመንጃዎች ታጥቀዋል ። ”

“ በአቅራቢያ የወታደር ሰፈር ሊኖራቸው ይገባል ” አለው ዶብ ኪን ።

“ በጣም ቅርብ አይደለም ። ያላቸው በሻሚያ በረሃ ውስጥ ነው ። ይህም ማለት በኤፍራጥስ ወንዝ ጀርባ ከዚህ 100 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ መሆኑ ነው ።”

“ ሪሽ አለቃቸው ነው ? ” ብሎ ሆስነር ጠየቀው ።

“ ነው ። የእርሱ የመቶ አለቃና የብዙ ጊዜ ወዳጁ ሳሌም ሀማዲ ነው ። ሀማዲ ፍልስጥኤማዊና አሸባል ነው ። ቀደም ብሎም የአሻባል ፕሮግራም ተቆጣጣሪ ነበር ። እንደምታውቀው ሪሽ አሸባልም ፍልስጥኤማዊም አይደለም ። የኢራቅ ተወላጅ ነው ። የተወለደበት መንደር ከዚህ እሩቅ አይደለም ። ከጥቂት ጊዜ በፊት አባትና እናት የሌላቸው ሴቶችና ወንዶች ከልዩ ልዩ መጠለያ ሰፈሮች ሰብስበው አሰለጠኑ ። ከእነዚህ የነብር ግልገሎች ውስጥ ሃያዎቹ ሴቶች ናቸው ። በሻሚያ በረሃ ውስጥ ለብዙ ዓመቶች ፈጽሞ ተግባራዊ ሲሆን የማይመስል ልዩ ሥልጠና የተሰጡ መሆናቸውን መሐመድ ገልጿል ።

“ እዚህ ለምን እንዳሉ ያውቃሉ ? ” ብሎ ዶብኪን ጠየቀው ።

“የተነገራቸው የሪሽ ሌየር ለማረፍ ሲያንጃብብ እንደነበርና አንድ ወይም ሁለት ኮንከርድ እንደሚመጣ በግልጽ አያውቁም ነበር ” ብሎ ዶብኪን ከንኮርድ 01 ትዝ ስላለው መናገሩን ለትንሽ ጊዜ ቆም ካደ ረገ በኋላ “ በልዩ ልዩ የፖለቲካ ምክንያቶች ፣ ጥቂቶቹ ለመሐመድ ግልጽ ያልሆኑለት ፣ እኛን መያዣ አድርገው እንደሚያቆዩን ተነግሯቸዋል ። እኛ በፈጸምነው መደናገጣቸውን ነግሮኛል ። እንደገመትኩት በውጊያ ወቅት ማሸነፍና መሸነፍ እንደዚሁም ከወገን በኩል መሞት እንደሚኖር በሥነልቦና ትምህርት አላዘጋጁአቸውም ። የተነገራቸው ሁለት አውሮፕላኖች ወታደር ያልሆኑ እስራኤሎችን ያሳፈሩ ከበው እንዲጠብቁ ነበር ። በድንገት በተደረገው የተኩስ ልውውጥ ሰዎቻ ቸው ተገደሉባቸው ። ”

“ እንደ አባባልህ ከሆነ በሚገባ የሰለጠኑ ወታደሮች አይደሉም” አለው ሆስነር ።

“ አላልኩም ። ያልኩት በሚገባ የሰለጠኑ ናቸው ነው ። አንደኛ ቸውም በጦር ሜዳ ውለው አያውቁም ። እንደምታውቀው አባትና እናት የሌላቸው ልጆች ከሕጻንነታቸው ወሮች ጀምረው ለውትድርና መሰልጠን የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም ። በታሪክ ውስጥ ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ክርክሮች ተደርገዋል ። ተገደው ከገቡ ቋሚ ወታደሮች በጣም የተሻሉ ወይም በጣም ያነሱ አይደሉም ። በትክክለኛው አነጋገር ግን ብዙ ጊዜ በጣም ያነሱ ናቸው ። እነዚህ የቲም ልጆች በየትኛውም ቦታ እንዳለው ሁሉ በአንድ ድርጅት ውስጥ ተከልለው ያደጉ በመሆናቸው

ከቤተሰቦቻቸው ጋር ከአደጉ ልጆች ሲነጻጸሩ የደደቡነት ወይም የማሰብ ችሎታ ማነስ ያጠቃቸዋል ። ይህ ችግር በአሽባሎቹ ላይ እንደሚያንጸባርቅ እርግጠኛ ነኝ ። በተለይም ጥሩ ውትድርና አይኖራቸውም ። የማስተዋል ዘዴአቸውም ያነሰ ይሆናል ። በሕይወታቸው የራሳቸው የሆነ አላማ አይኖራቸውም ። ከውትድርና ሕይወት ውጭ የሌለ ልምድ የማካበት ዕድል ስለማይኖራቸው የፍላጐታቸው ዕድገት በአንድ ክልል ብቻ እንዲወሰን ይሆናል ። ከጦር ሠፈራቸው ውጭ የሚያውቁት ስለ ሌላቸው ለምን እንደሚዋጉ እንኳን በግልጽ አያውቁም ። ነገር ግን ጓዶቻቸውንና ሠፈራቸውን ላለማስያዝ እስከ ሞት ድረስ እንደሚዋጉ እርግጠኛ ነኝ ። ከዚያ ውጭ ግን ለቤተሰብ ወይም ለአገር የሚሉት ነገር የላቸውም ። አስተማማኝ ወታደሮች ለመሆን ለምን እንደማይችሉ ብዙ ምክንያቶች መኖራቸውን ከሙሐመድ ሁኔታ ለመገንዘብ ይቻላል ” ብሎ ወደ ዶብኪን ተመለከተ ።

ዶብኪን ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ እስማማለሁ ። ግን አሁንም ከአንድ መቶ በላይ የሚሆኑ አሉ ። እኛንም በመሣሪያ ጭምር ይበልጡናል ። እንደዘላን አረቦች ድንኳኖቻቸውን በሌሊት ጠቅልለው ሹልክ ብለው የሚጠፉ አይደሉም ” አለው ።

“ አይደሉም ። ምክንያቱም ሁለት ጥሩ መሪዎች አሏቸው ” አላቸው ሆስነር ።

ዶብኪን እንደገና ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። “ ዋናው ቁም ነገር አመራር ከመሰጠቱ ላይ ነው ። በእማካይ የአረብ ወታደር ሲታይ መሪው ሲሞት የሚያሳየው ፍላጐት መጠነኛና ያነሰ ሥነ ሥርዓት ነው ። በተጨማሪም የአረብ ወታደሮች ከዘመናዊ መሣሪያዎች አያያዝ ጋር ብዙ ልምድ የላቸውም ። እኔ እንደምገምተው አሽባሎቹም ከዚህ ውጭ አይደሉም ። በተጨማሪም በጥላቻ ፕሮፓጋንዳ አዕምሯቸው እንዲደነዝዝ ከመደረጉም በስተቀር እንደ ወታደሮች በሙያቸው የሚኮሩ ” አይደሉም ።

“ እኔም እስማማለሁ ። ብቃት ያለው መሪ ካላገኙ ወይም በሚሸመው ካላመኑበት ትተው ይሔዱ ይሆናል የሚል አስተሳሰብ አለኝ ። አሁን ግን የሚያደርጉት አይመስለኝም ። በሌላ በኩል ግን እኛ ትተን የምንሔድበት ቦታ የለንም ወይም መሸሽ አንችልም ። የምንዋጋው ለሕይወት አድን ወይም ሕይወታችንን ለማትረፍ ነው ። የምናደርገው መስዋዕትነትና የሚደርስብን ችግር ሁሉ በእኛ ዘንድ ተቀባይነት አለው ። ሌላ ምርጫ የለንም ” አላቸው በርግ ።

ሆስነር “ ምርጫ ይኖራል ፤ ለመወያየት ይጠይቃሉ ” አላቸው ። “ ግን ሌላ ተጨማሪ ውጊያ ከማድረጋቸው በፊት አይጠይቁም ” ብሎ

ዶብኪን ስማዩን አንጋጠ ከተመለከተ በኋላ “ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ከባድ ጥፋት ካደረስንባቸው ለማየት ዕድል ይኖረናል ። ጨረቃዋ እየጠለቀች ናት ” አላቸው ።

— 13 —

ብሪን ነብራማ ዩኒፎርም ለብሰውና አውቶማቲክ ጠመንጃዎቻቸውን ተሸክመው አቀበቱ ግማሽ ላይ መድረሳቸውን አካባቢውን በመቆጣጠር መልዕክት እንዲያስተላልፉ የተመደቡት ሁለት ሰዎች ከማየታቸው በፊት አያቸው ። በብሪን ጠመንጃ ላይ የተገጠመው በኮከብ ብርሃን የሚሠራው መነጽር እጅግ በጣም ትንሽ የሆነውን የጨለማ ብርሃን ስለሚያጉላው የጨለማ ፍጥረቶች እንኳን ሊያዩት የማይችሉትን — ሰዎች በላያቸው ላይ ያሉትን ነገሮች የማያዩአቸውን ጭምር ለማሳየት የሚችል ነበር ። በኮከቡ ብርሃን የነበራቸውን ጥላ ፣ በዓይኖቻቸው ሥር የነበረውን ነጭ ቀዳ ፣ ከንፈሮቻቸው ሲንቀሳቀሱ ፣ በፍርሃት ሲወራጩ ፣ የጸጉር መያዣቸው ሳይቀር ልቅም አድርጐ ለማየት ቻለ ። ብሪን አንዲት ሴት የአንድ ወጣት እጅ ጭብጥ ስታደርግ ጭምር አየ ።

ዓይኑን ከመነጽሩ ላይ አንስቶ ለናኦሚ ሀበር “ እየመጡ ናቸው ” ብሎ ሹክ አላት ።

ናኦሚ ራስዋን ነቅንቃ ክንዱን ነካ ካደረገችው በኋላ ማስጠንቀቂያውን ለማስተላለፍ ሮጠች ።

በተራራው ምሥራቅ ክፍል ያሉት ተከላካዮች እንደሰሙ በተጠንቀቅ ላይ ሆኑ ።

በምዕራብ በኩል ግን ጸጥታ ነበር ። ከኤፍራጥስ ወንዝ የሚንጸባረቀው ብርሃን ወደ ተራራው የሚጠጋ ካለ ጥላውን ለማየት ያስችል ነበር ። ወንዶችና ሴቶች የሚንቀሳቀስ እንዳለ ለማየት አትኩረው ወደ ወንዙ ተመለከቱ ።

ዶብኪን ፣ በርግና ሆስነር በአንድ ትንሽ ጉብታ — አሸዋ የለበሰ የመጠበቂያ ማማ — ላይ ቆመዋል ። ጉብታው ለትዕዛዝ ማስተላለፊያና ለመመልከቻ ማዕከል እንዲሆን የተመረጠ ነው ። በዚያ ቦታ ላይ ሆነው በምሥራቅ ቁልቁለት ያለውን 500 ሜትር እርቀት ድረስ አመራር እየሰጡ ለመዋጋት እንደሚችሉ ተስፋ አድርገዋል ።

ከኮንኮርዱ ጅራት ክፍል ተገንጥሎ የወጣ አንድ ረጅም አሉሚኒየም ጠቅልለው ዘንግ በማድረግ በሸክላው አፈር ላይ ስገው አቆሙ

ት ። በኒውዮርክ ለአንድ ሰው ስጦታ የተዘጋጀ የቴልአቢብን ከተማ ገጽታ የሚያሳይ ስዕል ያለበት የልጅ ሸሚዝ እንደባንዲራ አድርገው በተከሉት ዘንግ ላይ ሰቅለው እንዲውለበለብ አደረጉት ። ያትዕዛዝ መስጫውና የተመልካች ማዕከል ዋና ሥራው ከማዕከል ወደ ተከላካዮች ምሽግ ፤ ከተከላካዮች ወደ ማዕከል ትዕዛዝ የሚያስተላልፉበትና የሚቀበሉበት ነው ። ይህ ዓይነቱ አሠራር ቀድሞ ራዲዮ ፣ ቴሌግራምና የመስክ ስልክ ባልነበረበት ጊዜ የሚጠቀሙበት ዘዴ ነበር ። ሦስቱ አዛገሮች በጉብታው ላይ በሰንደቅ አላማቸው ሥር ቦታ ቦታቸውን ይዘው ይጠባበቃሉ ። ሁለት ሰዎች ከዋናው ትዕዛዝ መስጫ ጉብታ ሥር ደርሰው ከናታን ብሪንና ከናኦሚ ሀበር የተገኘውን “ እየመጡ ነው ” የሚለውን ሪፖርት ሲያስተላልፉ ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ ይል ነበር ።

* * *

አጥቂዎቹ በጸጥታ ሆነው የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ እስከተራራው ጥግ ድረስ የቀጠሉ መሆናቸውን ብሪን ተመለከተ ። እንደቀድሞአቸው በአንድ መስመር ላይ ሆነው ተከታትለው አልመጡም ። ወደ አንድ መቶ ያህል የሚሆኑ ወንዶችና ሴቶች በየአምስት ሜትሩ ተራርቀው 500 ሜትር እርቀት ላይ ያለውን የተራራ ጥግ መውጣት ጀምረዋል ። አሰላለፋቸውና መስመር አጠባበቃቸው የሰለጠነ የእግረኛ ጦር ይመስል ነበር ። አደጋ እንዳያገኛቸው በጉብታ ወይም በሌላ የተፈጥሮ መከላከያ በመጠቀም ራሳቸውን አልደበቁም ። ሁሉም በኤኬ—47 ጠመንጃዎቻቸው ላይ ሳንጃዎች ሰክተው ወደፊት በማድረግ ይሔዳሉ ። ተመልካችን በጣም የሚያስፈሩ ነበሩ ። ለብሪን ግን የታዩት ለሰልፍ የሚሰለጥኑ ሰዎች መስለው ነበር ። ጥይት ከላይ ሲዘንብባቸው ምን እንደሚያደርጉ ለማየት ቸኩሏል ። ምናልባት ከተኩሱ በኋላ ዘመናዊ ሥልጠናቸውን በመከተል በየፈፋውና በየቦዩ እየተሰገሰጉ ይዋጉ ይሆናል የሚል ጥርጣሬ አደረበት ። ከድንጋይ ወደ ጉድጓዳ ቦታ ከዚያም ወደ ዲብ ሥር ይሯሯጡ ይሆናል ። አሁን በጨለማው እንደሚያደርጉት ከሆነ ለራሳቸው ሰልፍ የሚያሳዩ ይመስላሉ ።

የሚያያቸው ብቻውን ሆኖ ስለነበረ በአደረበት ውጥረት ላቡ እየተንጠባጠበ በፊቱ ላይ ወረደ ። ይሁን እንጂ አሁንም ገና እሩቅ ነበሩ ። በመጀመሪያ 500 ሜትር ፣ ከዚያም 400 ሜትር እርቀት ላይ ደረሱ ።

ጀኔራል ዶብኪንና ይስሐቅ በርግ በጦሩ ስልት ላይ አልተስማሙም ።

ዶብኪን በሚቻል መጠን በከባድ መሣሪያ በመጠቀም በውጊያ ክልል ውስጥ እንዳይገቡ ማድረግ ይገባል የሚል አስተሳሰብ አለው ፤ ከመጠጋታቸው በፊት በቁልቁለቱ ላይ በናዳ ጭምር በመጠቀም ፍርሃት የበለጠ እንዲያድርባቸው ይረዳናል ። እስረኛው የእጅ ቦምብ የላቸውም ቢልም አባባሉን ዶብኪን ሊያምን አልቻለም ። ምንም ይሁን ምን የእጅ ቦምብ ለመወርወር እሚችሉበት ክልል ውስጥ እንዲገቡ ዶብኪን አይፈልግም ።

በርግ በበኩሉ ቀርበው በእጅ ጠመንጃ ተኩስ ክልል ውስጥ ሲገቡ ውጊያው እንዲጀመር ይፈልጋል ። ይህም በጠላት ላይ ከባድ ጉዳት ለማድረስ ከማስቻሉም በላይ በሚቻል መጠን የጥይት መባከንን ይቀንሳል የሚል እምነት አለው ።

ሆስነር ባይጠየቅም ከነበሩበት ተጨባጭ ሁኔታ ዶብኪን ያቀረበው ሃሣብ እውነትነት ያለው መሆኑን አምኗል ። ቢሆንም ለመጨረሻ ዶብኪን በወታደርነቱ ሲቪል ከሆነ መንግሥት ባለሥልጣን ጋር በሃሣብ እንደሚለይ ሆስነር ያውቃል ። በአጠቃላይ ጊዜው የሚሰጠው ውሳኔ ያለጥናት ስለነበረ በኃላፊዎቹ ዘንድ ይህን የመሰለ ክርክር ማስከተል ይኖርበታል ።

ሆስነር ይቅርታ ጠይቆ ከጉብታው ላይ ዘሎ በመውረድ ተንበርክኮ ወደሚመለከተው ብሪን ሔደ ። አሸባሪዎቹ እየቀረቡ በመምጣታቸው የብሪን ሰውነት ሲንቀጠቀጥ በግልጽ ይታይ ነበር ። ይህ በመሆኑ ሆስነር ሊወቅሰው አይችልም ። በለሰለሰ አነጋገር “ እየቀረቡ ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ብሪን ቀና ሳይል “ 350 ሜትር እርቀት ላይ ናቸው ” አለው ።

“ እርምጃ ለመውሰድ እንዘጋጅ ? ”

“ አሁን በአንድ አቅጣጫ ላይ ናቸው ። አብዛኞቹ በግልጽ ይታያሉ ። ሳንጃዎቻቸውን ሰክተዋል ። ”

ናኦሚ ከሔደችበት ተመልሳ እየተቀመጠች በኃይል አለከለከች። ሆስነር ወደ እርስዋ ዞሮ “ ኤኬ—47 ጠመንጃ የያዙት ተኩስ እንዲጀምሩ ሒጂና ንገሪአቸው ” አላት ። እርስዋም በፍጥነት ተነስታ አቆልቁላ ሮጠች ።

ሆስነር ወደ ብሪን ዞሮ “ የት ደረሱ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ 300 ሜትር እርቀት ላይ ናቸው ። ”

ቀስ ብሎ “ ተኩስ ጀምር ” አለው ።

ብሪን እያነጣጠረ ደጋግሞ ተኮሰ ። ሌሎቹም ኤኬ—47 የያዙት የወገን ተከላካዮች ተኩስ ጀመሩ ። በላይም በታችም ያሉት ወደ ጠላት

ያንደቀድቁት ጀመሩ ። ባለኡዚውም እያነጣጠረ ጠላትን መለብለብ ቀጠለ ። አካባቢው በተኩስ ድምጽ ተደበላለቀ ።

አረቦቹ በኤኬ—47 ጠመንጃዎቻቸው ለተኩሱ መልስ ሰጡ ። ድምጹ ጆሮ እሚያደነቁርበት ደረጃ ደረሰ ። ከጠላት የሚተኮሱት ጥይቶች በእስራኤል መከላከያ ምሽጎች ላይ ሲያርፉ ሆስነር አይቷል ። የተመታ ስለመኖሩ ግን ገና አላወቀም ።

የብሪን ሥራ የቡድን መሪዎችን እየፈለገ በጥይት መጥበስ ነበር። የጠመንጃውን መነጽር እያዟዟረ ሲመለከት አንድ የመስክ ራዲዮ አንቴና በአንድ መልዕክት በሚያስተላልፍ ሰው ጀርባ ላይ አየ ። የራዲዮ ስልክም እንዳለው አረጋገጠ ። አንድ ወጣት ሰው የራዲዮ ስልኩን ክር ስቦና መናገሪያውን ወደ አፉ አስጠግቶ ሲንበረከክ ተመለከተው። ብሪን በሰውየው አፍ ላይ አነጣጥሮ ስለተኮሰ ስልኩና የሰውየው ፊት እንዳልነበሩ ሆኑ። እንደገና አነጣጥሮ የራዲዮ ኦፕሬተሩን በልቡ ላይ መትቶ በአፍጢሙ ደፋው ።

አሽባሎቹ ከሰልፋቸው በመበታተንና በትናንሽ ቡድኖች በመከፋፈል መከላከያ ያላቸው ቦታዎች እየፈለጉ ስለሔዱ የአጸፋ ተኩሳቸውን አቆሙ ። ግስጋሴአቸው ቢቀንስም እርምጃቸውን ወደፊት ቀጠሉ ። ብሪን ዋና መሪዎቻቸውን ለማየት በአሽባሎቹ በስተጀርባ ያለውን ቦታ ተመለከተ ። ሪሽን ለአንድ ጊዜ ያየ መሰለው ። ግን ከመቅጽበት ተሰወረበት ። በሴኮንድ ውስጥ በእርሱ ፋንታ እንዲት ወጣት ሴት አየ ። ያለምንም ማወላወል ብሪን ተኩሶ ሲመታት ወድቃ ተንደባለለች ።

አረቦቹ ወደ ተራራው እየተጠጉ ሲመጡ ቁጣቸው ገንፍሎ እንደነበረ ዶብኪን ስለተገነዘበ ራሱን ነቀነቀ ። በመሠረቱ በደንብ ሰልጥነው ይሆናል ። ለጦር ስልታቸው ግን ዝቅተኛ አስተያየት ነበረው ። እስራኤሎቹ ካለፉት ግጥሚያዎች ካገኙት ልምድ መሠረት ኮሽታ ሳያሰሙ በፍጥነት መሮጥ በጨለማ ጦርነት ጊዜ እጅግ በጣም ጥሩ ውጤት እንደሚያስገኝ ተገንዝበዋል ። የጠላት ወገን አብዛኛውን ጊዜ የሚጠነቀቀው በከፊል ስለሆነ በጨለማው ውስጥ ወደ እነርሱ የሚመጣውን ሲያዩ ፤ የሚያዩትን የሚያምኑት በከፊል ነው ። መዋጋት በሚጀምሩበት ጊዜ አጥቂዎቻቸው በእጅ ቦምብ እሚዋጉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ ። ከአንድ ሴኮንድ በኋላ የመከላከያ ጉድባቸውን ይነጥቋቸዋል ። ሙሉ ትጥቅ ያለው አንድ እግረኛ ወታደር እንኳን ከሁለት ደቂቃዎች ባነሰ ጊዜ ውስጥ ግማሽ ኪሎ ሜትር እርዝመት ያለውን ቦታ መሸፈን ይችላል ።

ዶብኪን በጨለማው ውስጥ የሚተኮሱትን ጥይቶች ብልጭታ ተመለከተ ። እነዚህ አሸባሎች እየተኮሱ ሲሮጡ አንድ ቦታ ላይ ሲደርሱ ሽፋን ፈለጉ ፤ ይህ ደግሞ በትክክል ሊደረግ ከሚገባው ሁኔታ ቀጥታ ተቃራኒ ነበር ። በኮረብታው ላይ ያሉት ተከላካዮች የሚተኩሱት የጥይቱ ብልጭታ የተነሳበትን በመከተል ሲሆን ተዋጊዎቹ ግን ደሮጡ ነበር ። ዶብኪን እንደገመተው ከሆነ የአሸባሎቹ ጥይት እስራኤሎቹን አላጠቃም ። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ከወገን በኩል አደጋ የደረሰበት አንድ ሰው ብቻ እንደነበረ ሪፖርት ደርሶታል ።

በብዙ የጦር ሜዳዎች ላይ ለብዙ ዓመቶች በመዋሉ በአካባቢው የሥራ ልምድ መሠረት በብርሃን ብልጭታና በድምጽ ፤ በሰዎች ጩኸትና በሌሊት የአየር ሽታ የጦርነቱ ሒደት በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ያውቃል ። ከሁሉም በበለጠ ደግሞ ግጥሚያው መቼ በትክክል እንደሔደና ሽንፈት መቼ እንዳስከተለ የውስጥ ወታደራዊ ስሜቱ ለይቶ ይነግረዋል ።

በአጠቃላይ ዶብኪን የጨበጣ ውጊያ እስኪገጥሙ ድረስ በሁለቱም ወገኖች ላይ የሚደርሰው ጉዳት ቀላል እንደሚሆን አውቋል ። ምክንያቱም ባለፈው ዘመን ከታየው ድርጊት የተወሰደው ግንዛቤ እንደዚያ ስለነበረ ነው ። ይሁን እንጂ በዚህ ወቅት ድል ይገኛል የሚል እምነት አላደረበትም ። ወደ በርግ ዞሮ “ እነርሱ ዝርክርክ ወታደሮች ቢመስሉም በጣም ቆራጦች ናቸው ። ምናልባትም በአጭር ጊዜ ውስጥ ጥይቶቻችንን ጨርሰን እንዳንችገር ያስፈልጋል ። የኛ ሰዎች ወደዚህ ተራራ እንዲሰበሰቡ ማድረግ ይኖርብን ይሆናል ” አለው ።

በርግ ራሱን በአሉታ ነቀነቀ ። ቀድሞ በደህንነት ሥራ ተሰማርቶ አገልግሏል ። የአንድ ሻለቃ አዛዥ ሆኖ በነጻነት ጦርነት ላይ ተዋግቷል ። በአሁኑ ሁኔታዎችም ላይ የራሱ ስሜት አለው ። “ ግጥሚያውን ትተው ይበታተናሉ የሚል ስሜት ስላለኝ እስኪ ለትንሽ ጊዜ እንቆይ ። ”

ዶብኪን ለዚህ መልስ አልሰጠውም ።

በርግ የተተከለውን የአሎሚኒየም ዘንግ ለመነሳት እንዲረዳው በአንድ እጁ ይዞ ከመቀመጫው ተነሳ ። ከመሣሪያዎቹ በሚወጣው የጥይት ብልጭታና ያለማቋረጥ በሚያፏጩት ጥይቶች በጣም የተገረመ መሰሏል ። በመሰማት ላይ የነበረው የጥይቶች ጩኸት የአሜሪካ የፊልም ተዋንያን እንደሚተኩሱት የሽጉጥና የጠመንጃ ጩኸት መስሎ ተሰማው ።

" ከእኛ ትዕዛዝ ውጭ ሆስነር ተኩስ እንዲከፈት ያደረገ ይመስ ልሃል ፡ ጄኔራል ? " ብሎ ጠየቀው ።

ዶብኪን በዚህ ላይ ውይይት ለመክፈት የፈለገ አልመሰለም ። " እንደሚመስለኝ አድርጓል ። ግን ብዙ ልዩነት የሚያመጣ አይመስ ለኝም ። ለአንተ ይመስልሃል ? "

በርግ " ለእኔ ትልቅ ልዩነት ያመጣል " ካለው በኋላ በድጋሚ " ትልቅ ልዩነት አለው እንጂ " ብሎ ነገረው ።

ጥይት ለመቆጠብ ተብሎ ተኩስ እንዲቆም ቢደረግ ለአጥቂዎቹ የጦርነቱ መፈጸሚያ የተቃረበ ስለሚመስላቸውና ያለመሰልቸት ስለ ሚገፉበት ፤ በእስራኤሎቹ በኩል የነበራቸው ምርጫ ተኩሱን ያለማ ቋረጥ መቀጠል ነበር ። በእርግጥ የነበሩአቸው ጥይቶች እየመነመኑ ስለሚመጡ ጥቂት ጠመንጃዎች ጥይት አልባ እንደሚሆኑ ግልጽ ነበር። በተለይም የኤኬ—47 ጠመንጃዎች ጥይቶች ማለቅ ጀምረዋል ። ጆሹዋ ሩቢን ያለማቋረጥ ተኩሱን ቀጥሏል ። ብሬን እየቆጠበ ቢተኩስም እያ ለቀበት ነበር ።

አሸባሪዎቹ ከመከላከያ መስመሩ 100 ሜትር ያህል እርቀት ላይ ደርሰዋል ። ይሁን እንጂ 10 ሜትር ወደፊት በተንፏቀቁ ቁጥር ጉዳ ታቸው በጣም እየጨመረ መጣ ።

ከምዕራብ ዘቅዛቃ ቦታ አንድ ሰው እየሮጠ ወደ ዋናው የእዝ ማስ ተላለፊያ መጣ ። በዚያ በኩል ባለው ወንዝ ዳር አሸባሪዎቹ ጦርነት መክፈታቸውን የሚናገር ሰው የመጣ መስሎአቸው በርግና ዶብኪን ይህን መጥፎ ወሬ ለመስማት ተዘጋጅተው ጠበቁት ። ዳርቻው የሚ ጠበቀው አንድ ሽጉጥ በያዘው በመክለርና ድንጋይና ከስብርባሪ አሉ ሚኒየም እንደጦር እያሾሉ በያዙ አሥራ ሁለት ወንዶችና ሴቶች ነበር። ሩዋጩ እያለከለከ በዲቡ ላይ ወጥቶ በኃይል ከተነፈሰ በኋላ በምዕራብ ቁልቁለት በኩል ጸጥታ ነው " ብሏቸው ፈገግ አለ ።

ዶብኪን ፈገግ ብሎ የሰውየውን ጀርባ ቸብ ካደረገ በኋላ " ትና ንትና ማታ በቴልአቪቭ ውስጥ አንዲት ሴት እሺ በማለት ካሰማችኝ ቃል ወዲህ ይህ የአሁኑ የመጀመሪያ ጥሩ ዜና መሆኑ ነው " አለው ።

ሆስነር በብሬን ጉን ተንበርክኮ ጦርነቱ በሚቀጥሉት ጥቂት ደቂ ቃዎች ውስጥ ያልቃል ብሎ ገመገመ ። ምክንያቱም በቂ ጥይቶች ስለ ሌሏቸው ተኩሱ እንደዚህ እንደአሁኑ ሊቀጥል እንደማይችል ግልጽ ነበር ።

ምንም እንኳን ተከላካዮቹ አስተሳሰቡን ከፊቱ ላይ ቢያነቡትም በአረቦቹ ላይ ውጥረትና ፍርሃት ለመፍጠር ቶኩሱን በበለጠ አፋፋ

ሙት ። ሆስነር በጨለማው ውስጥ አረቦቹ እየገፉ ሲመጡ በከፊል ቢያያቸውም የጥይቱ ተኩስ እየጨመረ በመምጣቱ አመነቱ ። ቢያዘ ግሙም አላፈገፈጉም ። እያየለ የመጣው ውጊያቸው ወደዚያው ቆመ። ሆኖም ወደፊት ለመግፋት ቢፈሩም ወደኋላ አልተመለሱም ። አዛገ ቻቸው እየጮሁ ብርታት እንዲያገኙና ወደፊት እንዲገፉ ምከሩ ። በመ ሆኑም ጥቂት ቡድኖች እያመነቱ ወደፊት ቀጠሉ ።

በዚህ ጊዜ አዛገሮቹ በግልጽ እየታዩ ስለመጡና ብሪንም በዚህ ዕድል በመጠቀም ከሰላሣ ሴኮንዶች ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሁለቱን ዘረራ ቸው ። የቀሩት ሁኔታውን ስላዩ ተገን እየፈለጉ መጠለል ጀመሩ ። ብሪን አህመድ ሪሽን ለማግኘት በኃይል መፈለጉን ቀጠለ።የሪሽን ፎቶ ግራፍ ከሆስነር ማስታወሻ ውስጥ ወስዶ ስለአጠናው ላለፈው አንድ ሰዓት የአዕምሮው ዓይን በእያንዳንዱ አረብ ላይ የሪሽን ፊት ሲመለከት ይሰ ማው ነበር ። ያንን ፊት ካየው ሌላ እንዳልሆነና እንደሚያውቀው እር ግጠኛ ነበር ።

እስራኤሎቹ የአረቦቹን ጫጫታ ሲሰሙ ሁኔታቸው ገባቸው ። በአረቦቹ አለቆች መካከል ችግር እንደተፈጠረ ገመቱ ። ከእስራኤሎቹ ውስጥ የጦር ልምድ የነበራቸው ምን ማድረግ እንደሚገባቸው አውቀ ዋል ። ሆስነር ተደንቆ እየተመለከተ ባለበት ጊዜ ከማንም ትዕዛዝ ሳይ ቀበሉ ሃያ የሚሆኑ ወንዶችና ሴቶች አቆልቁለው መሮጥ ጀመሩ ።

ዶብኪን ነገሩ ምን እንደሆነ አውቋል ። የማሸነፍ ዕድል እንዳ ለም አምኗል ። እስራኤሎቹ ይህን ያደረጉት በወጊዎቻቸው ልብ ውስጥ ፍርሃት ለመስደድ ነበር ። ይህ ዓይነቱ ስሜታዊ ድርጊት የጠላት ደም ወይም ወኔ እንዲቀዘቅዝ ያደርገዋል ። በመጀመሪያ ፈሪዎቹ መፈር ጠጥ ይጀምራሉ ። ልባሙ እንኳን ቢሆን አጥቂ የነበረው ሲጠቃ ሲያ የው አብሮ ይሸሻል ። የተዘጋጀ ደጀን ወይም ተከላካይ ባለመኖሩ ነፍሴ አውጭኝ ብለው ሲሮጡ ይታያሉ ።

ነገር ግን አሸባሎቹ በወንዙ ዳርቻ ሌላ ኃይል ቢኖራቸው ኖሮ ውጤቱ ምን ይሆን ነበር ? በዚያ በኩል ውጊያ ቢጀምሩ ኖሮ ዶብኪን ተጨማሪ ኃይል መላክ አይችልም ነበር። በምሥራቃዊ ሸንተረር በኩል ያልተፈቀደ የአጸፋ መልስ ለመስጠት ከግማሽ የበለጠ መንገድ ወር ደዋል ። ሰዎች ለትዕዛዝ ተገዥ በማይሆኑበት ጊዜ የዚህ ዓይነት ያጋ ጥማል ። ዶብኪን ወደ ምሥራቃዊ ዘቅዛቃ ቦታ እየሮጠ ሔደ ።

ሆስነር ከብሪን ላይ ኤም—14 ጠመንጃ ተቀብሎ አጉልቶ በሚ ያሳይ የኮከብ ብርሃን ባለው መነጽር መመልከት ጀመረ ። ለጊዜው ሁሉም ነገር የተስተካከለ መስሎ ታየ ። አሸባሎቹ በድንጋጤ ተርበድ

ብደው በዶብታቱ ኖር ከፍተኛ እልቂት ይደርስ ነበር ። እስራኤሎቹ የነ በራቸው መሣሪያዎች ቀላል ከመሆናቸውም በላይ በብዛትም አምስት ለአንድ ነበሩ ። አሸባሎቹ አምሳ ሜትር እርቀት ላይ ደርሰው ስለነበረ እስራኤሎቹ እያነጣጠሩ ያለስህተት ግባቸውን መቱ ። ጆሹዋ ሩቢን በሁኔታው እንደ እብድ ሆነ ። እየሮጠ ሔዶ በኡዚው ያለማቋረጥ ተ ኮሰ ። ሆስነር የኡዚው ካርታ ግሎ እንዳይፈነዳ ፈርቶ ነበር ። ሆስነር ከተኩሱ ይልቅ የሰዎቹ ጩኸት ተሰማው ።

ሩቢን እንዳይመታ ለመከላከል ሆስነር በኤም—14 ጠመንጃው እያነጣጠረ ተኮሰ ። አንድ ሰው መስመሩን ለቆ ሲሮጥ አየው ። ሁለት ወጣት ሴቶች ተከተሉት ። ከዚያም ሌሎች አብረው ተግተለተሉ ። በመሸሸ ላይ የነበሩት አሸባሎች በአረብኛ አፈግፍጉ እያሉ ጮኸው ሲናገሩ ሰማቸው ። ጥቂት መሪዎቻቸውና የአምሳ አለቆች ተመልሰው እንዲፃ ጉ ለማድረግ ሞከሩ ። ሆስነር አነጣጥሮ አንደኛውን ጠበሰው ። የኮከብ ብርሃን መነጽር ባለው መሣሪያ እንደሚጠቀሙና በዚህም ብዙ ጉዳት እንደደረሰባቸው ለመሪዎቻቸው ግልጽ ሆነ ። ከአሁን በኋላ ለመቋቋም ቢሞክሩ ራሳቸውን በራሳቸው እንደመግደል መሆኑን ተገ ነዘቡ ። ሆስነር እንደገና አነጣጥሮ ሌላውን መሪ ፈነገለው ። መሣሪያ ውንም ለብሪን መለሰለት ።

በመጨረሻም የነበረው ጩኸት በጦርነቱ ለቆሰሉት መሪዎቻ ቸው መሸከሚያ ወሰካ (ቃሬዛ) እንዲሁም የሕክምና ባለሙያዎች ለማ ግኘት ነበር ። የቀሩት የአሸባል መሪዎች የሚያፈገፍጉትን ተከትለው ነጐዱ ።

እስራኤሉቹ በንዴትና በወኔ ተሞልተው ጠላቶቻቸውን ወግተ ውና አሳደው በማብረራቸው በርዶላቸዋል ። አሻባሎቹም ከእስራኤ ሉ ቹ እየራቁ ስለሔዱ በመስመር ገብተው መንገዳቸውን ቀጠሉ ።

አሸባሎቹ የወደቁ መሣሪያዎቻቸውን ፡ ሙታናቸውንና ቁስለኞ ቻቸውን ሰብስበው እስኪሔዱ ድረስ የሚከላከልላቸው ዘብ አቁመው ነበር ። በቁልቁለቱ ላይ ሲወርዱ ናዳዎች በላያቸው ላይ ስለጐረፉ ባቸው ቁስለኞቻቸውንና ሙታናቸውን ትተው እንዲሔዱ ተገደዱ ። እስራኤሉቹ አሸባሉቹን ለመሸፈን ወደ ቆሙት ዘቦች እየተጠጉ በሚሔዱበት ጊዜ ከዶብኪን የተላከው ሩዋጭ እንዲመለሱ መታዘ ዛቸውን ስለነገራቸው መሔዳቸውን አቆሙ ። በጨለማው ውስጥ ሊያዩአቸው የቻሉትን የወደቁ መሣሪያዎች ሰብስበው በቆሻሻ ተበክ ለው በላብ ተጨማልቀውና ደክሟቸው ወደ ተራራው ጫፍ ተመ ለሱ ። ሩቢንና አንዲት ሩት ማንዴል የምትባል ጸሐፊ ቀላልጉዳት ደርሶባቸዋል ።

ምንም እንኳን በወንዙ ዳርቻ ጸጥታ የሰፈነ ቢሆንም ሆሰኔር እር ግጠኛ ለመሆን ሁለት ሰዎች ኤኬ—47 ጠመንጃዎች የያዙ ላከ ። በኮ ረብታው ላይ ጸጥታ ሰፈነ ። በአየሩ ውስጥ አፍንጫ የሚሰነፍጠው የባ ሩድ ሽታ ብቻ ነበር ።

ሆስነር ከብሪን ላይ ኤም—14 ጠመንጃውን ወስዶ በመሸሽ ላይ የነበሩትን አሸባሪዎች ተመለከተ ። በኤም—14 ተኩሶ ለመምታት ከሚ ቻልበት ውጭ ቢሆኑም የት እንደደረሱ ሊያያቸው ቻለ ። አንድ ሰው በትከሻው ላይ ረጅም ጸጉር ያላት ሴት ተሸክሞ በጉብታው ላይ በመ ቆም አሸባሪዎቹ ጨርሰው እስኪያልፉ ድረስ ይመለከት ነበር ። የብዙ ወንድሞቹ ሕይወት የተቀጨበትን ተራራ አቃንቶ ተመለከተ ። በእ ጁም አንድ እንቅስቃሴ አሳየ — ሰላምታ ወይም እርግማን — ሆስነር ሰውየው የትኛውን ለማለት እንደፈለገ ለይቶ ለማወቅ አልቻለም ። ሆስነር በእዚያ እርቀት ላይ ሰውየው ማን እንደነበረ በውል ለይቶ ባያ ውቅም ያለጥርጥር አህመድ ሪሽ እንደነበረ ገብቶታል ።

## —14—

የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር በቴል አቪቭ ውስጥ ባለው የምሽግ መሥሪያ ቤት ሥራ ማስኬጃ ክፍል መምጣቱን ሳያስታውቅ በድንገት ገባ ። የአየር ኃይል ሰዎች ፈጣን እይታ አድርገው ወደ የሥራቸው ተመ ለሱ ። የስልኮች ፣ የቴሌታይፕስና የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ጩኸት ነበር — ጠቅላይ ሚኒስትሩ በክፍሉ ውስጥ የሰማው ድምጽ በ1973 በዮም ኪፑር ከሰማው በጣም ይበልጥ እንደነበረ አስታወሰ ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሳያስበው በድንገት ወደ ጄኔራል ታልማን ትልቅ ክፍል ከተመለከተ በኋላ ነገሩን አስታውሶ ወደ ተካው ወደ ጄኔ ራል ሞርዲኬይ ሁር ሔደ ። ክፍሉ ሪፖርት በሚቀበሉና ትዕዛዝ በሚ ያስተላልፉ ሠራተኞች ተሞልቷል ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጄኔራል ሁር አጠገብ ቆሞ “ ከኮንኮርድ 01 ተሳፋሪዎች ውስጥ በሕይወት የተገኘ አለ ? ” ብሎ ጠየቀው ። ሁር ልክ እንደቀድሞ አለቃው ዓይነት ነበር ። በእንግሊዞች የሰለጠነ ፣ ቁጥብ ፣ ትክክለኛ ፣ ጥሩ ተናጋሪና ጥሩ የሚለብስ ነበር ። ጠቅላይ ሚኒ ስትሩ ከእነዚህ ነገሮች አንዱም አልነበረው ። የሚፈልገው ግን ከታ ልማን ጋር ጥሩ መግባባት ስለነበረው ከሁር ጋርም ይኸው እንዲኖ ረው ተስፋ አድርጓል ።

ጄኔራል ሁር ራሱን በአሉታ ነቅንቆ “ የለም ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ፤ እስከ አሁን ድረስ ከተሳፋሪዎቹ የግማሾቹን አሬሳ አግኝተናል” ብሎት በትካዜ ንግግሩን ቆም ካደረገ በኋላ “ በሕይወት የሚገኝ አንድም እንደማይኖር አንተም ታውቃለህ ” አለው ።

“ አውቃለሁ ” ብሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ኤሌክትሮኒኩ መሣሪያዎች ተመልክቶ “ ኮንኮርድ 02 ያለው የት ነው ሞቲ ? ። ” ብሎ ጠየቀው ።

ሁር ስሙ ተጠቅሶ በመጠየቁ በመጠኑ አስደንቆታል “ አላወኩም ። በየደቂቃው የት ቦታ እንዳሉ አለማወቃችን ያሉበትን ቦታ እያራቀው ከመሔዱም በላይ ነዳጅ መሙላታቸውንም ሆነ እስከ አሁን በአየር ላይ መሆናቸውን አላወቅንም ። ”

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራሱን ነቅንቆ “ በሱዳን ውስጥ በአሜሪካን ሳተላይት የተነሳው ፎቶግራፍ እንዴት ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ሁር ከአንድ ረጅም ጠረጴዛ ላይ አንድ ወረቀት አንስቶ “ በዚያ በመሬት ላይ ካለው ወኪላችን የተላከው ይህ ነው ። ፎቶ ግራፉ የሚያሳየው በመሬቱ ላይ ያለውን የአሉሚኒየም ስባሪ ሲሆን የኮንኮርድ ስፋትና ቅርጽ አለው ። ”

“ ጠላትን ለማታለል ነው ወይስ አደጋ ደርሶ ? ”

“ የሃሣብ ልዩነት አለ ። እኔ ጠላትን ለማታለል የተደረገ ዘዴ ነው እላለሁ ። ጥቂት ሰዎች ደግሞ በአጋጣሚ የታየ ተመሣሣይ እንጂ ኮንኮርዱ አይደለም ይላሉ ። ቢሆንም ስመከታተል የሚያስችሉ ሦስት ወይም አራት ፎቶግራፎች አግኝተናል ። ግልጽ ካልሆኑልን ፎቶግራፎቹን በልዩ ልዩ መሣሪያዎች በመመርመር የተሻለ ውጤት ለማግኘት እንጥራለን ። ከራዳር ፣ ከራዲዮና ከሌሎች እይታዎች የተገኙ ሪፖርቶች አሉ ። ”

“ ይህ በደንብ ታልሞ የተፈጸመና ድርጊቱም ከውስጥ ባለ ሰው መሆን አለበት ፤ አይደለም ? ”

“ [illegible] ሥራ ስላልሆነ ሺን ቤትዝን ጠይቀው ። ”

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከ[illegible] ጋር ለአንድ ሰዓት ያህል ተወያየ ። በተፈጸመው ድርጊት የውስጥ ደህንነት ክፍል እንደማንኛውም ተደንቋል ። ይሁን እንጂ ማዛር እንደ ሌሎቹ አሥራ ሁለት ሰዎች የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ አላቀረበም ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ “ በተግባር ጊዜ ሥራን መልቀቁ የሚረዳው ወይም የሚጠቅመው ነገር የለም ” የሚ

ዴብኮዱ በመሆኑ ·

ለውን አነጋገር ተግባራዊ የሚያደርገውን ሰው ያደንቃል ። ቢሆንም ማዛር በመጨረሻ እንደሚለቅ ያውቃል ።

አንድ ረዳት መኰንን የስልኩን መነጋገሪያ ይዞ በመምጣት የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ” አለው ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የስልኩን መናገሪያ ተቀብሎ “ አቤት ፤ ክብርት ጸሐፊ ” አላት ። ቀደም ብሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለጠየቀው ጉዳይ የቀረበውን ዘገባ ከጸሐፊዋ አዳመጠ ። የአረብ የሰላም ልዑካን አሁንም በኒውዮርክ ውስጥ አሉ ። እንዲመለሱ የጠራቸው የለም ። ግን ሁኔታው ያሰጋል ። ምናልባት እስራኤል በነገሩ በመቆጣትና እርምጃ በመውሰድ ለአረቦቹ ችግር ትፈጥር ይሆን ? ጠቅላይ ሚኒስትሩ በየትኛውም መንገድ ቢሆን አስተያየት አልሰጠም ። በግድግዳው ላይ የተሰቀለውን ሰዓት ሲመለከት ገና እኩለ ሌሊት ነበር ። ዋና ጸሐፊዋ ድካም የተሰማት ስለመሰለው “ አመሰግናለሁ ክብርት ጸሐፊ ፤ ወደ እስራኤል የሰላም ተልዕኮ ጽሕፈት ቤት ስልኩን ልታዛውሪልኝ ትችያለሽ ? ” አላት ።

በተባበሩት መንግሥታት ከእስራኤል ቋሚ መልዕክተኛና ለሰላም ተልዕኮው ስብሰባ ስኬታማነት ቀደም ብለው በመሔድ ሲያዘጋጁ ከነበሩት ከፍተኛ ሰዎች ጋር ተነጋገረ ። ብዙዎቹ በጠፋው አውሮፕላን ውስጥ ዘመዶችና ጓደኞች ነበሯቸው ። አንዳንዶቹ የቁጣ ፤ የምኞትና ተስፋ ያለመቁረጥ የተቀላቀለበት ሃሣብ ነበራቸው ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚነጋገርበት ጊዜ የራሱ ድምጽ እንደ ገደል ማሚቶ እየተመለሰ ተሰማው ። “ ሰላም የሚያድግበት ለምለም ቦታ አዘጋጅታችኋል ። ” ገበሬ ስለነበረ ይህን አባባል ይወደዋል ። “ ገና ዘሩን አልዘራንም ። መሬቱን እንደተዘጋጀ አቆዩት ። ነገር ግን መሬቱን ከጨው ጋር ቀላቅሎ ማረስ ከአስፈለገ — ” ብሎ ንግግሩን ቆም አደረገ ። የስልኩ መስመር አስተማማኝ አልነበረም — ቢያንስ የአሜሪካ ዋና የደህንነት ድርጅቶች እያዳመጡት እንደነበረ አያጠራጥርም ። እርሱም እንዲሰሙት ፈልጓል — ሌሎቹም ማወቅ ይኖርባቸዋል — ንግግሩን በመቀጠል “ ጨው ቀላቅለን እናርሰዋለን ። ዘሩም ለአስር ዓመቶች ሳይበቅል እንደሞተ ሆኖ ይቆያል ” ብሎ ስልኩን ዘጋው ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ጄኔራል ሁር ዞሮ “ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቴፑን እስኪያዳምጥና አስኪደውል ድረስ ጥቂት ደቂቃዎች ስለሚፈጅበት እስከዚያው ቡና እንጠጣ ” አለው ።

በክፍሉ ውስጥ ወደ ነበረው ቡና ቤት ሔደው ለየራሳቸው ቀዱ ። በመጀመሪያ ገጾቻቸው ላይ ኤል አል የተጻፈበት የኮንኮርድ ፎቶግራፍ ያሉባቸው የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጋዜጦች በአንድ ጠረጴዛ ላይ

ተከምረዋል ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀደም ብሎ ከሕዝብ ጋር ለማስተዋወቅ የኮንከርድ 01 በረራ የሚከበርበትን ምክንያት በማድረግ የተላከ ፎቶ ግራፍ እንደነበረ ገባው ። ሁሉም የተጻፉት በተለያዩ ቋንቋዎች ቢሆኑም አንድ ዓይነት አርዕስት ነበራቸው ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥቂቶቹን ጋዜጦች በጉጉት ተመለከታቸው ። " አንዳንድ ጊዜ በዚህ ትልቅ ዓለም ላይ ብቻችንን ነን የሚል ይሰማኛል ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ሰዎች ስለእኛ ያስባሉ የሚል ይሰማኛል " አለው ።

ጄኔራል ሁር በስኒው ውስጥ የነበረውን ጥቁር ቡና ተመለከተ ። ስለሰላሙ ስብሰባ ይወራ በነበረበት ጊዜ ፈጽሞ አላመነም ። አሁን ግን ብዙ ሰዎች ስለሰላም በሚደረገው ስብሰባ ማመናቸውን ስላየ ቀደም ብሎ በነበረው የተሳሳተ አመለካከት ጥፋተኛነቱ የተሰማው ከመሆኑም በላይ በትንሽ ነገር እንዳይደናቀፍ ተስፋ አደረገ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩን ቀና ብሎ እየተመለከተ " በወታደርነቴ ካገኘሁት የሥራ ልምድ ሰዎች ስለሰላም የሚጨነቁት በ11ኛው ሰዓት ላይ ነው ። በዚያ ሰዓት ግን ሁኔታዎች አብዛኛውን ጊዜ ሊለወጡ እማይችሉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ " አለው ።

" ታዲያ አሁን ያለነው በየትኛው ሰዓት ላይ ነው ብለህ ትገምታለህ ጄኔራል ? "

" መናገር አልችልም ጠቅላይ ሚኒስትር ። የተነጋገርነው ስለ 11ኛው ሰዓት ነው ። ለ11ኛው ሰዓት እሩብ ጉዳይ እስኪሆን ድረስ እንኳን ፈጽመው አያስቡም ። ማጣፊያው አጠረን የሚሉት ሁሉ ነገር አልቆ ደቆ አምስት ደቂቃ ካለፈ በኋላ ነው ። "

ረዳት መኰንኑ እንደገና ስልክ መነጋገሪያውን ይዞ በመምጣት " ከዋሽንግተን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው " አለው ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ጄኔራል ሁር መልከት ብሎ ስልኩን ተቀበለ ። "አቤት ሚኒስትር ። በቨርጂኒያ ያለው እርሻህ እንዴት ነው ? አዎን ፣ አውቃለሁ ። አያቶችህ በዚያ ኑሮ ከመሠረቱ ጀምሮ በባሕሩ ሞገድ ምክንያት አካባቢው ጨዋማ ሆኗል ። ጊዜዎች ይለወጣሉ ። የባሕሩ ሞገድ ምሕረት የሌለው ጨካኝ ነው ። እዚህም ተመሳሳይ ችግር አለብን ። ውሃው እንደፈለገ ለመንቀሳቀስ በቂ ቦታ አለው ። ግን ተጨማሪ መሬት የሚፈልግ ይመስላል " አለው ። ነገሮችን ግልጽ ባለማድረግ ለጥቂት ደቂቃዎች ከተነጋገሩ በኋላ ስልኩን ዘግቶ ወደ ሁር በመመለስ " በሽብር ፈጣሪዎች ላይ ደጋግመን በወሰድነው እርምጃ ያገኘነው ዝና አልጐዳንም ጄኔራል ። አሁንም ቢሆን ውይይቱን ለመቀጠል

የምንችል ስለመሆናችን እያንዳንዳቸው እርግጠኛ ለመሆን ይፈልጋሉ” አለው ።

ጀኔራል ሁር ሙያውንና ቦታውን በመዘንጋት “ ታዲያስ በእኛ በኩል ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥራ ማስኬጃ ክፍሉን ዙሪያ ካማተረ በኋላ ለብዙ ጊዜ ሳይናገር ቆየ ። ቀጥሎም “ አላውቅም ጀኔራል ፤ በ01 ላይ የተፈጸመውን መለወጥ አንችልም ። እኔ እንደምገምተውና እንደማ ስበው ከሆነ የሕዝቡ ሁኔታ የሚያተኩረው 02 ምን እንደሆነ ነው ። በእስረኛነት ከያዘው ሰው ለምን አልሰማንም ጀኔራል ? ” ብሎ ጠየ ቀው ።

“ መገመት አልችልም ። ”

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ ምናልባት አይ ሆንም ይሆናል . . .” አለው ።

“ ምኑ ? ”

“ ግድየለም ። ከኤይሮስፔሻል የደረሰንን ሪፖርት አይተኸዋል ?”

“ አዎን ፤ ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ እንደሚባለው የቀድሞ ምሳሌ ዓይነት ነው ። እኛን ሊረዳ የሚችል ምንም ነገር በሪፖርቱ ውስጥ አልሰፈረም ። ”

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደገና ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ የፍልስ ጥኤማውያን አዳፍኔ ሰዎች ምንም ነገር የሚያውቁ አይመስሉም ” አለው ።

“ የአደረጉት አውቀው እንደሆነ እደነቃለሁ ። ”

“ የረሳነው ሌላ ነገር አለ ፣ ሞቲ ? ”

ሁር ራሱን በአሉታ ነቅንቆ “ አይመስለኝም ። እዚህ ማድረግ የሚገባንን ሁሉ እየሠራን ነው ። ከቴህራን እስከ ማድሪድ ድረስ ካሉ የአየር ኃይል ማዕከሎች ጋር ባደረግነው ግንኙነት መሠረት እር ዳታ እያደረጉልን ነው ። የሚቀረው በደህንነት ክፍላችን ትከሻ ላይ የወደቀው ኃላፊነት ነው ” አለው ።

“ እንግዲህ አንተ በአልከው በኩልም ሆነ ከአህመድ ሪሽ የሚ መጣውን ጠብቀን የሚሆነውን እናያለን ።”

“ ምናልባትም ሁኔታውን ራሳችን እንደርስበት ይሆናል ። ”

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለመጨረሻ ጊዜ ክፍሉን በዐይኑ ጐብኝቶ "ሥራህን ቀጥል ፤ ሞቲ ፤ ቆይቼ አነጋግርሃለሁ" አለው ።

"እሺ ጠቅላይ ሚኒስትር ፤ የምንደርስበት ነገር ቢኖር የት አገኝሃለሁ ?"

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ነገሮችን አወጣ አወረደ ። የቴል አቪቭ ከተማ የመገናኛና የትራንስፖርት አገልግሎቶች በጣም ዘመናዊ ናቸው ። እንደዚሁም ለደህንነትም የተሻለ ነው ። በጦር ሚኒስቴር ጥናት መሠረት ማንኛውም ዓይነት ችግር በሚፈጠርበት ወቅት ቴል አቪቭ የሥራ ክንውን ማዕከል መሆን እንደሚገባው አረጋግጧል ። ይሁን እንጂ ኢየሩሳሌም ዋና ከተማ ነው — የፖለቲካ ማዕከል ብቻ ሳይሆን የእስራኤል ልብና ነፍስ — መሠረተ ሃሣብ ነው ፤ የአዕምሮ አመለካከት ነጸብራቅ ፣ የመንፈሳዊና የዘላለማዊ መታወቂያ — ቅጥ ያጣ ወይም ጨዋማ መሬትና ሮማውያኖች ትተውት እንደሔዱት ዓይነት ቢሆንም ኢየሩሳሌም ነው — "ኢየሩሳሌም — እኔም የምሔደው ወደ ኢየሩሳሌም ነው ።"

ሁር በአዎንታ ራሱን እየነቀነቀ ፈገግታ አሳየው ። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሔደ ።

* * *

ቴዲ ላስኮቭ በሎድ አውሮፕላን ማረፊያ በወታደራዊ ክፍል አጠገብ ብቻውን ቆሟል ። ከምሥራቃዊ ሰማይ ትክክለኛ ያልሆነ የጕህ ብርሃን የሚመስል በርቶ በሻሮን ሜዳ ላይ የሚገኘውን የሰማርያን ተራራ ወለል አድርጐ አሳየው ። ብርሃኑ እየደበዘዘ መጥቶ እጅግ በጣም የጨለማው ሰዓት እስኪጀምር ድረስ ትኩር አድርጐ ወደ ሰማይ ተመለከተ ።

ፊቱን አዙሮ በአስፋልቱ የአውሮፕላን ሜዳ ባሻገር ኤፍ—14 የሆኑ አሥራ ሁለት ጄት አውሮፕላኖች ወደቆሙበት ተመለከተ ። የሥልጣኔንና የሰውን ልጅ ክብር የሚጠብቁ ዘቦች መስለው ቆመዋል። ሰዎች የጦር አውሮፕላኖች ናቸው ብለው ይጠሯቸዋል ። ላስኮቭ ግን የሰላም ጠባቂ አውሮፕላኖች ተብለው መጠራት ይገባቸዋል የሚል ሃ ስተሳሰብ በልቦናው አደረበት ። በሩስያ ከነዳው የመጀመሪያ አውሮፕላን እስከ አሁን ድረስ ላለፉት 40 ዓመቶች በየአውሮፕላኖቹ ውስጥ ያጋጥሙት የነበሩትን የወንበር ቆዳ ሽታ ፣ የቡና ቤቱ ፣ የራዲዮኑና የሠራተኞቹ ትውስታና እነዚህንም ዳግመኛ እንደማያገኛቸው በአዕምሮው ውስጥ ተሰማው ።

ከቆመበት ዞሮ መኖሪያ ቤቱ ወዳለበት ሔርዝሊያ ለመውሰድ ወደ ሚጠብቀው ጂፕ ሔደ ። በጂፑ ላይ ሲሳፈር እንደገና ወደኋላው ዞሮ

ተመለከተ ። የመኪናው ነጂ ሞተሩን ቀስቅሶ ፡ መብራቱን አብርቶና ማርሹን አስገብቶ መንገዱን ቀጠለ ።

ላስኮቭ ባርኔጣውንና ኮቱን አውልቆ በጭኑ ላይ አስቀምጦና ወደ ኋላው ተለጥጦ በመቀመጥ ስለሚሪያም አሰበ ። ዕድልዋ ለጥቂት ደቂቃዎች በእርሱ እጅ ውስጥ ነበር ። የጦር አውሮፕላኖቹ በቁጥጥሩ ሥር በነበሩበት ጊዜ የሕዝቡ ዕድል በእርሱ ላይ ያረፈ ነበር ። አሁን ግን ከኮቱና ከባርኔጣው በስተቀር በእጁ ውስጥ አንድም ነገር የለም ። አዛዥነቱን መተው ጥሩ ሆኖ ታየው ። በሌላ በኩል ደግሞ ባዶነት ተሰማው ። ብቸኝነትም በቶሎ አጠቃው ። ያለ ሚሪያም ደግሞ የባሰ ብቸኝነት ይሰማዋል ።

ነጂው በጉን በኩል ዘወር ብሎ ተመለከተው ።

ላስኮቭ ከራሱ ዘወር ብሎ ራሱን በማስገደድ ፈገግታ አሳየው ።

ወጣቱ ነጂ ጉሮሮውን አፍታቶ “ ወደቤት ነው ፡ ጄኔራል ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ አዎን ፡ ወደ ቤት ነው ። ”

# 15

የጥዋትዋ ፀሐይ ብልጭ ብላ መውጣት የጀመረችው በ12 :03 ሰዓት ነበር ። ንጹሁ ሰማይ በብርሃን ወገግታ ተሞላ ። የጥዋቱ አየር ትንሽ ቀዝቀዝ ያለ ቢሆንም የወንዙ እርጥበት ተራራውን አወርዝቶታል ። አየሩ እየሞቀ ስለመጣ በውሃው ላይ የነበረው ጭጋግ መትነን ጀምሯል ። ደብዘዝ ባለው ብርሃን ውስጥ በያለበት የወፎች ዝማሬ ተሰማ ። 12 :09 ሰዓት ሲሆን በሩቅ የሚታየው በኢራን ውስጥ ባለው በዜግሮስ ተራራዎች ላይ ፀሐይ ስለወጣች ጭጋጉ መልቀቅ ጀመረ ።

በጤግሮስና በኤፍራጥስ ሸለቆዎች ውስጥ ጥንት ነዋሪ የነበሩ ሰዎች እነዚያን በጭጋግ የተሸፈኑ ምሥራቃዊ ተራራዎች ጧት ጧት በፀሐይ ብርሃን ባዩ ቁጥር ምን ያስቡ ነበር ብሎ ሆስነር ለራሱ አሰላሰለ ። አንድ ወቅት ከፊል አረመኔና ደም የጠማቸው የፕሩሲያ ሰዎች ወግተው የጤግሮስንና የኤፍራጥስን የቆየ ሥልጣኔ አጥፍተዋል ። ተዋጊዎቹ ቀስ በቀስ በሸለቆው ውስጥ ነዋሪ የነበሩትን የጥንት ሰዎች ባሕል ተቀብለዋል ።

በአሁኑ ጊዜ ኢራንና ቱርክ ተብለው ከሚጠሩት አገሮች በየምዕተ ዓመቱ እየፈለሱ በመጡ የተራራ ሰዎች ይወጉ ነበር ። የጥንቶቹ

ከተሞች ፥ መንደሮችና የእርሻ ቦታዎች በየጊዜው ይመጡ በነበሩ ተዋጊዎች የጥፋት ፥ የንብረት ዘረፋ ፥ ከፍተኛ ግድያዎች በማድረስ ሁሉንም እንደፈለጉት ካመቻቹና ግድያውን ካቆሙ በኋላ በአዲስ ገዥዎች ይተዳደሩ ነበር ። ቀጥሎም ከደቡባዊ በረሃዎች የመጡ አረቦች የቀድሞዎቹን የማምለኪያ ጣኦቶች አጠፉ ።

እጅግ በጣም አስከፊ የሆነው ድርጊት የተፈጸመው በሞንጐሊያ ሰዎች ነበር ። እነዚህ ተዋጊዎች የጥንት ከተሞችንና የመስኖ ሥራዎችን ጨርሰው በማጥፋታቸው ሜሶፖታሚያ እንደገና እንዳታገግም ሆና ጠፋች ። በዚያ ዘመን በዓለም ላይ ከግብጽና ከቻይና ውጭ ከ20 እስከ 30 ሚሊዮን የሚደርስ ሕዝብ የነበራት አገር በደረሰባት ጥፋት ምድረ በዳ በመሆን በበሽታ የተጠቁና በፍርሃት የተዋጡ ጥቂት ሚሊዮን ሕዝብ ብቻ የሚኖርባት ሆነች ። ለአራት ሺህ ዓመቶች ያለማቋረጥ ይታረስ የነበረው መሬት ወደ አቧራነት ተለወጠ ። የወባ መራቢያ እረግረግና የአሸዋ ክምር ተተካበት ። መንቶቹ ወንዞች እንደፈለጉ ፈሰሱ። ከጥቂት ምዕተ ዓመታት በኋላ ቱርኮች በመጡበት ጊዜ አገሪቱ የባሰ እየቀዘቀዘች ሔደች ።

በ1917 እንግሊዞች ቱርኮችን በጦርነት አብርረው በያዙበት ጊዜ ሥልጣኔ የመነጨባት አገር ነበረች ብለው ማመን አልቻሉም ። በቁርና ውስጥ የኤደን አትክልት ተብሎ በታሪክ ይነገርለት የነበረው ቦታ መርዘኛ ሕዋሳት የሚኖሩበት እረግረግ ሆኗል ። የእንግሊዝ ወታደሮች ሲቀልዱ “ ይህ የኤደን አትክልት ከሆነ ፥ ገሃነመሳትን ማየት አጠ ላለሁ ” ይላሉ ።

ዘመናዊ የኢራቅ ሰዎች ቀድሞ ደርሶባቸው የነበረውን ሰቀቀንና ከጥንት ሲያያዝ የመጣውን የጀግንነትና የኩራት ባሕላቸውን አሁንም አልረሱም ። አህመድ ሪሽም ይህ ጠባይ አለበት ። በቴል አቪቭ ወይም በኢየሩሳሌም ውስጥ የሚኖር አንድ ሰው ይህ ሁኔታ ከገባው “ የባቢሎን ምርኮኞች ” ማለት ይችላል ።

ሆስነር የመከላከያ መስመሮቹን አንድ በአንድ ፈተሸ ። ሁለት ተጨማሪ ኤኬ—47 ጠመንጃዎች አግኝተዋል ። ምናልባት እንደትናንትና ማታው ተኩስ ቢከፈትባቸው በእነዚህ መሣሪያዎች ለመጠቀም የሚያስችሉ በቂ ጥይቶች አሏቸው ። ጥቂት ሰዎች በምሥራቅ ቁልቁለት በኩል የወደቁ መሣሪያዎች ለመፈለግ በፈቃደኛነት ከሔዱት በስተቀር አብዛኞቹ የመከላከያ ምሽጋቸውን በማዘጋጀት ላይ ነበሩ ። የሞቱትን ሁለት አረቦች መቃብር መቆፈሪያ የሚሆኑአቸው ከቁርጥራጭ አሉሚኒየም እንደዶማ አድርገው ሠርተዋል ።

በእስራኤሎቹ በኩል ሰባት ሰዎች የቆሰሉ ሲሆን የሰላሙ ተል ዕኮ አባል የነበረው ቼይም ታሚር በጣም ተጐድቷል ። ቁስለኞቹ ከካ ፕላን ጋር በጐጆው ውስጥ ተጠልለው በሁለት የሴት አስተናጋጆች ተገቢው እንክብካቤ ተደርጐላቸዋል ።

ከኮንኮርዱ ላይ ለመውረድና ለመውጣት እንዲችሉ ጭቃና ሸክላ እየጠፈጠፉ በደረጃ መልክ ሠርተዋል ። ለመደልደል ያስፈለገውን አፈር ያጋዙት በሻንጣዎቻቸውና በብርድ ልብሶቻቸው ነበር ።

ሆስነር በከፊል በአለቀው መወጣጫ ላይ አልፎ ወደ ኮንኮርዱ ውስጥ ገብቶ በተሳፋሪዎቹ መቀመጫ ክፍል በርግንና ዶብኪንን ስላ ገኛቸው " እንደምን አደራችሁ " አላቸው ። ያ ክፍል የጦር ፍርድ ቤት መሆኑ ይሆን ? በክፍሉ ውስጥ አሁንም የተቃጠለ የናፍታ ሽታ ነበር ።

ሁለቱም ራሳቸውን በአዎንታ ነቀነቁ ።

ዶብኪን ጉሮሮውን አፍታቶ " ያዕቆብ ፣ ይህ እኛን በጣም አሳ ዝኖናል ። በዚህ አካባቢ ጥሩ ዲሲፕሊን እንዲኖር ከፈለግን ትዕዛዝ በሚጥሱት ላይ አስከፊ እርምጃ መውሰድ አለብን " አለው ።

ሆስነር ሰዓቱን ተመልክቶ " ስሙ ፣ እዚህ ያላችሁት እኔ ትዕዛዝ ባለመቀበሌ በእኔ ላይ ክስ ለመመስረት አስባችሁ ከሆነ ፣ ትዕዛዝ በመ ጣስ እኔ ልከሰስ ስለማልችል ትልቅ ስህተት አድርጋችኋል ። ነገር ግን ሌላ ሰው እናንተም ጭምር ትዕዛዝ የማይቀበል ቢኖር ተሰብስበን ውሳኔ በማሳለፍ ለፍርድ እናቀርበዋለን " አላቸው ።

ዶብኪን ጐብደድ ብሎ " እያመጽክ ነው ? " ብሎ ጠየቀው ።

" እንደዚያ ብየ አልጠራውም ። "

" እኔ ግን አባባሉን እለዋለሁ ። በመካከላችን ከፍተኛ ሥልጣን ያለው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ነው ። የምክር ቤት ተመራጭ አባል ስለሆነ እርሱ — "

"እርሱን እርሳው ፣ ጄኔራል ። በውጭ ባሉት የታጠቁ ሰዎች በአብ ዛኞቹ አድራ ተጥሎብኛል ። ሕጋዊ ባለሥልጣን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ቢሆንም በተግባር ግን ሥልጣኑን የወሰድን እኛ መሆናችንን አንተም ታውቀዋለህ ። ለዚህም ነው በዚህ ትንሽ ስብሰባ ላይ እንኳን እንዲ ገኝ ያላደረከው ። አሁን ትልቁ ቁም ነገር እዚህ ካለነው ሦስቱ ሰዎች ውስጥ ኃላፊው ማን ይሁን ነው ። እኔ በበኩሌ እኔ ነኝ እላለሁ ። ነገር ግን ትዕዛዙ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በኩል ወይም ከእናንተ በአንደ

ኞችሁ በሙል እንዲደርሰኝ ቢደረግ እስማማለሁ ። ሁላችሁም ትዕዛዝ ማን እንደሚሰጥ ከገባችሁ ችግር አይኖርም ፤ ትስማማላችሁ ?'' ብሎ ሆስነር ነገራቸው ።

በመካከላቸው የረጅም ጊዜ ጸጥታ ሰፈነ ። በርግ ለመጀመሪያ ጊዜ '' የውጊያው ሒደት እንደ ጥንት ዓይነት ነው ብየ አምናለሁ ። ያዕቆብ ሥልጣኑን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አላግባብ ወስዷል ። የእኛም በዘዴ የተሞላ ተቀባይነት ተጨምሮበታል ። ከዚህ በኋላ ወደኋላ ሒደን የምናደርገው ነገር የለም ። እንግዲህ ያዕቆብ በረቀቀው ችሎታው ይጠቀማል '' ብሎ ሲናገር ለማንም ወገናዊ ባለመሆን ነበር ።

ሆስነር ምንም አልተናገረም ።

እንደገና የረጅም ጊዜ ጸጥታ ሆነ ። ዶብኪን በለሰለሰ አንደበት '' ይህን ለምን ታደርጋለህ ያዕቆብ ? '' ብሎ ጠየቀው ።

ሆስነር ትከሻውን ከፍና ዝቅ አድርጎ '' ምክንያቱም እኔ እንደ ምገምተው ይህን ሁኔታ ልቋቋም የምችለው እኔ ብቻ ነኝ ። ለዚህም ራሴን አምነዋለሁ ። የአንተ ሁኔታ ስሜቴን በመጠኑም ቢሆን ነክቶታል '' አለው ።

ዶብኪን ራሱን በአሉታ አነቃነቀ ። '' አይደለም ። ምክንያቱ እዚህ ስለአገኘኸን ነው ። አሁን እኛ ከነገሩ እንድንወጣ ትፈልጋለህ ። አንተ ጀግና ተብለህ ለመጠራት ትጥራለህ ። ወደ አገራችን ስንመለስ ዝናህ እንዲስፋፋ ትመኛለህ ። አንተ ይህ እስከ ተሟላልህ ድረስ ለሌላው ግድየለህም '' አለው ።

ሆስነር ይህን ሲሰማ ፊቱ ቀላ ። '' የፈለግኸውን ብትናገር ጄኔራል '' ብሎ ወደ በሩ ከተራመደ በኋላ ከትከሻው ዘወር ብሎ '' በዚህ አውሮፕላን ውስጥ ልክ እኩለ ቀን ሲሆን ስብሰባ ይኖረናል '' ብሏቸው ሔደ ።

ሆስነር እንደወጣ ቤከርንና ካንን አገኛቸው ። አሁንም ጀምረውት የነበረውን የረዳት ኃይል ማስጫውን ጥገና ሥራ እያከናወኑ ነበሩ። በጕናቸው በኩል በርከክ ብሎ '' ትናንትና ማታ በራዲዮ የማስተላለፍ ዕድል እንዴት አላገኘንም ? '' ብሎ ጠየቃቸው ።

ካን በአካባቢያችን በነበረው ከፍተኛ ድምጽና ጫጫታ ምክንያት በሥራችን ላይ ተመስጦ አልነበረንም '' አለው ።

ሆስነር ፈገግ ብሎ '' አዝናለሁ ፤ ዛሬ ማታ ሁሉም ነገር ጸጥ እንዲል እንሞክራለን '' አላቸው ።

“ በዛሬው ቀን እስከ ምሽት ድረስ እግዚአብሔር ከዚህ እንደሚ ያወጣን ተስፋ አደርጋለሁ ” አላቸው ካን ።

ሆስነር ተመልክቶ “ ይህ በአብዛኛው ጕኑ በእናንተ ትከሻ ላይ የወደቀ ስለሆነ የእናንተ የሁለታችሁ ጥረት ለችግራችን መፍትሔ ይሆናል ብለን እናምናለን ” አላቸው ።

“ ካፒቴኑ እኔ ስለሆንኩ የራዲዮ ግንኙነት ካደረኩ ምስጋናውን የማገኘው እኔ ነኝ ። ካልሆነ ደግሞ ወቀሳው የሚያርፈው በእኔ ላይ ነው ” ብሎ ቤከር ሲናገር ድምጹ ቀዝቃዛ ነበር ።

ሆስነር ቆሞ “ በእርግጥ አውሮፕላን በሰማይ ላይ ሲበር ለማየት እያንዳንዱ እየተመለከተ ነው ። ማንም ቢሆን እንዳየ እየሮጠ መጥቶ እንዲነግርህ ለሁሉም ትዕዛዝ ተሰጥቷል ። መወጣጫው በጥቂት ሰዓ ቶች ውስጥ ተሠርቶ ስለሚያልቅ እናንተ በአውሮፕላኑ ውስጥ ሆና ችሁ አውሮፕላኑ በታየ በሁለት ደቂቃ ውስጥ ማሰራጨት ትጀምራላ ችሁ ። አባባሌ አጥጋቢ ነው ? ” ብሎ ጠየቃቸው ።

“ መልካም ነው ” አለው ቤከር ።

ሆስነር አሻቅቦ የአውሮፕላኑን ክንፍ ተመልክቶ ወደ አንድ ውሳኔ ላይ የደረሰ መሰለ ።

“ የሚቀረውን ነዳጅ በሙሉ እንዲወጣ ላደርግ ነው ” አለው ሆስነር ።

ቤከር ትኩር አድርጐ ከተመለከተው በኋላ “ ረዳት የኃይል ማመ ንጫውን ለማንቀሳቀስና በምናገኘው ኤሌክትሪክ ራዲዮኑ እንዲሠራ ለማድረግ ነዳጅ ያስፈልገኛል ” አለው ።

“ ረዳት የኃይል ማመንጫው እየሠራ አይደለም ፤ ወደፊትም አይሠራም ። የመጀመሪያ ቀደምትነት የምንሰጠው አረቦቹ እዚህ እን ዳይደርሱ ማድረግ ነው ። እንደ አጋጣሚ የኃይል ማመንጫው ቢሠ ራም እንኳን አህመድ ሪሽ በመስመራችን ላይ ኃይለኛ ሞገድ መስደ ዱን ስለሚቀጥል ጥቅሙ ያነሰ ነው ። ስለዚህ ነዳጁን ሊፈነዳ በሚችል ባቸው ዕቃዎች ውስጥ በማዘጋጀት ልንጠቀምበት ይገባል ፤ ካፒቴን ።”

“ ነዳጁን እንድትነካ አልፈቅድልህም ። ”

ሆስነር በአንክሮ ተመለከተው ። “ የቴክኒክ ሠራተኞች ጀብዱ ሳይሠሩ እንደማንኛውም ተራ ሰው መሞት አይፈልጉም ። በረዳት የኃይል ማመንጫው ላይ ጊዜ በከንቱ እያጠፋህ ነው ። ዋጋ የሌለው ነገር ነው ። ስለዚህ ወደ መንጃ ክፍልህ ሒደህ ባትሪዎቹ እስከ አለቁ

ድረስ ራዲዮኑን ሞክር ። ለኋላ ብለን ኤሌክትሪክ ለማመንጨት የምን ጨነቅበት ጊዜ የለንም ። ትናንትና ማታ እንደ አደረግነው ባገኘነው ሁሉ በመጠቀም ለመዋጋት አሁን ካልሠራን በስተቀር ለኋላ የሚባ ለው ነገር አይጠቅመንም ” ብሎ ወደ ቤከርና ካን ተመለከተ ። ቀጥ ሎም ድምጹን ዝቅ በማድረግ “ በተጨማሪም ነዳጁ በሙሉ በዚያ ውስጥ እንዲቀመጥ አልፈልግም ። በአንድ ምክንያት እሳት ቢነሳ ሁለ ታችሁም በዚያው ትቀቀላላችሁ ” አላቸው ።

በሆስነር ሃሣብ ቤከርም ተስማማ ። ወደፊት ለሚያጋጥሙ ችግ ሮች ብዙ መፍትሔ ሊገኝላቸው ይችላል ። “ ስማ ራዲዮኑ ለመቀ በል የሚያስችለው ጊዜ እስኪመጣ ድረስ ረዳት የኃይል ማመንጫ ውን ለመጠገን እንሞክራለን ። የምትፈልገውን ነዳጅ ውሰድ ። ምና ልባትም ከምንገምተው በላይ ይቀር ይሆናል ። ስለዚህ ዕቃዎችህ የሚ ይዙትን ያህል ከወሰድህ በኋላ የሚቀረው በዚያው በጋኑ ውስጥ ይቆይ ፤ ትስማማለህ ? ” አለው ቤከር ።

ሆስነር ፈገግታ አሳየው ። “ አውሮፕላኑ ውስጥ በነበርንበት ጊዜ በጠየከው መሠረት ሙሉ ታዛዥነቴን አሳይቼሀለሁ ። ሌሎቹም ያለ አንዳች ክርክርና ግልግል ተቀብለዋል ። ምክንያቱም ካፒቴኑ አንተ ስለነበርክ ነው ። አሁን ደግሞ ከአውሮፕላኑ ውጭ አዛዡ እኔ ነኝ ። ታዲያ አውሮፕላኑ ውስጥ ያደረግነውን በዚህ በውጭ እኔ ለምን አል ጠይቅም ? ”

ቤከር ራሱን በአሉታ ነቅንቆ “ አንድ አይደለም ፤ በአውሮፕላኑ ውስጥ የሚደረገው ሁሉ በተጨባጭና በቴክኒክ ላይ የተመሠረተ ስለ ሆነ ልዩ ነው ። እዚህ ግን የሚቀርበው ሃሣብ በግል ስሜት ላይ የተጸ ነሰ ስለሆነ ለመወያያ የሚያስችል መድረክ አለ ” አለው ።

ሆስነር አንጋጦ በፀሐይ ምክንያት የሚያብረቀርቀውን ከተመለ ከተ በኋላ “ የመጨረሻ ውሳኔ አደርጋለሁ ። እስከዚያው ድረስ በነዳጁ የምንጠቀምበት ፈንጂ ለመሥራት እሔዳለሁ ” ብሏቸው መን ገዱን ቀጠለ ።

በኮንኮርዱ ጅራት ጥላ ሥር ሺሞን ፔልድና ኤሸር አሮንሰን ከተ ባሉ የበታች ረዳት መኩንኖች ጋር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በመሬት ላይ ተቀምጧል ። የሰላሙ ድርድር ተካፋዮች ያአኮብ ሳፒር የግራ ክንፍ የምክር ቤት አባል — ሆስነር ከምንም የማይቆጥረው — ሚሪያም በርንስቴይን — እንክብካቤ የሚያደርግላት — አብረው ከሚኒስትሩ ጋር ተቀምጠዋል ።

ስብሰባቸውን በዕረፍት ምክንያት አቋርጠው ስለምክር ቤት ክር ክር ያደርጉ እንደነበረ ገብቶታል ። ሆስነር ወደ እነርሱ ተጠጋ ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሆስነርን በዚያ በማየቱ የተደነቀ መሰለ ። ነገሩንም አብሰለሰለ ። ዶብኪንና በርግ ሆስነርን በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ያደረጉት ሙከራ እንዳልተሳካላቸው በትክክል ገመተ ። ስለሁኔታው በፍጥነት ግምገማ ስላደረገ ሆስነርን ለማነጋገር ከመቀመጫው ተነስቶ “ ማታ ስላደረከው አመርቂ ተጋድሎ ምስጋና ለማቅረብ ትክክለኛ ጊዜ አላገኘሁም ነበር ” አለው ።

ሆስነር ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ አመሰግናለሁ ሚኒስትር” ካለው በኋላ በቸልታ እየተመለከቱት በአቧራው ላይ የተቀመጡትን አራት ሰዎች አንገቱን ቀለስ አድርጎ እያያቸው “ ዛሬ ጧት ለእናንተ የሥራ ድርሻችሁን ለመስጠት ጊዜ ባለማግኘቴ አዝናለሁ ” አላቸው ።

“ መልካም ነው ፤ ልንጠቅም በምንችልበት ቦታ ላይ መሠማራቱ ያስደስተናል ” ብሎ ሚኒስትሩ የጀመረውን ሳይጨርስ ሆስነር “እስ ቤላችሁ የነበረው ፡ ሚኒስትር ፤ በአውሮፕላኑ ውስጥ የነበሩ ዕቃዎች በያለበት ተበታትነው ስለወደቁ እንድትሰበስቡ ነው ። ጥቂቶቹ እየተ ሽከረከሩ ከተራራው በታች ስለአረፉ ተጠንቅቃችሁ በመውረድ አም ጥታችሁ በሻንጣዎቹ ውስጥ ያሉትን ዕቃዎች ካወጣችሁ በኋላ ባዶዎ ቹን ሻንጣዎችና ልብሶች የመስመራችንን ድንበር ለሚጠብቁት ወን ዶችና ሴቶች ወስዳችሁ ትሰጣላችሁ ። ለመከላከያ እንዲያገለግሏቸው በሻንጣዎቹ ውስጥ አሸዋና አፈር ይሞላሉ ። በጨርቆቹ ደግሞ አሳሳች ምስሎች ይሠራሉ ። ለፋሻና ለሌላም የሚጠቅሙ ጨርቆች ሰብስባ ችሁ ያዙ ። እንደዚሁም እንደ አልኮል መጠጥ ፡ መድኃኒት ፡ ምግብና የመሳሰሉትን ሰብስባችሁ አምጡ ” ብሏቸው ለትንሽ ጊዜ ንግግሩን ቆም ካደረገ በኋላ ዝቅ ባለ ድምጽ “ ከመድኃኒቶቹ ውስጥ በብዛት ሲወሰድ ያለሕመም ቶሎ የሚገድለውን መድኃኒት ለይታሁ ያዙ ። ይህን ግን ለማንም እንዳትናገሩ ። ግልጽ ነው ? ” አላቸው ጮኾ ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ ጥሩ ነው ። ስብሰባው እንዳለቀ እንጀምራለን ” አለው ።

ሆስነር የአሉታ መጠነኛ የራስ ንቅናቄ አደረገ ። “ መልካም እን ግዲህ ስብሰባው ቢበተን ይሻላል ” አላቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ። ቀጥሎም ተቀምጠው ወደ ነበሩት ዞሮ “ ሁላችሁም ተስማማችሁ ፤ አዎን በሉ ” አላቸው ።

ጥቂት የሹክሽክታ ድምጽ ከተሰማ በኋላ ከሚሪያም በርንስቴይን በስተቀር ሁሉም ተንስተው ሔዱ ። ሆስነርም ዞሮ ወደ ሌላ አቅጣጫ መራመድ ጀመረ ።

በርንስቴይን ተከትላ " ያን መልካም ሰው አዋረድከው " አለችው ።

መልስ አልሰጣትም ።

" አልሰማሽኝም ማለት ነው አንተ የተረገምህ ? "

መሔዱን ቢያቆምም ፊቱን ወደ እርስዋ ሳያዞር " ማንም ሰው በእኔ ላይ አላግባብ ቢቀልድ ራሱን ለውርደት ያጋልጣል ። በከፍተኛ አደጋ ላይም ይወድቃል ። አንቺ ለምታደርጊው ማንብንብ ጊዜም ሆነ ትዕግሥት የለኝም ፤ ሚሪያም " አላት ።

ዞራ ከፊቱ ከቆመች በኋላ በለሰለሰ አነጋገር " ምን ነካህ ፥ ያዕቆብ ? እንደዚህ ታደርጋለህ ብየ ማመን አልችልም " አለችው ።

ወደ እርስዋ ጠጋ ብሎ አቆልቁሎ ዓይኖቿን ሲመለከት እንባ እንዳቀረሩ አየ ። ነገር ግን የቁጣ ወይም የሀዘን እንባ መሆኑን ከሁኔታዋ ሊረዳ አልቻለም ። አንዳንድ ጊዜ ስለሰላምና ዕርቅ ስትናገር መዘውሩ እንደተሞላ ሮቦት ትመስላለች ። እርስዋ ግን ደምና ሥጋ አላት ። በኮንኮርዱ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ በፍላጐትና ደካማነት ፤ በብርቱነትና በራስ መተማመን ለማያምን ወንድ ቀድመው መልስ ከሚሰጡት ሴቶች አንዷ መሆንዋን ሊያውቅ ችሏል ። ይህም በልጅነትዋ ትለብሰው ከነበረው ጥቁር ዩኒፎርም ጋር ግንኙነት ይኖረው ይሆን የሚል ግምት አደረበት ።

ስለእብሪተኛና ትዕቢተኛ እስራኤላዊ ቢያውቅም እንደ ሚሪያም በርንስቴይን ያሉ በካምፕ ውስጥ ያደጉ አይሁዳውያን ጋር መግባባት ያዳግተዋል ። ያለፍላጐቱ ጉንበስ ብሎ ቁጥሮች ይነቀሱባቸው ወደነበረው የእጅ አንጓዋ ተመለከተ ። ብዙ ሰዎች የፕላስቲክ ቀዶ ጥገና በማድረግ ቁጥሮቹ እንዲጠፉ አድርገዋል ። የእርስዋ ግን በእድገትዋ ምክንያት የቁጥሮቹ ቀለም ስለደበዘዘ በግልጽ አይታይም ።

" መልስ አትሰጠኝም ማለት ነው ? "

" ምን ? አዎን ፤ ምን ነካኝ ? ደህና ፤ እነግርሻለሁ ሚሪያም ። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ጄኔራል ዶብኪንና በርግ በጥይት በሚገድሉ ወታደሮች ፊት ሊያቀርቡኝ ተዳርሰው ነበር ።" አለማመንዋን ለመግለጽ አፍዋን ስትከፍት በእጁ ዝም እንድትል ካደረጋት በኋላ ንግግ

ሩን በመቀጠል “ በሌላ ነገር አትመልከችው ። እኔ በእነርሱ አልተቆጣሁም ። እንደዚያ እንዲያደርጉ በገፋፋቸው ሃሣብ እስማማለሁ ። እርምጃ ለመውሰድ በመረጡት ሃሣብ ግን አልስማማም ። አየሽ ፣ ነገሮችን ሁሉ ከእናንተ በበለጠ አበጥረው ያውቃሉ ፤ ይገባቸዋል ም ። እዚህ ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ያውቃሉ ሚሪያም ፤ የምነግርሽ በእውነት ነው ፤ ይህ ጉዳይ ለሚቀጥሉት 48 ሰዓቶች ቢቆይ ምግብ በሚከለክሉት ፣ በመጥፎ አሳቢዎች ፣ በከዳተኞች ፣ በዘብ ሥራቸው ጊዜ በሚተኙት ሰዎች ላይ ሞት እንዲፈረድባቸው ሁላችሁም ትጮሃላችሁ ። ለደስታ የምናውለው ጊዜ የለንም ። ዛሬ ከባድ መስሎ የሚታይሽ ነገ ቀላል መስሎ ይታይሻል ” ብሎ ነገራት ።

ከዓይኖቿ ላይ እንባዋን ጠርጋ ራስዋን በአሉታ ነቀነቀች ። “አንተ በሰው ልጅ ወይም በርኅራኄ ላይ ያለህ እምነት ትንሽ ነው ። አብዛኞቻችን እንደዚያ አይደለንም ። አንድ ሰው እንዲገደል ምርጫ ከማድረግ ይልቅ ራሴ እንድሞት እመርጣለሁ ” አለችው ።

“ ይህን ሃሣብ ይዘሽ ከቀጠልሽ ትሞቻለሽ ። ስንት ነገር ያየ እንደ አንቺ ያለሰው በሰው ልጅ መሠረታዊ ደህንነት እምነት እንዴት ሊኖርሽ እንደሚችል አላውቅም ” አላት ።

“ እኔ ያልኩት አብዛኛቹ የሰው ልጆች ጨዋ ናቸው ። ሁልጊዜም ቢሆን ጥቂት ፋሽስቶች አሉ ነው ። ”

“ እንደ አንቺ አባባል በሁላችንም ውስጥ ትንሽ ፋሽስትነት አለ። ሁኔታዎች እየከፉ በሚመጡበት ጊዜ አንቺንም የእዚህ ዓይነቱ ነገር ያስገድድሻል ። እኔም ይህን የማደርገው ሕይወታችንን ላለማስነጠቅ ነው ። በማወቅና በፈቃደኝነት በሰው ልጅ ላይ የሚደረጉ ጭካኔንና ክፋትን ለማሸነፍ እሞክራለሁ ። ”

አንጋጣ በችኮላ አየችው ። የገረጡ ጉንጮቿ ቀለም ተቀየረ ። “አንቻ — ” ብላ ለመናገር የፈለገችውን ሳትጨርስ ዞራ በሩጫ ሔደች ።

## —16—

ሆስነር ከብሪንና ከናኦሚ ሀበር ጋር አብሮ በጥበቃ ቦታቸው ተቀምጦ ወደ ምሥራቃዊ ቁልቁለት እየተመለከተና ሲጋራ እያጤሰ ከሁለቱ ወጣቶች ጋር ያወራል ። “ የጠመንጃህን መነጽርና አተኳኮስ እያስተማርካት ነው ? ” ብሎ ብሪንን ጠየቀው ።

ብሪን ትከሻውን ከፍ አድርጎ “ መማር አትፈልግም ” አለው ። ሆስነር ወደ ልጅቱ ዞሮ “ ለምን አትማሪም ? ” ብሎ ጠየቃት ።

በሰማያዊ ሱሪዋ ላይ የነበረውን አቧራ አራግፋ “ ጥሩ ተኳሽ አይደለሁም ። ጥሩና ፈጣን እሩዋጭ ነኝ ። ለዚህም በፈቃደኛነት እዚህ መጣሁ ” አለችው ።

ሆስነር መልስ ሊሰጣት ሲጀምር በድንገት ዶብኪን መጣ ። ሆስነር በፍጥነት ወደ እርሱ ከተመለከተ በኋላ ወደ ጠመንጃው ዞረ ። ግን ማንም አልነበረም ። ብሪንም የበረገገ መሰለ ።

ዶብኪን በኮንኮርዱ ውስጥ የተነጋገሩትን የረሳው ይመስላል ። ከራሱ ጉንበስ ቀና ብሎ ተቀመጠ ። ለጥቂት ጊዜ እንደኛቸውም አልተናገሩም ።

ሆስነር ዞሮ በደቡብ አቅጣጫ ሜዳውን አልፎ ወዳሉት ጉብታዎች እያመለከተ “ ያ ምንድን ነው ? ” ብሎ ጠየቃቸው ።

ዶብኪንም ወደዚያው ተመለከተ ። በቡናማው ሜዳ ላይ የቤቱ ጥላ አርፏል ። አልፎ አልፎ ካለው እረግረግ ላይ ጭጋግ ይወጣል ። “ በትልቁ አሌክሳንደር ምናልባትም ልዩ ልዩ ትርዕይት ለማሳየት የተገነባው ሞላላ የግሪክ አዳራሽ ነበር ። በ323 ዓመተ ዓለም ባቢሎንን በቁጥጥሩ ሥር ባደረገ ጊዜ ከተማው የጥንት ስለነበረ በመፈራረስ ላይ ሆኖ አገኘው ። እንደገና ለመጠገንና ለማሳመር ቢሞክርም አልቻለም። አሌክሳንደር የሞተው እዚህ ነው ። ይህን ታውቁ ነበር ? ” ብሎ ጠየቃቸው ።

“ አላውቅም ነበር ” ብሎ ሆስነር ሲጋራ አቀጣጠለ ።

“ ለስብሰባ ቶሎ ይመጣሉ ” አለው ዶብኪን ።

“ እነማን ፤ ግሪኮች ? ”

ዶብኪን ፈገግ ካለ በኋላ “ ከግሪኮቹ ጋር እኔም መሰብሰብ እችላለሁ ። እኔን ያስጨነቀኝ ጉዳይ የአረቦቹ ነው ” አለው ።

ሆስነርም የመልስ ፈገግታ ሰጠው ። በመካከላቸው የነበረው ውጥረት እየቀዘቀዘ መጣ ። “ ምናልባት ይመጡ ይሆናል ” ብሎ ወደ ብሪንና ናኦሚ ዞሮ “ እናንተ ሁለታችሁ ሔዳችሁ ለትንሽ ጊዜ ለምን በጥላው ስር አታርፉም ? ” አላቸው ።

ልጅቱ ቆመች ። ብሪንም ካቅማማ በኋላ ተነሳ ። ኤም—14 ጠመንጃውን አንስቶ ሲሔድ ተከተለችው ።

ትንሽ ራቅ ብለው ከሔዱላቸው በኋላ "በቀን ሊወጉን አይሞክሩም ይሆናል ። ይህን ነገር እልባት ለማስያዝ እስከማታም አይቆዩም ይሆናል " አለው ዶብኪን ።

" ልክ ነህ " አለው ሆስነር

" ምን ብለን እንንገራቸው ? "

ሆስነር ወደ እርሱ ተመልክቶ " ከእኔ ጋር ትተባበራለህ ? " አለው

ዶብኪን አቅማምቶ " እኔ . . . የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩና በርግ የበላዮቻችን ናቸው " አለው ።

" ደህና አስብበት ። "

ዶብኪን የውይይታቸውን ርዕስ በመለወጥ " ዛሬ ማታ የማልመ ለስበት ጉዞ አደርጋለሁ " አለው ።

" አውቃለሁ ። "

" ወደምፈልገው ቦታ ለማለፍ ብዙ ዕድል የለኝም ። የምሄደው እዚህ ያሉትን ሰዎች ተስፋ ለማደንደንና ሞራላቸውን ከፍ ለማድረግ ብቻ ነው ። "

" እኔም የምሰድህ ለዚህ ነው ። እኔም እንደማስበው አስቸጋሪ ጉዞ ነው ። ሊያሳዩህ የሚችሉ ሰዎች የሉም ። ያልከው ትክክል ነው ፣ ጀኔራል " ከአለው በኋላ ሆስነር እንደገና ተመልክቶት " ስለዚህ ከእኔ ጋር ትተባበራለህ ? " ብሎ ጠየቀው ።

ዶብኪን ትከሻውን ከፍ አድርጎ " ምን ልዩነት ያመጣል ? ሁሉንም በእጅህ አድርገሃል " አለው ።

" ለራሴ ማወቅ እፈልጋለሁ " ከአለው በኋላ ወደ ደቡብ እያመለከተ " በነገራችን ላይ ያ ምንድን ነው ? " ብሎ ጠየቀው ።

" ከአንተ ጋር ነኝ በማለት ጥሩ እንዲሰማህ አልፈልግም ። ከማንኛውም ገለልተኛ መሆን ያቀለኛል" ብሎ ወደ ደቡብ ከተመለከተ በኋላ ያ የካሳር ጉብታ መሆን አለበት ። ከጉብታው በስተጀርባ የናቡከደናጸር ቤተ መንግሥትና በዓለም ላይ በአስደናቂነታቸው ከሚታወቁት አንዱ የሆነው የባቢሎን የአትክልት ሥፍራ አለ ። በዚያ አጠገብ የኢሽታር በር ፣ ቤተ መዘክርና የእንግዶች ማረፊያ ቤት ይገኛል" ብሎ ለትንሽ ጊዜ ንግግሩን ቆም ከአደረገ በኋላ "ዛሬ ማታ ያንን ለማየት እሄዳለሁ " አለው ።

ሆስነር “ ይህን በመስማቴ እደሰታለሁ ” አለው ። ቀጥሎም ረዘም ላለጊዜ በመካከላቸው ጸጥታ ሰፈነ ።

ሆስነር በድንገት ተቅበጠበጠ ። በደቡባዊ ምዕራብ ወደ ኤፍራጥስ አቅጣጫ እያመለከተ “ በዚያ የሚታየው ጢስ ነው ? በፍርስራሾቹ ውስጥ ያለ መንደር ይመስላል ” አለው ።

ዶብኪን ሳይመለከት ራሱን በአዎንታ እየነቀነቀ “ ልክ ነህ ፣ የክዌሪሽ መንደር ነው ” አለው ።

“ ከእነርሱ እርዳታ ማግኘት ይቻል ይሆናል ብየ አስባለሁ ።”

“ አይመስለኝም ። ገበሬዎች ናቸው ። ከሌላው ዓለም ጋር ግንኙነት የላቸውም ። በተጨማሪም አሽባሎቹ አካባቢውን እንደሚቆጣጠሩት እርግጠኛ ነኝ ። ”

በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የተሠሩ የኢጣሊያን መንደሮች ጨርሰው እንዳይጠፉ በሮም ከተማ ዳርቻ እንዲቆዩ እንደተደረገው ዓይነት ተፋፍገው ከጭቃ የተሠሩትን ጐጆዎች ሆስነር ከሩቅ አየአቸው ።

አካባቢው ዓይንን የሚስብ ልዩ ልዩ መልክ አለው ። በምሥራቅ በኩል በረሃዎችና ረግረጐች፣ከእነዚያም ባሻገር የጢግሮስ ወንዝና ተራራዎች ይታያሉ ። በኤፍራጥስ ወንዝ ምዕራባዊ ዳርቻ ደግሞ እስከ አድማስ የሚደርስ በአሁኑ ወቅት ጭቃ የሆነ ከቅርብ ጊዜ በኋላ ግን በፀሐዩ ሙቀት ስንጥቅጥቁ የሚወጣ በጣም ሰፊ ሜዳ አለ ። በተጨማሪም በኤፍራጥስ ወንዝ ዳርቻ የተምርና ሌሎችም ዛፎች ይታያሉ ።

በጉብታው አካባቢ ጡቦች ፣ የተሰባበሩ ድንጋዮች ፣ በጣም ትናንሽ ወጣ ገባዎችና ረግረግ ሜዳዎች እንዳሉ ሆስነር አስተውሎአል ። በከተማው ክልል ዙሪያ በተገነቡት የአጥር ግድግዳዎች አልፈው አልፈው ከፍ እየተደረጉ ለመመልከቻ ወይም ለመጠበቂያ ተሠርተው የነበሩ ግዙፍ የግንብ ማማዎች አሉ ።

ነፋስ ፣ ውሃ ፣ አሸዋና ገበሬዎች ለብዙ ሺህ ዓመታት የአደረጉት ቁፈራ ተዳምረው በአንድ ወቅት በዓለም ላይ ተደናቂ ከነበሩት ከተሞች አንድዋ የነበረችውን ከተማ ታሪኳን ወደኋላ ለማየት በሚያስቸግር ሁኔታ ላይ በማድረስ አጥፍተዋታል ። ይህ ድርጊት እንግዳና የዓለምን መጥፎ ገጽታ የሚያሳይ ነበር—የበለጸገች ባቢሎን — በብሉይና በአዲስ ኪዳን ባቢሎን የሰው ልጅ ኩራት ፣ የምግባረ ቢስነትና የሐጢአት ምልክት ነበረች ። ለዘመናዊ አይሁዳውያንና ክርስቲያኖች ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተነገረው ትንቢት መፈጸሙን የሚያሳይ ምልክት ነው ።

ሪሽ እዚህ ለምን አመጣቸው ? የባቢሎን ምርኮኛ ? ሆስነር ይህ መሆን አለበት ብሎ ገመተ ። ወይስ እንዲያው በአጋጣሚ ? ምናልባ

ትም እርሱ ለሚፈልገው ተስማሚ ቦታ ስለሆነ ይሆናል — በፍልስ ጥኤማውያን ሠፈር አጠገብ ። ነገር ግን የእነእርሱ ሠፈር ከዚያ በረሃ ውን አቋርጦ 100 ኪሎ ሜትር ይርቃል ። እንግዳውማ የባቢሎን ምር ኮኛ ለማድረግ ነው ። በዓለም ቤተ መጻሐፍት ውስጥ በሚገኙ ትላልቅ መጽሐፎች ውስጥ ስለ ባቢሎን ሥልጣኔና ውድቀት ተጽፎአል ። ወደ ፊት እነዚህ መጽሐፎች እንደገና ሲጻፉ በግርጌአቸው ኮንኮርዱ በዚያ በወደቀ ጊዜ ስለአስከተለው ሁኔታ የሚገልጽ እንደሚጻፍ ሆስነር አል ተጠራጠረም ። ሲጋራውን አርመጥምጦ አጥፍቶ ቁራጩን እንደያዘ “ እነዚያውና መጡ ” አለ ዝቅ ባለ ድምጽ ።

* * *

ታቹን በመንገዱ በኩል ከአለው አቅጣጫ አምስት ሰዎች ወደ ተራራው ጥግ እየመጡ ነበር ። ከፊት የነበረው ሰው ነጭ ጨርቅ በረጅም ዘንግ ላይ አስሮ ይዞአል ። ብሪንና ሀበር ከሄዱበት ተመልሰው በሩጫ መጡ ። ብሪን በጠመንጃው መነጽር እየተቃረቡ ሲመጡ ተመ ለከታቸው ። “ ሪሽ አብሮአቸው የመጣ አይመስለኝም ” ብሎ ጠመ ንጃውን ለሆስነር ስለሰጠው ተንበርክኮ በመነጽሩ ተመለከተ ። ሆስ ነር ማየቱን አቁሞ ራሱን በአሉታ በመነቅነቅ “ እርሱ እኛን አያምነ ንም ። ለነጭ ባንዲራ ክብር አይሰጡም ብሎ ያስባል ። ይህ አስተሳሰብ ደግሞ በጣም ያስቆጣኛል ፣ ጄኔራል ” አለው ።

ዶብኪን በአዎንታ ራሱን አነቃንቆ “ በበኩሉ እምነት እንደሚ ጐድለው ያሳያል ” ብሎ ለትንሽ ጊዜ ከአሰበ በኋላ “ በእውነት ከእኛ ጋር ላይግባባ ይችላል — ይህ ደግሞ ያስፈራኛል ” አለው ።

ሆስነር ተነስቶ ወደ ብሪንና ሀበር በመዞር “ ሁሉም እንዲጠነ ቀቁ ንገሩ ፣ እያንዳንዱ ከእይታ እንዲሰወር እፈልጋለሁ ። አንድም ሰው ከክልሉ መነቃነቅ የለበትም ፣ ናታን ። ማንም ሰው ለመሄድ ቢሞክር አቁመው ” ከአለው በኋላ ልብሱን አራግፎ “ ጄኔራል ፣ አብረኸኝ ትሄዳለህ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ ያለ ጥርጥር ” ብሎ በመቆም ልብሱን አስተካከለ ። ቀጥሎም “ አየህ ነገሩ የተገላቢጦሽ ነው ። እኛ በኒውዮርክ ውስጥ ለማድረግ የምንፈልገውን እነእርሱ በአሁኑ ወቅት እዚህ መነጋገር ይፈልጋሉ ማለት ነው ። በበኩሌ ስለዚህ ጉዳይ ለመነጋገር እርግጠኛ አይደለ ሁም ” አለው ዶብኪን ።

ሆስነር ከጉብታው ላይ ወረድ ብሎ “ ምን ማለትህ እንደሆነ ገብ ቶኛል ። አሥራ ሁለት አዋቂ ተደራዳሪዎች ሳይመጡብን እንሂድ ” ብሎ ወደታች መውረድ ጀመረ ። ዶብኪንም ተከተለው ።

አረቦቹ ወደ ጉድጓዳው ስለገቡ ለጊዜው ከእይታ ተሰወሩ ። ከአ ቀበቱ በታች 100 ሜትር እርቀት ላይ ሰቅለው የያዙት ነጭ ጨርቅ ብቅ አለ ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ አረቦቹንም እንደገና አዩአቸው ። መጣ ሪያ የታጠቁ ከመሆናቸውም በላይ ፍጥነታቸውን ወደፊት ጨመሩ ። ለጊዜው ሆስነር ግራ ስለተጋባ ነጭ መሃረብ እያውለበለበ በአረብኛ ጮሆ ተናገረ ። አረቦቹ ያለበትን ቦታ በማየት መልስ ሰጡት ። ሁለ ቱም ወገኖች ቀስ ብለው ተቀራረቡ ። አረቦቹ በአንድ እንደመደብ በሆነ ረባዳ ቦታ ላይ ቆሙ ።

ሆስነር ፈጠን ብሎ ወደ እነእርሱ በመራመድ በአረቦቹ ሥርዓት መሠረት እንደሚደረገው መሪያቸውን ተጠግቶ በመቆም “ ሪሽ የትነው ? የምነጋገረው ከእርሱ ጋር ብቻ ነው ” አላቸው ።

ሰውየው ለረጅም ጊዜ ትኩር አድርጐ ተመለከተው ። ጥቁር ዓይ ኖቹ በጥላቻና በንቀት የሚንበለበሉ መሰሉ ። ለዚህ ጉዳይ መምጣቱን እንዳልወደደው በግልጽ ማወቅ ይቻል ነበር ። ለስለስና ረጋ ባለ አነጋ ገር “ እኔ ሳሌም ሀማዲ የአህመድ ሪሽ የመቶ አለቃ ነኝ ። እጃችሁን አሁኑኑ እንድትሰጡ ከበሬታ የመላበት መልዕክቱን ይዘን መጥተናል” አለው ።

ሆስነር ሰውየውን በአንክሮ ተመለከተው ። ሀማዲ እንደ ሪሽ ተማርኮ እንደማያውቅና ስለ እርሱም የሚጠቁም ፎቶግራፍ ወይም የሚያስታውሰው ነገር አልነበረም ። ሰውየው የቲም የነበረና በኋላም የልዩ ልዩ የፍልስጥኤማውያን ነጻ አውጭ ድርጅቶች የአሸባል ፕሮ ግራም ሐላፊ እንደነበረ አውቋል ። ለጥቅም ? ለግብረ ገብነት ? ለክ ብር ? የየትኛው እንደሆነ ለይቶ ለመናገር አስቸጋሪ ነው ። ከሆስነር አንድ ሜትር እርቆ የቆመው ሰው አጭር ቢሆንም የተደላደለ መጠን ነበረው ። የፍየል ጢም ዓይነት ነበረው ። ንጽሕናውም ሆስነር በራ ምላ ወህኒ ቤት ውስጥ ከአያቸው ሽብር ፈጣሪዎች በጣም የተሻለ ነበር። ሆስነር በጣም ተጠግቶ “ ያለው የት ነው ? ከእርሱ ጋር መነጋገር እፈ ልጋለሁ ” አለው ።

ሀማዲ ቀስ አድርጐ ራሱን በአዎንታ ከነቀነቀ በኋላ “ አንተ ያዕ ቆብ ሆስነር ነህ ?’ ’ ብሎ ጠየቀው ።

“ ነኝ ። ”

“ ተከትለኸኝ ትሔዳለህ ? ”

“ ምናልባት ። ”

ሀማዲ ከአቅማማ በኋላ “ ምንም ዓይነት ችግር እንደማያጋጥ ምህ አረጋግጥልሃለሁ ” አለው ።

“ እርግጠኛ ነህ ? ”

ሀማዲ እያለቀ የመጣውን ትዕግሥቱን ለመሸሸግ ከንፈሩን እየ ነካከሰ “ ቃሌ ነው ” ከአለው በኋላ “ እመነኝ ። በዚህ ጉዳይ ላይ በፈ ለከው ዓይነት መነጋገር እንችላለን ” ብሎት በድንገት ፈገግ አለ ። “ ይህ ያዕቆብ ሆስነርን ለመግደል የተጠነሰሰ ወጥመድ አይደለም ። ይህን በዚሁ ቦታ አሁኑኑ ማድረግ እንችላለን ። ከዚህም ሌላ አንተ ይህን ያህል ተፈላጊ አይደለህም ” አለው ።

“ ሪሽ ግን እኔን እንደሚፈልግና እንደ አረፍንም እንደሚገድለኝ ተናግሮአል ። ”

“ ሳሌም ሀማዲ ወደ ሰማይ ተመልክቶ “ ያን ,ቃለ መሃላ ሽሯል ” አለው ።

ሆስነር ወደ ዶብኪን ዞሮ “ ጄኔራል ? ” አለው ።

ዶብኪን ትኩር አድርጐ ሀማዲን ተመለከተው ። መደራደር አል ፈለገም ። ግን ሪሽ ያለበትን ቦታ ለማየት ፈልጓል ። ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ ሊሆን ይችላል ” አለው ።

ሆስነር በመነጽሩ ይከታተል ወደ ነበረው ብሪን ዞሮ እጁን ስለአ ውለበለበ ብሪን ያየው መሆኑን ገለጸለት ። ለመከላከያ ከተሠሩት ቦታ ዎች አካባቢ የሰዎች ራሶች ብቅ ብለው ይመለከቱ እንደነበረ ሆስነር አየ ። አፈር ከተቋጠረባቸው ሻንጣዎች ጥቂቶቹ የሚያብረቀርቅ ቀለም እንደአላቸው ስለአየ ቀለማቸውን የሚያጠፋ አቧራ መልበስ እንደሚ ኖርባቸው አመነ ። ወደ ሀማዲ ዞሮ ሲመለከት ሀማዲ ከብሪን ጠመ ንጃ መነጽር ብልጭታ ስለአየ የነበረበትን ቦታ ለማስታወስ ሳይሞክር አልቀረም ። የሀማዲን እይታ ለማደናቀፍ ሆስነር በአጠገቡ ሲያልፍ ሆን ብሎ ገፋ ከአደረገው በኋላ “ መልካም ፡ ብዙ የምሠራቸው ነገ ሮች ስለአሉኝ እንሒድ ” አለው ።

ይህ ትንሽ ቡድን ለልዩ ልዩ ትርዕይቶች ማሳያ በተሠራው በግ ሪኮች ግንብ መጨረሻ ላይ ሲደርስ ወደ ምዕራብ በመዞር የኤፍራጥ ስን ወንዝ አቅጣጫ ተከትሎ በፍየሎች መንገድ ሔደ ። ሰዎቹ በሚያ ልፉበት ጊዜ በለስላሳው ነፋስ ምክንያት የተምር ዛፍ ቅጠሎች ተንኮ ሻኮሹ። ሙቀቱ እየጨመረ በመምጣቱ ሆስነር በተራራው ላይ ለአሉት ሰዎቹ የሚጠጣ ውሃ ያለው ለ24 ሰዓት እንኳን የማይበቃ መሆኑን አስ ታወሰ ። ምግባቸው ምናልባት ለ48 ሰዓት በቂ ሊሆን ይችላል ። በኮን ኮርዱ ላይ የነበረው አሉሚኒየም እንደ ዋድያት ተሠርቶ የዝናብ ውሃ ለማጠራቀም ተዘጋጅቷል ። ይሁን እንጂ በቂ ደመና ስለሌለ ዝናብ የሚጥል አይመስልም ።

ያለምንም ንግግር ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። በሚሔዱበት ጊዜ ዶብ ኪን መንገዱን በሚገባና ልብ አድርጐ እያጠና ነበር ። በአንድ ትንሽ ተረተር ላይ ሲደርሱ ቆሙ ። ሆስነር በሰሜን በኩል 1.5 ኪሎ ሜትር ያህል እርቀት ላይ ያለውን ኮንኮርዱ ያረፈበትን ተራራ ተመለከተ ። የኮንኮርዱ የላይ አካል አሁን ከአሉበት በመጠኑ ይታያል ። ተራራው— ወይም የተቀበረው ምሽግ — ከዚህ በኩል ገፍቶ ለመግባት የማይቻል በመሆኑ ምክንያት አሽባሉቹ ለመደራደር እንደፈለጉ ተገነዘበ ።

በምዕራብ በኩል የኤፍራጥስ ወንዝ ከፍየሎቹ መንገድ ወደታች 500 ሜትር እርቀት ላይ አለ ። በወንዙ ዳር ያሉት የክዌሪሽ አሮጌ መንደሮችን ሆስነር በግልጽ ሊያያቸው ቻለ ። ጐጆዎቹ የተሠሩት ከጭቃ ሲሆን ቀለም ያልተቀቡና ያላጌጡ ነበሩ ። ፊታቸውን በስስ ጨርቅ የሸፈኑ ሴቶች፥ ያገለደሙና በራሳቸው ላይ ጨርቅ የጠመጠሙ ወንዶች አዩ ። ፍየሎች ያረባሉ ። ኑሮአቸውና አኳኋናቸው ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ቅድመ አያቶቻቸው እንደሚያደርጉት ዓይነት ነበር ። ሆስነር ከአየው ሁኔታ እንደገመተው ከሆነ ለአለፉት 4 እና 5 ሺህ ዓመታት ይደረግ ከነበረው የተለየ አልነበረም ። ሕዝቡ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ በመሆኑ በልዩ ልዩ ነገሮች አያመልክም — እንደ ቀድሞ የባቢሎን ሰዎች —

የፍየል መንገዱን ትተው በአንድ ትልቅ ጉብታ ላይ ደረሱ ። ከዚያም ደረጃ በተሠራበት አቀበት ወደ ላይ ከወጡ በኋላ በመጨረሻ በሁለት ጉብታዎች መካከል ባለ ሜዳ ላይ ደረሱ ። በዚያም የባቢሎን አንበሳ ስዕል የተቀመጠበት ድንጋይ አዩ ። ዕድሜውንና ለምን እንደተሠራ የሚያሳይ ነገር አልነበረም ። ሀማዲ “ ሰውነታችሁን በርብረን ዐይኖቻችሁን በጨርቅ እናስራለን ? ” አላቸው ።

ሆስነር “ አይሆንም ” አለው ።

ሀማዲ ወደ ዶብኪን ዞሮ “ አንድ ጠላት ወደ ጦር ሠፈር ተይዞ ሲመጣ እንዳያይ ማድረግ በዓለም ውስጥ የወታደር ሕግ ነው ። ይህን ታውቃለህ ፡ ማዋረድ ወይም መናቅ አይደለም ” አለው ።

ዶብኪን መስማማት ነበረበት ።

ሆስነርም ተስማማ ።

ልብሳቸውን አስወልቀው አንድ በአንድ ከመረመሩ በኋላ እንደገና አልብሰውና ዓይኖቻቸውን በጨርቅ ሸብበው የቀረውን ደረጃ ይዘዋቸው ወጡ ። መሬቱ የተስተካከለና ምናልባትም በጡብ የተለጠፈ ይመስል ነበር ። ቀጥለውም ጥቂት ደረጃዎች እንዲወርዱ ከተደ

ረጉ በኋላ በድንገት ቅዝቃዜ ተሰማቸው ። ወደዚያው ዓይኖቻቸው የታ ሠሩባቸው ጨርቆች ተነሱላቸው ። ሆስነር በጨለማው ክፍል ውስጥ ደህና አድርጐ ማየት ባይችልም ሰዎች በሹክሹክታ ሲያወሩ ድምጻቸ ውን ሰማ ።

ከጥላው ሥር " አህመድ ሬሽ ነኝ " የሚል ድምጽ በእብራይስጥ ቋንቋ ተሰማ ። " ይህ ያዕቀብ ሆስነርን እንደገና ለማየት የቻልኩበት ቀን ሲሆን ዝነኛው ጄኔራል ዶብኪንን በመገናኘቴ ክብር ይሰማኛል ።"

ሆስነርና ዶብኪን ምንም መልስ አልሰጡም ። በዚያ ግድግዳ ጥላ ሥር አካባቢ ሌሎች ሰዎች እንደነበሩ ገብቶአቸዋል ። የፈረሰው አዳራሽ ጣሪያ ባይኖረውም በቂ የፀሐይ ብርሃን አይገባበትም ። ዐይ ኖቻቸው ጨለማውን እየተለማመዱት ስለመጡ አካባቢያቸውን ተመ ለከቱ ።

ሬሽ እንደገና " ተቆፍሮ በተገኘው በደቡብ ቤተ መንግሥት ፍር ስራሽ ውስጥ እንገኛለን ። የናቡከደነጾር አንጋፋ ልጅ የነበረው ቤል ሽጻር በዚህ በዘውድ ክፍል ውስጥ ባለ በተለሰነ ግድግዳ ላይ የተጻፈ ውን አስቃቂ ጽሑፍ ያየበት ነው ። በእርግጥ ታሪኩን ከነቢዩ ዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ ታገኛላችሁ " አላቸው ።

ዝምታ ሆነ ።

አሁንም ሬሽ በጨለማው ውስጥ ሆኖ " በዚህ በፈረሰ አዳራሽ ውስጥ ለዘውድ ማስቀመጫ እንዲሆን ወደ ግድግዳው ገባ ብሎ በተሠ ራው ሥፍራ ላይ ቆሜአለሁ ። ወደ ጨለማው አተኩራችሁ ብትመለ ከቱ ናቡከደነጾር ኢየሩሳሌምን በአጠፋበት ጊዜ የተወሰዱትን የወር ቅና የብር ሳህኖች ፣ ብልጭ ድርግም የሚል የሻማ መብራት ፣ የባቢ ሎንን ውድቀት የጻፈው ጣረሞት ያረፈበትን እጅ በዓይነ ሕሊናችሁ ማየት ትችላላችሁ " ከአላቸው በኋላ ንግግሩን ለማጠንከር ለትንሽ ጊዜ ቆም ከአደረገ በኋላ " ይህ በይሁዶች ተወዳጅ ከሆኑት ታሪኮች አንዱ ነው ። እኔም ልዩ አስተያየት አድርጌ እዚህ ያመጣኋችሁ ለዚህ ነው " አላቸው ።

ሆስነርና ዶብኪን አሁንም መልስ አልሰጡም ።

ሬሽ ንግግሩን በመቀጠል " በዚያ ክፍት የሆነ ትልቅ ምድጃ ነበር። ናቡከደነጾር ወደዚያ ወደሚነዳው የእሳት ነበልባል ውስጥ ሲድራ ቅን ፣ ሚሳቅንና አብደናጐንን እንዲጥሏቸው አዘዘ ። እነእርሱ በእግ ዚአብሔር ተአምር ተረፉ ። ሆኖም ይሁዶች በዚያ ዓይነት ተአምር ሁልጊዜ አልዳኑም " ብሎአቸው ንግግሩን ለትንሽ ጊዜ ቆም ሲያደርግ

የጨለማው ክፍል በሰዎች ድምጽ ተሞላ ። ሪሽ ቀስ ብሎ በረጋ አነጋ ገር "ባቢሎን ለይሁዶች መጠን የሌለው የሐዘን ቦታ ነው ። እንደዚ ሁም ተአምር የሚታይበት ቦታ ነው ። በአሁኑ ጊዜ የትኛው ይሆን የሚሆነው ፤ ሆስነር ? " ብሎ ጠየቀው ።

ሆስነር ሲጋራውን አቀጣጥሎ "ግሩም የሆንክ አንደበት ርቱዕ ነህ ፣ አህመድ ሪሽ ። በአጭሩ የምትፈልገው ምንድን ነው ? " ብሎ ጠየቀው ።

"ያን ትልቅ አውሮፕላን በዚያ ተራራ ላይ ማሳረፋችሁ ጀብደ ኝነት ነው ። ሰዎቹ በሙሉ ሊያልቁ ይችሉ ነበር ። "

"ምን ማለትህ ነው ? "

"ውሀ ወይም ምግብ ትፈልጉ እንደሆን ሳልጠይቃችሁ ችላ በማ ለቴ ይቅርታ አድርጉልኝ ። "

ዶብኪን "የጠየቅኸን ሁሉ በብዛት አሉን ፣ ሪሽ " ብሎ መለሰ ለት ።

ሪሽ ስቆ "አይመስለኝም " አለው ።

ሆስነር ጮኾ "ወደ ነጥቡ ናና የምትፈልገው ምንድን ነው ? " ብሎ በድጋሚ ጠየቀው ።

የሪሽ ድምጽ ከቀድሞው ጠንከር አለ ። "ከመንግሥታችሁ ጋር እስክንደራደር ድረስ እናንተ ሁላችሁም በእግት እንድትቆዩ እፈልጋ ለሁ ። ተጨማሪ የደም መፋሰስ እንዲኖር አልሻም " ብሎ ነገራቸው ።

የሆስነር ዐይኖች አሁን ብርሃኑን እየተለማመዱ መጥተዋል ። ሪሽ ከግድግዳው ገባ ብሎ በተሠራው ስፍራ ቆሞአል ። ነጭ ጨርቅ አገልድሞአል ። ነጠላ ጫማ ተጫምቷል ። ሆስነር በራምላ ከአየው የተለየ አልሆነም ። ከአረቦቹ ጋር ሲነጻጸር የተለየ ረጅም ነው ። ሪሽ የሰርካሲያን ወይም የፕሩፕያ ደም እንዳለበት ሆስነር አስታወሰ ። "ት ናንትና ማታ ማግኘት ከሚገባህ ትንሽ አግኝተሃል ። ከሰዎችህ 30 ያህሉ የሞትና የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል ብየ እገምታለሁ " አለው።

"አሁን እዚህ ያለሁት ስለአለፈው ሪፖርት ለመስማት አይደለም። ለምንና ስለምን እንዳደረግን፡ስለአላማችን ወይም ያንን ስለመሳሰሉት የፖለቲካ ንግግር ከአንተ ጋር አልከፍትም ። እነዚህን ጉዳዮች ከመን ግሥትህ ጋር እነጋገርባቸዋለሁ ። ለአንተ አንድ ዋስትናና የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እሰጥሃለሁ ። ዋስትናው እጃችሁን በሰላም ከሰጣችሁ አንድም እስራኤላዊ አይገደልም ። የመጨረሻው ማስጠንቀቂያዬ ደግ

ም እጅ የምትሰጡት ፀሐይ ከመጥለቅዋ በፊት መሆን አለበት።በዚ ህ ትስማማለህ ? ”

ሆስነር “ የምታቀርበውን ጥያቄ መንግሥቴ ባይቀበለው ምን ታደርጋለህ ? ለእኛ መያዣዎችህ ወይም ምርኮኞችህ ለሆነው ደህን ነት እንዴት ዓይነት ዋስትና መስጠት ትችላለህ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ ሃሳቤን መንግሥትህ ባይቀበለው እናንተን እለቃችኋለሁ ።

በእርግጥ ይህን የምናውቀው እናንተና እኔ ነን ። ለማንኛውም ቃል እገ ባላችኋለሁ ። ”

ሆስነርና ዶብኪን ቀስ ብለው ተመካከሩ ።

“ እንደሚመስለኝ ዓላማህን አውቄዋለሁ ፣ ሪሽ ። የመጀመሪያው ዓላማህ የሰላም ውይይቱ እንዳይካሄድ አንድ እንከን ለመፍጠር ነው ። ሃሳብህ ተሚልቶልህ ይሆናል፤ላይሟላልህም ይችል ይሆናል ። ሁለተ ኛው ዓላማህ ከፍተኛ የእስራኤል ባለሥልጣኖች የተሳፈሩባቸውን ሁለት አውሮፕላኖች አስገድደህ በመያዝ ስለፖለቲካና ስለወታደራዊ ይዞታ ለመጠየቅ ነው ። ይህ ጉዳይ ግን በግልጽ በውይይት መድረኩ ላይ ቢደረግ የበለጠ ውጤታማ ይሆን ነበር ። አይሆንም ነበር ? የመ ጨረሻው ዓላማህ አንዳንድ ግልጽ ላልሆኑ ጥያቄዎች እኛን መያዣ ለማድረግ ነበር ። እነዚህ ጥያቄዎችህ ተቀባይነት ባያገኙ እኛን ለመ ልቀቅ ፈቃደኛ መሆንክን መንገር የነበረብህ ምሥጢሩ በመካከላችን የተጠበቀ መሆን አለበት ብለህ ከመናገርህ በፊት ነበር ። ልክ ነኝ ? ማን ኛችንም ብንሆን እንድንጠየቅ ወይም ምንም ዓይነት ተጽዕኖ እንዳይ ደረግብን ቃል ትገባልናለህ ? ” ብሎ ሆስነር ጠየቀው ።

ሆስነር ንግግሩን በመቀጠል “ ስለእስራኤላውያን አረቦችስ እን ዴት ነው ? በሰጠኸኝ ዋስትና ውስጥ እነእርሱ የተጨመሩ አይመስለ ኝም ” አለው ።

አሁንም ሪሽ መልስ አልሰጠውም ። ነገር ግን ሆስነር ግልጽ ባል ሆነው ብርሃን ውስጥ ሲመለከተው በፊቱ ላይ አንድ ጉልህ የሆነ ለውጥ አየ ። ሪሽ አይሁዶችን ሁልጊዜም ጠላት አድርጎ ቆጥሮአቸዋል ። ነገር ግን አይሁዶች አማኞች ስለአልነበሩ በአረብና በእስላምና አስተሳ ሰብ መሠረት ለአብዛኛው ጥፋታቸው የመጨረሻው ቅጣት አይፈጸም ባቸውም ። ይሁን እንጂ አንድ እስላም በተለይም አረብ ከሆነ በሃይማ ኖቱም ሆነ በሕዝቡ ላይ ለአደረሰው ጥፋት ወይም የሕግ መተላለፍ ምሕረት አይሰጠውም ። ጀባሪና አሪፍ በሪሽ በኩል የሞቱ ሰዎች ነበ ሩ ። ይህን አስተሳሰብ ሆስነርም አውቋል ።

“ እያስቆጣኸኝ ነው ሆስነር ፤ የአንበሶቹ ጉድጓድ አንበሶቹ እን ዲቆጡ የሚነካካበት ቦታ አይደለም ። ከሩቅ ቦታ አድርገው ሆስነር” አለው ሪሽ ።

ሆስነር ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ ሪሽን ትኩር አድርጐ ተመለከ ተው ። ከጦሩ ሜዳ ተሸክሞ ስለአመጣት ሴት ሪሽን ሊጠይቀው በጣም ፈለገ ። ተሸክሟት የነበረው ሰው እርግጥ ሪሽ ነበር ። ከሆነስ ሴትዮዋ ማን ነበረች ? ሞታ ይሆን ? ይህን ጥያቄ ማንሳቱ ግን ሪሽ መኖ ሩን በመጠራጠር ላይ የሆነውን በኮከብ ብርሃን የሚሠራውን መነጽር መኖር ማረጋገጥ ይሆናል ። ወይም ያን የመሰለ ጥያቄ በዚያ ሰዓት ማን ሳቱ ሪሽን ራሱን መቆጣጠር ወደሚያቅተው ብስጭትና ቁጣ መገፋ ፋት ይሆናል ። ሪሽ አሁን ትዕግሥተኛ ይመስላል ። ነገር ግን ተለዋ ዋጭ ባሕሪ ያለው ሰው ለመሆኑ በራምላ ወህኒ ቤት ውስጥ በነበረበት ጊዜ የአእምሮ ጠበብቶች አረጋግጠዋል ። ሌሎች የአእምሮ—በሽተ ኞች የሆኑ ገዳዮች እንደሚያደርጉት ሪሽም ሊያደርግ ይችላል ። የማ ባበልና የመሳብ ጠባይ በሚያሳይበት ጊዜ ለሁኔታው በመማረክ በሚ ደረገው ንግግር አንድ ስህተት ቢፈጠር ያለማወላወል የሰውን ጉሮሮ ያርዳል ።

“በእኛ ላይ ሀይለኛ ጥላቻ የሌለህ መሆንህንና ሁላችንንም እንደ ማትገድለን እንዴት አውቃለሁ ? አንተ . . . ዕብድ አለመሆንህን እን ዴት አረጋግጣለሁ ? ”

ዶብኪን በዝቅተኛ ድምጽ “ ስለእግዚአብሔር ብለህ ሆስነር ? ” ብሎ ክንዱን አፈፍ አደረገው ።

ሪሽ እነእርሱን ለመግደል የገፋፋውን የግንፍልታ ስሜት እስኪ ቆጣጠር ድረስ ጸጥታ የሰፈነ መሆኑን ሆስነር ገብቶታል ። እነእርሱን መግደል ሌሎች እጃቸውን እንዲሰጡ የሚደረገውን ዕድል ማከተሚያ እንደሚሆን ሆስነር እንደሚያውቅ ሁሉ ሪሽም ያውቃል ።

ሪሽ የገነፈለበትን ስሜት ተናንቆ በማመቅ ጉርና ባለ ድምጽ “የሰ ጠሁህን ዋስትናና ማስጠንቀቂያ ብቻ ነው ደግሜ የምነግርህ ። እስከ ጀንበር መጥለቂያ ድረስ ጊዜ አለህ ። ከዚያ ለአንድ ደቂቃ እንኳን ሊራ ዘም አይችልም ። ሁለታችንም እንደምናውቀው ከጀንበር ጥልቀት በኋላ ራዲዮ መቀበያው የተሻለ ይሆናል። ስለዚህ ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ እንዲራዘም እንዳትጠይቅ ። ” ሪሽ ገባ ብሎ ከተሠራው እንደመው ጣት ብሎ “ ሁለታችንም እንደምናውቀው የኢራቅ ባለሥልጣኖች በዚህ ያለውን የእኛን ትንሽ ችግር ለማወቅ ብዙ ጊዜ አይፈጅባቸውም። ነገር ግን እዚህ መኖራችንን ከአወቁ በኋላ ከ24 ሰዓት በፊት እርምጃ

ይወስዳሉ ብለህ እንዳትጓጓ።ነመንቀሳቀሳቸው በፊት በጉዳዩ ላይ እንደ ሚወያዩ አረጋግጥልሃለሁ ። ከባለሥልጣኖቹ ውስጥ ወዳጆች ስለይ ሉኝ የሚወሰደውን እርምጃ እንደሚያዘገዩትና ውሳኔዎቹን ሁሉ አስ ቀድመው ይነግሩኛል ። የኢራቅ ወታደር ቢንቀሳቀስም ዝግመቱ የሚ ያቅለሸልሽ ነው ፡ ሆስነር ። ይህም ሆኖ እኔ በምፈልገው ዓይነት ይፈጸ ማል ። ስለዚህ አሁንም ደግሜ የምነግርህ ጀንበር ከመጥለቋ በፊት ባትነግረን እንወጋችኋለን ” አለው ።

ሆስነርና ዶብኪን መልስ አልሰጡም ።

ሪሽ የሰላም ምልክት የሚያሳይ የእጅ ማንሳት እያሳየ “ ድል የመ መታት ውጤቶች ምን እንደሚሆኑ አስብበት ፡ ሰዎቼ በሙሉ አሽባ ሎች ናቸው ። ይህንንም ከማረከው ሰው ታውቀዋለህ ” አለው ።

አሁንም መልስ አልነበረውም ።

ሪሽ ንግግሩን በመቀጠል “ በተፋፋመ ጦርነት ውስጥ ለሚደር ሰው ጉዳት ኃላፊ መሆን አልችልም ። የእኔ ሰዎች ማምሻቸውን ተራ ራውን በቁጥጥራቸው ስር ከአዋሉ የአገኙትን ሁሉ እንደ እብድ ሆነው ይገድላሉ ። ትናንትና ብዙ ጓዶቻቸው ስለሞቱባቸው መበቀል ይፈል ጋሉ ። ስለቤቶቻችሁ ማሰብ አለባችሁ . . . የተናገርኩት ይገባችኋ ል ? ” አላቸው ።

ሆስነር አረቦች ከሚጠሉትና መጥፎ ነው ብለው ከሚያስቡት የመቃወሚያ ቃል በአረብኛ ተናገረ ። በግድግዳው አካባቢ ከሚሰ ማው ማጉረምረም በስተቀር ሌላ ነገር አልነበረም ።

በዚህ ጊዜ ሪሽ ከጨለማው ውስጥ ትንሽ ወጣ በማለት ፈገግታ እያሳየ “ በእኔ ቋንቋ መርጠህ የተናገርከው አስገራሚ ነው ። ለመሆኑ የተማርከው የት ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ እጅግ በጣም የልብ ወዳጆቼ የሆኑ ጥቂት አረቦች አሉ ። ”

“ እውነትህን ነው ? ” ብሎ ሪሽ ከነበረበት ወጥቶ ከዘውድ ክፍሉ መካከል ሁለት ሜትር ያህል ከሆስነርና ከዶብኪን እርቆ ቆመ ። “አንድ ወቅት የአንተ እስረኛ ነበርኩ ። አሁን ደግሞ አንተ የእኔ ለመሆን ተቃ ርበሃል ። በራምላ በነበርኩበት ጊዜ ይቅርታ ወይም ተጨማሪ ጥቅም በሚፈልጉ ወገኖች በሆኑ አረቦች ልገደል እችል ነበር ። እንደተደረ ገም አውቃለሁ ። ግን አንተ እንዲሠራ እንደፈለግኸው አላደረግኸ ውም ። ትክክለኛ የመሆን ስሜት ነበረህ ። እኔን በጥፊ መትተህ ስለ አዋረድከኝ ልገድልህ ምያለሁ ። ግን ሕይወቴን አትርፈሃል ። ስለዚህ እጅህን አሁኑኑ ከሰጠህ ጉዳት ላደርስብህ አልችልም ።”ሆስነርን ትኩር

አድርጐ ከተመለከተው በኋላ ተራምዶ አንድ ሜትር እርቀት ላይ ቆሞ “ በጥሬ የመታኸኝ እስከ አሁን እንደሚያቃጥለኝ ታውቃለህ ፣ አታውቅም ? ” ብሎ ተንጠራርቶ ሆስነርን አፉቱ ላይ በጥፊ አቀመ ሰው ።

ሆስነር ወደ ኋላው ለአንድ ሴኮንድ ያህል ተለጠጠ ። ቀጥሎም ወደ ሪሽ ጠጋ ሲል ዶብኪን ጨምድዶ ያዘው ።

ሪሽ ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ አሁን ሁሉም ነገር አልፏል ። የስድቡም ትዝታ ተሰርዟል—ዐይን ያወጣ ዐይኑ ይውጣ ፣ ጥርስ የሰ በረ ጥርሱ ይሰበር— ከዚህ የበለጠ የለም ፡ ከዚህም ያነሰ የለም ” አላ ቸው ።

ሆስነር ራሱን አደላድሎ ዶብኪን እንዲለቀው አደረገ ።

“ እሺ እስማማለሁ ፡ ሪሽ ። ግን አሁንም 50 ሰዎች ያሳፈረውን አውሮፕላን ማቃጠል ድፍረት ነው ። ”

ሪሽ ወደ ሌላ ቦታ እየተመለከተ “ ስለዚያ አልወያይም ። የቀሩ ትን 50 ሰዎች ለማደን ዕድልአለህ ” ከአለው በኋላ ወደ ዶብኪን እየ ተመለከተ “ በወታደር ኃይል በኩል የሚደረገው መፍጨርጨር ተስፋ የለውም ” አለው ።

ዶብኪን ወደ ሪሽ ተጠጋ ። በጨለማው ውስጥ የሚንቀሳቀስ ድምጽ ሰማ ። ሪሽ በሚገባ የማይታይ የእጅ መንቀሳቀስ ቢያደርግ ዶብኪን በጣም ተጠጋው ። “ ትናንትና ማታ ከወታደር አቋም ሲታይ በእርግጥ ተስፋ አልነበረም ። ይሁን እንጂ አሸነፍናችሁ ። ዛሬ ማታ ደግሞ ሁሉም ስለሚስተካከል የተሻለ ይሆናል ። ”

ሪሽ ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ ዛሬ ማታ ተራራውን በቁጥጥራ ችን ሥር እናውለዋለን ፡ ጄኔራል ” አለው ።

ሆስነር እጁን በዶብኪን ትከሻ ላይ አስቀመጠ “ በቂ ውይይት አድርጌአለሁ ፣ አሁን መመለስ እፈልጋለሁ ” አለው ።

“ እያንዳንዱ ምርጫ እንዲያደርግ የዲሞክራሲ መብቱን እንደ ማትነፍገው ተስፋ አለኝ ፣ ሆስነር ” አለው ሪሽ ።

“ አዎን ፣ በዚያ ተራራ ላይ ሁሉን የምናደርገው በምርጫ ነው ፣ ሪሽ ። ጀምበር ከመጥለቋ በፊት አስታውቅሃለሁ ። እስከዚያው ድረስ ያሰርነውን ሰው እልክልሃለሁ ። ህክምናም ያስፈልገዋል ። በቂ የሕክ ምና አገልግሎት ትሰጣለህ ? ” አለው ።

ሪሽ ከት ብሎ ከሳቀ በኋላ “ ይህ እኛ ያለንን የሕክምና ዕቃ ለማ ወቅ የተደረገ ፌሊጥ ነው ። ለማንኛውም ነገር ሰውየውን እንቀበላ ለን ። ለዚህም አመሰግናለሁ ” አለው ። እንደገና በእርጋታ አንድ በአንድ በየተራ ተመለከታቸው ። “ የእኔ ሰዎች ማታ ተራራውን በቁ ጥጥራቸው ሥር ያደረጉ እንደሆነ ልቆጣጠራቸው እንደማልችል በድ ጋሚ ላስጠነቅቃችሁ እወዳለሁ ። ”

“ አንተ መጥፎ አዛዥ ወይም መጥፎ ውሸታም ነህ ” አለው ዶብኪን ።

ሪሽ ወደ ነበረበት ዞሮ እየሄደ “ እኔ ሐቀኛና ጨዋ ሰውነኝ ። አንተ ግን አይደለህም ። ይልቅስ እነዚያን ሰዎች አድናቸው ፤ ጄኔ ራል ። ሕይወታቸውን አትርፍ ሆስነር ” አላቸው ።

“ አደርጋለሁ ” ብሎ ሆስነር ለመሄድ ዞረ ።

“ አንድ የምነግራችሁ ተጨማሪ ነገር አለ ። ይህም አንድ ውሳኔ ላይ እንድትደርሱ ይረዳችኋል ። ከሰዎቻችሁ ጥቂቶቹ የሚፈልጉት ዜና አለኝ ” ብሎ ሪሽ ንግግሩን ቆም አደረገ ።

ሆስነር የፍርሃት ቅዝቃዜ ሰውነቱን ተሰማው ። ወደኋላው አልዞ ረም ። መልስም አልሰጠውም ። ዶብኪን በበኩሉ ለሪሽ ጀርባውን ሰጥቶ ቆመ ።

“ ከሰዎቻችሁ ጥቂቶቹ የሚያፈቅሯቸው ቤተሰቦች አሉአቸው ። እነርሱም የሚገኙት በአረብ አገሮች ነው ። የእነዚያን ሰዎች ዕድል አውቃለሁ ። እነእርሱ የት እንዳሉ ማወቅ ትፈልጋላችሁ ? እጃችሁን ከሰጣችሁ ስለእያንዳንዳቸው ልነግራችሁ እችላለሁ ። ይህም ስቃይንና እርግጠኛ አለመሆንን ያስቀርላቸዋል ። ምናልባት በሕይወት ከአሉ የት እንዳሉ ማወቁ ቤተሰቦቻቸው ወደ እስራኤል እንዲመለሱ ያፋጥ ነዋል ”

ዝምታ ሆነ ።

“ ለምሳሌ በ1973 በጦርነት ላይ እንዳሉ የጠፉትን የአብደል ጀባሪን ቤተሰቦችና ወይም የራሄል ባኡምን ወንድም መጥቀስ ይቻ ላል ። ”

ሆስነር ወደፊት መራመዱን ጀመረ ። ዶብኪንም ተከተለው ።

“ በ1967 በሲናይ ውስጥ ከሚስትህ ዘመዶች አንድ አልጠፋም ፥ ጄኔራል ? ”

ዶብኪን ያለምንም መደናቀፍ እርምጃውን ቀጠለ ።

“ የሚሪያም በርንስቴይን ባል ዮሴፍ በስራያ ውስጥ እስከ አለ ፈው ስድስት ወር ድረስ ነበር ። በኋላ ግን አንድ ቀን ማታ ወስደው እርሱን ወይም የራሄል ባሉምን ወንድም ረሸነዋል ። ”

በዚህ ጊዜ ሆስነር እርምጃውን ቀነሰ ።

“ እኔ እንደምገምተው በርንስቴይን ዮሴፍ አሁንም በሰሪያ ውስጥ አለ ። ስለሁሉም የዘገብኩት አለኝ ። በኋላ አንድ በአንድ አየዋለሁ ? ”

የሆስነር ሰውነት በንዴትና በቁጣ ተንቀጠቀጠ ። እንደልቡ ለመ ራመድ ችግር ፈጠረበት ። በስተጀርባው የሪሽ ድምጽ እንደገደል ማሚ ቶ ጮኸበት ።

* ከአዳራሹ ውስጥ አውጥተው የፀሐይ ብርሃን ወደ አለበት ወሰዱ አቸው ። አጀቢአቸው የሁለቱን ዐይኖች በጨርቅ ሸፍኖ ለማሰር ፍጥ ነት አልነበረውም ። ዶብኪን በምሥራቅ በኩል 100 ሜትር እርቀት ላይ በኢሽታር መግቢያ አጠገብ የነበሩትን ግዙፍ ማማዎችና የጦር ሜዳዎች በጨረፍታ ተመለከተ ። በአቅራቢያው የእንግዶች መቀበያ ቤትና ቤተ መዘክሩ ነበሩ ። የባቢሎን ከወርቅ የተሠሩ አንበሶችና ማም ለኪያዎች በፀሐዩ ብርሃን ያብረቀርቁ ነበር ። በዓለም ላይ በአስደናቂ ነታቸው ከታወቁት አንዱ የሆነው የባቢሎን የአትክልቶች ሥፍራ ግንቦች ተሰነጣጥቀውና አቧራ ለብሰው አንድም የአትክልት ዓይነት ምልክት ሳይኖርባቸው ይታዩ ነበር ። ሆስነር ዐይኖቹ በጨርቅ ከመሸ በባቸው በፊት የቆሙበት ተራራ ሁለት ኪሎሜትር እርቀት ላይ እንደ ሆነና ኮንኮርዱ ከሚገኝበት ተራራ ጋር ከፍታው እኩል እንደሚሆን ገመተ ። እንደዚሁም ከነበረበት ተራራ ላይ ሆኖ አሻግሮ ሲመለከት ኮንኮርዱን አየው ። ሰዎቹም ወዲያና ወዲህ ሲሉ ተመለከታቸው ።

ዐይኖቻቸውን አስረው እየመሩ ወሰዱአቸው ።

አረቦቹ ትተዋቸው ከሄዱ በኋላ ዶብኪን በሃይል ተንፍሶ “ በሃ ይል ተጋፋኸው ፡ ትክክል አልነበርክም ” ብሎ ከትከሻው ዞሮ እየ ራቁ የሄዱትን አረቦች ተመለከታቸው ። “ ስማ ፡ ከዚህ የበለጠ ሰይ ጣን ነው ብየ ገምቼ ነበር ። ”

“ ከምታስበው በላይ የበለጠ ሰይጣን ነው ። ”

“ስለእርሱ እገረማለሁ ፡ በበኩሌ እብድ ለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ ።”

“ እኔ እንደማስበው ጤናማ በሚሆንበት ጊዜ በእውነት መወ ደድንና መሞገስን ይፈልጋል ። ”

" ይወዳል ፡ ሌላ ዕድል የምናገኝ ከሆነ በዚያ መልክ እንጠቀም በታለን ። "

ሆስነር ዳገቱን በሚወጣበት ጊዜ ያቃስት ነበር ። አሻቅቦ ተመ ልክቶ ለብሪን እጁን አውለበለበለት ። ብሪንም አጸፋውን ሰጠው ። ያለ ምንም ችግር ዳገቱን ይወጣ ወደነበረው ወደ ዶብኪን ዞሮ " በእ ርግጥ አንተ ልክ ነህ ። በተራራው ላይ ያሉት ሰዎቻችን ለእኛ ሬሽ ሰይ ጣን መሆኑን ያስመሰከረ ስለሆነ ለእነርሱም አደገኛ እንደሚሆን በም ንወያይበት ጊዜ ስለምናስረዳቸው ለምንወስደው እርምጃ ተቀባይነት ያስገኝልናል ። "

" እጃቸውን ለመስጠት ተስማሙ ወይ ? " ብሎ ብሪን ጮኾ ጠየቀው ።

ሆስነር ፈገግታ እያሳየና ወደ ላይ እየተመለከተ " የመጨረሻ ማስጠንቀቂያህን አስተላልፌልሃለሁ " ብሎ መለሰለት ። አሁን ከአ ለበት ሆኖ የቦታቸው አቀማመጥ ምን እንደሚመስል አብሰለሰለ ። ስለናዳዎቹ ፡ ስለገደላገደሎቹና ጐርፍ ስለቦረቦራቸው ቦታዎች አወጣ አወረደ ። በጨለማ ጊዜ መጥፎ አካባቢ መሆኑንና እርሱ ወገ ቢሆን ኖሮ በጥቂት ጊዜ ውስጥ የሞራል ውድቀት ይደርስበት እንደነበረ ተገነዘበ ።

ሁለቱ ሰዎች በተራራው ጫፍ ላይ እንደደረሱ በሥራ ላይ ያል ነበሩት መጥተው ከበቧቸው ። ዶብኪን የሆነውን ሁሉ አጠር አድርጐ ነገራቸው ። ብዙ ጥያቄዎች በመነሳታቸው ውይይቱ የሞቀ ሆነ ። ሆስ ነር ነገሩን በማሳጠር ከምሽት በፊት ምርጫ እንደሚያደርጉ ከነገራ ቸው በኋላ ወደ መከላከያ ድንበራቸው ተመልሰው ምሽጋቸውን እን ዲሠሩ ነገራቸው ። ይህ እጃቸውን መስጠት የሚባል ነገር እንደማይ ኖር አረጋገጠላቸው ።

ወንዶቹም ሴቶቹም ከሚደርስባቸው ግድያ ለመዳን የሚያስችሏ ቸውን ምሽጐች መሥራት ጀመሩ ። የተሠራውንም እያስተካከሉ አጠ ነከሩት ። ምሽግ መሥሪያ የሚሆኑ በቂ መሳሪያዎች ባይኖሩአቸውም የአውሮፕላኑን ስብርባሪ በሚፈልጉት ዓይነት እየሠሩ ተጠቀሙበት ።

በአውሮፕላኑ ክፍል ውስጥ መቀመጫና ወለል የተሠሩባቸውን በረቶችና ሽቦዎች ፈታትተው በመውሰድ ለምሽጐቻቸው እንዲያገ ለግሉ አድርገው አቀነባበሩአቸው ።

አንድ የምክር ቤት አባል የግሪክ የፊዚክስ ሊቅ የነበረው አርኪ ሜዲስ ለሲራኪዩስ መከላከያ እንዲሆን የሠራውን ያስታወሰው በዚህ

ጊዜ ነበር ። ታሪኩ እንደሚለው አርኪሜዲስ የሮማንን መርከቦች ሊያቃጥል የሚችል አጉልቶ የሚያሳይ ትልቅ መስታዋት ሠራ ። ይህን ፈለግ በመከተል ከአውሮፕላኑ ጅራት ላይ አሉሚኒየሙን እየላጡ በመውሰድ በመከላከያ ክልላቸው ዙሪያ አልፈው አልፈው አስቀመጡ ። የዚህ ድርጊት ዋና ዓላማው ምናልባት አሸባሎቹ በቀን ውጊያ ቢከፍቱ በፀሐይ ብርሃን እያንጸባረቁ በጠላት ዐይኖች ላይ እንዲያርፍ ለማድረግ ነበር ። ከዚህም ሌላ አሸባሎቹ ስለሚያብረቀርቅባቸውና ዓይኖቻቸውን ስለሚያቃጥለው ማነጣጠር አይችሉም ነበር ። በተጨማሪም አሉሚኒየሙ ስለሚያብረቀርቅ በዚያ አካባቢ በመሬትም ላይ ሆነ በሰማይ ላይ የሚያልፉና የሚበሩ ቢመጡ እንዲያዩአቸው ይረዳቸው ነበር ። እንደዚሁም ጥቂት ወንዶችና ሴቶች አሉሚኒየሙን ይዘው በመቆም ዓለም አቀፍ የሕይወት አዳኞች በዚያ በኩል እንደ አጋጣሚ ቢያልፉ እንዲያዩአቸው ሙከራቸውን ቀጠሉ ።

ቀኑን ሙሉ ጉድጓዶች በጥልቀት ተቆፈሩ ። የመከላከያ ምሽጎች በእርዝመት ተሠሩ ። ለመከላከያ ያስቀመጡአቸው አፈር የተሞሉ ሻንጣዎችና እንደ ጦር እየተሾሉ የተተከሉ ብረቶች እንዳይታዩ የባቢሎንን አቧራ አለበሷቸው ። ወንዶችና ሴቶች ልብሶቻቸውንና ፊቶቻቸውን በላባቸው የራሰውን አቧራ አንዳንድ ጊዜም አቧራውን በሽንታቸው እያራሱ እንዲቀቡ ዶብኪን አዘዛቸው ። የመዋጊያ ቦታዎች በሚገባ ተዘጋጁ ። በጉርፍ የተቀደዱ ቦዮች በእርቀት አልፎ አልፎ አፈርና ድንጋይ ተሞሉ ። የዚህ ሥራ ዋና ዓላማው ጠላት በቦዩ ውስጥ ተሹለክልኮ ቢመጣ እሙሊቶቹ አጠገብ ሲደርስ በግድ ዘሎ ማለፍ ስለሚኖርበት እንዲታይ ለማድረግ ነበር ።

አልፎ አልፎ የበቀሉ ችፍግ ያሉ እሾሃማ አጫጭር ዛፎች የጠላት መሸሸጊያ እንዳይሆኑ እየመነጠሩ ወደ ክልላቸው አገቧቸው ። ከታች የሚመጡ ጠላቶችን ለማጥቃት የሚያስችሉ በየተራ እየተገፉ የሚሰደዱ ናዳዎች አንዳንዶቹ እስከ 100 ኪሎ ግራም የሚመዝኑ ተዘጋጁ ። የአሉሚኒየምና የብረት ቁርጥራጮች አሹለው እየተከሉ አፈር በማልበስ ጠላትን እንዲያደናቅፉና እንዲጎዱ አድርገው አዘጋጅዋቸው ።

ለመከላከያ የሚያገለግሏቸውን ብረታ ብረትና ሌሎች ዕቃዎችንም ለማግኘት አውሮፕላኑን የመገነጣጠሉ ሥራ ያለመሣሪያ በመሆኑ ብዙ ጊዜ ቢፈጅባቸውም የፈለጉትን አድርገዋል ። እያንዳንዱ ሰው የራሱን ዘዴና ብልሃት በመጠቀም በብዛት የጅራቱን ክፍል እየገነጣጠለ በሥራ ላይ አዋለ ። በቅዱስ ናዛየር ኮንኮርዱን ለመሥራት እንደ ተደረገው ሁሉ ፤ እያሌ እስራኤላውያን ትልቁን ኮንኮርድ ለመገነጣ

ጠል እንደ ጉንዳን በላዩ ላይ ሰፈሩበት ። ኑሪ ሰላሜ ቦምቡን ለማስቀመጥ በነበረበት ቦታ ላይ ቆመው ይሠሩ ነበር ። ቦምቡን እንዴት አድርጐ እንዳስቀመጠው አዩ ። በፍንዳታው የተበታተኑትን ዕቃዎች እየለቀሙ በሥራ ላይ አዋሏቸው ። ከቁርጥራጮቹ ብረቶችና ቧንቧዎች ለራስ መከላከያ የሚያገለግሉ ጩቤዎችና ጦሮች ሠሩ ። የተገኙ ጠርሙሶች ሁሉ የያዙት ፈሳሽ ወደ ሌላ ዕቃ ላይ እየተጋባ በአውሮፕላኑ ነዳጅ ተሞሉ ። በጥቂት ጠርሙሶች ውስጥ በተጨማሪ ሳሙና ተደረገባቸው ። ሁሉም ለፈንጂነት እንዲያገለግሉ ተደርገው ተዘጋጁ።

የሰላም ውይይቱ አባላት (ሴቶችና ወንዶች) በተባበረ ፍላጐትና ወኔ በመሞላት ያለአንዳች ዕረፍት ሠሩ ። አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት ለተወሰነ ደቂቃ እየተሰበሰቡ ሃሳብ ይለዋወጡ ነበር ። በቀድሞ ዘመን ስለ ተደረጉ ጦርነቶች በመወያየት የሚያገኙትን አዲስ ዘዴ እየተጠቀሙ ጠላቶቻቸውን ድባቅ ለመምታት የሚያስችላቸውን መንገድ ተለሙ ። አርኪሜዲስንና ዳ ቪንቺን አስታወሱ ። የትሮይ ፣ የሮም ፣ የሲራክየስ ፣ የካርቴጅ ፣ የኢየሩሳሌምና የባቢሎን ከበባዎች እንዴት እንደነበሩ በትምህርት ቤት በነበሩበት ጊዜ የተሰጣቸውን ትምህርት በማስታወስ በሥራ ላይ አዋሉት ። ለማሸነፍ ያስቻሉ ባሕርያት ምን ነበሩ ? ሽንፈትን ያስከተሉስ የትኞቹ ነበሩ ? ስለእስራኤል የስለላ ድርጅት ማሰብ ይቻል ነበር ። ስለሚያደርጉት ሁሉ በመመካከር ተመሳሳይ ስምምነት ላይ ደረሱ ።

በተከላካዮቹ አዕምሮ ውስጥ አንዳንድ ነገሮች መጉላላት ጀመሩ ። አዋቂና የሰለጠነ ቡድን በተወሰነ መሣሪያ ፣ ዝቅተኛ ሥልጣኔና የተሻለ ትጥቅ ያለውን ቡድን መቋቋም ይችላል ? ሆስኒር የረጅሙን መስመር የመከላከያ ሥራ ቅርጽ ተመለከተ ። የጉብታው ግራና ቀኝ አቀማመጥና የምዕራባዊ ቁልቁለትን ለመውጣት አስቸጋሪ መሆኑን ከአስተዋለ በኋላ ለመከላከያ እንዲሆኑ የተሠሩት ምሽጐች በጣም ጥሩ እንደነበሩ ተረዳ ። ከአየር ላይ እንደተመልካች ሆኖ ቢያይ — አሁን አህመድ ሪሽ በሌየሩ ጄት ሆኖ እንደሚያደርገው — እነዚህን በችኮላ የተሠሩ ምሽጐች ሰብሮ ለመግባት አስቸጋሪ እንደሚሆን ሊረዳ ይችል ነበር ።

ሆስኒር የሚያውቀው ትክክለኛ ጥያቄ ለምን ያህል ጊዜ ለመቋቋም ይቻል ይሆን የሚል ነበር ። አንድ ቀን በጣም እረጅም ሊሆን ይችላል፣በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሳምንት እረጅም ላይሆን ይችላል። የዚህ ሁሉ ማሠሪያ በራሳቸው ወገኖች የሚገኙበት ጊዜ ነው ። በወቅቱ ይገኙ ይሆን ? በእስራኤል ውስጥ ምን እየተካሄደ ይሆን ?

የሎድ አየር ሞቃት በመሆኑ ምክንያት ለመቋቋም በጣም አስቸ ጋሪ ደረጃ ላይ ደርሷል ። ቴዲ ላስኮቭ ከቡና ቤቱ ውጭ ባለው በረንዳ በወንበር ላይ ተቀምጦ ቢራ ይጠጣል ። በአካባቢው የነበሩ የሱቆች መስኮቶች በመጋረጃዎች ተሸፍነዋል ። የሰንበት ቀን ትራፊክ ከቀድ ሞው ቀንሶአል ። ባለቤቱ ክርስቲያን የሆነው የሚቸል ቡና ቤት ግን በሕዝብ ተጨናንቋል ። ሀማሲን የተባለው ሞቃት አየር ቶሎ የሚለቅ አይመስልም ። ላስኮቭ ያላበውን ብርጭቆውን ጐንበስ ብሎ ሲመ ለከት በብርጭቆው ዙሪያ ያቀረረው ውሃ የራሱን ቦይ ቀዶ ከእብነበ ረድ በተሠራው ጠረጴዛ ላይ ተንኳሎ በእግሩ ላይ ሲንጠባጠብ አየው። ቴዲ ላስኮቭ የለበሰው ሰማያዊ ቀለም ያለው የሲቪል ሱሪ እንደማን ኛውም ግለሰብ ያደረገው መሰለው ። ለአለፉት 40 ዓመታት አንድ ዓይነትም ይሁን ወይም ሌላ ሲለብስ ቢቆይም የአሁኑ እንግዳ ስሜት አሳደረበት ። ከሥራ ውጭ የሲቪል ልብስ እንደሲቪል ሆኖ መልበስ ትልቅ ልዩነት እንደነበረው ላስኮቭ አስታወሰ ። ልብሶቹ አንድ ቢሆ ኑም አለባበሳቸው ልዩ ነበር ።

የሚቸል ቡና ቤት የሚሪያም ትዝታ ድቅን እንዲልበት አደረገ ው ። እዚያ የሔደው በዚህ ምክንያት ሳይሆን በሰንበት ቀን አንዳንድ ሥራዎችን ለማከናወን ምቹ ቦታ ስለነበረ ነው ። ይሁን እንጂ ለሚሠ ራው ምንም ውሳኔ ሳይሰጥ እንዲሁ ነገሮችን በአእምሮው ውስጥ ሲያ ወጣና ሲያወርድ ከመኖሪያ ቤቱ ከወጣ አንድ ሰዓት አልፎታል ። አሁን ግን አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ቆረጠ ።

ጄኔራል ታልማን ሁልጊዜ ላስኮቭ እንደሚለው በቄንጠኛ አረ ማመድ ሲመጣ አየው ። ሁልጊዜም ቢሆን በሁለተኛው የዓለም ጦር ነት ፊልም ውስጥ እንዳለ የሮያል አየር ኃይል መኰንን ይመስል ነበር። አሁን እንኳን ዩኒፎርሙን ሳይለብስ ሁኔታው የማዕረግ ልብሱን የለ በሰ ይመስላል ። እየቀረበ ሲመጣ ላስኮቭ የፊት አለቃው መንፈስ ከቀ ድሞው የተሻለ ሆኖ አላገኘውም ። ታልማን ራሱን በአዎንታ አነ ቃንቆ ሲቀመጥ ሪዙ እንደመንቀጥቀጥ አለ ።

“ በጣም ሙቀት ሆኖአል ” አለው ታልማን ።

“ አጢኘዋለሁ ። ”

“ እሺ እንግዲህ ሥራችንን እንጀምር ፣ ማዛር ይመጣል ? ”

“ መምጣት አለበት ። ”

“ ባይመጣም እንጀምር ” አለው ታልማን ።

“ መልካም ” ብሎ ለስኮቭ ከኪሱ ወረቀቶች አወጣ ። ቀጥሎም

" ይጠቅማሉና ይሆናሉ የምንላቸውን የራዳር እይታዎች እንደ ዚሁም የእስራኤልና የአሚሪካ ራዲዮ ሪፖርቶች ለማሰባሰብ ያልቆፈ ርኩት ፣ ያልወጣሁበትና ያልወረድኩበት የለም " ብሎ ወረቀቶቹን አገንብሶ እየተመለከተ " እንደማስበው ከሲናይ ተራራ ጫፍ ወደ ምሥራቅ አምርተዋል " አለው ።

ታልማን በጣቱ ጠረጴዛውን ቆርቆሮ " ከሁር ጋር ተነጋግሬአ ለሁ ። በእርግጥ በቃል እንጂ በጽሑፍ እንዲያዝ አልፈለግሁም። እንደ ነገረኝ ፍልስጠኤማውያኖች የጠነሰሱት ውስብስብ ሳይሆን አይቀርም። ሆኖም ብዙዎቹ የጸጥታ ሠራተኞች ወደ ምዕራብ ሔደዋል በሚለው ሃሳብ ላይ አተኩረዋል ። ወደዚያ ከሆነ የሔዱት በፖለቲካ አንጻር ሲ ታይ ትክክል ይመስላል ። ጥቂት የሥራ አመራር ሰጭ ሰዎች ደግሞ ወደ ደቡብ ጉዞአቸውን በመቀጠል ሱዳን ገብተዋል በሚለው አስተ ሳሰብ አምነዋል ። ይህም የፖለቲካውን ሁኔታ ሲመለከቱት እውነት ነት ያለው ይመስላል ። በሰሃራ አርፈው ቤንዚን ከሞሉ በኋላ ከፈለጉ ወደ ዩጋንዳ መሄድ ይችላሉ ። በዚያ አካባቢ ብዙ ራዳሮች የሉም ። በብ ዛት ያለው ገላጣ ቦታ ስለሆነ ነዋሪዎቹ ጥቂት ቢሆኑም ሊያዩአቸው ይችላሉ ። በፖለቲካ ፣ በሎጂስቲክና በተግባር እረገድ ሲያዩት ወደ ሊቢያ ወይም ሱዳን ሄደዋል የሚለው አስተያየት ሊታመን ይችላል" ብሎ ለትንሽ ጊዜ ንግግሩን ቆም አድርጎ የላስኮቭን ዓይን እየተመ ለከተ " እኔ ግን የሄዱት ወደዚያ ሳይሆን ወደ ምሥራቅ ይመስለኛል" አለው ።

ላስኮቭ ፈገግ ከአለ በኋላ " ጥሩ ነው ። አሁን እንግዲህ ለምን እንደሆነ አሳይሃለሁ " ብሎ ማስታወሻዎቹን አንድ በአንድ መመል ከት ጀመረ ።

ታልማን ጂንና ቶኒክ አዞ ያዳምጥ ጀመረ ።

ቼይም ማዛር አልፎአቸው ወደ ታችኛው መንገድ ከሄደ በኋላ ተመልሶ መጣ ። ያልተያዘ ጠረጴዛ የሚመለከት መስሎ ላስኮቭና ታል ማን የት እንደተቀመጡ ከአየ በኋላ ፈገግታ አሳይቶ ወደ እነእርሱ ሄዶ " አብሬአችሁ ብቀመጥ ቅር አይላችሁም ? " ብሎ በአንድ ትንሽ የሸቦ ወንበር ላይ ተቀመጠ ።

ላስኮቭ በአሉታ ራሱን ነቅንቆ " የሺን ቤትዝ ሐላፊ እንጂ የሥራ አመራር ሰጭ ባለመሆንህ ደስ ብሎኛል ። አንተ በሕይወቴ ሙሉ ከአ የሁት እጅግ በጣም መጥፎ ተዋናይ ነህ " አለው ።

" እሞክራለሁ " ብሎ ዙሪያውን ከቃኘ በኋላ " ከሁለታችሁ ጋር መታየት የሚያመጣው ፋይዳ የለም " ብሎአቸው የሎሚ ጭማቂ

ከእዘዘ በኋላ " አሁን በቀጥታ ከጋዜጣዊ መግለጫ መምጣቴ ነው ። ምቃቱ ነፋስ እዚህ ያስቸገራችሁ ከሆነ እዚያ ጥግ መቀመጥ ነበረ ባችሁ " አላቸው ።

ታልማን ወደፊት ሰግደድ ብሎ " ይህን ማለትህ ጥሩ ስለሆንክ ነው " አለው ።

" ማዛር ትከሻውን ከፍና ዝቅ አድርጐ " ስሙ ፤ ሥራየን በራሴ ፈቃድ መተው ወይም በፈቃዴ ራሴን ከሥራ ማግለል ነበረብኝ " አላ ቸው ።

" ለምን ? " ብሎ ላስኮቭ ከጠየቀው በኋላ " የአዳፍኔውን ውጊያ ከአከሸፍህ በኋላ የሰዓቱ ጀግና አንተ ነህ ። መንግሥትም በዚህ ወቅት ጀግና ይፈልጋል ። ለሁላችንም ያለኸን አንተ ነህ " አለው ።

አሁንም ማዛር ትከሻውን ከፍና ዝቅ አድርጐ " ነገሩ በሚረጋጋ በት ጊዜ አገኘዋለሁ ። በአዳፍኔ አደጋ ለማድረግ ቀደም ብሎ የተጠ ነሰሰ እንደነበረ ነግሬአችኋለሁ ። ይህ እንዲፈጸም የአደረጉ ሰዎች የአ ውሮፕላኑንም ጠለፋ ያዘጋጁ ናቸው ። ነገሩ እንደዚህ ነበር — በአ ንድ ምክንያት የሪሽ ሌየር እንደፈለገው ባይሆንለት በአዳፍኔው በመ ጠቀም ዓላማውን ተግባራዊ ሊያደረግ ነበር። ሌየሩ ተዘጋጅቷል ። ስለ አዳፍኔው መጠመድ ከፍልስጥኤማውያኖቹ አንዱ ነገረኝ ። ስለእነ እርሱ ግን አስቀድሜ ደርሼበታለሁ " አላቸው ።

የአገር ውስጥ ደህንነት ሐላፊ እንደመሆንህ ሁሉ ማድረግ የሚ ገባህን አድርገሃል ። የዚህ ተጠያቂዎች ሆስነር . . . እና . . . ነበርን ። ስለዚህ አንተ ለደረሰው ጥፋት እንዴት ሐላፊ ትሆናለህ ? ብሎ ላስ ኮቭ ጠየቀው ።

" በከፊል ነኝ ። አያችሁ ፤ ሌየሩ ኮንኮርዶቹን ለመጥለፍ እን ዲችል የመነሻውን ትክክለኛ ሰዓት ማወቅ ነበረበት ። የመነሻው ሰዓት በካይሮ አየር መንገድ ለሪሽ በእስራኤል ውስጥ ባለ አንድ ሰው መተ ላለፍ አለበት ። ያም ሰው በአገራችን ውስጥ ሆኖ የስለላ ሥራ የሚ ያካሂድ በአየር መንገዳችን የነበረ መሆን አለበት ። ይህ አካባቢ በእኔ ሐላፊነት ሥር ሆኖ ሳለ ያንን ሰላይ ማንነቱን ለይቼ ማወቅ አልቻል ኩም ። ጥቆማ እንኳን አልደረሰኝም " ብሎ ሲጋራ ከአቀጣጠለ በኋላ " ማንም ይሁን ማን ከሎድ ጥሪ አድርጐ ግንኙነት በማድረግ አዲ ሱን የበረራ መነሻ ጊዜ ተናግሮአል ። ሁለታችሁም ሪሽ በራዲዮ ግን ኙነት አለው ብላችሁ ማሰባችሁን ከመናገራችሁ በፊት ከካይሮ ጋር ግንኙነት አድርጌ ተባብረውኛል ። ሪሽና ጓደኞቹ በስውር ስም ወደ ቆጵሮስ የሚሄዱ ነጋዴዎች መሆናቸውን ከአስመዘገቡ በኋላ ሃሳባቸ

ውን ወደዚያው ለወጡ ። የእስክንድርያ አየር ትራፊክ ተቆጣጣሪ ቀደ ም ብለው ለመነሳት ያቀረቡትን ጥያቄ ባለመቀበል ችግር ስለፈጠረባ ቸው ፣ እኔ እንደጠረጠርኩት ከሆነ በብዙ አካባቢዎች እንደሚደረገው ጉርሻ በመስጠታቸው ተፈቅዶላቸዋል ። ያም ሆነ ይህ የሆነውን ታሪክ ይመዘግበዋል ” በማለት ዘርዝሮ ነገራቸው ።

ታልማን በአዎንታ ራሱን ነቅንቆ “ የሚያስደንቅ ነገር ነው ። እንዳልከውም ታሪክ ነው ” ከአለው በኋላ “ ኮንኮርድ 02 አሁን ያለው የት ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ ይህ የእሥራኤልን መንግሥትና የውጭ ጸጥታ ተከታታዮቿ ንና የጦር ኃይልዋን ቅንብር የሚጠይቅ ነው ። በሺን ቤትዝ ሐላፊነቴ የሚፈለገው ሰላዩ ማን እንደሆነ ማወቅ ነው ። ይህን ከባድ ሥራ ለመ ወጣት ወኪሎቼንና የአረብ ወሬ አቀባዮቼን አስተባብሬ መሥራት አለብኝ ። ”

“ ለምን ? ” ብሎ ታልማን ጠየቀው ።

“ ምክንያቱም ይስሐቅ በርግ የሚቪትዛን ኤሎሄም ሐላፊ ስለ ሺን ቤትዝ ብዙ ያውቃል ። በርግ በጠላቶቹ እጅ ከወደቀ አሰቃይተ ውና አስጨንቀው ሊያውቁ የሚችሉት የእርሱን ድርጅት ብቻ ሳይ ሆን በእኔም ውስጥ የሚሠራውን ይሆናል ። ”

ላስኮቭ ራሱን በአሉታ ነቅንቆ “ ዘበት ነው ። እርሱን በእጃቸው ውስጥ ከማስገባታቸው በፊት ራሱን ይገድላል ” አለው ።

ማዛር በአዎንታ ራሱን በመነቅነቅ “ ጠመንጃ አለው ። ስለዚህ ራሱን ለመግደል ጊዜ ከአገኘ በእነእርሱ እጅ አይወድቅም ” አላቸው።

ታልማን ሌላ ጂን አዞ “ ዶብኪንስ እንዴት ነው ? በአማን ውስጥ ነበር ፣ አልነበረም ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ዶብኪን ከወታደራዊ የደህንነት ሥራ ጋር የቅርብ የሥራ ግን ኙነት አለው ። በተጨማሪም የሚኒስትሮች (ካቢኔ) ምሥጢር ያው ቃል።የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ. . . ሁሉንም ነገር ያውቃል።ስለዚህ የሚ ያውቀውን ሁሉ አውጥቶ ይናገራል ብየ አላስብም ። ” ማዛር ጠረ ጴዛውን ከተመለከተ በኋላ እንደገና ወደ ላስኮቭ ትኩር አድርጐ አስ ተዋለ ። “ ሚሪያም በርንስቴይን ስለክበሬው የማታውቀው ነገር የላ ትም ። የሚደርስባትን ከባድ ችግር የምትቋቋም አይመስለኝም ። አን ተስ ምን ይመስልሃል ? ” ብሎ መልስ ጠበቀ ።

ታልማን ወደ ላስኮቭ ዞሮ ቢመለከትም በፊቱ ላይ ምንም ለውጥ አልነበረም ። በመሃከላቸው ጸጥታ ሰፈነ ።

በመጨረሻም ማዛር በኃይል ተንፍሶ " ሁሉም ይሞታሉ ብየ ተስፋ የአደረኩት ላለፈው 30 ዓመት በጸጥታ ሥራ ውስጥ ያሳለፍኩ ትን ጊዜ ምክንያት በማድረግ ነው " ብሎ ለትንሽ ጊዜ ንግግሩን ቆም ኮአደረገ በኋላ " ስለሆስነር እርግጠኛ ነኝ " አላቸው ።

ለብዙ ደቂቃዎች አንደኛቸውም አልተናገሩም ። እየጠጡ በመ ንገዱ ላይ የነበረውን የአየር ሁኔታ ተመለከቱ ። ላስኮቭ ጉሮሮውን አፍ ታቶ " ስለሪሽ ያምትነግረን ነገር አለህ ? " ብሎ ጠየቀው ። ማዛር በርሳውን ከፍቶ አንድ ማኅደር ክአወጣ በኋላ " እርሱ እብድ ነው ። ማንኛችሁም የጸጥታ ሥራ ልምድ ፡ ፈቃድ ወይም የማወቅ ፍላጐት ወይም ግንዛቤ የላችሁም " ብሎ ማኅደሩን ለታልማን ሲሰጠው " የእኔም ግንዛቤ ይህን ያህል አይደለም " አላቸው ።

ታልማን ወረቀቱን አንድ በአንድ በጣቱ እያገላበጠ " ያንን እኛ ም እናውቃለን " አለው ።

" ያካባቢ ፎቶግራፎች አግኝተሃል ? " ብሎ ላስኮቭ ጠየቀው ።

" አዎን ፡ አለው ማዛር ። ከአሜሪካ ሳተላይቶችና ኤስ አር— 71 ሰላይ አውሮፕላን የተገኙ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አሉ ። ከምንጠረ ጥራቸው ጥቂቶቹ እነዚህ ናቸው ። አሜሪካኖቹ ከአማን ጋር በጣም ተባባሪዎች ናቸው ። ነገር ግን ለምን ሺን ቤትዝ እንደሚፈልጋቸው ለመግለጽ ብዙ ችግር አጋጥሞኝ ነበር ። ለማንኛውም እነዚህን ልታ ነቧቸውና በፎቶግራፎቹ ላይ አስተያየት ልትሰጡባቸው ትችላላችሁ ብየ አስባለሁ ። "

" ከ40 ዓመት በኋላ ተስፋ አደርጋለሁ " አለው ላስኮቭ ። ከማ ዛር ላይ ብዛት ያላቸው ፎቶግራፎች ወስዶ የመጀመሪያውን ተመለ ከተ ። በሕዳጉ ላይ ቀጥ ባለው መስመርና ኬንትሮስ ላይ በእርሳስ ምልክት ተደርጓል ። ፎቶግራፉ የሲናይ ጫፍ ነበር ። በዓመቱ ውስጥ በዚህ ጊዜ ደመና የሚበዛበት ወቅት ነበር ። "

" ወሩ እኮ ጸደይ ነው ። ለማንኛውም በግብጽ ፡ በሱዳንና በሊ ቢያ ለመሆናቸው ከፍተኛ አስተሳሰብ አሳድሮአል ። እኔ ይህን ብገ ምትም እናንተ ግን አሁንም ወደ ምሥራቅ ሔደዋል ብላችሁ ታስባ ላችሁ ? " ብሎ ማዛር ጠየቃቸው ።

" እኛ እንደዚያ እናስባለን " አለው ላስኮቭ ። " ሪሽ የኢራቅ ሰው ነው ። አይደለም እንዴ ? "

ማዛር ፈገግ ከአለ በኋላ " እንደምትለው ቀላል ቢሆን ኖሮ እደ ሰት ነበር ። ግን መታወቅ ያለበት አብዛኞቹ ፍልስጥኤማውያን የሪሽ

ቡድኖች ናቸው ። ይሁዳውያኖች የዓለም ተንከራታቾች እንደነበሩ ሁሉ ፍልስጥኤማውያንም የእስላም ተንከራታቾች ናቸው ። አባባሉ ፉተታ ነበረው ። “ ከሞሮኮ እስከ ኢራቅ ባለው በማንኛውም ቦታ ሊኖሩ ይችላሉ ” አለው ።

ላስኮቭ የጤግሮስንና የኤፍራጥስን ፎቶግራፎች በተከታታይ ይመለከት ስለነበረ የአዳመጠው በከፊል ነበር ። ፎቶግራፎቹ የተነሱት ያን ቀን ጧት በአንድ ሰዓት 25 ኪሎ ሜትር ከፍታ ላይ በኤስ አር—71 የስለላ አውሮፕላን ነበር ። እንደዚሁም በኢራን ውስጥ የሻሚያ በረሃ ፎቶግራፎች ነበሩ ። ፀሐይ ሙሉ በሙሉ ብርሃንዋን አዳርሳ ስለአል ነበረ በፎቶግራፎቹ ላይ በብዛት ጥላ ይታይ ነበር ። ወደ ማዛር መለስ ብሎ “ በእኩለ ቀን አካባቢ የተወሰዱ የኢራቅ ፎቶግራፎች አሉ ?” ብሎ ጠየቀው ።

ማዛር በማስታወሻው ውስጥ ተመልክቶ በ6 : 17 ሰዓት በሳተላይት የተወሰዱ ፎቶግራፎች አሉ ። እስከ ነገ እኩለ ቀን ድረስ በስለላ አውሮፕላን ፎቶግራፍ ለማንሳት በአሜሪካኖች ዕቅድ አልተያዘም ” ብሎ ነገረው ።

“ እንግዲያው በሳተላይት የተነሱትን ፎቶግራፎች ስጠኝ ” አለው ላስኮቭ ።

“ እሞክራለሁ ” ብሎ ማዛር ተነሳ ። “ ለጦር ፍርድ ቤት ሊያስቀርበኝ ለሚችል ክስ ራሴን እያዘጋጀሁ ነው ” ብሎ ባዶ ቦርሳውን ከዘጋ በኋላ “ ከመለኮት መልዕክት ቢደርሳችሁ እንዳውቀው ይደረግልኝ ። እስከዚያው አሳልፎ የሰጠንን መፈለግ አለብኝ ” አላቸው ።

ታልማን የሪሽን የሕይወት ታሪክ ከሚዘረዝረው ጽሑፍ ቀና ብሎ “ ለአራቱ ፍልስጥኤማውያን የአዳፍኔ ሰዎች ጥያቄ አቀረብክላቸው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ አዎን ፣ በእርግጥ የሚያውቁት ነገር የለም ። አናውቅም ቢሉም እንኳን ለእነእርሱ ጠቃሚ መስለው ያልታዩአቸውን ነገሮች እኛ የራሳችንን አስተያየቶች በማከል እንከታተላለን ። የአሠራር ዘዴአችንን አንተም ታውቀዋለህ ” አለው ማዛር ።

“ ታዲያ ያገኘኸው ወይም ያገናዘብከው ነገር አለ ? ” ብሎ ታልማን ጠየቀው ።

“ እነዚህን የዋሆች ሪሽ ያዘጋጃቸው መሆኑን ላምን ችያለሁ ። እንደዚሁም ሌሎች ፍንጮች አሉ ። ግን የራሴን ሃሳብ ከመገምገሜ

በፊት ጉዳዮቹን በሚገባ መረዳት አለብኝ ። ሁሉቱንም ነገሮች እንድ ታውቃቸው አድርግሃለሁ ። ”

ላስኮቭ ተነስቶ የማዛርን እጅ በመያዝ “ አመሰግናለሁ ” ካለ ለው በኋላ “ ይህን የምታደርገው የዋህ ስለሆንክ ነው ” አለው ።

“ አዎን ” ብሎት ከግንባሩ ላይ ላቡን ከጠረገ በኋላ “ እዳ አለ ብህ ። ለመሰብሰብ አንድ ቀን ተመልሼ እመጣለሁ ” አለው ።

“ አሁን ብሰጥህስ ” ብሎ ላስኮቭ በወረቀት የተጠቀለለ “ ክፍ ያህ ይኸውልህ ” ብሎ ሰጠው ። ማዛር ዓይኖቹን በኃይል በልጥጦ እየ ተመለከተ “ እርግጠኛ ነህ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ አይደለሁም ፤ እርግጠኛ መሆን የአንተ ሥራ ነው ” አለው ።

ማዛር የተጠቀለለውን ወረቀት በኪሱ ውስጥ አስገብቶ ፈጠን ባለ እርምጃ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ አደባባይ ሂዶ ታክሲ ጠራ ።

# 18

ሌየሩ ጂት ቀስ በቀስ ዝቅ እያለ መጣ ።

“ መትተን እናውርደው ” ብሎ ብሪን ሃሳብ አቀረበ ።

ሆስነር ስቶ ጀንበር እስክትጠልቅ ድረስ ስለተስማማን እኛው ራሳችን ስምምነታችንን ማፍረስ አንችልም ። ስለዚህ ሌላ ጣጣ አታ ምጣ ፤ ብሪን ” አለው ።

“ ለማንኛውም ቀን አይወጉንም ። ስምምነቱን ያፈረስን ለመ ሆናችን ምንም ምልክት የላቸውም ። ”

ዶብኪን የጦርነት ዕቅድ የሚያሳዩ ፕላኖች መሳሉን አቋርጦ ቀና በማለት “ የምትለው ሙሉ በሙሉ እውነት አይደለም ። ቀኑን ሙሉ በማንዣበብ ስምምነቱ በእኛ በኩል የፈረሰ ለማስመሰል ሊተ ነኩሱን ይችላሉ ። እናንተ ከምትቀበሉት ስምምነት ሌላ ማድረግ አል ፈልግም ። ግን ተጨባጩን ሁኔታ እንከተል ” ብሎት በወረቀቱ ላይ ፕላኑን መንደፍ ቀጠለ ። ከፊት ለፊቱ በአቀበቱ ላይ ያለውን ወጣና ገባ ሳለ ። የሠራው አንድ ተኳሽ ንድፉንና በላዩ ላይ የተጻፉትን ተመ ልክቶ ቀንም ሆነ ማታ በተወሰነ እይታ ጠላቱን በትክክል ለማጥቃት የሚያስችል ሥዕል ነበር ። “ ይኸው ” ብሎ ለብሪን ሰጠው ።

“ በኮከብ ብርሃን የሚያሳይ መነጽር ያለው ጠመንጃ ስለአለኝ አያስፈልገኝም ጄኔራል ። ”

"የባትሪዎቹ ኃይል እየቀነሰ ነው ፤ መነጽሩም ሊሰበር ይችላል ።"

" እግዜር ከእንደዚህ ዓይነቱ ያውጣን ። በሩቅ የምናይበትና ከመሳሪያዎቻችን ሁሉ እጅግ የሚጠቅመንና የምንተማመንበት ነው " አላቸው ሆስነር ።

" በመሳሪያው እኔ ብቻ የምጠቀምበት ለዚህ ነው " ብሎ ብሪን ቅር እያለው ንድፉን ተቀበለው ።

ናኦሚ ሀበር እንደ አረቦቹ ዓይነት በራስዋ ላይ ፎጣ ጠምጥማና ለመከላከያ የተቆለለውን አፈር ተደግፋ በመቀመጥ " አንተ ግሩም ሰው ነህ " አለችው ።

ብሪን እንደ አልሰማ ሆኖ ችላ አላት ።

ዶብኪን ተመለከታት ። ፎጣው ረጅሙንና ጥቁር ጸጉርዋን እንዲሁም ግንባርዋን ሸፍኖታል ። አሁን የተለማመደች መስላለች ። "የመጨረሻው ስምሽ ሀበር ነው ፤ ልክ ነኝ ? " ብሎ ጠየቃት ።

በጥንቃቄ ከተመለከተችው በኋላ " አዎን ፥ ልክ ነህ " አለችው። " መልካም ፥ በዳቢ ክሮኬት ምድብ ውስጥ እንደነበርሽ አልጠራጠርም ። "

" ማን ? "

" ተይው ግድ የለም " ብሎ ወደ ሆስነር በመዞር " ይህች ልጅ በወታደራዊ ተኳሽ ቡድን ውስጥ ነበረች " አለው ።

ብሪን በአድናቆት ከተመለከታት በኋላ " እስከ አሁን ለምን አልነገርሽኝም ? " ብሎ ጠየቃት ።

ተነስታ ወደ ዶብኪን በመዞር " ጄኔራል . . . እኔ . . . ማለቴ የእርሱ አረዳት . . . ሩዋጭ እንድሆን በፈቃዴ መርጫለሁ ። በዚህ በኩል እንድሠራ የመረጥኩት ጠመንጃና አጉልቶ የሚያሳይ የኮከብ ብርሃን ያለው መነጽር መኖሩን በማወቄ ነው ። ግን . . . በኢላማ ላይ መተኮስና በሰው ላይ መተኮስ የተለያዩ ናቸው ። አይደሉም እንዴ ? እኔ አይመስለኝም—" አለችው ።

ዶብኪን በሀዘኔታ ከተመለከታት በኋላ " ያዕቆብ" ብሎ መጣራት ጀመረ ።

ሆስነር ቆሞ ክንድዋን አፈፍ አድርጐ በመያዝ " ስሚ ፥ አንቺ ወጣት ሴት ፥ ብሪን በአለቤት አስፈላጊ ቦታ አካባቢ ከእኔ ሰዎች አንድ እንኳን የለም ። የአንቺን ዓይነት ሥልጠና ያለው ሰው ስጠይቅ በዚህ

ተራራ ላይ አንድም አልመጣም ። ለምን እንደአልነገርሽኝ በእግዚአ ብሔር ስም እጠይቅሻለሁ ። አሁን ግን የደፈጣ አደጋ ጣይ ትሆኛለሽ ። ከእነዚያ አሸባሎች አንዱ ዛሬ ማታ ወደ ተራራው ሲመጣ ብታዪና ወደ ዚህ ለመድረስ ቢችል በአንቺ ላይ ስለሚፈጽመው አስቢ ” አላት ።

ልጅቱ ዞራ የተራራውን ግርጌ አቆልቁላ በትኩረት ተመለከተች። ብሪን ሀፍረት የተሰማው መሰለ ። ቀጥሎም “ እኔ እቆጣጠረዋ ለሁ ፣ አለቃዬ ” አለው ።

“ ያልከውን አድርግ ” ብሎት ሆስነር ኮንኮርዱ ወደ አለበት ሄደ ። ዶብኪንም ተከተለው ።

ሙሉ ጧት ሥራው ውልፍት አላደረጋቸውም ። ነገር ግን እቀ ትር ላይ የፀሐዩ ሙቀት እጅግ በጣም ከፍተኛ ስለሆነ በእስራኤልም ሆነ በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ሁሉም እንደሚያደርጉት እረፍት አደረጉ ። ከኃይለኛው ፀሐይ ለመጠለል በኮንኮርዱ ክንፍ ጥላ ሥር ተቀመጡ ።

ጭራሮ ለቃቅመው በማቀጣጠል ቆርቆሮ ጥደው ባለፈው የተረ ፉቸውን ምግብ አሞቁ ። ጣፋጭ ወይንና ጭማቂ ጠጡ ። የአውሮፕ ላኑን ሚዛን ለመጠበቅ ልዩ ልዩ የእስራኤል ምግብ ዓይነቶች ጭነው ስለነበር ለጊዜው የጐላ ችግር አላጋጠማቸውም ። ሆኖም ከባዱ ሥራ የምግብ ፍላጐታቸውን አባብሶታል ።

ያእኮቭ ሌይበር የምግብ ሐላፊ ሆኖ እንዲሠራ በሆስነር ተሾሞ ስለነበር አያያዙ ደህና ይመስላል ። ሆስነር በትንሹ ሰውዬ ትከሻ ላይ እጁን ጣል አድርጐ “ ሁኔታው እምን ላይ ነው ፣ አስተናጋጅ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ሌይበር ራሱን አስገድዶ ፈገግ በማለት “ ለአንድ ቀን እንደ ንጉሦች ልንበላና ልንጠጣ እንችላለን ” አለው ።

“ ምን ይኖርሃል ፣ እንበል ለሁለት ተጨማሪ ቀኖች ? ”

“ ልንራብና ልንጠማ እንችላለን . . . ግን እንኖራለን ። ”

“ ለሦስት ቀኖችስ ? ”

“ በጣም እንጠማለን ። ”

ሆስነር ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። የጉልበት ሥራውና የፀሐዩ ኃይለኛነት እንደዚሁ ከቀጠለ ከሰዎቹ ብዙ ላብ ስለሚወጣ የውሃ ጥሙ ችግር በሚቀጥሉት ሦስት ቀኖች ውስጥ እስከፊ ሁኔታ ላይ ይደርሳል ። ምናልባት ይህ ችግር በጣም ቀድሞ ሊደርስ ይችላል ። የማንኛውም ሰው ሃሳብ በውሃ ላይ ስለሚያተኵር ከዚያ በኋላ በትክክል ሊያስብ

የሚችል አይኖርም ይሆናል ። የመከላከያው ሥራ ጠንካራ ቢሆንም ውሃ አለማግኘቱ እባስ አደጋ ላይ ይጥላል ። በዚህ ምክንያት ስንት ምሽጐች ድል ተመተዋል ? ሰዎች ያለ ምግብ ለሳምንታት መኖር ስለ ሚችሉ ችግሩ ምግብ አልነበረም ።

" የአለውን ውሃ በጥንቃቄ ለክቼአለሁ ፤ ለአንድ ሰው በቀን ግማሽ ሊትር ሊሰጥ ይችላል " ብሎ ሌይበር ነገረው ።

" በቂ አይሆንም ። "

" እንደዚህ አይደለም ጌታዬ " ብሎ ወደ መሬት አጐንብሶ የተከመረውን አፈር በእግሩ ገፋ አድርጐ " ውሃ ቆፍረን ማውጣት እንችላለን " አለው ።

ዶብኪን በጐጆው አጠገብ ስለነበር ሆስነር ጠርቶት " ይህ እውነት ነው ወይስ አፈ.ታሪክ ነው ? " ብሎ ጠየቀው

" እርግጠኛ ነኝ ፤ ነው ። በአቧራና በናዳ የተደፈነ ምሽግ ነው ?" ብሎ ቀረብ ከአለ በኋላ " ለምንድን ነው ? " ብሎ ጠየቀው ።

" የውሃ ጉድጓድ መቆፈር እፈልጋለሁ " አለው ሆስነር ።

ዶብኪን ራሱን በአሉታ ነቅንቆ " በጣም ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች በውስጡ ታገኝ ይሆናል ። ውሃ ግን አታገኝም ። ውሃ ለማግኘት በኤፍራጥስ ትይዩ እስኪ ሆን ድረስ መቆፈር አለብህ " ብሎ ወደ ሆስነርና ሌይበር መጥቶ " አንድ ቡድን ወደ ወንዙ ለምን አትልኩም ? " ብሎ ጠየቃቸው ።

ሆስነር ራሱን በአሉታ ነቅንቆ " እንደምታውቀው ጠላቶቻችን ዘብ ጠባቂዎች አሏቸው " አለው ።

" ዛሬ ማታ በወንዙ አጠገብ ያለውን ዘቅዛቃ ቦታ ከአልውጉ እኔ የቡድኑ መሪ ሆኜ እሄዳለሁ ። "

" ዛሬ ማታ ከእንግዳ ማረፊያው ቤት የስልክ ጥሪ ለማድረግ ትሄዳለህ ። "

ዶብኪን ስቆ " የዚህ አገር ሳንቲም የለኝም " አለው ።

ሆስነር የፈገግታ መልስ ሰጠው ።

ዶብኪን በመጀመሪያ ወደ መሬቱ ቀጥሎም ከበታቻቸው ወደ አለው የኤፍራጥስ ወንዝ ተመለከተ ። " ጭቃውንና ዝልግልጉን ነገር እያቀላቀሉ የእንጨት ቅርጽ አሲዘው ከሠሩ በኋላ በፀሐይ ላይ ሊያስቀምጡት ይችላሉ " አለው ። " ጡቦቹ በፀሐይ ከደረቁ በኋላ ከኤፍራጥስ የሚያገኙትን ዝልግልግ በሸክላው ላይ በማድረግ የአንበሶች ወይም የሚፈልጉአቸውን የማምለኪያ ስዕሎች መቅረጽ ይችላሉ ። ንጉሦቹም በጡቦቹ ላይ ናቡከደነጾር የባቢሎን ንጉሥ ፤ የናቢፓላስር ልጅ

የባቢሎን ንጉሥ ብለው ሊቀርጹባቸው ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜም እጡ ቦቹን በእሳት ደጋግመው በማቃጠል ቀይ፣ሰማያዊ፣ ቢጫና አረንጓዴ ያ ደርጓቸዋል ። ሰው እስከ አሁን ያያቸውን እጅግ በጣም ውብና በቀለም ያሸበረቁ ከተሞች ገንብተዋል ። ” ዶብኪን ቡናማ የሆነውን የተቆለለ አቧራ በእግሩ እረገጥ ከአደረገ በኋላ ጥቂት እርምጃዎች ተራመደ ። እልቆ የሌለውን የጭቃ ሜዳ አቋርጦ ወደ ምዕራብ ሲመለከት በአድ ማሱ ላይ ቀይና ቢጫ ቀለም አብርታ በማዘቅዘቅ ላይ ያለችውን ጀን በር ተመለከተ ። “ እስራኤልን በቁጥጥራቸው ሥር ከአዋሉ በኋላ እስ ራኤሎችን በባቢሎን ወንዝ አጠገብ እንዲኖሩ ወሰዱአቸው ። ቦታ ውም በትክክል ይህ ነበር፤ ያዕቆብ ። ይሁዳዊው እዚህ ቆሞ የፐርሻው ንጉሥ ሳይፐረስ እንዳይወጋው ለመከላከል ይህ ምሽግ ተጠናክሮ እን ዲሠራ አደረገ ። ይህም ከ2500 ዓመት በፊት መሆኑ ነው ። ይሁን እንጂ ይህን አገር ሳይፐረስ ወግቶ በቁጥጥሩ ሥር ከአደረገ በኋላ የመጀመ ሪያ ሥራው አይሁዳውያንን እንዲሄዱ መፍቀድ ነበር ። ይህን ያደረ ገው ለምን ይሆን ? ማን ያውቃል ? ተመልሰው ወደ እስራኤል ሄዱ ። ኢየሩሳሌም ፈርሶ አገኙት ። ግን አንጡራ ሃብታቸው ስለነበረ ወደ እርሱ ተመልሰው ሄዱ ። ዋናው ቁም ነገርም ይኸው ነበር ። ” አሻ ቅቦ ከተመለከተ በኋላ ከቀን ሕልሙ የነቃ መሰለ ። “ ለእኛ ግን በጣም ተፈላጊው ነገር አይሁዳውያኖቹ በሙሉ ተመልሰው አልሄዱም ።”

“ ምን ማለትህ ነው ? ”

“ ተማርከው የነበሩ ይሁዳዎች አሁንም በባቢሎን ወንዝ አጠ ገብ ሊኖሩ ይችላሉ ። ”

“ እርግጠኛ ነህ ? ” ብሎ ሆስነር ጠየቀው ።

ሌይበር በዶብኪን አነጋገር ትንሽ የተደናገረው መሰለ ። ትንሽ ሜትሮች እራቅ ብሎ በተመስጦ አዳመጠ ።

“ የምናገረው ከምሬ ነው ” ብሎ መልስ ሰጠው ። “ በኢራቅ መንግሥት ወደ ባግዳድ ከአልተወሰዱ በስተቀር የምናገረው ስለ ኢራ ቃዊ ይሁዶች ሲሆን ቁጥራቸውም አምስት መቶ ያህል ነው ። ” እነእ ርሱን ከዚህ መልሶ ለመውሰድ እየሞከረ ነበር ። በሰላሙ ውይይት ላይም ከሚነሱት ነጥቦች አንዱ ይህ ነበር ። ”

“ አሁንም እዚህ አሉ ብለህ ታስባለህ ? ”

“ ለ2500 ዓመታት እዚህ ኖረዋል ። አሁንም እዚህ ይኖራሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን ። ዋና የመኖሪያ መንደራቸው ከኤፍራጥስ ዳርቻ ፊት ለፊት በሚገኝ ኡማ በሚባል ቦታ ነው ። ይህም ወንዙን

ተከትሎ ሁለት ኪሎ ሜትር ተሄዶ ነው ። ከአየነው ከዌሪሽ ከተባለው የአረብ መንደር በስተሰሜን በኩል ነው ። ”

“ ይረዱን ይመስልሃል ? ”

“ አህ ! ጥያቄው ያ ነው ። አይሁዳዊ ምንድን ነው ? አይሁዳዊ ማነው ? የእነዚህ አይሁዳውያን አያቶች በዚህ ኃጢአት በመላበት በባ ቢሎን ውስጥ ለመኖር ለምን መረጡ ? ማን ያውቃል ? ከዚህ ሁሉ ዓመ ታት በኋላ ከሃይማኖታቸው ግንድ ተቋርጠው አይሁዳዊነታቸውን ጠብቀው ኖረዋል ። እስከዚህ ድረስ እናውቃለን ። ምናልባት ይናገሩ እንደሆን . . . ምን ዓይነት ዕብራይስጥ እንደሚናገሩ እግዜር ያው ቃል ። ነገር ግን ይህን ያውቃሉ ” ብሎ ከኮቱ ኪስ የዳዊትን የብር ኮከብ አወጣ ።

ሌይበር “ እዚህ መኖራችንን ያውቁ እንደሆነ እገረማለሁ ” አላ ቸው ።

ሆስነር እጁን በሌይበር ትከሻ ላይ ጣል አድርጎ “ ከእስራኤልና ከኢራቅ መንግሥታት በስተቀር እዚህ መሆናችንን ሁሉም እንደሚያ ውቅ እርግጠኛ ሁን ” ከአለው በኋላ የሌይበርን ትከሻ ጠብጥቦ “በቅ ርብ ጊዜ ግን ያገኙናል ። አሁን አንተ ይህን ቦታ አንድ በአንድ ጭረህ በቂ ስንቅ ማግኘት አለብህ ” አለው ።

ሌይበር ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ ሄደ ።

“ ዛሬ ጧት እንደ አየሁት ከሆነ ብቻየን የኢሽታርን በር ዛሬ ማታ አገኘዋለሁ ብየ አላስብም ። መሬቱ ወጣ ገባና ያልተለመደ እንደዚ ሁም በየአለበት ምልክት የማይታይባቸው አያሌ ጉድጓዶች የሞሉበት ከመሆኑም በላይ በየማለፊያው ጠባቂ ዘቦች እንደሚኖሩ እርግጠኛ ነኝ ” ብሎ ዶብኪን ነገረው ።

“ ታዲያ ምን ሃሳብ ታቀርባለህ ? ”

“ ከኤፍራጥስ ማዶ ያለው መሬት ሜዳ ነው ። ምናልባትም ፍል ስጥኤማውያን በዚያ ላይ ሊኖሩ ይችላሉ። ዛሬ ማታ እዚያ እወርዳለሁ ። ከፈለግህ ውሃ የሚያመጣው ቡድን አብሮኝ ሊሄድ ይችላል ። ከኤፍ ራጥስ ወንዝ ውሃ ቀድተው ያመጣሉ — ወንዙን በዋና አቋርጬ እሄ ዳለሁ ። ”

“ ዘቦቹ ” አለው ሆስነር ።

ዶብኪን ትከሻውን ከፍና ዝቅ አደረገ ። “ በተራራው ምሥራቃዊ ጐን ተኩስ ቢጀመር በወንዙ ዳርቻ ያሉት ዘቦች በብቃት አይሰሙትም ፤ ቢሰሙም አያጨንቁበትም ። ከሌሊቱ በስምንት ወይም በዘጠኝ ሰዓት ብርድና ድካም ይሰማቸዋል ። የጦርነቱ ተካፋይ ባለመሆናቸው ለኮከቦቻቸው ምሥጋና ያቀርባሉ ። ስለዚህ ያለ ችግር አልፋለሁ ”

ሆስነር ግራ የተጋባ መሰለ ። “ ወንዙን አቋርጠህ ብትሻገርና ወደ አይሁዳውያኑ መንደር ብትደርስ በሚቀጥለው ምን እርምጃ ትወስዳለህ ? እዚያ ለማግኘት የምትጠብቀው ተስፋ ምንድን ነው ? ”

ዶብኪን ምን እንደሚፈልግ አላወቀውም ። ምናልባት ለእርሻ በጋራ የሚጠቀሙበት የተሸከርካሪ ዓይነት ቢኖራቸው እንኳን መንገዶቹ የሚያስኬዱ አይደሉም ። በእርግጥ ስልክም አይኖርም ። በእህያ ተጉዞ ባግዳድ ለመግባት ደግሞ ብዙ ቀኖች ይፈጃል ። ሂላ ለመድረስ ይቻላል ። ነገር ግን ወንዙን እንደገና ማቋረጥ ያስፈልጋል ። ምናልባትም በጀልባ — በሞተር ጀልባ ባግዳድ ለመድረስ ከ5 እስከ 6 ሰዓት ይፈጃል ። ሞተር በሌለው ጀልባ ወደ ሂላ ለመውረድ ከአንድ ሰዓት ያነሰ ጊዜ ይፈጃል ። ከዚያስ በኋላ ? ሀሎ የእስራኤል የጦር ሠራዊት ጄኔራል ዶብኪን ነኝ ። እና . . .

“ ፈገግ እንድትል ያደረገኸ ምንድን ነው ? ” ብሎ ሆስነር ጠየቀው ።

“ የግል ቀልድ ነው ። ስማኝ ፤ ስለዚህ መንደር የማስታውሰው ነገር አልነበረም ። ልክ ባቢሎን መድረሳችንን እንደ አወቅሁ ስለመንደሩ አሰብኩ ። ግን እነዚህን ሰዎች በዚህ ጉዳይ ውስጥ ልናስገባቸው እንፈልጋለን ? በቂ የሆኑ ችግሮች የሉባቸውም ? ”

“ ከእኛ የበለጠ የለባቸውም ” አለው ሆስነር ። “ ለወደፊቱም እንደዚህ ያለ ሃሳብ እንዳታሳድር እመከርሃለሁ ፣ ጄኔራል ። እኔ እንደሚሰማኝ ሁለት ምርጫዎች አሉህ — በኢሽታር በር ያለው የእንግዶች ማረፊያ ቤት ወይም በኡማ የአይሁዳውያን መንደር — ”

ዶብኪን ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። ግን በኤፍራጥስ ወንዝ ዳርቻ ጽዳት በሌለው ከጭቃ በተሠሩ ደሳሳ ጐጆዎች ውስጥ ነዋሪ የሆኑት ኋላ ቀር አይሁዳውያን ዘንድ በመሄድ ዝምድናውን ቆጥሮ እርዳታ መጠየቅ ይቻለው ይሆን ? ይሳካልኛል ብሎ አሰበ ። ግን ሪሽ ነገሩን ቢደርስበት በእነዚያ ጉስቋላ ምስኪኖች ላይ የበቀል እርምጃ ይወስድባቸው ይሆን ? በእርግጥ ያደርጋል ። ታዲያ አማራጮቹ ምንድን ናቸው ? ምንም አማራጭ አልነበረም ። “ ዛሬ ማታ በኡማ በኩል እሞክራለሁ ። ”

" መልካም ነው ፣ የእኔ ምርጫ ወደ እንግዳ ማረፊያው ቤት እን ድትሄድ ቢሆንም ፣ ውሳኔው ግን የአንተ ነው " ብሎት ከዶብኪን ጋር ወደ እረኛው ጐጆ ሄዱ ። በመንገድ ላይ እያሉ ሆስነር ወደ ዶብኪን ዞሮ " ጠመንጃ ልሰጥህ አልችልም " አለው ።

" እሺ ። "

ሳይነጋገሩ ጥቂት እርምጃዎች እንደሄዱ ፣ ሆስነር ጉሮሮውን አፍ ታትቶ " የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ጠይቄው — " ሲል ዶብኪን አቋ ርጦት " አዎን ፣ መድሃኒቱን አግኝቻለሁ ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ረዳት መኰንን ፔሌድ መጥፎ የልብ በሽታ ስለአለው ለአንድ ወር የሚሆን ይዞ ስለመጣ ፣ ከእርሱ ለሁለት ሳምንቶች የሚጠቀምበትን ወስጃለሁ " አለው ።

" የወሰድከው እንደሚበቃህ ተስፋ አደርጋለሁ ። "

" እኔም እንደዚሁ ። "

በርግ ከሁለት ሴት አስተናጋጆች ከራሔል ባኡምና ከቤተ አብ ራምስ ጋር ሆኖ ከጐጆው ወጥቶ መጣ ። ሰማያዊ ዩኒፎርማቸው በላ ብና ደም በሚመስል ቀለም ተበክሎአል ። ለሆስነር ፍርሃትና ጺያፍ ያለበት ሁኔታ በማሳየት በአጠገቡ አለፉ ።

በርግ ትካሻውን ነቅንቅ አድርጐ " ለእኔም የእዚያው ዓይነት መልክ አሳይተው ነው ያለፉት ። ቁስለኛው ሙሐመድ ምሕረት አድ ርጌለት እስኪሄድ ድረስ ደህና እየሠሩ ነበሩ ። የእኛን ፍላጐት በት ክክል የሚያውቅልን የለም ፣ ያዕቆብ " አለው ።

" ሌላ የተናገረው ነገር አለ ? " ብሎ ሆስነር ጠየቀው ።

በርግ የፒፓውን ጫፍ እያኘከ " ጥቂት ነገሮች " አለው ። ሌየሩ በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ ወደ ምዕራብ ሲያመራ በርግ ተመልክቶ "ምና ልባት በዚያ በኩል አዳፍኔና ቦምብ በማዘጋጀት የጦር ሠፈር ይቆረቁር ይሆን ? " አለው ።

ሆስነር ሌየሩ ወደ ፀሐይ መጥለቂያ ገብቶ ሲጠፋ አይቶ " እንደ ዚያ ከአደረገ ዛሬ ማታ የከፋ ነገር ያጋጥመን ይሆናል " አለው ።

ዶብኪን ሲጋራውን አቀጣጥሎ " በአካባቢው ስለማልኖር ደስ ብሎኛል " አለው ።

" ልትሄድ ነው ? " ብሎ በርግ ጠየቀው ።

" አዎን ፣ ዛሬ ማታ እናንተ ከጥይት ጋር ተፋጣችሁ በምትታገሉበት ጊዜ እኔ ፍራፍሬና የተጠበሰ የበግ ሥጋ እየበላሁ እዝናናለሁ " አለው ።

" ፀሐዩ በጣም የጐዳህ ትመስላለህ ጀኔራል ። "

ዶብኪን ለበርግ ስለይሁዳዊው መንደር ነገረው ።

በርግ ሰምቶ ራሱን በአዎንታ ከነቀነቀ በኋላ " ስለቀልዱ ይቅርታ አድርግልኝ ። አባባሉም ትክክል አይመስለኝም ቤን ። ስለዚህ በመጀመሪያው ዕቅድህ ላይ አተኩር " አለው ።

" እኔም ያለኝ የዚያ ዓይነት ስሜት ነው ። "

በርግ ትከሻውን ሰበቀ ። ሁለቱም መንገድ ራስን አሳልፎ መስዋዕት መሆን ነው ። " በነገራችን ላይ ሙሐመድ እንደሚለው የሪሽ የመቶ አለቃ የሆነው ሳሌም ሀማዲ የግብረ ሰዶም ባሕርይ አለው ። በዚያ ዓይነት ማደግ ይህን የመሰለውን ክስተት ሊያስከትል ይችላል ። "

" ማን ግድ አለው ? " አለው ሆስነር ።

" የመናገሪያችንን የመጨረሻ የድምጽ ከፍታ በመጠቀም ይህንኑ ስለምናሰራጭ ሳላሜ ሀማዲ ግድ ይኖረዋል ። "

ሆስነር በነገሩ ስቆ " የመናገሪያችን መዛሪያ ድምጽ ዝቅተኛ ስለሆነ አይሰማውም " አለው ።

" ለመሆኑ ከመናገሪያው መዛሪያ ጋር በማያያዝ ገመዱ እስከ ምሽግ ክልላችን ድረስ ተዘረጋ ይሆን ? "

" ተዘርግቷል " አለው ዶብኪን ።

ሆስነር በኮንኮርዱ ክንፍ ሥር ወደ አለው ጥላ ሄደ ። ከአፈርና ከእጡብ የተሠራው መወጣጫ አልቋል ። በጀርባው ተደግፎ እንደቆመ ሞቃት አየር ተሰማው ። የኮንኮርዱ የአየር መለኪያ መሳሪያ ቀኑን ሙሉ በፍጥነት እየቀነሰ መምጣቱን ቢክር ሪፖርት አድርጓል ። " የምሥራቅን ነፋስ ስም የሚያውቅ አለ ? "

" ሼርጂ ይባላል ። ተሰማህ እንዴ ? " ብሎ ዶብኪን ጠየቀው ።

" የተሰማኝ መሰለኝ ። "

“ በጣም መጥፎ ነው ። በእስራኤል ውስጥ ከአለው ሙቅ አየር (ሀማሲን) በጣም የከፋ ነው ።

“ ለምን ? ”

“ በመጀመሪያ ደረጃ በጣም ይሞቃል ፤ በሁለተኛ ደረጃ እዚህ ያለው አሸዋና አቧራ ነው ። አቧራውን ስለሚቀሰቅሰው ያፍናል ። በተለይ በእንደዚህ ባለ ተራራ ላይ ሊገድልም ይችላል ” አለው ዶብኪን ። ሆስነር ወደ ተራራዎቹ አሻግሮ ሲመለከት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አቧራው ከአሁኑ መቆለል ጀምሯል ። አቧራው እንደ አዟሪት እየሆነ በመነሳት እነእርሱ ወደ አሉበት ወደ ምዕራብ አመራ ።

ዶብኪንም እንደሆስነር ተመልክቶ “ ከወታደራዊ አስተሳሰብ በኩል ሲታይ አቧራ የቀላቀለው ነፋስ የበለጠ ለማን እንደሚጠቅም አላውቅም ” አለው ።

“ በቂ ችግሮች አሉን ። ያለሌላ ተጨማሪ መሥራት እችላለሁ ” ብሎ ሆስነር ወደ በርግ ከተመለከተ በኋላ “ ከእስረኛው ጋር ጨርሰህ እንደሆነ ልናሰናብተው እንችላለን ” አለው ።

“ እንደሚመስለኝ ይሒድ ማለትህ ነው ። ”

“ አዎን ።”

አባባሉን ዶብኪን ተቃወመ ።

ሆስነር ሲጋራ ሰጠው ። “ አንድ ወይም ሁለት ታሪክ ልንገርህ” ብሎት ያልደረቀውን የመወጣጫ ግድግዳ ተደገፈ ። “ በአስራሁለተኛው መቶ ዓመት ሚላን በተከበበት ጊዜ ነዋሪዎቹ የእህል አቅማዳዎቻቸውን አሸዋ ሞልተው ለመከላከያ ማጠናከሪያ ተጠቀሙባቸው ። በጀርመን ንጉሠ ነገሥት ባርበሮሳ የሚታዘዙት ከባቢዎች አቅማዳዎቹ በእህል የተሞሉ መስለዋቸው ተስፋ ቆረጡ ። በእርግጥ ከተማው እየተራበ ነበር ። ባርባሮሳ ግን አላወቀም ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ባርባሮሳ የኢጣሊያ ከተማ የነበረችውን አሌሳንድሪያን ከበበ ፤ አንድ ገበሬ ላሙን ሳር ለማብላት ከከተማው ውጭ ይዞ ሂዶ እንዳለ በባርባሮሳ ወታደሮች ተማረከ ። ላምዋን ለምግባቸው በአረዷት ጊዜ የላምዋ ሆድ በጥሩ እህል ተሞልቶ አገኙት ። በከተማው ውስጥ የድርቆሽና የገለባ እጥረት ቢኖርም ለከብቶች ጭምር ብዙ እህል እንዳለ ገበሬው ገለጸላቸው ። ባርባሮሳ እንደገና ተስፋ ቆርጦ ከበባውን አቆመ ። በእርግጥ አሌሳንድሪያዎቹ በረሃብ እየተሰቃዩ ነበሩ ። ገበሬውና ላሟ የተላኩት ግን ለጠላት ማታለያ የአደረጉት ዘዴ ነበር ።

“ አንድ ነጥብ ላይ ለመድረስ እየሞከርክ ነው ” አለው በርግ ።

" አዎን ፣ በመጀመሪያ ትንሽ ፓርቲ አድርገን መጠነኛ ዳንስና ዘፈን እንጫዎት ። ጥቂቶቹ የበሉና የጠጡ መ(ሰ)ሉ ። ያሉትን መሳሪያ ዎች ሁሉ በእረኛው ጐጆ ውስጥ አስቀመጡ ። መሣሪያዎቹ የጐረሱ እንዲመስሉ ትርፍ በሆኑ ካርታዎች ውስጥ አንዳንድ ጥይት አስቀ መጡ። ልዩ ልዩ የጠላት ማታለያ ዘዴዎች ፈጠሩ ። በእረፍትና በመዝና ናት ላይ ያለ ሦስተኛ ብረት ለበስ ዲቪዝዮን ያላቸው አስመሰሉ ። ከዚ ህ ሁሉ በኋላ ሙሐመድ አሳድ ተለቀቀ ። "

ዶብኪን በሃሳብ ተመሰጠ ። " ለሪሻና ለመኰንኖቹ ሊመስል ይችላል ። አሸባሎቹን ግን እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል " ብሎ ወደበርግ ተመለከተ ። " ለምን ? እኔ በእርሱ ሃሳብ እስማማለሁ " አለው በርግ ።

ሦስቱ ሰዎች ወደ ጐጆው ሄዱ ። ካፕላን አሁንም በልቡ ተደፍቶ ተኝቷል ። ሆኖም ደህና ይመስላል ። ሌሎች የመቁሰል አድጋ የደረ ሰባቸው አራቱ ማለትም ጀሹዋ ሩቢን ጭምር ካርታ ይጫወቱ ነበር ። ጸሐፊዋ ሩት ማንዴል ግን በብርድ ልብስ ተጠቅልላለች ። ትኩሳትም ያላት ትመስላለች ። እስረኛው በርግን የፈራው መሰለ ። ሆስነር እስ ረኛው አፍንጫውን ክፉኛ መመታቱን አየ ። ሰውየውን ከቁስለኞቹ ጋር አብሮ የማስቀመጡን ሃሳብ ሆስነር አልወደደውም ። ችግሩ ግን ከኮንኮርዱ በስተቀር የነበረው ከፍተኛ መጠለያ ጐጆው ነበር ። ኮን ኮርዱ ደግሞ በነበረው ኃይለኛ ፀሐይ ምክንያት እንደ ጋለ ብረት ምጣድ ሆኖአል ። ቁስለኞቹ በእስረኛው ላይ ዓይኖቻቸውን በመጣል ይጠባ በቁት ነበር ። በአጠቃላይ የደረሰው አደጋ ቀላል ስለነበረ ሙሐመድ አሳድ ይህንንም ሄዶ ሊናገር ይችላል ።

የቤት አስተናጋጆቹ ተመልሰው ስለመጡ ቤተ አብራምስ የካ ፕላንን ቁስል ፈታ አጸዳችለት ። መግል መያዝ በመጀመሩ በጣም ሸ ቷል ። ከጡብ የተሠራው ጐጆ ውስጡ በላብና በሌሎችም ሽታዎች ተሞልቷል ። ቤተ አብራምስ አፉን በከፈተው ቁስል ላይ ቢጫ ቀለም ያለው መድኃኒት አደረገችለት ።

" ምንድን ነው ? " ብሎ ሆስነር ጠየቃት ።

ቤተ አብራምስ ቀና ብላ ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ከተመለከተ ችው በኋላ " የአገር ባሕል መድኃኒት ነው " አለችው ።

" እንዴት አወቅሽው ? "

" በአንድ ወታደራዊ የሕክምና ክፍል ስሠራ በነበረበት ጊዜ ከአንድ የሕክምና መጽሔት ውስጥ አንብቤአለሁ " ብላ እየነገረችው

ቀስ አድርጋ አፉን በከፈተው ቁስል ውስጥ ቀበረችው ። ፍሬው ቢጫ የሚመስል ቀለም ያለው ድቡልቡልና ለስላሳ ነበር ። የሚገኘውም ከሐ ረግ መሰል ተክሎች ሲሆን በአረሁ ውስጥ ይገኛል ።“ይህን መድኃኒት በእያንዳንዱ ቁስል ላይ እያደረግሁ ነው ። የተረፈ አልኮል የለም ” ብላ ቁስሉን መልሳ ከአሰረች በኋላ ሄደች ።

ሆስነር ወደ ካፕላን ዞሮ “ በቂጥህ ላይ የተመታኸው እንዴት ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ካፕላን እንደምንም ብሎ ከሳቀ በኋላ “ እነዚህ ሁለት አስተናጋ ጆች ያን ቢጫ ቀለም ያለውን ፍሬ አደረጉልኝ ። በኤል አል ብረሩ ፣ እንደ ንጉሥ ሰሎሞን እንክብካቤ ይደረግላችኋል፣የሚሉት ቀልዳቸው አለመሆኑን ማወቅ ችየአለሁ ” አለው ።

ሆስነር ፈገግታ ሰጠው ። ካፕላን ስለ ማቲ ያዲን አስታወሰው ። ካፕለን የተሻለው መሆኑን ማወቅ አለበት ። “ ያቺ ትንሽ ልጅ ቤተ አብራምስ የሕክምና ሥርዓት ባልተከተለ መንገድ የቂጥህን ቁስል አከመችልህ ። ወደ ሎድ በምትመለስበት ጊዜ ይህን በአዕምሮህ ውስጥ እንድታስታውስ ። ”

“ ዛሬ ማታም አልዘነጋውም ። ”

ቼይም ታሚር በአለፈው ማታ በተደረገው የአጸፋ ጦርነት በኃ ይል መቁሰሉንና አሁን ለጥ ብሎ መተኛቱን ሆስነር ተመለከተ ።

ሆስነር ጠባቡን ክፍል አቋርጦ ቀላል የመቁሰል አደጋ ወደ ደረ ሰባቸውና ካርታ ወደሚጫወቱት ሄደ ። ለጆሹዋ ሩቢን “ ንክ እንደነ በርክ ፈጽመህ ነግረኸኝ አታውቅም ” አለው ሆስነር ።

ሩቢን የሃያ ዓመት ጐልማሳና ጸጉረ ቀይ ነው ። ካርታውን ሰብ ስቦ ቀና በማለት ተመለከተው ። “ ጠይቀኸኝ ስለማታውቅ ነበር ። ለመሆኑ ኡዚዬን የያዘው ማን ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ በአመጣልህ ጊዜ በካርታው ውስጥ ቀርተው የነበሩት ጥይ ቶች ሦስት ብቻ ስለነበሩ ከአሁን በኋላ አንጠቀምበትም ። ”

“ አምጣልኝ ፣ ያስፈልገኛል ። በአጋጣሚ ወደዚህ መድረስ ቢ ችሉ ቀድሞ ወደዚህ በር የሚመጣውን ሰው ራሱን እበትነዋለሁ ። ”

“እሺ፣አመጣልሃለሁ ”ብሎ እንደገና መጫወት የጀመሩትን ሰዎች ተመለከታቸው ። ሰዎቹ ተራና ሲቪሎች ነበሩ።ትናንትና ማታ በጣም ተደናግጠው የነበሩ ፣ በአሁኑ ጊዜ ግን በደህና ሁኔታ ላይ የሚገኙ በመ ሆናቸው በካርታው ጨዋታ ይጨቃጨቃሉ ። ሚሪያም በርንስቴይን

ስለዚያ ምን ታስብ ይሆን ? ጥሩ ሰዎች ገዳዮች ፥ ገዳዮች ደግሞ ጥሩ ሰዎች መሆናቸው ገብቷት ይሆን ? እንደ ይስሐቅ በርግ ያለ ሰው ፈገግታ የሚሰጥና እየተሹለከለከ ሄዶ በፒፓው ሰው የሚማርክ ፥ በኋላም የቆሰለውን እስረኛ አፍንጫ - የሚሠብርና አሁንም ቢሆን መልካም ሰው መሆኑ ገብቷት ይሆን ? የመጨረሻው እርምጃ ሕይወትን ማትረፍ ነበር ። ለመኖር መደረግ ያለበት በሕይወት ለመኖር ከሆነ መሆን ያለበት ተደርጓል ።

## — 19 —

ፀሐይዋ ከኮንኮርዱ ጋር ትንጸባረቅ ስለነበረ ከቀድሞው በበለጠ የምትሞቅ መሰለች ። ሆስነርና በርግ በመገነጣጠል ላይ የነበረው የአውሮፕላን ጅራት እንዳያብረቀርቅባቸው ዓይኖቻቸውን ከልለው ቆመዋል ። ሆስነር በኮንኮርዱ ጅራት ውስጥ የነበረው ዝግ ክፍል ቀደም ብሎ እንዲፈተሽ አለማሰቡ አስገርሞታል ። አውሮፕላኑ በኤክስሬይ በታየበት ጊዜ በውስጡ የነበረውን ጥላ የሚመስል ነገር ከመጤፍ የቆጠረው አንድም ሰው አልነበረም ። ስለዚያ ምንነት ለምን አላሰበም ነበር ?

ሆስነር ስለዚህ ጉዳይ እንደጥፋተኛ ያልቆጠረው አህመድ ሪሽን ነበር ። ሪሽ መሆን ይገባዋል ያለውን ሠርቷል ። ነገር ግን ያ እንዳይፈጸም መቆጣጠርና መግታት የሆስነር ሥራ ነበር ። ሆስነር ማንኛውም ነገር ትክክል እንዲሆን ቢሻም በዚህ በኩል አህመድ ሪሽ በከፍተኛ ብልጫ እንደ አስከነዳው ተገነዘበ ። ባለው የእምነት ኩራት ምክንያት እነዚህን ሰዎች ወደ ሞት አፋፍ እየመራቸው ነበር ። አልነበረም ? ለብዙ ዓመታት በእስራኤሎች ላይ የተፈጸመውን እየተከተለ ነበር ። በዚህ ምክንያት ለሽብር ፈጣሪዎች መንበርከክ ፥ መስገድ ወይም ከእነርሱ ጋር መደራደር የሚባል ነገር አይፈልግም ። ይህ ሃሳብ የራሱ ብቻ ባይሆንም የሚስማሙና የሚያምንበት ነበር ። ድርጊቱ ቆጠቆጠው ፥ ቆጨውም ። ወደበርግ ዞሮ " ከዚህ የበለጠ ሌላ አስቸኳይ ነገር አለ ? " ብሎ ጠየቀው ።

በርግ ከኮንኮርዱ ጅራት ፊቱን አዙሮ ከ200 ሜትር እርቀት ላይ ወደአለው ዝቅ ያለ ቦታ አመለከተ ። አብደል ማጂድ ጃባሪና ኢብራሂም አሊ አሪፍ እንደ ቦይ አድርገው የዓይነምድር ጉድጓድ ሲቆፍሩ አየአቸው። መቆፈሪያቸው ሌሎቹ እንደአደረጉት ከቁርጥራጭ አሉሚኒየም የተሠራ ነበር ። ያለሰለሰውና ሸካራው አሉሚኒየም እንዳይጐዳቸው እጃቸውን በጨርቅ ጠቅልለዋል።"ጥያቄ አቀረብኩላቸው" አለው በርግ ።

“ ሁኔታው ስለአስገደደኝ ነው እንጂ ሁለቱም የምክር ቤት አባሎች ስለሆኑ ታማኝነታቸውን መጠራጠር አልነበረብኝም ። በጥያቄው ትንሽ ቅሬታና ቁጣ ተሰምቷቸዋል ። ምናልባት አንተ አለስልሰህ ልትነግራቸው ትችላለህ ። ”

ሆስነር ለትንሽ ጊዜ ወደ አረቦቹ ተመለከተ ። “ በእርግጥ ተመልሰን ብንሄድ ለሠራናቸው ነገሮች ሁላችንም መልስ መስጠት ይኖርብናል ። የለብንም እንዴ ፡ ይስሐቅ ? እነእርሱ በአስፈሪ ሁኔታ ላይ ናቸው ለእነእርሱ መክዳትከአህመድ ሪሽ ጋር ምንም መፍትሄ አይሰጣቸውም ። በዚህ ተራራ ላይ ሪሽን ፈጽመው አይፈልጉትም ። ቢያገኛቸው ግድያ ብቻ ሳይሆን ያሰቃያቸዋል ። አንተም የከዱአቸውን ምን ዓይነት ቅጣት እንደሚሰጡ ታውቃለህ ። ”

በርግ ራሱን በአዎንታ አነቃንቆ “ የሚያሳዝን ነገር ነው ” ብሎ የፒፓውን ቀዳዳ ጐረጐረ ። “ ወዳጅህ በርንስቴይን ስለጀባሪና አሪፍ ታማኝነት ስለተደረገው ጥያቄና ስለእስረኛው የነበረኝን የአጠያየቅ ዘዴ ያጥላላችብኝ በጣም ነው ። ሥራችን ሁሉ በጣም ጭካኔ የተሞላበት መሆኑን ነገረችኝ።በእርግጥ ልክ ልትሆን ትችላለች ። እኛ ግን ይህን ያህል መጥፎ ነው ብለን አናስብም ። እናስባለን እንዴ ያዕቆብ? እርስዋ ግን ታስባለች ። ደም የሚያነቡ ልቦች ዓለምን እንደአለች ለማየት እምቢ የሚሉት ለምንድን ነው ? ” አለው ።

“ መልካም እንደሆነ አድርገው ያዩታል በርግ ። ሁሉን ነገር በወረቀት ላይ አስፍሮ በመሄድ ስለ ዓለም ሰላምና የጦር ቅነሳ ጉዳይ በቀላሉ ተወያይቶ መስመር ማስያዝ ይቻላል የሚል ሃሳብ ያላቸው ሰዎች ከጠላት ጋር በሚደረገው ትግልና ትንቅንቅ በሞራል የበላይነት ማግኘት ጥቅሙ አይታያቸውም ። ”

“ አንተ ግን የእዚያ ዓይነት ሰው አይደለህም ። ለማንኛውም ችግር እየፈጠረችብኝ ስለሆነ አንድ ነገር ማድረግ አለብህ ብየ እገምታለሁ ። ”

“ ምን ዓይነት ? ” ብሎ ወደ በርግ ትኩር አድርጐ ተመለከተ ። በርግም ትኩር አድርጐ በመመልከት “ያ የራስህ ፋንታ ነው” አለው።

ሆስነር መዳፉን በሱሪው ላይ አብሶ “ የሚደረገውን አያለሁ ” አለው ።

ሆስነር በሚሄድበት ጊዜ በደቡብ ጉብታ በኩል የነበረውን ሸለቆ ሊብ አለ ። ዶብኪን አካባቢው ምሽግ እንደነበረና ደቡባዊው ጉብታ ካትማውን እያካለለ በወንዙ ዳርቻ አልፎ በደቡብ በኩል ወደ ካሳር

ቱራራ እንደሚደርስ ተገነዘበ ። የሰሜኑም ቱራራ እንደዚሁ የከተ ማው ምሽግና ክልል እንደነበረ ያስታውቅ ነበር ። ጉብታዎቹ በጣም ዘቅዛቃ ባይሆኑ ኖሮ የአሽባሎቹ መመላለሻ መንገድ ይሆኑ ነበር ። ሆስነር ጉብታዎቹ የተፈጥሮ እንዳልነበሩ አስተውሏል ። ዶብኪን በሃ ሳቡ ውስጥ ምሽጉቹ ቢቆፈሩ የሰው አጽም በብዛት እንደሚገኝባቸው አልተጠራጠርም ።

ሆስነር እንደደረሰ ሁለቱ አረቦች ቀና ብለው ተመለከቱት ።"ትና ንትና ማታ ባቢሎንን ለመከላከል ስለአደረግኸው አኩሪ ውጤት የምሥራች ለማለት ዕድል አላገኘሁም " አለው ጃባሪ ።

" ጥሩ ቅንብር ነበር " አለው ሆስነር ። አሪፍ ራቁት ደረቱን ገልብጦ እያለከለከ " እኔም የምሥራች ልልህ ፈልጌ ነበር "አለው።

ሆስነር ራሱን በአዎንታ አነቃንቆ ሳይናገር ለትንሽ ጊዜ ከቆየ በኋላ "እናንተን የምጠራጠርበት ምክንያት አለኝን ? ብሎ ጠየቃቸው።

ጃባሪ በጣም ተጠግቶ " የለም " አለው ።

" እንግዳው እውነቱ ይኸው ነው ። በርግ ይቅርታ ሊጠይቃችሁ እንደሚፈልግ አውቃለሁ ። ግን በሥልጠና ጊዜ የወሰደው ትምህርት ይህን እንዲያደርግ አይፈቅድለትም " ብሎ ዙሪያውን ከቃኘ በኋላ " ዛሬ ማታ ለሁለታችሁ የሚሆን በጣም አስፈላጊ የሆነ ሥራ አለኝ" አላቸው ።

" ሠገራ ቤት ከመቆፈር በጣም የባሰ ? " ብሎ አሪፍ ጠየቀው ።

" ይመስለኛል " ብሎ ሆስነር በአላለቀው ሽንት ቤት ጫፍ ላይ በእግሮቹ ቁጢጥ ብሎ ገለጻ ሲያደርግላቸው ተቀምጠው አዳመጡት።

* * *

ዶብኪንና በርግ እንደገና የእረፍት ጊዜ እንዲሆንና ሁሉም የተ ዘጋጀውን ትርዕይት ለእስረኛው እንዲያሳዩ ትዕዛዝ አስተላለፉ ። አምስት ኤኬ -47 ጠመንጃዎችና አስር ያህል ሽጉጦች ትርፍ በማስመ ሰል እንደ አልባሌ በጐጀው ግድግዳ ላይ ተሰቅለዋል ። ጥይቶቹ በቆ ሻሻው ወለል ላይ ተዝረክርከው ተቀምጠዋል ። የፀጥታ ሠራተኛ የሆ ነው ማርከስ ኡዚ አንግቶ መጥቶ ለሩቢን ሰጠው ። እርሱም መሣ ሪያው እንዲታይለት ከአደረገ በኃላ በብርድ ልብሱ ስር አስቀመ ጠው ። ማርከስ ለትንሽ ጊዜ አነጋግሮት ተመልሶ ሄደ ። ካፕላን ንና ሩቢንን ለመጐብኘት ሌላው የፀጥታ ሠራተኛ የሆነው አል ፐርን መጣ ። እርሱም ከፊተኛው ትንሽ አዒራ የለበሰ ኡዞ ይዞ ነበር። ይህ አሁን ይዞት የመጣው ሩቢን በግድግዳው ቀዳዳ ውስጥ አሾልኮ ያሳለፈው ያው የቀድሞው ኡዚ ነበር ።

ብሪን በበኩሉ ኤም - 14 የኮከብ ብርሃን መነጽር ያለውን ጠመንጃ ይዞ መጣ ። ሙሐመድ አሳድ ይህን መሣሪያ በመደነቅ ትኩር አድርጐ አየው ። ብሪን አስተያየቱን ልብ አድርጓል ። በምሥጢር ተደብቆ እንዲያዝና እስረኛውም እንዲያየው ሆስንር አዞ ነበር ። ብሪን በእብራይስጥ ቋንቋ “ ወዳጄ ፣ ይህ ወደ እናንተ ጥይት የምንተ ኩስበት መሣሪያ አይደለም።ሌላ ኦለን ። ስለመሣሪያው ግን ማሰብ አለብህ ” ብሎ ቢነግረውም እስረኛው ቋንቋው አልገባውም ።

አሳድ ለአውሮፕላኑ ተሳፋሪዎች ከተዘጋጀው ምግብ እስኪገ ለማው ድረስ ከበላና ከጠጣ በኋላ በአየው የምግብ ዓይነት በጣም ተደ ነቀ ። ከአስተናጋጆቹ አንደኛዋ በፕላስቲክ ብርጭቆዎች በገፍ ውሃ እየቀዳች ለቁስለኞቹ ሰጠች ። ጆሹዋ ግማሹን ጠጥቶ ቀሪውን በግ ድግዳው ቀዳዳ ውስጥ ወደ ውጭ አፈሰሰው ። ቀደም ብለው ለውሃ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጉ እንደነበረ አሳድ ያስተዋለ ለመሆኑ ፍንጭ አላሳየም ።

አሳድ በሁለት የፀጥታ ሠራተኞች በጃፍና በአልፐርን ተወ ስዶ ዓይኖቹ በጨርቅ ከመሸበባቸው በፊት በጐጆው አጠገብ በተቆ ፈረ ጉድጓድ ውስጥ የተቀመጡ ብዙ ገረዎይናዎች ውሃ ተሞልተው አየ ። በአስተናጋጅ ዳንኤል ጃኮቢ ሌሎችም ሲሞሉ ተመለከተ ። ከመ ኰንን ረዳቶቹ አንድዋ ኤሽር አሮንሰን ከጨርቅ እየተረተረች የከር ገመድ ስትሠራ አያት ።

ኤሸር አሮንሰን ዓይን የሚታሰርበትን ጨርቅ እንድትወረው ርለት አልፐርን ጠየቃት ። እርስዋ ግን በታዘዘችው መሠረት ሆን ብላ መወርወሩን አዘገየችው ። በዚህ ጊዜ በፍጥነት እንድትሰጠው በቁጣ ተናገራት ።

ጃፍ ወደ ምሽጋቸው አሳድን አዙሮ ሲያመለክተው ብዙ የጦር መሣሪያዎች ያየ መሰለው ። ከስብርባሪ ዕቃዎች ተጠረቃቅሞና ቀለም ተቀብቶ ለማስመሰያ የተዘጋጀ ነበር ። እንደዚሁም አሳድ ጥይት ያለባቸው የሚመስሉ ዝናሮች በየአለበት ተሰጥተው ስለአየ እስራ ኤሎቹ ይህን ሁሉ በአውሮፕላን ጭነው በማምጣታቸው ቢያስደን ቀውም አልጠየቀም ። እንዲያያቸው የተዘጋጁትን በጥቂት ሴኮንዶች ውስጥ እንደተመለከተ በዓይኖቹ ላይ በፍጥነት ጨርቅ ጠመጠሙባ ቸው።ከክልላቸው አልፎ በቁልቁለቱ አጋማሽ ላይ እንደደረሰ ዓይኖቹ የታሠሩበትን ጨርቅ ፈተውለት ነጭ መሃረብ በዘንግ ላይ አስረው ሰጡት ። ጃፍ ድምጹ ሳይቀር እግዚአብሔር ለሎጥ ሚስት እንደነገ ራት ዓይነት አድርጐ ወደኋላ ዞሮ እንዳይመለከት አስጠነቀቀው ። አሳድ ቁስለኛ ቢሆንም ያለምንም ችግር ቁልቁለቱን ወረደ ።

ሆስነር ሁሉም በየሥራቸው እንዲሠማሩ አዘዘ ። ትናንትና ማታ የትዕዛዝና የመቆጣጠሪያ ማዕከል እንዲሆን በመረጡት ጉብታ ላይ በርግና ዶብኪን የሥራውን ሒደት ሲያዩ አገኛቸው ። ይህ ጉብታ ቀድሞ ግዙፍ የመመልከቻ ማማ የነበረና በአሁኑ ጊዜ ግን በአሸዋና በአቧራ የተቀበረ ነበር ። “ የሚቀጥለው ቀደምትነት የሚሰጠው ሥራ ምንድን ነው ? ” ብሎ ጠየቃቸው ።

በርግ “ ከቤከር ጋር እንደገና እንነጋገር ” ብሎ ሃሳብ አቀረበላ ቸው ።

ወደ ኮንኮርዱ ሄደው ለመወጣጫ የተሠራውን አዩ ። ካን በላ ብና በዘይት ተጨማልቆ አገኙት ። ከዚህ ሁሉ አጉል ልፋት ለሰው መዳኛ የሚሆን ጉድጓድ በመቆፈር ጉልበቱን ቢያፈስ ኖሮ ይሻል ነበር የሚል ሃሳብ በሆስነር አእምሮ ውስጥ ቢጠነሰስም አልተናገረ ውም ።

ዶብኪን “ የተገኘ ዕድል አለ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ካን ተጋድሞ ከሚሠራው ውስጥ ተንፏቆ በመውጣት ከቆመ በኋላ “ እስከ አሁን ምንም የለም ። ግን ውጤት ለማግኘት እየተቃ ረብኩ ነኝ ብየ አስባለሁ” አለው ። ዶብኪን “ ጥሩ ነው ” አለው። ካን ወደ ሆስነር እየተመለከተ “ ጥገናውን ሠርቼ ውጤት ባገኝ በቂ ባትሪዎችና ነዳጅ እንደሚኖሩን ተስፋ አለኝ ” አለው ።

“ ለምን ?” ብሎ ሆስነር ጠየቀው። “የአየር ማቀዝቀዣውን ማን ቀሳቀስ እንችላለን ? ” ብሎት በመወጣጫው ላይ እየተራመደ “ እና ንተ ሁለታችሁ በባትሪዎቹ በመጠቀም የራዲዮ ግንኙነት ማድረግ ከአልቻላችሁ የጄነሬተሩ መሥራት ልዩነት ያመጣል ብየ አላስ ብም ” አለው ።

ካን መልስ አልሰጠውም ።

ሆስነር አዲስ በተሠራው መውጫ ላይ ወጥቶ ወደ አውሮፕላኑ ከደረሰ በኋላ ወደ ኮንኮርዱ አፍንጫ ተመለከተ ። “ የቴክኒክ ሠራ ተኞች በተፈጥሮአቸው መጐራጐር ይወዳሉ ። አንድ ነገር ከተበላሸ መጠገን ትፈልጋላችሁ ። ካንም የተበላሸውን ረዳት የኃይል መስጫ ለመጠ ገን እየጣርክ ነው ። ነገር ግን ቢጠገንስ የሚያስከትለው ጥሩ ነ ገር ምን ይሆናል ? ” ብሎ ወደ ክንፉ ላይ ዘለለ ።

ዶብኪንና በርግ ወደኋላ ቀርተው ረጋ በማለት ከካን ጋር ተነጋ ገሩ ። የተሳፋሪዎቹ መቀመጫ ክፍል በሙቀቱ የተነሳ በኃይል ግሏል። ሆስነር ለጥቂት ጊዜያት ውሃ ከአለመጠጣቱም በላይ በተጨማሪ

ላቡ መንጠባጠብ ጀመረ ። የአውሮፕላኑን ጅራት ሲገነጣጥሉ ድምጹ ይሰማው ነበር ። በሚያልፍበት ጊዜ ቢከር በአስቸኳይ ኃይል መስ ጫው ሲጠቀም ስለአየው በመጠኑም ቢሆን በስጨት አለ ።

ሆስነር ወደ በረራው ክፍል ከመግባቱ በፊት አንድ ነገር ስለ ሸተተው ወደ ውስጥ ሲመለከት የሐሺስ በድን አብጦ አየው ። ሞቃቱ ነፋስም በተሠበረው መስታዎት ውስጥ እየገባ ነበር ። ቢከር ማዳመጫ በጆሮው ላይ አድርጐ ራዲዮ ያዳምጥ ነበር ።

ሆስነር ገብቶ “ አስከሬኑ ከዚህ እንዲወጣ እፈልጋለሁ ” ብሎ ጮኾ ነገረው ።

ቢከር ማዳመጫውን ከጆሮው ላይ አንስቶ “ ኃላፊነት ስላለብኝ መቃብሩ እስኪዘጋጅ ድረስ እዚህ መቆየት አለበት ” አለው ።

ሆስነር በቢከር አዕምሮ ውስጥ ምን እንዳለና ሃሣቡ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ አልሞከረም ። ሬሳው የትስ ቦታ ቢቀመጥ ምን ልዩነት ይኖረዋል ? ምናልባትም ሌሎቹ ሰዎች እንዲያዩት ማድረጉ የተሻለ ነበር ። ያ ቂስ ብቻ ባይኖር ኖሮ . . .

“ እኔ የምለው ራዲዮኑን ብቻህን መነካካት ትፈልጋለህ ? ”አለው ቢከር ።

“ ምን ? አልፈልግም ፡ የሰማኸው ነገር አለ ? ለማስተላለፍ ሞክ ረሃል ? ”

“ቀደም ብየ እንደተናገርኩት በቀን ማስተላለፍ አስቸጋሪ ነው።”

“ እሺ ፡ ምናልባት ዛሬ ማታ የተሻለ ዕድል ይኖረን ይሆናል ።”

“ አይኖረንም ። ”

“ ለምን ? ”

“ አንድ የማስተላለፊያ መስመር አግኝቻለሁ ። ”

ሆስነር በጣም ተጠግቶ “ ማነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ ስሙ አህመድ ሪሽ ይባላል ። በሰማይ ላይ ሲያበር በነበረበት ጊዜ ያዕቆብ ሆስነር ሕይወታቸው በአስጊ ሁኔታ ላይ ስለአሉት ሰዎች እንደሚያስብበት ተስፋ አለኝ ብሏል ። ስላደረኩት በረራ የምስጋና አስተያየት ሰጥቷል ። የሚያስገርም ሰው ነው ” ብሎ ቢከር ከሳቀ በኋላ “ እስከ ጀንበር ጥልቂያ ድረስ እጃችንን ካልሰጠን መጥቶ እንደሚከበንና ራዲዮኑንም እንዳይሠራ እንደሚያደርገው ነግሮኛል” አለው ።

“ ይህ ቀጣፊ ። ”

“ የሚናገረው ሁሉ የሚያስገርምና መጥፎ ነው ” ብሎ ቤከር ራዲዮኑን ካጠፋ በኋላ “ ተኩሰህ ልታወርደው ትችላለህ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ሆስነር ላቡን ከአንገቱ ላይ ጠርጎ “ አንተ እንዳትነጋገር የሚያ ደርግህ የበረራው ከፍታ ምን ያህል ሲሆን ነው ? ” አለው ።

“ ከፍታው የሚፈልገውን ያህል ይሆናል ። ኃይልም አለው ። ጥራት ባለው ሰማይ ላይ እይታው ትይዩ መሆን ይኖርበታል ። ”

“እንግዲያው ልዩ መሣሪያ ከሌለን በስተቀር መትተን ልናወር ደው አንችልም ። ”

ቤከር ቆሞ “ይህንን አውሮፕላን በተመለከተ የመጨረሻ ሥል ጣን እንዲሰጠኝ እፈልጋለሁ ፡ ሆስነር ። ከጥቂት ጊዜያት በፊት የአ ንተ ሁለት ሰዎች ይህን ራዲዮ ከባትሪዎቹ ጋር የሚያገናኘውን ሽቦ ለመውሰድ ሞክረዋል ” አለው ።

ሆስነር ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ እሺ ” አለው ። የቤከር ፊት መለዋወጡንና ከንፈሮቹም መሰንጣጠቃቸውን አይቶ “ እባክህ ውሃ ጠጣ ” አለው ።

ቤከር ወደ በሩ እየተራመደ “ ሔጄ መቃብሩን መቆፈር አለ ብኝ ” ብሎት የበረራውን ክፍል ትቶ ወጣ ።

ሆስነር ራዲዮኑን ትኩር አድርጎ ከተመለከተ በኋላ ተከትሎት ሔደ ።

* * *

ለሰላሙ ድርድር ከተመረጡት ጥቂት ወንዶችና ሴቶች ጋር ብኮንኮርዱ ክንፍ ላይ ቆማለች ። እርሱ ወደ እርስዋ መሔድ ባይፈ ልግም አማራጭ አልነበረውም ። ከሌሎች ረዳት መኰንኖች ወይም ከበረራ ሠራተኞች ጋር አልተቀላቀለችም ። ሁሉም እንደየብጤው በቡድን እንደተሰባሰበ ልብ አድርጓል ። የአውሮፕላኑን ጅራት የሚገነጣጥሉትን ሰዎች ለመርዳት ሁሉም እየመጡ ነበሩ ። እጆችዋ በአሉሚኒየሙ ስብርባሪ እንዳይጎዱ በጨርቅ ጠቅልላቸዋለች ። ሰውነቷ በአቧራና በላብ ተሸፍኗል ። ሌሎቹ ወደ አውሮፕላኑ ሌላ ክፍል ሲሔዱ እርስዋም የሚያቃጥለውን ክንፍ አቋርጣ ቀስ ብላ ትራ መድ ነበር።የሰውነትዋን ሚዛን ለመጠበቅ እግሮችዋን ከፍታ ቆመች። “ እያንዳንዱ ሰው አንተን ጀግና ነህ ብሎ የሚያስብ ይመስልሃል ?” አለችው ።

“ ነኝ ። ”

" ነኻ ! ጀግኖችን የሚወድ የለም ። ይፈራሉ - ጀግኖችን አጥ ብቀው ይጠላሉ ። ይህን ታውቃለህ ? "

" አሳምሬ ። "

" ከአንድ ዓመት በፊት በፈረንሳይ አገር በአውሮፕላኑ ጅራት ውስጥ የተጠመደው ቦምብ ሳይታይ በመቅረቱ ላይደረሰው ችግር ካላ እገኘህለት ? እንደገና ከሰው ዘር ጋር ለመደባለቅ ትችላለህ ? " አለ ችው ወደ ኮንኮርዱ ጅራት እያመለከተች ።

" ሁኔታውን ጋባዥ እያደረግሽው ነው ። "

" ታዲያ ለምን አታደርገውም ። "

መልስ አልሰጣትም ።

" ሪሽ ከዚያ ሌላ ምን አለ ? "

" በራምላ ስለአሳለፉቸው ጊዜዎች ለመናገር ፈለገ ። "

" የማወቅ መብት አለን ። "

" ይህን እንደገና መጀመር የለብንም ። "

" ምን ዓይነት ድርድር አቀረበልህ ? "

" ለማንኛውም ለሚቀርብልሽ ነገር ራስሽን አሳልፈሽ መስጠት ትፈልጊያለሽ ? " ካቅማማች በኋላ " ሕይወት ለማዳን ብቻ " አለ ችው ።

"ሕዝባችን ሲዋረድ ከማየት ውድ ሕይወታችን ቢጠፋ ይሻላል።"

" ከአንተ የሚወደድ ነገር ያየሁት ምንድን ነው ? አንተ በእው ነት ክፉ ሰው ነህ " አለችው ።

" እውሬውን ለማዳ ማድረግ አትፈልጊም ፡ ሚሪያም ? አንቺ ጥሩ ሥራዎች አድራጊ አይደለሽም ? " ብሎ ጠየቃት ። በአውሮፕ ላኑ ውስጥ በተገናኙበት ጊዜ ሰው እንደሚያስፈልገው የነበራትን የጋለ ስሜት አስታወሰ ።

በሁኔታው ግራ የተጋባች መሰለች ። ቀጥላም " በእኔ እየቀለ ድህ ነው ? " አለችው ።

የሲጋራ ቁራጭ አውጥቶ ለብዙ ጊዜ ተመለከተው ። በድንገት ረዳት የሌላት መሰለች ። እርሱም ተመለከታት ። " ስሚ ፡ በርግ በአ ንቺ ተቀይሟል ። የሰውን ሞራል ትጥላለህ አለችኝ ብሏል ። ስለዚህ በምክር ቤት መድረክ እስኪሰጥሽ ድረስ የምትናገሪውን መቆጣጠር

አለብሽ ። ቀልድ እንዳይመስልሽ ፡ ሚሪያም ። በምታደርጊው ጠን
ካራ የሃሳብ ልዩነትና አለመግባባት ሊከስሽ ቢወስን ልረዳሽ አልች
ልም ” አላት ።

ወደ እርሱ ተመለከተች ። ሃሣብዋን እስክታብላላ ድረስ ትንሽ
ጊዜ ወሰደባት ። አዕምሮዋ ያውጠነጥን የነበረው ቀደም ብሎ በተና
ገረው ላይ ስለነበረ በድንገት ድምፅዋ ተለዋወጠ ። “ ምን ? ሊያስከ
ስሰኝ የሚችለው ምክንያት ምንድን ነው ? እንደፈለገው የምነዳ
መደዴ አይደለሁም ። ይህ የዲሞክራሲ መብቴ ነው ፡ ኤሜ ። ”

“ ይህ ባቢሎን ነው ። ይህ የብቀላ ሕግ ( ክፋትን በክፋት ) የሚፈ
ጸም በት አገር ነው - ዓይን ያወጣ ዓይኑ ይውጣ ፡ ጥርስ የሰበረ ጥርሱ
ይ ሰበር-የሚለውን ሕግ ሙሴ ለእኛ ከመስጠቱ በፊት በሀሙራቢ የተ
ደነገገ ሕግ ነው ። መሠረታችን ጨካኝና ርኅራኄ የሌለው ነው ። ለዚ
ህም ምክንያት አለው - ጨካኝ ዓለም ነበር ። ከዚያ በኋላ የዓለም
ታዋቂ ሰላም አብሳሪዎች በመሆናችን የደረሰብንን ተመልከቸው ።
ከዚህ ሁሉ ምዕተ ዓመታት በኋላ አሁን ተዋጊ ወንዶችና ሴቶች እያ
ሳደግን ነው ። ጠባያቸውን አንወደውም ይሆናል ። እነእርሱም ግድ
የላቸውም ። አውሮጳዊ አስተሳሰባችንን በጣም አይወዱትም ። ወላ
ጆቼ በአውሮጳ ውስጥ ቢቆዩ ኖሮ እንደ አንቺ ዞሪያውን ዝግ በሆነ
መኪና ውስጥ ተወስደው ድራሻቸው በጠፋ ነበር። አንድ ዓይነት ጠባይ
ነበራቸውና ። አሸር አቪዳር በጣም ቂል ነበር - ግን ለምን እንደሆነ
ታውቂያለሽ ? የዚያን ዓይነቱን ቂል ሰው እኔም በጣም እወደዋለሁ ።
እንደ አንቺ ያሉ ሰዎች ግን ያልሆነ ፍርሃት ይፈጥራሉ ። ”

መንቀጥቀጥ ጀመረች ። ቍንፋሽዋ እጥር ፡ እጥር አለባት ። ለመ
ናገር ምላስዋ ተያያዘባት ። “ የ . . . የአንተ ወላጆች አውሮጳ ቢቆዩ
ኖሮ የናዚን ጠባይ ይዘህ ታድግ ነበር ። እነእርሱም የራሳቸው የሆ
ነውን ለይተው ያውቁ ነበር ። ”

ሆስነር በመዳፉ በጥፊ ሲመርግባት በክንፉ ላይ ወድቃ ጥቂት
ሜትሮች ከተንከባለለች በኋላ ያልተሸፈነውን ጉልበትዋን በፀሐይ
የጋለው ብረት እያቃጠላት ተጋደመች ።

ሆስነር ተከትሎ ሔዶ አፈፍ አድርጎ በማንሳት እንድትቆም
አደረጋት ። በዚያ በኩል የነበሩት ሰዎች ትኩር አድርገው ተመለከ
ቷቸው ። ሆስነር ክንዶቿን ጥርቅም አድርጎ በመያዝ ፊትዋን ወደ
እርሱ ፊት አስጠጋው ። “ እርስ በእርሳችን የምንነታረክና የማ
ንግባባ ከሆነ በምንም ዓይነት አብረን መጓዝ አንችልም ፡ ሚሪያም”
ብሎ ሲመለከታት ዓይኖቿ እንባ ቋጥረዋል ፡ በጉንጮቿ ላይም መን
ከባለል ጀምረዋል ።

“ አዝናለሁ ” አላት ።

በሚያስደንቅ ኃይል መነጨቀኝ ው ። “ ገሃነመሳት መግባት ትች ላለህ ! ” ብላ በቦጠ. ልትመታው እጅዋን ስታነሳ የእጅ አንጓዋን ያዘው ።

“ መንፈሱ ደህ ነው ፡ ሚሪያም ። ሌላውን ጉንጭ አዙሮ ከመስ ጠት ይልቅ ደህ የተሻለ አይደለም ? ገና ተዋጊ ትሆኛለሽ ። ”

ቀስ አድርጋ ራስዋን ካስለቀቀች በኋላ በፈጣን እርምጃ የሚያ ብረቀርቀውን የኮንኮርዱን ክንፍ አቋርጣ አደጋ ሲያጋጥም በሚጠ ቀሙበት በር ወጥታ ሔደች ።

## —20—

ሆስነር ቀስ ብሎ በመወጣጫው ላይ ወረደ ። በርግ እየጠበቀው ነበር ። ሆስነር በኃይል ተንፍሶ “ የሚቀጥለው ምንድን ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ እኔ የአንተ ረዳት መኰንን ብሆን እመርጣለሁ ። ”

“ እረዳቴና የመረጃ መኰንኔ ጭምር ነህ ። ዶብኪን ከፍተኛ ረዳት መኮንኔ ነው ። ሌይበር የዕቃ አቅርቦት የሃምሳ አለቃዬ ነው። እያንዳንዱ ሥራ አለው ወይም በሚቀጥሉት ጥቂት ሰዓቶች ውስጥ ሥራ ይሰጠዋል ። ”

“ ሚሪያም በርንስቴይን ሳትቀር ? ” ብሎ በርግ ጠየቀው ።

ሆስነር ተመልክቶት “ አዎን ፤ እርስዋም የምትሠራው አላት ። ሐቀኛ እንድንሆን ታተጋናለች ። የሰለጠን ሰዎች መሆናችንንም ታስ ታውሰናለች ” አለው ።

“ በአሁኑ ጊዜ ስለዚያ ማንም እንዲያስታውሰኝ አልፈልግም ። ለማንኛውም በማይመለከታት ጉዳይ እየገባች የማታውቀውን ታናፍ ሳለች ። ጉዳዩን በጥልቀት የሚያውቀውና ባለሙያው ከአንተ ጋር መነጋገር ይፈልጋል ። የሚቀጥለውም ይኸው ነው ።”

“ቄሱስ ? ”

“ በመጀመሪያ ከቄሱ ጋር ቀጥሎም ከመክለርና ከሪቻርድሰን ጋር መነጋገር ይገባሃል ብየ አስባለሁ ። የመረጃ መኰንንህ እንደ መሆኔ መጠንና እንደምገምተው በዚያ በኩል ሙሉ በሙሉ ግልጽ አይደለም ። ”

“ ለምሳሌ ያህል ? ”

“ እርግጠኛ አይደለሁም ። ለማንኛውም ረዳት መኰንንህ እንደ መሆኔና እንደማስበው ከእኛ ጋር ያሉ ብቸኛ የውጭ ዜጐች ሁለቱ ብቻ ስለሆኑና ከእኛ ጋር ችግሩን ለመጋፈጥ አብረው በመሰለፋቸው ከፍተኛ የሞራል ድጋፍ አትርፈውልናል ። እኔ እነእርሱን ብሆን ኖሮ ቀደም ብየ እሔድ ነበር ። ”

“ መከለር እንደ አለት ድንጋይ ጠንካራ ነው ፤ ሪቻርድሰን በመ ጠኑ ልል ይመስለኛል ። ለማንኛውም አነጋግራቸዋለሁ ። ሌላስ ነገር አለ ? ”

“ ሪሽ ያቀረበውን ጥያቄ ለመቀበል ምርጫ ለማካሔድ ካልፈ ለግህ በስተቀር ሌላ ላስታውስህ የምችለው ነገር የለኝም ። ቀኑም እየተጣደፈ ነው ። ”

ሆስነር ፈገግ ካለ በኋላ “ ጧት እናደርገዋለን ” አለው ።

በርግ ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “እሺ ፤ እናስብበታለን” አለው ።

“ ዶብኪን የት ነው ? ”

“ ለሙጨረሻ ጊዜ ያየሁት ስለመከላከያ መከታዎች ፤ ጉድባ ዎች ፤ የቀበሮ ጉድጓዶችና ካቦች ትምህርት ሲሰጥ ነው ። ”

“ ለምረቃ የሚያበቃ ሥልጠና ነው ? ”

“ ይመስለኛል ፤ የመጨረሻው ፈተና የሚሰጠው ዛሬ ማታ ነው ። ”

ሆስነር ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ እኔም ጀንበር ከመጥለቅዋ በፊት ስለመሣሪያዎች አጠቃቀም ስልጠና እንደምሰጥ ንገረው ።የሚ ቻለውን ያህል ሰዎች እንዲመጡና እንዲያጠኑ እፈልጋለሁ ። እንደ አጋጣሚ አንድ ተኳሽ ቢወድቅ ማንኛውም ሰው አንስቶ መተካት አለበት ” አለው ።

“ መልካም ከፈለግኸኝ በእረኛው ጐጆ እገኛለሁ ። ለእነዚያ ሁለት ሰዎች የሚገባቸውን ሥራ ለመስጠት ቃል ገብቸላቸዋለሁ ። ”

“ እዚህ የምንሰጣቸው ባይኖርም የምንችለውን እናደርግላቸ ዋለን ። እስከዚያው ድረስ የሚፈልጉት ሁሉ ያላቸው መሆኑን አረ ጋግጥ ። ”

“ እሺ ። ”

ሆስነር ቄስ ሌቪንን ከቤከር ጋር ሲወያይ አገኘው ። ቤከር ኤፍ ራጥስን አቆልቁሎ በሚያሳይ በትንሽ ኮረብታ ላይ መቃብር ይቆፍ ራል ።

ሆስነር ቄሱ እስኪያየው ድረስ ትንሽ ራቅ ብሎ ቆመ ።

ቄሱ ለቤከር አንድ ነገር ከተናገረ በኋላ ሆስነር ወደ ቆመበት ሔዶ “ ያዕቆብ ሆስነር ፣ የባቢሎን አንበሳ ” ካለው በኋላ “ ወደ ኢሺታር በር በጉዞ ላይ በነበርክበት ጊዜ ሞክሼህን አየኸው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ ምን ልረዳህ እችላለሁ ፤ መምህር ? ”

“ ሪሽ ያቀረባቸውን ድርድሮች በአጭሩ በመንገር መጀመር ትችላለህ ። ”

“ ምን ልዩነት ያመጣል ፤ እኛ እንደሆን ድርድሮቹን አንቀበ ላቸውም ። ”

“ አንተ አትቀበልም ፤ እኔ አልቀበልም ፤ እዚህ ካሉት አብዛ ኞቹ ሰዎች አይቀበሉም ። ይሁን እንጂ ጥቂት ሰዎች ለመቀበል ይፈ ልጋሉ ። የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም እያንዳንዱ ሰው የራሱን ዕድል በመጠቀም የራሱን ውሳኔ ማድረግ እንደሚገባው ሕግ ያስተ ምረናል ። ”

“ ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መኖሩን አላስታውስም ። እነ ዚህ ሕጐች የአንተን ፍላጐቶች ለማሟላት የተዘጋጁ ናቸው ብየ አስ ባለሁ ። ”

ቄስ ሌቪን ስቆ “ አንተን ማታለል ቀላል አይደለም ። ያዕቆብ ሆስነር ። ግን ሕጉ ምን እንደሚል እነግርሃለሁ ። ራስን መግ ደል ኃጢአት ነው ይላል ” አለው ።

“ ታዲያስ ? ”

“ ታዲያማ ? የበለጠ ልታውቅ ይገባሃል ። ስድስት ወጣት አነ ጋጋሪዎችና ጸሐፊዎች -ሁለት ሴቶችና አራት ወንዶች ይመስሉኛል— የማያወላውል የኅቡዕ መከላከያ ማህበር ( የማሳዳ ቡድን ) አባሎች አሉ ።

“ እናስ ? ”

“ እና እኛ ባንችል የራሳቸው የሆነ መፍትሔ ለመስጠት እየ ተሯሯጡ ናቸው ። ያን ሃሳብ እኔ አልቀበለውም ፤ አንተም አታደር

ገውም ብየ አገምታለሁ ” ብሎ ከነገረው በኋላ ሆስነርን አፍጥጦ ተመለከተው ።

ሆስነር በአንገቱ ላይ ይንቆረቆር የነበረውን ላብ ጠረገ ። ከተ ራራው ባሻገር ነፋሱ የአቧራ አዟሪት መሥራት ጀምሯል ። አንድ ወቅት ዛፎችና እህል ያበቅል የነበረው የኤፍራጥስ ዳርቻ ጭቃማ ሜዳ ከሩቅ ተንጣሎ ይታያል ። እንደዚሁም ከምዕራብ በረሃ በኩል በጥንቱ የደማስቆስ መንገድ ተጉዘው የመጡ ሰዎች ባቢሎንን ማየት ችለ ዋል ። የአይሁዳዊ ምርኮኞች የመጡት በዚህ ዓይነት ሲሆን ሁኔታው በዚያን ጊዜ የሚያስጐመኝ ይመስል ነበር ።

ሆስነር ተመልክቶት ረጋ ባለና በለሰለሰ አንደበት “ ምርኮኛ ነቱ . . . ሠፈራዎቹ . . . እልቂቱ . . . እነዚህን ግፎች ለመቋቋም ሕይወት ያለው ሰው ያስፈልጋል . . . ነገር ግን ለመቋቋም ሲያቅት... ኃይል ሲያንስ . . . ከዚያ በኋላ ራስህ ለራስህ ወሳኝ ትሆናለህ ። ለው ርደት : . . . ለመዘባበቻ . . . ለስቃይ . . . ለመታረድ . . .
ራስህን አሳልፈህ አትሰጥም ። ጠላቶችህ በአንተ ላይ ይህን ሁሉ ከመፈጸማቸው በፊት አንተ ታደርገዋለህ ” አለው ።

“ ማን እንደሚሞትና ማን እንደሚኖር የሚወስነው እግዚአብ ሔር ነው ። ሰው መወሰን አይችልም ። እኔም አላደርገውም ። የራ ሳችንን ሕይወት የማጥፋት መብት የለንምና ። ”

ሆስነር በመጀመሪያ ስለአቪዳር ቀጥሎም ስለበርንስቴይን እንደ ገና አሰበ ። በሁለቱ ፍልስፍናዎች መካከል አንድ አስታራቂ ሃሳብ መኖር አለበት ። “ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ በሚደርስበት ጊዜ ምር ኮኛ ለመሆን የሚሹ እጃቸውን ሊሰጡ ይችላሉ ። እስከ መጨረሻው ለመዋጋት የሚፈልጉም ይችላሉ ። ሕይወታቸውን በራሳቸው ለማ ጥፋት የሚመኙ ደግሞ ያደርጉታል ። ሌላስ ነገር አለ ፤ መምህር ? ”

ቄስ ሌቪን ብስጭትና ብሶት ባለበት አመለካከት ካየው በኋላ“የሰ ሎሞንን ጥበብ ታስታውሳለህ፡ ያዕቆብ ሆስነር ። ለአንተ የሚሆን በባሕል ላይ ያልተመሠረተ አንድ ትንሽ ጥበብ ልንገርህ።እነዚያ ሁለት ሴቶች የሰሎሞንን ፍርድ በመከተል ተስማምተው ሕፃኑን ለሁለት ቢሰነጥቁት ኖሮ ሰሎሞንን ገዳይ ያሰኘዋል እንጂ ትክክለኛ ዳኛ አያ ስብለውም ነበር ። አንተም የምትሆነው እንደዚያ ነው - ገዳይ ። ያመ ጣኸው አስታራቂ ሃሣብ በእኔ ዘንድ ተቀባይነት የለውም ” ካለው በኋላ እጁን አወናጭፎና ድምጹን ከፍ አድርጎ “ እጃቸውን ለመ ስጠት የሚፈልጉትን ሰዎች አሁኑኑ እንድትፈቅድላቸው ፤ ራስን መግደል የሚለውን እንድታወግዝና ስለራስን መግደል የምታወራ ውን እንድታቆም አጥብቄ እጠይቅሃለሁ ” አለው ።

ቄሱ አንድ ነገር በእጁ ላይ ይዞ ሆስነር አየው ። ሌቪን አሁንም እየጮኸ በመናገር ላይ እንዳለ ሆስነር እጁን በቄሱ ትከሻ ላይ ጣል በማድረግ ዝም እንዲል ካደረገው በኋላ በለስለስ አነጋገር “ አላውቅም ” ብሎ ራሱን ዝቅ አደረገ ። ቀጥሎም “ ምን እንደማደርግ አላውቅም ፡ መምህር ። ይህ ነገር እያሰለቸኝ መጥቷል ። ከአሁን በኋላ ኃላፊ ሆኜ የምሠራ አይመስለኝም ፡ ስሜቴም እየቀዘቀዘ ነው ፡ እኔ . . . ” አለው

ቄስ ሌቪን የሆስነርን ክንድ ይዞ “አዝናለሁ ፡ ለአሁን ይብቃን ፡ የደከምህ ትመስላለህ ። በሌላ ጊዜ ስለምንነጋገርበት እስከዚያው በዚህ ነገር እንዳላስቸግርህ ቃል እገባልሃለሁ — የተሻለ ስሜት እስኪያድርብህ ድረስ ” ብሎ ነገረው ።

ሆስነር በድንገት ደህና ስሜት አደረበት ። እጁን ከቄሱ ላይ አንስቶ “ ጥሩ ፡ የመጨረሻ ለመስማት የምፈልገው ይህን ብቻ ነው ” ብሎ በቄሱ እጅ ላይ የነበረውን ነገር ተመልክቶ “ ይህ የያዝከው ምንድን ነው ?” ብሎ ጠየቀው ።

“ ምኑ ? ” ብሎ ቄሱ በእጁ ላይ ያለውን ከተመለከተ በኋላ “እህ! ይህ መጥፎ ነገር ነው ። ለመንካት እንኳን እጠላዋለሁ ። ይህ ጣኦት ነው ” ብሎ ወደ ላይ አንስቶ በፀሐይ ብርሃን እየተመለከተ “ ቤከር መቃብር ሲቆፍር ያገኘው ነው ” አለው ።

ሆስነር በበለጠ ተጠግቶ ተመለከተው ። በመጀመሪያ እንዳይፈርስ በመድኃኒት የተጣበቀ የሰው አጽም የሚመስል ነገር በመሆኑ አፍጥጦ ካየው በኋላ ከነጭ አፈር በሙጫ ነገር የተሰሩ ክንፎች ያለው ጣኦት መሰለው ። ቁላው ከመነመነው ሰውነቱ ጋር ሲተያይ በጣም ትልቅ ከመሆኑም በላይ በፊቱ ላይ የነበረውን ሆስነር ምንጊዜም አይረሳውም ። “ ይህ የሽማግሌው ዶብኪንን ሃሳብ ያሟላል ብየ አስባለሁ ። ሰዎቹ በሚያርፉበት ጊዜ ፍርስራሹን አንድ በአንድ እያዩ እንዲመረምሩ አዟቸው ስለነበረ ሁሉም ተናደዋል ።

ለእኔ ስጠኝ ። ”

ቄሱ የስዕሉን ፊት ወደ እርሱ አዙሮ ከተመለከተው በኋላ “ይህን አስቀያሚ ነገር በእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ በፀሐይ ብርሃን ማየት ተገቢ አይደለም ። በጨለማ ውስጥ መቆየት ይገባዋል ” ብሎ የእጁ ስሮች እስኪገታተሩ ድረስ በኃይል ጨምዶ ያዘው ።

ሆስነር እንደ በድን ሆኖ ሳይንቀሳቀስ ቆመ ። አውሎ ነፋስ የአካባቢውን አቧራ አንስቶ ስላለበሰው ለሴኮንድ ያህል ለማየት አልቻለም ። በነፋሱ መካከል ጮኾ “ አትጃጃል ፡ በሃያኛው መቶ ዓመት እንደዚያ አናደርግም ፡ ለእኔ ስጠኝ ” አለው ቄሱን ።

ቁሉ ፈገግ ብሎ ጣአቱን በኃይል የያዘውን እጁን አላላ ። ነፋሱም እቆመ ። ቡናማው አቧራ ረግቶ በመሬቱ ላይ አረፈ ። ወደሆስነር እጁን ዘርግቶ ‘‘ እንካ ፣ ትርጉም የሌለው ነገር ነው ። ብሰባብረው እግዚአብሔር በአጉል እምነቴ ይስቃል ። ከምስጋና ጋር ለጄኔራል ዶብኪን ስጠው ’’ አለው ።

ሆስነር ተቀብሎ ‘‘ አመሰግናለሁ ’’ ካለው በኋላ ለጥቂት ሴኮንዶች እርስ በእርሳቸው ተያዩ ። ቀጥሎም ሆስነር ፊቱን አዞሮ ሔደ።

* * *

ሆስነር በአፋፉ ላይ እየገሰገሰ ሔደ ። የኤፍራጥስን ወንዝ አቀልቁሎ እሚያይበት ቦታ ላይ ደረሰ ። ቀጥ ያለው ቁልቁለት እስከ ወንዙ ዳርቻ ድረስ 100 ሜትር ያህል ይሆናል ። ዶብኪን ቀን ይቅርና በጨለማ እንኳን ሳይታይ በዚያ ላይ እወርዳለሁ ማለቱ አስገርሞታል ።

በተራራው ግርጌ ያለው በአቧራ የተሸፈነው የወንዙ ዳርቻ - አንድ ወቅት የምሽጉ መሠረት የነበረ - ልዩ ልዩ የወይራ ዘይት ዛፎች የሚመስሉ ቁጥቋጦዎች በቅለውበታል ። እንደዚሁም እጅብ ያሉና አልፈው አልፈው የተጋደሙ ቁጤማዎች ስለነበሩ አሽባሎቹ በእዚያ ተመድበው እንደነበረ ሆስነር ገመተ ።

የኤፍራጥስ ወንዝ ቀዝቃዛና የሚያባብል መሰለ ። ሆስነር የተሰነጣጠቀ ከንፈሩን ልሶ የራሳቸውን ክልል ተከትሎ ወደ ደቡብ በኩል አመራ ። በሚያልፍበት ጊዜ በሥራ ላይ የተጠመዱ ወንዶችና ሴቶች ቁፋሮአቸውን እያቆሙ ተመለከቱት ። እርሱ ግን በችኮላ እየተራመደ ነጐደ ።

መክለርና ሪቻርድሰን ወደ አሉበት ክልል ሲደርስ ሆስነር ቆሞ የሠሩትን አስደናቂ ሥራ ተመለከተ።ለተኩስ አመቺ የሆኑ ጉድጓዶች በመቆፈርና በመደልደል ሠርተዋል ። ሁለቱም ሰዎች ከራስ እስከ እግራቸው በላብና በአቧራ ተለውሰዋል ።

ሆስነር ሥራቸውን ካደነቀ በኋላ ‘‘ ምናልባት ሰምታችሁ እንደሆን የዕርቅ ድርድር ቀርቦልናል ። እኛ ግን ልንቀበለው አንችልም። ቢሆንም እናንተ ያለአንድ ሀፍረትና ፍርሀት መቀበል ትችላላችሁ ። ሪሽ ይዞ የሚያቆያችሁ ይህን ቦታ ዓለም እንዳያውቀው በምሥጢር ለማቆየት ስለሚፈልግ ብቻ ነው ። የፈለገው ይሁን ነፃ ይለቃችኋል። እኔ እስከምገነዘበው ድረስ ከመንግሥታችሁ ጋር ችግር ለመፍጠር ስለማይፈልግ በእናንተ ላይ ሌላ እርምጃ አይወስድም ። ስለዚህ ለእናንተ የተሻለ ስለሚሆን እንድትሔዱ እጠይቃችኋለሁ ’’ አላቸው።

መክለር ለመከላከያ በተቆፈረው ጉድጓድ አፋፍ ላይ ቅልጥ ሙን ሰብስብ ኢድርጎ በመቀመጥ “ እዚህ በመገኘቴ ኩራት እንዲ ሰማኝ አድርጎኛል - ማለቴ በዚህ በምዕራቡ ክፍል እኔ ብቻ አንድ ጠመንጃ ይዤ ለመከላከል በመብቃቴ ነው ። ባለፈው ማታ ብቻዬን ሆኜ እነዚያ ጠላቶቻችን ቢመጡ ኖሮ አፈር ድሜ አበላቸው ነበር ። በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ በዚህ አካባቢ ብዙ ማሻሻያዎች ስለሠራሁ እዚሁ እቆያለሁ ” አለው ።

ሆስነር ራሱን በአሉታ ነቅንቆ “ እናንተ ሁለታችሁ ከእኛ ጋር እንድትቆዩና ችግር እንዲያጋጥማችሁ አልፈልግም ” አላቸው ።

መክለር ጉንበስ ብሎ ጫማዎቹን ለጥቂት ጊዜ ከተመለከተ በኋላ “ እውነቱን ለማወቅ ከፈለግህ እኔ እዚህ መሆን አልፈልግም ። በሌላ በኩል ደግሞ እጄን አሳልፌ ለሪሽ መስጠት በምንም ዓይነት አልሻም ። ዛሬ ማታ እያጠቃሽው ከሔድህና እኛን ካገኘ ከሁለታችንም ወገን አይደላችሁም ብሎ አይተወንም ። እንዲያውም እዚህ ያለውን ምሥጢር ለማግኘት ሲል አጥንታችን እስኪሰባበር ድረስ ይቀጥቅጠናል ። ታዲያ አንተም ስለዚህ ጉዳይ ጭምር ማሰብ አለብህ” አለው ።

ሆስነር ስለነገሩ ካሰላሰለ በኋላ ወደ ሪቻርድሰን ተመልክቶ“አንተስ ኰሎኔል?” ብሎ ጠየቀው። ሪቻርድሰን ደስተኛ አይመስልም ነበር ። በሁለቱ መካከል አንድ ነገር ይካሔድ እንደነበር በግልጽ ይታወቅ ነበር ።

ሪቻርድሰን ጉሮሮውን አፍታትቶ “ እኔ እዚህ እቆያለሁ ። ነገር ግን ጀንበር ከመጥለቅዋ በፊት እንደገና ስብሰባ ለማድረግና ለመወያየት ቢሞከር ጥሩ ይመስለኛል ” አለው ።

“ ምክርህን አስብበታለሁ ፤ ኰሎኔል ። ከሁለት አንደኛችሁ ሀሳባችሁን ብትለውጡ መክለር ስለአለው ጭምር አስብበታለሁ ።”

“ ጥሩ ነው ። ለፈንጂነት በጠርሙስ ከአዘጋጃችኋቸው ውስጥ ጥቂቶቹን ብትልኩልን በዚያ ታች ባሉት ጢሻዎችና ቁጠማዎች ላይ ወርውሬ የወንዙን ዳርቻ በብርሃን እሞላዋለሁ ” አለው መክለር።

ሆስነር ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ ለመላክ እወድ ነበር ። ግን እንደአጋጣሚ ጀኔራል ዶብኪን ፀሐይ እንደጠለቀችና ጨረቃ ከመውጣትዋ በፊት በዚህ በኩል ከእኛ ክልል ወጥቶ ያሔዳል ። ከታች ያለውን ሁኔታ ተረኛ የዘብ ጠባቂዎችም ቢኖሩ እየተከታተላችሁ ተቆጣጠሩ ። የምትችሉትን እርዳታ ሁሉ አድርጉለት ” አላቸው ።

መክለር ሌላ ምንም ጥያቄ ሳያነሳ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ።

ዶብኪን ከአንድ ከፍታው እስከ ደረቱ ከሚደርስ ትልቅና ጥቁር ደቡልቡል ነገር አጠገብ ቆሟል ።

ሆስነር ከመክለርና ከሪቻርድስን ጋር ተመልሶ ሲሔድ አንድ እንደ ኳስ ድቡልቡል የሆነ ነገር ዶብኪን ሲመለከት ስላገኘው ተጠግቶ " ይህ ከየት የመጣ ነው ? " ብሎ ጠየቀው ።

ዶብኪን ቀና ብሎ ከተመለከተው በኋላ " የኮንኮርዱ ጅራት በፈንዳ ጊዜ ተፈንጥሮ የወጣ ነው ። በደቡባዊ ጉብታ በኩል ባለው ወጣ ገባ መሬት ውስጥ ወድቆ ስለነበረ ሌይበር የወያቁ ዕቃዎች በሚፈልግበት ጊዜ ያገኘው ነው።እዚህ ያመጣሁት ግን እኔ ነኝ " አለው ።

" መልካም ነው ፤ ግን ምንድን ነው ? "

ዶብኪን ዕቃውን እየቆረቆረ " የታመቀ ናይትሮጂን ያለበት ዕቃ ነው ብሎ ካን ነግሮኛል " አለው ።

ሆስነር ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ "ልንጠቀምበት እንችላለን ?" ብሎ ጠየቀው ።

" ይመስለኛል ። "

" ሙሉ ነው ? "

" ካን ሙሉ ነው ብሎአል ። መቆጣጠሪያም ስላለው ለመክፈትና ለመግጠም ከቻልን ልንጠቀምበት እንችላለን " ።

ሆስነር በአፅቁ መታ መታ አደረገው ። " በዚህ ላይ አዲስ ሃሣብ ሊያመጣ በሚችል ዘዴ ላይ መወያየት ያስፈልጋል ። እግረ መንገዱንም አዲስ ሃሣብ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት ለሰዎቻችን ሥራ ይፈጥርላቸዋል ። ሥራ የፈታ አዕምሮ መጥፎ ሃሳብ ያመነጫል የሚለውን ምሳሌ ያስታውሰኛል ። " ሆስነር ክንፍ ያለውን የጣኦት ሥዕል ወደ ላይ ይዞ " ይህ ምንድን ነው ? " አለው ።

ዶብኪን በጥንቃቄ ተቀብሎ በትልቅ እጁ በመያዝ ተመለከተው ። ቀጥሎም " ይህ ፓዙዙ ነው " አለው ።

" ምን ማለት ነው ? " ብሎ ፈገግ አለ ። ዶብኪን ግን የፈገግታ መልስ አልሰጠውም ።

ዶብኪን በአውራ ጣቱ ጥፍር በሥዕሉ ቁላ አካባቢ የነበረውን አፈር እየፋቀ አስለቀቀው ። " የነፋስ እርኩስ መንፈስ ነው ። ሕመምና ሞት ያመጣል ። "

ዶብኪን ሥዕሉን አንድ በአንድ ሲመረምር ሆስነር ለአንድ ደቂቃ ያህል ከተመለከተው በኋላ “ ይህ . . . ጥቅም አለው ? ” ብሎ ጠየ ቀው ።

ዶብኪን ቀና ብሎ በመመልከት “ይህን ያህል አይደለም።ከጡብ የተሠራ ነው ። ይህም ያልተለመደ ምሳሌ አይደለም ። ይዞታው ግን በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ ነው ። ለመሆኑ ያገኘው ማነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ ቤከር የሔስን መቃብር ሲቆፍር አገኘው ። ”

“ ጥሩ ነው ” ካለ በኋላ የሥዕሉን ፊት ምራቅ እያስነካ አጸዳው።

“ በእውነቱ ከዚህ ብዙ ነገር ይገኛል ብየ አልጠብቅም ። ይህ የምሽጉ መጨረሻ ሲሆን የጦር ሠፈሮችና ግዙፍ የመመልከቻ ሕንጻ ማማዎች ነበሩበት ። በላያቸው ላይ ከፍታቸው ከብዙ ሜትሮች ያላ ነሰ አቧራ መከመር አለበት ። በዚህ ትንሽ ጉድጓድ ውስጥ ምንም ዓይነት ነገር መገኘቱ ያስገርማል ” ካለ በኋላ ቀና ብሎ ወደ ሆስነር ተመልክቶ “ አመሰግናለሁ ” አለው ።

ለመሰባበር ገፋፍቶት የነበረውን መሠረተቢስ ሀሳብ አሸንፎ “ ለሰጠኝ ቄስ ምሥጋና ይገባዋል ። ”

ዶብኪን በአዎንታ ራሱን አነቃንቆ “ ሊሰብረው የነበረው በመ ሠረተቢስ ሃሣብ ላይ በመንተራስ ከሆነ እገረማለሁ ” አለ ።

* * *

የቀረው የሰዓት በኋላው ጊዜ አድካሚ ሥራ የሞላበት ነበር ። እንደ ቦይ የተቆፈሩት ቦታዎች በእርዝማኔና በጥልቀት ከመሠራ ታቸውም በላይ ከአንዱ ጫፍ ወደ ሌላው የማገናኘቱ ሥራ በመጠ ናቀቅ ላይ ቢሆንም አብዛኛው ተገናኝቷል ። ምናልባት ለብዙ ጊዜ በዚያ የሚቆዩ ከሆነ ከኤፍራጥስ ሰሜን ጉብታ ወደ ኤፍራጥስ ደቡብ ጉብታ ያለችግር ለመገናኘት የሚያስችል ሥራ ነበር ። በምዕራብ ቁል ቁለት በኩል የተሠሩት የመከላከያ የቀበሮ ጉድጓዶች ለአንዳንድ ሰው እንዲያገለግሉ ታስቦ ነበር ።

ፀሐይ ከመጥለቅዋ በፊት ሆስነር እየአንዳንዳቸው እንዲጸዳ ዱና ፀጉራቸውን እንዲያበጣጥሩ የእረፍት ጊዜ እንዲሰጣቸው አዘዘ። ወንዶቹ ጢማቸውን እንዲላጩ ታዘዙ ። ሆስነር በዚህ ላይ ንትርክ ይነሳል ብሎ ቢያስብም ምንም አልነበረም ። ጢማቸውን ሲላጩ የተረፋቸውን ውሃ ለማስመሰያ ምስሎች ለማሠራት ለሚጠቀሙበት ጭቃ ማቡኪያ አደረጉት ።

ሼርጂ የተባለው ነፋስ በጣም እየጠነከረና በጣም እየሞቀ በመ ምጣቱ አቧራው እያንዳንዱን ሰውና ማንኛውንም ነገር ማልበስ ከመጀመሩም በላይ ሰዎቹ ለመተንፈስ ችግር ፈጠረባቸው ።

ፀሐይዋ በ12.16 ሰዓት ጠለቀች ። የስምምነቱ ሰዓት ተፈፀመ ። ዕድላቸው እንደገና በራሳቸው እጅ ውስጥ ወደቀ ። ሆስኒር በምዕ ራብ ጭቃማ ሜዳ ላይ ፍም የመሰለችው ክብ ፀሐይ እየተንበለበለች ስትሰናበት ተመለከታት ። የቀኑ ብርሃን በጨለማ ተተካ ። የመጀመ ሪያዎቹ ኮከቦች በጨለማው ውስጥ ከሰማይ ታዩ ። ምሥራቃዊው ሰማይ ጥቁር ከፋይ መሰለ ። በጥንታዊዎቹ አይሁዳውያን የቀን አቆ ጣጠር መሠረት ቀኑ ስለአለቀ የሰንበት ቀን አብቅቷል ።

ሆስኒር ብዙ ጠባቂዎች ወደ አልተመደቡበት የምዕራብ ቁል ቁለት ሔደ ። ራቅ ብሎ አንድ ትንሽ ስርጉድ ሥፍራ ስላገኘ በአቧ ራው ላይ ተጋድሞ በመለወጥ ላይ የነበረውን ሰማይ አሻቅቦ ተመለ ከተ ። አየሩ በየትኛውም በረሃ እንደሚሆነው ሁሉ እዚያም በቶሎ ቀዘቀዘ ። ነፋሱም በመቀነሱ ለስላሳ ሽውታ ሆነ ። ሆስኒር ዓይኖቹን ብልጭ ድርግም ሳያደርግ ከልጅነቱ ወራት ወዲህ ያላያቸውን ኮከ ቦች በሚያስደንቀው ጥቁር ሰማይ ላይ በጣም ተጠግተውና ብርሃናማ ሆነው ተመለከታቸው ። ቀኖቹ በፀሐይ ብርሃን ይሞላሉ ። ጨለማ ዎቹ ደግሞ አስደናቂ በሆኑት የኮከቦች ብርሃን ይንፀባረቃሉ ። እን ደዚህ እንደ አሁኑ በጀርባው ላይ ተንጋሎ ኮከቦች አሻቅቦ እያየ ከቤት ውጭ የቆየው ከብዙ ጊዜ በፊት ነበር ።

በሙቁ አሸዋ ላይ በስሜት ቋምጦ በጀርባው ተዘርሯል ። በግ ማሽ ሰማይ ላይ የነበረው ጨለማ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ እየተጓዘ ብርሃኑን እያመነመነ ወደ ምዕራብ ገፋው ። ሁሉም ነገር ሊታመን በማይችል ሁኔታ ቆንጆና የሚማርክ ነበር ።

ከጭቃማ ሜዳው ውጭ ቀበሮዎች ጮኹ ። ጩኸታቸው በፍ ጥነት እየቀረበ መጣ ። ሆስኒር ወደ ኤፍራጥስ እየሮጡ በመምጣት ላይ መሆናቸውን ገመተ ። ጨለማውን ተገን በማድረግ ውሃ ለመ ጠጣት የወጣ አንድ ትንሽ አውሬ እያባረሩ ነበሩ ። ደጋግመው እየተ ነጫነጩ ጮኹ ። በመጨረሻም የመንገጫገጭና የመፍጨርጨር ድምፅ ከተሰማ በኋላ ፀጥታ ሆነ ።

አስደናቂዋ የበረሀ ጀንበር ለመጥለቅ የፈጀባት ጥቂት ደቂቃ ዎች ነበሩ ። ከጀንበር መጥለቅ ቀጥሎ ያለውን ጊዜ አውሮፕላን ነጂ ዎችና ወታደሮች የፀሐይ ጥልቀት ብርሃን - ከዚያም ጨለማ ብለው ይጠሩታል ።

ጨረቃዋ ለብዙ ሰዓቶች ሳትወጣ ትቆያለች ። ሪሽ እንደቀበሮዎቹ ጨለማውን ተገን አድርጐ ይወጋን ይሆን ፣ ወይስ ጨረቃዋ እስ ክትወጣ ይጠብቅ ይሆን ? ብሬን አሽባሎቹ ከኢሽታር በር ወደውጊያ ቦታቸው ሲንቀሳቀሱ አላያቸውም ። በተራራው ሥር ተረኛ ዘብ ጠባ ቂዎች የሚጠቀሙበት ቀጭን መንገድ ብቻ ነበር ። ያንንም ቢሆን አይጠቀሙበትም ማለት አይደለም ። ሪሽ በዚህ አሁን ባለው ጨለማ ለመውጋት ከፈለገ ጨለማው እንደጀመረ ሰዎቹን ወደ ውጊያው ቦታ ማንቀሳቀስ ነበረበት ። ሌላም አዛዥ የሚያደርገው ይህንኑ ነበር ። ይህ ጦርነት ከመጀመሩ በፊት ለእስራኤሎቹ ሰላሳ ደቂቃዎች ያህል ስለሚኖራቸው ሙሴ ሔስን ለመቅበር በቂ ጊዜ አላቸው ።

ሆስነር በተኛበት ስርጉድ ሥፍራ አጠገብ መጥታ በመንበር ከክ “ መጥፎ ስለሆነ ከዚህ ውስጥ ውጣ ” አለችው ።

“ እንደ ማህፀን ድሎት ያለውና ድብቅ ሥፍራ ነው ። ” ፈጽሞ ሊያያት አልቻለም ። እንዴት አድርጋ ፈልጋ አገኘችው ? እርሱስ መሆኑን እንዴት ለማወቅ ቻለች ? ብርሃን በነበረበት ጊዜ በዚያ አካ ባቢ መኖር አለባት ።

“ አንተ እንደምትለው አይደለም።ደረቅና መጥፎ ስለሆነ ተነሳ ፤ የመቃብሩ ሥነ ሥርዓት እየተጀመረ ነው ። ”

“ አንቺ ሒጂ ። ”

“ በጣም ስለጨለመና ስለምፈራ ሸኘኝ ። ”

“ ከሴት ጋር በምወጣበት በመጀመሪያው ቀን ወደ መቃብር ቦታ ፈጽሞ ሔጄ አላውቅም ። አሥራ አምስት ደቂቃ ስላለን በግብረ ሥጋ ልገናኝሽ እፈልጋለሁ ። ”

“ አልችልም ። ”

“ ላስኩሽ ? ”

“ አዎን ፣ ከባለቤቴ ጋር እንጂ ሌላ ውስብስብ ነገር አልፈል ግም ። ”

“ እኔ ብዙ ነገሮች ነኝ ፣ ሚሪያም ። ግን አንደኛቸውም የተወ ሳሰቡ አይደሉም ” ብሎ ሲነግራት ትንፋሽዋ ይሰማው ነበር ። በጣም ከመጠጋትዋ የተነሳ የምትርቀው ምናልባትም ከአንድ ሜትር ያነሰ በመሆኑ ሊነካት እሚችልበት ቦታ ላይ ነበረች ።

“ ስህተት ነው ። የቴዲ መሆኔን ላረጋግጥልህ እችላለሁ ። ለአ ንተም ሆነ ለሌላ ሰው ምናልባትም ለራሴም ጭምር በቂ ምክንያት ለመስጠት አልችልም ይሆናል ። ”

እርሱም ሳቀ ፣ እርስዋም ሳቀች ፣ ሁለቱም በአንድ ጊዜ ተንሰቀ ሰቁ ። ወደዚያው ተንፍሳ “ ያዕቆብ ፣ እኔን ለምን ? በእኔ ላይ ምን አይ ተሃል ? ” ብላ ንግግርዋን ለትንሽ ጊዜ ቆም ካደረገች በኋላ “ እኔስ በአንተ ላይ ምን አይቻለሁ ? ስለአንተ ሁሉን ነገር አጥላላለሁ ። እነ ዚህ ነገሮች በሰዎች ላይ ለምን ይሆናሉ ? ደግሞስ የማጥላላህ ከሆነ እዚህ ለምን መጣሁ ? ” አለችው ።

ሆስነር በዳበሳ የእጅ አንጓዋን ያዘው ። “ ለምንድን ነው የምት ከታተይኝ?” ሲላት እጅዋን መንጭቃ ለማስለቀቅ ብትሞክርም አል ሆነላትም ። “ አደገኛ የሆነ እንስሳ ተከትለሽ እያበረርሽው በጐሬው ደርሶ በሚገባበት ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚኖርብሽ ማወቅ አለብሽ። በተለይም ትተሽው ለመሔድ በምትመለሽበት ጊዜ በመግቢያው ላይ ቢቆም የምትወስጂውን እርምጃ አስቀድመሽ ማወቅ ይኖርብሻል ። መናገር ቢችል ኖሮ በምታበሪው ጊዜ በአዕምሮሽ ውስጥ ምን እንደ ነበረ ይጠይቅሻል ። ጥሩ መልስ ሊኖርሽ ይገባል ። ”

መልስ አልሰጠችውም ። የልብዋ ትርታ እየጨመረ መሆኑን ግን አውቋል ። አንድ ነገር ሰውነትዋን ወረረው ። ይህም ሆስነር በጨበጠው እጅዋ ላይ ተሰማው። አተነፋፈስዋም እየተለወጠ መጣ ። ስሜትዋ እየጋለ መምጣቱንም አረጋገጠ ። በዚያ ጨለማ ውስጥ ሰው ነትዋን ሊያየው ባይችልም ፈቃደኛነትዋን አወቀ ። የእርሱም ስሜት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ ተገረመ ። የእጅ አንጓዋን ይዞ ወደ እርሱ በእርጋታ ሲጐትታት ተንከባላ እርሱ በተኛበት አቧራ ላይ አረፈች ።

በላዩ ላይ ስለተኛች እንድታወልቅ ረዳት ። ቀጥለውም ፊት ለፊት ሆነው በጐናቸው ከተኙ በኋላ የራሱን ሱሪ ዝቅ አደረገ ። እርሱ እን ደገመተው ቆዳዋ ለስላሳና ቀዝቃዛ ነበር ። ከንፈሮቹን በከንፈሮቿ ላይ ሰ ያዳብላቸው የእርስዋም መልሱን በደስታ አበሰሩ ። በትጨባ በጡት ልብሶቻቸው ላይ በጀርባዋ ተንጋላ ሁለት ጉልበቶቿን ቀና አድርጋ ፈርከክ አደረገችለት ። ሆስነር በመሃከላቸው እንደገባ ቅልጥ ሞችዋ በእርሱ ላይ ተጠላልፈው በአስደናቂ ሁኔታ አጣብቀው ያዙት ። ለሴኮንድ ያህል ያለአንዳች ችግር ነካ ካደረጋት በኋላ ፊቷን ለማየት ሞክሮ ባለመቻሉ ሀዘኑን ነገራት ። ፈገግታ እያሳየች መሆንዋን ነገ ረችው ። ዓይኖችዋም ጭምር በፈገግታ ተሞልተው እንደሆነ ስለጠ የቃት ዓይኖችዋም በደስታ የፈኩ መሆናቸውን ገለፀችለት ።

ሳይጣደፍ ረጋ ብሎ መንቀሳቀስ ሲጀምር እርስዋም መልሱን በፍጥነት ሰጠችው ። ጡቶቿ ደረቱን ሲገፋትሩትና በአንገቱና በጉ ንጩ ላይ ቁና ቁና የምትተነፍሰው ሙቅ አየር እንደ ጥሩ ሙቅ ውሃ አስደሰተው ። ዳሌዎቿን ከቂጥዋ ጭምር በእጁ ደግፎ ወደ እርሱ

በኃይል አስጠጋቸው ። በኃይል ሲገባ ሕመም ስለተሰማት የማንቋ ረር ድምጽ አሰማች ። አሁንም ከራስዋ ቀና አድርጐ ፊትዋን ለማ የት እየሞከረ ትኩር አድርጐ ተመለከታት ። በጣም ጨለማ ቢሆንም የኮከቦቹ ብርሃን እየጨመረ ስለመጣ እንደ ጥቁሩ ሰማይ ጥቁር የሆ ኑትን ዓይኖቿን በመጨረሻ ማየት ቻለ ። እንደ ኮከቡ ብርሃን የሚፈ ነጥቁ ይመስሉ ነበር ። በዓይኖቿ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ለማንበብ የሚችል መስሎት ነበር ። ግን አልሆነለትም ።

ከበታቹ ሆና ንቅናቄዋ እንደ እንዝርት መሾር ጀመረ። ቂጧ በሞ ቀው አሸዋ ላይ በስሜት ተንከባለለ ። ሆስነር ጥቅጥቅ ባለው ጨለማ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር በሌላ ቦታ የማይናገረውን ነገር ለእርስዋ ሲያንሾካሹክ የራሱ ድምጽ ተሰማው ። እርስዋም የሚያስደስት መልስ እየሰጪችው ባለችበት ጊዜ ትንፋሽዋ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ማቃሰት ጀመረች ። ሰውነትዋን ኮምተር የሚያደርግ ነገር ወረራት ። ቀጥላም በረጅሙ አቃሰተች ። የሆስነር ሰውነትም ለሴኮንድ ያህል ውጥር ጥር ካለ በኋላ በኃይል ተንዘፈዘፈ ።

አሁንም እንደተቃቀፉ ተጋድመዋል ፤ በላያቸው ላይ የሚያል ፈው ነፋስ የሰውነታቸውን ላብ አበረደላቸው ።

ሆስነር ከእርስዋ ላይ ተንከባሎ በጐኑ ተኛ ። እጁን በጡቶቿ ላይ ሲያደርገው ወደታችና ወደ ላይ ሲሉ ተሰማው ። ይህ በቴል አቪቭ ቢሆን ኖሮ ጥሩ ነበር ። እዚህ ግን ቦታው ባለመሆኑ ጥሩ አልነበረም ። ቢሆንም እንደዚህ እንደ አሁኑ ሊሆን የሚችለው በዚህ ቦታ ብቻ ነበር ። በጦር እቅድና በልዩ ልዩ ሃሳብ ውጥረት ጐን ያፈቅራት እንደ ነበረ ወይም በቅርብ ጊዜ እንደሚያፈቅራት እርግጠኛ ነበር ። ስለላስ ኮብና ስለባልዋ ሊጠይቃት ቢፈልግም የመጠየቂያው ጊዜ አሁን ባለ መሆኑ ለሌላ ጊዜ አስተላለፈው ። ከዚህ ይልቅ እርስዋ ለመስማት የም ትፈልገውን ለመናገር አወጣ አወረደ ። ነገር ግን ምንም ሊመጣለት አልቻለም ። “ ምን እንድነግርሽ ትፈልጊያለሽ ? ” ብሎ ከጠየቃት በኋላ “ ምን እንደምልሽ አላውቅም ” አላት ።

“ ምንም አትበል ” ብላው እጁን ጐትታ በጡቶቿ ላይ አስቀ መጠችው ።

ኮከቦቹ በሰማዩ ላይ እየበረከቱ መጡ ። የኤፍራጥስ ውሃ ቀጭ ኑንና ቀዝቃዛውን የኮከብ ብርሃን አጐላው ። ሆስነር ከሰፊው ወንዝ በሚንጸባረቀው የኮከብ ብርሃን የሃያ ያህል ሰዎች ቅርጽ ያለበት ጥላ በመቃብሩ ዙሪያ ለማየት ቻለ ። ወደ እነእርሱ ተጠግቶ ከኋላቸው ቆመ ። ሚሪያም ለሴኮንድ ያህል በጐኑ ከቆመች በኋላ በመቃብሩ አጠገብ ወደ ቆሙት ሰዎች ሔደች ።

የሙሴ ሔስ አስከሬን ወደ መቃብሩ ተንሸራቶ ገባ ። ቄሱ ለሙታን የሚፀለየውን ጸሎት ጮኾ ሲናገር ከቁልቁለቱ በታች በወንዙ ባሻገርና በጭቃማው ሜዳ ላይ ይሰማ ነበር ።

ቤከር መቃብሩን ከበው ከቆሙት ሰዎች በስተጀርባ ቆሟል ። ተበሳጭቶ እንደነበረ ሆስነር አስተውሏል ።

ሆስነር ምን ዓይነት እንግዳ ነገር እንደአጋጠማቸው አሰበ ።በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ይሁዳውያን በባቢሎን ተቀብረዋል ። በዛሬው ቀን ደግሞ ሌላ በዚህ መቀበሩ የሚያስገርምና እንግዳ ነገር ነው ። የቄሱ ድምጽ በአዕምሮው ውስጥ ተላወሰ ።"... ጽዮንን ባሰብናት ጊዜ አለቀስን ። መሰንቆችንን በውስጥዋ ባለው ሀያ ዛፍ ሰቀልን . . . " የሚለውን ጥቅስ አስታወሰ ። ሆስነር ግን አንዱን እንኳን ባለማየቱ እነዚያ የሀያ ዛፎች እንደጠፉ አመነ ።

ሚሪያም በርንስቴይን ቀስ ብላ ቄሱን ስለአነጋገረችው ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። በጣም በማይሰማና በለሰለሰ ድምጽ በጨለማው ውስጥ ለተሰበሰበው ሕዝብ " አብዛኞቻችሁ የራቬንስብሩክ ጸሎት ተብሎ የሚጠራውን ታውቃላችሁ " ብላ መናገር ጀመረች ። የተጻፈው በአንድ ስሙ ባልታወቀ ደራሲ ሲሆን እስር ቤቱ ነፃ ከወጣ በኋላ በአንድ ቁራጭ ወረቀት ተጠቅልሎ የተገኘ ነው ። ስለሰላም ለመወያየት በባቢሎን ፣ በኢየሩሳሌም ወይም በኒውዮርክ ውስጥ እንሁን በዚህ የመቃብር ሥርዓት ላይ በዛሬው ቀን ይህን መስማት ትክክል ነው " ከአለች በኋላ አፏን ወደከፈተው መቃብር በመዞር አጕንብሳ መናገር ጀመረች ።

እኩይ ሃሣብ ላላቸው ሰዎች ሰላም ይውረድ ፤
ለበቀልም ሁሉ የመጨረሻው ፍፃሚ ይሁን ፤
ስለ ቅጣትና ስለ ግሳጼ የሚነገረውም ያክትም ።
ክፋት የቆየ ወግንና ሥርዓትን ያነውራል ፤
ከሰብአዊ አስተሳሰብ ውጭም በመሆኑ ፤
ክፋት ለብዙ ሰዎች መስዋዕትነት ምክንያት ይሆናል ።
ቢሆንም እግዚአብሔር ሥቃያቸውን በእናንተ የፍርድ ሚዛን አይመዝነውም ፤
እናንተ ክፋትን በክፋት እንደምትመለከቱት እሱ አያየውም ፤
እንዲያውም ትክክለኛ በሆነ መንገድ እንጂ ።
ይልቅስ ስለቀታሊዎች ፤ ከሐዲዎችና ሰላዮች በጐ በጐውን ጻፉ ፤
እንዲሁም ለመጥፎ ሰዎች ሁሉ ተገቢውን አድርጉላቸው ፤
ለሌሎች ሰዎች የሕይወት ብርታትና ጥንካሬ ምክንያት እንደሆኑ ሁሉ ።

ይህን በስሜት የተሞላ ጸሎት በምትናገርበት ጊዜ የሚርያም ድምጽ ተርገበገበ ። ወደ መጨረሻው እየተቃረበች ስለመጣች ድምጽዋም ጥንካሬ ለገኘ ።

መመዘን ያለበት በጉ በጉው እንጂ መጥፎው መሆን የለበትም ፤
በጠላቶቻችን አሰምር ውስጥ ፡
እኛ ተጠቂዎቻቸው ሆነን መኖር የለብንም ፡
በቅዠታቸውና በብዥብዥታዊ መናፍስታቸው ውስጥም መገኘት አይኖር ብንም ፡
ይልቁንም ረዳቶቻቸው መሆን ይገባናል ፤
እነርሱም ቁጣቸውን ሊያቀሙ ይችሉ ዘንድ
ከእነርሱ የሚፈለገውም ይኸው ብቻ ነው ፤
ይህ ከሆነ በኋላ ፡
እኛም በሰዎች መካከል እንደሰዎች ሆነን እንኖራለን ፤
በዚች ምስኪን ዓለም ላይም እንደገና ሰላም ይሰፍናል ፤
መልካም ለሚያስቡ ሰዎች የሚመጣው ይህ ሰላም ፤
ለሌሎችም ሊሆን ይችላልና ።

ሆስነር የሚሪያምን የመጨረሻ ንግግር የሰማው በከፊል ነበር ። የማይረባ ጸሎት ነበር - ካሉበት መከራ ሊድኑ ከቻሉ በቀልንና ጥላቻን በልባቸው ይዘው ለሚኖሩ ሰዎች አደገኛ ጸሎት ነበር ። ሚሪያም ፤ መቼ ይሆን የምትማረው ?

የመቃብሩ ሥነ ሥርዓት እንደተፈጸመ ከሆስነር በስተቀር ሁሉም ሔዱ ። ከኤፍራጥስ ባሻገር ፡ ከሩቅ ባለው ጥቁር ጭቃማ ለጥ ያለ ሜዳ ባሻገር ፡ በጣም በሩቅ ያለውን ጥቁር ከፋይ የሚመስለው ሰማይና ጥቁር አድማስ የተገናኙበትን ፡ ከዚያም አርቆ ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ ተመለከተ ። የጥንታዊቱን የኢየሩሳሌምን ከተማ መብራቶች ያየ መስለው ። ያየው ግን በአድማሱ ላይ የሚጠልቀውን ኮከብ ነበር ። ኮከቡ ተሰወረ ። በዚያ ደቂቃ ወደ ቤቱ እንደገና ተመልሶ እንደ ማይሔድ አወቀ ።

# ክፍል ሦስት

## ባቢሎን ፡ የኢሽታር በር

ከባቢሎን ውጡ ከከልዳውያን ኮብልሉ ።
በእልልታ ቃል ንገሩ ይህንንም አሰሙ ወደ ምድር ዳር አውሩ በሉም ።
እግዚአብሔር ባሪያውን ያዕቆብን ተበጀ ።
አልተጸሙም በምድረ በዳ በመራቸው ጊዜ
ከደንጊያ ውሀ አወጣላቸው ድንጊያውንም ሰነጠቀው
ውሀም አፈለቀ ።

ኢሳያስ 48 ፡ 20 - 21

## —21—

የመቃብሩ ሥነ ሥርዓት እንደተፈጸመ ቶሎ ተመለሱ ። አካሔዳቸው ግን እንደትናንትናው ማታ አንድ ጋር ሆነው ግር በማለት ሳይሆን በሦስት ፣ በስድስትና በዘጠኝ እየሆኑ ነበር ። ከአንዱ ተገንና መደበቂያ ወደ ሌላው በጸጥታና በፍጥነት እየተሹለከለኩ ሔዱ ። ትናንትና ማታ ለአካባቢው እንግዳ በመሆናቸው ችግር አጋጥሟቸው ነበር ። አሁን ገን መንገዳቸውን እየመረጡ ያለችግር መሔድ ችለዋል ። ጉርፍ በቀደደው ቦይ ውስጥ እንደ እባብ እየተሳቡና እየዳሁ ወደ ተራራው ጫፍ ላይ ደረሱ ። የተሰጡ ትዕዛዞች ሁሉ በጉዞአቸው ላይ በሚገባ ተከብረዋል ። ትእዛዝ ያልፈጸመ በሞት እንዲቀጣ መወሰኑን ያላስታወሰ አልነበረም ።

አህመድ ሪሽ ከመቶ አለቃ ሳሌም ሀማዲ ጋር ሆኖ ወደፊት ከሚገሰግሱት ወታደሮቹ ትንሽ ወደ ኋላ ራቅ ብሎ መምጣት ጀምሮአል ። ሁለቱም ይህ የመጨረሻ ጥረታቸው እንደሚሆን አውቀዋል ። በውጊያቸው ላይ ውጤት አልባ ቢሆኑ የሚጠብቃቸው ውርደት የከፋ ከመሆኑ የተነሳ በመጨረሻ በራሳቸው ሰዎች መገደል ወይም በሌሎች ፍልስጥኤማውያን ለፍርድ ቀርበው የሞት ቅጣት መቀበል ነበር ። ከሁሉም መጥፎው ደግሞ ሕይወታቸውን ሙሉ በእስራኤል የጸጥታ ክፍል መታደናቸው ፤ ምናልባትም ቀሪው ሕይወታቸውን በራምላ ወህኒ ቤት ውስጥ ማሳለፍ ሊሆን ይችላል ። በሀሳባቸው ግን የጸጥታው ኃላፊ ይስሐቅ በርግ በሙዳፋቸው ውስጥ እንደ ወደቀላቸው በመቁጠር እንደዝና ፤ ዕድልና ክብር አድርገው ቆጥረውት

ነበር ። ለሪሽና ለሀማዲ ይህ ምሽት ለሕይወታቸው ዘለቄታ ሁሉ እጅግ አስፈላጊ ነበር ። ሪሽ ነፋሱ የአቧራ አዟሪት ሠርቶ ሲመጣ ብት ዓይኖቹን ሸፍኖና አፉን ወደ ሀማዲ ጆሮ አስጠግቶ “ ጥን ታዊ አማልክት ከእኛ ጋር ናቸው ፤ ፓዙዙ ይህን ነፋስ ላከልን”አለው።

ሀማዲ ነፋሱ ለማንኛው ወገን እንደተላከ እርግጠኛ አልነበረም ። ወደ አፉ የገባውን አሸዋ ተፍቶ አጉረመረመ ።

* * *

ናታን ብሪን ዓይኖቹን አሻሽቶ እንደገና ከተመለከተ በኋላ የመ መልከቻ መነጽሩን ዘጋው ። አጠገቡ ተቀምጣ የነበረችውን ናኦሚ ሀበርን አቅፎ “ ከፀሐይ ጥልቀት ጀምሮ ያየሁበት ዓይኔ ፈዘዘ ” ብሎ ጠመንጃውን በጐኑ ባለው ዲብ አጠገብ አስቀምጦ “ ይኸው ተመ ልከች ” አላት ።

ናኦሚ ጸጉሩን እየደባበሰች በግንባሩ ላይ የነበረውን ላብና ቆሻሻ ጠረገችለት ። ለሰዓታት አብረው በሥራ ላይ መቆየታቸውና ወደፊ ትም ለብዙ ጊዜ ለመኖር የነበራቸውን ዕድል አለማወቃቸው ተደ ምረው ሊቋቋሙት ያልቻሉት ሁኔታ ሰውነታቸውን ነዘራቸው ። በቴል አቪቭ ውስጥ በአንድ ቡና ቤት እርሱን ሁለት ጊዜ ለማየት የሚያስችል ዕድል እንደሚኖራት ተጠራጠረች ። አሁን ግን የሚገኙት ብባቢሎን ውስጥ ነው ።

ወሲባዊ ግንኙነታቸውን በፀሐይ ጥልቀትና በመቃብሩ ሥነ ሥርዓት መጨረሻ መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ እንደ ሆስነርና በር ንስቴይን በችኮላ ቢያደርጉትም የበለጠ ጭንቀት ፈጥሮባቸዋል ።የግ ብረ ሥጋ ፍላጐታቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ መዓት የመጣባቸው እየመሰላቸው ሰውነታቸው ይሸበር ነበር ። አካባቢያቸውን መመል ከቱን ለጊዜው አቁመው ነበር ። በመጨረሻም በሠሩት ሥራ ሁለ ቱም ሳቁ ። ይህን ያደረጉት ግን አሸባሎቹ በዚያ የመገኘት ዕድላ ቸው ይህን ያህል ባልሆነበት ጊዜ ነበር ። አሁን ግን ልብሳቸውን ለብሰዋል ፤ የውጊያው ፍርሃትም ጠንካራ ሆኗል ።

ናኦሚ መነጽሩን በዓይንዋ ላይ አድርጋ ተመለከተች ። ይህ ከማ ነጣጠሪያው በጣም የተለየ ነበር ። በዚህ የሚንቀሳቀሰውን ሳይቀር ያለስህተት መምታት እንደምትችል አመነች ። ይሁን እንጂ እን ደዚህ ወጣ ገባ በበዛበት ቦታ ላይ የትኛውን ኢላማ እንደምትመርጥ አታውቅም ። የመሬቱንም አቀማመጥ በጨለማ ጊዜ ገና አልተለማ መደችውም ።

“ ያየሽው ነገር አለ ? ” ብሎ ብሪን ጠየቃት ።

“ ከዚያ መጥፎ ነፋስ በስተቀር ሌላ የለም ” አለችው ።

" አውቃለሁ " አላት ብሪን ። ሸርጂ የተባለው ነፋስ አቧራ ውን ወደ ላይ እያጥመለመለ በመሬቱ ላይ የሚጥለው ጥላ በሚገባ ተለይቶ ሊታይ የሚችለው በኃይለኛው መነጽር ነው ።

በውስጥዋ ተራግማ ጠመንጃውን ለብሪን በመመለስ " በዚህ ጥሩ አይደለሁም " አለችው ።

ብሪን አጉልቶ የሚያሳይ መነጽር የተገጠመበትን ጠመንጃውን ወደ ሰማይ አድርጐ ሌየሩ የት እንዳለ ከማየቱ በፊት ለሦስት ደቂቃ ዎች ያህል አሻቅቦ ተመለከተ ። ሌየሩ የነበረበት ከፍታ ከሁለት ኪሎ ሜትር እንደማያንስ ገመተ ። ሆስነር ሌየሩን በሚያይበት ጊዜ መትቶ እንዲጥለው የነገረው ቢሆንም በእርቀቱ የተነሳ ቢተኩስም ጥይት ከማባከን በስተቀር ፋይዳ እንደማይኖረው ተገነዘበ ። የመነጽሩን ባትሪ አጥፍቶ በመቀመጥ ሲጋራውን አቀጣጠለ ።

አሸባሎቹ ከአንዱ የመሸሸጊያ ቦታ ወደ ሌላው በፍጥነት እየተ ሹለከለኩ አለፉ ። እስራኤሎቹ ከሩቅ የመመልከቻ መሣሪያዎችና መምጣታቸውንም የሚያሳውቁ ምልክቶች እንደአሉአቸው አሸ ባሎቹ አውቀዋል ። በተጨማሪም ተኩስ ቢከፈትባቸው እንኳን ወደ ኋላ እንዳይመለሱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል ። በጸጥታና በፍ ጥነት የመሮጥ ልምድና ዘዴ ቢኖራቸው ኖሮ እስራኤሎቹ ለመከላከያ በሠሩት ጉድባና ቦይ ውስጥ በደቂቃ ለመድረስ ይችሉ ነበር ።

ሁለት ሰዎች ያሉበት የደፈጣ ተዋጊ ቡድን አሸባሎቹ ከነበሩ በት ቀድሞ ወደፊት እንዲሔድ ተደርጓል ። ከተላኩት ውስጥ አንዱ አምናህ ሙራድ የሚባለው በሩሲያ ውስጥ የተሰራ አጉልቶ የሚ ያሳይ ልዩ መሣሪያ ይዟል ። ሙራድ በሚንቀሳቀስበት ሁሉ መሳ ሪያውን በጥንቃቄ አቅፎ በመያዝ ነበር ። ሌላው ሰው ሞኒኤም ሳፋር የሚባል ሲሆን አንድ ኮምፓስና አንድ ኤኬ - 47 ጠመንጃ ይዟል ። ሙራድና ሳፋር ከአምስት ዓመት ዕድሜአቸው ጀምረው ያልተለያ ዩና አብረው የሰለጠኑ ነበሩ ። ከወንድማማች የበለጠ ይቀራረባሉ ። በጣም ከመቀራረባቸው የተነሳ አንዱ ሌላውን ይጠብቀው ነበር ። በቃላት ሳይጠቀሙ በመንካት ፣ ቅንድብን በመሰብሰብ ፣ አፍን በማላወስና በመተንፈስ ይግባባሉ ። ከሰዓት በኋላ ከበረሃው የጦር ሠፈራቸው በሌየሩ አሁን ወደ አሉበት ቦታ መጡ ።

ሁለቱ ሰዎች የእስራኤሎቹ አጉልቶ የሚያሳየው መሳሪያ አለ ብለው ወደ ጠረጠሩበት ቦታ ኮምፓሳቸውን በማስተካከልና በኮ ምፓሱ በመመራት ጉዞአቸውን ቀጠሉ ።

ሁለቱ ወጣት ሰዎች አሻቅበው ዳገቱን ሲመለከቱ አልፎ አልፎ በኮከቦች በተንቆጠቆጠው ሰማይ ሥር ጥቁሩን ጉብታ አዩ ። እር

ቀ ቱም አሁን ካሉበት 500 ሜትር እንደሚሆን ገመቱ ። ሙራድ በጨ ለማ አጉልቶ የሚያሳየውን መሳሪያውን ካስተካከለ በኋላ ተንበርክኮ ሲመለከት ቦታውንለማየት ቢችልም የእስራኤሎቹን በዚያ መኖር ማየት አልቻለም ። ጠመንጃውን በአንድ አባጣ መሬት ላይ አጋድሞ በሆዱ በመቶኛት እየተመለከተ ተዝናና ።

* * *

ቁጥር ሁለት የጦር ሠፈር በቁልቁለቱ መሐል ከወንዙ 500 ሜትር ያህል እርቀት ባለው ጉብታ ላይ ነበር ። የሚጠበቀው የእስራኤል ምክር ቤት አባል በሆነው በይጋልቴኮና በጸሐፊው በደቦራህ ጌዲዮን ነው ። ቴኮ በመጀመሪያ በፊት ለፊቱ ቀጥሎም በስተግራው በኩል አንድ የሚያስፈራ ነገር የሰማ መሰለው ። የጸሐፊውን ትከሻ በእጁ በመንካት " እንደሚመስለኝ ከበውናል " በማለት በጆሮዋ ሹክ አላት ።

በጨለማው ውስጥ ራስዋን በአዎንታ ነቀነቀች ። ድምጽ እንደ ሰሙ በጣም ፍርሃት ተሰማቸው ። በጠላት በስተኋላ በኩል በመሆና ቸው አምልጠ ለመሔድ የሚያስችል መንገድ የላቸውም ።

በትክክለኛ የወታደራዊ ሕግ መሠረት የድምጽ ማጉሊያ መሣ ሪያ ፣ በጨለማ ለማየት የሚያስችል መሣሪያ ፣ ጠመንጃዎች ፣ ራዲ ዮኖች ወይም ከዋናው የጦር ሠፈር ጋር የሚያገናኝ የመስክ ስልክ መኖር እንደነበረበት ቴኮ አውቋል ። እዚህ ግን የጦር ሠፈሩ ራስን ለማጥፋት ግዴታ እንዳለ ዓይነት በመሆኑ ለመሰዋት የቀረቡ በጐች ሆኑ ። አሁንም ቢሆን ለሦስቱ የጦር ሠፈሮች ስድስት በራሳቸው ፈቃ ደኞች የሆኑ ለማግኘት ችግር የለም ።

ቴኮ ሌሎች እንዲነቁና እንዲዘጋጁ ባለማድረጉ ከፍተኛ ሽን ፈት ተሰማው ። በእስራኤሎቹ በኩል ምንም የተኩስ ድምጽ ባለመ ስማቱ አሸባሪዎቹ ውጤታማ አደጋ እንደሚጥሉ አወቀ ። በዚህ ዓይ ነት አንድም ጥይት ሳይተኮስ የእስራኤሎቹን ቦታ ሊወሩ ይችላሉ ።

" ጩኸት በማሰማት ማስጠንቀቂያ መስጠት አለብኝ ።"

ደቦራህ እንደ ትንሽ ጥንቸል ኩርትምትም ብላ ቀረች ።

" አዝናለሁ ፤ እኔ ግን ማድረግ አለብኝ " አላት ።

ከመብረክረክዋ እንደመጽናናት ብላ ጉንጩን በመንካት " በእ ርግጥ መጮኸ አለብህ " አለችው ።

ቴኮ በቅርብ የሰው ኮሽታ ሰማ ። አፉን አፍኖ ይዞ በቀበሮ ጉድጓዳቸው ውስጥ በግርግዳው ተለጥፎ ቆመ ።

ድምጽ እንዲሰጡ ቆርቆሮዎችና እንደቃጭል ያሉ ብረቶች የተ ሰቀሉበት ሽቦ አንደኛውን አሽባል አደናቀፈው ። ጸጥ ባለው አየር ውስጥ ተንኳኩ ። ነገር ግን ከአካባቢው የወገኖች እንቅስቃሴ ባለ መስማቱ ቴኮ ከፍተኛ ሀዘን ተሰማው ።

ብሪን ኤም - 14 ጠመንጃውን አፈፍ አድርጐ በመያዝ ማነጣጠ ሪያውን አስተካክሎ መመልከት ጀመረ ። ነገር ግን በቁልቁለቱ ላይ የሚንቀሳቀስ ምንም ነገር አልነበረም ።

የአቧራና የደመና ጥላ እንቅስቃሴ እንኳን አልታየም ። እስራ ኤሎቹ በክልላቸው ዙሪያ በአለው መከላከያቸው ምንም ድምጽ አል ሰሙም ። ከቁልቁለቱ በአሻገር አረቦቹም እንደዚሁ ያለ እንቅስቃሴ ቦታቸውን ይዘዋል ። ብሪን በገመድና በሽቦ ላይ ለማስጠንቀቂያ የተ ሰቀሉት ቆርቆሮዎች የሚንኳኩት በነፋስ ወይም በእንስሳ ወይም በናዳ ይሆን በማለት አሰበ ። የዚህ ዓይነት ሁኔታ ቀኑን ሙሉ ለብዙ ጊዜ ስለተሰማ አዘናግቶአቸዋል ። ብሪን ቢዝናናም መመልከ ቱን አላቋረጠም ።

* * *

ሁለቱ የደፈጣ ገዳዮች በተጠንቀቅ ላይ ሆነዋል ። ሙራድ ወንዙ ሳይቀር ለመመልከት አመቺ የሆነውንና የእስራኤሎቹ መመልከቻ ይሆናል ብሎ ወደ ገመተው ጉብታ በጥንቃቄ ተመለከተ ። የእስራኤ ሎቹ የብርሃን ኮከብ መነጽር አረንጓዴ ቀለም ያለው ስለነበረ ሲንጸ ባረቅ ታየው ። የአሜሪካ የኮከብ ብርሃን ተብሎ የሚጠራው በጨለማ የሚያሳየው በጠመንጃ ላይ የሚሰካና በባትሪ የሚሠራ መሆኑን ለማ ወቅ ቻለ ። የአሜሪካኑ የተሻለ ቢሆንም አረንጓዴ ቀለም ባለው የሚጠቀመው ተኳሽ ቀይ ቀለም ባለው ከሚጠቀመው ተኳሽ የተ ሻለ ነው ማለት አይደለም ። በዚህ ምክንያት ሙራድ በራሱ ላይ እምነት አደረበት ። በአረንጓዴው ቀለም ላይ አስተካክሎ በማነጣጠር የሰውየው ራስ እስኪታየው ድረስ ጠበቀ ።

ብሪን በዲቡ ላይ ከፍ ብሎ በመውጣት ለናኦሚ ሀበር “ እስከ አሁን ድረስ ምንም እንደ አላየሁ መንገር ትችያለሽ ” ብሎ በሹክ ሹክታ ነገራት ።

ናኦሚ ራስዋን በአዎንታ አነቃንቃ ድምጽ ሳታሰማ በባዶ እግ ርዋ ወደ ዋናው ትዕዛዝ ማስተላለፊያና መቆጣጠሪያ የጦር ሰፈር ሄደች ።

ሙራድ የብሪንን ራስ ስለአየ በተከታታይ ሦስት ጥይቶች ድምጽ በሌለው ጠመንጃ ተኩሶ የብሪንን ግንባር በረቃቀሰው ። ብሪን ወደ ኋላው ፍንግል ብሎ በአቧራው ላይ ሲወድቅ መሳሪያው ከሥሩ አረፈ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አሸባሎቹ ወደፊት ገሰገሱ ። ሌላ ሰው ሽቦውን ስለነካው አሁንም ቀርቀሮዎቹ ተንኳኩ ።

በዋናው የትዕዛዝ ማስተላለፊያና መቆጣጠሪያ ሠፈር ሆስነር ከዶብኪንና ከበርግ ጋር ቆሟል ።

ናኦሚ ሀበር በጨለማው ውስጥ ዋናውን የጦር ሰፈር ለማግኘት ብትቸገርም በመጨረሻ ስለአገኘችው ለሦስቱ ሰዎች የተላከችውን ነገረች ።

ሆስነር ለማስጠንቀቂያ በሽቦ ላይ የተንጠለጠሉት ቀርቀሮዎች እንደገና ድምጽ ሲሰጡ ቢሰማም ሌላ ነገር አላየም ፤ ወይም አልሰ ማም ። ወደ ሀበርና ሌሎች ሁለት ወጣት ሯጮች ዞሮ “ ወደ መከ ላከያ መስመራችን ሂዳችሁ የእኔን ፊሽካ ሲሰሙ ለአስር ሴኮንድ እሩምታ እንዲተኩሱ ንገሩአቸው ” አላቸው ።

ሯጮቹ በልዩ ልዩ አቅጣጫ ሄዱ ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሆስነር ፊሽካውን ስለነፋ የሰሙት እሩምታ መተኮስ ጀመሩ ። ይህ ሌሎቹም ተኩስ እንዲጀምሩ ምልክት ሆና ቸው ።

አሸባሎቹ ደንግጠው በመሬቱ ላይ ተነጠፉ ። ጥቂቶቹ ቢመቱም አለቆቻቸው አንቀው እንዳይገድሏቸው በመፍራት የሕመም ድምጽ እንኳን አላሰሙም ። የበላይ አለቆችና የበታች ታዛዦች እንዳይተ ኩሱ ጭንቀት የሞላበት ሹክሹክታ አሰሙ ። “ ከጠላት በኩል ለማ ወቅ የተተኮሰ ስለሆነ አጸፋ እንዳትሰጡ አሏቸው ጥርሳቸውን ገጥመው። አንድ ሴኮንድ አልቆ ሌላው ሲተካ ዓመት መሰለ ። በአምስት እስራ ኤላውያን ቢኤኬ - 47 ጠመንጃዎች አቆልቁሎ የተተኮሰው ጉበዞቹ ሳይቀሩ ለሕይወታቸው እንዲፈሩ አደረጋቸው ። አንድ ወጣት የአ ጸፋ ተኩስ ለማድረግ ሲቃጣ የእስራኤሎቹ እንደ አጀማመሩ በአንድ ጊዜ ቆመ ። ለአሥር ሴኮንድ የተተኮሰው እሩምታ የቆመው ጥይት ለመቆጠብ ሲባል ነበር ።

የተተኮሰው ጥይት ባሩድ ሽታ ከምሥራቅ በኩል በሚነፍሰው ነፋስ ተወሰደ ። በመጨረሻም የተተኮሱት ጥይቶች ጩኸት ተራራውን አናግቶ ከተከላካዮቹ ጆሮ ጠፋ ። አሸባሎቹ ያ ሁሉ ሲተኮስባቸውና ናዳ ሲወርድባቸው የአጸፋ ተኩስ አይተኩሱም ወይም ተመትተው

እንደሆነ ጩኸት ሳያሰሙ ሕመማቸውን አፍነው ይይዛሉ ብሎ እንድም ሰው አልገመተም ።

ሆስነር ወደ ዶብኪንና በርግ ዞሮ " እየበረገግን መሰለኝ " አላቸው ።

በርግ " የመቆጣጠሪያና የመልዕክት ተቀባይ ክፍሎች ጉዳት እንደአልደረሰባቸው ተስፋ አለኝ " አላቸው ።

" እያንዳንዱ የተሰጠውን ትዕዛዝ ከፈጸመና ተቆጣጣሪዎቹ ወይም መልዕክት ተቀባዮች እንዲቆዩ በታዘዙበት ቦታ ከቆዩ ምንም ነገር ሊደርስባቸው አይችልም " ብሎ ዶብኪን መለሰላቸው ። ቀጥ ሎም ወደ ም/ሥራቃዊ ቁልቁለት እየተመለከተ " የጦር ሠፈሮቻችን ምንም ነገር ካልሰሙ የሚፈጠር ችግር ይኖራል ብየ አላስብም ። በእ ንስሳዎች ፡ ወይም በነፋስ ፡ ወይም በናዳ ለማንቂያ ቆርቆሮዎች የተ ሰቀሉባቸው ሽቦዎች ሲነኩ ሊንኳኩ ይችላሉ ። በ1967 በስዊዝ ተዘ ርግቶ በነበረው ሽቦ ላይ አንዲት ድንቢጥ አረፈች - ግን ስለስዊዝ ከቁም ነገር የቆጠረው ማን ነበር ? " አላቸው

" ማንም አልነበረም " በማለት ሆስነር አረጋገጠለት ።

ሚካ ጐረንና ሀና ሺሎ-ሁለቱም ጸሐፊዎች የነበሩ-በሰሜን ቁል ቁለት ላይ የሚገኘውን ቁጥር አንድ የጦር ሠፈርና የመልዕክት መቀ በያ ጠባቂዎች ነበሩ ። ተከበው እንደነበረ ያወቁት በጣም ዘግይተው ነበር ። እሩምታው እስኪያበቃ ድረስ በቀበሮ ጉድጓዳቸው ውስጥ ተሸጉጠው ተቀመጡ ። ስለሚቀጥለው እንቅስቃሴያቸው ሲያሰላስሉ በነበረበት ጊዜ ሦስት አሸባሎች የሚያብረቀርቅ ጩቤ ይዘው ዘለው በመግባት መሳሪያ አልባ የሆኑትን ሁለት እስራኤላውያን አረዷቸው።

ሪዩብን ታበርና ሊ ኢልሳር — አስተርጓሚዎች የነበሩ - በደቡ ባዊ ቁልቁለት ጫፍ አቅጣጫ ላይ በነበረው ቁጥር ሦስት የጦር ሰፈ ርና የመልዕክት መቀበያ ጣቢያ ተቀምጠው ይጠብቁ ነበር ። የደረ ሰውን ሁኔታ ስለአወቁ ከጉድጓዳቸው ወጥተው ወደ ተራራው ጫፍ መሄድ ጀመሩ ።

ሙራድ በጫፉ ላይ ቀይ ቀለም ባለው በኮከብ ብርሃን አጉልቶ በሚያሳየው መነጽር ከተጋደመበት 40 ሜትር ያነስ እርቀት ላይ አያ ቸው ። አረቡ አነጣጥሮ ሁለቱንም በመሃል ግንባራቸው ላይ መትቶ አጋደማቸው ።

አሸባሎቹ ቀስ በቀስ ወደፊት መጠጋታቸውን በመቀጠል ከተራራው ጫፍ 300 ሜትር ያህል እርቀት ላይ ደረሱ ።

ቴኮ እሩምታው ለምን እንደነበረና እስራኤሎቹ እስከ አሁን ምንም እንዳላዩ የሚያስረዳ መሆኑን ተገነዘበ ። ወደ ደቦራ ዞሮ "መል ካም ዕድል" ከአላት በኋላ መንጋጭላዋ ላይ ሲመታት በቀበሮው ጉድጓድ ውስጥ በጸጥታ ተጋደመች ። ጉድጓዱን በአፈርና በቅጠላ ቅጠል ከአለበሰ በኋላ ዘሎ በመውጣት ወደ ተራራው ጫፍ ሮጠ ። ሁለት እጆቹን በአፉ ላይ እንደ ፋካ አድርጐ በመያዝ "ከቁጥር ሁለት ቴኮ ነኝ ፣ ቁልቁለቱን አንድም ሳይቀር ወረውታል" በማለት ደጋ ግሞ ጮኸ ።

በአረብ ወይም በእስራኤል በተተኮሰ ኤኬ - 47 ጥይት ተመ ትቶ ወደቀ ። የተኮሰበት የማንኛው ወገን እንደሆነ አላወቀም ፣ ቢያ ውቅም ግድ አልነበረውም ።

አሸባሎቹ ውጊያቸውን ቀጠሉ ። እስራኤሎቹ ለጠላት ማደናቀ ፊያ በሠሩት ቦይ ውስጥ አንዲት ሴት ስትገባ በኃይል ጮኸች ። ግን አልሞተችም ። ጩኸቷ ከተኩሱ የበለጠ ቢሆንም ወደዚያው ዝም አለች ።

እስራኤሎቹ አሸባሎቹ እንደዚያ መቅረባቸውን በመስማታቸው በመጠኑም ቢሆን ሞራላቸው ተነካ ። በየጣቢያዎቹ የተመደቡትን ምን በላቸው ? ማስጠንቀቂያ እንዲሰጡ የተሰሩትስ ምን ሆኑ ? ለማ ስጠንቀቂያ የተደረገው የሩምታ ተኩስ ለምን አልሠራም ? ብሪንና አስደናቂው በኮከብ ብርሃን አጉልቶ የሚያሳየው መነጽር የት ደረሱ ?

ሦስት የአሸባል ተኳሾች ወደ ተራራው ጫፍ ቢያመሩም እስራ ኤሎቹ ለማጥቂያ በሠሩት ጉድቢያ ውስጥ በመግባት አንዱ አንገቱ ላይ ሌላው ደግሞ እደረቱ ላይ ጉዳት ደረሰባቸው ። ሦስተኛው ደግሞ አቤል ጊለር ከሆስነር በወሰደው ኮልት ሽጉጥ ተገደለ ።

ጠላትን ለማጥቃት የተዘጋጀው ወጥመድ የተጠበቀውን ያህል አላገለገለም ። አሸባሎቹ ሳያውቁት በጉድጓድ ውስጥ ሲዘቅጡ ጩኸት በማሰማታቸው ሌሎቹ እንዲጠነቀቁ አደረጋቸው ። ካስ ማዎቹ ከሞቱት ሰዎች ላይ እየተሰኩ በመቅረታቸው ለሚቀጥለው በጥቅም ላይ ሊውሉ አልቻሉም ።

በአሁኑ ጊዜ እስራኤሎቹ አምስት ኤኬ - 47 ጠመንጃዎች አሏ ቸው ። አሸባሎቹ መጀመሪያ ለውጊያ መጥተው ከነበሩት አሁን ቀን ሰዋል ። ይሁን እንጂ አሸባሎቹ ከፍተኛ አድናቆት ያለው ሥራ ሠር ተዋል ። ጆሹዋ ሩቢን ከኡዚው ጋር የት እንዳለ አይታወቅም ። ናታ ንም የኮከብ ብርሃን ካለው ኤም - 14 ጠመንጃ ጋር የለም ። ሁለቱም ምን እንደሆኑ እስከ አሁን አልታወቀም ።

አንድ የአሸባል ቡድን የኮከብ ብርሃን መነጽር በአቧራው ላይ ወድቆ አብረቅራቂ አረንጓዴ ቀለሙን በማየት በአሁኑ ጊዜ ጠባቂ ወደ ሌለው ጉብታ አመራ ።

በየአቅጣጫው አሸባሎቹ እየተጠጉ በመምጣትና በእስራኤሎቹ መከላከያ ድንበር አቅራቢያ በመድረሳቸው በአረቦቹ እየተተኮሰ ከአፈ ሙዙ የሚወጣው ብርሃን ለእስራኤሎቹ እየታያቸው ስለ መጣ ምሽጋቸውን ላለማስያዝ ወደ ግራና ወደ ቀኝ እየተዟዟሩ መተኮስ ነበረባቸው ።

ለአሸባሎቹ ሌላው ውጤት ያስገኘላቸው በዚህ ምሽት ተዋጊ ዎቻቸው የብዙ ጊዜ ልምድ የነበራቸውን ወታደሮች ይዘው መም ጣታቸው ነበር ። ባለፈው ምሽት መጥተው የነበሩት ወጣት ወንዶ ዶችና ሴቶች በጦር ሜዳ ተሠማርተው የማያውቁ ስለነበሩ እስራኤ ሎቹ በወሰዱት የማጥቃት እርምጃ ተደንቀዋል ። የአሁኖቹ በልምድ ካላቸው ጤናማ ፍርሀት በስተቀር ከጠላት በሚተኮሰው ጥይት አልተ ደናገጡም ። ብዙ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ስለተገደሉባቸው ለመበቀል ቆርጠው መጥተዋል ። ከድል በኋላ የእስራኤልን ወንዶ ችና ሴቶች እንደፈለጉ እንዲያደርጓቸው ሀማዲ ቃል ገብቶላቸዋል ። አህመድ ሪሽ ምርኮኞቹን ለማስለቀቂያ ከሚከፈለው ቤዛ ለየግላቸው የሚሆን ከፍተኛ ሀብት ለመስጠት ቃል ገብቶላቸዋል ። ሌላው ካለ ፈው ሌሊት የነበረው ልዩነት በሀማዲ የተደረገው መንፈስ የሚያነ ሳሳና የሚያጠናክር ንግግር ነበር ። አሁን እያንዳንዱ ለምን እንደሚ ዋጋ እንዲያውቅ ተደርጓል ።

የሆስነር ሰው የሆነው ጃፍ ከመከላከያ ጉድጓዱ ወጥቶ ካስማ ከተሳገባቸው ሰዎች ላይ ኤኬ - 47 ጠመንጃዎች ለማምጣት ሔዶ ጠመ ንጃዎቻቸውን ወደ ክልላቸው ወርውሮ ለመመለስ ሲሞክር ስለተ መታ በዳገቱ ላይ ተንከባለለ ። ሌላው የሆስነር ሰው ማርከስ በአቤል ጊለር ከተገደለው አሸባል ላይ አንድ ኤኬ - 47 ጠመንጃና ጥይቶች ገፎ አመጣ ።

አሁን በተጨማሪ ያገኙአቸውን ሦስት መሣሪያዎች በዶብኪን ለሰለጠኑ ሁለት ወንዶችና አንዲት ሴት ታደሉ ። አልፎ አልፎ በጦ ርነት ጊዜ ወደፊት ከመግፋት ተቆጥቦ ማፈግፈግ በሚደረግበት ጊዜ የበለጠ ጉዳት እንደሚደርስ የታወቀ ቢሆንም አሸባሎቹ ወደፊት በመግፋታቸው ወደ ተራራው ጫፍ እየተቃረቡ መጡ ።

እስራኤሎቹ ከነበሩበት ቦታ ፊት ለፊት ያለውን መሬት በመ ደልደልና ጉብታዎቹን በማስተካከል ቁልቁለቱን ግልጽ አድርገው ታል ። ይሁን እንጂ አሸባሎቹ በጣም ስለተጠጉና የተሻሉ መሣሪያ

ዎችና እጅግ በጣም ብዙ ጥይቶች ስለነበሯቸው በተራራው ላይ በሚ ገኘው የእስራኤሎች ምሽግ ላይ ጥይት በማርከፍከፍ እሚይዙበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ አስችሏቸው ነበር ። ተከላካዮቹ ራሳቸውን በምሽጋቸው ውስጥ በመቅበር ለአጸፋ ተኩስ አይቻኩሉም ነበር ። ራሳቸውን ከምሽጋቸው በዘዴ ብቅ እያደረጉ ባዩ ቁጥር ከጠላት አፈ ሙዝ የሚወጣውን የተኩስ ብልጭታ ካለፈው ጊዜ አሁን እየተጠጉ መምጣታቸውን አዩ ። በጊዜያዊ ምሽጉ ላይ ጥይቶች ሲወርዱበት መጠነኛ የአፈር መንሸራተት ከማድረሱም በላይ በግድግዳዎቹ ላይ የተበሳሱ ቀዳዳዎች ነበሩ ። በጠላት ዓይን ላይ እንዲያብረቀርቁ ተሠ ርተው የነበሩት አሉሚኒየሞች ከተሰቀሉበት እየረገፉ ወደቁ ። ከኮ ንኮርዱ ላይ እየተገነጣጠሉ ለመከላከያ የተገጣጠሙት ብረቶች በብዙ ሺህ ጥይቶች ከተመቱ በኋላ እየነተቡና እየተቀዳደዱ መጡ ። ለማደ ናቀፊያ ከአሉሚኒየም የተሠሩት ካስማዎች በጥይት እየተነቃቀሉ ስለ ወደቁ ምሽጉ እየተራቆተ መጣ ። በጦርነቱ ላይ ተሠማርተው የማያ ውቁት እስራኤሎች በጥቂት መሣሪያዎች ተኩስ ምን ያህል ጥፋት እንደሚያደርስ በማየታቸው መደነቃቸውን መደበቅ አልቻሉም ።

ሆስነር ፣ በርግና ዶብኪን በእዝ ቦታቸው ላይ ቆመው ከሯጮቹ ሪፖርት ተቀበሉ። ዶብኪን አሸባሎቹ የተራራውን ጫፍ ለመያዝ እንደ ሚፈልጉና በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ወደ ተራራው ጫፍ እንደሚ መጡ አወቀ ። እጁን በሆስነር ትከሻ ላይ አድርጐ “ እኔ እዚሁ እቆ ያለሁ ” አለው ።

ሆስነር ከትከሻው ላይ ክንዱን በኃይል ገፍቶ “ አሁን ትሔዳለህ ጄኔራል ፤ ይህ ደግሞ ትዕዛዝ ነው ” አለው ።

ዶብኪን ድምጹን ከፍ አድርጐ “ ስማ - አንተ አሁን በዚህ የወታደር አዛዥ ያስፈልግሃል ። ከአሁን በኋላ እርዳታ ለማግኘት የእኔ መሔድ ፋይዳ አይኖረውም ” አለው ።

“ ልክ ነው ፤ ሁሉም አልቋል ፤ እዚህ የተሻለ ሰላም ያለ በሚ መስልበት ጊዜ ለመሔድ ፈቃደኛ ነበርክ ። ስለዚህ አሁንም ራስ ህን ለማዳን እንድትሔድ እፈልጋለሁ ። ከሞት የሚተርፉትን ሰዎች በምርኮኝነት እዚህ መኖራቸውን የሚነግር ሰው እፈልጋለሁ ። ይህም ተስፋ ስለሚያሳድርባቸው መሔድ አለብህ ። ስለዚህ አንተ አሁኑኑ ሒድ” አለው ሆስነር ።

ዶብኪን ግን አቅማማ ።

“ ሒድ ” ብሎ ሆስነር ጮኸበት ።

ሰርግ “ ሒድ ቤን 1 በዓለም ውስጥ እጅግ በጣም ስመጥር የሆነ አዛዥ ከዚህ ሁኔታ ሊያድን አይችልም ። ሁኔታው በወታደሮችና በእግዚአብሔር እጅ ነው ። ስለዚህ ሒድ ” አለው ።

ዶብኪን ዞሮ ከጉብታው ላይ ዘሎ በመውረድ ለአንድም ሰው አንድ ቃል እንኳን ሳይተነፍስ መከለር ወደሚጠብቀው ምዕራብ ቁል ቁለት ሔደ ።

በምሥራቅ ቁልቁለት በኩል ጠመንጃና ሽጉጥ አልባ በሆኑ ሰዎች የሚጠበቀውን ለመቆጣጠር ሁለት አሸባሎች በተጠጉ ጊዜ ዳንኤል ጃኮቢና ራሄል ባኡም ከአሉሚኒየም የተሰሩ ጦሮች በመወርወር የማ ስጠንቀቂያ ጩኸት አሰሙ ። አሸባሎቹ ከተጋደሙ በኋላ ተኩሰው ሁለቱንም መቷቸው ። አሸባሎቹ ለመከላከያ የተተከሉትን ካስማ ዎችና የተቆፈሩትን ቦዮች ሰልተው በማለፍ በእስራኤሎቹ ክልል ውስጥ ገቡ ።

የጽጥታ ሠራተኛ የነበረው አልፐርን ኤኬ - 47 ጠመንጃ እንደ ያዘ ሮጦ ወደ መስመሩ ሲወርድ ሁለቱ አሸባሎቹ በቦዩ ውስጥ ወድ ቀው ገቡ ። አልፐርንም ዘሎ ወደ ቦዩ በመግባት በእጅ በሰሩት ጦር ሁለቱንም ገደላቸው ። ሁለት ሰዎች ዳንኤል ጃኮቢንና ራሄል ባኡሙን ተሸክመው ወደ እረኛው ጉጆ ወሰዷቸው ። አልፐርን ያል ታጠቁ ሁለት ሴቶች ጠርቶ ከአሸባሎቹ የወሰዳቸውን ጠመንጃዎች ሰጣቸው ። ይህ ዕድል አሁን ቢያጋጥማቸውም በ1973 ጦርነት ላይ ተካፋይ የነበረው አልፐርን በመጨረሻ ያቀዱት የመከላከያ ስልት ከከሸፈ የሁሉም ነገር መጨረሻ እየተቃረበ መሆኑን ተገነዘበ ።

## —22—

ካፒቴን ዴቪድ ቤከር በኮንኮርድ 02 በአውሮፕላኑ ነጂ ክፍል ውስጥ በወንበሩ ላይ ተቀምጦ የመጨረሻ ሲጋራውን አቀጣጠለ ። በአሜሪካ ስለአሉት ልጆቹና ስለአዲሲቱ እስራኤላዊት ሚስቱ አሰበ ። ራዲዮኑ ከፍተኛ ጫጫታ ቢያሰማም እርሱ ግን ያላጤነው መሰለ ። አልፎ አልፎ አውሮፕላኑን ጥይት ይመታው ስለነበር የውጭ ልባሱ ሲወድቅ ድምጹ ይሰማ ነበር ። ጥቂት ፍንጣሪዎች በአውሮፕላኑ ክፍል ውስጥ አረፉ ። የአውሮፕላኑን ነጂ ክፍል መስኮቶች ሁለት ጥይቶች ሸንቁረው ሲገቡ መስታዎቶቹ እንደሸረሪት ድር ብትንትን ብለው ተሰነጣጠቁ ። ቤከር ሲጋራውን አጥፍቶ በወለሉ ላይ ጣለው። ረዳት ኃይል መስጫውን ለማጥፋት እጁን ከዘረጋ በኋላ ላቀዱት ጉዳይ

መቆየት እንደነበረበት አስታወሰ ። ትክሻውንም አነቃነቀ ። በዓለም ውስጥ ያለ ዘዴኝነትና ብልህነት በመንጋ ከተሰለፈ ቡድን አንጻር ምንም ትርጉም አይሰጥም - መንጋ ቡድን - በኮርያ ጦርነት ጊዜ የአሜሪካን እግረኛ ጦር ቀልድ ነበር ። የቻይና ቡድን በሦስት መንጋ ከሚተራመስ ሕዝብ የተሰበሰበ ነበር ። የመንጋው ቡድን የሰለጠነውን ዓለም እያሸነፈው ነበር - ቀስ በቀስ - እንደ ሮማ አወዳደቅ ። ለመሔድ ተነሳ ።

ራዲዮኑ ከትንሽ ጊዜ ጸጥታ በኋላ ጥዝ አለ ። ባልተጣራ እብራይስጥ በመናገሪያው ውስጥ ድምጽ ተሰማ ። ፍጥነት ባለው አነጋገር “ እጅህን ስጥ ፤ ሆስነር እጁን እንዲሰጥ ንገረው ” የሚል ሰማ ። ራዲዮኑ በሴኮንድ ውስጥ ተመልሶ እንዲንጫጫ ተደረገ ። ቤከር “ አመዳም ” ብሎ ከነበረበት ክፍል ወጥቶ ከሚዋጉ ወገኖቹ ጋር ለማበር ሔደ ።

* * *

አብረቅራቂ አረንጓዴ ቀለም ያለው የኮከብ ብርሃን መነጽር አለበት ሥፍራ ለመድረስ የአሽባሉ ቡድን 100 ሜትር ያህል ቀርቶታል። ሁለቱ የደፈጣ ተዋጊዎች ተመቻችተው ቦታቸውን በመያዝ ጊዜያዊ ምሽግ በሆነው ጉብታ ላይ ብቅ የሚለውን ሁሉ ሙራድ እያነጣጠረ መምታት ጀምሯል ።

በርግ ወደ ሆስነር ዞሮ “ እንደማስበው በጣም ተጠግተዋል ” አለው ። ሆስነር ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። ዶብኪን ፍጹም አስፈላጊ እስኪሆን ድረስ የመጨረሻ የመከላከያ እርምጃ እንዳይወስዱ ነገራቸው ። ሆስነር በበኩሉ ከአሁን የባሰ እንደማይመጣ አውቋል ። ለመልዕክተኛዋ የመከላከያ እርምጃ ለመውሰድ እንዲዘጋጁ እንድትነግር አዘዛት ። ቀጥሎም ወደ በርግ ዞሮ “ ብሪን እንዴት እንደሚዋጋ ለማየት መሔዴ ነው። አንተ አዛዥ ስለሆንክ እዚሁ ቆይ” አለው።

በርግ አባባሉን ተቀበለ ። ሆስነር እንደ ሔደ ከሯጮቹ መልዕክተኞች አንድዋ ከኋላ መጥታ “ በወንዙ በኩል ወደ ላይ እየመጡ ነው ” አለችው ።

በርግ ሲጋራውን አቀጣጠለ ። ከተራራ ጫፍ ላይ ሆኖ ጦር ለመምራት ለእርሱ አመርቂ ሆኖ አላገኘውም ። ከ30 ዓመት በላይ በወታደርነት አገልግሏል ። ዶብኪን ሔዷል ። ሆስነርም ወደ ክልላቸው ድንበር ሲሔድ ራሱን ለማጥፋት ያለመጠራጠር ነበር ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ይሙት ፣ ይቁሰል ፣ ወይም ሕይወቱን ለማትረፍ እንደሌሎቹ በመዋጋት ላይ ይሁን አንድም ሰው የሚያውቅ የለም ። በርግ ከቦር

ሳው ጋር ብቻውን ቀረ ። የሚያማክረው አልነበረም ። ስብሰባ ለማ ድረግም አልተቻለም ። የሆስነር መሔድ የትዝታ ሀዘን አስከተ ለበት ። ኤሸር አርንሰን በአጠገቡ ቆማ እየተንቀጠቀጠችና ምላስዋ እየተያያዘ “ ምን ማድረግ እንችላለን ?” ብላ ጠየቀችው ።

በርግ በአሁኑ ጊዜ 10 ኤኬ - 47 ጠመንጃዎች የምሥራቃዊ ቁል ቁለትን በሚጠብቁ ሰዎች እጅ መኖራቸውን ሰምቷል ። ጠመን ጃዎቹን እንደሚፈልጓቸው ቢያውቅም በምዕራብ ቁልቁለት በኩል አረቦቹ ያላንዳች ተቃውሞ እንዲመጡ አልፈለገም ። ይህን ክልል የሚጠብቀው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ቢሆንም ለጦርነት ሥራ ብቃት አልነበረውም ። በዚያ በኩል በጠቅላላ መስመሩ የሚጠበቀው በስ ምንት ሰዎች ብቻ ነበር ። በተጨማሪም ሪቻርድሰንና መክለር ነበሩ ። ወደ ምሥራቅ ቁልቁለት እያመለከተ “ ሒጂና ሁለት ኤኬ - 47 እና ቢያንስ ሁለት የጉረሱ ሽጉጦች ለምነሽ ወይም ተበድረሽ ወይም ሰር ቀሽ ወደ ምዕራብ ቁልቁለት ውሰጂ ። ከዚያም እንደተመለስሽ ዌይ ዝማን የመጨረሻ የመከላከል እርምጃ መውሰድ እንዲጀምር ንገሪው” ብሎ አዘዛት ።

“ እሺ ” ብላ በጨለማው ውስጥ ራስዋን በአዎንታ ነቀነቀች ።

በርግ ተመለከታት ። የተሰጣት ኃላፊነት በግለሰብ ደረጃ ከባድ ነበር ። ጠመንጃዎቹንና ጥይቶቹን በዚያ በጨለማ ብዙ መቶ ሜትር ተሸክማ በመውሰድ በበለጠ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግና በተጨማሪም ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ-ምናልባትም በአሁኑ ጊዜ ግራ ተጋብቶ ይሆናል — የተላከችውን ትዕዛዝ ማስተላለፍ ነበረባት ። ይህ ሁሉ አረቦቹ ወደ ተራራው ሳይወጡ በፊት መፈጸም ነበረበት ። በት ከሻዋ ላይ ቸብ አድርጓት “ አይዞሽ ሁሉም ነገር የተስተካከለ ይሆ ናል ። የተሰጠሽን ትዕዛዝ በየደረጃው ፈጽሚው ” አላት ።

“ አደርገዋለሁ ” አለችው በልበ ሙሉነት ።

“ ጥሩ ። በዚያ በኩል ጄኔራል ዶብኪንን አይተሽዋል ? ”

“ አላየሁትም ። ”

“ እሺ ፤ ግድየለም ፤ ጉዞሽን ቀጥዪ ፤ መልካም ዕድል ። ”

* * *

የጥይት ድምጽ ወደሚሰማበት አቅጣጫ ሮጠች ።

ዶብኪን ከሪቻርድሰንና ከመክለር ጋር ሆኖ በቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ቆሞ “ በመጨረሻ በዚህ በኩል መሞከራቸው እንደ ማይቀር አውቃለሁ ” አላቸው ።

መክለር በሁለት እጆቹ ሽጉጡን ይዞ በመንበርከክ በሦስት አቅጣጫዎች እየተዟዟረ ሁለት ሁለት ጥይቶች ተኩሶ አንድ ጥይት ሲቀረው ከተንበረከከበት ተነሳ ። " ከ500 ሜትር " እርቀት ላይ ሆኖ በዚህ መሣሪያ መከላከል ከባድ ነው " ብሎ ሌሎች ጥይቶች ለማውጣት ኪሱን በረበረ ።

" ባልደረቦቻችን መሳሪያ ይልኩልናል " በማለት ዶብኪን አረጋገጠለት ። " ተስፋ አለኝ " ብሎ መክለር መልስ በመስጠት ሽጉጡን ማጉረስ ጀመረ ።

ተኩሱ በቆመ ጊዜ ሪቻርድሰን አቀልቁሎ ተመለከተ ። አልፎ አልፎ በቆርቆሮ ውስጥ ያሉ ጠጠሮች ሲንኳኩ ወይም አንድ አረብ ዳገቱን በሚወጣበት ጊዜ ሲራገም ድምጽ ይሰማ ነበር ።

" የመጨረሻውን የመከላከል ጦርነት የሚጀምሩት መቼ ነው ? ሯጭዋ የሔደችው ወዴት ነው ? ኤኬ - 47 ጠመንጃዎች የታሉ ? "

ዶብኪን ከጉድጓዱ ወጥቶ " ከአሁን በኋላ እዚህ ስለማልሠራ ጄኔራል ሆስነርን ጠይቀው " አለው ። ለመሮጥ እንደተዘጋጀ ሰው ቁጢጥ በማለት " ደህና ሁን ፤ በሀይፋ ወይም በሂውስተን እንገናኝ" አለው ለመክለር ። ቁጢጥ ካለበት ተነስቶ ሲዘል በአየር ላይ ለብዙ ጊዜ የሚቆይ መሰለው ። አቀልቁሎ ሲመለከት ከወንዙ ዳር ጀምሮ እንደግድግዳ እሩቅ መሆኑን አየ ። ቀጥ ያለውን ሸርተቴ ዘሎ በሚያርፍበት ጊዜ ከመሬቱ ጋር ተጋጨ ። በመጀመሪያ አስር ሜትር ቀጥሎም ሃያ ሜትር አከታትሎ በመዝለል ትንሽ ደልደል አለ ቦታ ላይ አረፈ ። ከጠቅላላው ቁልቁለት ግማሹን ያህል ሦስት ሴኮንድ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ወረደ ። በፊት ለፊቱ አሻቅበው የሚወጡ ሁለት አረቦች ከጨለማው ውስጥ በድንገት ብቅ አሉ ። ሳንጃ የተሰካባቸውን ኤኬ - 47 ጠመንጃዎቻቸውን በድንጋጤ አዞሩበት ።

* * *

ናኦሚ ሀበር በጥይት የፈረሰውን የናታን ብሪንን ራስ በጭንዋ ላይ አድርጋ ተቀምጣ ሆስነር አገኛት ። አሁን በመከላከያዎቹ ላይ ከደረሱት ችግሮች አንዱን ክፍል ለማወቅ ቻለ ። " ጠመንጃው የት ነው ? " ብሎ ጠየቃት ።

ቀና ብላ " ሞቷል " አለችው ።

" ይገባኛል ፤ መሣሪያው የት ነው ? "

ራስዋን በአሉታ አወዛወዘች ።

ሆስነር በርከክ ብሎ በዓይኑ ሲቃኝ ብሪን መሣሪያውን የት እንዳስቀመጠው በከፊል አየው ። ጥይቱ ሰንጥቆ የገባበትን መሬት በእጁ

ሲነካው ሙቀትና እርጥበት ነበረው ። እጁን ካባበሰ በኋላ ማንኛውም ጥይት እንዳልሆነ ተመለከተ።አረቦቹ እያነጣጠሩ በሩቅ የሚተኩሱበት አንድ ልዩ መሳሪያ እንዳላቸው ለማወቅ ቻለ ። የብሬንን ቢያገኙ ኖሮ ሌላ ተጨማሪ ይኖራቸው ነበር። ተንሸራቶ በመከላከያ ጉድጓዱ ውስጥ ሲገባ የሚያብረቀርቀውን አረንጓዴ ቀለም ሲያይ ዘሎ በላዩ ላይ አረፈ።

ሙራድ አጉልቶ በሚያሳየው መሣሪያው ሆስነርን ስለአየው መሣሪያውን ለመማረክ በመሔድ ላይ የነበሩትን ዘጠኝ ሰዎች ተጣራ። እነርሱ ግን ሆስነርን አላዩትም ።

ሆስነር መሣሪያውን ይዞ ተንከባሎ የነበረበትን ቦታ እንደለወጠ በ30 ሜትር እርቀት ላይ ስለአያቸው አከታትሎ አምስት ጥይቶች በመ ተኮስ አንዱን ወይም ሁለቱን ስለአጓናቸው የቀሩት ተበታተኑ ። የኮከብ ብርሃን ካለው መሳሪያ ተዋጊ ጋር ለመቋቋም እንደማይችሉም አወቁ።

ሙራድ ቢተኩስም ሆስነር ቦታውን ለውጦ ስለነበረ ሊያገኘው አልቻለም ። የተተኮሰው ጥይት በእግሩ አጠገብ አርፎ አፈሩን ሲበ ትንበት ሆስነር ቢሰማውም ከተኛበት ሳይንቀሳቀስ መመልከት ጀመረ ። አረቡ ሆስነር የት እንዳለ ያውቃል ፤ ሆስነር ግን አረቡ የት እንዳለ አያውቅም ። በጥቂት ሴኮንዶች ውስጥ አረቡን ለማየት ካል ቻለ እንደሚገድለው አውቋል ።

ሙራድ በሆስነር ራስ ላይ አስተካክሎ በማነጣጠር ምላጩን መሳብ ሲጀምር በሙራድ በስተጀርባ የነበሩት አሽባሎች በጨለ ማው ውስጥ አከታትለው ተኮሱ ። የጥይቶቹና የፍንጣሪዎቻቸው ብልጭታ ለሙራድ መሳሪያ አመቺ ሁኔታን ባለመፍጠሩና ኢላማ ውን ሊመታ ባለመቻሉ እየተራገመ “ አቁሙ፣አቁሙ ” እያለ ጮኸ ። ቢሆንም ባይሆንም በማለት ደጋግሞ ተኮሰ ። ኃደኛው ሳፋር በኤኬ - 47 ጠመንጃዎች የሚጠቀሙትን ስለጮኸባቸው ተኩሱን አቆሙ ።

ሆስነር የሆነውን አውቋል ። እስከ አሁን የተገኙትን ድሎች በማየት ሌላ ሰው ቢሆን ኖሮ አሁንም እግዚአብሔር ከሆስነር ጋር እንደሆነ በተናገረ ነበር ። ሆስነር ግን በደረሰበት አሰቃቂ ሁኔታ ስለተሰቃየና እንደ እርግማንም ስለቆጠረው ፍጻሜው ለምን በቶሎ አይደርስም የሚል አስተሳሰብ አደረበት ።

ሙራድ በመሣሪያው እንደገና ቢመለከትም ሆስነር ቦታውን ለውጦ ስለነበረ ሊያየው አልቻለም ። ሆስነር ቀድሞ በተሠራ ጉድ ቢያ ውስጥ ስለገባ እንደ እግረኛ ጦር ወታደሮች ሰውነቱን እንደፈ ለገ በማዘዝ ኩርትምትም ብሎ መቀመጥ ቻለ ።

ሙራድ የተጋለጠ መሆኑ ስለገባውና በድንገት ፍርሃት ስለተ ሰማው አንድ ትንሽ ጉድጓዳ ቦታ አግኝቶ ዘሎ ገባ ።

በአካባቢው የነበረው የጠመንጃ ጩኸት በዚያ ደቂቃ ውስጥ ጸጥ ብሏል ። ሆስነርና ሙራድ አጉልተው የሚያሳዩና ድምጽ የለሽ መሣሪያዎቻቸውን ይዘው አንዱ ሌላውን ይፈልጋል ።

የአሸባሉቹ ዋና ቡድን በእስራኤል ክልል ውስጥ በሆነው 100 ሜትር ገብቷል ። ጥቂት የሰለጠኑ የአሸባል የጠላት ምሽግ ሠርሳሪ ዎች ደግሞ ጩቤዎችና ሽጉጦች ይዘው ወደ እስራኤሎቹ ምሽግ በመ ቃረብ የአሸባሎቹ ዋና ቡድን አጠቃላይ ውጊያ የሚያደርግበትን ጊዜ ይጠብቃሉ ። የእነዚህ ዓይነት ተዋጊ ሊኖረው የሚገባውን የእጅ በምብ ፡ ወይም የሚወረወሩ ፈንጂዎች ቢይዝ ኖሮ በእስራኤሎቹ መስ መር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርስ ነበር ። ደግነቱ እስራኤሎቹን በእግት ለመያዝ ተራራ ማፍረስ ይገባል ብሎ ማንም ያሰበ አልነበረም ። እነ ዚህ የእግረኛ ጦር ክፍል ቁንጮ የነበሩት በሙያው የተካኑ ቢሆኑም ዋናው ጦር ገፍቶ ካልመጣ በስተቀር ብቻቸውን እየዳሁ ወደ እስራ ኤሎቹ ምሽግ መቅረቡ ራስን መግደል መሆኑን አውቀዋል ። አሁን አሉበት ቦታ ቢደርሱም የመጨረሻው ውጊያ እስኪካሔድ ድረስ ምንም ማድረግ አልቻሉም ። የደጀን ተዋጊዎቻቸው ወደፊት በሚገፉበት ጊዜ ወደ እስራኤሎቹ ምሽግ እየዘለሉ በመግባት በጩቤና በሽጉጥ ለመግ ደል ዝግጁ ነበሩ ። ነገር ግን ፈንጂዎች ቢኖሩአቸው ኖሮ በመጀመ ሪያ የሚያደርጉትን ያውቁ ነበር ።

* * *

ዶብኪን በሁለቱ አረቦች አጠገብ ዘሎ ሲሮጥ አረቦቹ ተገላብ ጠው ጀርባቸውን በዳገቱ ላይ አስጠግተው ኤኬ - 47 ጠመንጃዎቻ ቸውን አነጣጥረው ሰውየው ወደ ወረደበት ሲተኩሱ ጡንቻዎቻ ቸውን የጠመንጃዎቹ ሰደፎች ነዘሩአቸው ።

ዶብኪን ወደፊት እየገሰገሰ በነበረበት ጊዜ የተተኮሱት ጥይቶች በኋላውና በጐኑ ሲያርፉ ተሰማው ። ተረከዞቹ በቁጥቋጦዎች ተሞ ዠዠቁ፤እግሮቹም ጐርፍ በቀደደው ቦይ ውስጥ በመግባታቸው ተጐዱ። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ሳይበግረው በኃይል እየሮጠ በአየር ላይ ዘለለ ።

መሬቱን ሳይነካ በአየሩ ላይ እየተገለባበጠ በአለበት ጊዜ በአየሩ ውስጥ ተንሳፎ የቆመ መሰለ ው።ከላይ በኮከቦች የተንቆጠቆጠው የሜ ሶፖታሚያ ሰማይ ፤ ከታች ደግሞ በኮከቦች ብርሃን የሚንጸባረቀው የኤ ፍራጥስ ወንዝ ታዩት። ሰውነቱ እንደዚያ አዟሪት እየሠራ በሚሄድበት ጊዜ በመጀመሪያ ጭቃማውን ሜዳ ቀጥሎም ሰማዩን አየ ። በዚህ ጊዜ ጥይቶቹ በተከታታይ ይተኮሱ ስለነበረ ለምን እንዳልተመታና እንዳል ወደቀ ተገረመ ። በመጨረሻም በጥይት ስለተመታና ሕመሙም በኃ ይል ስለተሰማው ከሕልሙ እንደነቃ ሆኖ አረማመዱ የተስተካከለ መሰለው። የውሃ እርጭት ሰማ ፤ ቀጥሎም የኤፍራጥስ ጭቃ አለበሰው።

ቦታው ግልጽ ከመሆኑም በላይ አካባቢው በአረቦቹ ስለተወረረ ተመልሶ ወደ እስራኤሎቹ ምሽግ ለመሔድ እንደማይችል ሆስነር አወቀ ። አሁን ባለበትም ሆኖ ከፊት ለፊቱ ካለው ቦታ በስተቀር እየ ተዘዋረ ጠላትን ለማጥቃት አመቺ ቦታ ስለአልነበረ በጠመንጃው ሙሉ ለሙሉ መጠቀም አልቻለም ። በቂ ጥይትም አልነበረውም ።

የጫማውን ተረከዝ ጥይት መትቶ ሲገነጥለው ቅልጥሙ በድ ንገት ተርገፈገፈ ። ተራግሞና ራሱን ቀና አድርጐ ሲያነጣጥር አረቡ ወደ ጉድጓዱ ገባበት ። የጠላት ቡድን ቦታውን በመለወጥ አከታትሎ ወደ ሆስነር እሩምታ መተኮስ ጀመረ ። የተተኮሱት ጥይቶች ከየት አቅጣጫ እንደመጡ ሆስነር አየ ። ቀጥሎም ሆስነር አነጣጥሮ በመ ተኮስ ሳፋሪን መታው ።

ሙራድ ስለተኮሰ ሆስነር አንድ ነገር ጆሮውን የነደፈው መሰ ለው ። ተገላብጦ ጥይቱ ወደ መጣበት አቅጣጫ ተኩሶ ወደ ጉድጓዱ እንደተመለሰ ሆስነር በጆሮው ላይ ሙቀት ያለው ፈሳሽ ተሰማው ። በድንገት ሳያውቀው ስለሚሪያም አሰበ ።

ሆስነር ምንም ፋይዳ ያለው ነገር እንደማይፈጽምና አሸባሎ ቹም ከሁለት ወገን እርሱ ወደ አለበት እየተቃረቡ መሆናቸውን ስለ ተገነዘበ ተስፋው መነመነ ። ወደ ኋላው ዞሮ “ ሀበር ” ብሎ በጣም ጮኾ ተጣራ ።

መልስ አልነበረም ።

እንደገና “ ሀበር ” ብሎ ተጣራ ።

ቀና ብላ ተመለከተች ። አሁንም በደም የተበከለው የብረን ራስ በጭንዋ ላይ ተጋድሟል ። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ሆስነር በዚያ እንደነበረ አስታወሰች ። አሁን ግን ምን እንደደረሰበት አላወቀችም ። እንደገና ጩኸቱን ሰማች ። ግን መልስ አልሰጠችውም ።

ሆስነር ሸሚዙን ቀዶ የብርሃን ኮከብ መነጽር ያለበትን ጠቅልሎ ካሰረ በኋላ በግድ ተነስቶ በኃይል ሲወረውረው ከናኦሚ ሀበር ትንሽ ራቅ ብሎ በለሰለሰ አቧራ ላይ ሲያርፍ ድምጽ ሰማች ። ምን እንደሆ ነና ምን ማድረግ እንደሚገባት ስላወቀች ብትንትኑ የወጣውን የና ታምን ራስ ጕንበስ ብላ ሳመችው ።

* * *

በክልላቸው ያሉ ሁሉ የመጨረሻ የመከላከያ እርምጃ እንዲ ወስዱ ትዕዛዝ ተላለፈላቸው ። እንቅስቃሴውን በጥንቃቄ እንዲጀ ምሩ ተደረገ ። ጠላትን ለማጥቃት ቀን በልዩ ልዩ መልክ የተዘጋጁት ነገሮች ሁሉ በሥራ ላይ እንዲውሉ ትዕዛዝ ተሰጠ ። ይሁን እንጂ በጨ ለማው ምክንያት ብዙ ጥርጣሬዎች ነበሩ ።

በሰሜን በኩል ከነበረው የመቆጣጠሪያ ግዙፍ የሕንጻ ማማ 100 ሜትር እርቀት ላይ የነበረ አንድ አረብ “ እዚህ ! በዚህ መስ መር በኩል ጉድጓድ አለ ! በዚህ በኩል ተከተሉኝ ! ” ብሎ በጩኸት ተናገረ ።

አስራ ስምንት ሰዎች ያለው ሁለት የአሸባል ቡድን ጩኸቱን ስለሰማ ድምጽ ወደ ተሰማበት ቦታ ቢተኩስም የአጸፋ ተኩስ አል ነበረም ። ባዶ ወደነበረው ምሽግ 50 ሜትር ያህል ስለተቃረቡ በጥ ቂት ሴኮንዶች ውስጥ በምሽጉ ውስጥ ስለሚገቡ የውጊያው ፍጻሜ ይሆናል ።

“ እዚህ ! ፍጠኑ ! በተራራው ላይ ! ” አለ ድምጹ እንደገና ።

ድምጹን የሰሙት በተኩሱ ጊዜ ስለነበረ የሰውየው ድምጽ አጣ ጣል ሙሉ በሙሉ ትክክል እንዳልነበረ አላጤኑትም ። ምናልባትም ከአዛዦቻቸው አንዱ ድምጹ እንዲጐላ በከብት ቀንድ ተጠቅሞ ይሆ ናል ። ድምጹን ተከትለው ወደ እስራኤሎቹ መከላከያዎች በጣም እየ ተጠጉ መጡ ።

ኢብራሂም አሪፍ ከመከላከያው በስተ ጀርባ ባለ ትንሽ ጉድጓድ ውስጥ ተቀምጦ በመናገሪያው “ አሁንም ወደ ላይ ! ከዚያም በላይ !” አላቸው ።

የድምጽ ማጉሊያው ሳጥን ከመከላከያው ምሽግ ፊት ለፊት 30 ሜትር እርቀት ላይ ነበር ። “ አሁን ! ከዚያና ከዚያም በላይ ! ሞት ለእስራኤል እያላችሁ ጩኹ ፤ ወደፊትም ግፉ ” የሚል ሰሙ ።

አሸባሎቹ በተርታ ቆመው “ ሞት ለእስራኤል ! ” ብለው በመ ጮኽ ወደፊት ሮጡ ።

ቁስሉን ታክሞ የዳነው ካፕላን ፣ ማርከስና ርብቃ ሊቪን በኤኬ - 47 ጠመንጃዎቻቸው የጥይት መዓት በአሸባሎቹ ላይ አርከፈከ ፉባቸው ። አሸባሎቹ ከአፈሙዞቹ በሚወጣው ብልጭታ ተደናግ ጠውና ፈዘው ቆሙ ። በድንገት በተደረገባቸው ተኩስ አንዱ በአንዱ ላይ እየተነባበረ ወደቀ ። ሰውነታቸውም በጥይት ተበሳሳ ። ይህ እስከ አሁን ድረስ ከደረሰባቸው ሽንፈት ሁሉ እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ ለእስራኤሎቹ ጊዜያዊ እፎይታ አስገኘላቸው ።

* * *

ኤሸር አሮንሰን ያገኘችውን ሁሉ እንዲሰጡአት ብትለምንም እያ ንዳንዱ በሞትና በመኖር መካከል ስለነበረና ያጋጠማቸውን ችግር ለመወጣት በመጣደፍ ላይ ስለነበሩ የታዘዘችውን ለማግኘት አልቻ ለችም ። በርግ ለምና ፣ ተበድራ ወይም ሠርቃ እንድታመጣ አዟታል ።

ልመናዋ ግን አልሠራም ። ጥያቄዋን የሰማ ሁሉ ከማዘን በስተቀር ሌላ መልስ አልሰጣትም ። ሆስነርን በኃይል ፈለገችው ። ሆስነር አንድ ትንሽ ትዕዛዝ ከሰጠላት እንደምታገኝ አውቃለች ። ግን አንድም ሰው በዚያ አካባቢ አላየውም ፤ ምናልባትም የሞት አደጋ ሳይቀር ደርሶበት ይሆናል ።

በድምጽ ማጉሊያው የሚነገረውን ስለሰማች የመጨረሻው የመ ከላከል ዘዴ እንደተጀመረ ገባት ። በምዕራብ ቁልቁለት በኩል ግን የዚያ ዓይነት አልነበረም ። ጠመንጃዎች ለማግኘት ከፉኛ ትፈልጋ ለች ። ስለዚህ ማርከስና ርብቃ ወዳሉበት በጥንቃቄ ሮጣ ስትሔድ እነእርሱ ከገደሏቸው ላይ መሣሪያ ለመውሰድ እየተሹለከለኩ ሲሄዱ አገኘቻቸው ። ሌሎች እንዳይተናኮሏቸውና አደጋ እንዳይጥሉባቸው ካፕላን ከኋላ ሆኖ ይመለከታል ። ካፕላንን አልፋ ለጠላት ማጥቂያ በተሠሩት ካስማዎችና ጊዜያዊ ምሽጐች መካከል ተጠንቅቃ እየዘ ለለች አልፋ በማርከስና በሌቪን ፊት በመድረስ “ በማስቸገሬ አዝ ናለሁ ፤ እየወጉን ስለሆነ ለምዕራባዊ ቁልቁለት ጠመንጃዎች እፈ ልጋለሁ ” ካለቻቸው በኋላ ወደሞቱትና በሕይወትም ወዳሉት ዘላ በመሔድ ኤኬ - 47 ጠመንጃዎችና ጥይቶች ነጥቃና ተሸ ክማ ተመለሰች ። ማርከስና ሌቪን ተከትለው በመሔድ ረዷት ። ማርከስ በሕይወት ያሉ ቢኖሩ አደጋ እንዳያደርሱባቸው እንድትጠ ነቀቅ ቢነግራትም ኤሸር አሮንሰን ግን ለመስማትም ሆነ ለመጠን ቀቅ ደንታ ያላት አልመሰለችም ። አንድ ሰው ጠመንጃውን ለማን ሳት ሲሞክር ማርከስ በጥይት ቆነደደው ።

አሮንሰን “ አመሰግናለሁ ” ብላ ያን በጣም ከባድ የሆነ መሳ ሪያ ተሸክማ ሮጠች ።

ማርከስና ሌቪን እንዳይመቱ በካፕላን ኤኬ - 47 በመሸፈን የቀ ሩትን ጠመንጃዎች ሰበሰቡ ። በድምጽ ማጉሊያው “ ተመለሱ ! ተመ ለሱ ! ተመለሱ ! ጓዶች ! ይሁዶች በዚህ በኩል በሚገባ ተጠናክረ ዋል ” የሚል ጩኸት ተሰማ ። አሸባሪዎቹ ረድፋቸውን ጠበቁ ።

* * *

ናኦሚ ሀበር አዲስ ካርታ በኤም - 14 ውስጥ አስገብታ ስትመ ለከት ቁልቁለቱ በሚድሁ፣በሚንቀ ሷቁና አጉንብሰው በሚሔዱ ሰዎች ተትርመስምሷል ። በስርዋ ያለውን ረባዳ ስትመለከት በጉድጓዱ ውስጥ ሆስነር ተጋድሟል ። መጐዳት ወይም አለመጐዳቱን ለማወቅ አልቻለችም ። መሣሪያውን ያን ያህል እርቀት ሊወረውረው የቻ ለው ቆሞ መሆን አለበት ። ምናልባትም በደፈጣ ተዋጊዎቹ ተመትቶ ይሆናል ።

የቀኝ እጅዋን አጽቅ ጥይት ጨረፍ ስለአደረገው ጮኸች ። ጠመንጃውም ከእጅዋ ላይ ሊወድቅ ተቃርቦ ነበር ። ከቤታችዋ ወደነበረው ጉድጓድ ተንበርክካና ተንፏቃ በመግባት ድንጋጤዋ እስኪለቃት ድረስ ትንሽ ቆየች ። እንስሳ ይመስል ቁስልዋን ስለላሰችው ሕመሙ ትንሽ ታገሰላት ። ሊገድላት ተቃርቦ የነበረው ሰው የወዳጅዋን ሕይወት ያጠፋው ሰው መሆኑን አወቀች ። በዚህ ምክንያት - ከሁሉም ምክንያቶች የበለጠ - ያ ሰው መገደል አለበት ብላ ስላሰበች ቀስ ብላ ከቆመች በኋላ በተከመረው አፈር ላይ አሾልቃ አየች ።

ሙራድ ከልጅነቱ ጀምሮ ጓደኛው የነበረው ሳፋር የሞተ መሆኑን አምኗል ። ብቸኛ ወዳጁና ፍቅረኛው ነበር ። ያ ይሁዳዊ ገድሎታል ። ለመሆኑ ይሁዳዊ መሣሪያውን ሲወረውር ሙራድ መቶት ይሆን ? ጠመንጃውና አጉልቶ የሚያሳየው መነጽር ተወስዷል ? አሁን በማን እጅ ይሆን ? በሆስነር ጉድጓድና በመመልከቻው ማማ መካከል አነጣጥሮ ተመለከተ ። አደጋው በጉብታው ላይ ነበር ። በመጨረሻ ያንን እርጉም ይሁዳዊ ካየበት ቦታ ላይ ዓይኖቹን እንዳይነቅል ስሜቱ አስገደደው ።

ሀበር አየር ወደውስጥ ስባ ስትመለከት የደፈጣ ተዋጊውን ሙሉ ሰውነት ስምንት ሜትር እርቀት ላይ ተዘርሮ አየችው ። በራሱ ላይ አልሞ መተኮሱ ጭንቅላቱንና መሣሪያውን ጭምር ብትንትኑን ማውጣት ይቻላል ። ግን በጀርባው በኩል ሙሉ ለሙሉ ለመምታት አጠራጣሪ ስላልነበረ አነጣጥራ ሁለት ጥይት ተኮሰች ።

እስራኤሎቹ ብዙ ጊዜ ፈጅተው የሠሩአቸውን የማስመሰያ ምስሎች ተኩሰው በጥይት መትተው ከጣሉአቸው በኋላ መልሰው አቆሟቸው ።

አሥራ ሁለት የሚሆኑ ያልታጠቁ ሴቶችና ወንዶች የኮንኮርዱን ነዳጅ የተሞሉ ቆርቆሮዎች ይዘው የሚወጣውን ትነት ሲያቃጥሉት የጥይት ብልጭታ መሰለ ። አረቦቹ ተኩስ ወደሰሙበትና የጥይት ላንቃ መስሎ ወደሚታያቸው አቅጣጫ ተኮሱ ። የብልጭታውንም ብዛት በማየታቸው እስራኤሎቹ ብዙ መሣሪያዎች ማርከዋል ብለው ገመቱ ።

በተማረኩት ኤኬ - 47 ጠመንጃዎችና ጥይቶች መጠቀም የጀመሩት ገና አሁን ነበር ።

ሁለት ያልታወቁ ሴቶች ያለፈውን ሠላሳ ደቂቃ ያሳለፉት የሰላም መልዕክተኞቹ ሊጠቀሙባቸው ባመጡአቸው ሃያ አራት ክሮች ( ካሴቶች ) የቀዱትን የጦርነት ፊልም ቀን አልፈው አልፈው በሰቀሉአቸው የድምጽ ማጉሊያዎች በመጠቀም አሁን እንዲሰሙ በማድረግ

ቸው በእስራኤሎቹ በኩል የሚተኮሰው ጠንካራና ከፍተኛ መስሎ በጠ ላት ዘንድ ተገመተ ።

ሁሉም ነገር እንደገና ተንቀሳቅሶ መሥራት ጀመረ ። መልዕክ ተኞች ወደ መቆጣጠሪያውና አመራር መስጫው ጣቢያ እየመጡ ለበ ርግ ትዕዛዝ እንዲያስተላልፍ ጠየቁ ። በርግ ሕይወቱን ሙሉ ሲያደ ርገው እንደነበረው አሁንም ትዕዛዞችን አስተላለፈ ። የመጨረሻው መከላከል ሥራ ግቡን እየመታና የሰዎቹም ሞራል እየጨመረ ቢመ ጣም በርግ ሁኔታው አስጊ እንደነበረ አውቋል ።

ኤሸር አሮንሰን በጨለማው ውስጥ እየተንገዳገደች ወደ ምዕራብ ቁልቁለት መጥታ ተጣራች። ነገር ግን ማንም የሰማት አልመሰላትም።

* * *

አሽባሎቹ ዶብኪን በተኮሰው ተደናግጠው ለጥቂት ጊዜ መንቀ ሳቀሳቸውን ቢያቆሙም ከትንሽ ቆይታ በኋላ እንደገና እየተሽሎከ ለኩ ወደ ተራራው ጫፍ መውጣት ጀመሩ ። በቶሎም እንደሚደርሱ አምነዋል ። አዛዣቸው ሰይድ ታሊብ ያጋጠማቸውን ጥሩ ዕድል ሊያ ምን አልቻለም ። አልፎ አልፎ ከሚደረግባቸው የሽጉጥ ተኩስ በስ ተቀር በተራራው ጫፍ ላይ ምንም አልነበረም ። ይህ ግን ለብዙ ጊዜ ስለማይቀጥል ሰዎቹ በፍጥነት እንዲራመዱ አዘዘ። ዳገቱን ሲወጣ የታ ሊብ ደም በፊቱ ላይ ተለዋወጠ ። እስራኤሎቹ ጋር እስኪደርስ ድረስ አላስቻለውም ። በከፊል የተተለተለውን ፊቱን ዳበሰ ። ፓሪስ ውስጥ ይኖር በነበረበት ጊዜ ከፈረንሳይ የይለፍ ሚኒስቴር ደብዳቤ ደረሰው ። ከፍቶ ሲያነበው የተላከው ከእስራኤል የጸጥታ ድርጅት መሆኑን አወቀ። በችላ ባይነቱ በቀኝ ፊቱ ላይ ጉዳት ስለደረሰበት ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሕይወቱ እንደቀድሞው ሊሆን አልቻለም ። የቀድሞ ውብ ፊቱን አይተው የነበሩ ሴቶች ሁሉ አሁን ሲያዩት ይጮሀሉ ። ወን ዶች ሳይቀሩ ፊታቸውን ያዞሩበታል ።

ታሊብ ይስሐቅ በርግን በሕይወት እንዲያገኘው ጸለየ ። በአዕ ምሮው ውስጥ ሊወስደው ስለሚችለው የበቀል እርምጃ አውጥቶና አውርዶ የደረሰበት የመጨረሻ ውሳኔ የእስራኤልን የጸጥታ ኃላፊ በሕይወቱ ቆዳውን ለመግፈፍ ነበር ። ከሃያ አራት ሰዓት በላይ በሚ ፈጅ ጊዜ ደረጃ በደረጃ ቆዳውን እየገፈፈና እየቆራረጠ በርግ በዓይኑ እያየ ለውሻ ለመስጠት ቋምጧል ። አሻቅቦ ሲመለከት በተራራው ጫፍ ላይ ለመድረስ ሃያ አምስት ሜትር ያህል ይቀራቸዋል ።

* * *

መክለር ሽጉጡን ስድስት ጥይቶች አጉርሶ ጸጥ ብሎ ወደ ቆመው ወደ ሪቻርድሰን እየተመለከተ “ በአረብኛ ወደ አሜሪካን ቆንሲል ውሰደኝ የሚባለው እንዴት ነው ?” ብሎ ጠየቀው ።

" ይህን ትናንትና ሆስነርን መጠየቅ ነበረብህ ።"

" ምንም አረብኛ መናገር አትችልም ?"

" አልችልም ፣ ለምንስ ብየ ።"

" አላውቅም ፤ እንዲያው ለማወቅ ብየ ነው " ብሎ ከጉድጓዱ ብቅ ብሎ አቀልቁሎ ሲመለከት ሰዎች በጨለማው ውስጥ እንደ እን ሽላሊት እየተሳቡና እየዳሁ ወደ ላይ ሲመጡ ስለአያቸው ወደ አንዱ ላይ አልሞ ተኮሰ ።

ሚሪያም በርንስቴይንና አርኤል ዌይዝማን እየተሹለከለከች ስትመጣ ኤሽር አሮንሰንን አገኟት ። ወደዚያው ስምንት ኤኬ - 47 ጠመንጃዎች ከእነጥይቶቻቸው ተቀብለው ግማሽ ኪሎ ሜትር እርቀት ወዳለው የክልላቸው መስመር በተለያየ አቅጣጫ ጠመንጃ ዎቹን ይዘው ሮጡ ። በየመንገዳቸው ላይ ለሚያገኙአቸው ጓዶቻቸው እንዳንድ ጠመንጃ ከነሙሉ ትጥቁ አደሉ ። በርንስቴይን የመክለርን ጉድጓድ አልፋ ሔደች ። በደቡብ ቁልቁለት መጨረሻ ላይ የመ ጨ ረሻውን ኤኬ - 47 ጠመንጃ ይዛ ቆመች ። አንዲት አሽባል ሴት በሜ ዳው ላይ ወጥታ አምስት ሜትር እርቀት ላይ ኤኬ - 47 ጠመንጃ አንግታ ቆመች ። ሚሪያምን ስለአየቻት ጠመንጃዋን ቀስ አድርጋ አወረደች ።

ሚሪያም በኤኬ - 47 ጠመንጃዋ ለመጠቀም ብትፈልግም ዘዴ ውን አታውቀውም ። ተጠብቆ ይሆን ? ጉርሶስ ይሆን ? መቀባበልስ ይኖርበት ይሆን ? በእርግጥ ቀድሞ ጠመንጃውን ይዞት የነበረው ሰው አቀባብሎ እንዲጠበቅ አላደረገውም ። እርስዋ ግን ስለዚህ አላሰ በችም ። አንድ የምታውቀው ነገር ቢኖር ጠመንጃው ምላጭ ያለው መሆኑን ነው ። ጣትዋን በምላጩ ላይ አድርጋ አቅማማች ። አሽ ባሊቷ አ.ላማ ሳታደርግ እሩምታ ወደፊት ተኮሰች ።

ሚሪያም ከአፈ ሙዞ የወጡትን ብልጭታዎች አየች ። ዓይኖ ችዋንም ሸፈንዋት፤በኢየሩሳሌም ውስጥ በአንድ ቡና ቤት ውስጥ በሚ ያብረቀርቅ ፀሐያማ ቀን ያለች መሰላት። አንድ ወጣት እግረኛ ወታ ደር በጐላን ተራራ ላይ አንድ አረብ ከቤት ውስጥ ዘሎ ወጥቶ በጥቂት ሜትር ላይ ስለተከሰተበት ታሪክ የነገራት ትዝ አላት ። ወጣቱ እግ ረኛ ወታደር ከአንድ ዛፍ ፊት ቆሞ እንዳለ አረቡ ደጋግሞ የተኮሰው ጥይት በወታደሩ ኋላ የነበረውን ዛፍ ስለመታው ቅርንጫፎቹ እየተቆ ረጡ ሲወድቁ በወጣቱ ላይ አረፉ ። ከዚያ በኋላ አረቡ ሔደ ። እግ ረኛው ወታደር " በዚያ ዕለት መልአክ ከፊቴ ቆሞ ነበር " አለ ።

ሚሪያም ሌላ የእሩምታ ተኩስ ሰማች ። ጠመንጃዋም በእጇ ላይ ዘለለ ። ወጣትዋ ሴት ወደ ኋላዋ የዘለለች መሰለች ።

ሚሪያም ተንበርክካ የራስዋን ፊት ሸፈነች ።

* * *

በኮንከርዱ ውስጥ ያእኮቭ ሌይበር ተቀምጦ አንድ የአሜሪካን የጦር ፊልም ይመለከት ነበር ። ከሰዓት በኋላ ፊልሙን ባየበት ጊዜ ማስታወሻ ወስዶ ነበር ። ፊልሙ ወደፊት እንዲሮጥ አድርጐ እጦርነቱ ላይ ሲደርስ በትክክለኛ ሒደት እንዲሔድ ካደረገ በኋላ ድምጹ በኃይል ከፍ እንዲል አደረገው ። የድምጽ ማጉሊያው በክልላቸው ካሉት መስመሮች ጋር ተያይዞ ስለነበረ ከባድ የአውቶማቲክ ተኩስ የተከፈተ አስመሰለው ። ሙሐመድ አሳድ በእስራኤሎቹ ተፈቶ ከሔደበት ጊዜ ጀምሮ ከባድ መሣሪያዎች ያሉአቸው መሆኑ በአሸባሎቹ ሰፈር ውስጥ ወሬው ተራብቷል ። አሳድ በክሕደት ከመገደሉ በፊት ይጠብቁት ለነበሩት ዘቦች ስለ እስራኤሎቹ ጥንካሬ ብዙ ታሪኮች ነግሯቸዋል ።

አሸባሎቹ አሁን ማወላወል ጀመሩ ። ከእስራኤሎቹ መስመሮች በኩል የጠመንጃ ተኩሶች ብልጭ ድርግም ማለት ጀመሩ ። በቁልቁለቱ የጠመንጃ ተኩስ ጩኸት እየጨመረ መጣ ። በተጨማሪም የከባድ መሳሪያዎች ጩኸት ተሰማ ። እስራኤሎቹ ከሰዎቻቸው ብዛት የበለጠ መሣሪያ ያላቸው አስመሰላቸው ። አሸባሎቹ የመሸነፍ መንፈስ ስላደረባቸው በጉጉት ወደ አዛዦቻቸው መልከት ማለት ጀመሩ ።

ናኦሚ የተዋጊው አረብ ሰውነት ሲነጥር አየችው ። በሰውየው ጀርባ ላይ ሁለት ጥይቶች የሰደደችበት ለመሆንዋ በትክክል ስለአረጋገጠች ሰውነትዋ ተንዘፈዘፈ ። ድምጽዋን ዝቅ አድርጋ “ ሆስነር ! ሰውየው አልቆለታል ። እከላከልልሃለሁ ” ካለችው ብኋላ አቆልቁላ ስትመለከት የሆስነር ሰውነት አይንቀሳቀስም ። “ ሆስነር ! ሰውየው አልቆለታል ! እኔ. . . ስትል ሆስነር በእጁ ምልክት ሰጣት ። እርስዋም ወደ አመለከታት አቅጣጫዎች ወደፊት 80 ሜትር ፣ ከዚያም 90 ሜትር ፤ ቀጥላም ወደ ግራና ቀኝ እስከ 50 ሜትር እርቀት ላይ ድረስ ደጋግማ ተኮሰች ።

ሆስነር የመመልከቻው ማማ ግድግዳ ቀጥ ያለ በመሆኑ ለመውጣት ባለመቻሉ በቀኝ በኩል ዞሮ ከወጣ በኋላ ወደ ተራራው ገሰገሰ ። ከፊት ለፊቱ በግራ በኩል የኤም-14 ጠመንጃ ተኩስ ደጋግሞ ሰማ ። በፊት ለፊቱ በእስራኤሎቹ የተሠራው ጊዜያዊ ምሽግ አለ ። ኤም - 14 ከያዙት በስተቀር በዚያ ማንም እንዲኖር አልተደረገም ። ነገር ግን

ሊታመን የማይችል የአፈሙዝ ብልጭታዎች አየ ። ይህን ሁሉ ጠመንጃ ከየት አገኙ? ወይስ በአዘጋጅዋቸው ቦምቦች እየተጠቀሙ ነበር? ከፊት ለፊቱ የሚያየው ከአፈ ሙዞች የሚተፋው ነበልባል ከጋዝ ከተሞሉ ቆርቆሮዎቹ እንዳልሆነ ገባው ። ጥይቶች ጥዝ እያሉ ከኋላ ጆሮው በኩል ሲያልፉ ተሰማው ። “ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ ተኩሱን አቁሙ ፤ ሆስነር ነኝ ” ብሎ ከጮኸ በኋላ እየዘለለና እየተንከባለለ እስራኤሎቹ ለምሽግ በአዘጋጁት ቦይ ውስጥ ደረሰ ። ኤኬ - 47 ጠመንጃዎች የያዙ አንድ ወንድና አንዲት ሴት እወደቀበት ቦታ ላይ እንዳለ ተገርመው ተመለከቱት ። ሆስነር ቆሞ “ እንደ እናንተ ያለ መጥፎ ተኳሽ አላየሁም ” አላቸው ።

“ ዕድለኛ ነህ ” አለችው ወጣትዋ ሴት ።

ያልታጠቁት ተዋጊዎች የተከመረውን የናዳ ድንጋይ እየገፉ ወደታች ሲሰዱት እየተንከባለለና ሌሎች ናዳዎችንም በመጨመር እየወረደ የብዙ አሸባሎችን እግርና ሰውነት በመምታት ከፍተኛ ጉዳት አደረሰባቸው ።

በተጨማሪም ከእስራኤሎቹ መስመር በኩል የበሩ ችቦዎች የሚመስሉ ወደ ሰማይ እየተውዘገዘጉ ከወጡ በኋላ በአሸባሎቹ ክልል ማረፍ ጀመሩ ። እስራኤሎቹ በዚህ ዓይነት እንዲወረወሩ ባደረጓቸው መሣሪያዎች ላይ ሲያርፉ የሚሠበሩ በነዳጅ የተሞሉ ጠርሙሶችና ሌሎችም ዕቃዎች አስረውባቸው ስለነበረ ሲያርፉ አካባቢውን ሁሉ አቀጣጠሉት ። እሩቅ ለሆኑ ቦታዎች ጨርቆቻቸውን እየቀደዱ እንደወንጭፍ በመሥራት ቦምቦቹን አቀልቁለው ወረወሩ ። ቁልቁለቱ በእሳትና በብርሀን ስለተሞላ አሸባሎቹን በግልጽ ማየት ስለተቻለ ከእስራኤሎቹ የሚተኮሰው ኢላማውን መታ ።

አሸባሎቹ ግራ ተጋብተው ተተረማመሱ ። ጥቂቶቹ የነጭ ጋዙ ብርሃን ወደ ማያሳይበት ጨለማ ቦታ ተሯሯጡ ። አልፎ አልፎ አንዳንዶቹ በሚነደው ነጭ ጋዝ ስለተቃጠሉና ጩኸታቸው በያለበት ስላስተጋባ በሌሎቹ ላይ ፍርሀት ሰደደባቸው ።

እስራኤሎቹ ለማጥቂያ ከሠሩአቸው ሹል እንጨቶችና ብረቶች ስድስት ያህል በሚሆኑ የጠላት ወገኖች በታፋዎቻቸው ፣ በአንገቶቻቸውና በሆዶቻቸው ላይ ስለተሳጉባቸው ለመንቀል ሲሞክሩ ጩኸታቸው የባሰ ሆነ ።

የእስራኤሎቹን ጊዜያዊ የመከላከያ ምሽግ ለመያዝ በጣም ተጠግተው የነበሩት የአሸባል ምርጥ ወታደሮች እንደተሸነፉ አወቁ ። ከራሳቸው ወገን በሚተኮሰው ጥይት ጥቂት ወገኖቻቸው ከመገደላ

ቸውም በላይ እስራኤሎቹን ለመውጋት የነበረው ዕድል እየመነመነ መጣ ። በጠላት መንጋጋ ውስጥ ጨርሰው ለመግባት ተቃርበዋል ። ነገር ግን የወሰዱትን የሥልጠና ዘዴ በመጠቀም ቀስ በቀስ እየተን ከባለሉና እየተሹለከለኩ ወረዱ ። የተከላካዩን ክፍል ዝንባሌ ስለአወቁ ከአንድ ሜትር ያላነሰ እየተራራቁ ከጓዶቻቸው ጋር ሆነው ሸሹ ። ከአብዛኞቹ ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ ያልተመታ አልነበረም ። ሁኔ ታው በጣም አሰቃቂ ነበር ። ከእነዚህ እውቅ ሃያ ተዋጊዎች ውስጥ አስር የሚሆኑ የተሰለፉት በሌላ በኩል ስለነበረና አደጋውም ስለአ ልደረሰባቸው ወደ ተጐዱት መጥተው ጨርሰው እንዳያልቁ አዳኑ አቸው ።

በምዕራብ ቁልቁለት በኩል የነበረው ጦርነት እስራኤሎቹ በኤኬ - 47 ጠመንጃዎች መጠቀም በጀመሩ በስድሳ ሴኮንድ ውስጥ አብ ቅቷል ።

በልዩ ልዩ ዘዴ በእስራኤሎቹ የተተኮሱት አረኹንና ቁጥቋጠውን ሁሉ አቃጥለውታል ። በናዳና በኤኬ - 47 ጠመንጃዎች የተደረገው ተኩስ ረባዳውንና ቁልቁለቱን ከጠላት አጽድተውታል ። ዳሪዮስ ከ2500 ዓመት በፊት በመጀመሪያ እንደ አየው ወይም ከዚህ ጥቂት ዓመታት በኋላ በአሌክሳንደር አስተያየት እንደሰጠበት ምሽጉ የሚደፈር አልሆነም ። በቁጥቋጠው ውስጥ የነበሩት አሸባሎች አብ ዛኞቹ ሞተዋል ወይም ወደ ሞት የሚያደርስ የመቃጠል አደጋ ደርሶ ባቸዋል ። ጥቂቶቹ እየተንከባለሉ በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ የወደቁት እንደሌሎቹ አረቦች መዋኘት ስላልቻሉ ሰጥመዋል ።

የይስሐቅ በርግን ቆዳ ሕይወቱ እያለ ለመግፈፍ ቋምጦ የነበረው ሰይድ ታሊብ ሕልሙን በመርሳት በሚቃጠሉት ቁጥቋጠዎች ሙካ ከል እየጮኸ ሮጠ ። አውሮፓ ውስጥ በነበረበት ጊዜ የውሃ ዋና ተምሮ ስለነበረ ዘሎ በመግባት በውሃው ኃይል ወደ ደቡብ አቅጣጫ ተወ ሰደ ። አብረውት እየዘለሉ የገቡት ጥቂት ሰዎች ከተንቦጫረቁ በኋላ ሰመጡ ። ሕይወቱን ያላጣ እርሱ ብቻ እንደነበረ አምኗል ።

ሆስነር ወደ መቆጣጠሪያውና ትዕዛዝ መስጫው ጣቢያ ሲደ ርስ በርግን ቆሞ ስላገኘው “ ከትልቁ አሌክሳንደር በኋላ አንተ እጅግ በጣም ጥሩ አዛዥ ነህ ወይም ያለ ሥራ እዚህ ቆመህ መቀለድ የም ትፈልግ ሰው ነህ ” አለው ።

ምንም እንኳን አስተያየት ከመስጠት ቢቆጠብም በርግ በሕ ይወት ሆስነርን በማየቱ ተደሰተ ። “ ከሁለቱም በመጠኑ ነኝ ብየ አስባለሁ ። ” የሆስነር ደረት እራቁቱን እንደ ነበረና ጫማም ያላደ

ረገ መሆኑን እንደዚሁም ፊቱ በደም ሙበከሉን በርግ ተመለከተ ፡፡ የት ነበርክ ” ብሎ በረግ ጠየቀው ፡፡

“ እታች በቁልቁለቱ ላይ ነበርኩ ” ብሎት አቆልቁሎ ወደ ክል ላቸው ከተመለከተ በኋላ “ ብሪን በደፈጣ ተዋጊዎች ተገድሏል ” አለው ፡፡

“ እንደዚህ ሆነ ” ብሎ በርግ ሳይቀጣጠል ለትንሽ ጊዜ የቆየ የውን የፒፓ ትንባሆ አቀጣጠለ ፡፡ “ ብዙ ጉዳት ደርሶብናል ፡፡ ጣቢ ያዎቻችንም አለቀላቸው ብየ ፈርቼ ነበር ” አለው ፡፡

“ እኔም እንደ አንተ ገምቻለሁ ” አለው ሆስነር ፡፡

ሁለት ሴቶች ከምዕራብ ቁልቁለት ወደ እዝ ጣቢያው እያንዳ ንዳቸው ብዙ ጠመንጃዎች አንግተው መጡ ፡፡ አንደኛዋ ኤሸር አሮ ንሰን “ በእኛ በኩል ድል ተመትተዋል ፡፡ ከእኛ ጉዳት ያገኘው የለም ፡፡ አንዲት ሴት ግን የት እንደደረሰች ማወቅ አልተቻለም ” ብላ ለበ ርግና ለሆስነር ነገረቻቸው ፡፡

“ አስደናቂ ሥራ አከናውነሻል ” አላት በርግ ፡፡

“ እነዚህ ጠመንጃዎች በምስራቅ ቁልቁለት በኩል ላሉት ሰዎ ቻችን ይጠቅማሉ ብየ እገምታለሁ ” አለችው ፡፡

“ ልክ ነሽ ” ካላት በኋላ “ ለመሆኑ የጠፋችው ማናት ” ብሎ በርግ ጠየቃት ፡፡

“ ሚሪያም በርንስቴይን ትሆን አሁንም የእኛ ሰዎች በፍለጋ ላይ ናቸው ፡፡ ”

ሆስነር ለመናገር የፈለገ አልመሰለም ፡፡

ሁለቱ ሴቶች በጨለማው ውስጥ በችኮላ ሔዱ ፡፡

ሆስነር እጁን ዘርግቶ “ ፒፓህን ስጠኝ ” አለው ፡፡

በርግ ፒፓውን እየሰጠው “ ይህ ተአምር ነበር ?” ብሎ ጠየቀው፡፡

“ ለማለት አይቻልም ” አለው ሆስነር እጆቹ እየተንቀጠቀጡ፡፡

“ ለምን ? ”

“ ምክንያቱም የአምላክን ድምጽ አልሰማሁም ፡፡ ”

“ መስማት አለብህ ? አንተ ብቻ መስማት ይኖርብሃል ? ”

“ ትክክል ነው ፡፡ ”

በርግ ሳቀ ፡፡

ሆስነር ፒፓውን እየመለሰለት “ ዶብኪንስ ? ” ብሎ ጠየቀው ።
በርግ ትከሻውን ሰብቆ “ በሕይወት ካለ ተአምር አለ ” አለው።
“ ልክ ነህ ፤ ስማ — እኔ ወደ ምዕራብ ቁልቁለት ልሔድ ነው ። ”
“ ሁሉም ነገር ስለተፈጸመ መሔድ አስፈላጊ አይደለም ። ”
“ ይህን ጦርነት እንዴት እንደምናካሒደው አትንገረኝ በርግ ”
ብሎት ከጉብታው ላይ ዘሎ በመውረድ ወደ ምዕራብ ቁልቁለት ተራመደ ።

በርግ ከኋላው ተመለከተው ።

* * *

ኢብራሂም አሪፍ በድምጽ ማጉሊያው ድምጹን ከፍና ዝቅ እያደረገ “ እናንተ ትናንሽ ልጆች ወደ ቤታችሁ ሒዱ ። በጥሩ ሁኔታ ተመትታችኋል ። አሁን ወደ ቤታችሁ ተመልሳችሁ ፊታችሁን ሸሽጉ። ሳሌም ሀማዲ ትሰማኛለህ ? ወደ ቤትህ ተመልሰህ ከወጣት ወዳጅህ ጋር በአልጋ ላይ ተኛ ። በዚህ ሳምንት ተራው የማንኛው ነው ? የአሊ ? የአብደል ? የሳልማን ? ወይስ የአብደላ ? መሐመድ አሳድ በዚህ ሳምንት ከፍቅረኛህ ከአብደላ ጋር እንደ ነበርክ ታውቋል — ” አላቸው ።

አሪፍ በአልተለመደ ሁኔታ ለአረቦች ነገሩን እየቆሰቆሰ ተናገረ ። እንደዚያ እያንጐረ በሚናገርበት ጊዜ የልቡ ምት በደረቱ ላይ በኃይል ይታይ ነበር ። ቀደም ብሎ በውሀ እጦት ምክንያት ደርቆ የነበረው አፉ አሁን እንደ በረሃ ውስጥ አሸዋ ሆኖ ተሰማው ። በእርሱና በሪሽ የጭካኔ የማረጃ ጩቤ መካከል ጥይቶቻቸው በማለቅ ላይ ያሉ መሣሪያዎች የያዙ ጥቂት አይሁዳውያን ነበሩ ። በአላህ ተአምር በሕይወት ከዚህ ቦታ ቢወጣ እንኳን በአዲስ ብቀላ ጭምር ዕድሜውን ሙሉ አንድ ወቅት ወንድሞቼና እህቶቼ ብሎ በሚጠራቸው ሰዎች ሳይቀር እንደሚታደን ያውቃል ። ይህ የነገው ጭንቀት ነው ። የዛሬው ማታ ጭንቀት ግን ከሪሽ ጩቤ ማምለጥና የሆስነርን ትዕዛዝ በሥራ ላይ ማዋል ነው ። “ ወይም ሳሌም ፥ የዛሬ ማታህ አህያ ነው ወይስ ግመል ነው ? ወይስ ምናልባትም ጌታህና አለቃህ አህመድ ሪሽ ነው ? ”

ወጣቶቹ አሽባሎች በመደናገርና በመጨነቅ ለጩኸቱ አጸፋውን ሰጡ ። ሁለቱ ከተሸሸጉበት ወጥተው ወደ ተራራው ሲተኩሱ ወደዚያው በጥይት ተመቱ ። ጥቂቶቹ ከመሣሪያዎቻቸው ምላጮች ላይ ጣቶቻቸውን ሳያነሱ በብዛት ያለማቋረጥ ስለተኮሱ የኤኬ - 47 ጠመንጃዎቻቸው ካርታዎች በኃይል በመጋላቸው ፈነዱ ።

አህመድ ሪሽ ከራዲዮኑ ሠራተኛው ጋር በአንድ ቦይ ውስጥ ቁጢጥ ብሎ ተቀምጧል ። ሳሌም ሀማዲም ትንሽ ሜትሮች እልፍ ብሎ ተቀምጧል ። በጨለማው ውስጥ የሚያለቅስ ወይም የሚጸልይ ይመስል ከራሱ ጋር ይነጋገራል ። ሪሽ ጠርቶ “ ተነሳ ! አንድ የመጨረሻ ሙከራ ማድረግ አለብን ። የጠላቶቻችን ጥይቶች እያለቁባቸው መሆን አለባቸው ። ጨረቃዋም ገና አልወጣችም ። ስለዚህ ተነሳ ! የመጨረሻ ሙከራ እናድርግ ። እኛው ራሳችን ጠሩን መምራት አለብን ” አለው ።

ሀማዲ ተነስቶ በአህመድ ሪሽ ጐን ቆመ ። የቀሩት አብዛኞቹ አሽባሎቹ በድናቸውን ሆነው ተከተሏቸው ።

እስራኤሎቹ ነጭ ጋዝ እየሞሉ በወረወሩአቸው ፈንጂዎች አሽባሎቹ ተቃጥለዋል ፤ በጥይት ተጠዝጥዘዋል ። በተጨማሪም ከላይ የወረዱት ናዳዎች የግማሾቹን እግሮች አቁስለዋቸዋል ። ሌሎቹንም ተደርብቶባቸዋል ።

በመጨረሻም እንዲያፈገፍጉ ከኋላቸው ጥሪ በማድረግ “ ተመለሱ ! ተመለሱ ! አብቅቷል ! ወደ ኋላ አፈግፍጉ ! ” የሚል ድምጽ ሰሙ ።

አብደል ጃባሪ በእረኛው ጐጆ አጠገብ ተቀምጦ በድምጽ ማጉሊያው “ ተመለሱ ! ተመለሱ ! አልቋል ! ወደኋላችሁ ተመለሱ ! ” አላቸው ። የድምጽ ማጉሊያው ሽቦ ከቁጥር ሁለት የትዕዛዝ ማስተላለፊያ ጀምሮ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት መቅረቱ የሚያስደንቅ ነበር። ደቦራ ጌዲዮን በድምጹ ነቅታ የቀባችውን የሸክላ አፈር ከፊቷ ላይ ጠርጋ በጉድጓዱ ውስጥ ሆና አሻቅባ ወደ ሰማይ ተመለከተች ። ውበታቸው የማይታመን የሆኑና የሚያንጸባርቁ ኮከቦች በራስዋ አቅጣጫ አየች ። ቀጥላም ከበላይዋ በኩል ፍጥነት ያላቸው የሰዎች እርምጃዎች ሰማች ። የኮከቦቹን ብርሃን የሚጋርድ ጥላ ከላይ ሲያር ፍባት ዓይኖቿን ጨፈነች ።

“ ተመለሱ ” ብሎ ጃባሪ ጮኸ ። ወጣት አሽባሎቹ የአሁኑም ድምጽ ቀድሞ የሰሙት እንደነበረ ቢያውቁም የተመለሱት አሁን በሰሙት ድምጽ እንዳልሆነ አስመሰሉ ። እንደ አህመድ ሪሽ ያለ ሌላ ጠንካራና ኃይለኛ ድምጽ ወደፊት እንዲሔዱ አዘዛቸው ። ድምጹ በጨለማው ውስጥ እየሰነጠቀ ከመምጣቱም በላይ በመስክ ራዲዮኖች ጭምር ይጠቀሙ ነበር ። “ ወደፊት ! ተዋጉ ! ተከተሉኝ ! ” የሚል ድምጽ ሰሙ ። ከሩቅ የሚሰማው ሌላው ድምጽ ደግሞ “ተመለሱ ! ወደኋላ አፈግፍጉ ! ” የሚል ነበር ። ወደ ላይ ከመውጣት

ወደ ታች መሔድ በጣም ቀላል ለመሆኑ የተረጋገጠ ነው ። ሁኔታውን በመስማት በተወሰደው እርምጃ መሠረት ከእስራኤሎቹ የሚሰማው ተኩስ ቀነሰ ። አሽባሎቹ ነገሩን እንደተመለከቱት ትርጉሙ ግልጽ ነበር ። “ በቁልቁለቱ ላይ ስላልተከበባችሁ ተመልሳችሁ ለመሔድ ትችላላችሁ ” ብለው እስራኤሎቹ የሚናገሩ መሰሉ ።

በምሥራቃዊ መከላከያ መስመር አቅራቢያ ፒተር ካንና ዴቪድ ቤከር ናይትሮጅን በያዘ በአንድ ትልቅ ደንበኛን አጠገብ ቆመዋል ። ካንና ቤከር በነጭ ጋዝ የጨቀዩትን ወንበሮችና ጉማዎች በእሳት አያ ይዘው የናይትሮጂኑን ማስተንፈሻ ካን ሲከፍተው የተቀጣጠሉት ወንበሮችና ጉማዎች ወደ አየር ተሽከርክረው በመውጣትና እንደገና አቀልቁሎ በመውረድ ካረፉ በኋላ እንደገና እየነጠሩ በቁልቁለቱ ላይ ስለወረዱ ያለፉበትን ቦታ አሽባሎቹ የነበሩበትን ጭምር በእሳት አያ ያዙት ። በደቡብ አቅጣጫም እንደዚሁ ስላደረጉ በጠላት ላይ ከፍ ተኛ ጥፋት አደረሱ ።

በዚህ ጊዜ አሽባሎቹ በመጀመሪያ በከፊል ቀጥሎም አዛዥ መኰ ንኖችና የአምሳ አለቆች ጭምር በሙሉ ተመልሰው በሩጫ ሳይሆን መስመራቸውን ጠብቀው በፍጥነት ወደኋላቸው አፈገፈጉ ። እንደ አመቺነቱ ቁስለኞቹን ይዘው ሲመለሱ የሞቱትንና በጣዕር ላይ የነ በሩትን ለጥንብ አንሳና ለቀበሮ ትተዋቸው ሔዱ ።

የበርግ መልከተኛ ከመድረሱ በፊት እስራኤሎቹ ተኩሱን አቆሙ።

እስራኤሎቹ ተኩስ በማቆማቸው ምክንያት አሽባሎቹ የወደቁ ባቸውን ብዙ ዕቃዎች ለመሰብሰብ ቻሉ ። የጦር ማቆሙን እርምጃ የወሰዱት አሽባሎቹ እንጂ አለቆቻቸው አልነበሩም ። በርግ በበኩሉ የተወሰደው እርምጃ አስፈላጊ ሆኖ አገኘቶታል ።

በተራራው ላይ ሆነ በቁልቁለቱ በጠቅላላው በአካባቢው ጸጥታ ሰፈነ ። ከምሥራቅ በኩል የነፈሰው ነፋስ የነበረውን የጥይት ፣ የነጭ ጋዝና የሌሎቹንም ሽታ ወሰደው ። ቀበሮዎቹ በጨለማው ውስጥ መጮኽ ጀመሩ ። በአገኙት የተደሰቱ መሆናቸውን ከጩኸታቸው ለማ ወቅ ይቻል ነበር ።

በርግ ሰዓቱን ተመልክቶ ጦርነቱ በጠቅላላው 39 ደቂቃ የፈጀ መሆኑን ተገነዘበ ።

## —23—

ዶብኪን በኤፍራጥስ ወንዝ ምዕራብ ዳርቻ አጠገብ ተጋድሞ ደሙ በመፍሰስ ላይ ነው ። ጸጥታውን ስለሰማ ምን ማለት እንደሆነ አልገባውም ። በእርግጥ ሁለት ትርጉም ሊሰጠው ይችል ነበር ። ባለ

ፈው 15 ደቂቃ ውስጥ የነበረውን ድምጽ በአዕምሮው ውስጥ ለማብላላት ሞከረ ። ግን በጭኑ ላይ የነበረው ሕመም ትዕግሥት ስላልሰጠው ማውጠንጠን አልቻለም።አረቦቹ ቢያሸንፉ ኖሮ ሲቦርቁ ይሰማው ነበር። ሕመሙን ውጦ በጥንቃቄ ለማዳመጥ ቢሞክርም ከጸጥታ በስተቀር ምንም አልነበረም ። ሕመሙና ድካሙ ነፍሱን እንዲስት አደረጉት።

* * *

ሆስነር በምዕራባዊ ቁልቁለት በደቡብ ጫፍ አጠገብ አገኛት ። ወደ ወንዙ አቆልቁላ እየተመለከተች ነበረች ። በአንድ እጅዋ በጉንዋ በኩል ጠመንጃ ይዛለች ። ሆስነር ጥቂት ሜትሮች እራቅ ብሎ በጉንዋ በመቆም ከወንዙ በሚንጸባረቀው ብርሃን ትኩር አድርጎ ተመለከታት ። “ አንድ ሰው ገድለሻል ” አላት ።

ራስዋን በፍጥነት አዙራ “ እኔ . . . አንተ ግን ደህና ነህ ? ” ብላ ጠመንጃውን በመሬቱ ላይ ጥላ ወደ እርሱ ዞረች ።

ሆስነር ያቅማማ መሰለ ። የግብረ ሥጋ ግንኙነት አንድ ነገር ነው ። ሌላው ደግሞ ጥልቅ ግዴታ ውስጥ ከገቡ በኋላ ሲነጋ ፍቅር ማሳየት ነው ። እርሱ ግን ለዚያ ዝግጁ መሆኑን አላወቀም ።

“ አንቺስ . . . ”

እርስዋም ከአቅማማች በኋላ “ እዚህ ነኝ ፤ አልተማረኩም ” ብላው ሳቅ አለች ።

“ እኔም እንደአንቺው ነኝ ። ተወጥተነዋል ። ”

“ አንዲት ወጣት ሴት ገደልኩ ። ”

“ በጦርነት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥይት የተኮሰ ሁሉ ሰው የገደለ ይመስለዋል ። ”

“ በእርግጥ ገድያታለሁ ። በቁልቁለቱ ላይ ወድቃለች ። ”

“ በጨረፍታ ተመትታ ሮጣለች ። ”

“ የመታኋት እደረቷ ላይ ነው ። ”

“ እባክሽ አትጃጃይ ። ” አለመግደልዋን አውቋል ። “ ጉበዝ ሚሪያም ፤ ወደ ክበባችን እንኳን ደህና መጣሽ ” ሊላት ቢፈልግም ከአፉ አውጥቶ መናገር አላሻም ። “ ስለተኮሽ አንድ ሰው ገድያለሁ ብለሽ አስበሻል ። ለመሆኑ ስትጮኺ ሰምተሻል ? ”

“ እኔ . . . አላውቅም ። ሊሆን ይችላል ። ”

“ መመለስ ስላለብኝ ከእኔ ጋር ነይ ። ”

ጠመንጃዋን አንስታ ተከተለችው ። እግዜር ይስጥልኝ ማለት ፈልጋ ነበር ። ግን በዚያ ፋንታ " አፈቅርሃለሁ " አለችው ። በድጋሚ ዞራ " አፈቅርሃለሁ " አለችው ።

ቆመ ፡ ግን አልዞረም ። ሊያደርገው እንደማይችል አውቋል ። እርስዋም ለማድረግ እድሉ አላጋጠማትም ይሆናል ። የምትሞት ብት ሆን ኖርና እንደሚያፈቅራት ባይነግራት ኖሮ ከባድ ጸጸት ይሆን ነበር። የምትኖር ብትሆንና " አፈቅርሻለሁ " ቢላት ደግሞ የበለጠ ሀዘን ያሆንባታል ። ወደፊት እርምጃውን እንደቀጠለ የእርስዋንም የእግር ኮቴ ሰማ ።

* * *

ቄስ ሌቪን የቆሰሉትን ወደ ጐጆው አብሮ ተሸክሞ በመውሰድና የሚያከሙትን በመርዳትና ቁስለኞቹን በማጽናናት ከፍተኛ አስተዋ ጽኦ አደረገ ። ዓይኖቹ ወደ ውስጥ ጐርጉደውና በደም ተበክሎ ላየው ሰው ራሱ የተመታ ይመስል ነበር ።

በጐጆው ውስጥና በዙሪያው የነበሩትን ቁስለኞች የትናንቱንና የዛሬውን እየለየ በዝርዝር በማስታወሻው ውስጥ እየጻፈ ስለሕመ ማቸው መሻሻል ወይም መጥናት ይከታተል ነበር ። ከሕመምተኞቹ ውስጥ ታሚር ለውጥ አላሳየም ። የሆስነር ሦስት ሰዎች - ሩቢን ያዝ ለቀቅ ያደርገዋል ፤ ጃፍ ለውጥ አላሳየም ፤ ካፕላን እንደገና እየደማ ነው- ብሪን መሞቱ ተነግሮታል ። ማርክስና አልፐርን ከሆስነር ስድስት ሰዎች ውስጥ አሁንም በጥንካሬ መሥራት ይችላሉ ። ሩት ማንደል አሁንም ትኩሳት አላት ። ዳንኤል ጃኮቢና ራሄል ባኡም ይህን ያህልም አይደሉም ። አቤል ጊለር ደሙ እየፈሰሰ በወለሉ ላይ ከመንጣለሉም በላይ ነጭ ልብሱ ቀልቷል ። ቄስ ሌቪን ይሠራና ሕመምተኞቹን ያጽናና የነበረው በተንጣለለው ደም ላይ እየተመላለሰ ነበር ። ሌሎች ስድስት ሰዎች የቆሰሉና ያላያቸው ስለነበሩ ስማቸው እስኪ ደርሰው ድረስ በማስታወሻው ውስጥ ተራ ቁጥር ሰጣቸው ።

ቄሱ አየር ስለአስፈለገው ወደ ውጭ ወጣ ። ግን በዚያም የበለጠ እልቂት ነበር ። ሺሞን ፔልድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ረዳት የጐ ጆውን ግድግዳ እንደ ተንተራሰ ሞቷል ። የሞተው በደረሰበት መጠ ነኛ ቁስል ሳይሆን በልብ ድካም ነበር ። በጦርነት ላይ እንዳይሠማራ ቢከለከልም አሻፈረኝ ብሎ ጠመንጃ ወስዶ ተዋጋ ። ቄሱ ራሱን በአ ሉታ በማነቃነቅ ሀዘኑን ከገለጸ በኋላ ፎጣ ፈልጐ ፊቱን ሸፈነው ። የሙ ታኖችን ፊት መሸፈን የተለመደ ባሕል ነበር ። እንደዚሁም ሁለት ወጣት ሴቶች ግድግዳውን እንደተደገፉ ሞተው ስለነበረ አይኖቻቸውን ጨፍኖና አስተካክሎ ካስተኛቸው በኋላ ፎጣ አለበሳቸው ። ይህም

ሌላ የተለየ አስደናቂ ባሕል ነበር ። የስማቸውን ዝርዝር በኋላ ያገ ኘዋል ።

በየትዕዛዝ መስጫ ጣቢያዎች የሞቱት ስድስት ወንዶች እጅግ በጣም ከፍተኛው ጉዳት ነበር - ደቦራ ጌዲዮን ፣ ይጋል ቴኮ - ሚካ ጉረን ፣ ሀና ሺሎ ፣ ሪዩበን ታቦርና ሊ ኤልሳር ስለነበሩ የሁሉንም ስም በማስታወሻው ውስጥ ጻፈ ። የአንድ ወይም የሁለት ደቂቃ ጊዜ ሲኖረው ለሞቱት ጸሎት ያደርግላቸው ነበር ።

ሆስነር የት ይሆን ? ይሙት ወይም በሕይወት ይኑር ወይም ይማ ረክ አልታወቀም ። ይሁን እንጂ ያዕቆብ ሆስነር በአንድ ጊዜ ሦስቱን መሆን አይችልም ። ቄስ ሌቪን ያለ ሆስነር በጣም የተሻለ ወይም በጣም መጥፎ መሆን ይቻል ይሆን ብሎ አሰበ ። ጄኔራል ዶብኪንስ ? ቤን ዶብኪን አላማው ተሳክቶለት ይሆን ? ለቤን ዶብኪን ልዩ ጸሎት ማድ ረግ አለበት ።

ቄሱ ወደ ጉጆው ውስጥ እንደተለመለሰ ቤተ አብራምስ በሙ ቀቱና በክርፋቱ ተዝለፍልፋ ስለአገኛት ታቅፎ ወደ ውጭ ይዟት ሲወጣ እጁ ላይ እንዳለች ወደ ሕክምና ሥራዋ እንድትመለስ ጠየቀችው ። ቄሱ ተንፍሶ እንድትሔድ ፈቀደላት ። በእርግጥ ረጅምና አስቸጋሪ ሌሊት ሊሆን ነው ። ቄሱ ትክክል ያልሆነ ሃሣብ ነበረው - እያንዳ ንዱ በመጀመሪያ ራሱን ከጠበቀ ፣ እያንዳንዱ ቢያንስ እርሱን የሚ ጠብቀው አንድ ሰው ይኖራል - ይህ ከአንድ ቄስ ሊነገር የሚገባው አልነበረም ። ግን ቄሱ አባባሉን ይወደዋል ። በኃይል ተንፍሶ ወደ ጉጆው ተመልሶ ሔደ ።

በዚህ ሌሊት በእስራኤሎቹ መካከል ክብረ በአል አይኖርም ። ምንም እንኳን ሊታመን የማይቻል ጀብዱ ቢፈጽሙም ወደፊት ከፍ ተኛ ጉዳት ብቻ ሳይሆን እጅግ አስከፊው ገና እንደሚመጣ አውቀዋል ። ቁስለኞቹ ውሀ በብዛት እየጠጡ ነበሩ ። እንደዚሁም ማንቋረርና ጩኸታቸው በስፋት በመሰማቱ የሌሎቹን ሞራል እየነካው ነበር ።

ጥቂት ሰዎች የወደቁ መሣሪያዎችን ለመሰብሰብ ወደ ቁልቁለቱ ወረዱ ። ሦስት ሌሎች ቡድኖች ደግሞ በየጣቢያዎቹ የደረሰውን ጉዳት ለማየት ሔዱ ። የተበረቃቀሰውን የሚካ ጉረንንና የሀና ሺሎን ሬሳ ዎች ይዘው በመጡ ጊዜ በዚያ ከነበሩት ተከላካዮች አብዛኞቹ እንባ በእንባ ሆኑ ። በራሳቸው ላይ ተመትተው የሞቱት የሪዩበን ታቦርና የሊ ኤልሳር ሬሳዎችም በአረኛው ጉጆ በስተጀርባ ከሌሎች ጋር እንዲ ቀመጥ ተደረገ ።

አልፎ አልፎ በቁልቁለቱ ተኩስ ቢሰማም በተራራው ላይ የነ በሩት ወንዶችና ሴቶች ተኩሱን እንዳልሰሙ ለማስመሰል ሞክረዋል። ይሁን እንጂ ከአረቦቹ ቁስለኞች በኩል ብዙ ማንቋረር እንዳልነበረ አስታውሰዋል ።

እስራኤሎቹ ይጋል ቴኮ እንደአደረገው ምራላቸውን ከፍ የሚ ያደርግ በጣም ይፈልጋሉ ። እርሱ ለሕይወቱ ሳይሳሳ ከቀበሮ ጉድ ጓድ ወጥቶ ሁሉም እንዲሰሙ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት እየዞረ ጮኸ። ጀግናው ይጋል አሁን በሕይወት ካሉት ቁስለኞች አንዱ ነው ። ወደ ክልሉ ሲያመጡት ነፍሱን ስቶ እየቃዠ ደቦራ ጌዲዮንን ለማ ዳን የሠራውን በመንገርና አሁን የት እንዳለች ጠየቃቸው ። እርሱ በነ ገራቸው መሠረት ክትትል እንዲደረግ መልዕክተኛ መላካቸውን አረ ጋገጡለት ።

በቁጥር 2 ጣቢያ አጠገብ በአሸዋው ላይ ተጋድማ እንደነበረ ምልክት አግኝተዋል ። አሁን ግን በዚያ ግድም ባለመኖርዋ እየተ ጣሩ በአካባቢው ሁሉ ፈልገው ስላላገኟት በጠላት ተወስዳ ይሆናል ብለው አሰቡ ።

* * *

ያዕቆብ ሆስነር ከበርግ ጋር ሆኖ በሕንጻው ማማ ላይ በመቆም በምሥራቅ በኩል ሙሉ ጨረቃ ስትወጣ አየ ። ጨረቃዋ ያለምንም ግርዶሽ ከጠለቀች አህመድ ሪሽ ዛሬ ማታ እንደ እብድ ይጮኻል ። ቁልቁለቱና ዳገቱ በሙሉ በብርሃን ስለሚሞላ የሚደርሰው እልቂት አንድ በአንድ ይታያል ። “ ጨረቃዋ እስክትጠልቅ ድረስ የሚኖረው ይኸው ነው ” አለ ሆስነር ።

በርግ በአዎንታ ራሱን አነቃነቀ ። የሚቀጥለው ጨለማ የሚ ሆነው እንጋት ላይ ጨረቃ ስትጠልቅና ንጋት ሲጀምር የሚኖረው ድንግዝግዝ ነው ። ይህም አንድ ሰዓት ተኩል ያህል ይፈጃል ። ምናል ባት አህመድ ሪሽ በዚያን ጊዜ ለመውጋት ይሞክር ይሆናል ። በድን ግዝግዙ ምክንያት በዳገቱ ላይ ቢቆዩ አህመድ ሪሽና ተከታዮቹ ያበ ቃላቸዋል ።

በጦር ሠፈሩ ቁስለኞቹ ሲያንቋርሩ ፣ ሲጮሁ ፣ ሲያለቅሱ ፣ ሠራ ተኞች ከአንዱ ወደ ሌላው ሲሯሯጡ ፣ ሪፖርት ሲያመላልሱ ሌሊቱን ሙሉ አሳለፉ ።

* * *

ሆስነር ከወደቀበት ያልተነሳውን የናታን ብሪንን ሬሳ ትኩር አድርጎ ተመለከተው ። ጮኾ አንድ ነገር ለመናገር ወይም ሬሳውን በእጁ ለመንካት ፈለገ ። ግን ናኦሚ ሀበር የኮከብ ብርሃን ያለውን

መሣሪያ ይዛ ከመቆየቷም በላይ በብርክ መንገዳገድ ጀምራ ነበር ። ከፍተኛ አስተሳሰብና ጀግንነት የነበረው ናታን ብሪንን ሳይናገረው በውስጡ ደህና ሁን ብሎት በማለፍ በሴትዮዋ ላይ እጁን ጣል አደረገ ። ወጣት ሰዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ምን ያህል በፍቅር እንደሚተሳሰሩ አድንቆ በራሱ ላይ የደረሰውን ሁኔታ አስታወሰ ። " እኔ በጣም የማከብራት አንዲት ሴት ዛሬ ማታ ሰው ለመግደል ተገዳ ነበር ። የታወቀች የሰላም ታጋይ ናት ። ይሁን እንጂ በግድያው እንድትገባ ሁኔታው አስገደዳት ። "

ናኦሚ ጠመንጃውን አስቀምጣ " ደህና ነኝ ፤ ስለምቋቋመው ሥራዬን እቀጥላለሁ " ብላ እንባዋን ከዓይኖቿ ላይ ጠርጋ ወደ ሥራዋ ተመለሰች ።

ሆስነር ብቻውን የከልላቸውን መስመር እየተዘዋወረ ፍተሻውን ቀጠለ ። ሌሊቱ እየገፋ ሲሔድ የቁስለኞቹ ሰቀቀን እየቀነሰ መጣ ። በተራራው በመከላከል ሥራ ላይ የተሰማሩት ሞራል እንደ ቀድሞው ስለተመለሰ ሁሉም በሚገባ መሥራት ጀመሩ ።ያለውን ውሃና ጥይት አከፋፈሏቸው ። ቁስለኞቹም ጥሩ እንክብካቤ ተደረገላቸው ። በሚቻልበት ሁሉ ለመከላከያ ምሽጎች ጥገና ተደረገላቸው ።

ሆስነር ፍተሻውን ከጨረሰ በኋላ ከበርግ ጋር ተገናኝቶ ሁለቱም በኮንኮርዱ ውስጥ ወደ አለው የነጂዎች ክፍል ሔደው ሲገቡ ቤከር ራዲዮኑን ሲሠራ አገኙት ። የራዲዮኑ ጫጫታ ክፍሉን ሞልቶታል ። አጥፍቶ በስተጀርባው ላሉት ሁለት ሰዎች " ሌየሩ አሁንም በሥራ ላይ ነው ። ምናልባትም ፀሐይ እስክትወጣ ድረስ ነዳጅ ለመሙላት አይሔድም ይሆናል " አላቸው ።

" መልካም ፀሐይ ስትወጣ እንደገና እንሞክረዋለን " ብሎት ሆስነር የቤከር ድርሻ የሆነውን ጣፋጭ ወይን ጠጣ ። ስለሪሽ የተጻፈውን ማስታወሻ አንስቶ ገጹን እያገላበጠ ተመለከተ ። " አዋቂ ከሆኑት አንዱ የአዕምሮ ሐኪማችን አህመድ ሪሽ መታከም እንዳለበት ጽፏል ። ግን ምን ዓይነት ሕክምና እንደሆነ አልገለጸም ። እኔ እንደሚመስለኝ ራሱን ማለቱ ነው " ካለው በኋላ ቀና ብሎ በመመልከት "ይስሐቅ ፣ አንተ ሪሽን ብትሆን ኖሮ በሚቀጥለው የምታደርገው ምን ይሆን ነበር ? " ብሎ ጠየቀው ።

በርግ በክፍሉ ውስጥ በተሽከርካሪ ወንበሩ ዞሮና እግሮቹን አነባብሮ " እብድነት ካለብኝ በብቀላ ምኞት በመሠየት እነዚያ ምስኪኖች ወደ ተራራው ተመልሰው እንዲወጡ በማስገደድ እንዲዋጉ የማደርግ ይመስለኛል " አለው ።

" ግን ይከተሉታል ? " ብሎ ቤከር ጠየቀው ።

“ አስቀድመን መገምገም ያለብን ይህን ነው” አለው ሆስነር። “ እንደማስበው ሪሽ አባብሎ እሺ ሊያሰኛቸው ይችላል ። ይህን ማድረግ ይችላል ። በአሁኑ ጊዜ አንዲት ሴት በምርኮኝነት ይዟል ። ስለእኛ የተናገረችውን ብትናገር ሪሽ የሚሰጠው ትርጉም ለእርሱ እንደሚስማማው አድርጎ ነው ። ”

በክፍሉ ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ጸጥታ ከሰፈነ በኋላ እያንዳንዳቸው ራሳቸውን በደቦራ ጌዲዮን ቦታ አድርገው ሲመለከቱ ራቁቷን ፣ ግፍ እየተፈጸመባት ፣ ሰውነቷ ደቆ ፣ ብቻዋን . . . በመሞት ላይ እንዳለች ታሰባቸው ። ሆስነር የምታውቀውን ምሥጢር ሁሉ አውጥታ በመናገር ሕይወትዋን እንደምታተርፍ ተስፋ አደረገ ። ምሥጢር መጠበቁ ለሚደርስባት ሥቃይ ወይም መከራ ተመጣጣኝ አይደለም። ስለሚያስደስታቸው ብቻ ያሰቃዩዋት ይሆናል የሚል ፍርሀት አደረበት ።

ቤከር ከበርሜ ፒፓ ትንባሆ ወስዶ በወረቀት ከጠቀለለና ጉሮሮውን ካፍታታ በኋላ “ አሁንስ ጠላቶቻችን በምን ሁኔታ ላይ ይገኙ ይሆን ? ” ብሎ ጠየቃቸው ።

ቤከር ጥንቁቅ መሆኑን ሆስነር ያውቃል ። “30 ጠመንጃዎች ቢኖሩንም ከቀድሞው የበለጡ ጥይቶች የሉንም ። የሚኖሩን ለእያንዳንዳቸው ከ100 ያላነሱ ጥይቶች ይሆናሉ ። የመከላከያ መስመሮቻችንም የተመሰቃቀሉ ስለሆኑ እንደገና ለመገንባት ውሃም ሆነ የሰው ኃይል የለንም ። በልዩ ልዩ መልክ ቀድሞ ያዘጋጀናቸውን ጨርሰን ስለተጠቀምንባቸውና ስለተኮስናቸው ጠላት በድጋሚ የሚታለል አይሆንም ። ብሬን ሞቷል ። የኮከብ ብርሃን መነጽሩ ባትሪው እያለቀ ስለሆነ ከጥቅም ውጭ እየሆነ ነው ። ለማንኛውም ለኤም - 14 አሥር ጥይቶች ብቻ ቀርተዋል ። ሁለት ሰዎች የማጉሊያ መነጽሩን በኤኬ 47 ላይ ለመግጠም እየሞከሩ ናቸው ”ካላቸው በኋላ አንድ ጉንጭ የወይን ጠጅ ጠጥቶ “ በነገራችን ላይ ነጭ ጋዝ እንዴት ነው ? ” ብሎ ጠየቃቸው ።

ቤከር ፈገግ ብሎ “ መሣሪያዎቹ በትክክል አይመቱም ብሎ ለማመን ከባድ ነው ። እቃዎቹን ግን ከየት እንደምታመጧቸው አላውቅም ” አለው ።

ሆስነር ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ “ ቄሱ እንዲያውቀው አታድርጉ ፤ የሰማ እንደሆን በቅባ ቅዱስ ኃይል የተደረገ ተአምር ነው በማለት ይሰብካል ። የሆነው ይሁን የመያዣ ዕቃዎች የሉንም ። ለፈንጅነት ያዘጋጀናቸው ዕቃዎች በሥራ ላይ ውለዋል ” ካላቸው በኋላ የወይን ጠጁን ጨርሶ ጠጥቶ ጠርሙሱን በወለሉ ላይ ጣለው ።

" ጥያቄህ የተደቀኑብን ችግሮች እንዴት ናቸው የሚል ነበር ። ሁሉም ነገር በአሸባሎቹ ውሳኔ የሚሆን ነው ። እኛ እዚህ የምናቀርበው ወይም የምንሰጠው ውሳኔ የለንም ። እኛ ያለብን እነእርሱ በሚቀጥለው የሚያደርጉትን መጠበቅ ብቻ ነው " ብሎ ስለ አህመድ ሪሽ የተጻፈውን እንደገና ገልብጦ የአህመድ ሪሽን ፎቶግራፍ ትኩር አድርጎ ተመልክቶ በረጋ አነጋገር " አህመድ ሪሽ ትንሽ የሚያስብ አዕምሮ ካለህ ባቢሎን መቀበሪያህ ከመሆኑ በፊት ጓዝህን ጠቅልለህ ከዚህ መውጣት አለብህ ። ነገር ግን እንደማታደርገው የታወቀ ነው " አለ።

## —24—

ቴዲ ላስኮቭ የሪሽን ፎቶግራፍ አቆልቁሎ እየተመለከተ "ንገረኝ አህመድ " አለው ፎቶግራፉ መልስ ይሰጠው ይመስል ።

ኢዝሐቅ ታልማን ከብርጭቆው ፉት ካለ በኋላ የሪሽ የሕይወት ታሪክ የተጻፈበትን ማስታወሻ እያገላበጠ " እስከ አሁን ከእርሱ ምንም ነገር አልሰማንም ? የሚፈልገው ምንድን ነው ? " ብሎ ጠየቀ ።

የሚቸል ቡና ቤት በሰው የተሞላ ከመሆኑም በላይ እያንዳንዱ የሚያወራው ስለሰላም ተደራዳሪዎች ነበር ። ስለሌላ ማውራት የአገር ፍቅር የሌለው ያስመስል ነበር ። በቡና ቤቱ ውስጥ የነበሩት ሁሉ ሁለቱን ጀኔራሎች ቢያውቋቸውም ወደ እነእርሱ የሚመለከት አልነበረም ።

ላስኮቭ ቮድካውን ቀምሶ " በቁጥጥሩ ሥር አውሎአቸዋል ብየ አላምንም።ቢማረኩ ኖሮ ከሪሽ እስከ አሁን እንሰማ ነበር"አለው።

" ካልተማረኩ ሞተዋል ማለት ነው ቴዲ ። "

ላስኮቭ ቮድካውን እየጠጣ በጠረጴዛው ላይ ጉብደድ በማለት " በሕይወት እንዳሉ ይሰማኛል " አለው ።

" ታዲያ የተማረኩት የት ነው ? "

" ባቢሎን ። " ቃሉ ታልማንን ያስደነቀውን ያህል እርሱንም አስገርሞታል ። ምክንያቱም ምናልባት እነእርሱ የተጠቀሙበት ቃል " ጁሆ " ( መያዣ ) የሚል ሳይሆን ምርኮኛ ወይም እስረኛ የሚል በመሆኑ ይሆናል ። የተነገረውን ቃል አዛምዶ በጥልቀት መመርመር አማራጭ የሌለው ነው ። ምናልባት ቮድካው ረድቶት ይሆናል ። ወይም በአጋጣሚ በመጠጥ ጊዜ ፈንቅሎ ከአዕምሮ የሚወጣ ቃል ሊሆን ይችላል ። ላስኮቭ " ባቢሎን " ብሎ ደግሞ ተና

ገረ ። አሁንም እንደገና ቆሞ “ ባቢሎን ” አለ ። ጮኾ “ ባቢሎን ” ስለአለ ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ ዞሩ ። ታልማን ክንዱን ቢይዘውም ላስኮቭ መነጨቀው ። ለታልማን ጥቂት ማስታወሻዎች በጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ የቀሩትን ወረቀቶቹን ሰብስቦ በቦርሳው ውስጥ ካስገባ በኋላ እየሮጠ ወደ ጐዳናው ሔደ ።

ላስኮቭ በተሳፈረበትና ለመሔድ መንቀሳቀስ በጀመረው ታክሲ ላይ ታልማን ዘሎ በመውጣት በላስኮቭ ጐን ተቀመጠ ። “ ኢየሩሳሌም ” ብሎ ላስኮቭ በነጂው ላይ ጮኸበት ። ቀጥሎም “ ለአስቸኳይ ብሔራዊ ጉዳይ ! ” አለው ። ታልማን መኪናው በመሔድ ላይ እያለ መዝጊያውን ዘጋው ። ነጂው “ ለአስቸኳይ ብሔራዊ ጉዳይ ” ተብሎ ለተነገረው የፍጥነት ሕግን ለመተላለፍ ልምድ ባይኖረውም የቅዱስ ጊዮርጊስን አደባባይ ዞሮ ወደ ኢየሩሳሌም መንገድ አመራ ።

ላስኮቭ አሁን ከቀድሞው ረጋ ብሎ “ ባቢሎን ” አለ ።

ነጂው በመስታዎቱ አማካይነት የተሳፋሪዎቹን ፊት ተመለከተ ።

“ ባቢሎን ፤ አዎን ፤ አዎን ፤ ይሆናል ፤ ባቢሎን ” አለ ታልማን ያለጽኑ እምነት ።

* * *

“ ባቢሎን ” ብሎ ያዕቆብ ሆስነር የሪሽ ታሪክ የተጻፈበትን ማስታወሻ ተመለከተ ። “ ባቢሎን ብቸኛ ሆና የመቆየቷን ያህል ከሰው ልጅ አዕምሮ መጥፎ ድርጊት ጋር ሲነጻጸር እይታዋ በጣም አስፈሪ አልነበረም ። ይህን በአንድ ወቅት በአንድ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦታል ። ሆስነር የካን ድርሻ የሆነ ግማሽ ጠርሙስ የወይን ጠጅ ስላገኘ አንስቶ “ የተሻለ ነው ፤ ግን አሁንም ጥሩ አይደለም ” ካለ በኋላ አፉን ከፍቶ በኃይል ቢጠጣም ለመዋጥ ስላልቻለ ተፋው ። “እንደገና ወደ ኃይፋ የመመለስ ዕድል ቢያጋጥመኝ አቅሜንና ችሎታዬን የማውለው የአገር ውስጥ የወይን ጠጅ በተሻለ ሁኔታ በሚስፋፋበት ላይ ይሆናል ። ”

ቤከር በሆስነር አስተሳሰብም ሆነ የወደፊት ዕቅድ አልተማረከም ። “ እኔን የሚያበሳጨኝ በዚህ እብድ ምክንያት እዚህ መቆየታችን ነው ። ችግር ፈጣሪዎቹ እኛ አይደለንም ። ”

“ ምናልባት እኛ መሆን ይገባን ይሆናል ። ምናልባትም ከመከላከል ወደ ማጥቃት መሔድ ያለብን ጊዜው አሁን ነው ” አለው ሆስነር ።

በርግ የአደጋ ምልክት ይዞ ከተነሳ በኋላ “ ትርጉሙ ምንድን ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ሆስነር ተነስቶ "ምናልባት ጊዜያዊ ምሽጋቸው ወደ አለበት ኢሽ ታር መግቢያ ተመልሰው ይሆናል ። ጨረቃ ስትጠልቅ እንደገና የሚ ወጉን ከሆነ ከቁልቁለቱ መድረሻ ላይ ካለው ሜዳ ራቅ ብለው መሰ ብሰብ ይኖርባቸዋል ። ያም የወታደር ሥርዓት ነው ። ለዚህም የሚ ሆናቸው በጣም አመቺው ቦታ ከተማውን ከልሎ የሚገኘው የግንብ አጥር ይሆናል ። ስለዚህ እኛ ከአስር እስከ አሥራ አምስት የሚሆኑ የደፈጣ ተዋጊዎች በዚያ በኩል ማሠማራት አለብን " አላቸው ።

በርግ ራሱን በአሉታ አነቃንቆ " ስለእግዚአብሔር ብለህ ሆስነር ራስህን እንደ አንድ ጄኔራል አድርገህ ማሰብ አትጀምር ። ማድረግ የምንችለው ጠላቶቻችን ወደዚህ ተራራ ላይ እንዳይወጡ መከላከል የምንችለው ከዚህ ነው ። ከክልላችን ውጭ አንድም ሰው መላክ አን ችልም ። ደፈጣ ተዋጊዎቹ ቢያገኙአቸውና የጠላት ጦር ውጊያ ቢጀ ምር 10 ወይም 15 ሰዎች ከእነጠመንጃዎቻቸው እናጣለን " አለው ።

" እንዲህ ከሆነማ የደፈጣ ተዋጊዎቹ ጠላትን ከኋላው ይጠዘ ጥዛሉ ። ወይም ጊዜያዊ ምሽጋቸውን በማጥቃት ቁስለኞቻቸው ንና የቀ ሩትን ይገድላሉ ። የመገናኛ መሳሪያዎቻቸውን ይሠባብራሉ ። የዕቃ ማስቀመጫዎቻቸውን ያቃጥላሉ ። ምናልባትም ደቦራ ጌዲዮንን ያመ ጣሉ " አለው ሆስነር ።

በርግ ፒፓውን አተኩሮ ካየ በኋላ "አንተ ማነህ ሆስነር . . . አቲላ ዘ ሀን ወይስ የኤል አል የጸጥታ ኃላፊ ? ቁስለኞቻቸውን መግደል - ዕቃ ግምጃ ቤታቸውን ማቃጠል - አበድክ እንዴ ? ከጨረቃው ብርሃን ፈቀቅ በል " አለው ።

ቤከር ሙሉ በሙሉ በቀልድ ሳይሆን " ቢያንስ ቢያንስ ለኤል አል በመሥራት ላይ ካለሁበት ጊዜ ጀምሮ እብድ ነው " አለ ።

" አንድ ነገር ማድረግ አለብን ፡ ይኸውም ቢያንስ አንድ ቡድን በምዕራብ ቁልቁለት በኩል ወርዶ ውሃ ማምጣት አለበት " አላቸው ሆስነር ።

በርግ አሁንም ራሱን በአሉታ አወዛውዞ " በዚያ በኩል አንድ አሸባል እንኳን ቢኖር ውሃ ሊያመጣ የሚሔደው ቡድን ምንም ውጤት ሊያመጣ አይችልም ። ወደዚያ አካባቢ መሔድ ወይም ሰው መላክ ራስን በራስ ማጥፋት ይሆናል ። በፈቃደኝነት ለመሔድ የሚፈልጉ ብዙ እንደሚኖሩ አውቃለሁ ። እኔ ግን ከክልላችን ውጭ አንድ ሰው እንኳን ተልኮ ይሔድ የሚለውን ሃሣብ አጥብቄ እቃወማለሁ ። የሚ ያስከትለው እልቂትና ፍጅት ነው " አላቸው ። በርግ ተሰሚነት በማ ግኘቱ በራሱ ላይ የበለጠ እምነት አደረበት ። በተራራው ላይ ሰዎቹ

እንደ እዛዥ ትዕዛዝ ድርገው ተመልክተውት ስለነበረ እርሱም ሁኔታውን ተጠቅሞበታል ። ሆስነር ከአሁን በኋላ የበርግን ሃሣብ መቀበል ይኖርበታል ። " የተጠናከረ መከላከያ መኖር አለበት ። መበታተን አያስፈልግም ። ያለንን ውሃ እየተቆናቆንን የመጠቀም ግዴታ አለብን ። በያለበት የጦር ሰፈሮች አናደርግም ። ኤሊ በጠንካራ ድንጋይ ልብስዋ ውስጥ እንደምትሸሸግ እኛም ከያለበት ተሰባስበን እዚህ መኖራችን እስኪታወቅ ድረስ እንዋጋለን " አላቸው በርግ ።

ሆስነር ከተቀመጠበት ተነስቶ በርግን በእንክሮ ተመለከተው ። " እንደሰማኸው የሰላም ተከራካሪ የነበሩትን ወደ ዕውቅ ገዳዮችነት መለወጡ ተአምር ነው ። እኔ እንደማየው ትልቁ ተአምር ግን ይስሐቅ በርግን ከቁንፅል አስተሳሰብ አላቆ ወደ ቁም ነገረኛነት ማሸጋገሩ ነው ። ሥጋና ደም ፤ ሃሣብም ጭምር ። ፊልድ ማርሻል ሽን በርግ ፤ የራስህ ዕድል ወሳኝና የሌሎችን ዕድል በእጅ ውስጥ ማስገባት መልካም ነው ። ዛሬ ማታ ስህተት ብትሠራ እኔ ከምሠራው ስህተት ይልቅ የአንተ ስህተት የጐላ ይሆናል ። ግን ብታሸንፍ - ዋናው ቁም ነገር ያ ነው ይስሐቅ - ብታሸንፍ እንደ ሮማው አጼ በደጃፍ በር መካከል ተሸከመውህ በሰልፍ ያልፋሉ ። "

በርግ ተነስቶ " የሆነ ያልሆነውን ከምትናገር የሚጠቅም ሃሳብ ብታመጣ ይሻላል ። የፈጣሪ ያለህ ! ሆስነር ለመሆኑ እርዳታ አትፈልግም ? " አለው ።

ቤከር የማስታወሻ ደብተሩን አውጥቶ መመልከት ጀመረ ። "እርዳታውን የምቀበለው በቂ ችሎታ ካላቸው ወታደሮች ነው ። ያም ሰው ዶብኪን መሆን አለበት ። አንተ አይደለህም " ካለው በኋላ ድምጹን ቀዝቀዝ አድርጎ " እወድሃለሁ ይስሐቅ ፤ ግን በእኔ ሥራ አትግባብኝ " አለው ሆስነር ።

" ወደድከም ጠላህም መግባት አለብኝ ። ማለትም በዚህ አካባቢ በሚወሰደው ውሳኔ የመናገር መብት አለኝ " ብሎ ሲነግረው ፒፓው በአፉ ውስጥ ተንቀጠቀጠ ።

ሆስነር ማምረሩን አይቶ ሳቀ ። " አንተ የማትረባ " ብሎት ወደ መውጫው በር እየሔደ " እሺ ፣ አቋም ለመውሰድ ይህን ያህል ፍላጐት ካለህ ለአንተ ይሁንልህ ። ወደ ከፍተኛው ቁንጮ እንኳን ደህና መጣህ ። ትቼህ ከሔድሁ እንደገና ብቻህን ትሆናለህ " አለው ። በክፍሉ ውስጥ አልፎ እበሩ ላይ ሲደርስ ሳቀ ። ወደኋላው ዞሮ " አንተ የማትረባ " አለው በድጋሚ ።

ቤንጃሚን ዶብኪን አቀልቁለው የሚመለከቱትን የስድስት ወይም የሰባት አረቦች ፊት ቀና ብሎ ተመለከተ ። አንደኛው በጣም አጉንብሶ የዶብኪንን ትከሻ ነካው ። በተሰባበረ አረብኛ አነጋገሩት። አረቦች ትክክለኛ አረብኛ የማይናገሩት ለምንድን ነው ?

ከአንዱ የወንዝ ዳርቻ ወደ ሌላው ይድህ እንደነበር አስታወሰ ። የራሱን የጦር ምሽግ ትቶ ከወጣ ወዲህ ምን ያህል ጊዜ እንዳለፈ አያውቀውም ። ጨረቃዋ ሙሉ በሙሉ ወጥታና ጊዜውም ቀዝቃዛ እንደ ነበረ ግን አስታውሷል ። እንዳይፈሩት በማሰብ እጁን ቀስ አድርጎ አንቀሳቀሰ ። ከአረቦቹ አንዱ መድኃኒት የያዘበትን ከረጢት አንስቶ በፊቱ ላይ ሲያወዛውዘው ዶብኪን አፈፍ ሲያደርገው ሰውየው ቀማው። ቀጥሎም በተሠባበረ አረብኛ “ መድሀኒት ነው ፤ ትፈልጋለህ ? ” አለው ።

“ አዎን ፤ የምፈልገው መድሐኒት ነው ” አለው ዶብኪን ።

ይህ ትንሽ ማጉረምረምን ፈጠረ። ሌላው አረብ አጉንብሶ አንድ ነገር በእጁ ይዞ “ ፓዙዙ - ማምለኪያ ! ” አለው ።

ዶብኪን ከፊቱ ትንሽ ራቅ ያለውን ጣኦት ትኩር አድርጎ ተመለከተው ። ይህን ይዞ መምጣቱ በእስላሞቹ ዘንድ ተቀባይነትን የሚያሳጣቸው መሰለው ። በአረብኛ አርኪኦሎጂስት የሚለውን ቃል ቢጠቀምም የሰሙት አልመሰሉም ። ሰውየው ጣኦቱን በመሬቱ ላይ ጥሎ ዞረ ።

እርስ በእርሳቸው ማውራት ጀመሩ ። ዶብኪን ቀስ በቀስ የእብራይስጥ ቃላት ከአረብኛው ጋር እየቀላቀሉ እንደሚናገሩ ለማወቅ ቻለ ።

እጁን ወደ ኪሱ ሲያስገባ ኮከቡ መኖሩን አረጋገጠ ። አውጥቶ በሰንሰለቱ አንጠልጥሎ ሲያሳያቸው በጨረቃዋ ብርሃን ያብረቀርቅ ነበር ።

ውጤቱ ከሰማይ ተልኮ ይዞ እንደመጣ ዓይነት ሆነ ። ሰዎቹም ንግግራቸውን አቋርጠው አይኖቻቸውን አፍጥጠው ተመለከቱት ።

ቀስ አድርጎ የቀድሞ ቃሎችን በመጠቀም በእብራይስጥ አነጋገራቸው ። “ እኔ ቤንጃሚን ዶብኪን ፥ አሉፍ ነኝ ፤ ” አሉፍ የጥንት የእብራይስጥ ቃል ሲሆን ጄኔራል ማለት ነው ። “ የእስራኤል ጄኔራል ነኝ - ከ - ጋር መጣሁ ። ” አውሮፕላን የሚለው ቃል በእብራይስጥ ስለማይገባቸው በአረብኛ ከነገራቸው በኋላ “ እርዳታ እፈልጋለሁ ፥ በተራራው ላይ ያሉት ይሁዳውያን - በባቢሎን ውስጥ - እርዳታችሁን ይፈልጋሉ ። ትረዷቸዋላችሁ ? ” አላቸው ።

ከእነርሱ መካከል እጅግ በጣም ሽማግሌ የሆነው በዶብኪን ጕን ተንበረከከ ። ዶብኪን እንደ አሰበው ባቢሎናውያን ይሁዶች ነበሩ ። ሽማግሌው ቆዳው በፀሐይ ቀለሙን የለወጠ ሲሆን ነጭ ጢምና ጥቁር ዓይኖች ነበሩት ። ጨርቅ አገልድሚል ። “ የእስራኤሎችን ጄኔራል ያለጥርጥር እንረዳዋለን ። ዘመዳሞች ነን ” አለው ።

“ እሺ ፤ ኢየሩሳሌምን አረሳችኋትም ” አላቸው ዶብኪን ።

* * *

ሆስነር ክልላቸውን ደጋግሞ ዞረ ። ብቻውን ነበር ። ደክሞታል ፤ ጠምቶታል ፤ እርቦታል ፤ ከአሥራ ሁለት በላይ በእሾህና በእንቅፋት የቆሰለው ሰውነቱ አንገብግቦታል ። በጥይት የተመታው ጆሮው እሳት እንደተለቀቀበት ዓይነት ሆኖበታል ። የጠጣው የወይን ጠጅ ራሱን ስላዞረው አቅለሽልሾታል ። አስጠምቶታልም ።

አሻቅቦ ኮከቦቹን ፤ አሽቆልቁሎ በጨረቃ ብርሃን የተሞላውን የመሬት ገጽታ ተመለከተ ። እነዚያ በጨረቃ ብርሃን ስለተሞሉት የመሬት አካሎች ሲል እርምጃ እንዲወስድ ተገዷል ። በተራራው ጫፍ ላይ ተሰባብሮ ከተገነጣጠለ ጅራቱ ጋር ስለቆመው ኮንኮርድና ራሱም ስለሠራው ስህተት በጣም ተጨንቋል ። ለሕዝቡና ለአላቸው አንድነት እጅግ አስቧል ። በጊዜያዊው ምሽግ ውስጥ ያሉ ሰዎች እንደሚሰቃዩት ሁሉ እርሱም እየተሰቃየ ነበር ። እዚያ የነበረው ለ24 ሰዓት ያህል ቢሆንም ባየው ሁሉ ስለተሳቀቀ በአዕምሮው ውስጥ ለዘላለም በዚያ የኖረ መሰለው ። ተራራው ትልቅ ነበር ። ሕዝቡ ግን ትንሽ አደረገው። ዓይኖቻቸው ወደ ሚሔድበት ሁሉ ተከትለው ተንከዋረሩ ።

በምዕራብ በኩል መጥቶ መጨረሻ የሌለውን አውላላ ጭቃማ ሜዳ ተመለከተ ። እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶ “ እግዚአብሔር ሆይ ! ወደ ቤቴ መመለስ እፈልጋለሁ ፤ ደከመኝ እናም ወደ ቤቴ መሔድ እፈልጋለሁ ! ” አለ ። “ እግዚአብሔር ሆይ ፤ ለምን እኔን ? ” የሚ ለውን ዝነኛ ጥያቄ አስታወሰ ። ለዚህም መራራው መልስ “ ለምን አንተ አትሆንም ? ” የሚል ነበር ። ስቆና ጮኸ “ አዎን ፤ ለምን እኔ አልሆንም? ያዕቆብ ሆስነር እንደማንኛውም ሰው ነው ። እግዚአብ ሔር ሆይ ምስጋና ይድረስህ ፤ ይህንም አስታውሳለሁ ” አለ ።

እንደገና ሳቀ ። ቀጥሎም እንባ ስላነቀው በሞቀው መሬት ላይ ተደፋ።በእንባው ውስጥ የኢየሩሳሌም ልዩ ልዩ ክፍሎች በምትጠልቀው ጸሐይ አጊጠው ታዩት ። በከተማው ከፍተኛ ቦታ ላይ ሆኖ ከአሮጌው ከተማ ክልል ውጭ ወጣት ልጆች በጕች ሲነዱ ታዩት ። የአይሁዶች በአልና የፋሲካ እሁድ ስለነበረ ከተማው በሰዎች ተጥለቅልቋል ። በድንገት ሀይፋ ውስጥ ባለው አባቱ ቤት ውስጥ ሆኖ ሰማያዊ ቀለም

ያለው የባሕር ወሽመጥ ታየው ። ጊዜው መጸው በመሆኑ ምስጋና የሚቀርብበት ነበር ። የአባቱ ቤት በልዩ ልዩ የመኸር እህል ተሞል ቷል ። በጠረጴዛውም ላይ ልዩ ልዩ የምግብ ዓይነቶች ነበሩ ። እርሱ ወጣት ስለነበረ ለጦርነት መሔድ ነበረበት - በእንግሊዝ የጸጥታ ክፍል ውስጥ መሥራት ነበረበት ። ኑሮ እንደወትሮው ጥሩ ነበር ። በጦርነቱ ውስጥ ብዙ ወጣት ሴቶች ስለነበሩ ብዙ ቀልዶችና አስደ ሳች ሁኔታዎች ነበሩ ። ሚሪያምን የምትመስል አንዲት ሴት ነበረች ። በዚያ ጊዜ ሚሪያም ግን ሕጻን እንደነበረች አስታወሰ ። በናዚ እርስ ዋና ቤተሰቦችዋ ራቁታቸውን እንደከብት ሲነዱ እርሱ በሀይፋ ውስጥ በአባቱ ቤት ተቀምጦ ስለጀርመን ፈላስፎች ያነብ ነበር ። ይህ የእ ርሱ ጥፋት አልነበረም ። በጠላት እጅ የወደቀ ማንም ሰው ቢሆን በሕይወት ያሉ ሚስት ፣ ባል ፣ ወንድ ልጅ ፣ ሴት ልጅ ፣ ወዳጅ ፣ ፍቅረኛ ይኖሩታል ።

ጥፋተኛነት የሚሰማው ለምንድን ነው ? አሁንም ሆነ በኋላ እያንዳንዱ ለመሰቃየት ተራ ይኖረዋል ። ለእርሱ የመጣው በጣም ቆይቶ ነበር ። በመጣ ጊዜ ግን ምንም ሳያጓድል ነበር — ሀፍረት ፣ ውር ደት ፣ ጥፋት ፣ ሥቃይ ፣ እርባናቢስ ፣ ወደፊት አላማ የሌለው ፍቅር እናም . . . ሞት - ሞት ። መቼና እንዴት ? አሁን ለምን አይሆንም ? ወደ ሰፊው የኤፍራጥስ ወንዝ አቀልቁሎ ከተመለከተ በኋላ ቆመ ። ከዚህ ጉብታ ዘሎ የማይገባው ለምንድን ነው ? ግን ተመልሶ ወደ ቤቱ መሔድ ይፈልጋል ። ሚሪያምን ይዞ ወደ አባቱ ቤት በመሔድ በበአላ ቸው ቀን እራት አብሮ መብላት ይፈልጋል - በሕጻንነቷ ያጣችውን ምግብ ሁሉ - በጦርነቱ ጊዜ ኑሮ ይህንም ያህል አስደሳች እንዳልነበረ ሊገልጽላት ይፈልጋል ። የእናቱ ቤተሰቦች ተገድለዋል ። ይህን ታውቅ ይሆን ?

ከሃሣብ ሰመመን የነቃው ከዚህ ሁሉ ትዝታ በኋላ ነበር ። ዓይ ኖቹንና ፊቱንም ጠረገ ። ለማንኛውም ወደ ሀይፋ ተመልሶ የበዓል ቀን እራት እንደገና እንደሚበላ አላመነም ። በተአምር ቢመለስም ከሚሪያም በርንስቴይን ጋር አይሆንም ።

ኃይለኛ ነፋስ መጥቶ አሸዋና አቧራ በብዛት አነሳ ። ሼርጂ የሚ ባለው ነፋስ በኃይል እየመጣ ነበር ። ሆስነርም በወደቀው አውሮፕ ላን መካከል ነፋሱ ሲያፏጭ ተሰማው ።

ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ዞሮ ሲመለከት ነፋሱ ወደ እርሱ ሲመጣ አየው ። ከፍተኛ አቧራ ይዞ ከተራራዎቹ ወደ ባቢሎን ሲመጣ ተመ ለከተው ። አሸዋና አቧራ የቀላቀለው ነፋስ እየተሽጎደጎደ ተራራ ዎቹንና ሌሎቹንም ቦታዎች ጋረዳቸው ። የኤፍራጥስ ውሃ በነፋሱ ግፊት ከዳርቻው ጋር ሲጋጭ ይሰማ ነበር ። በጭቃው ላይ የከተረው

ውሀ በነፋሱ ኃይል ተንቃንቀ ። ቀበሮዎች ጸጥ አሉ ። በሺህ የሚቆጠሩ የማታ ወፎች ሜዳውን ኣቋርጠው ወደ ምሥራቅ በረሩ ። የባሕር ውስጥ ተክሎች ተንቃቀሉ ። እንቁራሪቶች ወደ ሌላ ቦታ ተተፉ ። አውሬዎች አጓጉሩ ። ሆስነርም በሁኔታው ተንቀጠቀጠ ።

## —25—

ቴዲ ላስኮቭ በሰፊ ክፍል ውስጥ ባለ ረጅም ጠረጴዛ ጫፍ አጠገብ ቆሟል ። ነፋሱ መስኮቶቹን አንገጫገጫቸው ። የቴዎዶር ሄርዝልና የቼይም ቼይዝማን ፎቶግራፎች በግድግዳው ላይ ተሰቅለዋል ። አሜሪካዊው ጠፈርተኛ ዋሊ ሺራ ከአፖሎ ላይ ሆኖ ያነሳው የእስራኤል ባለቀለም ፎቶ ግራፍ በሌላው ግድግዳ ላይ ተሰቅሏል ። በስብሰባው ጠረጴዛና በዙሪያው ባለው ወለል ላይ ልዩ ልዩ ጉዳዮች የተጻፉባቸው ወረቀቶች አሉ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያለፈቃድ የገቡትን ሁለት ሰዎች ትኩር አድርጎ ተመለከታቸው ። የካቢኔ ሚኒስትሮች ፣ ከፍተኛ የጦር መኰንኖችና የብሔራዊ ደህንነት ኮሚቴ የጋራ ስብሰባ አድርገው በነበረበት ጊዜ ውስጥ እንደዚያ ያለ ጸጥታ ታይቶ አይታወቅም ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ “ ባቢሎን ? ” ብሎ ተናገረ ።

“ አዎን ” ጠቅላይ ሚኒስትር ።

“ በግምት ? በስሜት ? በመንፈስ ? ”

“ በመሳሰሉት ” ብሎ ላስኮቭ ከንፈሮቹን ላሰ ። በእስራኤል ውስጥ በበታች መኰንኖችና ሠራተኞች ላይ መጮህ ወደ በላይ ለመሔድ ያስችላል ። በኢየሩሳሌም የተቋቋመው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ጠባብ ስለነበረ ላስኮቭ በበሩ አጠገብ ሆኖ ጮኾ የሚናገረው ይሰማው ነበር ። ላስኮቭ አጠገቡ ወደ ቆመው ታልማን አየት አደረገ ። እንደ እንግሊዛዊ ክብሩን ከፍ አድርጐ በማየት የሚኩራራ ይመስላል ። ላስኮቭ በክፍሉ ውስጥ የነበረውን ዝምታ ለመቆስቆስ “ ከኤሌክትሮኒክ ዳታ ፣ ማለትም ከራዳር እይታዎችና ከራዲዮ ማሰራጫዎች ከአገኘናቸው መረጃዎች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚያመለክቱት ወደ ኢራቅ መሔዳቸውን ነው ” አለው ።

“ እውነትህን ነው ? መረጃውን ከየት አገኘኸው ጄኔራል ? ”

ላስኮቭ ትከሻውን ከፍና ዝቅ አደረገ ። በክፍሉ ውስጥ ያሉት ሰዎች እርስ በእርሳቸው ተንሾካሾኩ ። ሰዎቹን ተመለከተ ። ጡረታውን ተቀብሎ ገለል የማይለው ለምንድን ነው ? ለሰላም ተልዕኮ ስለሔዱት ሰዎች የት እንዳሉ መንግሥት ይጨነቅበት ። ይህን

ሃሣቡን ሚሪያም ከጠፉት ውስጥ አንድዋ ባትሆን ኖሮ በሥራ ላይ ያውለው ነበር ።

" እሺ ፤ ጄኔራል ፡ መረጃዎቹን ከየት እንዳገኘሃቸው ስላለው ጥያቄ በኋላ እንመለስበታለን " አለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንገቱን በመሃረብ ጠራረገ ። ቁመቱ ዘላጋና ቀጭን ሲሆን የግንፍልታ ጠባይ ስለአለበት በሚናደድበት ጊዜ ወረቀት ይቦጫ ጭቃል ። " መልካም በአንተ መረጃ መሠረት እንድንሠራ የምታ ቀርበው ሃሳብ ምንድን ነው ። ምናልባትም በመንፈስ ስለአገኘሽው ማለት ይገባኝ ይሆናል ? "

ላስኮቭ ግልጽ በሆነ አነጋገር " አካባቢውን የሚቃኝና የሚ መለከት ዝቅ ብሎ የሚበር የስለላ አውሮፕላን አሁን ዛሬ ማታ ወደ ባቢሎን ፡ መላክ አለብን ። ከተቻለ ፎቶግራፎች ያነሳል ፤ አካባቢውን በሚገባ ያያል ። በዚያ አካባቢ ካሉ ዝቅ ብለን በመብረር ምልክቶች ልናሳያቸው እንሞክራለን ። ተስፋም እንሰጣቸዋለን ። ይህን የሚከ ተል አየር ወለድ ይኖራል - ኤፍ - 14 ቀደም ብሎ ከእነዚህም በኋላ ሲ - 140 ከኮማንዶዎች ጋር የማረፊያ ቦታ ካለ ወይም የማረፊያ ቦታ ከሌለ ሲ - 130 አየር ወለድ ወታደሮች ይዞ መሔድ አለበት ። ምና ልባትም በእነዚህ ፋንታ የጦር ሔሊኮፕተሮች ሊሆኑ ይችላሉ ። ይህን ወታደሮቹ ሊያስቡበት ይገባል ። ሰላዩ ወይም የሚቃኘው አውሮፕ ፕላን መኖራቸውን ከአረጋገጠ ተዋጊ ኃይል ይወርዳል " አለው ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በያዘው እርሳስ ጠረጴዛውን እየቆረቆረ "ለዮ ርዳኖስ ንጉሥ በግዛቱ ላይ አውሮፕላናችን እንዲበር እንዲፈቅድልን ብነግረው ትቃወማለህ ? " ብሎ ጠየቀው ። ጮክ ያለ የሳቅ ድምጽ ስለተሰማ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግሩን ቆም አደረገ ። ቀጥሎም ወደ ፊት ጐብደድ ብሎ " ለኢራቅ ፕሬዚዳንት ደውየ ቀስ በቀስ አገሩን እንደምወር - የጥንቱን መሠረት በማድረግ ባቢሎንን ለመውጋት - ብነግረው በእውነት በኃይል አትቃወመኝም " አለው ።

ላስኮቭ ሳቁ እስኪያበቃ ድረስ ጠበቀ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከም ክር ቤት አባሎችና ከጄኔራሎች ጋር የሚያደርገውን ቀልድ ካቆመ በኋላ በነገሩ በበለጠ በመመሰጥ ግልጽ ከሆኑት የፖለቲካ ሰዎች አንዱ ነበር ። " ጠቅላይ ሚኒስትር ለድንገተኛ አደጋ የዚህ ዓይነት ፕላን ይኖራል ። የሰላም ተደራዳሪዎቹን እናገኛቸዋለን ብለን የምናስ በው የትነው ? በሔርዚሊያ ባሕር ዳርቻ ? በምናገኛቸውስ ጊዜ የምን ወስደው እርምጃ ምንድን ነው ? "

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወንበሩ ላይ ለጠጥ ብሎ ሲቀመጥ የፊቱ ገጽታ ጠቆረ ። " በመሠረቱ የምናድንበት ዕቅድ አለን ። ግን ኢራቅ

ወዳጅ ከአልሆኑት አገሮች አንድዋ ስለሆነች ሙሉ ትብብር አታደርግልንም ። ስለዚህ እነእርሱን ማስቆጣት አንፈልግም ። ወዳጅም ባለመሆናቸው በአገራችን ላይ ጦር ነት ሊያውጁ ይችላሉ ” በማለት ተናገረ ።

“ አዝናለሁ ጠቅላይ ሚኒስትር ፤ እንደሌሉቹ ጄኔራሎች ሁሉ ፖለቲካ አይገባኝም ” አለው ።

እንደ ሌሎቹ ጄኔራሎች ሁሉ ጥሩ አድርገህ ስለፖለቲካ ታውቃለህ ። ስለሌሉቹ መጨነቅም ሆነ ማሰብ የለብህም ። ከእኔ ጋር የምታደርገውን ቀልድ አቁም ፤ ላስኮቭ ። ከኢራቅ ጋር ያለውን ሁኔታ ታውቃለህ ። ስለዚህ በመጀመሪያ የማደርገው ከባግዳድ ጋር መነጋገር ነው ። ”

ላስኮቭ ተግሳጹን መቀበሉን የሚያሳይ በአዎንታ ራሱን ቢነቀንቅም የተባለውን በሙሉ ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑን ገለጸ ። ድምጹን ስሜት እየተናነቀው “ ጠቅላይ ሚኒስትር ፣ የእስራኤሎችን ደህንነት ለውጭ መንግሥታት አሳልፈን የሰጠነው ከመቼ ወዲህ ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ በውጭ መንግሥት መሬት ላይ በሚገኙበት ጊዜ ፤ ጄኔራል ላስኮቭ ” ።

“ በዩጋንዳ ። ”

“ በተለያየ ጊዜ በተለያየ ቦታ ። ”

“ የቀድሞው ዓይነት አንገት መታረድ ” ብሎ በኃይል ተነፈሰ። “ ጠቅላይ ሚኒስትር ፤ የምዕራብ ጀርመን ኮማንዶዎች በሶማሊያ ውስጥ አድርገውታል ። እኛም በዩጋንዳ ውስጥ አድርገነዋል ። አሁንም እንደገና በባቢሎን ውስጥ ማድረግ እንችላለን ። ”

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የብስጭት ድምጽ በማሰማት “ ቅር ባይልህ በእውነት በመጀመሪያ መንገር አለብኝ ” ብሎ ወደፊት በጠረጴዛው ላይ ጐብደድ በማለት “ ለማንኛውም በባቢሎን ውስጥ ካሉ ፤ ይሙቱ ? በሕይወት ይኑሩ ? ምርኮኞች ይሁኑ ? አናውቅም ጄኔራል። በዚህ ጉዳይ በበለጡት ነጥቦች ላይ ከአንተ ጋር በትክክል እስማማለሁ ። በስብሰባ ላይ ሳናቋርጥ ለ30 ሰዓቶች ስለቆየን በጣም ድካም ተሰምቶናል ። አንተ ደግሞ ባቢሎን እያልክ በመጨኸ ወደዚህ ስብሰባ ስለመጣህ ለመናገር ዕድል ሰጠንህ ። ሌላ ጠቅላይ ሚኒስትር ቢሆን ኖሮ ከዚህ አስወጥቶ ያበርህ ወይም በጣም መጥፎ ነገር ይደርስብህ ነበር ” ብሎት ስኒውን አንስቶ ቡና ፉት አለ ።

ጸጥ ብሎ የነበረው ክፍል በነፋስ ሽውሽውታ ተሞላ ። የመስታ ዎት መጋረጃዎችና መወጠሪያዎች እንደገና መንገጫገጭ ጀመሩ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሰማ ድምጹን ከፍ አድርጎ “ የምትናገረው ትርጉምና ተቀባይነት ያለው ነው ። በእግዚአብሔር አምናለሁ ። ስለ ሆነም እግዚአብሔር በጀርህ ሹክ ብሎህል ብየ አምናለሁ ፤ ቴዲ ላስ ኮቭ - ቢሆንም ለእኔ ሳይሆን ለአንተ ለምን ይህ ምሥጢር እንደተገ ለጸልህ አላውቅም ። ለማንኛውም አሁኑኑ የኢራቅን ፕሬዚዳንት እናነጋግረዋለን ። እርሱም የስለላ አውሮፕላኖችና የአየር ኃይል ሰዎች ልኮ የሚያገኙትን ውጤት ይነግረናል ። ትስማማለህ ? ”

“ አልስማማም ጠቅላይ ሚኒስትር ፤ በከንቱ ብዙ ጊዜ አጠፋን።”

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተቀመጠበት በቁጣ ተነስቶ “ አንተ የማ ትረባ - ባልሆነ መጥፎ ሥራ ላይ ጠርቼ ከምመድብህ በፊት ከዚህ ውጣ ” ካለው በኋላ ወደ ታልማን ዞሮ “ ሁለታችሁም ከመሔዳ ችሁ በፊት የምትናገረው አለህ ፤ ጄኔራል ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ታልማን ምራቁን ዋጠ ። ሪዙ ተንቀጠቀጠ ። ቀጥሎም በኃይል ተነፈሰ ። “ መልካም ጠቅላይ ሚኒስትር ፤ እንደማስበው ፍለጋውን ራሳችን ማድረግ አለብን ። እንደምታውቀው እኛ በዚህ ሥራ ከእነ እርሱ የተሻልን ነን ። በተጨማሪም ከእነእርሱ ጋር ቀጥታ ግንኙ ነት ስለማናደርግ ነገሮቹ የበለጠ እየተወሳሰቡ የባሰ ውላቸው ይጠፋል ። ቢያንስ ቢያንስ እስከዚያው የአሜሪካን መንግሥት በኤስ አር - 71 በሕዋው ላይ ሆኖ አካባቢውን ፎቶግራፎች እንዲያነሳልን መጠየቅ እንችላለን ። ዝቅ ብለው ለማየት ባይችሉም ግልጽ የሆነ ፎቶግራፍ ሊያነሱልን ይችሉ ይሆናል ” አለው ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እጁን ወደላይ አንስቶ “ አቁም ” ብሎት መቁነጥነጥ ወደ ጀመሩት አጠገቡ ወደ አሉት ሰዎች ዞሮ ስለጠየ ቃቸው ራስ ለራስ ገጥመው በሹክሹክታ ተነጋገሩ ። ጠቅላይ ሚኒ ስትሩ ቀና ብሎ “ አመሰግናለሁ ፤ ሁሉንም ነገር እዚሁ ሆነን እንፈ ጽማለን ፤ መሔድ ትችላላችሁ ” አላቸው ።

ላስኮቭ ቀስ ብሎ ከታልማን በኋላ ወደ በሩ ተራመደ ። ስለአገር ጉዳይ ምስጢራዊ ውይይት በሚደረግበት ጊዜ ከስብሰባ እንዲወጣ የቀረበው ጥያቄ የሚያስገርም - ከማስገረሙም ይልቅ በጣም መጥፎ - መሆኑ ላስኮቭ ተሰማው ። ይህ የአዛዥነትን ሥልጣን መተው ከውጤ ቶቹ አንዱ ነው ። የተወሰዱትን እርምጃዎች ለማወቅ በየወሩ ማስታ ወሻዎችን ከጠረጴዛ ላይ እየሰበሰቡ በማንበብ ይወሰናል ። ሥልጣን ማጣት ደግሞ ለአዕምሮ ጸጥታንና ሰላምን ይሰጣል ። መሰልቸትን ግን ያስከትላል ። ላስኮቭ እበሩ ላይ ሲደርስ ዞረ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩን

ከበው ያንሾካሽኩ የነበረው ምን እንደሆነ አላወቀም ። ነገር ግን የካቢኔ ሚኒስትሮች ባለመሆናቸው ትንሽ አስተንፍሶታል ። ከመሔዱ በፊት ግን የመጨረሻ ንግግር ማድረግ እንደሚገባው ተሰማው ። “ ባቢሎን ውስጥ ናቸው ። በሕይወትም እንደ አሉ ይሰማኛል ። በደህንነታቸው ላይ ለመጫወት መብት የለንም ። የምትሠሩት ሁሉ በእነእርሱ ደህ ንነት ላይና ለወደፊቱም በሕዝባችን ደህንነት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት ። ከአፍንጫችሁ ባልራቀ አላማ ላይ በመመሥረት ውሳኔ እንዳ ታሳልፉ ። ”

ላስኮቭ ማን መሆኑን ያላወቀው ጠርቶት “ ሥራህን እንደምት ለቅ ከተነገረህ በኋላ አፍህ ላይ የመጣውን ሁሉ መናገር ቀላል ነው ፤ ጀኔራል ” አለው ።

ላስኮቭ ሰምቶ እንዳልሰማ ሆኖ ዞሮ ሔደ ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ላስኮቭና ታልማን ራቅ ብለው እስኪሔዱ ድረስ ከቆየ በኋላ “ ላስኮቭ ይህን መረጃ ከየት እንዳገኘው አላወ ኩም ። አሁን እናንተም እንደነገራችሁኝ ቼይም ማዛርም መረጃውን ከየት እንዳገኘው አናውቅም ። ነገር ግን ማዛር ከአሜሪካ አየር ኃይል አታሼ - ሪቻርድሰን - ማግኘቱ ትክክለኛ ከሆነ አሜሪካኖቹ ይተባበ ሩናል ብየ አምናለሁ - ” ብሎ በግድግዳው ላይ የተሰቀለውን ከአ ሜሪካኖች የተሰጣቸውን ባለቀለም ፎቶ ግራፍ ተመለከተ ። “ አዎን ፤ ልክ ነው ። ስለሆነም በኤስ አር - 71 ለስለላ ሥራ በኤፍራጥስ ላይ ልዩ በረራ እንዲያደርጉልን መጠየቅ እንችላለን ። ከዚያ በኋላ ላስኮቭ ትክክል መሆኑን እናያለን ” ካላቸው በኋላ እንደገና ከቡናው ፉት አለ ። “ አልፎ አልፎ መልአክ ወይም የሰማይ ፍጡር እየዞረ ለአንዳንድ ሰዎች በጆሮአቸው ሹክ ይላቸዋል ። በዚህ ዓይነት ማንኛ ውንም ዓይነት ቢሆን መረጃ የሰማ ሰው አለ ? የለም ? እንግዲያውስ ከተመረጡት ሰዎች ውስጥ አይደለንም ። ክቡራንና ክቡራን ለ10 ደቂቃዎች እረፍት እናድርግ ” አላቸው ።

## —26—

ሼርጂ የተባለው ነፋስ አያሌ አቧራና አሸዋ ይዞ ባቢሎንን አቋ ርጦ ሔደ ። ለጊዜያዊ መከላከያ እንዲሆኑ የተሰሩት ቦታዎችና የቀ በሮ ጉድጓዶች በደቂቃ ውስጥ እስከ አፋቸው ድረስ በአሸዋና በአ ቧራ ተሞሉ ። ጠላትን ለማጥመድና ለማስጠንቀቂያ እንዲሆኑ የተ ሠሩት ሁሉ ጠፉ ። ሰው ሠራሽ ቦምቦች የተቀመጡበት ጉድጓድ በአ ሸዋ ተሸፈነ ። በጠላት ዓይኖች ላይ እንዲያብረቀርቁ የተሠሩት የአሉ

ሚኒየም ቁርጥራጮች በነፋስ ተወሰዱ ። በእረኛው ጐጆ ላይ የነ በሩት የዘንባባ ቅጠሎች በነፋሱ እየተገነጣጠሉ ስለተወሰዱ በቁስለ ኞቹ ላይ አሸዋ ዘነበባቸው ። መሣሪያዎች በአቧራውና በአሸዋው እንዳ ይበላሹ በፕላስቲክ ወይም በጨርቅ መጠቅለል ነበረባቸው ። ወንዶ ችና ሴቶች እንደበረኸኛ አረብ ፊቶቻቸውን በጨርቅ ሸፈኑ ።

እንደመጀመሪያው ክብሩን ሳያስነካ እንደኮራ ሳይነቃነቅ የቆ የው ኮንኮርዱ ብቻ ነበር ። ነፋሱ በተሸነቋቆሩት ቀዳዳዎች በመግባት በውስጡ ቆሻሻ እንዲከማች አድርጓል ።

ሆስነርና በርግ ቁስለኞቹን ከጐበኙ በኋላ ከቄሱና ከቤተ አብ ራምስ ጋር ተወያዩ ። አብዛኞቹ ቁስለኞች ደህና መሆናቸውን ቄስ ሌቪን ገለጸላቸው ። ይሁን እንጂ ትክክለኛ ሕክምና በቶሎ ካልተደ ረገላቸው በቁስል ማመርቀዝና በሌላም ከዚሁ ጋር በተያያዘ ምክንያት ሊሞቱ እንደሚችሉ አስረዳቸው ።

ሆስነርና በርግ ከጐጆው ወጥተው ወደ መከላከያ ክልላቸው እንደ ገና ሔዱ ። በርግ ጮኾ “ አረቦቹን አውቃቸዋለሁ ። ነፋሱ ለውጊያ ችን ጥሩ የገድ ምልክት ነው ብለው ይወስዱታል ” አለው ።

ሆስነር በበኩሉ ጮኾ “እኔ ደግሞ የማስበው ነፋሱ ከዚህ መጥፎ ቦታ እንዲወጡ የሚያሳይ የገድ ምልክት ነው ብለው እንደሚያምኑ ነው” አለው ። ወደ ሰማይ አንጋጦ ሲመለከት ጨረቃዋ ለመጥለቅ የተ ቃረበች ብትሆንም አቧራው ጨረቃዋን ሊሸፍናት ምንም ያህል አል ቀረውም ነበር ። አልፎ አልፎ በኃይል ወደ ላይ የወጣው አቧራ የጨረ ቃዋን ብርሃን ቢሸፍነው ለጥቂት ሴኮንዶችም ቢሆን የተራራው ጫፍ ሙሉ ጨለማ ሊሆን ይችላል ። በአጋጣሚ ወደ ምሥራቅ ቁልቁለት ተመልክቶ እርሱ ከአለበት 10 ሜትር እርቀት ድረስ ቢመጡ እንኳን ሊያያቸው ወይም ሊሰማቸው የሚችል እንዳልነበረም ተገነዘበ ።

በርግ ካናቴራውን በፊቱ ላይ አድርጐ “ በተአምር የት እንዳለን ቢታወቅ እንኳን የአዳኙ ቡድን በዚህ ሁኔታ እኛን ለማግኘት ያለው ዕድል ዝቅተኛ ነው ” አለው ።

ሆስነር በዚህ ነገር ላይ የበለጠ በማሰብ “ አንድ ሊነግረን ወይም ሊያስጠነቅቀን የሚችል ነገር ካላደረግን በስተቀር ያለጥርጥር ያልቅ ልናል ” አለው ።

“ሰው ወደዚያ ታች መላክ ራስን በራስ እንደመግደል ይቆጠራል።”

ሥልጣንን ማካፈል ስህተት ይመስላል ብሎ ሆስነር አሰበ ። በመ ሠረቱ ቢያናድድም ስህተት አይደለም ። “ ሁሉም ያው ነው ፊልድ

ማርሻል ። አንድ ወንድ ወይም አንዲት ሴት መላክ አለብኝ ። እንዳውም እኔ ራሴ እሔድ ይሆናል ። ”

በርግ ያ ጥሩ ሃሣብ ሊሆን አይችልም ይሆናል የማለት ስሜት ቢያድርበትም አልተናገረም ።

ወደ ምዕራብ ዞረው በረባዳው ላይ ሲሔዱ ነፋሱ ገፍትሮ እንዳ ይጥላቸው ወይም ወደፊት እንዳያሮጣቸው ታገሉ ። በመጀመሪያ ወን ዙን አቆልቁለው ተመለከቱ ። ቀጥሎም የኤልአል ሰማያዊ ብርድ ልብስ የለበሱ ሁለት ሴቶች በቀበሮው ጉድጓድ ውስጥ የተኙ የሚ መስሉና አሸዋ በላያቸው ላይ በኃይል ሲነሰነስባቸው አዩ ።

ሆስነር ያለመንቀሳቀስ የተጋደሙትን ሰዎች ካየ በኋላ በዚህ በኩል አሸባሎቹ ለመውጋት የሚችሉበት መጠነኛ ዕድል እንደነበ ራቸው ተገነዘበ ። ደግነቱ በዚህ በምዕራቡ ቁልቁለት አንድም አሸባል የቀረ ላይኖር ይችላል ። ቢኖርስ ኖሮ ነፋሱን ለመጋፈጥ ይችል ነበ ርን ? ሆስነር የተኙትን ሁለት ሰዎች እንዳየ የልቡ ትርታ በመጠኑ ጨመረ ። ፍተሻ በሚያደርግበት ሁሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ መኰ ንኖችና የሃምሳ አለቆች በጥበቃ ሥራ ላይ እንደእርሱ ተሰማርተው እያሉ አንድ እንኳን ጠባቂ ተኝቶ እንደማያገኝ ተስፋ ነበረው ። መተ ኛት በሲቪሎች ዘንድ በየዋህነትና በተፈጥሮ ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን በየትኛውም የወታደር ዓለም ውስጥ ማንም ሰው ቢሆን ጥበቃ ውን ዘንግቶ ተኝቶ ቢገኝ በሞት በሚያስቀጣ ወንጀል ይከሰሳል ።

ሆስነር በጕናቸው በርከክ ብሎ ጉሮሮውን ለማፍታታት እህ ! እህ ! ሲል ዘለው ይነሳሉ ብሎ ተስፋ ቢያደርግም አንደኛቸውም አልተንቀሳቀሱም ። ብርድ ልብሱን ከላያቸው ላይ ገፎ ሲመለከታቸው ኤሸር አሮንሰንና ሚሪያም ነበሩ ። ቢነካቸውም አልነቁም ።

ከተኙት አንደኛዋ በጥበቃ ሥራ ላይ ነበረች ። ሌላዋ ግን የመ ተኛት መብት ነበራት ። አንደኛዋ የመኖር ዕድል ሊኖራት ይችላል ። የቀረችው ግን በሚቀጥለው ሰዓት ውስጥ ልትገደል ትችላለች ።

በርግ ጐንበስ ብሎ አጠገባቸው ተጋድሞ የነበረውን ኤኬ - 47 ጠመንጃ አነሳ ። ሆስነር ይህ የወታደር ሕግ መሆኑን አውቋል ። ወሬ ውም በየአለበት እንደሚናፈስ ገብቶታል ።

ሆስነር የሚሪያምን ትከሻ ይዞ እየነቀነቀ “ ደህና ነሽ ? ” አላት ።

በፍጥነት ነቅታ “ አህ ! ” አለች ።

በርግ እጅዋን ይዞ ከአነሳት በኋላ ” የምትጠብቂው ከስንት እስከ ስንት ነው ? ” ብሎ በድንገት ጠየቃት ።

ሙሉ በሙሉ ስለአልነቃች " ምን ? አሀ ! ዘብ ፤ ከግማሽ ሌሊት እስከ 8-10 ሰዓት ጉሀ እስኪቀድ ፤ ለምን ? " ብላ ዙሪያዋን አፍጥጣ ስትመለከት ሆስነርን አየችው ። ቀጥላም ኤሽር አሮንሰን ከአጠገብዋ ተኝታ ስለአየች ነገሩ ገባት ።

በርግ ሰዓቱን በፍጥነት ሲመለከት ከሌሊቱ 6 :15 ሰዓት መሆኑን አየ። "ኤሽር አሮንሰን ለሥራ ቀስቅሳሽ ነበር ? " ብሎ ጮኾ ጠየቃት ።

ሆስነርን ትኩር አድርጋ ተመለከተችው ።

" የቀሰቀሰችሽ ለተረኛ ሥራሽ ነበር ? " ብሎ እያርገፈገፋት በድጋሚ ጠየቃት ።

" አዎን " አለችው ።

" በሥራ ላይ እያለሽ በመተኛትሽ በቁጥጥር ሥር ውለሻል ።በር ንስቴይን ይሀ በሞት የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑን ልነግርሽ እወ ዳለሁ ። "

ሚሪያም ተነስታ በነፋሱ ላይ ስትቆም ነፋሱ ጸጉርዋን አመስ ቃቀለው ፤ ልብስዋንም ገለባበጠው ። ፊትዋም ነፋሱ ባመጣው አሸ ዋና አቧራ ለበሰ ።

ቀጥ ብላ በመቆም ወደ በርግ እየተመለከተች " ገብቶኛል የሌ ሎችን ሕይወት በአደጋ ላይ እንዲወድቅ ስላደረኩ የጥፋቴን ዋጋ ማግኘት አለብኝ " አለችው ።

" ትክክል ነሽ " ብሎ በርግ ወደ ሆስነር በመዞር " እርምጃው ትክክል አይደለም እንዴ ? " ብሎ ጠየቀው ።

ከዳገቱ ጋር በርግን ለማጋጨት ያደረበትን ስሜት ሆስነር ተቋ ቁሞ በመጀመሪያ ተኝታ ወደ ነበረችው ኤሽር አሮንሰን ቀጥሎም ወደ ሚሪያም ተመለከተ ። ጠንካራና የቀድሞ ወግ አጥባቂ በመሆኑ ተወዳ ጅነቱን ቀንሶበታል ። ይሁን እንጂ እርሱ ከምንም ቁም ነገር አይቆ ጥረውም ። አሁን በሚኖርበት የሥልጣኔ ዘመን ውስጥ ብዙ ሰዎች አምባገነንነቱን እንዲያለስልስ ጥረዋል ። አሁን ደግሞ አብሮት ያለው ሰው የሚናገረው ለማስፈራራት ይሁን ወይም በእርግጥ ሚሪያምን ለሌሎች ምሳሌ እንድትሆን ለመግደል መሆኑን ለይቶ ሊረዳው አልቻለም ። የማይታመን ቢሆንም በዚህ ቦታ የሚፈለገውን እር ምጃ መውሰድ ይቻላል ።

" ትክክል አይደለም ? በርንስቴይን 50 ያህል የሚሆኑ የወንዶ ችና የሴቶች ሕይወት በአደጋ ላይ እንዲወድቅ በማድረግዋ ለጥፋትዋ ተገቢ ቅጣት ማግኘት የለባትም ? " ብሎ በርግ በድጋሚ ሆስነርን ጠየቀው ።

ሆስነር ትኩር አድርጐ ሚሪያምን ሲመለከታት ጨለማና አሸዋ ለብሳ በአንገቷ ላይ እንደጠፋ ሕጻን ልጅ ጨርቅ አንጠልጥላለች ። "ልክ ነው ፤ ጢት ለፍርድ መቅረብ አለባት ። "

"ለእኛ ጢት የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም ይሆናል ። የመስክ ሥነ ሥርዓት እስተማማኝና ትክክል መሆን አለበት ። አሁን መሠራት ያለበት እንደዚያ ነው ። መደረግ ያለበት አሁኑኑ ነው" አለው በርግ ።

* * *

ጀኔራል ዶብኪን በአንድ ከጭቃ በተሠራ ጐጆ ውስጥ ጭድ በተጐዘጐዘ መደብ ላይ ተጋድሟል ። በነፋስ በየቀዳዳዎቹ የሚገባውም አሸዋ በሰውነቱ ላይ ተከምሯል ። የመቅረዙ መብራት ቢውለበለብምና ብልጭ ድርግም ቢልም በግልጽ አይታይም ። በአጠገቡ ተኝቶ የነበረው ሰው ተንቀሳቅሶ አቃሰተ ። ዶብኪን ሰውየው እንደነቃ ስለአወቀ በአረብኛ "አንተ ማነህ ?" ብሎ ጠየቀው ።

ሰውየው "አንተስ ማነህ ?" ብሎ ጥያቄውን በጥያቄ መለሰለት።

ሰውየውን ከወንዙ ውሀ ውስጥ አግኝተው ያመጡት መሆኑን ለዶብኪን ሰዎቹ ነግረው ታል ። ጫማና ሸሚዝ አልነበረውም ። እንደ ነብር ቆዳ የተዝጐረጐረ ሱሪ ታጥቋል ። ሺር ጃሹብ የተባለው ሸማግሌ አሁን የተገኘው ቁስለኛ ሰው አይሁዳዊ እንደሆነ ዶብኪንን ጠይቆት ነበር ። ዶብኪን ግን እውነቱን ሸሽጐ እንደማያውቀው ነግሮታል። አሁን በማነጋገር ላይ ያለው ሰው አሽባል እንደሆነ ዶብኪን አውቋል።ሆኖም ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ አልነበረም ። ሺር ጃሹብ የአካባቢው ቄስ ፡ አስተማሪና ኃላፊ ስለነበረ ቁስለኛው ሰው እንክብካቤ እንዲደረግለት ወይም እርሱ በሚተኛበት ጐጆ ውስጥ እንዳይተኛ የሚከለክል ምክንያት እንደ አለው ዶብኪንን ጠየቀው ። ዶብኪን ግን በበኩሉ የተጠየቁት ነገሮች የማይፈጸሙበት ምንም ምክንያት የሌለ መሆኑን ለሽማግሌው ነገረው ።

ዶብኪን ለቁስለኛው ሰው መልስ ከመስጠቱ በፊት ትኩር አድርጐ ተመለከተው ። "እኔ አሳ አጥማጅ ነኝ ። ጀልባዬ በነፋሱ ኃይል ተገልብጦ ቆስያለሁ ። እነዚህ አይሁዶች አግኝተው እርዳታ አደረጉልኝ ። "

ሰውየው ተገላብጦ ወደ ዶብኪን ዞረ ። የመቅረዙ መብራት በሰውየው ፊት ላይ ብልጭ ድርግም ይል ስለነበረና ዶብኪንም ፊቱን ስላየው ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ አለ ። አስቂኝና አስደናቂ የሆኑትን የሰውየውን ዓይኖች ዶብኪን ተመለከታቸው ። በፊቱ ላይ የተተለተለው ጠባሳ የአሁን ሳይሆን የቆየ መሆኑን አረጋገጠ ። ሰውየውም የእ

ርሱን የጸጉር አቆራረጥ ፣ እጆቹንና ያለበሱ ክንዶቹን አንድ በአንድ ያይ እንደነበረ ዶብኪን ገብቶታል ። የዶብኪን ጫማዎች ራቅ ብለው በጨለማው ውስጥ ስለተቀመጡ ሰውየው ያላያቸው ይመስላል ። ዶብ ኪንን ሰውየው በሚገባ ስለአየው በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ አሳ አስ ጋሪ እንዳልነበረ ሰውየው በተመለከታቸው ነገሮች ያወቀ መሆኑን አውቋል ። ተገላብጦ በጀርባው ተኛ ። " መልካም አሳ አስጋሪ ፤ እነዚህ ይሁዶች ስለአደረጉልን እርዳታና እንክብካቤ የማመስገን ግዴታ አለብን ። "

" የቀን መጉደል ከማያውቁት ጋር ያስተኛል " በሚለው አነጋ ገር ዶብኪን ተስማማ ።

ዶብኪን ወደሰውየው ተመለከተ ። በተራራው ቁልቁለት ላይ አይቶታል ። ፊቱን በብዥታ አስታወሰው ። ነገሩ ግን ቅዥት ሳይሆን እውን ነበር ። ያለጥርጥር ፊቱን በትክክል አይቶታል ። " ማን ብየ ልጥራህ ? "

" ሰይድ ታሊብ ፤ አንተስ ? "

ዶብኪን አቅማማ ። ቤንጃሚን ዶብኪን ፡ እስራኤላዊ ወታደር ፣ የእግር ጦር ጄኔራል ! ብሎ ለመንገር ከተመኘ በኋላ ይህን ሃሳብ ትቶ " አሳ አጥማጅ ብለህ ጥራኝ " አለው ።

የዶብኪን አረብኛ ጥሩ ባይሆንም ታሊብ ቀልዱን እንዲቀጥል ለማድረግ እንዲገባው እያደረገ ተናገረ ። አንዱ የሌላውን ጉሮሮ አንቆ ሲጥ ለማድረግ ይጠባበቃሉ ። ይህንም አንድ ስህተት የሆነ ቃል ሊያፋጥነው ይችላል ። ታሊብ በተራራው ላይ በትክክል አላየኝ እንደሆን እደነቃለሁ የሚል ሀሳብ አደረበት ።

የሰውየውም ሆነ የራሱ ቁስል ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ ዶብ ኪን አሰላሰለ ። ቀጥሎም ክንዶቹን በብርድ ልብሱ አልብሶ ተነፈሰ ። የልብ ትርታውም ቀነሰ ። ብርታቱም ተመለሰለት ።

ከሸክላ የተሠራው መቅረዝ ከላይ እንደሳህን ሆኖ የሚበራው ፈትል የተነከረበት የቀለጠ ሞራ ያለው ሲሆን የሚሰጠው ብርሃን ደብዛዛ ነበር ። መቅረዙ በሁለቱ መካከል ባለው ወለል ላይ የተቀ መጠ ሲሆን ለታሊብ ይቀርባል ። አሽባሉ መቅረዙን ይመለከት እንደ ነበረና ለመሣሪያነት ለመጠቀም እንዳሰበ ዶብኪን ገብቶታል ። ዶብ ኪን በበኩሉ ዙሪያውን ሲመለከት ከብርድ ልብሱ በስተቀር ሌላ ምንም ነገር የለውም ። መሣሪያው በውሀ ተወስዷል ። በላይኛው ኪሱ ውስጥ አንድ ነገር እንዳለ ተሰማው ። መልሰው የሰጡት የጣእት ማምለኪያ ( ፓዙዙ ) መሆኑን አረጋገጠ ።

ዶብኪንና ታሊብ ነፋሱን እያደመጡና የመቅረዙን ደብዛዛ መብ ራት እየተመለከቱ በጕናቸው ተኝተው አንዱ ሌላውን ያይ ነበር ።

" አሳ መያዙ እንዴት ነበር ፤ አሳ አጥማጅ ? "

" እስከ ዛሬ ማታ ድረስ ጥሩ ነበር ። የአንተ ንግድ ምን ነበር ያልከኝ ? "

" ተምር ገዥ ነኝ ። "

አልፎ አልፎ ብርድ ልብሶቻቸው ከዓይኖቻቸው ላይ ሸርተት ሲሉ አንዱ በሌላው ላይ የነበረውን ጥላቻ ፣ ፍርሃትና ዛቻ ለማየት ይቻል ነበር ።

" ወደ ወንዙ እንዴት ልትመጣ ቻልክ ? "

" ልክ እንደ አንተው ። "

ንግግራቸውን አቁመው ሁለቱም ሳይንቀሳቀሱ ለብዙ ጊዜ ቆዩ። ዶብኪን አፉ እየደረቀ መምጣቱንና የጡንቻው ሥር ሲነዝር ተሰማው።

ኃይለኛው ነፋስ የመስኮቱን መዝጊያ ከፍቶ ስለገባ የመቅረ ዙን መብራት አጠፋው ። በጨለማው አንዱ የሌላውን ስሌ ለማነቅ ሲተናነቁ ሁለቱም ጩኸት አሰሙ ።

* * *

ደቦራ ጌዲዮን በእንግዳ መቀበያው ቤት በሥራ አስኪያጁ ክፍል ውስጥ በወለሉ ላይ እርቃንዋን ተጋድማለች ።·በረጅም ቀበቶ በጀር ባዋ ላይ የተገረፈችው ሰንበር በሲጋራ በአቃጠሉዋት ቁስል ተሸፍኖ አል ። በአሰቃቂ ሁኔታ በፈጸሙባት ድርጊት በጭንዋ ፣ በቅልጥም ዋና በቂጥዋ ላይ ከነበረው ቁስል ደም ይፈስ ነበር ።

አህመድ ሪሽ በጕድጓዳ ሳህን ላይ በነበረ ውሀ ፊቱንና እጁን ከታጠበ በኋላ ለሀማዲ " ግደላት " አለው ።

ሀማዲ በፊት ለፊቱ የቆመውን ተረኛ ዘብ የነበረውን " ካሲም" ብሎ ጠራው ።

ሪሽ እጆቹን በፎጣ ጠርጎ አደረቀ ። ደቦራ ስለብዛታቸው ፣ ስለ ጊዜያዊ መከላከያቸውና ስለአመዳደባቸው የነገረችው ሲዋጋ ካየው የበለጠ አልነበረም ። አሁን ደቦራ የተናገረችው እያስመሰለ የራሱን ሃሣብ እንደሚስማማቸው እያደረገ ይነግራቸዋል ። " ሳሌም ፣ የሼር ጂው ነፋስ እንደዚሁ ከቆየልን በአንድ ሰዓት ውስጥ በተራራው ላይ እንደርሳለን ። ሰዎቻችንን ከቁልቁለቱ በላይ ወስደን እንቅስቃሴ ሳያ ደርጉና ድምጽ ሳያሰሙ ተሸሽገው እንዲቆሙ እናደርጋለን ። "

ሀማዲ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። ነፋሱ የተላከው በአላህ መሆን አለበት ። ነፋሱ ባይመጣ ኖሮ ሁለቱም በራሳቸው ሰዎች ይገደሉ እን ደነበረ አውቋል ። ሬሽ ግን ይህን እንደማያውቅ ሆነ ። " ሰዎቻችንን እሰበስባለሁ " አለው ።

ሬሽ " ጥሩ " ብሎ በመጀመሪያ ወደ ሴትየዋ ፣ ቀጥሎም ትኩር አድርጎ ወደሚመለከታት ተረኛ ዘብ ተመለከተ ። " አዎን ፣ አዎን ! ካሲም ልትጠቀምባት ትችላለህ ። ከዚያ በኋላ ገድለህ ሬሳዋን በማ ቃጠል አመዱን ወደ ወንዙ በትነው ። ለዚህም ማስረጃ አልፈልግም" ብሎ ከነገረው በኋላ ወደ ሀማዲ በመዞር " የወታደር ሥራ እንቅስቃሴ አንድ ራሱን የቻለ ጉዳይ ነው ። ማሰቃየትና መግደል ደግሞ ሌላ ነገር ነው ። ስለጁሆ ( መያዣ ) ጉዳይ ነገ ከእስራኤል ጋር መደራደር አለ ብን " አለው ።

ሀማዲ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። ሬሽ አንድ እብድ ሊያደርገው የሚችለውን ቀጭንና ትርጉም የማይሰጡ መስመሮች ሠራ ። በፍል ስጥኤማውያን ሕዝብ ዘንድ ጀግና ተብሎ ባይታወቅ ኖሮ ሀማዲ ቀደም ብሎ ይገድለው ነበር ። ደቦራን በእጆቹና በጉልበቱ እንደዚሁም በኃ ይለኛ ንክሻ ሬሽ ሲያደርጋት የነበረው ሀማዲን አሳዝኖታል ። ሀማዲ አስቀድሞ አሰቃይቷታል ። ሬሽ ያደረገው ግን ፍጹም ልዩ ነበር ። ግርፊያውና በሲጋራ ማቃጠሉ ያለጥርጥር ከንክሻው የበለጠ ጐድቷ ታል ። እየጮኸ በጥፊ እየጠፈጠፈ ፣ እየሚጨረ ፣ ሰውነቷን እየቀደደ ያደረገው የእብድነት ሥራ የሚፈልገውን ሁሉ እንድትናገር አድርጓ ታል ። ሀማዲ ተሰቃይታ በተናገረችው እንደ ጥፋተኛ አድርጎ ሊቆ ጥራት አልቻለም ። ተስፋ ያደረገው በውጭ ያሉ ሰዎች እዚህ በመ ደረግ ላይ ያለው ምን እንደሆነ እንደማያውቁ ነበር ። ሀማዲ ፊቱን አዞሮ ከክፍሉ ውስጥ ወደ በረንዳው ወጣ ።

የመጨረሻዎቹ 50 የሚሆኑ ሴቶችና ወንዶች በድንኳናቸው ውስጥ ተራዳዎቹን እየተደገፉ እግሮቻቸውን አጣምረው ተቀምጠዋል ። ሀማዲ ፊሽካውን እንደነፋ ከድንኳኑ ውስጥ ሁሉም ተግተልትለው በመውጣት ወደ በረንዳው መጡ ። ራሶቻቸውን ፣ አፎቻቸውንና ፊቶ ቻቸውን ከዓይኖቻቸው በስተቀር ሸፍነው በኃይለኛው ነፋስ ውስጥ ቆሙ ። ሀማዲ እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶና እንዲሰማቸው በኃይል ጮኾ " አላህ ይህን ሺርጂ የተባለውን ንፋስ ላከልን " በማለት ንግ ግሩን ጀመረ ።

* * *

ሆስነር በአውሮፕላኑ ክንፍ አጠገብ ቆሞ ሰዎቹ ልዩ ልዩ ጨር ቆች ጠምጥመው በነፋስና በአሸዋው ውስጥ በመጥለቅ ላይ በነበ ረው የጨረቃ ብርሃን ጣረሞት ይመስል ወዲያና ወዲህ ሲንከላወሱ

ተመለከታቸው ። ተመልሶ ወደ እውኖንላት ውስጥ ገባ ። ዶኑን እንጂ በክፍሉ ውስጥ በገባው ነፋስና አቧራ ምክንያት ለመናገርም ሆነ ለመ ስማት አስቸጋሪ ነበር ። ለሙቀት መውጫ በማሪያው ላይ ተሠርተው የነበሩት ቀዳዳዎች አሁን የአቧራ መግቢያ ሆነዋል ። በመግቢያው በኩል ወደ ክፍሉ መጨረሻ ሔደ ።

ሚሪያም በከፊል የተቃጠለ ጨርቅ ደልድላ ቅልጥሞቿን ወደ ሽንጉበትዋ አስጠግታ ተቀምጣለች ። አንድ ሰው በስጣት በአንድ ትንሽ የእጅ መብራት እየተጠቀመች መጽሐፍ ታነባለች ። የአስቸ ኳይ ሁኔታን የሚያሳይ መብራትም ከላይ አለ ። ሆስኑ እንደቆመ አቆልቁሎ ተመለከታት ።

እርስዋም ከመጽሐፍዋ ላይ ቀና ብላ በመመልከት “ ጊዜው ደረሰ ? ” ብላ ጠየቀችው ።

ጉሮሮውን አፍታቶና ጮኾ “ እንዳልቀሰቀስችሽ ተናግራለች ፤ በስዓትዋ ላይ መተኛቷንና ፈጽማ እንዳልቀሰቀስችሽ በተጨማሪ ተና ግራለች ” አላት ።

ሚሪያም መጽሐፉን አጥፋ በጉልበቷ ላይ በማስቀመጥ “ እኔን ለማዳን ዋሽታለች ። ከቀሰቀሰችኝ በኋላ ተኝቻለሁ ” አለችው ።

“ ጨዋ አትሁኚ ፤ ሚሪያም ” ብሎ በቅልጥሟ ላይ ያስቀመጠ ችውን መጽሐፍ ተመለከተ - ካሙስስ ዘ ስትሬንጀር - ”

“ ለምን አልሆንም ” ብላ የያዘችውን መብራት አጠፋች ። ቀጥ ላም “ ለዚህ ቡድን አንድ የለውጥ ትምህርት ወይም እርምጃ ይሆ ናል ። ይልቅስ ሰዓቱ ደረሰ ወይ ? ” ብላ ጠየቀችው ።

“ ገና ነው ። ”

ቁጣና ሳቅ በተቀላቀለበት አነጋገር “ አዝናለሁ ፤ መውቀስ የለብኝም ፤ አሁን ከአንተ አንድዋ ነኝ ። ማለትም አንዲት ሴት ገድያለሁ ” አለችው ።

“ አዎን ፤ ምናልባትም ገድለሽ ይሆናል ። ”

“ ታዲያ ለፍርድ የሚቀርበው ማነው ? ”

“ ስህተቱን የፈጸመችው ገልጻ ካልተናገረች በስተቀር ሁለታች ሁም ትቀርባላችሁ ። ”

“ ገልጬ ነግሬሃለሁ እኮ ። ”

“ ምን ማለቱ እንደሆነ ይገባሻል ። ”

“ ሁለታችንም እንዋሻለን ። ”

“ እንደምታደርጉ እርግጠኛ ነኝ ። በተጨማሪም የወታደር ሥነ ሥርዓት አለ ። ቀድሞም የሆነ ነው ። በበርግና በእኔ መስካሪነት ሁለታችሁም ጥፋተኛ ትሆናላችሁ ።”

“ ይህ ሁሉ የሚያሳየው ወይም እናንተ በእውነት አንደኛችንን ወይም ሁለታችንንም ለመግደል ፈልጋችኋል ? ”

ሆስነር ሲጋራውን አቀጣጠለ ። የሚገድል ቡድን ማቋቋም ይቅርና በወታደር ፍርድ ቤት ተሰይሞ የሚዳኝ አንድ ሰው ለማግኘት የ ሚችል ቢሆን እንኳን ሆስነር ይደነቃል ። ታዲያ የዚህ ድርጊት አላማው ምንድን ነበር ? ሥልጣንን ለማሳየት ሕጉ እስከ መጨረሻው ተግባራዊ መሆን እንደሚገባው ለማረጋገጥ ነበር ? ወይስ በሥራ የደከሙ ወንዶችና ሴቶች በግዳጅ ላይ እንዳሉ መተኛት የሚፈልጉትን ወይም ትዕዛዝ ለመፈጸም ችላ የሚሉትን ለማስፈራራት ነበር ? ወይስ አንድ ወይም ሁለት ችካል እንዳመጣለት በርግ የቀየሰው ሃሳብ ነበር ? ሆስነር ከላይ በአዕምሮው ውስጥ የተከሰቱትን ጥያቄዎች አብላላ ።

“ መልካም ፤ እኛን ለመርዳት አስባችኋል ፤ ወይስ አላሰባችሁም ? ካልሆነ የምሠራው ስላለኝ ከዚህ ልውጣ ። ለፍርድ የምታቀርቡን ከሆነ እስከ ጧት አታቆዩን ። አሁኑኑ አድርጉት ። ”

ሆስነር ሲጋራውን ወርውሮ አቀልቁሎ ተመለከታት ። በቀዳዳ የገባው ብርሃን በፊትዋ ላይ አርፏል ። ቀና ብላ ተመለከተችው ። እንደ ኃይለኛ አነጋገርዋ በፊትዋ ላይ ቁጣ አልታየም ። የሚሆነውን ለመቀበል የተዘጋጀች ትመስላለች ። በድንገት ማንኛውም የሚያደርጉት ስብሰባ የመጨረሻ እንደሚሆን አመነ ።

“ አንተ ራስህ ምላጩን ትስበዋለህ ፤ ያዕቆብ ? ”

ሆስነር ወደ እርስዋ ተራመደ ። ምን እንደሚያደርግ ወይም እንደሚል ገና የወሰነ አልመሰለም ። በፍጥነት በፊትዋ ተንበርክኮ እጆቹን እራቁታቸውን በሆኑት ጉልበቶቿ ላይ አስቀመጠ ። “ እኔ . . . በአንቺ ላይ ጉዳት ከማድረሴ በፊት ራሴን እገድላለሁ ። አንቺን ለመጉዳት የሚሞክረውን ማንኛውንም ሰው እገድላለሁ ፤ አፈቅርሻለሁ ። ” ቃሎቹ እርስዋን ያስደነቃትን ያህል እርሱን አላስደነቁትም ።

ዞራ በቀዳዳው መካከል ወደ ውጭ ተመለከተች ። ጉልበቶቿን አፈፍ አድርጎ እየወዘወዛቸው “ አፈቅርሻለሁ ” አላት ። ወደ እርሱ ዞራ ራስዋን በአዎንታ በመነቅነቅ እጆችዋን በእርሱ እጆች ላይ አስቀመጠች ። ዝቅ ባለና በጐረና ድምጽ “ በዚህ ዓይነት ደረጃ ላይ ስለ አደረስኩህ አዝናለሁ ፤ ያዕቆብ ” አለችው ።

" መልካም ፤ እንደምታውቂው የአንድ ሰው የሕይወት ሙሉ እምነቶች በዚህ ዓይነቶቹ ውሳኔዎች ላይ ውጤት አይኖራቸውም - ውሳኔዎቹ ከልብ የመነጩ ናቸውና - " ብሏት ከአንገት በላይ ፈገግታ አሳያት ።

እርስዋም የፈገግታ መልስ ሰጠችው ። " ያ እውነት አይደለም። አንተ ሃሳበ ጽኑ ሰው ነህ ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ ስለአደረስኩህ አዝናለሁ ። ኤሸር አሮንሰንን ለመግደል ጊዜ ይኖርሃል ? " አለችው።

" ስለዚያ አታንሺብኝ። ሁለታችሁንም ከዚህ አወጣችኋለሁ ። "

እጁን በጣም ጨበጠችው ። " ያዕቆብ፣ ሥራ ፈተህና ሀብታም ሆነህ ባባትህ ቪላ መቆየት ይሻልህ ነበር ። "

" በበአል ቀን ወደ አባቴ ቪላ ትመጫለሽ ? "

ፈገግ ብላ እጆቹን ወስዳ በፊቷ ላይ አደረገቻቸው ።

ለብዙ ፤ ለብዙ ዓመቶች ያልተሰማውን አሁን ልቡ ትር ትር ሲል ተሰማው ። ለመናገር እስኪችል ድረስ ለጥቂት ጊዜ ቆየ ። "እኔ... አዝናለሁ . . . እኔ . . . እኔ ቀድሜሽ እሔዳለሁ ። "

በለሰለሰ ድምጽ " ይገባኛል " አለችው ።

" ይገባሻል ? "

" ወደፊት ፣ ወደፊት ዕድል አይኖረንም " ብላው ጉንጭዋን በደረቱ ላይ አስጠጋች ።

እርሱም ወደ እርሱ አስጠጋት ። " አይኖረንም ። " መኖር ይፈልጋል ። ቢኖርም እርስዋን እንደማያገኛት አውቋል ። ላስኮቭ ወይም ባለቤትዋ ወይም ሌላ ሰው ይጐዳኛታል ። እንባዋ ተዝረከረከ ። እንባዋ በፊቱ ላይ ተሰማው ። በመጀመሪያ የራሱ መስሎት ነበር ።በእርግጥም የራሱ እንባ ነበር ። ተቃቀፉ ። ራስዋን በለመቆጣጠር ጮኸች። ማልቀስዋን እንድታቆም ለማድረግ የሚችልበት ሃሣብ አልመጣለትም ።ከፈለገች ለማልቀስ መብት አላት ብሎ አሰበ ። ጩኺ ፣ አልቅሺ የፈለግሺውን አድርጊ ፣ ሚሪያም ፤ በልብሽ ብቻ በመያዝ አትሰቃዩ የሚፈልጉትን ደብቀው በመያዝ የሚሰቃዩ ቂሎች ናቸው ። በቴል አቪቭና በኢየሩሳሌም ውስጥ እያንዳንዱ የሚያውቃት ሚሪያም ናት ። ሕመምሽን ዓለም ይወቅልሽ ። እያንዳንዱ ለማንኛውም ለሚደርስበት በደል ፤ ለሚፈጸምበት ለማንኛውም አረመኔያዊ ድርጊት ፤ ለማንኛውም ለሚደርስበት ክፋት ከጮኸ ወደ እውነተኛ ርኅራኄና ትክክለኛነት የሚያመራውን የመጀመሪያ እርምጃ እንወስዳለን ። ሰዎች ለመገደል ሲወሰዱ ተቃውሞ የ ማያሰዩት ለምንድን ነው ? ይጩኹ ፤ ያልቅሱ ፤ ያስተጋቡ ።

ሃሳቡን ለማንበብ እንደቻለች ሆና ራስዋን ወደኋላ አድርጋ በረጅሙ አለቀሰች ።

ልክነሽ ሚሪያም ። ጨኺ ። ዘርሽን አጠፉ ፤ ቤተሰቦችሽን ጨፈ ጨፉ ፤ የልጅነት ጊዜሽን አበላሹ ፤ ባልሽን ወሰዱ ፤ ልጅሽን ገደሉ ፤ ወዳጆችሽን ቀተሉ ፤ በመጨረሻም እዚህ ብቻሽን እንደ ያዕቆብ ሆስነር ካለ ሰው ጋር ጣሉሽ ። ስለዚህ የማልቀስ መብት አለሽ ።

መንሰቅሰቅዋ እየጨመረ ሔደ ። ቤከር ለቅሶዋን እንደሚሰማና ምናልባትም እውጭ ያሉት ሌሎቹም ጭምር እንደሚሰሙ ሆስነር አውቋል ። በበኩሉ ቢሰሙም ደንታ አልነበረውም ። “ በመጠኑም ቢሆን የተሻለ ለማድረግ ከቻልኩ እፈጽመዋለሁ ፤ ሚሪያም ። ”

የገባት መሆንዋን ለማሳወቅ ራስዋን በአዎንታ ነቀነቀች ። ቀጥላም በድንገት በእጆቹ ራሱን ይዛ ባልዋ ለጦርነት በሔደበት ቀን እንደሳመችው አድርጋ ሳመችው ። “ ዮሴፍ ” ብላ ስሙን በመጥራት ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ። ቀጥላም “ ያዕቆብ ” ብላ ሆስነር ሊሰማው ያልቻለ ቃል ተናገረች ።

ከንፈሮቹ ፊትዋንና አንገትዋን ሲዳስሱ እንባዋን ቀመሰው ። ዮሴፍ ፣ ቴዲ ፣ ያዕቆብ ፣ ሰላም እስከ አመጡላትና እስካልጐዱት ድረስ ለእርስዋ ምን ልዩነት ያመጣል ? ሆስነር እንደገና ባለቤትዋ በሕይወት በመጣላት ብሎ ተመኘላት ። ሪሽ ያውቃል ብሎ ሊነግራት ይገባው ይሆን ? ፈጽሞ አይሆንም ። ያንን ፈጽሞ አይነግራትም ። ዮሴፍን እየጠበቀች በምትኖርበት ጊዜ ቴዲ ላስኮቭ ወይም ሌላ ሰው የምትፈልገውን እንደሚያደርጉላት ተስፋ አለው ። እርሱ ራሱ ቢሆን ይወድ ነበር ። እንደማይሆን ግን ያውቃል ። ኢየሩሳሌምን እንደገና አያ ያትም ። ቢያያትም ከባቢሎን ውጭ ደስታ አይሰጣትም ። እንስሳ የሌላውን ቁስል እንደሚልስ ሁሉ እርሱም የሚሪያምን እንባ ላሰ ።

* * *

ዶብኪን ደምም ሆነ የሌላ ሰው ላብ ቀምሶ አያውቅም ። ሁለቱም እንዴት ጨው ጨው እንደሚሉ አስደንቆታል ። አረቡ የብልት ፍሬውን ጨምዶ ያዘ ። ዶብኪን ደግሞ የመተንፈሻ ስሌውን ነክሶ ያዘ ። የሁለቱም ትግል የቀደመ እንዲገድል ነበር ። በመጀመሪያ ያለ መሣሪያ ትግሉን ለመጀመር እርግጠኞች አልነበሩም ። ራስና ደረታቸውን በሙማታት ጀመሩ ። ታሊብ መቅረዙን አንስቶ በዶብኪን ራስ ላይ ሰበረው ። የዶብኪን ደም በአንገቱና በጀርባው ላይ ሲፈስ ተሰማው ። ሁለቱም አንዱ የሌላውን ደካማ ጐን ለማግኘት ታገሉ ።

ዶብኪን የሚሰማውን አሰቃቂ ሕመም ከምንም ባለመቁጠር በኃይል መተንፈሻውን ነክሶ ያዘ ።

ታሊብ የዶብኪንን የብልት ፍሬ በበለጠ አጥብቆ ለመያዝ ቢሞክርም የትልቁ ሰው ቅልጥሞች ስለአስቸገሩት እንደፈለገው አልሆኑለትም ። ታሊብ ፈልጐ የዶብኪንን ዓይኖች ስለደረሰባቸው በጣቶቹ ለመሠርሰርና ለመውጋት ሞከረ ። ግን ዶብኪን በኃይል ጨፍኖ ፊቱን ወደ ታሊብ አንገት ሥር ቀበረው ። ሁለቱም ሕይወታቸውን ለማትረፍ ትግሉን የሚያካሂዱት በፀጥታ ነበር ። አንደኛቸውም ይቅርታ አልጠየቁም ።

ሁለት ጠባቂዎች ከመንገዱ ባሻገር ባለው ጐጆ ውስጥ ከልዩ የዛፍ ቅጠል ሻይ እያፈሉ እንቅልፍ እንዳይወስዳቸው ተረት ያወራሉ ። ከነፋሱ ማፏጨትና መንገጫገጭ በስተቀር ሌላ የተለየ ድምጽ አልሰሙም ።

ዶብኪን ሕመሙን ሊቋቋመው አልቻለም ። በተጨማሪም በጭኑ ላይ የነበረው ቁስል ፈንድቶ መድማት ጀመረ ። ነፍሱን የሚስት መስሎ ተሰማው ። ደመነፍሱን ኪሱን ሲዳብስ ለጣእት ማምለኪያ የተሠራውን ስለአገኘ አውጥቶ የታሊብን ጆሮ ሲመታበት አንድ ክንፉ ተሰበረ ። የአረቡ ጩኸት ነፋሱ በሚያንገጫግጨው መስኮት ተዋጠ ።

ታሊብ አያያዙን ስለአላላለት ዶብኪን ወደኋላው አፈገፈገ ። ዶብኪን በጠንካራ እጁ ተንጠራርቶ ማምለኪያውን በታሊብ ዓይን ውስጥ ሻጠው ። ሰውየው ጮኾ ፊቱን ሸፈነ ። እንደገና በማምለኪያው ክንፍ የታሊብን አንገት ስለወጋው ደሙ ቲን ብሎ በዶብኪን ፊት ላይ ተረጨ ።

ታሊብ አንገቱን በሁለት እጆቹ ይዞ እያጓጐረ በክፍሉ ውስጥ ተሯሯጠ ። በትንሿ ጐጆ ውስጥ ሁለቱ ሰዎች እየተገለባበጡ ታገሉ ። በመጨረሻ የታሊብ ደም በወለሉና በግድግዳው ላይ ተረጨ ።

ዶብኪን በግድግዳው ጥግ ወድቆ አልተንቀሳቀሰም ። አረቡ መሞቱን እስኪያረጋግጥ ድረስ አዳመጠ።ተጋድሞ ነፍሱን ላለመሳት ታገለ። ከአፉ ውስጥ የደሙን ጣዕም ለማጥፋት ደጋግሞ ቢተፋም አልቻለም ።

— 27 —

ላስኮቭ ፎቶግራፍ ተንታኝ ወጣት እዝራ አዳም የሰጠውን መግለጫ አዳመጠ ። ተንታኙ አድላዊና ስሜታዊ ባልሆነ ሁኔታ ዘርዝሮ በግልጽ አስረዳ ። “ የጠፋውን ኮንኮርድ አግኝቼዋለሁ ፤ እመኑኝ ፤ ሔዳችሁ አምጧቸው ” የሚል መሆኑን ላስኮቭ ከሰውየው አነጋገር ማወቅ ቻለ ። ላስኮቭ ባለፉት ዓመታት ብዙ የፎቶግራፍ ተንታኞች በትር

ጉም አሰጣጥ ላይ ሲሳሳቱ አይቷል ። ሰውየው በኤስ አር - 71 በከፍ ተኛ እርቀት ላይ በሚያጐላ መሣሪያ እስራኤሎቹ ከመጠየቃቸው ከአንድ ሰዓት በፊት አሜሪካኖቹ ያነሱአቸውን 12 ፎቶ ግራፎች አንድ በአንድ መርምሯል ።

ከልዩ ልዩ ክፍሎች የመጡት ሚኒስትሮችና ጄኔራሎች በፎቶ ግራፉ ላይ ከነበሩት ቀይና ጥቁር ምልክቶች ምንም ነገር ለይተው መና ገር የማይችሉ ቢሆኑም የተሰጡአቸውን ፎቶግራፎች በመመልከት አዳም የተናገረውን ተከታትለዋል ።

አዳም ሌላ ፎቶግራፍ አንስቶ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመመ ልከት “ ማየት ትችላላችሁ - የምትጠሩት ምን ብላችሁ ነበር ? - ያለ ዚያ መሣሪያ በጨለማ የተነሱ ፎቶግራፎችን ለማንበብ አስቸጋሪ ቢሆ ንም በሸርጂው ነፋስ የተነሳውን አቧራ ፣ የቦታውን ከፍታና ሌላው ንም ተመልከቱት ። የፖለቲካ ችግር ያለ መሆኑ ቢገባኝም ዝቅ ባለ ሁኔታ በራሳችን ማንሳት ይኖርብናል ።

አንድ የአየር ኃይል ጄኔራል “ ስለፖለቲካው የምክር ቤት አባላት ይጨነቁበት ፣ አንተ ግን ቀጥል ” አለው ።

“ መልካም ፤ ቁጥር አስር ፎቶ ግራፍ ከሌሎቹ ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው ቀደም ብየ አይቼዋለሁ ። ምናልባትም በጦርነት ያሆናል ። አንዳንድ የተቃጠሉ ሥፍራዎች ያሉ ይመስላል ” አላቸው ።

“ ወይም የእረኞች ሠፈር ” አለ አንድ የጦር ሠራዊት ጄኔራል።

“ ወይም መንደር ” አለ ከአንድ ሰዓት በፊት አጉልቶ በሚያሳይ መነጽር ስለተነሱ ፎቶ ግራፎች ምንም እውቀት ያልነበረውና በቶሎ ነገሩ የገባው አንድ ሚኒስትር ።

አዳም “ አዎን ፤ ከሁለት አንዱ ሊሆን ይችላል ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ስለእነዚህ ነገሮች በትክክል ሊታወቅ ይችል ይሆናል ። አር ኪዮሎጂስቶች የሚጠቀሙበትን የባቢሎንን ካርታ ተመልከቱ ። የክዌሪሽ መንደር ከዚህ ካየነው ነገር ወደ ደቡብ በኢሽታር በር አቅ ራቢያ አንድ ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ነው ። በተጨማሪም መንደሮቹ የተለያዩ ናቸው ። ሌሎችም ልዩ ልዩ ነቆጥቋጦች ይታያሉ ። ይህንም በክዌሪሽ ውስጥ ማየት ይቻላል ። በዚህ ምክንያት አቀበቱ ላይ የተ ቃጠለ ፎስፎረስ አለ የሚል እምነት አለኝ ። የዚህ ቃጠሎ ዝቃጭ የተለያየ ስፋት አለው ። ደብዛዛ ነው ። ትልቅ መሆን አለበት ። ምና ልባትም አንድ አውሮፕላን ሞተሩ ላለፉት 24 ሰዓቶች ያልተንቀሳ ቀሰ ይመስላል ። በተርታ ያሉ መኪናዎች የሚመስሉ ይንቀሳቀሳሉ ።

አንድ ትንሽ አውሮፕላን ለመብረር በመነሳት ላይ የነበረ ይታያል ። በፎቶግራፉ ላይ ትናንሽ ምልክቶች ይታዩአችኋል ? ይህም አንድ ትንሽ አውሮፕላን በተራራው ላይ የሚበር ይመስላል ” ብሎ በዝርዝር አስረ ዳቸው ።

በክፍሉ ውስጥ የነበሩት የዚህ ዕውቀት የሌላቸው ሰዎች ነገሩ አጠራጣሪ እንደሚመስላቸው ላስኮቭ አውቋል ። በጣም ያስደነቀው ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አዳምን በንግግሩ መሃል አቋርጦ “ የአምላ እለቃ አዳም ፣ አምንሃለሁ ፤ ለምን እንደሆነ እግዚአብሔር ያውቃል ፤ ግን አምንሃለሁ ” ብሎ የተናገረው ነበር ። ሌላው በበለጠ ያስደነቀው ደግሞ ከእርሱ ረዳት መኰንኖች ይልቅ ወደ ላስኮቭ ዞሮ “ ላስኮቭ ፣ በእነዚህ ነጥቦች ላይ መሠረት በማድረግ ታሪኩን ንገረኝ ” ያለው ነበር ።

ላስኮቭ ዙሪያውን ተመልክቶ “ እንግዲህ ይህን የምናየው በግ ምት ላይ ተንተርሰን...” ብሎ ሳያ ጨርስ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አቋርጦት “አይሆንም፤ አይሆንም፤ በግምት እንድትነግረኝ አልፈልግም ። የምፈ ልገው በመንፈስ የተገለጸልህን ነው ” ካለው በኋላ አንድ ፎቶ ግራፍ አንስቶ እያራገበ “ ይህ ምን ማለት ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ላስኮቭ ፊቱን በመሀረብ ጠርጎ “ እንግዲያውስ ይህ ማለት ኮንኮርዱ በሌየሩ ተገዶ ባቢሎን ወርዷል—ይህንም እንዴት እንደ ተደረገ እናውቃለን ። በእኛ አውሮፕላን ውስጥ ጠላፊ አልነበረም ። ስለዚህ የኮንኮርዱ አብራሪ—ቤከር—ሽብር ፈጣሪዎቹ ሊቆጣጠሩት በሚችሉት ቦታ እንዲያርፍ የጠየቁትን ትቶ በሌላ ቦታ አሳርፎታል” አለው ።

ላስኮቭ ዓይኖቹን ጨፍኖ የሚያስብ መሰለ ። ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ ዓይኖቹን ቢከፍትም በሀሳብ እርቆ ሔዷል ። ንግግሩን በመቀጠል “በዚያ ሰዓት ተሳፋሪዎች የመሸሽ ወይም የመዋጋት ምርጫ ነበራቸው? ምርጫ አልነበራቸውም ። ኮንኮርዱ በኤፍራጥስ ባሻገር ያለ ይመስ ላል ። ስለዚህ ወደ ውሀው ከመግባት በስተቀር ሌላ መንገድ አልነ በራቸውም ። በዚህ ምክንያት መውጫ አልነበራቸውም ። ሽብር ፈጣ ሪዎቹ እያንዳንዱን የመውጫ በር ወደዚያው በመከበብ ይይዙባቸዋል። ስለዚህ በዚያው ለመቆየትና ለመዋጋት ወስነዋል ። በጥንታዊ ምሽግ ውስጥ ናቸው ። መጥፎ የመከላከያ ቦታ አይደለም ። በካርታው ላይ ተመልከቱ ፤ አንድ ኡዚና አንድ ኤም - 14 የኮከብ ብርሃን ማጉ ሊያ ያለውና ምናልባትም ስድስት የእጅ ጠመንጃዎች ነበሩአቸው ። ሽብር ፈጣሪዎቹ እስራኤሎቹ ምንም አይኖራቸውም ብለው ወደ ተራ ራው ሲወጡ ሲተኩስባቸው ተደናግጠው ሲመለሱ የጣሉት አንድ

ወይም ሁለት መሣሪያ በተጨማሪ ያገኙ ይሆናል ። በእርግጥ እንደገና ለውጊያ ይመለሳሉ . . . ”

ላስኮቭ ለትንሽ ጊዜ ንግግሩን አቆመ ። የኮንኮርዱ ራዲዮ እንዳ ይሠራ ስለአደረጉባቸው ለማስተላለፍ አይችሉም ። ባለን መረጃ መሠረት በሂላ አካባቢ በራዲዮው ጣልቃ እየገባ እንዲንጫጫ የሚያደርግና መሰናክል የሚፈጥር ማስተላለፊያ እንዳለ ለማወቅ ችለናል ። ይህን በሚመለከት ብዙ ሪፖርቶች ስላሉ አዲስ ነገር አይደለም ። የአሁኑ ግን ልዩ ትርጉም ሊኖረው ይችላል ። ስለዚህ ለእርዳታ የሚመጣላቸውን ይጠብቃሉ ” ብሎ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተመለከተ ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ላስኮቭ ዞሮ “ የሚያስገርም ታሪክ ነው ጄኔራል ። አንተ በምትነጋገርበት የራዲዮ መስመር እኔንም ብታገናኘኝ ” ካለው በኋላ በእርሳሱ ጠረጴዛውን ቆርቁሮ “ እንግዲያው ጥቂት ሽብር ፈጣሪዎች ብቻ ናቸው ያሉት ማለት ነው ? በመከላከል ላይ ያሉት ከጥቂቶቹ ጋር በመዋጋት ራሳቸውን መከላከል ይችላሉ ” አለው ።

ፎቶ ተንታኙ “ በዚህ ፎቶግራፍ ላይ የምናየው ጦርነት የተካሔደበትን ከሆነ በጣም ከፍተኛ ውጊያ ነበር ። ግማሽ ኪሎ ሜትር የጐን ስፋት ያለው ቦታ በሙሉ የቃጠሎ ቅሬት አለበት ” አላቸው ።

“እንዲህ እንደምትለው ከሆነ የእኛ ሰዎች አይደሉም ። ከከፍተኛ የአረብ ጦር ጋር ሙሉ ጦርነት ሊያካሒዱ አይችሉም ” ብሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥዕሉን በመንካት “ ምናልባት በዚህ ላይ የምናየው የውስጥ የእርስ በርስ ጦርነት ይሆናል ” አለው ።

“ ትልቁ አውሮፕላንስ ” ብሎ አዳም አስታወሰው ።

“ ትልቁ አውሮፕላን በብዥታ የሚታይ ግልጽ ያልሆነ ነገር ነው” ብሎ ፎቶግራፎቹን ከፊቱ ከገፋቸው በኋላ በእርሳሱ ቆርቁሮና ጥቂት ወረቀቶች በጫጭቆ ከተነፈሰ በኋላ ቀና ብሎ ተቀመጠ ። “ እሺ ! ትልቅ አውሮፕላን ፣ ትልቅ ጦርነት ፣ ለምን አይሆንም ? ” ብሎ ወደ ስልከኛው ዞሮ “ እስከ አሁን የባግዳድን መስመር አላገኘህም ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ የባግዳድ መስመር ተገኝቷል ። በአንድ ደቂቃ ውስጥ ፕሬዚዳንታቸው በመስመሩ ላይ ይገኛል ። ”

ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ጸጥታ ከሰፈነ በኋላ ስልከኛው “ የኢራቅ ፕሬዚዳንት በቁጥር አራት ላይ ይገኛል ” ብሎ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነገረው ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዙሪያውን ተመልክቶ ስልኩን አንስቶ ቁጥር አራትን ከተጫነ በኋላ በሚገባ አረብኛ " እንደምን አደርክ ፕሬዚዳንት ፤ የደወልኩልህ ኮንኮርዱን በሚመለከት ነው ። ባቢሎን ፕሬዚዳንት ፤ አዎን ፤ ባቤል " በማለት ተነጋገረ ።

* * *

ሚሪያምና ኤሽር አሮንስን በኮንኮርዱ ክፍል ውስጥ በእስር እንዲ ቆዩ ተደርገዋል ። በርግ ወደዚያው ለፍርድ እንዲቀርቡ ብሎ ያቀረ በውን ሃሳብ ሆስነር እንዲዘገይ አድርጎታል ። ይሁን እንጂ ሰውየው ደጋግሞ ቢጠይቅም ሆስነር ከእርሱ ጋር ጥላቻ መፍጠር ስላልፈለገ ችላ ማለቱን መርጧል ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሥልጣኑን በእጁ ለማስገባት የሚያደ ርገው ቅስቀሳ ሌላው ተጨማሪ ችግር ነበር ። በዚህ በኩል ብዙ ተከ ታዮች አግኝቷል ። ሚኒስትሩ የቡድኑ የሕግ ኃላፊ በመሆኑ ብቻ ሳይ ሆን ለችግራቸው መፍትሔ የሚያመጣ የሚመስል ሃሳብ ነበረው ። ይህም በአሪኤል ዌይዝማን የተነገረ ንድፈ ሃሣብ ሲሆን ይኸውም ከአ ሁን በኋላ በኤፍራጥስ ወንዝ ዳርቻ አንድም አረብ አይኖርም ። ስለ ዚህ እስራኤሎቹ በምዕራብ ምሽግ በኩል ወርደው የኤፍራጥስን ወንዝ አቋርጠው መሔድ ይችላሉ ። የኮንኮርዱ የሕይወት ማዳኛ ከረጢቶች ለቁስለኞቹና መዋኘት ለማይችሉት መስጠት ይቻላል የሚል ነበር ።

ሆስነርና በርግ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ባቀረበው ሃሣብ ላይ ለመወያየት ተስማምተዋል ። ስብሰባው የተካሔደው ቆሻሻ በሞላ በት በአውሮፕላኑ ክፍል ውስጥ ሲሆን ስብሰባው የተመራው በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ነበር ።

ሆስነር " ሃሣቡ የተወሰነ እውነትነት አለው ። ነገር ግን አህ መድ ሪሽ ጠላት እንዳያመልጥ ዋና ዋና በሮች እንዲያዙ የሚለውን እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነውን የወታደር ዘዴ ሳይጠቀም ይቀራል የሚል እምነት የለኝም " አላቸው ። ይህን ለብዙዎቹ ለመግለጽ ቢሞ ክርም ለሚናገረው ሁሉ የበለጠ ተቃውሞ ደረሰበት ።

የሆስነር ኃይል ተመስርቶ የነበረው ታማኝና ጀግና በነበሩት ሰዎቹ ብሪን ፣ ካፕላን ፣ ሩቢን ፣ ጃፍ ፣ ማርከስና አልፐርን ላይ ነበር ። ብሪን ሞተ ። ካፕላን ፣ ሩቢንና ጃፍ ቆሰሉ ። በተጨማሪም በተራራው ላይ የታጠቁት የእርሱ ብቻ መሆናቸው ቀርቷል ። አሁን ጥሩ ምክር እንኳን ቢሰጥ የሚያገኘው መልስ ተቃውሞ ሆነ ።

በርግ የሆስነርን ሃሣብ በመደገፍ " ወንዙን ለማቋረጥ ቢችሉም እንኳን ሪሽ ተራራው መለቀቁን ካወቀ ስለሚከታተላቸው ብዙ እር ቀው ሊሔዱ እንደማይችሉና በአውላላ ጭቃማ ሜዳ ላይ በመሔድ

በቀበሮዎች እንደተያዙ ጥንቸሎች ማለቅ - ወይም እጅግ በጣም መጥፎ ለሆነው ነገር ተገዶ ራስን አሳልፎ መስጠት ይሆናል ” አላቸው ።

ይህም ሆኖ ከሰዎቹ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከባቢሎን ወጥተው መሔድ ይፈልጋሉ ። ሆስነር ያለውን ኃይል ሁሉ በመጠቀም ሰዎቹ እንዳይለያዩ ማድረግ እንዳለበት አውቋል ። የከፈሉት መስዋዕትነትና ጀግንነት ሁሉ በዚህ ዓይነት በከንቱ እንዳይቀር ያስፈራል ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ስለ ሚሪያም በርንስቴይንና ስለኤሸር አሮንሰን ለመነጋገር ደጋግሞ በርግን ቢጠይቀውም በርግ ሃሣቡን አልተቀበለውም ። በርግ የጦር ፍርድ ቤት አቋቁሞ ሰዎች እስኪመርጥ ድረስ ሴቶቹ እንደታሠሩ ይቆያሉ ። ቄስ ሌቪን በብስጭት አህያ ብሎት ወጣ ። ጊዜያዊ ስብሰባው እንደገና ለመሰብሰብ ምንም ውሳኔ ሳያደርግ ተበተነ ።

ሆስነርም ሆነ በርግ እንደዚሁም ብዙዎቹ ስብሰባው ቶሎ በማለቁ አልተቆጩም ። ምክንያቱም በዲሞክራሲያዊ መንገድ ተብሎ ምርጫ ቢደረግ ኖሮ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከባቢሎን ይዞአቸው እንዲወጣ ሥልጣን ይሰጠው ነበር ። በቶሎ የስብሰባውን መበተን የወደዱት ጉዞው በአሰቃቂ ሀዘን ያልቅ እንደነበረ ስለአወቁ ነው ። አሪኤል ዌይዝማን ሙሴ አልነበረም ። ውሃው ለእርሱ ደርቆ የአህመድ ሪሽን ወታደሮች እያሰምጥለትም ነበር ።

* * *

አህመድ ሪሽና ሳላሜ ከሞት የተረፉ ወታደሮቻቸውን በኢሽታር በር አልፈው በቅዱስ መንገድ በኩል አድርገው የኒንማክ መቅደስ ሲደርሱ ወደ ምዕራብ ዞረው ወደ ግሪክ ቲያትር ሔዱ ። አንድ የቀድሞ የበይ ድልድይ ተሻግረው የመሃል ከተማውን የግንብ አጥር አለፉ ። ወደ ምዕራብ አንድ ኪሎ ሜትር ከሔዱ በኋላ የከተማውን የውጭ ግንብ ግድግዳ አልፈው ወደ ሰሜን ምሽግ አቅጣጫ አመሩ ።

ሪሽ ወደ ሀማዲ ጆሮ ተጠግቶ “ እዚያ መድረሳችንን እንኳን ሳያውቁ በቀጥታ በመሀላቸው እንገባለን ” አለው ።

“ ልክ ነህ ” አለው ሀማዲ ። ሀማዲ ከተራራዎቹ የሚመጣውን የነፋስ ድምጽ ሰማ ። በአጥሩ ግንብ ግድግዳ ጐን እየሔዱ ነበሩ ። ነገር ግን ጥንታዊ ፍርስራሽ ምሽጉ በአንድም ቦታ እንኳን ከሁለት ሜትር በላይ ከፍታ ስለአልነበረው በነፋሱ አማካይነት በሚመጣው አቧራና አሸዋ ምክንያት በደንብ ለመተንፈስ ስለአልቻሉ የሪሽን እርምጃ ተከትለው መሔድ አልቻሉም ። “ ቀስ ብለን እንሒድ አህመድ ” አለው ሀማዲ ።

“ አይሆንም ፤ ነፋሱ በአልታሰበ ጊዜ ሊቆም ይችላል ። ”

ሀማዲ ሰዎቹን ሲመለከት በጨለማው ውስጥ እየተጥመለመሉ ነበሩ ። ብዙዎቹ ፋሻ አስረዋል ። ጥቂቶቹ ያነክሳሉ ። ሥነ ሥርዓት ሊከተሉ ካለመቻላቸውም በላይ ሊተማመኑባቸው እማይችሉበት ደረጃ ላይ መድረሳቸው በግልጽ ይታይ ነበር ። ውጊያው እንደፈለጉት ካል ሆነላቸው እንደሚያምጹና አዛዦቻቸውን እንደሚፈጁ ሀማዲ አውቋል ። በውጊያው ላይ አሸናፊ ከሆኑ ደግሞ እስራኤሎቹን በመማረክ ፋንታ በሙሉ ይገድሏቸዋል ። ምርኮኞች ከሌሉአቸው ደግሞ ሪሽና እርሱ ለመደራደር ኃይል አይኖራቸውም ። በየትኛውም መንገድ ቢሆን እርሱና ሪሽ እንዳለቀላቸው ሀማዲ አውቋል ። ሪሽ ግን ይህ የገባው መስሎት ስለአልታየው ሀማዲ ሊነግረው አልፈለገም ።

ሪሽ እርምጃውን እየጨመረ ስለሔደ አሽባሎቹም ተከተሉት ። ዕድላቸውን ለማየት ወደፊት የሚሮጡና ለሚቀጥለው አስር ዓመት ወይም በላይ በአይሁዳውያንና በአረቦች መካከል የማይበርድ ግጭት ለመፍጠር የሚገሰግሱ መስሎ ለሀማዲ ተሰማው ። ሀማዲ ላለፉት ሀያ አራት ሰዓቶች የባግዳድን ራዲዮ ይከታተል ስለነበረ ፋይዳ ያለው ነገር ባይሠሩም እንኳን የሰላም ድርድሩን ስብሰባ አደጋ ላይ እንደጣሉት ተገንዝቧል ። ነገር ግን ከግል ስሜትና ፍላጐት ጋር ሲተያይ የዓለምን ታሪክ ለመለወጥ የሚኖረው ችሎታ የደበዘዘ ነው ። ሆስነር በባቢሎን አንበሳ ጐን በሚያቃጥለው ፀሐይ ላይ ራቁቱን ቆሞ ሲበረብረው በነበረበት ጊዜ እጁን በገላው ላይ ሲያንቀሳቅስ የቆዳው ስሜት እንዴት እንደነበረ ሀማዲ አስታወሰ ። ሆስነርን በግብረ ሰዶም ለመገናኘትና ለማዋረድ ፤ በመጨረሻም ለማሰቃየትና ገላውን ለመቆራረጥ በሃሣብ ቋመጠ ።

ሆስነር ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ስብሰባ ወጥቶ ብቻውን በነፋሱ ውስጥ ሲሔድ አሸዋው በፊቱ ላይ ተነሰነሰበት ። የተቀዳደደ ልብሱንም ነፋሱ አውለበለበው ።

ብሪን ለብዙ ጊዜ ይጠብቀው በነበረው ቦታ ካፕላንን አገኘው ። የኮከብ ብርሃን ማጉሊያው በኤኬ - 47 ላይ የተገጠመ ቢሆንም በዚያ በጨለማ ውስጥ ከጨረቃው ብርሃን የበለጠ ማሳየት አልቻለም ። ካፕላን በቁስሉ ምክንያት ትኩሳቱ እያንቀጠቀጠው ቢሆንም በዚያ መሳሪያ በጨለማው ለመጠቀም በተራራው ላይ ካሉት ሁሉ እጅግ የተሻልኩ እኔ ነኝ በማለት ትቶ ለመሔድ አሻፈረኝ ብሏል ።

ናኦሚ ሀበር በቀድሞው የከተማ ክልል ግንብ አጠገብ በአቧራው ውስጥ የሚንቀሳቀስ እንዳለ በማለቷ ወደታች ተመለከተች ። ፊት

ዋን በነፋሱ የሚመጣው አቧራና አሸዋ እንዳይነካት አድርጋ ሸፍና ዋለች ። ፊትዋን የሸፈነችበት መሣሪያ እዚያው ከልዩ ልዩ ነገሮች ገጣጥመው የሠሩት ሲሆን አርቆ ለማሳየት የሚችል ነበር ።

ሆስነር ካፕላንን ወደጐን ሳብ አድርጐ “ አቧራ በቀላቀለው ነፋስ ውስጥ ለማጥቃት ጨረቃ እስክትወጣ ድረስ እንደማይጠብቁ ታውቃለህ ” አለው ።

“ አውቃለሁ ” ። ካፕላን በሚገባ ሆስነርን ያውቀዋል ፤ ጠባዩንና በአነጋገሩ የሚፈልገውን ያውቃል ። አንድ የማያስደስት ነገር እን ደሚመጣ ገብቶታል ።

“ ጊዜያዊ የጦር ሠፈርም ሆነ መልዕክት አመላላሽ ስለሌለን እውሮች ሆነናል ። ”

“ አውቃለሁ ። ” አሁን ግልጽ እየሆነለት መጣ ።

“ እንደሚባለው እጅግ በጣም የተሻለው መከላከያ ጥሩ አድርጐ ማጥቃት ነው ። ትናንትና ማታ እንደ አደረግነው ውጊያውን መቀ ጠል አለብን ። ”

“ አዎን ። ” ሆስነር ከጨለማውና ከአቧራው ውስጥ ወጥቶ ወደ እርሱ በመምጣት እንደ መልአከ ሞት ተመስሎ ስለነካው አሁን የሚ ሞት መሰለው ።

“ ካልተዋጋን ምንም ከማድረጋችን በፊት በአቧራው ውስጥ ወደዚህ ተራራ ይመጣሉ ። በዚያ በኩል ተመልከት ። ”

ካፕላን ወደሚጥመለመለው አቧራ ተመለከተ ። ከክልላቸው አምስት ሜትር ውጭ ለማየት በጣም ችግር ነው ። ድንገተኛ ብርክ የሚሰጥ ፍርሃት ስለወረረው ጠመንጃውን አጥብቆ ያዘ ። በጨለማው ውስጥ በዳገቱ ላይ ምን እንዳለ ለማየት እንዲሮጥ ወኔው ገፋፋው ።

“ በዚያ ውስጥ ያለው ምንድን ነው፤ ሞሼ ? በዚያ ውስጥ ያለው ምንድን ነው ? ”

“ አላውቅም ። ”

“ ማወቅ አትፈልግም ? ”

ካፕላን መልስ አልሰጠውም ።

ሆስነር ከትንሽ ፋታ በኋላ ስለሁኔታው ገመገመ ። “ በአሁኑ ጊዜ እጅግ በጣም ውጤታማ የሚሆነው ዘዴ በደፈጣ አደጋ የሚጥሉ ሰዎች ወደ ታች መላኩ ይሆናል ። ይህ ቡድን የሚቀመጠው ከከ

ልላችን ውጭ ይሆናል ። ምክንያቱም አሽባሎቹ ከኢሽታር በር ወደ እዚህ የሚመጡት የግንቡን አጥር መከለያ አድርገው መሆን አለበት ። ደፈጣ ተዋጊ ማስቀመጣችን የሚጠቅመን ጠላቶቻችንን ለማጥቃት ብቻ ሳይሆን እኛም መምጣታቸውን አስቀድመን እንድናውቅ ያደርገናል" በሎ በኃይል ተነፈሰ ። " በርግ ግን ሰዎቻችንን አደጋ ላይ መጣል ወይም ኃይላችንን መከፋፈል የለብንም በማለት እምቢ ብሏል ። ይህ ተጨባጭነት የሌለው ውሳኔ ስለሆነ እኔ በነገሩ እገፋበታለሁ" ብሎ ንግግሩን ለትንሽ ጊዜ ቆም ካደረገ በኋላ " በሌላ በኩል . . . በሌላ በኩል አንድ ሰው ከአንድ አውቶማቲክ ጠመንጃና ከ100 ጥይቶች ጋር ሔዶ ቢያደፍጥ አሽባሎቹ በግንቡ ግድግዳ ጉን ሲያልፉ እርሱን አይተው ከመተኮሳቸው በፊት አሥራ ሁለቱን ሊገነጥላቸው ይችላል " ብሎት አሁንም እንደገና ንግግሩን ቆም ካደረገ በኋላ " ታውቃለህ ? ብሎ ጠየቀው ። "

ሆስነር በእጆቹ ነፋሱን ከልሎ ሲጋራ አቀጣጥሎ ለካፕላን ሰጠው ። ይህም ካፕላን ከሚያስበው በላይ የበለጠ ቅርበቱን የሚያሳይ ነበር ።

ካፕላን ሲጋራውን በኃይል ሳበ ። መልሶ ግን አልሰጠውም ። " እኔ . . . እስከ አሁን ዳገቱን አጋምሰው ወደ ላይ ካልመጡ በስተቀር እኔ እንደምገምተው ሃሳብህ ትክክል ነው ።"

"ልክ ነህ ፤ ሊሆን ይችላል ። ከቁልቁለቱ መጨረሻ ዘብ ጠባቂዎች ያለጥርጥር ይኖራሉ ። ይሁን እንጂ አንድ ሰው በዚህ በጨለማ ሾልኮ ሊያልፋቸው ይችላል " አለው ሆስነር ።

አስፈላጊ ሆኖ ከአገኘው ሆስነር ራሱ እንደሚሔድ ካፕላን ጥርጣሬ አልነበረውም ። ሆስነር ራሱ ለመሔድ ካልወሰነ የሚኖረው ብቸኛ ምክንያት በተራራው ላይ የሚፈጽመው በጣም አስፈላጊ የሆነ ተልዕኮ ስለሚኖረው ይሆናል ። ካፕላን በበኩሉ እስከ እርጅና ዘመኑ ለመቆየት ከፍተኛ ምኞት አድሮበታል ። ሆስነር ግን የዚያን ዓይነት ምኞት ዝቅተኛ አድርጎ ለማየት ይሞክራል ። " እዚያ ታች የሚሔድ ሰው የመመለስ ዕድሉ በጣም አነስተኛ ይሆናል ። "

" በጣም አነስተኛ ። "

" በተለይ የመንቀሳቀስ ኃይሉን የሚቀንስበት ቁስል ከአለው።"

ሆስነር በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ ። " ሞሼ ፣ እንደምታውቀው በዚህ ተራራ ላይ ጥቂት ሐቀኛ ወታደሮች ነበሩ ። እናንተ ስድስታችሁ፣ ዶብኪን . . . ጥቂት አባት ጠረኞች . . . በርግ ። አሁን ቁጥራቸው እየቀነሰ መጣ ። ምልምሎቹ እንዲያደርጉ የማይጠየቁትን በሙያ ላይ

የተሰማሩ ወታደሮች አንድ ቀን ለውትድርና ሥራ እንደሚጠሩ ያው ቃሉ ። ይህ አባባል ይገባሀል ? ”

“ በትክክል ይገባኛል ። ” ሆስነር ለምን ማርከስንና አልፐርንን እንዳላነሳ ካፕላን ገርሞታል ። አልቆሰሉም ። “ ይህ የክብር ጉዳይ ነው ። ” ሌሎች ምክንያቶች እንደነበሩት እርግጠኛ ነበር ። ካፕላን ግን የሆስነርን ሃሳብ ሊረዳው አልቻለም ።

“ መልካም . . . የቀባጀርኩትን ስለሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ ፤ ሞሼ ። ”

“ ምንም አይደለም ” ብሎ አቅማማ ። ሆስነር ለመሔድ አለመን ቀሳቀሱን ሲያይ “ በመሠረቱ አንድ ሰው የሌሎችን ሃሳቦች በመስማት የራሱ የሆኑትን ጥቂት ጥሩ ሃሳቦች ማግኘት ይችላል ” አለው ።

“ ልክ ነህ ። ”

ካፕላን እንደገና ካቅማማ በኋላ ዞሮ አንድ እርምጃ ተራመደ ። በትከሻው ላይ የሆስነር እጅ ሲያርፍበትና ሆስነር አንድ ትክክለኛ ነገር ሲናገር ቢሰማውም ቃሎቹን በሚገባ አልያዛቸውም ። ላለፉት 24 ሰዓቶች በቅርብ ያወቃቸውንና ክብር የሰጣቸውን ሰዎች እንኳን ደህና ሁኑ ማለት አልቻለም ። ጨለማውን ሰንጥቆ ሲሔድ ብቸኝነት በጣም ተሰማው ።

# —28—

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልኩን በጆሮው ላይ አስጠግቶ በመያዝ “ ቀጥል ” ብሎ ተቀመጠ ። በክፍሉ ውስጥ ስልኩን ጠልፈው በጆሮ ማዳመጫ ወደሚሰሙት ወንዶችና ሴቶች ዓይኑን ጣል አደረገ ። ከባ ግዳድ ጋር የሚያደርገው ንግግር በጥሩ ሁኔታ እየሔደ አልነበረም ። የኢራቁ ፕሬዚዳንት በጥሪው ከመደነቁም በላይ የተነገረውን በመ ጠራጠር የእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ያቀረበውን ሃሳብ አልተ ቀበለውም ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ነገሩን በግልጽና አጥብቆ “ ፕሬዚ ዳንት ፣ መረጃውን ከየት እንደአገኘሁት ለመናገር ያስቸግረኛል ። ግን ከታመነ ምንጭ ነው ” ብሎ ከነገረው በኋላ ከእውነተኛ ምንጭ የተገኘ መሆኑን ለማሳመን በክፍሉ ውስጥ ወደ አሉት ሰዎች ተመ ለከተ ።

ቴዲ ላስኮቭና ኢዝሐቅ ታልማን በመዝጊያው አቅራቢያ ቆመ ዋል ። የጠቅላይ ሚኒስትሩ አነጋገር እነ እርሱን የሚገመግም ይመ ስል ነበር ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአረብኛ ምን ማለት እንደሆነ የሚያውቀው አተነፋፈስ ፕሬዚዳንቱ አሰማ ። “ ነገሩ በጣም ያሳዝናል ፣ ግን እንድ

ንስማማ ሊያቀርበን የሚችል ነገር የለም ። ለማንኛውም ዝቅ ብለው የሚበሩ የስለላ አውሮፕላኖች መላክ አይቻልም ። ኃይለኛውና ሙቁ ነፋስም እየነፈሰ ነው ። ለማንኛውም በከፍተኛ እርቀት ላይ የሚመለከት የወዳጃችሁ የአሜሪካ አውሮፕላን ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ በአገራችን ላይ እንደበረረ እርግጠኛ ነኝ ። የተደረገው ይበቃል ” ብሎ የኢራቁ ፕሬዚዳንት ነገረው ።

“ ስለዚያ የማውቀው ነገር የለም ። ”

የኢራቁ ፕሬዚዳንት የተሰጠውን ማስተባበያ ወደ ጐን በመተው አስቸኳይ እርምጃ ለመውሰድ ያለውን ተቃውሞ አንድ በአንድ ዘርዝሮ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነገረው ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የፕሬዚዳንቱን ንግግር በከፊል እያዳመጠ እንዳለ ነፋሱ የመስኮቶቹን መከላከያዎች ሲያንገጫግጫቸው ሰማ ።በጐርፉ ፣ በአሸዋማው ውሽንፍርና በጨለማ መካከል በአየርም ሆነ በየብስ መንቀሳቀስ እንደማይቻል አውቋል።በበለጠ እንዲናገር በገፋፋው ቁጥር የኢራቁ የመጓጓገርና የመገናኛ መስመር እንደዚሁም ወታደሮቹ የገዛ አገራቸውን አቅጣጫ ለመለየት ብቃት የሌላቸው መሆኑን በበለጠ ለማወቅ ቻለ ። እነዚህ ችግሮች መኖራቸውን ለማሳመን አሁንም ፕሬዚዳንቱ ግልፍ እንዲለው ገፋፋው ። ነገር ግን ሂላ ቅርብና አንድ መጠነኛ ከተማ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስታወሰ ። “ በሂላ ውስጥ የጦር ሠፈር የለም ? ” ብሎ መኖሩን እያወቀ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠየቀው ።

የረጅም ጊዜ ዝምታ ሆነ “ ፕሬዚዳንቱ ከረዳቶቹ ጋር የሚነጋገር መሰለ ። በመጨረሻም “ ይህ መነገር የሌለበት መረጃ ነው ብየ እገምታለሁ ” አለው ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጣቶቹ ስልኩን አጥብቆ ሲይዝ የእጁ አጽቅ ወደ ነጭነት ተለወጠ ። “ ፕሬዚዳንት . . . ምን ሃሳብ አለህ ? ” ብሎ ሰዓቱን መልከት አደረገ ።

“ ነፋሱ እስኪያቆም ወይም ቢያንስ ቢያንስ እስኪነጋ ቆይ ። ”

“ እስከዚያ ጊዜ ላይኖር ይችላል ። ”

“ ጠቅላይ ሚኒስትር ፣ ሰዎችን ለማትረፍ ሌሎችን አደጋ ላይ መጣል ያለፈበት አባባል ነው ። በባቢሎን ውስጥ 50 ሰዎች ተከበዋል ብለህ ነገርከኝ ። አንተ አሁን ለእነእርሱ ሲባል የተከበቡትን ሰዎች ያህል ሕይወት አደጋ ላይ እንዲወድቅ እንዲደረግ ትፈልጋለህ ። ለማንኛውም በባቢሎን ውስጥ ምን እንዳለ - ካለም - የምናውቀው ነገር የለም ። ”

" ግን በዚያ አካባቢ አንድ ነገር በመካሄድ ላይ እንዳለ ታውቃለህ ፤ አታውቅም ? "

ፕሬዚዳንቱ ከአቅማማ በኋላ " አዎን ፤ በሂላ ከአለው መሥሪያ ቤታችን በባቢሎን ፍርስራሽ ክልል ውስጥ አንድ ነገር በመካሄድ ላይ እንዳለ አሁን ገና አረጋግጠናል " አለው ።

የኢራቁ ፕሬዚዳንት ይህን አዎንታ እንደተናገረ በክፍሉ ውስጥ የሰሙት ሰዎች ተቅበጠበጡ ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልኩን እንደያዘ ወደፊት ጐብደድ አለ ። ከአሁን በኋላ በጥንቃቄ እየገፋፋ እንዲናገር ማድረጉ ዋጋ እንደሌለው በማወቅ " ለእግዚአብሔር ብለህ ከሂላ ወታደሮች ላክ " አለው ቸኮል ብሎ ።

ከብዙ ጊዜ ቆይታ በኋላ ድምጹ ተመልሶ ሲመጣ ይቅርታ ያለው መሰለ ። " የሂላ የጦር ሠፈር 421ኛው የሻለቃ ጦር ነው - የኢንተ ወታደራዊ የጸጥታ ክፍል ያውቀዋል ። አብዛኛዎቹ ከፍልስጥኤማውያን የተውጣጡ ናቸው ። አንተን በመቃወም በ1967 እና በ1973 ተዋግተዋል ። መኰንኖቹ ኢራቃውያን ሲሆኑ ሌሎቹ ግን ስደተኞችና የስደተኞች ልጆች ናቸው ። እነ እርሱን በዚህ ዓይነት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ማዘዝ ታማኝነታቸውን መከፋፈልና እርስ በእርሳቸው ማጠላት ይሆናል ። የምናገረው ይገባሀል ። "

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገብቶታል ። ዙሪያውን ተመለከተ ፤ ጠል ፈው የሚሰሙት ሰዎች የተቆጡ መሰሉ ። በክፍሉ ውስጥ ከፍተኛ ስሜት እየተፈጠረ መጣ ። " ፕሬዚዳንት ፤ ስልኩን ይዤ ስለምጠብቅህ አሁን ወደ ሂላ ደውለህ ለሰዎችህ ወይም ለታማኝ መኰንኖችህ በባቢሎን ውስጥ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ጠይቃቸው ። "

" በነፋሱና በጐርፉ ምክንያት የስልኩ መስመር በትክክል አይሠራም ። በራዲዮ ከእነጋገርናቸው በኋላ ያለውን ሁኔታ እንዲገልጹልን እናደርጋለን ። "

" ገባኝ ። " ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመሬት ላይ ስለተዘረጉት የስልክ መስመሮች ችግር ፕሬዚዳንቱ የተናገረው ዋሽቶ ነው ብሎ የሚያምንበት ምክንያት አልነበረውም ። በተጨማሪ የሚነግረው አለው ። " ፕሬዚዳንት ፤ ወታደሮቼ እንደነገሩኝ በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ ወደ ባቢሎን ለመድረስ ምንም ችግር የለም ። ከሌላ የወታደር ሠፈር የተውጣጡ ሰዎች በአንድ ሰዓት ውስጥ ባቢሎን መድረስ ይችላሉ ። "

የፕሬዚዳንቱ ድምጽ ትዕግሥቱ ማለቁን ያሳይ ነበር ። " የኤፍራጥስ ወንዝ እንደ አንተ የዮርዳኖስ ወንዝ ትንሽ ነው ብለህ ታስ

ባለህ ? ይህ ትልቅና ኃይለኛ ወንዝ ነው ። በዓመቱ ውስጥ በዚህ ጊዜ እንደባዘነ በግ ሜዳውን በማጥለቅለቅ ይፏልላል ። ”

“ ፕሬዚዳንት ፣ በየወራቱ አገርህ የሚያጋጥመውን ትልቅ መከራና ችግር እናውቃለን። በዓመቱ ውስጥ ለማወቅ ከምንፈልጋቸው አንዱ - ሽብር ፈጣሪዎች ማለት አልፈለገም - የደፈጣ ተዋጊዎች የአንተን አገር የመረጡበት ምክንያት በእነዚህ ጥቂት ሳምንቶች ውስጥ ወደባቢሎን ለመግባት ያለውን ችግር በማወቅ ነው ። ይሁን እንጂ ፕሬዚዳንት ፣ በእጅህ ውስጥ ከአለህ ኃይል ልትረዳን እንደም ትችል አውቃለሁ ። ”

መልስ አልሰጠም ።

በዚህ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኩራት እንደተሰማው አወቀ ። የቀረው ስድብ አከል ነገር በመናገር ፕሬዚዳንቱን እንዲቆጣ በማድረግ እርምጃ እንዲወስድ መገፋፋት ነበር ።

“ ፕሬዚዳንት ፣ በሻሚያ ምድረ በዳ በፍልስጥኤም የጦር ሠፈር እንዳለ ታውቃለህ ? ምናልባትም እነዚህ ወደ ባቢሎን የመጡት ከዚያ ሊሆን ይችላል ። ”

አሁንም መልስ አልሰጠም ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አካባቢውን ቃኘ ። የኢራቅን ፕሬዚዳንት አቋም ለአለፉት ዓመታት ሲያጠና የነበረ አንድ ኰሎኔል “ ይህን ያህል ከአባበልከው በኋላ ነገሩን ቁረጥ ። ”

“ከአሁን በኋላ በተራቀቀ መንገድ መነጋገሩ ፋይዳ አይኖረውም” የሚል ጽሑፍ በጠረጴዛው ላይ አስቀመጠለት ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንብቦ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። አያይዞም “ ወታደሮችህ በዚህ ሰዓት መዝመት ይችላሉ ፣ ፕሬዚዳንት ? ” ብሎ ጠየቀው ።

አሁንም መልስ አልነበረም ። በመጨረሻም የፕሬዚዳንቱ ድምጽ መጣ ። ግን በጣም የቀዘቀዘ መሰለ ። “ አዎን ፣ ወንዙን አቋርጠው እንዲሄዱ ትዕዛዝ እሰጣለሁ ። ነገር ግን እስኪነጋ ድረስ አይነቃነቁም ። ላደርግ የምችለው ይህን ብቻ ነው ። ”

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያገኘውን ትንሽ ተስፋ ላለማበላሸት “ ጥሩ ነው ” አለው ።

“ የምትፈልገው እዚያ ምን እንድናደርግ ነው ? ”

“ ምንም ሃሳብ የለኝም ። ”

“ እኛም እንደ አንተው ነን ። ለአንተ ሲባል በዚያ አንድ ነገር እንደሚኖር ተስፋ አደርጋለሁ ። ግን ምንም ነገር ከሌለ ስለአንተ እፍራለሁ ። ”

“ አውቃለሁ ” ብሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግሩን ቆም አደ ረገ ። ከባድ ጥያቄ የማቅረቢያው ጊዜ አሁን ነበር ። “ እንድንረዳህ ትፈቅድልናለህ ? ፍለጋውን በጥምር ማካሄድ እንችላለን ። ”

ፕሬዚዳንቱ በጥድፊያ “ ይህ ፈጽሞ የማይቻል ጥያቄ ነው ” አለው ።

በዚህ ላይ መነጋገሩ ፍሬ ስለማይኖረው “ እሺ ፡ መልካም ዕድል ይሁንልህ ” አለው ።

የኢራቁ ፕሬዚዳንት ለትንሽ ጊዜ ጸጥ ከአለ በኋላ “ ባቢሎን ፡ ምርኮኛ ፡ የሚገርም ነው ” ብሎ ተናገረ ።

“ አዎን ፡ በእርግጥ ይገርማል ።” በመካከለኛው ምሥራቅ የፖ ለቲካና የዲፕሎማቲክ ጥረት ለማድረግ ሲታሰብ ከአምስት ሺህ ዓመት በላይ የነበረውን ታሪክና የደም መፋሰስ ሳያወሱ ለማለፍ ያስቸግራል ። ለምሳሌ ያህል አሜሪካኖች ፈጽሞ የማይገባቸው የዚህ ዓይነቱ ነገር ነበር ። ከሶስት ሺህ ዓመት በፊት የተፈጸሙ ጉዳዮች ከአንድ ሳምንት በፊት እንደተደረጉ ተቆጥሮ ለዓለም አቀፍ ስብሰባ ይቀርባሉ ። ይህም ሁሉ ሆኖ ለአንደኛቸው እንኳን ተስፋ አለ ? “ ነገር ግን በጣም አስገ ራሚ አይደለም ። ”

“ ምናልባትም አይደለም ” ብሎ የኢራቁ ፕሬዚዳንት ንግግሩን ቆም ከአደረገ በኋላ “ የሃዘንህ ተካፋይ እንዳልሆንን አድርገህ ማሰብ የለብህም ። ሽብር ፈጣሪዎቹም ለእኛ የሚሰጡን ጥቅም የለም ። ሃላ ፊነት የሚሰማው የአረብ መንግሥት የሠሩትን አይደግፍም ።” አሁ ንም ንግግሩን ቆም ሲያደርግ እስራኤሎቹ አረብኛና እብራይስጥ የተ ቀላቀለበት ድምጽ ስለሰሙ በስሜት ተዋጡ ። ወደዚያው ፕሬዚዳንቱ ጉሮሮውን አፍታቶ “ መሄድ አለብኝ ” አለው ።

“ ፕሬዚዳንት ከመንጋቱ በፊት አነጋግርሃለሁ ። ”

“ እሺ ። ”

ስልኩ ተዘጋ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀጥ ብሎ ተመለከተ ። “ አሁን መሄድ ይገባናል ወይስ እንቆይ ? ” ብሎ በግድግዳው ላይ ያለውን ሰዓት ተመለከተ።“በባቢሎን ላይ ፀሐይ ለመውጣት ከስድስት ሰዓት በላይ ጊዜ አለ ። ወይስ የኢራቅን መልስ እንጠብቅ ? ” ሲጋራ ለማቀ

ጣጠል የጫረው ከብሪት ጾጥ ባለው ክፍል ውስጥ ቱሽ የሚል ድምጽ አሰማ ፡፡ “ ይህ የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትርና የኢራቅ ፕሬዚዳንት … ለመጀመሪያ ጊዜ ንግግር ማድረጋቸው መሆኑን ታውቃላችሁ፡፡ከዚህ የሚገኘውን ውጤት ማጨናገፍ እንፈልጋለን ? እነዚህ ኮንኮርዶች የተነሱበትን የሰላም አየር አደጋ ላይ መጣል አለብን ? ” ብሎ በክፍሉ ውስጥ ያሉትን ሰዎች እየተመለከተ ፊታቸውን ለማንበብ ሞከረ። የብዙዎቹ ሰዎች ፊቶች ለኢንቴቤ በተደረገው ስብሰባ ላይ የነበረው ዓይነት ነበር። ይህ ግን ከኢንቴቤ ሁኔታ የበለጠ ውሉ የጠፋበት ጉዳይ ሆነ ፡፡ በተጨማሪም የኢንቴቤው የወታደር እርምጃ ለመውሰድ ስምምነት ላይ ከመድረሱ በፊት ብዙ ቀኖች ፈጅቷል ፡፡

እያንዳንዱ ጄኔራልና የፖለቲካ ሰው ከሁለት ደቂቃ በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ የሚሰማውን አስተያየት እንዲሰጥ ተፈቀደለት ፡፡ ስብሰባው እሁለት የተከፈለ መሰለ — መከፋፈሉ ግን ወታደርና ሲቪል በመባባል አልነበረም ፡፡ ከወታደሮቹ ግማሾቹ ስለሚወሰደው ወታደራዊ እርምጃ ከፍተኛ ጥንቃቄና ቁጥጥር እንዲደረግ ሲሉ ከሲቪሎቹ ግማሾቹ ደግሞ የወታደራዊ እርምጃ እንዲወስድ ደገፉ ፡፡

ጥቂቶቹ እስራኤሎቹን አህመድ ሬሽ በቁጥጥር ስር አውሎ አቹዋል ብለው ያመኑ ደግሞ የሚፈልገውን ጥያቄ በቶሎ ያቀርባል የሚል ስሜት ·አድሮባቸዋል ፡፡ እነዚህኞቹ ለማስለቀቅ ስለሚቀርበው ጥያቄ ለመስማማት የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ ፈለጉ ፡፡

ከሚኒስትሮቹ አንዱ ጆና ጋሊሊ ተነስቶ በኢንቴቤ ስብሰባ ጊዜ በእስራኤል ውስጥ ሁለት የቄስ አለቆች የታገቱ ሰዎች ለማስለቀቅ ከሽብር ፈጣሪዎች ጋር ስለሚደረገው ድርድር በይሁዳ ሃይማኖት ሥርዓት ላይ ስለሚያስከትለውና ስለሚያመጣው ትርጉም የተናገሩትን አስታውሳቸው ፡፡

የፍርድ ሚኒስትሩ ናታን ዳን ራሱ ቄስና የሕግ ባለሙያ የሆነ ዘሎ በመነሳት “ በዚህ ትርጉም ላይ እለያለሁ ” አላቸው ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተከመረው ወረቀት እስኪበታተን ድረስ ጠረጴዛውን በኃይል ጠልዞ “ ይበቃል ፤ ይህ የሃይማኖት ትምህርት ቤት ወይም በቴል አቪቭ ውስጥ ያለ ቡና ቤት አይደለም ፡፡ የቀድሞ የሃይማኖት ሥርዓት ወይም ጥንታዊ እብራይስጥ ወይም ሴማዊ ላይ ዝንባሌ የለኝም ፡፡ እኔን የሚያሳስበኝና የሚያጓጓኝ እዚህ አሁን ያለው ጉዳይ ነው ፡፡ ላስኮቭ የአንተ ተራ ስለሆነ ሁለት ደቂቃ ብቻ ” አለው።

ቴዲ ላስኮቭ ስለቀድሞ ወታደራዊ ግንዛቤዎች ቢናገር ተቀባይነት እንደማይኖረው አወቀ ፡፡ የአየር ወለድ ሰዎች በባቢሎን ላይ

አርፈው በሰዎች ፊንታ የምድረበዳ አውሬዎች ብቻ ቢያገኙ ስለሚ ከተለው ጣጣ በመፍራት ውሳኔው እንዲጓተት ሆነ ። የዚህ ዓይነት ውድቀት በሸንጐ በተቋቋመ መንግሥት ዘንድ ከደረሰ ከምክር ቤቱ አባላት ግማሽ ያህሉ ከመሰናበታቸውም በላይ ለመንግሥት ከፍተኛ አደጋ ይሆናል ። ግን መንግሥት እርምጃ ወስዶ ኮንኮርዱን ከሰላም ተደራዳሪዎቹ አባሎች ጋር - እግዚአብሔር አያድርገውና ሁሉም ሞተው ቢገኙ - በዓለም ዘንድ የሚመጣውን ተቃውሞ በሰ ብአዊ ርህራሄ ላይ በመመርኮዝ የተደረገ መሆኑን በማስረዳት መከ ራከር ይቻላል ። ነገር ግን ላስኮቨ ስህተተኛ ቢሆን - ፎቶ ተንታኙ ትክክለኛ ባይሆን - በዚያ ምንም ባይገኝ . . .

ላስኮቨ ባወጣ ያውጣው የሚለውን ውሳኔ በመውሰድ “ ችግሩ ምን እንደሆን ገብቶኛል ። ያሁን ግድየለም ። በማያጠራጥር ሁኔታ ሰዎቻችን በባቢሎን ውስጥ መኖራቸውን ለማረጋገጥ ብችል ከእ ናንተ ውስጥ ወደዚያ ሄደን እናውጣቸው የሚለውን ሃሳብ አንድ እን ኳን የሚቃወም ይኖራል ? ” ብሎ ጠየቃቸው ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ብድግ ብሎ “ ያ ፍሬ ነገሩ ነው፤ጄኔራል።አንተ በማያጠራጥር ሁኔታ በዚያ መኖራቸውን ከአረጋገጥህ ለመሄድ ድምፅ እሰጣለሁ ” አለው ። ይህ ለእያንዳንዳቸው መንገድ ከፈተላቸው ። ወደፊት ሁኔታዎች ተለውጠው ጥያቄ ቢያመጣባቸው የሰላም ተደ ራዳሪዎች በባቢሎን ውስጥ መኖራቸውን ፈጽመው የማያውቁ መሆ ናቸውን ለመግለጽ ዝግጁ ነበሩ ። ይህ እንደ ምክንያት ብቻ ሳይሆን እውነተኛ አስተሳሰባቸው ነበር ።

“ ታዲያ ጄኔራል ይህን የማያጠራጥር መረጃ የምታገኝልን መቼ ነው ? ” ብሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከጠየቀው በኋላ “ ሁላችንም እንደሰማነው ከአልተፈቀደልን በስተቀር ሌላ የመንፈስ መልዕክት አንቀበልም ” አለው ።

ላስኮቨ አልፎ አልፎ ይሰማ የነበረውን ሳቅ ችላ በማለት “ በአ ንተ ስም እንድሠራ ሙሉ ሥልጣን ይሰጠኛል ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ ይህ ከባድ ጥያቄ ነው ። ”

“ ጐህ እስኪቀድ ድረስ ። ”

“ መልካም በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ጥፋት ልታመጣ አት ችልም ብየ እገምታለሁ ። ስለዚህ እሺ ይሁን፤እስከዚያው የአየር ወለድ ወታደሮች ለመንቀሳቀስ በተጠንቀቅ ላይ መሆን አለባቸው ። ከንጋቱ 11:30 ሰዓት በፊት ተመልሰህ መጥተህ ቢያንስ ኮንኮርዱ በባቢ ሎን ውስጥ መኖሩን የማያጠራጥር ማስረጃ ይዘህ ከመጣህ ትዕዛዝ

ወደዚያው በመስጠት መልካም ውጤት እንዲገኝ በተስፋ ሁኔታውን እንጠባበቃለን ። ሆኖም ከዚህ በፊት ከኢራቅ መንግሥት በተደረገው ስለላ አውሮፕላኑ በዚያ ለመኖሩ ምንም መረጃ የለም የሚል መልስ ከአገኘን የፈለከውን ማስረጃ ብታመጣ አልቀበልህም ። ለማንኛውም ከንጋት በኋላ የኢራቁ መንግሥት ወደባቢሎን አንድ ኃይል ለመላክ ቃል የገባውን እንደሚጠብቅ እተማመናለሁ ። የእኛ ወታደሮች ከእነእርሱ ጋር ግጭት እንዲፈጥሩ አልፈልግም ። ስለዚህ ጉህ ሲቀድ 11:30 ሰዓት ኃይላችንን የምንልክበት ወሳኝ ጊዜ ያሆናል ። ይህ ለሁላችንም ጥሩ ይሆናል ብየ እገምታለሁ ። ”

“ ወደዚያ የሚሄደውን ቡድን ለመምራት እፈልጋለሁ ። ”

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተቀምጦ ራሱን በአሉታ ከነቀነቀ በኋላ “አንተ በአሁኑ ጊዜ በጦር ሠራዊት ውስጥ እንኳን አትሠራም ። ታዲያ ሙሉ ሥልጣኔን የምሰጥህ ለምንድን ነው ? ይህን ለማድረግ እብድ ነኝ ማለት ነው ” አለው ።

“ እባክህ ጠቅላይ ሚኒስትር ። ”

ክፍሉ በጸጥታ ተሞላ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለብዙ ጊዜ በሃሳብ የተዋጠ መሰለ ። ቀጥሎም ከመቀመጫው ተነስቶ ወደ ላስኮቭ በመመልከት “ እንድትሄድ ከአሳመንከኝና የሚሄደውን ቡድን ከመራህ ሃሳቡን በጣም እወደዋለሁ ። ሌላ የምልከው አለ ብየ ለማሰብ አልችልም ” የሚል ግልጽ ያልሆነ መልስ ሰጠው ።

ላስኮቭ እጅ ነስቶ በመዞር ቀስ ብሎ በአዳራሹ ውስጥ ሲራመድ ታልማን ተከተለው ። በሰው በተሞላው አዳራሽ ውስጥ ሲሄዱ በዝቅተኛ ድምጽ ታልማን “ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ምን ዓይነት መረጃ ልታመጣ ትችላለህ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ላስኮቭ ትከሻውን ከፍና ዝቅ አድርጎ “ አላውቅም ” አለው ። ከግቢው ወጥተው ወደ መንገዱ ደረሱ ። ሁለቱም በዝምታ ሄዱ ። ኢየሩሳሌም ከሙቀቱና ከደረቅ ነፋሱ በስተቀር ጸጥ ያለ ነበር ። ጨለማውና ሙቀቱም እያለ አየሩ ከሚያመጣው የአበቦች መአዛ ጋር ጥሩ ነበር ። ሰማዩም በጣም የጠራ ነበር ። ጨረቃዋ በመሃል ሰማይ ላይ ቅልጥጥ ብላ ቢጫ ብርሃን ሰጥታለች ። አበቦች ፣ የወይን ሐረጎችና ዛፎች እንደ ገጠር ከተማ በየረባዳው ቦታ በቅለዋል ። የመንገዱ ንጣፍ የጥንት ድንጋይ ነበር ። ቤቶቹ ከሃያ እስከ ሁለት ሺህ ዓመት ዕድሜ አላቸው ። በኢየሩሳሌም ውስጥ ምንም ነገር የተፈጠረ አይመስልም ነበር ።

" እንደዚያ ያልከው ለምንድን ነው ? ለመሄድ ድምጽ የሚሰጡበት ዕድል ነበር ። አሁን ግን መንገድ ከፈትክላቸው " አለው ታልማን ።

" እንድንሄድ ለመፍቀድ በፍጹም ድምጽ አይሰጡም ነበር ። "

በደካማው ብርሃን ላስኮቭን እየተመለከተ " በመጨረሻ በሰጠኸው ላይ ጥርጣሬ አለህ እንዴ ? " ብሎ ጠየቀው ።

ላስኮቭ በድንገት ቆሞ " ፍጹም የምጠራጠረው ነገር የለኝም ። በባቢሎን ውስጥ ናቸው ፣ ኢ.ዝሐቅ ። አውቃለሁ " ብሎ ከአቅማማ በኋላ " እሰማቸዋለሁ " አለው ።

" እርባን የሌለው ነው ። እናንተ ሩሲያውያኖች ከአምልኮት አትጠሩም ። "

ላስኮቭ በአዎንታ ራሱን ነቅንቆ " ትክክል ነህ " አለው ። "

" የማያጠራጥር ማስረጃ አመጣለሁ ስትል በአዕምሮህ ውስጥ ምን እንዳለ ማወቅ እፈልጋለሁ " ብሎ ታልማን ድርቅ አለበት ።

ላስኮቭ እንደገና መሄዱን ቀጥሎ " አንተ በከፍተኛ እርቀት በምርመራ ላይ ወይም በስለላ ላይ ላለ አውሮፕላን መልዕክት ለማስተላለፍ ብትፈልግ ያለ ራዲዮ እንዴት ማስተላለፍ ትችላለህ ? " ብሎ ጠየቀው ።

ታልማን ለትንሽ ጊዜ ከአሰበ በኋላ " የፎቶግራፍ መልዕክት ማለትህ ነው ? ከሆነ በመሬት ላይ ትልቅ ምልክት እሠራለሁ - ወይም ይህ የማይቻል ከሆነ ወይም አውሮፕላኑ ከፍተኛ እርቀት ላይ ከሆነና ጨለማም ከሆነ ወይም የአሸዋ ውሽንፍር ከአለ እሳት የሚነድበት ቦታ አዘጋጃለሁ ። ግን እሳት የነበረባቸውን አይተናል ። ይሁን እንጂ የመጨረሻ የማያጠራጥሩ አይደሉም ማለት አንችልም " አለው ።

" ከእነእርሱ አንዱ የዳዊት ኮከብን ቅርጽ ያለው ከሆነ የማያጠራጥሩ ይሆናሉ ። "

" ግን የዚያ ዓይነት ቅርጽ የሚመስል አልነበረም ። "

" ነበር ። "

" አልነበረም ። "

ላስኮቭ በሚራመድበት ጊዜ ከራሱ ጋር የሚያወራ መሰለ።" ያ ሁሉ አንጐል እያለ አንድ ሰው እንኳን ስለዚያ አለማሰቡ አስደንቆኛል ።

ግን ነገሩ በከፍተኛ እርቀት ላይ በሚበር አውሮፕላን አማካይነት አጉ ልቶ በሚያሳይ መሣሪያ የሚከናወን ነው ማለቴ ነው ። ምናልባትም አውሮፕላን ሲያዩ እሳት በማቀጣጠል ኮከቡ እንዲያብረቀርቅ ለማ ድረግ ይሞክሩ ይሆናል ። ምናልባትም ለዚህ የተረፈ ነጭ ጋዝ አይኖ ራቸውም ይሆናል ። በባቢሎን ላይ የስለላ ተግባር ይካሄዳል ብለው እንዴት ይጠራጠራሉ ? ”

ታልማን አቋርጦት “ ቴዲ ነጥቡ የዳዊት ኮከብ እንዲብረቀ ረቅ አላደረጉም ወይም እዚህ ነን ዘመዶች የሚል መልዕክት ወይም ያንን የሚመስል አላስተላለፉም ። ምናልባትም ቀደም ብሎ ጊዜ አል ነበራቸውም ይሆናል ። . . . ለማንኛውም የዚያ ዓይነት ምልክት ወይም መግለጫ አልነበረም ” አለው ።

“ ቢኖር ኖሮ . . . ? ”

“ እኔም ሆንኩ ሌሎቹ እናምን ነበር ። ”

“ እንግዲያውስ የአየር ኃይሉ የመረጃ ክፍል ይጠቁማሉ ” ብሎ ባለማሰብ “ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያላመጣቸውን ፎቶግራፎች ማየት አለ ብን ። እርግጠኛ ነኝ ፤ የዳዊት ኮከብ ቅርጽ ያለበት ማየት እንችላለን ። ”

ታልማን በድንገት ቆሞ ዝቅ ባለ ድምጽ “ አብደሃል እንዴ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ በጭራሽ ። ”

“የምትለው ከፎቶግራፎቹ አንዱን ለመለወጥ እሞክራለሁ ነው?”

“ በባቢሎን ውስጥ ናቸው - ወይም ነበሩ - ብለህ ታምናለህ ?”

ታልማን አመነ ፣ ግን ለምን እንደሆነ ሊያውቀው አልቻለም።

“ አዎን ። ”

“ ጅምራችን ለመጨረሻው ግብ ያበቃናል ? ”

“ ሚስትህ ወይም ሴት ልጅህ በዚያ ቢኖሩ የተለየ ታስባለህ ?”

ታልማን ስለላስኮቭና ሚሪያም በርንስቴይን ያውቃል “አላስብም ።”

ላስኮቭ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ፣ ታልማን እየዋሸ አልነበረም ። ከእንግሊዞች ጋር ለብዙ ዓመታት ኖሮአል ። ውሳኔ በሚያደርግበት ጊዜ ስሜታዊነት አያጠቃውም ። ብዙውን ጊዜ ጥሩ ባሕርዩ ያ ነበር ። አልፎ አልፎ ይሁዳዊነት ባሕርይ አለው ብሎ ላስኮቭ አሰበ ። “ ሔደህ ለት ንሽ ጊዜ ተኛ ያልኩህን በመርሳት ይቅርታ ለማድረግ ቃል ግባልኝ ። ”

" አይቻልም ። እንዲያውም አንተን በቁጥጥር ስር ማዋል አለ ብኝ የሚል ስሜት አድሮብኛል ። "

ላስኮቭ ትልቅ እጁን በታልማን ትከሻ ላይ አድርጐ " በባቢሎን ውስጥ እየሞቱ ናቸው፤ ኢዝሐቅ ። እባክህ ልርዳቸው፤ ማድረግ የሚገ ባኝን ላድርግ ። የነገርኩህን እርሳው ። አዛዡ በነበርክበት ወቅት ከአ ንድ ጊዜም ሁለትዬ አክብረኸኛል ። ግራ አትጋባ ። ወደቤትህ ሒደህ እስከ ግማሽ ቀን ድረስ ተኛ።በምትነቃበት ጊዜ ሁሉም ነገር ተፈጽሞ ታገኘዋለህ ። ብሔራዊ የደስታ ወይም የሃዘን በዓል ይሆናል ። ምና ልባትም ጦርነት ይነሳ ይሆናል ። ሌላ ምን ምርጫ አለን ? ይህን ነገር ከፈጸምኩ በኋላ የፈለገው ቢደርስብኝ ደንታ አይኖረኝም ። አሁን ልሂድ " ብሎ የታልማንን ክንድ ወደ እርሱ ጐን ሳበው ።

ሁኔታው ታልማንን ወረረው ። በጣምም ተሰማው " እንደማስ በው ወደ ቤቴ እሄዳለሁ . . . አይሆንም . . . አልለይህም . . . አብ ሬህ እሄዳለሁ ። እብደት እንደሆነ ታውቃለህ . . . በእውነት እብደት . . . ይሁን እንጂ እረዳሃለሁ ። አዎን እረዳሃለሁ ። "

ላስኮቭ ፈገግ አለ ። ታልማንም በነገሩ ተነካ ። " ጥሩ " ብሎ ታልማንን ለቆ ወደኋላ ተራመደ። " ስማ በቴል አቪቭ ውስጥ አንድ የአየር ኃይል ባልደረባ የሆነ የፎቶ ባለሙያ አውቃለሁ ። በመንገዳ ችን ላይ ይዘነው ወደ ምሽጋችን እንሄዳለን ። የምናዘውን ሁሉ ያለ ተቃውሞ የሚሠራ ሰው ነው ። "

ታልማን ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ ሁለቱም እየሮጡ ታክሲ ወደሚገኝበት ቦታ ሄደው ዘለው በታክሲው ውስጥ በመግባት " ለአ ስቸኳይ ሥራ ቴል አቪቭ " አለው ላስኮቭ ።

## —29—

ቤንጃሚን ዶብኪን የሺር ጃሹብን እጅ ይዞ ከኤፍራጥስ ወንዝ ወጣ ባለ የአፈር ቁልል ላይ ሁለቱም አብረው ቆሙ። በጥቂት አሥራ ሁለቶች የሚቆጠሩ ሰዎች የሚኖሩበት መንደር ከታች ወለል ብሎ ይታያል ። በሌላው በኩል ያለው ዳርቻ በነፋሱ በመጣው አቧራ መሸ ፈኑን በጨረቃው ብርሃን አየው ። እነእርሱ በአሉበት ዳርቻ በነፋሱ ኃይል የመጣው አቧራ ወደውሃው ይገባ ነበር።የድፍርሱ ውሃ ማዕበል ከፍ ከአለው ቦታ ጋር ሲጋጭ አዩ። ወንዙን አቋርጦም ሆነ በየብሱ ላይ ለመጓዝ ቀላል አልነበረም ። ዶብኪን ወደ ሽማግሌው ተመልክቶ " በጭቃው ሜዳ ላይ አውጥተህ ለተኩላዎቹ ጣልላቸው ። ሲነጋ ዝም ብለህ ወደ ሥራህ ሂድ " አለው ።

ሽማግሌው በትህትና ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። እንዴት ማድ ረግ እንደሚገባው ከማንም ቢሆን መመሪያ መቀበል አይፈልግም ። የሽማግሌው መንደር ለአለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት ከአውሮፓ እል ቂት ቀጥሎ ሊመዘን የሚችል የመከራ ጊዜ አሳልፏል ። " እግዚ አብሔር በመንገድህ ላይ ይከተልህ ፥ ቤንጃሚን " አለው ሽማግሌው።

ዶብኪን ከገደለው አሸባል ላይ የገፈፈውን እንደ ነብር ቆዳ ዝጉርጉር የሆነ ሱሪና በራስ ላይ የሚጠመጠም ጉፍታ ለብሷል ። የሞ ተው ሰው በቅርብ ቅርጭምጭም ተደርጐ በቀበሮዎች ከርስ ውስጥ ይገባል ። ሪሽ የታሊብን ደም ለመበቀል ወደ መንደሩ በመምጣት በሁለት ሺህ ዓመታት ውስጥ ቢዳከምም ያልጠፋውን ሙልጭልጭ አድርጐ ከገጸ መሬት ላይ እንዳያጠፋቸው ዶብኪን ያደረበት ሥጋት የራስምታት ሆነበት ። አቅበጠበጠውም ። " ሰዎችህ መምጣት ይፈልጋሉ ። ወደ ቤታቸው ወደ እሥራኤል - እንድትሄዱ ዝግጅት ቢደረግ ? " ብሎ ዶብኪን ጠየቀው ።

ሺር ጃሹብ ወደ ዶብኪን ተመልክቶ " ኢየሩሳሌም ? " አለው።

" አዎን ፤ ኢየሩሳሌም ፥ በእስራኤል ውስጥ በየትኛውም ቦታ ፥ ከፈለግህም ወደ ሂርዝላ የባሕር ወደብ ። " በሽማግሌው አዕምሮ ውስጥ የሚላወሰውን ሃሳብ በመጠኑም ቢሆን ሊገባው ችሏል ። እስ ራኤል ለእርሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚያውቀው ከይሁዳና ከጽ ዮን ጋር የተዛመደ ቃል ነው ። ለእርሱ እንደ ባቢሎን ጥሩ ቦታ ሆኖ ትርጉም አልሰጠውም ።

" ጥሩ አገር ነው ። መሬቱ ጥሩ ነው " አለው ዶብኪን ። እንዴት አድርጐ ሁለት ሺህ ዓመታት የኖረበትን አገር ይተዋል ? ልዩነት የሚ ያመጣው ቋንቋው ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰብና በኑሮም የሰማይንና የመሬትን እርቀት ያህል ተለያይተዋል ። " እዚህ በአደጋ ላይ ልት ወድቅ ትችላለህ ። "

" በዚህ ሁልጊዜም በአደጋ ላይ ነን ። "

ለመሆኑ ዶብኪን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለስ ቃል የሚገባለት ምን መብት ኖሮት ነው ? ጥያቄውን ቢቀበልስ እንዴት ይወስደዋል ?

ዶብኪን ውይይቱን በመቀጠል " በባቢሎን ውስጥ በጣም ብዙ ጊዜ ቆይታችኋል ። አሁን ግን ወደ ቤታችሁ የመመለሻው ጊዜ ነው" አለው ። ሁኔታቸው እንደ ልጆች ስለነበረ ወደ እስራኤል ሄደው መኖሩ ምን ያህል እንደሚያስደስታቸው አላወቀም ። በሌላ በኩል ደግሞ በእንደዚያ ዓይነት ገባር ሆነው የሚያሳልፉትን ኑሮ ማየት

አልፈለገም ። በዚህም ምክንያት አጥብቆ ነገራቸው ። በሚጓዝበት ሁሉ አይሁዶችን ሲያገኝ “ እናንተ ደንቆሮዎች ! ወደ ቤታችሁ ኑ ። ወደቤታችሁ መጥታችሁ ራሳችሁን ቀና አድርጋችሁ ኑሩ ። አሁን ለእ ናንተ ቦታ አለ ። ለእናንተ በደማችን ገዝተነዋል ይላቸው ነበር ። ” የሽማግሌውን እጅ አጥብቆ በመያዝ “ ወደ ቤትህ ና ” አለው ።

ሺር ጃሹብ ነጻ እጁን በዶብኪን ትከሻ ላይ አድርጐ “ ጀኔ ራል ፣ የመጣኸው ከምርኮኝነት ልታወጣን ነው ? ወይስ ሳታውቀው ለመጥፊያችን መሳሪያ ልትሆን ነው ? ቆይ ፣ በፊት ልጨርስ ፣ በመ ጽሐፉ ውስጥ ከዚያም በኋላ የይሁዳና የቤንጃሚን ነገዶች ፣ የቤተሰብ አለቆች ፣ ካህናትና ሌዋውያን እንዲሁም እግዚአብሔር ልቡን ያነሳ ሳው ሌላውም ሰው ሁሉ ፣ ተመልሶ ለመሄድና በኢየሩሳሌም የሚገ ኘውን የእግዚአብሔርን መቅደስ እንደገና ለመሥራት ተዘጋጀ ። እግ ዚአብሔር ግን የእኔን ቅድመ አያቶች ስለአላነሳሳቸው እዚህ እንዲቆዩ ሆነዋል ። ግን ቤንጃሚን አንድ ነገር ልንገርህ ። እነዚህ ከስደት የተ መለሱት ለሁለተኛ ጊዜ የሠሩት የእግዚአብሔር መቅደስ ስለፈረሰ ሕዝቡ በዓለም ላይ ተበትኖ በሚዞርበት ጊዜ የማያቋርጥ የትምህርት ችቦ ነበልባል ይዘው የቆዩት በባቢሎን ውስጥ የቀሩት አይሁዶች ነበሩ ። በዚያ ዘመን የአይሁዶች የትምህርትና የባሕል መናኸሪያ የነ በረው የመጀመሪያው ከተማ ባቢሎን እንጂ ኢየሩሳሌም አልነበረም ።

ኢየሩሳሌም ምናልባት እንደገና ብትጠፋ ሕጉ ሳያቋርጥ እንዲ ቀጥል እርግጠኛ ለመሆን ምንጊዜም ቢሆን እስራል ስደተኞቿን ትፈልጋቸዋለች ” ብሎት ፈገግ ከአለ በኋላ ያበራ የነበረው ፊቱ ሲጨ ማደድ በጨረቃው ብርሃን ታየው ። “ የእግዚአብሔር መንፈስ ሦስተኛውን መቅደስ እንድታንጽ አንድ ቀን ያንሳሳሃል ብየ ተስፋ አደርጋለሁ - ኢየሩሳሌም እንደገና ብትፈርስ አራተኛውን መቅደስ ተመልሰው የሚያንጹ በየአገሩ ተበታትነው እኛም ጭምር የሚኖሩ አይሁዶች እንዳሉ ማስታወስ ይገባሃል ” ብሎ የዶብኪንን ትከሻና እጅ ጨበጥ ከአደረገ በኋላ ቀስ አድርጐ ገፋ በማድረግ “ ሂድ ቤን ጃሚን ፣ ሂድና ሥራህን ፈጽም ፣ ጉዳይህ ከአለቀ በኋላ ምናልባት ስለኢየሩሳሌም እንደገና እንነጋገር ይሆናል ” አለው ።

ዶብኪን ዞሮ ወደ ውሃው ዳርቻ ሄደ ። ከትከሻው በከፊል ዘወር ብሎ በጨረቃው ብርሃን ውስጥ ለቆመው ሽማግሌ እጁን አወዛወ ዘለት። ትክክለኛ ያልሆነ ስሜት ወረረው ፤ ይህም የመጀመሪያ ጊዜው አልነበረም ። የቦታው ትርዕይቶች ፣ ድምጾችና በተለይም ሽታዎች እንደ ሃያኛው መቶ ዓመት ሰው በትክክል እንዳያስብ ችግር ፈጠሩበት።

ዶብኪን አቆልቁሎ ወደ ወንዙ ሲመለከት ከትልቅ ቅርጫት የማይበልጥ ለሰው ማጓጓዣ የሚሆን ክብ ነገር በውሃው ላይ ተንሳፎ አየ ። ይህ የመጓጓዣ መሣሪያ በተቀባው ብልጭልጭ ነገር አዲስ ቢመስልም ምናልባት ዕድሜው ጥቂት ቀኖች ወይም አንድ ሺህ ዓመታት ሊሆነው ይችላል ። ዶብኪን ገብቶ ሲቀመጥበት አብዛኛው ወደ ውሃው ውስጥ ሰመጠ ። ቺስሎን የተባለ አንድ ወጣት የመጓጓዣው የዚያን ያህል መስመጥ ምንም ያላሰጋው ዘሎ ሲገባበት ጨርሶ ሊሰምጥ ትንሽ ቀረው ።

ቺስሎን የሚቀዝፍበትን ሽመል አንስቶ መጓጓዣው የታሰረበትን ገመድ በመፍታት ወደ ፊት ገፋው ። የኤፍራጥስ ወንዝ እንደ አሁኑ በሞላበት ጊዜ የዚያ ዓይነት መጓጓዣ በሥራ ላይ ይውል እንዳልነበረ ዶብኪን ያደረገው ግምት ትክክል ነበር ። ይህም ልክ መሆኑን ያረጋገጠው ሰውየው ወደፊት እየተንጠራራ ሽመሉን ወደ ውሃው ውስጥ ቢሰድም መሬቱን መንካት ባለመቻሉ ቺስሎን ፍርሃት ስለአደረበት ዶብኪንን ቀና እያለ በማየት ደጋግሞ ፈገግታ ያሳየው ነበር ። ነፋሱ ኃይለኛ በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ መጓጓዣውን እያሽከረከረ ያዞረው ስለነበረ ዶብኪን ስለአጥወለወለው የጠጣውን የሎሚ ጭማቂና የበላውን አሳ አስታወከው ። ከዚያም ቀለል ስለአለው ጐንበስ ብሎ ፊቱን ታጠበ ። ቺስሎን እንደ እርሱ ታውኮ እንደነበረ ዶብኪን ተመልክቷል ።

ዶብኪን እርቀት ባለው ዳርቻ ላይ ጥቂት መብራቶች ስለአየ በእጁ ወደዚያ አመለከተ ። ቺስሎን "ክዌሪሽ ነው" አለው ።

በሚያልፉበት ጊዜ ዶብኪን በግራና በቀኝ የነበሩትን የወንዙን ዳርቻዎች ቃኘ ፡ በምሥራቅ በኩል ከፍተኛ የአሸዋ ክምችት መሬቱን ሸፍኖታል ። እንደዚሁም የጨረቃውን ብርሃን የአሸዋው ውሽንፍር ከልሎታል ።

ከክዌሪሽ በታች ወንዙ ቁልቁለትነት ስለነበረው የመጓጓዣው ፍጥነት ጨመረ ። ቺስሎን አሁንም በመወስወሻው እንጨት መሬቱን ለመንካት ቢሞክርም አልሆነለትም ። በፊት ለፊታቸው ወንዙ ወደ ምዕራብ ይታጠፋል ። እዚያ እስኪደርሱ የሚጓጓዙበት ከአልሰመጠ የከተማውን ደቡባዊ ክፍል ወደሚያሳየው የወንዝ ዳርቻ ይደርሳሉ። ከዚያ በኋላ ዶብኪን እስከ ኢሽታር በርና እንግዳ መቀበያው ቤት ድረስ ሁለት ኪሎ ሜትር ያህል መጓዝ አለበት ። ምናልባት እዚያ በደህና ቢደርስ ስለሚወስደው እርምጃ አሰበ ።

" ጥፋቶችና ድሎች በጣም በቅርብ የተዛመዱ ናቸው " ብሎ ሆስነር አሰበ ።

በርግ በፒፓው ቀዳዳ ውስጥ ትንባሆውን ጠቅጥቆ አቃጠለ ።

ሆስነርና በርግ በምሥራቃዊ ቁልቁለት በኩል በነፋሱ ኃይል በአሸዋ ሊሞላ ትንሽ በቀረው ቦይ ውስጥ ገብተው በቆይታ ተነጋገሩ ።

" ካፕላን የት ነው ? " ብሎ በርግ ለሁለተኛ ጊዜ ጠየቀው ።

የካፕላንን መሄድ በርግ እንዴት እንደ አወቀ ሁሉ ሰው ገምቷል። ምናልባትም ናኦሚ ሀበር ትሆናለች ። በርግ የራሱ ተከታዮች አሉት ። " በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ጊዜ ከዚህ ሩቅ በአልሆነ ኩርት በሚባል ቦታ የእንግሊዝ ወታደሮች በቱርኮች ተከበው ነበር " ብሎ ሲጋራውን ከአቀጣጠለ በኋላ " ከበባው ለብዙ ወሮች ስለቆየ ስን ቃቸው አለቀባቸው ። ረዳት ሰጭው የእንግሊዝ ወታደር አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ገፍቶ ወደ ኩርት ቢገባም በቱርክ ወታደሮች ተደጋ ግሞ ተባረረ ። በመጨረሻም ስንቃቸው በሚያልቅበት ጊዜ የእንግ ሊዞቹ ወታደሮች እጃቸውን መስጠት ነበረባቸው ። በእንግሊዝ አዛዥ ላይ ከደረሱበት እጅግ በጣም አስከፊ ከነበሩት ወቀሳዎች አንዱ ከኩርት ገስግሶ የቱርኮችን መስመር ከበ አለመውረሩ ነበር ። ሪፓርቱ አንድ ቦታ ተኮልኩሎ የተደረገውን መከላከል አውግዞ እየተዘዋወሩ በመ ዋጋት የተደረገውን እንቅስቃሴ ተቀብሏል ። በጦር የእንቅስቃሴ እቅድ እየተጠቀሙ መዋጋት አስፈላጊ ነው ። በዚህ ዘመን የወታደራዊ ሳይ ንስ ይህን ተቀብሎታል ። አንተ ታዲያ ለምን አትቀበልም ? " ብሎ ሆስነር ጠየቀው ።

በርግ ራሱን አስገድዶ ከሳቀ በኋላ " ከሰጠኸው ምሳሌ ጋር ያለው ግንኙነት በትክክል አይታየኝም ። ካፕላን ያለው የት ነው ? ወደ ቁልቁለቱ ወርዷል ? " ብሎ ጠየቀው ።

" ሁኔታው ከአልኩት ጋር ግንኙነት አለው ። ጥሩ ዘዴዎችበኩርት ሆነ በካርቱም ወይም በባቢሎን ምንጊዜም ጥሩዎች ናቸው ። ስለካር ቱምም በምንነጋገርበት ጊዜ በርግ መርሳት የሌለብህ አንድ ነገር አለ። ይኸውም የእንግሊዝ ረዳት ኃይል እዚያ ለመድረስ የዘገየው አንድ ቀን ብቻ ነበር ። ይህ በመሆኑ ጄኔራል ጐርደን ፣ ወታደሮቹና ሌሎቹም ሊድኑ አልቻሉም ። እኛም በሚቀጥሉት ጥቂት ሰዓቶች ውስጥ የውጭ እርዳታ ከአላገኘን ወይም ከአልደረሰልን የዚያ ዓይነት ዕድል ይደር ስብናል ፣ በርግ ። አንድ ሰው መጥቶ እስኪ.ተረክከን ድረስ እዚህ ተቀምጠን ለመንቀሳቀስ አለመሞከር ራሳችንን በተሳሳተ የመከላከያ ሁኔታ ላይ እንጥላለን ። እነዚያ ደም የጠማቸው አሸባሪዎቹ ያለአንዳች

ችግር እዚህ ድረስ እየጮኹ መጥተው አደጋ ቢጥሉ ፣ ሁላችንም በዚያ ጊዜ ይህንን ለምን አልሞከርንም ? ወይም ያንን ለምን አላደረግንም ? እን ላለን ። ለዝግጅት የበለጠ ጊዜ ለማግኘት የምንወስደው ማንኛውም እስከፊ እርምጃ ከሚከተለው አደጋ የተሻለ መሆኑን አሁን ግልጽ አድርጌ እየነገርኩህ ነው ፣ በርግ ። ”

“ ወዴት ነው የሄደው ? ወደ ኢሽታር በር ? ”

“ አይደለም ። አሽባሎቹ ይመጣሉ ብለን ወደ ገመትነው የከ ተማ ክልል አጥር ውጭ ወደሚገኘው ቦታ ነው ። ”

“ እንዴት እርግጠኛ መሆን ትችላለህ ? ”

“ በመስከ ላይ ለሚያጋጥሙ ችግሮች ሁሉ ሊደረጉ የሚችሉ መፍትሄዎች አሉአቸው ። ”

“ በምንመለስበት ጊዜ በጦር ኮሌጅ ውስጥ ሥራ እሰጥሃለሁ ።”

ሆስነር በቦዩ ግድግዳ ላይ ተደግፎና ዓይኖቹን ጨፍኖ ሲጋ ራውን ማገ ።

“ በርንስቴይንና አሮንስንን ለፍርድ የምናቀርባቸው መቼ ነው፣ የጦር ፍርድ ቤት ከመቋቋሙ በፊት ወይስ በኋላ ? ”

ሆስነር በቂ ትህትናና አክብሮት ቢያሳየውም አላዋጣውም። በቶሎ ብድግ በማለት የበርግን ደረት ነካ ከአደረገ በኋላ “ አትገፋፋኝ ፣ ይስ ሐቅ ። አላርፍ ከአልክ እችግር ውስጥ የምትገባው አንተ እንጂ እኔ አይደለሁም ። ጉዳዩ ወደ ድምጽ መስጠት ከደረሰ ከዚህ ችግር የሚያወጣቸውን እውነተኛ ሰው ይመርጣሉ እንጂ እንደ አንተ ያለውን ወይም ዌዝማንን አይመርጡም ። ስለዚህ አትቀስቁሰኝ። አንተ ከምታ ስበው መንገድም ሆነ ከግል ሕይወትህ በቅርብ ቀን ስለምርቅ አር ፈህ ተቀመጥ ። ”

በርግ አቆልቁሎ በፒፓው ውስጥ የሚቀጣጠለውን እሳት ትኩር አድርጎ ተመለከተ ። “ አላምንህም ፣ ያዕቆብ ። ድሎችና አደጋዎች ብዙ ጊዜ ተመሳሳይ ገጽታዎች አሏቸው ብሎ የሚያስብ ሰው ሁሉ ነገር በእጁ መሃል እያለ ሌላ የሚፈልግ ነው ። በጸጥታ በኩል የምን ጠቀምበት መንገድ የዚያ ዓይነት አይደለም ። ለሚደርስብን ጥቃት ኪሳራ በለውጡ ጥቂት ትርፍ ማግኘት አለብን ። ግን ሁኔታው ከፍ ተኛ ድል የሚያስገኝ ቢሆንም ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ አናደርግም ። ከትላልቆቹ አወናባጆች አንተ የመጨረሻው ነህ ። ግን በሌሎች ሰዎች ሕይወት ላይ ማድረግ አይ

ገባህም ። በአንድ ሰው ሕይወት ላይ እንኳን - ሞሼ ካፕላን - ጀግና ሰው የእርሱ ሕይወት ማለፍ ጥሩ ነገር ቢያስከትልልንም እንኳን የዚያ ዓይነት ጨዋታ ማድረግ የለብህም ። ”

“ አንተ የተረገምህ ግብዝ ሰው ነህ ፣ በርግ ፣ በሕይወት ዘመንህ ሁሉ በጣም መጥፎ ነገር ሠርተሃል ። ዶብኪንን እንዲሄድ በጠየኩት ጊዜ ደስተኛ እንዳልነበርክ ዓይነት ሆነህ አታስመስል ። ተልዕኮው በአብዝኻኛው ጐኑ የሚያጋጥመው ሞት መሆኑን ታውቃለህ ። አንተ ግን በዚያ ጊዜ ስለእርሱ መሄድ ቅሬታ አልተሰማህም ። ”

“ ያ ልዩ ነው ። ዶብኪን ባለሙያ ነው ። እንደ ዶብኪን ያለ ሰው በሕይወት ዘመኑ ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ የዚህ ዓይነት እንደሚያ ጋጥም ያውቃል ። ”

“ ያ ለእርሱም ሆነ ለእኔ ሊያቃልልልን የሚችለው ነገር የለም ። ለመሆኑ ሁለቱንም በመላኬ ተደስቷል ብለህ ታስባለህ ? ”

“ ያንን አላልኩም ። አትጨኽ ። የምነግርህ ሐቁን እንጂ እንቶ ፈንቶ እንዳይመስልህ ። ”

“ ከአሁን በኋላ ሐቁንም ሆነ ቀልዱን አልፈልግም - በርግ ። ማድረግ ይገባኛል ብየ የማስበውን አደርጋለሁ ። በኢየሩሳሌምና በቴል አቪቭ ውስጥ ያሉት ሰዎች ተጨባጭ በአልሆነ ንድፈ ሃሳብ ላይ መጨ ቃጨቃቸውን ትተው በወቅቱ እርምጃ ከአልወሰዱ የት ቦታ እንዳ ለን በሚያውቁበት ጊዜ የሚያገኙን ሁላችንም ሞተን ነው ። ይህም እንዳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ተስፋ አደርጋለሁ ። ”

በርግ ወደ ቁልቁለቱ ከተመለከተ በኋላ “ ለሌላ ጦርነት መነ ሳት ወይም ለሰላሙ ስብሰባ መፍረስ ምክንያት ከምንሆን መሞት ይሻ ለናል ” አለው ።

ሆሲነር ነገሩን በአንክሮ ተመለከተው ። በርግ የተሻለና ጥሩ ነው ብሎ ለሚያስበው ጉዳይ ሁሉንም ለሞት ሊዳርጋቸው ፈቃደኛ ሆኖ አል ። በጀግንነት ተዋግተው በመሞት እስራኤልን በመጥፎ ሁኔታ ላይ ከሚጥሉ ይልቅ እጃቸውን አጣጥፈው ሳይንቀሳቀሱ ቢሞቱ ይመ ርጣል ። ሆስነር ግን ራሱን ፣ ካፕላንን ወይም ሌላ ሰው ለከፍተኛ አላ ማና ግብ መስዋዕትነትን ለመክፈል ፈቃደኛ ነው ።

ሆስነር ራሱን አሳልፎ ለመስጠት ቢፈልግም ከመሞት ይልቅ በጣም መጥፎ የሆነ ሕይወት እንዲገፋ እጣ ዕድሉ አስገድዶታል ። ካፕላን ሕይወቱን አሳልፎ እንዲሰጥ የሆስነር ዓይነት ጥያቄ ቀርቦለት ቢሆን ወደፊት የተመቻቸ ሕይወት አይኖረውም ። እርሱን ግን

ያስጨነቀው መኖር ወይም መሞት ሳይሆን ጠብ አጫሪ ሆነው በመ ቆጠር ሌላ ችግር እንዳይፈጠር ነበር ። የእስራኤል አይሁዶች እንደ አውሮፓው የአይሁዶች እልቂት እጃቸውን አጣጥፈው አይሞቱም ።

የበርግ ክርክር ከሆስነር ባሕርይ ጋር ተቃራኒ በመሆኑ ሊጣጣ ሙና ሊግባቡ አልቻሉም ። ሆስነር በጠቅላይ ሚኒስትሩ በቀጥታ ቢጠ የቅ ኖሮ “ በአስቸኳይ ኃይል ልከህ ከዚህ አውጣን ። የሚጐትትህ ምንድን ነው ? ” ይለው ነበር ። በርግ ይህንን በእርግጥ ያምናል። በርግ አሁንም አንጉል ቀልዱን እንደቀጠለ ነበር ። እንደጠቅላይ ሚኒስ ትሩና - እንደ ሚሪያም ሆኖ መናገር ይፈልጋል ። በርግ ብዙ ባሕር ያትና ብዙ ተለዋዋጭ ምላሶች ነበሩት ። ግን በርግ በእውነት የሚና ገረውን አምኖበት ከሆነ ፣ በርግ ስህተተኛ ነበር ። በርግ በዓይነ ቁራኛ መታየት አለበት ። በርግ መሄድ ይኖርበታል ።

* * *

ሆስነር በመከላከያ ጉድባው ውስጥ ብቻውን ተቀመጠ ። አቧራውና አሸዋው በነፋሱ ኃይል እየመጣ በእግሩ ላይ ተከመረ ። በርግ ተቀምጦበት የነበረውም በአሸዋና በአቧራ ተሞላ ። በዚህ ዓይነት ለመከላከያ የሠሩአቸው ሁሉ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ከጥቅም ውጭ ይሆናሉ ። አውሮፕላኑም አንድ ቀን በአቧራውና በአሸዋው ይሸፈ ናል ። አጥንታቸው በአሸዋው ውስጥ የሚቀበር ሲሆን “ ሥራቸው ሌላው የሥቃይና የመስዋዕትነት ” ተብሎ በመጻፍ በኢየሩሳሌም ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ይቀመጣል ። በእግሩ ላይ ከተከመረው አሸዋ አፈስ አድርጐ በነፋሱ ላይ አዘራው ። ባቢሎን - ቦታውን ጠላው ። የባቢሎንን ግውዝ አቧራና ድንጋይ ጠላቸው ። ባቢሎን የሰዎች ምግ ባር ከንቱ አድራጊ ፣ የሕይወት ገዳይ - በሚሊዮን የሚቆጠሩ የመ ስዋዕትነት ፣ የባርነት ፣ የነውር ፣ የደም መፋሰስ ሥራዎች የተፈጸሙ ባት አገር ናት ። በእንደዚህ ያለ ቦታ ለእርስዋ ያለው ፍቅር እንዴት ሊያብብ ይችላል ?

ልኮባታል ። ግን እንደምትመጣ ዋስትና አልነበረውም ። ልቡ በደረቱ ላይ በኃይል ሲመታ ተሰማው ። አፉ ደረቀ ፣ እጆቹ ተንቀጠ ቀጡ ። ሚሪያም በፍጥነት ነዪ ። ቆይታዋን ሊታገሰው አልቻለም ። ሰዓቱን ሲመለከት በርግ ከሔደ አምስት ደቂቃ ሆኖታል ። ወደ ኮን ኮርዱ ሰው ከላከ ደግሞ ሦስት ደቂቃ አልፏል ። ተነስቶ ለመሄድ ቢፈልግም ስትመጣ ስለምታጣው ከዚያ ለመንቀሳቀስ አልፈለገም ።

የሁለት ሰዎች ድምጽ ሰማ ። ጥላቻውም ታየው ። አንድ ቅርጽ ከአሳየ በኋላ ተመልሶ ሄደ ። ሌላው ወደ እርሱ ስለመጣ ከንፈሩን አርሶና ድምጹን አለዝቦ “ እዚህ ነኝ ” አላት ።

ወደ ቦዩ ገብታ በጕኑ በመንበርከክ “ ነገሩ ምንድን ነው ፥ ያዕቆብ ? ” ብላ ጠየቀችው ።

“ እኔ . . . ላነጋግርሽ እፈልጋለሁ ። ”

“ ነጻ ወጣሁ ? ”

“ አይሆንም ፥ አይሆንም ፤ ማድረግ አልችልም ። በርግ — ”

“ የባቢሎን ንጉሥ ስለሆንክ እዚህ የፈለግሽውን ማድረግ ትችላለህ ። ”

“ ይህንን ንግግርሽን አቁሚ ። ”

ወደ ሆስነር ተጠግታ አንዳንድ ነገርህ ከበርግ ጋር ይመሳሰላል ። ይህም “ ሴትዮዋን አስሮ ማቆየት ነው ። እኔ ያዕቆብ ሆስነር ነኝ ። ጠንካራ ውሳኔዎች እወስዳለሁ ። ተግባራዊ እንዲሆኑም እገፋበታለሁ የምትል ትመስላለህ ” አለችው ።

“ እንዲህ አትበዪ ሚሪያም . . . ”

“ የምናገረው ስለራሴ ወይም ስለኤሸር አይምሰልህ ። እኔ የማስበው ስለአንተ ነው ። ይህን ቀልድህን ከቀጠልክ አደጋ ላይ ትወድቃለህ ። በዚህ ሁኔታ የምታሳልፈው እያንዳንዱ ደቂቃ ከትክክለኛው የሰውነት ባሕርይ እየቀነሰክ እንድትሄድ ያደርግሃል ። ሎደግነትና ለከፍተኛ ርኅራኄ አቋም ውሰድ ። እኔ የማውቀውን ያዕቆብ ሆስነርን ለሁሉ ሰው ለማሳወቅ አትፍራ ። ”

ራሱን በአሉታ በመነቅነቅ “ አልችልም ። እዚህ የምህረት ምልክት ባሳይ ሁኔታዎች በትክክል አይሔዱም ብየ እፈራለሁ ” አላት ።

“ የምሕረት ምልክት ብታሳይ ሁኔታዎች በትክክል አይሔዱም ብለህ ትፈራለህ ። ”

ሆስነር ስለሞሼ ካፕላን አሰበ ። በዚያ ሰው ላይ እንደዚያ ያለ ነገር እንዴት ይፈጸማል ? ስለወደፊቶቹ ሞሼ ካፕላኖች አሰበ ። ሚሪያም በመቃብሩ ሥነ ሥርዓት ያሰማቸውን ጸሎት አስታወሰ ።

ሚሪያም አዕምሮውን እንደምታነብ ሆና “ የአንተ ተገዥ ፥የአንተ የሌሊት ቅዠትና የአንተ ጣረሞት መሆን አልፈልግም ። ረዳትህ እንጂ ” አለችው ።

እንደ ልጅነቱ ወራት እግሮቹን ሰብስቦና ራሱን በጉልበቶቹ ላይ አድርጎ “ ከዚህ ሂጂልኝ ” አላት ።

“ አንተ እንደምትለው እንደዚህ ቀላል አይደለም፤ ያዕቆብ ። ”

ራሱን ቀና አድርጐ “ ቀላል አይደለም ” ካለች በኋላ በጨለማው ውስጥ ትኩር አድርጐ ተመለከታት ።

ተስፋ የቆረጠና ብቸኛ መስሎ ታያት ። “ ከእኔ የምትፈልገው ምንድን ነው ? ”

ራሱን አሁንም በአሉታ አነቃንቆ በጐረና ድምጽ “ አላውቀውም” አላት ።

“ እንደምታፈቅረኝ ልትነግረኝ ትፈልጋለህ ? ”

“ አንድ ወጣት ልጅ ከሴት ጓደኛው ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ሲወጣ እንደሚሰማው ዓይነት እየተንቀጠቀጥኩ ነው ። ”

በእጅዋ ጸጉሩን ዳሰሰችው ።

እጅዋን ጐትቶ በከንፈሮቹ ላይ አስቀመጠው ።

ሆስነር ሊስማትና ሊደባብሳት ፈለገ ። በዚህ ፋንታ ግን በእጆቹ መሃል አድርጐ አጥብቆ ያዛት ። ትንሽ ፈቀቅ አድርጓት በአንድ እግሩ ተንበርክኮ ከብር የተሠራ የዳዊት ኮከብ ከኪሱ ውስጥ አውጥቶ በመ ዳፉ ላይ አስቀምጦ እያሳያት “ በጉዞዬ መጨረሻ ቀን ከኒውዮርክ የገዛሁት ነው ” አላት ።

የዳዊትን ኮከብ ሲሰጣት ከልቧ ስቃ “ ይህ ለእኔ የመጀመሪያ ስጦታህ ነው ፡ ያዕቆብ ግን ፤ ስጦታ እንዳልሆነ አድርገህ ታስባለህ ። አመሰግናለሁ ፍቅሬ ” አለችው ።

በድንገት አስተያየትዋ ተለዋወጠ ። በቦዩ ውስጥ ተንበርክካ በመዳፍዋ ላይ ያለውን ኮከብ አጐንብሳ እየተመለከተች “ አሀ ያዕቆብ እባክህን ሕይወትህን በከንቱ አትስጥ ” ብላ ኮከቡን ጨብጣ በጡቷ ላይ ያዘችው ። ኮከቡን በኃይል ጨብጣ ሰውነትዋ እስኪንቀጠቀጥ ድረስ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ። ቀጥላም “ እዚህ እንድትሞት አልተ ውሀም ” አለችው ።

ምንም ባይናገርም ዓይኖቹ በእንባ ተሞሉ ።

* * *

ሞሼ ካፕላን በአንድ ገደል ጥግ ሆኖ በኮከብ ብርሃን ማጉሊያው አነጣጥሮ ተመለከተ ። የጨረቃ ብርሃኑ ከመድከሙም በላይ አካባ ቢው በአቧራ ተጠቅጥቋል ። ሆኖም ከግንቡ አጥር 20 ሜትር እር ቀት ላይ እንደነበር ቆዳ ዝጉርጉር የሆነ ልብስ ለብሰው በሰልፍ ይሄዱ የነበሩትን አሸባሎች ለማየት ችግር አልነበረበትም ።

የአጥሩን ግንብ ግድግዳ ተጠግተው ሲሄዱ በጨረቃው ብር ሃን ለአያቸው ያስፈሩ ነበር ።

በኮከብ ብርሃን ሰጭው መነጽር በሚመለከትበት ጊዜ በድንገት የመነጽሩ ብርሃን ስለፈዘዘ ባትሪው እያቆመ እንደነበረ አወቀ ። ባትሪው በሙሉ ሥራውን ከማቆሙ በፊት አነጣጥሮ ቃታውን ሳበው ።

በተራራው ላይ የነበሩት ሁሉ ጊዜው እንደ ደረሰ አወቁ ።

# —30—

ዶብኪን ተመልሶ እንዲሳፈር ቺስሎንን ከአስገደደው በኋላ መጓጓዣውን ከዳርቻው ወደ ውሃው ውስጥ ገፋለት ። ቺስሎን ብቻውን ስለነበረ እንደልቡ መንቀሳቀስ ጀመረ ። በተጨማሪም በአሁኑ ጉዞው የሚያስበው ስለዶብኪን ሳይሆን ስለራሱ ብቻ በመሆኑ ተዝናንቶ ጉዞውን ቀጠለ ። ዶብኪን እስከ ኡማ መንደር ድረስ ከቺስሎን ጋር መምጣቱን ሬሽ እንዲያውቅ አልፈለገም ። መጓጓዣው ወደ ሂላ በውሃው ላይ ተንሳፎ ሲሄድ ለዓይኑ እስኪሰወር ድረስ ዶብኪን ከተመለከተው በኋላ ወደ የብሱ ዞሮ ሄደ ።

ዶብኪን ቦታውን በፍጹም ያውቀው ስለአልነበረ ወደ ኤሽታር በር የሚወስደውን መንገድ በትክክል ባይለየውም በጨለማው የአሸዋ ውሽንፍር ውስጥ ቀስ ብሎ እርምጃውን ቀጠለ ። በየአለበት ትናንሽ ጉድጓዶች ስለነበሩ በጥቂቶቹ ውስጥ ለመውደቅ ተቃርቦ ነበር ። የጉድጓዶች መኖር በባቢሎን ውስጥ መሆኑን በእርግጥ አረጋግጠውለታል ። 300 ሜትር ያህል እንደሄደ በአንድ ጉብታ ላይ ወጥቶ አካባቢውን ተመለከተ ። እንግዳ መቀበያው ቤት መብራቶች የሚኖሩትና በእነእርሱ አማካይነት ፣ ጨለማውን ሰንጥቆ ለማለፍ የሚችል መስሎት ነበር ። ግን ምንም አላየም ።

ድምጽ ሰምቶ ወደ ኋላው ሲዞር አንድ ነገር በጨለማው ውስጥ ውልብ አለው ። እንደገና ሲንቀሳቀስ ቢጫ ዓይኖቹ በጨለማው ውስጥ ሲያበሩ አያቸው ።

ቀበሮው በአንድ በፈረሰ የአጥር ግንብ ላይ ወጥቶ ወደ ዶብኪን ዞሮ ቆሟል ። ዶብኪን ይህ አዳኝ ቀበሮ ሊጣላው የአሰበ መስሎ ታየው። “ እዚህ ምን እንደምትፈልግ አላውቅም ሽማግሌው አዳኝ ። እኔን እስከ አልሆነ ድረስ የምትፈልገውን እንደምታገኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ” ቀበሮው በፈረሰው አጥር ላይ እየተንጐራደደ ወደ ዶብኪን አቅጣጫ መጥቶ አፉን ወደ ላይ አንጋጦ ጮኸ ። ከወገኖቹ መልስ ስለእጣ ዘሎበመውረድ ወደ ጨለማው ገብቶ ሄደ ።

ዶብኪን ከቆመበት ጉብታ ላይ ወርዶ ለጊዜው ለመጠለል በአ ንድ እንደዋሻ በሆነ ፍራሽ ቤት ውስጥ ገባ ። በቤቱ ውስጥ ጨለማ ውን ተገን አድርገው የቆዩ ጉጉቶች ተንጫጩበት ። ዶብኪን በወ ለሉ ላይ ተቀምጦ የቁስሉን ሕመምና ድካሙን ለመቋቋም ሞከረ ። ዓይኖቹን ሲጨፍን አእምሮው ዋለለበት ። ባቢሎን - ምን ዓይነት የማይታመን የሞተ ቦታ ነው ።የሞተ ከተማ ሊገድለውና አጥንቶቹም ከተቃጠለው አፈሩ ጋ እንዲቀላቀሉ እየሞከረው ነበር ። በቀልቀሎ ከያዘው ውሃ በጣቶቹ ላይ አፍስሶ ዓይኖቹን አበሰ ። አሁን ከአለበት በከፊል ከተቀበረው ቤት ውጭ ወደ ሌሎቹ ፍርስራሾች የሚወስድ የእግር መንገድ በማግኘት ወጥቶ ወደ ሰሜን ዞሮ ወደ የኤፍራጥስ ወንዝ ዳርቻ የሚወስደውን መንገድ ተከትሎ ሄደ ። ከነፋሱ ለመከ ላከል አጐንብሶና ፊቱን በጥምጣሙ ሸፍኖ አንድ ኪሎ ሜትር ያሀል ተጓዘ ።

ነፋሱ ትንሽ ቀለል እንዳለ ድምጽ የሰማ ስለመሰለው ራሱን ቀና አድርጐ ተመለከተ ። አንድ አረብ በስተጀርባ ባለው መግቢያ በኩል ሆኖ አተኩሮ ሲመለከተው አየ ። ዶብኪን ከዌሪሽ መድረሱን አሁን አረጋገጠ ። ወደ አረቡ እንደገና ከተመለከተ በኋላ ተጠጋው ። “ የእንግዳ ማረፊያው ቤት ” አለው የፍልስጥኤማዊ አረብኛ የድ ምጽ አጣጣል በመጠቀም ።

ሰውየው በጨለማው ምክንያት መንገደ ከጠፋበት አሽባል ጋር የሚነጋገር መሆኑን አመነ ። ሰውየው ለፍልስጥኤሞቹ የነበረው ፍቅር እምብዛም ነበር ። ይሁን እንጂ የአካባቢው ባለሥልጣኖች እነእርሱ መስለዋል ። መሣሪያ አልባ የሆነ ፍልስጥኤማዊ ፈጽሞ አይቶ ስለማ ያውቅ በነገሩ በጣም ተገረመ ። ከታዛው ወጥቶ በዶብኪን በኩል ሲያ ልፍ በዓይኖቹ ገረፍ አደረገው ።

ዶብኪን ተከትሎት ሲሄድ የኡማው አይሁዳዊ የሰጠውን ጩቤ ከሰገባው አውጥቶ በጥንቃቄ በእጁ ያዘ ። ለጥቂት ደቂቃዎች በአ ንድ መጥፎ መንገድ ከሄዱ በኋላ ሰውየው በሁለት ሕንጻዎች መካከል በአለ ሰርጥ ሄዶ ተሰወረበት ። ዶብኪን በሰርጡ መንገድ ተከትሎ በጥንቃቄ ቢመለከትም ሊያየው አልቻለም ። ዶብኪን በቀኝ ጐድኑ ግድግዳውን ተጠግቶ በሚራመድበት ጊዜ ከአስፈለገ በጩቤው ለመጠቀም ተዘጋጅቶ ነበር ።

አረቡ በድንገት በግድግዳው ጥግ ከነበረ አንድ ጐድጓዳ ቦታ ወጥቶ በእጁ እያመለከተ “ መንገዱ በዚያ በኩል ነው ” አለው ።ሀማዲ እርሱንና ሆስነርን ወደ ኢሽታር በር የወሰደበት የፍየል መንገድ እንደ

ነበረ በእርግጥ አስታወሰ ። ራሱን በአምንታ በማነቃነቅ ምስ ጋና አቀረበለት ። በሰውየው አጠገብ ማለፍ ስለነበረበት ጩቤውን አጥብቆ በመያዝ እርምጃውን ቀጠለ ። አረቡም የራሱን ጩቤ አጥ ብቆ ያዘ ። አሽባል ነው ብሎ ያመነውን ሰው በመግደል ልብሱን ፣ ጫማውንና በኪሱ የሚገኘውን ለመውሰድ አሰበ ። አሽባሎቹ በክዌሪሽ ውስጥ የሰውየውን ፈለግ ፈጽመው አያገኙትም ።

ዶብኪን አንድ ሜትር ያህል በመራቅ ዓይኖቹን በሰውየው ላይ ጥሎ አለፈ ። አሽባሉ እንደዔት ትልቅና ጥንቁቅ እንደነበረ አረቡ ተመ ለከተ ። እንዲያውም አሽባሉ እርሱን ለመግደል ዕቅድ ይኖረው ይሆናል ብሎ አሰበ ። አረቡ አቅልቁሎ ሲመለከት ጩቤውን በጨ ረፍታ አየው ። በመጀመሪያ ይውጋው ወይስ ወደ ኋላው ተመልሶ በመቆም ሰውየው እንዳይገድለው ወደ አላህ ይጸልይ ይሆን ? በእርግጥ ሰውየው አረቡን ለእዚያ አሮጌ ግልድምና ለአሮጌ ጥልፍልፍ ጫማ ብሎ አይገድለውም ። አረቡ “ አላህ በምትሄድበት ይከተልህ ” ብሎ ራሱን ዝቅ አደረገ ።

ዶብኪን ሰውየውን ስለመግደልና ስለአለመግደል ያለውን ሃሳብ ከአብላላ በኋላ “ ከአንተም ጋር ይሁን ” ብሎት በቤቶቹ መካከል ባለው የፍየል መንገድ ሄደ ።

ዶብኪን ቀድሞ በካርታ ላይ የሚያውቀውን ለማስታወስ ቢሞ ክርም በደረሰበት ድካምና ጭንቀት ምክንያት ተምታታበት ። ስለ ምርኮኝነት የተነገሩት ታሪኮች እውነትነት ከአላቸው እርሱም እንደ ሌሎቹ አይሁዶች በዚያ የሚኖሩ ቅድመ አያቶቹ እንዳሉ ገመተ ። ሳይረስ እንዲሄዱ በፈቀደላቸው ጊዜ ቅድመ አያቶቹ አላወላወ ሉም ። የሄዱት ግን ከአንድ ምዕተ ዓመት በኋላ በሮማውያን እንደገና በየአገሩ እንዲሰደዱ ተደረጉ ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ 1948 ድረስ ቤታችን ብለው የሚጠሩት ቦታ አልነበራቸውም ። ዶብኪን ተብሎ የሚጠራው የቤተሰብ ስም ከሁለት ሺህ ዓመታት መንከራ ተት በኋላ በሩስያ ውስጥ ለመኖር መጣ ። ከሩስያ ጉዞአቸውን ጨር ሰው ወደ ፍልስጥኤም ተመለሱ ። ቤንጃሚን ዶብኪን ከፍልስጥኤም እስራኤል - ከዚያም ወደ ባቢሎን መጣ ። ወደ ኢየሩሳሌም ቢመ ለስ የቀረው ሁሉ ይታያል ።

ዶብኪን ቀድሞ የኤፍራጥስ ወንዝ ይሄድበት በነበረው ደረቅ ወንዝ ወደ ቤተ መንግሥቱ አካባቢ ሄደ ። ከሩብ ሰዓት ጉዞ በኋላ በኢሽታር በር የሕንጻ ማማ ላይ የተሠሩት የሚያብረቀርቁ የአንበሳ ስዕሎች ታዩት ። የእንግዳ መቀበያ ቤቱን መብራቶች እስኪያይ ድረስ በበሩ አጠገብ አልፎ ሄደ ። በአካባቢው የዘብ ጓድ ያለ አይመ

ስልም ። በእንግዳ መቀበያው ቤት በአሻገር ድንኳኖች ተተክለዋል ። ከዚያ ጥቂት እልፍ ብሎ ቤተመዘከሩን እንደሚያገኝ ገብቶታል ። አሽባሎቹ በዚያ ያሉ አይመስሉም ። እንደገና ለመውጋት ወደ ተራ ራው ሄደዋል ። ትንፋሹን አምቆ እንደቆመ ከወደ ተራራው በኩል የኤኬ - 47 ጠመንጃ ተኩስ ሰማ ። ወደ እዚያው ግን ጸጥ አለ ። ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። ቢያንስ ቢያንስ እንዲጠነቀቁ አድርጓቸዋል ። የሚያስደንቅም አልነበረም ። ማን እንደተኮሰው ከአሰበ በኋላ አካ ባቢውን ጠባቂ የሆነና ራሱን ለመሰዋት ያዘጋጀ ሰው እንደነበረ ተገነዘበ ።

በቤተ መዘከሩ ውስጥ ዶክተር አል - ታኒን ለትንሽ ጊዜ ለማግኘት ቢያስብም ጥሩ መስሎ አልታየውም ። የጊዜም ሽሚያ ነበር ። በተጨ ማሪም አል - ታኒን ያምነዋል ? ቢያምነውስ በዚህ ነገር ውስጥ እንዲ ገባ ይፈልጋል ?

አስቸኳይ የስልክ ጥሪ ከማድረግ ሌላ የተወሰነ ሃሳብ የለውም ። ሊታመን የማይቻለው ሥራ የሚፈጸመው በጀግንነት ፣ በድፍረትና በዕድል ነው ። እስከ አሁን በጣም ጥሩ ዕድል አጋጥሞታል ። የኡማን መንደር በማግኘቱ እንደ አሽባሎቹ መልበስ ችሏል ። የእንግዳ ማረ ፊያ ቤቱን አግኝቷል ። አሽባሎቹ ከድንኳኖቻቸው ለቀው የሄዱ መስ ለዋል ። አሁን ማድረግ የሚቀረው ወደ ውስጥ ገብቶ ሰው ከአገኘ መግደል ነው ። ምናልባትም በድንኳኑ ውስጥ ቁስለኞችና ረዳቶ ቻቸው ይሆኑ ይሆናል ።

ፊት ለፊት ወደ አለው በረንዳ ወጥቶ መዝጊያውን ከፈተው ። ከመብራቱ ጋር ለማለማመድ ዓይኖቹን አጨነቆራቸው ። ዝጉርጉር ልብስ የለበሰ አንድ ወጣት አረብ ተቀምጦ ጋዜጣ ያነባል ። ወጣቱ ሰው ቀና ብሎ ሲያይ ዶብኪን ሁኔታውን ተመለከተው ።

ሰውየው ካሲም ሲሆን አይሁዳዊቱን ሴት በግዴታ እንደገና - አልሞተች እንደሆን - ሊገናኛት ወስኖአል ።

ዶብኪን ቀስ ብሎ ወደ ካሲም በመጠጋት በግራ እጁ የሰውየውን ጸጉር አፈፍ በማድረግ በቀኝ እጁ በያዘው ጩቤ ማንቁርቱን ጉምዶ በወ ለሉ ላይ አጋደመው ። ደም የነካውን እጁን በጋዜጣው ጠርጐ አሁ ንም ቀስ ብሎ በማለፍ በአረብኛ የሥራ አስኪያጅ ጽሕፈት ቤት የሚል ወደ ተጻፈበት ደርሶ መዝጊያውን ከፈተ ። በትንሹ ክፍል ውስጥ አንድ የበራ ፋኖስ አለ ። በወለሉ ላይ አንዲት በደም የተበከለችና የምታጣ ጥር ወይም የሞተች ሴት በሆድዋ ተደፍታ ተኝታለች ። ዶብኪን በቆዳዋና በጸጉርዋ አቀራረፕ ሊጠቀሙባት ያመጡአት የአገር ቤት

ሴት እንዳልሆነች አወቀ ። ተጠግቶ ሰውነትዋን ገለበጠው ። ፊትዋ በግርፋት ያበጠ ቢሆንም የሚያውቃት መሰለችው ። ቀስ በቀስ የዶጋል ቴኮ ጸሐፊ መሆንዋን ቢረዳም ለጊዜው ስምዋን ሊያስታውሰው አልቻለም ። ተንበርክኮ ጆሮውን በደረትዋ ላይ አድርጐ ሲያዳምጥ ሕይወትዋ መኖሩን አረጋገጠ ። በደም የተለወሰውን ሰውነትዋን ተመለከተ ። ለማዳ ያልሆነ እንስሳ እየወጋ የፈነጨባት መስላለች ።

ሴትዮዋን አንስቶ በአንድ ሶፋ ወንበር ላይ ከአጋዳማት በኋላ ከሱፍ የተሠራ የሸርጥ ጨርቅ ከተሰቀለበት አውርዶ አለበሳት።ውሃ የያዘ ማንቆርቆሪያ ስለአገኘ በፊትዋ ላይ ሲያፈስባት ተንቃነቀች ። በመሰቃየት ላይ ላለችው ሴት ከዚህ የበለጠ አንድ ደቂቃ እንኳን ሊያጠፋ አልፈለገም ። ወደ ጠረጴዛው ሄዶ ስልኩን አነሳ ። በሲና በረሃ በአንድ በፈረሰ መንደር ውስጥ አንድ ያልተበላሸ ስልክ አግኝቶ በግብጻውያን እጅ ወደነበረ አንድ መንደር ደውሎ ለመድረስ ጥቂት የቀረው መሆኑን የተናገረው ትዝ አለው ። ስልኩን አንስቶ ለመደወል መስመር በሚጠብቅበት ጊዜ የእግር ኮቴዎችና የሚያንቋርር ድምጽ ሰማ ። ቁስለኞችና ረዳቶቻቸው ነበሩ ። እንደዚሁም በሌላው ክፍል ሰዎች ሲነጋገሩ ሰማ ። ካርታ ይጫወቱ እንደነበረ ገባው ። መስኮቶቹን ነፋስ አንገጫገጫቸው ። ዶብኪን ስልኩ ተበላሽቶ እንደሆን በማለት አጐንብሶ ተመለከተው ። የሚሠራው በማዞሪያ በኩል በመሆኑ መደወያ አልነበረውም ። ታዲያ ስልከኛውን እንዴት ማግኘት ይቻላል ? ስልኩን ደጋግሞ ጠበጠበው ።

በድንገት የአንድ ሰው ድምጽ በስልኩ ውስጥ ተሰማ ። " አዎን የሂላ ማዞሪያ ጣቢያ ፤ አዎን ። "

ዶብኪን ተንፍሶ " ሂላ ፤ የባግዳድን ዓለም አቀፍ ማዞሪያ እባክህ አገናኘን ። "

" ባግዳድ ? "

" አዎን ፤ ባግዳድ ። " ዶብኪን በጥንቃቄና በትዕግሥት መስመሩን ጠብቆ ማግኘት አለበት ። አንድ ስህተት ቢፈጠር ነገሩ ሁሉ ያከትማል ።

" ባግዳድን የሚፈልገው ማነው ? "

ዶብኪን ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ሕብረተሰቦች እስከአየ ድረስ የአገሩን ሠራተኞች ሙሉ በሙሉ አድንቋቸው አያውቅም ። ከአቅማማ በኋላ " ይህ ዶክተር አል - ታኒ " ከአለ በኋላ የሂላው ስልከኛ ይህን ድምጽ ለይቶ ሊያውቀው ስለሚችል ስህተት መሥራቱን

በመገንዘብ “ ማለት እኔ ዶክተር አማር ሰባህ የምባል የዶክተር አል-ታኒ እንግዳ ስለሆንኩ እባክህ ባግዳድን አገናኘኝ ” አለው ።

ለትንሽ ጊዜ ዝም ከአለ በኋላ “ ጠብቅ ” አለው ስልከኛው ።

ዶክተር አል-ታኒ ያለው በእንግዳ መቀበያ ቤቱ ውስጥ ይሁን ወይም በቤተ መዘከሩ ወይም ባግዳድ ውስጥ ዶብኪን አያውቅም ። የስልኩን መዣሪያ በጆሮው ላይ እንደያዘ በግድግዳው ላይ በነበረው ሰዓት ደቂቃዎቹ ሲበሩ ታዩት ። ስልኩን ወደ ደቦራ ጌዲዮን ይዞ በመ ሄድ ከአመጣው ውሃ ከንፈርዋን አረጠበው ። የደም ስርዋ ሲሠራ ተሰማው ። በድንጋጤ ላይ ብትሆንም ቶሎ ራስዋን እንደምታውቅ ተገነዘበ ። የቆሰሉ ሰውነቶቿን እየነካካ ተጠግቶ ተመለከታቸው ። በሰውነትዋ ላይ ያደረሱባትን ስቃይ ስለአየ ተረኛውን ሰው በመግ ደሉ ምንም ቅሬታ አልተሰማውም ።

ስልኩን በጆሮው አስጠግቶ በትካሻው ላይ በማድረግ ፣ ሰውነ ትዋን ልክ ሐኪሞች እንደሚያደርጉት እያሸ ስልኩን በመጠባበቅ ላይ እንዳለ የግድግዳው ሰዓት ደወለ።በሌላው ክፍል ውስጥ ካርታ ይጫወቱ የነበሩት ሰዎች ድምጽ እየጨመረ መጣ ። በወለሉ ላይ አንድ ነገር እድው አለ ። ምናልባትም አንድ ሕመምተኛ ከአልጋ ላይ ወድቋል ወይም ሞቶ በወሳካ ወይም በበሽተኛ ማመላለሻ አልጋ ላይ ተወርው ሯል ።

አንድ ሰው ወደ መተላለፊያው ወይም ኮሪደሩ መጥቶ “ ካሲም ! ካሲም ! ያለኸው የት ነው ? ” ብሎ ጮኾ ተናገረ ።

ዶብኪን ያ ምናልባት የሞተው ሰው ስም ይሆናል ብሎ ገመተ ። አንድ ሰው መጥቶ ወደ ወለሉ ይመለከት ይሆን ?

የሰው ኮቴ ወደ መዝጊያው እየተቃረበ ከመጣ በኋላ የመዝጊያው መከፈቻ ዞረ ። ዶብኪን ስልኩን እንደያዘ ተንፏቆ ፋኖሱን አጠፋው። ደጃፉ ሲከፈት ከውጭ የመብራት ብርሃን በመግባቱ ከዶብኪን አንድ ሜትር እርቀት ድረስ ያለውን ቦታና ሴትዮዋ ተኝታበት የነበረውን ወለል በግልጽ እንዲታይ አደረገው ። “ ካሲም ! አንተ የአህያ ልጅ ፣ ያለኸው የት ነው ? ”

የሂላው ስልከኛ “ ባቢሎን ? ባቢሎን? ባግዳድ በመስመሩ ላይ ነው ። ባቢሎን፣ የለህም እንዴ ? ” አለ ።

ዶብኪን ትንፋሹን እንኳን ሳያሰማ ጸጥ አለ ።

የሂላው ስልከኛ ለባግዳድ ስልከኛ " የባቢሎን ፈላጊ ሄዷል" ብሎ ነገረው ።

መዝጊያው ተዘግቶ ክፍሉም እንደገና ጨለማ ሆነ ።

ዶብኪን ቀስ ብሎ " ባቢሎን ፡ አለሁ " አለው ።

" ምን ? ቀጥል ፡ ቀጥል ። "

" ባቢሎን ቀርቧል ። "

" ባግዳድን መስማት ትችላለህ ባቢሎን ? "

" ባቢሎን ይሰማኛል ፡ ሂላ " አለች ሴቷ ስልከኛ ለሂላ ወንድ

ስልከኛ። የባግዳድ ስልከኞች ቀልጣፋ ናቸው ብሎ ዶብኪን አሰበ።

" ቀጥል ባቢሎን " አለች የባግዳድ ዓለም አቀፍ ስልከኛ ።

ዶብኪን የኢራቅን የመንግሥት መሥሪያ ቤት እንዲያገናኙት ለመጠየቅ አሰበ ። በአሁኑ ሰዓት የትኛው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ክፍት እንደሆነ ለመጠየቅና ስለእርሱም ማንነትና ስለሚፈልገው ጉዳይ ለመንገር ፈለገ ። ታሪኩን ከሰማች በኋላ የስልከኛዋ መልስ ምን ይሆናል ? በአንጐሉ ውስጥ ብዙ ነገሮች ተጉላሉበት ።

" ቀጥል ባቢሎን ። "

"ከ—አገናኘኝ" ። ከእስላም አገር ወደ እስራኤል ጥሪ ለማድረግ የሚቻልበት ምንም መንገድ የለም ። በኢስታንቡል በኩል እስራኤ ልን ማግኘት ይቻላል ። ግን የቱርክ ቋንቋ ስለማይችል በኢስታንቡል አረብኛ የሚናገር ስልከኛ ማግኘት አለበት ። በሌላ በኩል ደግሞ ቴል አቪቭን አገናኙኝ ብሎ ሲናገር ሌላ ስልከኛ ቢሰማ በነገሩ ይጠረ ጠራል ።

" ባቢሎን ፡ አለህ ? "

" አዎን ፡ አቴንስን አገናኚኝ ። "

" ለምንድን ነው አቴንስን የምትፈልገው ፤ ማነህ ? "

" እኔ ዶክተር አማር ሰባህ ነኝ ፤ ወጣቷ ቆንጆ ፡ በአቴንስ ውስጥ የሚኖር የሥራ ባልደረባዬን ማነጋገር እፈልጋለሁ ። ስለዚህ ያለ መዘ ግየት አገናኚኝ ። "

“ ትንሽ ጊዜ ይፈጃል ፣ ዶክተር ። እንደ አገኘሁ መልሼ እደ ውላለሁ ። ”

“ ለምን ቶሎ አታገናኘኝም ? ”

“ ለምን ? ስለማይሆን ነዋ ! ”

“ እዚህ ያለው ስልክ ደወሉ በትክክል ስለማይሠራ ጥሪው ሊደርሰኝ አይችልም ። ”

ጸጥታ ሰፈነ ።

“ ትሰሚኛለሽ ፣ ባግዳድ ? ”

“ አዎን ፣ አዎን ፣ መስመር እየፈለኩልህ ስለሆነ እስከዚያው በመ ስመሩ ላይ ቆይ ። ”

“ አመሰግናለሁ ። ” ዶብኪን ባግዳድ ከደማስቆስ ፣ ደማስቆስ ከቤይሩት ጋር ሲነጋገሩ ሰማቸው ። ቤይሩት የመካከለኛው ምሥራቅ ትልቁ የማዞሪያ ጣቢያ ስለነበረ ኢስታንቡልን በፍጥነት አገኘው ። ቤይሩት ከድንበሩ 200 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ የሚገኘውን ቴል አቪቭን የሚያገናኝበት ጊዜና ቀኖች ይመጡ ይሆናል ። አሁን ግን ወቅቱ ስለአልሆነ አገናኙኝ ለማለት አልደፈረም ። ዶብኪን ይህን ያህል ሰዓት ይኖረኛል ብሎ አላሰበም ነበር ። የቤይሩትና የኢስታንቡል ስልክ ኞች ሲነጋገሩ በአረብኛ እየቀላቀሉ በመሆኑ ግልጽ አልነበረም ። እርሱ ግን ለመገናኘት አሁንም ይጠብቃል ። በሌላ በኩል ደግሞ መዝጊያው እንዳይከፈት ፈርቷል ። በፊቱ ላይ ላብ ኮለል እያለ ወረደ። ምላሱም ደረቀ ። በጨለማው ውስጥ ልቡ ድም ! ድም ! ሲል ተሰማው።

በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ ካርታ የሚጫወቱት ሰዎች እየጨ ረሱ ነበሩ ። ለተረኛው ጠባቂ ሌላ ጥሪ ነበር ። ከቁስለኞቹ ውስጥ ጥቂ ቶቹ ጮኹ ። ዶብኪን ከሰሜን በኩል የአውቶማቲክ ጠመንጃ ተኩስ የሰማ መሰለው ። በወንበሩ ላይ የተጋደመችው ሴት በእንቅልፍ ልብዋ ስትጮኽ ትንፋሹን አፍኖ ያዘ ።

ኢስታንቡል ከአቴንስና ከቤይሩት ጋር ተነጋገረ ። ቤይሩት ደማስቆስን በማለፍ በቃጥታ ከባግዳድ ጋር ተነጋገረ ። ሂላ በመስመር ላይ ስለአልነበረ ባግዳድ በቀጥታ ከባቢሎን ጋር በመነጋገር “ አቴ ንስ በመስመር ላይ ነው ” አለችው ።

“ አመሰግናለሁ ። ” የመጨረሻው የአቴንስ ስልከኛ በቱርክኛ ተናገረ ። ግን ወደዚያው አረብኛ ወደሚናገረው ስለአዞሩት “ ቁጥር እባክህ ” አለው ።

እንግሊዝኛ ተናጋሪ ስልከኛ ሊጠይቅ ፈለገ ። ግን ሌላ ምስቅል ቅል ማስከተል መሆኑ ገባው ። ማንኛውም ስልከኛ የሚያዳምጠው ሌላ ጥሪ እስከአልመጣ ድረስ መሆኑን ያውቃል ። ስለዚህ በዘዴ ትንሽ ጊዜ ማጥፋት አለበት ።

“ ይህ አቴንስ ነው ? ” ብሎ በአረብኛ ጠየቀው ።

“ አዎን ፣ ጌታዬ ፣ እባክህ ቁጥርህን ? ”

“ ቁጥር ልትፈልግልኝ ትችላለህ ? ”

“ በትክክል ፣ የምትፈልገው ማንን ነው ? ”

ዶብኪን ዱር የሚያውቀውን የአርኪኦሎጂ ሊቅ የሆነውን

“ ዶክተር አዳማንዲዮስ ስታስቶስ ፣ የሚኖረው በኪፕሴል አው ራጃ ውስጥ ነው ” አለው ።

“ አንድ ጊዜ ፣ እባክህ ። ”

ዶብኪን እስከ አሁን ድረስ አረብኛ ተናጋሪዎቹ ስልከኞች ማዳ መጣቸውን እንደሚያቆሙ ቢገነዘብም የጸጥታ ተከታታይ ሰው በአ ንደኛው መስመር ላይ ሊኖር ይችላል ። ቢሆንም በዚህ ሰዓት ዓለም አቀፍ የስልክ ጥሪ በዚህ በኩል በአሉ አገሮች ብዙም የተለመደ አል ነበረም ።

ስልከኛዋ “ ለዶክተር ስታስቶስ እየደወልኩ ነው ” አለችው።

“ ጥሪውን አቁሚ ። ”

“ ለምን ጌታዬ ? ”

“ ይኸኛውን ትቼ ሌላ ሰው በቀደምትነት ማግኘት እንዳለብኝ አሁን አስታውሼ አለሁ ። ” ከዶክተሩ ጋር በመነጋገር ጉዳዩ ምናል ባት ይፈጸም ነበር ። ግን በምንም ዓይነት ከቴል አቪቭ ጋር ለመነ ጋገር ፣ ስለቀረጠና ስለተቃረበም “ ጥሪውን ሰርዥው ” አላት ።

የአቴንስዋ ስልከኛ ተናዳ ጥሪውን ለመሰረዝ “ እሺ ጌታዬ ” አለችው ።

“ ቴልአቪቭን አገናኚኝ ። ”

ቴል አቪቭ ለትንሽ ጊዜ ቆይታ ሆነ ። ይህ ከአሁን በፊትም ሆኖ አል ። ግድ አልነበራትም ። እስራኤልና ግሪክ በጥሩ ሁኔታ ላይ ነበሩ ። ፖለቲካ ቆሻሻ ነው ። ግን ያ ምስኪን ሰው ከኢራቅ ቴል አቪቭን ለማ ግኘት በሚሞክርበት ጊዜ መጠንቀቅ አለበት ። " እባክህ ጠብቅ" ስልከኞች ይለዋወጡ ስለነበረ በመስመሩ ላይ ድምጽ መጣ ። አዲ ስዋ ስልከኛ " ቴል አቪቭ በመስመር ላይ ነው " አለችው ።

አንዲት ሴት በእብራይስጥ " እባክህ ቁጥሩን " አለችው ። የዶ ብኪን ደረት መታ ። ለስልከኛዋ ሁሉን ነገር ሊነግራት ፈለገ ።

" እባክህ ቁጥሩን ? "

" ድምጹን ተቆጣጠረ ። " ጠብቂኝ ። " ብዙ ቁጥሮች ነበሩ ። አንዱ የራሱ ቁጥር ሲሆን ምናልባት ሚስቱ ከብዙ ዘመዶቹ አንዱ ጋር ትሆን ይሆናል ። የወዳጆቹ ፣ የመኰንኖቹ ፣ የፖለቲካ ሰዎች ቁጥ ሮች ነበሩ ። ግን ለአንድ ወገን ቢነግርና ያ ሰው ለመንግሥት ቢያሰማ የባሰ ምሥቅልቅል ይፈጠራል ።

" ጌታዬ አንተ - "

" በቴል አቪቭ ፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ጽሕፈት ቤት አገናኚኝ ። የጠቅላይ ሚኒስትሩን የምሥጢር የስልክ ቁጥር ሊነግራት አልፈለ ገም ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቴል አቪቭ ወይስ በኢየሩሳሌም ውስጥ ይሆን ብሎ አሰበ ። ቢያንስ ቢያንስ በቴል አቪቭ ውስጥ ከአንድ ተረኛ መኰንን ጋር መነጋገር ይችላል ። ዶብኪን በመተላለፊያው ላይ ሌላ ድምጽ ሰማ ። የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ የጠፋውን ሰው ያገኙታል ። በመ ስመሩ ላይ ስልኩ ሲደውል ተሰማው ።

" ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት " አለች አንዲት ስልከኛ ።

" የጸጥታው ስብሰባ እዚያ ነው ወይስ ኢየሩሳሌም ? "

ለትንሽ ጊዜ ጸጥታ ሆነ ። ዜናው በጋዜጣ ላይ ወጥቶ ስለነበረ መልስ የማትሰጥበት ምንም ምክንያት የላትም ።

" የሚናገረው ማነው ? "

" ጀኔራል . . . " ስለስሙ ምን ሁኔታ እንደምታሳይ አላወቀም። ጀኔራል ኮህን ። " ቆም ከአደረገች በኋላ " የቴል አቪቭ ስልከኛ ኢየ ሩሳሌምን እንድታገናኝህ አደርጋለሁ ፤ ጀኔራል " አለችው ።

" አመሰግናለሁ ። " በእንደዚህ ያለ ጊዜ ሁልጊዜም እንደሚ ደረገው ለወቀሳም ሆነ ለምክር ሁሉም ስለሚደውል መስመር ለማ ግኘት ችግር ይኖራል ።

" የኢየሩሳሌም መስመሮች በሙሉ ተይዘዋል ፤ ጌታዬ ። "



SIMIT LIBRARY

" ለመንግሥት ሥራ የምጠራው ከሩቅ ቦታ ስለሆነ በዚህ ስልክ አገናኝኝ " ብሎ የኢየሩሳሌምን የምሥጢር ቁጥር ነገራት ።

ወደዚያው ስልኩ ደወለ ።

" አቤት " አለ አንድ ድምጹ የደከመ የሚመስል ሰው እርሱነቱን ወይም ጽሕፈት ቤቱን ሳይገልጽ ። " ማን ልበል ? "

ዶብኪን የስልከኞቹን ድምጽ ሲሰማ ያ ምሽት ሥራ የበዛበት እንደነበረ አወቀ ። በድርጊቱም ደስታ ተሰማው ። " ተጠንቀቀህ ስማኝ ። ስልኩንም እንዳትዘጋው ። "

" አልዘጋም" ። ያን ቀን ማታ ጥቂቶቹ ጥሪዎች የሚያስደስቱ ቢሆኑም ብዙ ጥሪዎች ተቀብሏል ። በዚህ በጣም ተፈላጊ በሆነ ስልክ የተደወለውን ሁሉ ሳይዘጋ አስተናግዷል ።

" እኔ ጄኔራል ቤንጃሚን ዶብኪን ነኝ " ብሎ የምሥጢር ስሙንና ቁጥሩን ነገረው ።

" እሺ ጌታዬ " ብሎ አንድ መስመር ስለነካ ከቼይም ማዛር ሺን ቤት ሰዎች አንዱ በሌላው ክፍል ስልኩን አነሳ ።

" የምናገረው ከባቢሎን - ኢራቅ - ኮንኮርዱ ተገዶ ከወረደበት ነው ። "

" እሺ ጌታዬ ። "

" የምሥጢር ቁጥሬን አረጋገጥክ ? "

" አዎን ጌታዬ ። "

" ግን እስከ አሁን ጄኔራል ዶብኪን መሆኔን አላመንክም ? "

" አላመንኩም ጌታዬ ። "

" አልፈርድብህም ልጄ ። ስሜን ለይቶ ከሚያውቀው ሰው ጋር መነጋገር አለብኝ ። "

" እሺ ጌታዬ ። "

ዶብኪን ቀስ ብሎ ሳይጮኽ "የእነዚህን ጄኔራሎች ስሞች ጻፍና ከእነእርሱ አንዱ በዚያ ከአለ ስታገናኘኝ በድምጼ ያውቀኛል"አለው።

ዶብኪን የብዙ ጦር ሠራዊትና የአየር ኃይል ጄኔራሎች ስሞች ከነገረው በኋላ"ከእነዚህ ከአንዱ ጋር ብታገናኘኝ ያውቁኛል" አለው። መስመሩ አንድ ቦታ ይቆረጥብኝ ይሆን ብሎ አሰበ ።"በመስመር ላይ

ያለ ስልከኛ ቢኖር እብራይልዋ ይገባው ይሆን ? ቢሰማ ምን ያደርጋል?
አንተ ወጣት የምነግርህ ገብቶሃል ? ”

“ አዎን ጌታዬ ። ”

ስልኩን ጠልፎ ያዳምጥ የነበረ አንድ የደህንነት ሠራተኛ በስ ብሰባው ውስጥ ከነበሩት የጠቅላይ ሚኒስትሩ ረዳት መኰንኖች ለአ ንዱ በውስጥ ስልክ ነገረው ። ረዳት መኰንኑ በፍጥነት ማስታወሻ ጽፎ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰጠው ።

ቴዲ ላስኮቭ ግልጽ ያልሆነ የዳዊት ኮከብን የሚያሳዩ ከከፍተኛ የአየር እርቀት ላይ የተነሱ ስድስት ፎቶግራፎች ከቦርሳው ውስጥ አወጣ ። ነገሩ እንግዳና ግራ የሚያጋባ ነበር ። በየትኛውም መንገድ ቢሆን አሁን ወይም ቆይቶ ጥቆማው ይረጋገጣል ። እውነት ሆኖ ባይ ገኝ ውርደት እንደሚደርስበትና ምናልባትም እንደሚታሰር አውቋል ። በስብሰባው ላይ ላሉት ለእያንዳንዳቸው ሰዎቹ ባቢሎን ውስጥ መሆናቸ ውን ለማሳመን በሚያደርገው ጥረት የሚመጣውን ችግር ሁሉ መቀ በል አለበት ። ፎቶ ግራፎቹን አንድ በአንድ በጠረጴዛው ላይ አስቀ መጣቸው ። በአሻገሩ ታልማን ቆሞ ዓይኑን ተመለከተው ። ላስኮቭ ያዘነ ፣ የፈራና ነገሩ የተማታበት መሰለው ። ታልማን ግን ወደ ላስ ኮቭ ትኩር አድርጎ እየተመለከተና ራሱን እየነቀነቀ ቀጥል የሚል ምልክት በፈገግታ አሳየው ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማስታወሻውን ሳያነብ ወደ ጐን ገፋው ። “ ታዲያስ ጄኔራል ? በዚያ ላይ ያስቀመጥካቸው ምንድን ናቸው ? ኮን ኮርዱን የሚያሳዩ ከእግዚአብሔር በገብርኤል አማካኝነት ለቴዲ ላስ ኮቭ የተሰጡ ባለቀለም ፎቶግራፎች ? እስቲ አምጣቸውና እንያቸው ።”

ላስኮብ የሰማ አልመሰለም ።

ረዳት መኰንኑ ደጋግሞ በጣቱ ማስታወሻውን ስለአሳየው ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንስቶ አነበበው

ካሲምን ሲጠሩ ቤንጃሚን ሰማ ። ሴትዮዋ እንደገና ጮኸች ። በሌላው ክፍል ውስጥ የነበረ አንድ ሰው ስለሰማት ጸያፍ ነገር ተና ግሮ ሳቀ ። የተደጋገመ የመሳሪያ ጩኸት ስለሰማ ዶብኪን ብዙ ጊዜ እንደሌለው አወቀ ። በመስመሩ ላይ “ ኢየሩሳሌም ? ኢየሩሳሌም ? እስከ አሁን መስመር ላይ አለህ ? ” የሚል ድምጽ ሰማ ።

## —31—

የካፒላን አደጋ ላይ መውደቅ አጠራጣሪ ባይሆንም በተራራው ላይ ላሉት እስራኤሎች ማስጠንቀቂያ ሆናቸው ።

በተኩሱ ምክንያት አሽባሎቹ ተስፋ በመቁረጥ ሊበታተኑ ቢቃረቡም አዛገሮቻቸው ሪሽንና ሀማዲን ጨምረው ለተኩሱ አጸፋውን ሰጡ ። ካፕላን ሊሸሽ ይችል ነበር ። ግን ከንዴቱ የተነሳ ኤኬ - 47 ጠመንጃውን እያቀባበለ እስኪግል ድረስ ሳያቋርጥ በደቂቃ 200 ጥይቶች ያህል በመተኮስ ከአንድ ሺህ ያላነሱ ጥይቶች በአሸባሎቹ መስመር ላይ አዘነበባቸው ። ሆስነር ለካፕላን ጥይት ሲሰጠው ንፋግ አልነበረም።

ሪሽ ፣ ሀማዲና ሌሎች ጥቂት ሰዎች የሚተኩሰው አንድ ሰው ብቻ መሆኑን ስለአወቁ በስተጀርባው ዞረው እንዳይሰማቸው በተኩሱና በነፋሱ ድምጽ በመጠቀም ተሹለክልከው ወደ ካፕላን በመድረስ ዘለው በላዩ ላይ አረፉበት ።

የካፕላን ጩኸት በነፋሱ ኃይል ወደ ተራራው በመምጣት በአጠገባቸው በአለው ጉድባ ውስጥ እንደ አለ ዓይነት ሆኖ ለእስራኤሎቹ ተሰማቸው ። ለመሞት ብዙ ጊዜ ቢፈጅበትም ጩኸቱ ሁለት ነገሮች አስከትሏል ። አንደኛው አልበገር ባዮችን ቆራጥነታቸውን በበለጠ ሲያጠናክርላቸው የፈሪዎቹን አዕምሮ ደግሞ አናወጸው ።

ሆስነር የድምጽ ማጉሊያውን አንስቶ ጮኸ መናገር ጀመረ ። ድምጹ በነፋሱ አማካይነት ወደ ከተማው የግንብ አጥር ድረስ ተሰማ ። “ ሪሽና ሀማዲ አውሬዎች ናችሁ ። ከሰብአዊ ተግባር ውጭ የምትሠሩ መጥፎ ሰዎች ናችሁ ። ሪሽ በአገኘሁህ ጊዜ ራስህን እቆርጠዋለሁ ። ” የሆስነር ድምጽ ከመቅጠኑ ባሻገር ኃይለኛ ስሜትን የሚቀሰቅስና ከሚያስፈራው ከሞሼ ካፕላን ጩኸት ወይም ከተራራው ግርጌ ሆነው መጮኸ ከጀመሩት ቀበሮዎች ለመለየት አስቸጋሪ ነበር።

ሆስነር ራሱን መቆጣጠር እስኪያቅተው ድረስ አስጸያፊ የሆኑ ቃላትን በመጠቀም ሲጮኸ ፣ ሲያጓራና ሲያጉረመርም በነበረበት ጊዜ በተራራው ላይ የነበሩት ወንዶችና ሴቶች እርስ በእርሳቸው ተያዩ ።

አንድ ሰው - የበርግን ድምጽ የሚመስል - ከሆስነር ላይ መናገሪያውን ወስዶ ካፕላንን የሚያበረታታ ቃላት ቢናገርም ፋይዳ አልነበረውም ።

እስራኤሎቹ አቀልቁለው መተኮስ ጀመሩ ። የቀሩአቸውን በአየር ላይ እየፈነዱ ብርሃን የሚሰጡ ሰው ሠራሽ ፈንጂዎችን ቢወረውሩም በነፋሱና በአቧራው ምክንያት እንደፈለጉት አልሆኑላቸውም ።

ከአርባ ያላነሱ አሽባሎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ተራርቀው ተራ ራውን መውጣት ጀመሩ ። ነፋሱ ከኋላቸው ይገፋቸው ስለነበረ ተራራ ውን ለመውጣት ረድቷቸዋል ። አሸዋውና አቧራው እንቅስቃሴአቸው እንዳይታይ ጋርዶላቸዋል ። የነፋሱ ድምጽ ደግሞ ንግግራቸው እንዳ ይሰማ አድርጐላቸዋል ። ከአቧራው ጥቅጥቅ ማለት የተነሳ ከጠመ ንጃቸው አፈሙዝ የሚወጣው ብልጭታ እንኳን ለእስራኤሎቹ በግ ልጽ አይታያቸውም ነበር ።

እስራኤሎቹ ከመከላከያ ምሽጋቸው ሆነው ለተኩሱ አጸፋውን መስጠት ጀምረዋል ። ሆኖም በአቧራው ምክንያት መሳሪያዎቻቸው ሊሠሩ ባለመቻላቸው በስለጠኑ ቡድኖች በችኮላ ተወለወሉ ። በነፋስ ኃይል የሚመጣው አሸዋ በሁለቱም በኩል ችግር ቢፈጥርም በእስራ ኤሎቹ ላይ የባሰ ሆኖአል ።

መጥፎዎቹና አደገኞቹ ሁኔታዎች ይህ የአሁኑ መስለው ቢታ ዩም ሆስነር ፥ በርግና ሌሎቹም ይህ ሼርጂ የሚባለው ኃይለኛ ነፋስ የእስራኤሎቹን ውድቀት እንደሚያባብሰው ተገንዝበዋል ። በተጨ ማሪም መከላከያዎቻቸው እየተመናመኑ መጥተዋል ። ሰው ሠራሽ መሣሪያዎቻቸው አልቀዋል ። ከጥይቶቻቸው የቀሩአቸው ጥቂት ነበሩ። ውሃ ጥሙ በእስከተለባቸው ምክንያት የእስራኤሎቹ ውጊያ ውጤ ታማ እንዳይሆን እንቅፋት እየሆነባቸው መጣ ። የተፈጠረው የአ መ ራር አለመግባባት እስከታች ያሉት ወንዶችና ሴቶች ጭምር በሽታ የሆነባቸው መሰኋል ።

ከዚህ በተጨማሪ ብዙዎቹ አሪኤል ዌይዝማን ጭምር የምዕ ራብ ቁልቁለትና የኤፍራጥስ ወንዝ በአሽባሎቹ አልተያዘም ብለው አምነዋል ። በእርግጥ ሀማዲ ከሰይድ ታሊብ ጋር የራዲዮ ግንኙነቱ ከተቋረጠበት ደቂቃ ጀምሮ ከምሥራቅ ቁልቁለት ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ ዳርቻ አንድ ቡድን ልኳል ። ወደዚያ የተላኩት አሽባሎቹ የሚ ያፈገፍጉ ወይም የሚሸሹ እስራኤሎችን ለመያዝ በጉጉት ላይ ነበሩ ።

አሽባሎቹ እርምጃቸውን ወደፊት በቀጠሉ ቁጥር እንደ አሸዋ ብዛት ያለው ጥይት ስለነበራቸው በሩቅና ከአድማስ በላይ ጭምር ወደ እስራኤሎቹ ያለማቋረጥ ይተኩሱ ነበር ።

ሆስነር በጉብታው ላይ በአለው የእዝ ቦታ ላይ ከበርግ ጋር ቆሟል ። በመጠኑም ቢሆን ሆስነር ቀዝቀዝ ብሎ ስለነበረ በርግ ደህና ነው ብሎ አስቧል ። በርግ በፈጠረበት ብስጭት ምክንያት ሚሪያም በርንስቴይንን ልዩ መልዕክተኛውና ረዳቱ ሆና እንድትሠራ ጠየቃት ። በመሠረቱ ሚሪያምና ኤሸር እስከ አሁን በቁጥጥር ስር ነበሩ ። ነገር ግን ሆስነር

ከአዘዘ የሚቃወም አንድም አልነበረም ። ሚሪያም ስለካፕላንም ሆነ በድምጽ ማጉሊያ ስለተናገረው አላነሳችም ።

ሆስነር ጮክ ብሎ " ጥይታችን ወደማለቁ በሚቃረብበት ጊዜ ከሰዎቻችን ጥቂቶቹ ወደ ምዕራብ ቁልቁለት መርጥ አለባቸው " ብሎ ተናገረ ።

በርግ ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ " በዚያ በኩል የሚጠባበቁ አሽ ባሎች እንዳሉ እርግጠኛ ነኝ ። ስለዚህ ሰዎቻችን የጨበጣ ውጊያ ለማድረግ እንዲዘጋጁ በድጋሚ ትዕዛዝ ማስተላለፍ አለብን " አለው።

" ወታደሮች አይደሉም " ብሎ ሆስነር አስታወሰው ። " በመ ጨረሻ ተፈጥሮአቸው እንዲያደርጉ የሚነግራቸውን ማንኛውንም ያደርጋሉ ። " ቀጥሎም ድምጹን ዝቅ አድርጎ " ጥቂቶቹ ሕይወታ ቸውን ለማሳለፍ ወስነዋል ። - - - በካፕላን ላይ የደረሰውን ከአዩ በኋላ ራስን ማጥፋት የተሻለ መስሎ ታይቷቸዋል - - - ለዚህም አል ወቅሳቸውም - - - " አለው ።

በትንሹ ጉብታ ላይ ረጅም ጸጥታ ሰፈነ ። እንደሰንደቅ ዓላማ ሰቅለውት የነበረው ምልክታቸው አሁንም በኃይለኛው ነፋስ ውስጥ እንደቆመ ቢሆንም በላዩ ላይ የነበረውን ስዕል ቡናማው አቧራ ሸፍ ኖታል ።

ሚሪያም አንድ ነገር አጉተምትማ ዝም አለች ።

" ምንድን ነው ? " ብሎ ሆስነር ጠየቃት ።

" . . . ጥያቶቻችን ሳያልቁና አሽባሎቹም በምሥራቅ ቁልቁ ለት በኩል በእርቀት ላይ እንዳሉ ሳንበታተን በመጠናከር ተራራውን አቋርጠን በፍጥነት ወደ ምዕራብ ቁልቁለት መሄድ ይገባናል ። ብየ እገምታለሁ ። ምንም ዓይነት ትንሽ ኃይል በወንዙ ዳር ይኑራ ቸው ሰብረን መሄድ መቻል አለብን ። በጨለማው ውስጥ በውሃው ላይ እየዋኘን መሄድ እንችላለን " አለችው ።

ሆስነርና በርግ በመጀመሪያ እርስ በእርሳቸው ቀጥሎም ለትንሽ ሴኮንዶች ሚሪያምን ተመለከቷት ።

ሆስነር "ቁስለኞቹን የረሳሻቸው አይመስልሽም ?" ብሎ ጠየቃት።

" እነርሱ የበረራ ሥርዓትን እንዳልተከተለ አውሮፕላን ሥርዓ ዓትን ተከትለው ወደኋላ ሲያፈገፍጉ እንደጠፉ ዓይነት ይቆጠራሉ ። ለብዙሃኑ ኃላፊነት አለብን ። "

በርግ " ያመጣሽው ሃሳብ የተለያየ ስለሆነ የትኛውን እንከተል " አላት ።

" ከእኔ የሚመነጨው ሁሉ በጣም መጥፎ ሆኖ የሚታየው ለምን ድን ነው ? " ብላ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ጠየቀችው ። " ይሆናል፣ አይሆንም ብለህ ታስባለህ ?" ብላ ለትንሽ ጊዜ ንግግርዋን ቆም ከአ ደረገች በኋላ " ለማንኛውም እኔና ሌሎች በራሳቸው ፍላጐት ፈቃ ደኞች የሆኑ ሰዎች ቁስለኞቹን ለመንከባከብ እንቆያለን ። በመሠረቱ በሞት ፍርድ ለመቀጣት የተዘጋጀሁ ነኝ ፣ አይደለሁም እንዴ ? " አለችው ።

ሆስነር ራሱን በአሉታ አወዛወዘ ። " ጠንካራ ውሳኔዎች በምትወ ስድበት ጊዜ እንኳን ታለሳልሽዋለሽ ። በጣም ከባድ ግን - በሥርዓ ትም ሆነ ሥርዓት ባልተከተለ ሁኔታ ብናፈገፍግ - ወይም መጥተ ውብን በጨበጣ ብንዋጋ - አስቀድመን ቁስለኞቹን መግደል አለ ብን ። " እጁን ከፍ አድርጐ ቆይ አንድ ጊዜ ታገሽ ። " ቂል አትሁኝ ሚሪያም ። ካጥላንን ምን እንደአደረጉት ሰምተሻል ። በደቦራ ጌዲዮን ላይ የፈጸሙትን እግዚአብሔር ያውቃል ። "

" ለማፈግፈግ ወይም እጅ ለመስጠት ትዕዛዝ አልሰጥም ካልከ ወይም ራስን በራስ ለመግደል የሚወሰደውን ውሳኔ ለመገፋፋት ከአል ፈለግህ ምርጫዎቻችን ምንድንናቸው ? መጨረሻችንስ ምን ይሆ ናል " ብላ ሚሪያም ጠየቀችው ።

ሆስነር ፊቱን ከእርስዋ አዙሮ " አላውቅም " አላት። " ሊያድነን የሚችል ኃይል ከውጭ ከአልደረሰልን ፣ እያንዳንዱ ወንድ ወይም ሴት በጦርነቱ እየተዋጉ መሞት እጅግ በጣም የተሻለው ፍጻሜ ይሆ ናል ብየ አስባለሁ ። ይሁን እንጂ የሚማረኩና እጅ የሚሰጡ ስለሚ ኖሩ ከላይ ያልኩት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ አይሆንም ። ራስን በራስ ማጥፋትና መግደልም ይኖራል ። "

መልስ የሰጠው የለም ። ጦርነቱ የመጨረሻ ፍልሚያ የሚደ ረግበት ነው ። ሁለቱም ወገኖች ደክመዋል ። ሁለቱም ወገኖች ይህ የመጨረሻው ውጊያ እንደሚሆን ገምተዋል ። እያንዳንዱ የሚንቀሳ ቀሰው ብርታት አልባ ሆኖ በአልሞትባይ ተጋዳይነት ነው ።

አሸባሪዎቹ ከ300 - 400 ሜትር እርቀት ላይ ሆነው የእስራኤሎቹ ኃይል እንዲደክምና እንዲቀንስ ለማድረግና እጅግ በጣም ደካማ የሆ ነውን የእስራኤሎቹን ክፍል ለማግኘት እየሞከሩ ነበሩ ።

ለመንጋት ከሦስት ሰዓት በላይ ይቀራል ። ነፋሱ አቋርጠ አጟ ራው በመሬት ላይ ካላረፈ በስተቀር ብርሃን በመሬቱ ላይ የሚፈነጥ ቅበት ሰዓት ሊዘገይ ይችላል ።

ድርጊቱ የማዳከም ጦርነት ይመስላል ። ምንም እንኳን በሰው ኃይል ፣ በጠመንጃ ፣ ብዛት በአለው ጥይት ፣ በምግብ ፣ በሕክምና ፣ በውሃ ብልጫ ቢኖራቸውም አሸባሪዎቹ የሚያገኙት ውጤት ብዙ አይ ሆንም ። ሊያደርጉ የሚችሉት እስራኤሎቹ ጥይቶቻቸውን መጨረ ሳቸውን እርግጠኛ እስኪሆኑ ድረስ አድፍጠው ተኩሳቸውን መቀ ጠል ነበር ። እንደ አሻባሪዎቹ አስተሳሰብ እስራኤሎቹ ጥይቶቻቸውን በቁጠባ ቢይዙ እንኳን እስኪነጋ ድረስ አያቆያቸውም የሚል ነበር ።

በርግ በአዕምሮው ውስጥ ብዙ አሳቦች አወጣ አወረደ - አሁን መሸሽ ይሻል ይሆን ? የአጸፋ ውጊያ ማድረግ ? እስከ መጨረሻው ጠብቆ የጨበጣ ውጊያ ማድረግ ? ቁስለኞቹን መግደል ? ሆስነርን መግደል በመጨረሻው ሰዓት የሚያድን ኃይል ይደርስላቸው ይሆን ? ይኸኛው እንኳን አይመስልም ። ዶብኪን ምን አጋጥሞት ይሆን ?

ሆስነር ዞር የኡማ መንደር አቅጣጫ ይሆናል ብሎ ወደገመተው ወደ ደቡብ ምዕራብ ተመለከተ ። ከዶብኪን ጋር ግንኙነት እንደሚ ያደርግ ዓይነት ሆኖ በአርምሞ አብላላ ። እንደገና ወደ ደቡብ ዞሮ ወደ ኢሽታር በር አቅጣጫ ከተመለከተ በኋላ “ ደህና ነው የሚል ስሜት አድሮብኛል ” አለው ።

በርግ “ መልካም ” ከአለው በኋላ “ በተአምር ባለሥልጣን አግኝቶ አሁን ሊነጋገር ቢችልም በሰዓቱ እርዳታ ይደርስልናል ብየ የማምን አለመሆኔን እነግርሃለሁ ” አለው ። የተናገረው ለማጠናከ ሪያ አስመስሎ ወደ ሆስነር ተመለከተ ። አባባሉ ግን የሆስነርን ሃሳብ ለመቃረን ነበር ።

ሆስነር ጀርባውን ወደ ነፋሱ አዙሮ ወደ ምዕራብ ተመለከተ ። ወደማይታየው አድማስ እያመለከተ “ ቴዲ ላስኮቭ እንደ ቃሉ ጥሩ ይሆናል ብየ አስባለሁ - ከተዋጊ አውሮፕላኖቹ ጋር መጥቶ እኛን ለማግኘት እየተቃረበ ነው . . . ”

ሆስነር እጆቹን በደረቱ ላይ አጣምሮ ይዞ “ እየው በርግ በቴል አቪቭና በኢየሩሳሌም ውስጥ ያሉ ሰዎቻችን ጣቶቻቸውን ወደሰማይ እየቀሰሩ አርፈው ይቀመጣሉ የሚል ሃሳብ አልቀበልም ። ከእነእርሱ በጣም የበለጠ ነገር እጠብቃለሁ ። ምናልባትም በጣም ብዙ እጠብቅ ይሆናል ። እኔም ከእነዚያ ብልሆች አንዱ ነበርኩ ። ነገሮችንም እንዴት እንደማመሰቃቅላቸው ተመልከት ፣ ይስሐቅ ። እነእርሱም የጥቂት ቀኖች እረፍት ለመውሰድ መብት አላቸው ” አለው ::

በርግ ሳቁን አፍኖ ማስቀረት አልቻለም ። " ዛሬ አይደለም ።" ሆስነር የሚያመጣ ው ምክንያት ባጠራጠረው ቁጥር የመገረም ሁኔታ በፊቱ ላይ ይታይ ነበር ።

አንዲት መልክተኛ እየሮጠች ስለመጣች በርግ ሊገናኛት ወደ እርስዋ ተራመደ ።

ሚሪያም ጥቂት ሜትሮች ራቅ ብላ የሆስነርንና የበርግን ንግግር በጸጥታ አዳምጣለች ። ወደ ሆስነር ጐን መጥታ ክንዱን አጥብቃ ያዘ ችው ። ቀደም ብላ ስለቴዲ ላስኮቭ አሰበች ። እያደር ስለእርሱ የምታ ስበውን እየቀነሰች መጣች ። አደጋው ከደረሰ በኋላ ሆስነር እንዳለው በትልቁ አውሮፕላን መጥቶ እርስዋን . . . ሌሎቹንም ሲያድናቸው በሃሳቧ ታያት ። በእርግጥ ምናልባትም ሽንፈት እንደደረሰበት ታው ቃለች ። ለዚህም በከፊልም ቢሆን ኃላፊነት እንዳለበት ተረድታለች ። በመጀመሪያ በእርሱ ላይ ያደረገችው ተጽዕኖና እርሱ በአየር ላይ የሚፈጽመው ሥራ ያለውን ግንኙነት መቀበል አቅቷት ነበር ። ነገር ግን ሁለቱንም ለሚያውቃቸው ሰው ግንኙነቱ ግልጽ ነበር ። በመጀ መሪያ ይህን ሐቅ ተቀበለች ። ቀጥላም ብዙ እውነትነት ያላቸውን ነገሮች ለመቀበል ተገደደች ።

ሆስነር ከማንም የበለጠ ሐቅን እንድታውቅ አደረጋት ። ሌሎች ሰዎች እርስዋን ለማስደሰት ወይም በከንቱ ውዳሴ ለመደለል የምት ናገረውን ሁሉ ይቀበሏት ነበር ። እርስዋም የምትወደው የዚያ ዓይነት ሰው ነበር ። መነጽር ያደረጉ ቀጭን ሰዎች ለአውደ ጥናትም ሆነ ለጋራ ስብሰባዎች በአጠገብዋ ተቀምጠው የሆነ ያልሆነውንና ከሰው የሰሙ ትን ራሳቸው የሠሩት ወይም የፈጠሩት አድርገው የሚያወሩትን ታቀ ርባቸዋለች ።

ላስኮቭና ባልዋ ከብዙ ሰዎች የተለዩ ነበሩ ። ሁለቱ ሰዎች ተመ ሳሳይነት ስለነበራቸው ወግ አጥባቂዎች ዓይነት አድርጋ በመንፈስዋ ቀርጻቸዋለች ። ሆስነር ደግሞ ሌላው በጣም የባሰ ወግ አጥባቂ ነበር ። በባቢሎን ውስጥ ሆና ስለዓለም ያላትን አስተሳሰብ ሳትለውጥ መቆ የት ትችል ነበር ። ነገር ግን ሆስነር ዓይኖቿ እንዲከፈቱ አደረገ ። ይሁን እንጂ ያየችውን አልወደደችውም ። ነገር ግን ቁስለኞቹን መግ ደል ወይም አለመግደል የሚያስከትለውን ጥቅምና ጉዳት አመዛዝና እንድታይ አደረጋት ። ያ ጥሩ ወይስ መጥፎ ነበር ! ሁለቱም ነበር ።

" ቴዲ ላስኮቭን በደንብ ታውቀዋለህ ? " ብላ ሆስነርን ጠየ ቀችው ።

" ይህን ያህልም አላውቀውም ። ብቻ አልፎ አልፎ እንገናኛለን።

በአዎንታ ራስዋን ነቀነቀች ። ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ በማቅ ማማት " ትወደዋለህ ? " ብላ ጠየቀችው ።

" ማን ? ላስኮቩን ማለትሽ ነው ? ይመስለኛል ። ከአንቺ ይልቅ ስለፖለቲካ ከእርሱ ጋር መወያየት በጣም ቀላል ነው ።"

በጨለማው ውስጥ ፈገግ አለች ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ " አንተን አስታወስኝ " አለችው ።

" ማን ? ላስኮቭ ? ነው ? "

ክንዱን አጥብቃ ይዛ " ይህ ሁሉ የእርሱ ስህተት መሆኑን እንደ ሚያስብ እርግጠኛ ነኝ " አለችው ።

" መልካም ፤ ሁለታችንም የጋራ የሆነ አስተሳሰብ አለን ። "

" ሁለታችሁም ጥሩም ሆነ መጥፎ የሚመጣው ከድርጊታችን ነው ብላችሁ ታምናላችሁ ። "

" አይደለም እንዴ ? "

በድንገት " ቴዲ ላስኮብና እኔ ፍቅረኞች ነበርን " አለችው ።

በርግ ወደ ጉብታው ሲመለስ በጨረፍታ ሰማት ። እዚያ በመገ ኘትዋ ተበሳጭቷል ። አሁን ደግሞ ይህን ጨመረችበት ። ነገሩም ከሚ ችለው በላይ ሆነበት ። ጀርባውን ወደ እነእርሱ አዞሮ ትቶአቸው ሔደ።

" እንደገና ትፋቀራላችሁ " አላት ሆስነር ።

" አይመስለኝም ። "

" ጥያቄው በዚህ ሰዓት ሊነሳ የሚገባው አይደለም ፡ ሚሪያም" ሲላት በድምጹ ትዕግሥቱ እየተሟጠጠ እንደነበረ ያስታውቅ ነበር ።

" አንተ — አይደለህም ? "

" አይደለሁም ፤ ስሚ ፤ ወደ ኮንኮርዱ ሔደሽ ቤከር ስለራዲዮኑ ምን እያደረገ እንደሆነ እዩ ። ሪፖርት የሚደረግ ከሌለ - አይኖርምም- በዚያው ቆዪ ። "

" ለምን ? "

" እዚያው ቆዪ ። ለአንቺም ሆነ ለሌላ ሰው ትዕዛዜን ገልጨ መንገር የለብኝም ። "

አንድ እርምጃ ተራምዳ በመዞር " ሁለተኛ አላይህም ፤ አይህ ይሆን ? " አለችው ።

" ታይኛለሽ ። ለዚህም እርግጠኛ ነኝ ። "

ከተመለከተችው በኋላ “ እንደገና አላይህም ” አለችው በድ ጋሚ ። ምን እንደሚላት አላወቀም ።

ራሱን አፈፍ አድርጋ በመያዝና በማስጐንበስ ሳመችው ።

እጅዋን ይዞ እንድትለቀው ካደረገ በኋላ ረጋ ባለ አነጋገር “ ከአ ውሮፕላኑ አጠገብ እርቀሽ እንዳትሔጂ ፣ የፈለገው ቢመጣ ላለመ ሔድ ቃል ግቢልኝ ” አላት ።

“ እንደገና አይህ ይሆን ? ”

“ አዎን ። ”

ለጥቂት ጊዜ ቆመው እርስ በእርሳቸው ተያዩ ። ተንጠራርታ ፊቱን ከነካች በኋላ በፍጥነት ዞራ በጨለማው ውስጥ ሔደች ።

ሆስነር ከዓይናቹ እስክትሰወር ድረስ ተመለከታት ።

በጉሮሮው ውስጥ የተጠራቀመውን አሸዋ ኡሁና እክ ብሎ ከአ ወጣ በኋላ ዓይኖቹን እያሻሸ በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ መለኮታዊ ትርጉም ወይም መልዕክት ይኖር እንደሆነ ፣ ሊማሩት የሚገባ ጠቃሚ ትም ህርት እንዳለ ለይቶ ማሰብ አልቻለም ። ጀግንነትና ፍርሃት ፣ ራስን ወዳድነትና ለሌላው አሳቢነት ፣ ብልሃትና ጅልነት ፣ ምሕረትና ግፈ ኛነት የሰው ልጅ የሚመጻደቅባቸው የቀድሞ ባሕርያት ነበሩ ። የሚ ለያዩት በተግባር በሚጠቀሙባቸው ተዋንያን ብቻ ነበር ። በመጨ ረሻ የሚደርስባቸው ጥሩም ሆነ መጥፎ ነገር ሁሉ አስቀድሞ የተወ ሰነ መሆኑ እየታወቀ ሥቃያቸውን ለማራዘም እግዚአብሔር ለምን ብልሃትንና ኃይልን ሰጣቸው ? ሆስነር በዚህ ሰውነትን የሚያዝናና ስሜት እንደገና ተወጥሮ እንዳለ በመሃሉ ውስጣዊ ስሜትን የሚበረ ብር ቀልድ ተወረወረበት ። ወደ በርግ ዞሮ ከጠራው በኋላ “ ሲጋራ ላለማጤስ ለአባቴ ቃል ኪዳን የገባሁትን ባለመፈጸሜ እግዚአብሔር በዚህ እንድቀጣ አደረገኝ ” ብሎ ነገረው ። ቀጥሎም ሆስነር ወደ ነፋሱ ሳቀ ።

በርግ እጁን ወደ ኪሱ አስገብቶ ሽጉጡን ዳበሰ ።

## —32—

“ በመስመር ላይ አለህ ፣ ኢየሩሳሌም ? ”

“ አለሁ ጄኔራል ፣ ጠብቅ ” አለው ተረኛው ስልከኛ ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለብዙ ሴኮንዶች በእርሳሱ ጫፍ ጠረጴዛውን ቆርቁሮ ማስታወሻውን ከተመለከተ በኋላ ቀና አለ ። “ ብዙዎቻ

ችሁ የጄኔራል ዶብኪንን ድምጽ ብትሰሙ ታውቁታላችሁ ብየ እገምታለሁ ” አላቸው የአደረበትን ከፍተኛ ስሜት ለመቆጣጠር እየሞከረ ።

ሁሉም የጥያቄዎችና የአንክሮ ድምጽ በጩኸት አሰምተው ቆሙ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጸጥታ እንዲሰፍን ጠረጴዛውን ደበደበ ። “ ጸጥ ብላችሁ በጥንቃቄ አድምጡ ” ካላቸው በኋላ ስልኩን ለሚያገናኘው ሰው ምልክት ስለሰጠው በስብሰባው አዳራሽ ውስጥ በተቀመጡት የድምጽ ማጉሊያዎች ሁሉም ማዳመጥ ጀመሩ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልኩን ተጭኖ “ ማን ልበል ? ” አለው ።

ዶብኪን በመጠኑም ቢሆን ለውጥ ያለውን ድምጽ በአንድ ጊዜ አወቀው ። ዶብኪን ለሴኮንድ ያህል ስሜቱ ቢንቀጠቀጥም ሰውነቱን በመቆጣጠርና ራሱን በማረጋጋት “ ይህ ጄኔራል ቤንጃሚን ዶብኪን ነው ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ” ብሎት ትንሽ ቆም ካደረገ በኋላ “ ድምጼን አወቅኸው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ አላወኩትም ። ” ይሁን እንጂ በክፍሉ ውስጥ ድምጹን የሚያውቁ እንዳሉ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ግልጽ ነበር ።

ዶብኪን ድምጹን ግልጽ ለማድረግ የሚችለውን ጥረት አድርጓል ። “ የእኔን ድምጽ ሊያውቅ የሚችል ሰው በዚያ አካባቢ አለ ?”

“ ይኖራል ብለህ ተስፋ አድርግ ” ብሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዙሪያውን ሲመለከት ጥቂት ራሶች የአዎንታ ንቅናቄዎች ሲያደርጉ ተመለከታቸው ።

“ ቀጥል ጄኔራል ” አለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ። አሁንም መቶ በመቶ እርሱ ይሆናል ብሎ ባያምንም በከፍተኛ ጉጉት “ የምትደውለው የት ሆነህ ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ቴዲ ላስኮቭ ያመጣቸውን ፎቶግራራፎች በእጁ አጥብቆ ይዞ ቀስ አድርጎ ወደ ቦርሳው ለማስገባት ወሰዳቸው ።

በመናገሪያው ላይ “ ባቢሎን ” አለ ድምጹ ።

ክፍሉ በአድናቆት ከመሞላቱም በላይ ብዙ ራሶች ወደ ላስኮቭና ታልማን ዞሩ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጸጥታ እንዲጠበቅ ጠረጴዛውን ደጋግሞ መታ ። እንደገና ጮክ ብሎ “ የደወልከው የት ሆነህ ነው፡ ጄኔራል ? ስልክ የምትደውለው ማለቴ ነው ? ነጻ ነህ ወይ ? ”

“ አዎን ፡ ነጻ ነኝ ። የምደውለው በቤተ መዘክሩ አቅራቢያ ካለው የእንግዳ መቀበያ ቤት ውስጥ ሆኜ ነው ። “ ዶብኪን ድምጹን ለመቆጣጠር ቢሞክርም በመጠኑ ተለዋወጠበት ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩም ረጋ ብሎ ለመናገር ቢሞክርም ድምጹ ተለዋወጠ ። “ አዎን ፣ እሺ ፤ በምን ሁኔታ ላይ እንዳላችሁ ልትነግ ረኝ ትችላለህ ፤ ጄኔራል ? ምን አጋጥሟችኋል ? ”

የካቢኔ ሚኒስትሮችና ዋና ዋና የጦር ኃይል ሰዎች በሙሉ እያዳ መጡት እንደነበረ ዶብኪን ገብቶታል ። በሜዲትራንያን ባሕር ላይ ከጠፉበት ጊዜ ጀምሮ ያጋጠማቸውን ሁሉ በአጭሩ አስረዳቸው ።

ከስድስት የበለጡ ረዳት መኰንኖች ስለባቢሎን አካባቢ ፣ ከፍታ፣ ጧትና ማታ ስለሚኖረው የአየር ሁኔታ የሚያሳዩ የወታደር ካርታዎች ከአዳራሹ ውስጥና ከውጭም ከማጠናቀራቸውም በላይ ላስኮቭ ስለ ባቢሎን መናገር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የተጠናቀሩ ከመቶ የሚበ ልጡ ማስረጃዎችን ሰበሰቡ ። የመጨረሻ እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት እነዚህ ሁሉ በጥንቃቄ አንድ በአንድ መታየት አለባቸው ።

ዶብኪን ስልክ በሚነጋገርበት ጊዜ ወንዶችና ሴቶች መተላለ ፊያው ላይ ወዲያና ወዲህ ሲሔዱ ሰማቸው ። ምናልባትም ለመራ መድ የሚችሉ ቁስለኞች ይሆናሉ ። የመተላለፊያው መዝጊያ ተከፍቶ እንደገና ተዘጋ ። በሌላው ክፍል ውስጥ የነበሩት ሰዎች የካርታ ጨዋታ ቸውን ስለጨረሱ ራዲዮ ከፈቱ ። አንዲት ድምፀ ጉርናና ሴት የአረ ብኛ ዘፈን ታሰማ ስለነበረች በተጨማሪ ጥቂት አሽባሎች ወደ ክፍሉ ገብተው ማዳመጥ ጀመሩ ። የዘፈኑ ድምጽ ቢያስቸግረውም እንኳን ሰፆ ቹ ምናልባት በመዝጊያው አጠገብ ቢቀመጡ ሲነጋገር እንዳይ ሰሙት ረድቶታል ።

“ ምን ሃሳብ ትሰጠናለህ ፣ ጄኔራል ? ”

ዶብኪን የጄኔራል ጉርን ድምጽ በአንድ ጊዜ ኗወቀው ። “ ሃሳብ? የምሰጥህ ሃሳብ ጄኔራል ጉር በፍጥነት መጥታችሁ ከዚህ ሲኦል ውስጥ እንድታወጡን ነው ። ”

“ በምዕራብ ዳርቻ በኩል ያለው ጭቃማ ሜዳ እንዴት ነው ?” ብሎ የአየር ኃይል ጄኔራል ካዚር ጠየቀው ።

“ አሁንም እርጥብ ነው ። ነገር ግን ከወንዙ እየራቅህ በሔድህ ቁጥር ደረቅ ይመስላል ” አለው ዶብኪን ።

ያረፉችሁበት መንገድ ( ሜዳ ) ሲ-130 አውሮፕላን ማቆም ይችላል ብለህ ታስባለህ ? ” አለው ጄኔራል ካዚር ።

“ ያን ማለት አልችልም ፣ ጄኔራል ። እንደሚመስለኝ ለማረፍ በሞከርንበት ጊዜ ተሸረካክቷል ። ”

“ በሔሊኮፕተር መጠቀም እንችላለን ? ” አለ አንድ ያልታወቀ ድምፅ ።

“ አይቻልም ፤ እየወጉን ስለሆነ ጊዜ አይኖርም ። ”

ሌላ ሰው ተዋጊ አውሮፕላኖች ስለመላክ ተናገረ ። ዶብኪን ብዙ ሰዎች በድምጽ ማጉሊያው ሲነጋገሩ ሰማቸው ። የቴዲ ላስኮቭ ስምም ሲነሳ ሰማ ። በአሁኑ ጊዜ በጡረታ ከሥራው የተገለለ ቢመስለውም በስብሰባው ላይ ተገኝቷል ። የጋለውን ክርክር እያዳመጠ ዶብኪን ለጥቂት ጥያቄዎች መልስ ሰጠ ። በድንገት አቋርጦ “ ጠቅላይ ሚኒስትር መዘጋት አለብኝ ። ኤኬ - 47 ጠመንጃዎች የያዙ ሦስት ሰዎች እዚህ አሉ ። ምን እያደረግሁ እንደ ሆነ ከተረዱ ያለጥርጥር ስልኩን እንድዘጋ ያድርጉኛል ” አለው ።

በኢየሩሳሌም በስብሰባው ላይ የነበሩት ሰዎች ግብግብ የመያያዝ ቀጥሎም የጠመንጃ ተኩስ የሚመስል ፣ ወይም ምናልባትም የአንድ ነገር መሰበር ድምጽ ሰሙ ። በመጨረሻም ስልኩ ተቋረጠ ።

* * *

ሚሪያም በርንስቴይን በአውሮፕላኑ ነጂ ክፍል በዴቪድ ቤከር ጐን ተቀምጣ “ የሕይወት አዳኝ የሆኑ ሰዎች ስለእኛ የሰሙ አሉ ብለህ ታስባለህ ? ”ብላ ጠየቀችው ።

“ አላስብም ” ብሏት የራዲዮኑን ድምጽ ዝቅ አደረገው ። “ሌየሩ አሁንም በመብረር ላይ ነው ። ግን ችግር ያጋጠመው ይመስለኛል” አላት ።

“ ለምን ? ”

“ ለምን ? ” ብሎ ጥያቄዋን በጥያቄ መለሰላት ። ሆስነር ሪፖርት ለማግኘት ራሱ ሳይመጣ ሰው የላከው ፤ እያንዳንዱ ሰው ቤከር ያደርገው የነበረው ሙከራ ውጤታማ ይሆናል ብሎ የሚያስብ ስለሌለ ነው ። ይሁን እንጂ ሚሪያም በርንስቴይን የትራንስፖርት ምክትል ሚኒስትሪት በመሆንዋ የሆስነርና የቤከር አለቃ ነበረች ። ነገር ግን ይህ ማንንም አላስጨነቀም ። “ ለምን ? ምክንያቱም በዚህ አቧራ ውስጥ ማረፍ አይችልም ። ምክንያቱ ይኸው ነው ። ኃይለኛ የአቧራ ከምችት ወደሌለበት ሔዶ በማረፍ ነዳጅ መሙላት አለበት ። ምናልባት ያን ጊዜ አግኝቼ መነጋገር እችል ይሆናል ። ” ከጐን በኩል እየተመለከታት “ ሪፖርት ለማቅረብ መሔድ ትፈልጊያለሽ ? ያለኝ ይኸው የነገርኩሽ ብቻ ነው ” አላት ።

“ በኋላ ” ብላው በተሰነጣጠቀው መስታወት መካከል ወደ ውጭ እየተመለከተች “ ለመሞት ትፈራለህ ? ” ብላ በድንገት ጠየቀችው ።

ዞሮ ተመለከታት ። ከእርስዋ ዓይነት ጭምት ሴት የዚህ ዓይነት ጥያቄ አልጠበቀም ነበር ። “ አልፈራም ፡ እፈራለሁ ብየም አላስ ብም ። እኔ . . . እኔ የምፈራው እንደገና መብረር ነው ፡ መሞት ግን አልፈራም ። ነገሩ የሚያስገርም ነው ። ” እንደዚህ አቅርቦ ለምን እንዳጫወታት ሊገባው አልቻለም ። “ እና አንቺስ ? ” ብሎ ጠየ ቃት ።

“ በቅርብ የማውቃቸው አብዛኞቹ ሞተዋል ” በማለት የንግ ግራቸውን አርዕስት ከለወጠች በኋላ “ ስለያዕቆብ ሆስነር ምን ታስ ባለህ ? ” ብላ ጠየቀችው ።

በማስታወሻው ላይ መጻፉን አቋርጦ ቀና ብሎ ተመለከታት ። ሆስነርና በርንስቴይን በጣም የቀረበ ግንኙነት አላቸው የሚል ጥር ጣሬ አድሮበታል ። ነገር ግን ይህ በግልም ሆነ በሕዝብ ፊት ስለያዕ ቆብ ሆስነር ያለውን ሃሳብ ስለአለወጠው “ ናዚ ነው ” አላት ።

“ አንተን ይወድሃል ። ”

ቢከር ውይያ ቱ ለምን እንደተጀመረ ወይም ወዴት እንደሚያመራ አልገባውም ። በርንስቴይን በጣም ቢደክማትም ማውራት ፈልጋ ለች ። ሰዎች በፊታቸው ላይ ሞት ሲደቀንባቸው የሚያስቁ ነገሮች ይሠራሉ ። ለመብረር እንደሚፈራ አምኗል ። ይህን ግን ለአዕምሮ ሐኪሙ አይናገርም ። “ የተሳሳተ አመለካከት አትውሰጂ ፡ በርንስቴ ይን ። ሆስነር ከእኛ ጋር በመሆኑና በመገኘቱ ደስ ብሎኛል ። እርሱ ባይኖር ኖሮ እስከ አሁን ድረስ ነገሮች ተመሰቃቅለው ውላቸው ይጠፋ ነበር ” ካለች በኋላ ተመለከታት ። የደከመች አልመሰለች ም ። ደስተኛና ስሜቷ የነቃ ትመስላለች ። አጐንብሶ በማስታወሻው ላይ መጻፉን ቀጠለ ።

“ በፍቅሩ ሰንሰለት ተይዣለሁ ። ”

ቢከር የእርሳሱ ጫፍ ተሰበረበት ። ተኩሱ እየጨመረ ስለመጣ ቢከር ቀና ብሎ በመስታወቱ መካከል ወደ ውጭ ሲመለከት ሌሊቱ የበለጠ አስፈሪ ፡ የበለጠ አስከፊና መጥፎ ገጽ የሚኖረው መስሎ ታየው ።

በአውሮፕላኑ ክፍል ውስጥ ሆኖ በመስኮቱ መስታዎት መካ ከል ወደ ውጭ ሲመለከት ጨለማው ከቀድሞው የበለጠ አስፈሪ ፡ የበለጠ መጥፎና የባሰ አደጋ መስሎ ታየው ። ቀድሞ አስፈሪ ሆነው በመስታዎት ውስጥ ያያቸው ነገሮች ሁሉ አሁን በሚያይበት መስታ ዎት ውስጥ ፍርሃት ፣ አደጋና ሞት ታዩት ። በመኪና ወይም በቤት

መስኮት መስታዎት ለምን ሆዱን ባር ባር ይለው እንደነበር እስከ አሁን ድረስ ልብ አድርጐ አላጤነውም ነበር ። አሁን ግን ለምን እንደነበረ ቢያውቀውም በመጠኑም ቢሆን ዘግይቷል ። " አሀ ፤ ያ ነበር . . . እኔ . . . ነኝ ። "

" ምንድን ነው የምትጽፊው . . . . ዴቪድ . . . ብየ . . . ልጥራው?"

" አዎን ፤ በእርግጥ " ብሎ ማስታወሻውን ከዘጋ በኋላ " ስለ ጉዞአችን ነው " አላት ።

ወደ እርሱ ጐብደድ ብላ " ማስታወሻ ? የሆነውን ሁሉ አንድ በአንድ እየጻፍክ ነው ማለት ነው ? " ብላ ጠየቀችው ።

" ዋና ዋናውን ለመክተብ ሞክሬአለሁ ። "

" ላየው እችላለሁ ? " ብላ እጅዋን ስለዘረጋች ሰጣት ። ጐንበስ ካለችበት ቀና ብላ በመቀመጥ ገጾቹን አልፋ አልፋ እያገላበጠች ተመ ለከተች - " 16:02 ሰዓት አውሮፕላኑ ተነሳ ፤ ጄኔራል ላስኮቭ በራዳር እንደሚከታተለን ፤ በመሣሪያ ለመጠቀም ውሳኔው የራሳችን እንደ ሚሆንና አጃቢ አውሮፕላኖች እንደሚመለሱ መልዕክት አስተላለ ፈልን " የሚለውን ከአነበበች በኋላ ሌሎች ገጾችን ስታገላብጥ - " 18:31 አውሮፕላኑ ቆመ ፤ ሔስ የኮንኮርዱን መስታወት ሠብሮ የገባ ድንጋይ ራሱን ስለመታው ሞተ . . . " ብሎ የጻፋቸውን ከተመ ለከተች በኋላ ማስታወሻውን ዘግታ ቀና ብላ አየችው ። ራስዋን አስገ ድዳ ፈገግ በማለት የመጽሐፍ ቅዱስ ሕዝብ ብለው ጠርተውናል ። እንደዚሁም አፍቃሪያን መጽሐፍ ብለውም ጠርተውናል ። የተ ጻፈው ቃል በዓለም ላይ ከተበታተንን ጀምሮ በአንድነት ተሳስ ረን እንድንቆይ አድርጐናል ። ከአንተ በስተቀር ሌላ ሰው በዚህ የተደረገውን በዝርዝር ለመጻፍ አለመሞከሩ ያስገርማል " አለችው ።

" መልካም . . . " ብሎ ቤከር የሲጋራ ቁራጭ ስለአገኘ ከአቀ ጣጠለ በኋላ " ድርጊቶቹን አንድ በአንድ ይዟል ለማለት እንኳን ያስ ቸግራል ፤ በርንስቴይን " ብሎ ለትንሽ ጊዜ ካቅማማ በኋላ " ሚሪ ያም ለ - ሥራዬ ነው " አላት ።

" ነገር ግን ነጥቡ ያ ነው ፤ ዴቪድ ። ሁልጊዜም ጽሑፍ የአ ንድ ሰው ሥራ ነው ። በጽሑፍ ቅርስ አቆዩ - ምሑር - የአውሮ ፕላን ካፒቴን " ብላው ወደፊት ዘመም በማለት " ስለአንተ አስፈላ ጊነት ላሳምንህ አልችልም ። ነገር ግን ይህን ማስታወሻ በልዩ ቦታ ደብቀህ እንድታስቀምጠው እለምንሃለሁ " አለችው ።

" እንደሚመስለኝ ጥሩ ሃሳብ ነው ። "

ማስታወሻውን መልሳ ለመስጠት እጅዋን ከዘረጋች በኋላ አቅማማች ። " በዚህ ስለተፈጸመው የራሴን ሃሳብ ተቀምጬ ብጽፍ ቅር ይልሃል ? ብዙ ገጾች ላለመጻፍ እሞክራለሁ ። "

ቢከር ራሱን አስገድዶ ከሳቀ በኋላ " የምትችይውን ያህል ጻፊ። በእኔ በኩል የመጨረሻ ነው ብየ ያመንኩበትን ጽፌአለሁ — " አላት ።

" ፃምጽፈውን ግልባጭ ማድረግ ስለምፈልግ ካርቦን አለህ ? ዋናውን ማስታወሻ ቀብረን በመሸሸግ የእኔን ኮፒ በአውሮፕላኑ ውስጥ በአንድ ቦታ እናስቀምጠዋለን ። "

ቤከር አንድ ካርቦን ፈልጐ ስለአገኘ ሰጣት ። " ዋናውን ማስታወሻ በአውሮፕላኑ ውስጥ እናስቀምጠዋለን ። የእንቺን ኮፒ መቅበር እንችላለን ። "

" እሺ ፤ አመሰግናለሁ " ብላ ካርቦኑን ወሰደች ።

" ሁለቱንም ማንም ሰው ቢሆን እንደማያያቸው ታውቂያለሽ !"

ቀና ብላ ከተመለከተችው በኋላ " የራቬንስብሩክ ጸሎት የተጻፈው በቁራጭ ወረቀት ላይ ነበር ፡ ዴቪድ " አለችው ።

" ያ ጸሎት ለአንቺ ብዙ ትርጉም አለው ። "

" አዎን " ብላው በመስኮቱ መካከል ለትንሽ ጊዜ ወደ ውጭ አየች ። " እንደነገሩኝ . . . እናቴ የሞተችው በራቬንስብሩክ ነው ። ምናልባትም እርስዋ ጽፋዋለች ብየ እገምታለሁ " ብላ ስትነግረው ንግግርዋ ዝቅ ከማለቱም በላይ የውጭው ድምጽ ስለተጨመረበት በግልጽ አይሰማም ነበር ። " አንድ ወቅት ቃሎቹ ለእኔ በጣም ትልቅ ትርጉም ነበራቸው ። ነገር ግን አሁንም ቢሆን የጻፈው ሰው አምኖበት ስለሆነ ለእርሱ ትርጉም አለው ። ከሁሉም በበለጠ ከዚያ አስቃቂ ጊዜ በኋላ የሚተርፉት ሰዎች በዓለም ላይ ነጻ እንደሚሆኑ የሚያሳይ እምነት በመሆኑና ቃሉን የሚሰማው ሁሉ የሚበረታታበት እምነት ነበር ። ምናልባትም የጻፈው ሰው በሕይወት ባይኖርም በዚያ በቁራጭ ወረቀት ላይ የተጻፈው ግን አለ ። ይህ አንድ ሚሊዮን ጊዜ ተባዝቷል ። ይህም ለሚቀጥለው እልቂት ይተላለፋል " ብላ በሰፊው ከነገረችው በኋላ እንደገና ለቤከር ፈገግታ በማሳየት "ዘፍጥረት በመጀመሪያ የተጻፈው በፓፒረስ ወረቀት ላይ በተበጠበጠ የጥቀርሻ ቀለም ነበር ፤ ዴቪድ ። ይህ የመጀመሪያ ጽሑፍ እንደአንተ ባለ ሰው ባይጻፍ ኖሮ ዓለም እንዴት እንደተጀመረ አናውቅም ነበር " አለችው ።

አሁንም ራሱን አስገድዶ ፈገግ ካለ በኋላ “ ያልሽውን ተቀብያለሁ ” አላት ።

“ ጥሩ ” ካለችው በኋላ ብዕር ከቤከር ወስዳ በአብራይስጥ መጻፍ ጀመረች ።

በድንገት ወደ ላይ ቀና ስትል ዓይኖቿ በእንባ ተሞልተዋል ። “ ያ ጸሎት ለእኔ የተለየ ትርጉም ነበረው ። አሁን ግን ይህን ያህልም አይደለም ። ምክንያቱም የይቅርታ መጠየቂያ ጸሎት ሆነ - ሌላውን ጉንጭ ለማዞር የተደረገ ጥሪ - ያንን ጥራት ያለው ጽሑፍ የጻፈው ሰው እንዲኖር አልተፈለገም ፤ ፈተናም ተቀብሎበታል ። እኔም በዚህ ቦታ ፈተና ደርሶብኛል ። በእርግጥ እንደ ራቬንስብሩክ ከባድ እንዳልነበረ ልነግርህ እወዳለሁ ። ከአሁን በኋላ ይቅርታ አላደርግም ። በእርግጥ በዚህ ዓይነት መምጣቱ ደስ ብሎኛል ። በመጀመሪያ ወደዚህ ብቅ የሚለውን የጠላት ወታደር ተኩሼ ለመግደል ተዘጋጅቻለሁ ። ባል አልባዎችና የሙት ልጆች እንደዚሁም ልጆቻቸውን ያጡ ቤተሰቦች ፤ ሀዘንተኛ ወዳጆች ከመሞቴ በፊት እንዲኖሩ ባደርግ ለእድለ ቢሶቹ ሰዎች አዝናለሁ ። ግን የማደርገው የራሴን ፍላጐት ለማርካት አይደለም ። የምለው ይገባሀል ? በጣም አሰቃቂ ይመስላል ? ”

ራሱን በአሉታ እነቃንቆ “ ዓይን ያወጣ ዓይኑ ይውጣ እንደሚባለው ነው ” አላት ።

“ አዎን ፤ ጥርስ ያወለቀ ጥርሱ ይውለቅ የሚለው ሕግ ነው ” ብላ ከነገረችው በኋላ የማስታወሻውን ገጽ ገልብጣ መጻፍዋን ቀጠለች ።

ሆስነር ሰዓቱን ሳይመለከት ጐህ እየቀደደ በመምጣት ላይ እንደ ነበረ ተሰማው ። ከእስራኤሎቹ በኩል ጥቂት ጥይቶች ወደ ቁልቁለቱ እየተተኰሱ ስለነበር የጦርነቱ ፍጻሜ እየተቃረበ እንደመጣ ያስታውቅ ነበር ።

በአሸዋ ውሽንፍር ውስጥ አሸባሎቹ እርስ በእርሳቸው እየተሳሳቁና እየተጫጨኹ እርምጃቸውን ወደፊት በጥንቃቄ ቀጠሉ ። የእስራኤሎቹ ተኩስ እየቀነሰ መምጣት ለዘዴ ይሆናል የሚል ጥርጣሬ አሳድሮባቸዋል ። ሆኖም የተኩሱ ቅነሳ ለእዚህ ከሆነ ሳይዘገዩ ይጀምራሉ የሚል እምነት ተሰርጾባቸዋል ። በመሠረቱ በደቡብ በኩል የእስራኤሎችን ክልል ሰብሮ የገባ አንድ ቡድን ምሽጋቸው ባዶ ሆኖ ያገኘው መሆኑን አውቀዋል ።

ቀስ ብለው በነፋሱና በጨለማው ውስጥ ወደፊት ሔዱ ። የሚያገኙትን ለመግደል ተዘጋጅተዋል ። እስራኤሎቹ ለጠላት ማደናቀፊያ እንዲሆኑላቸው የተከሉአቸው ካስማዎች ሳይቀሩ በነፋስ ኃይል ስለ ወደቁና ስለተደመሰሱ አሽባሎቹ ወደ ተራራው ወጥተው ከጠላት ጊዜያዊ ምሽግ ምንም ነገር ሳይሠነዘርባቸው አልፈው በደህና ሔዱ ። ደስታም ተሰማቸው ።

ሆኖም አልፎ አልፎ ከእስራኤሎቹ የሚተኮሰው አንድ ወይም ሁለት ጥይት እንዲበታተኑና እርምጃቸውንም እንዲቀንሱ አድርጓቸዋል ። ከዚህና ከነፋሱ በስተቀር በተራራው ላይ ጸጥታ ሆኖ ነበር።

አሽባሎቹ አልፎ አልፎ ለሚተኮስባቸው ጥይት ያሉበትን ለማሳወቅ ስላልፈለጉ አጸፋ አልሰጡም ። አንዱ ከሌላው ጋር በቅርብ እየተጠቃቀሱና ምልክት እየተሰጣጡ በጨለማው ውስጥ ወደፊት በሚያደርጉት ግስጋሴ ላይ አንድም ስህተት እንዲፈጠር አልፈለጉም። በዕዝ ማዕከል የነበሩት አሽባሎቹ የአቧራው ውሽንፍር ቆም በሚልበት ጊዜ ኮንኮርዱ የት እንደቆመ ለይተው ለማየት ችለዋል ።

አሽባሎቹ ግስጋሴአቸውን እንዲቀንሱና እራቅ እንዲሉ እስራኤሎቹ ወደ ኋላ እያፈገፈጉ ይተኩሱ ነበር ። እስራኤሎቹ ከእዝ ማዕከል ጣቢያቸው ትዕዛዞች ስለአልደረሱአቸው በመጨረሻ ለመውሰድ ያሰቡት አላማ አልነበራቸውም ። ማፈግፈጋቸው ግን ሥርዓትን የተከተለ ነበር ። ከእስራኤሎቹ ከፊሎቹ በምዕራብ ቁልቁለት በኩል ለማምለጥ ወስነዋል ። ሌሎቹ ደግሞ ባሉበት ቦታ ቆይተው እጣ እድላቸውን ለመቀበል ቆርጠዋል ።

ቁስለኞቹ በእረኛው ጎጆ ውስጥ ከሚደርስባቸው ጊዜያዊ እልቂት ለመዳን የተሻለ ይሆናል ተብሎ ወደ ተገመተው ወደ ኮንኮርዱ ቢወሰዱም አሽባሎቹ ወደ ቁስለኞች ከመድረሳቸው በፊት ቁስለኞቹ ይገደላሉ የሚል ጭምጭምታ ተሰምቷል ።

በምዕራብ ቁልቁለት በኩል የነበሩት እስራኤሎች ምናልባት በዚያ በኩል አሽባሎቹ እንዳሉ ለማረጋገጥ ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ ተኮሱ ።

አህመድ ሪሽ በዚያ በኩል ለነበረው አነስተኛ ምድብ የአጸፋ ተኩስ እንዲሰጥ በራዲዮ አዘዘው ። አህመድ ሪሽ በተራራው ላይ እስራኤሎቹን ራሱ ሊፋለማቸው ስለፈለገ ወደዚያ ሔደው እንዲፈጁ አልፈለገም ።

በወንዙ ዳርቻ የነበሩት አሽባሎች በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት ወደ እስራኤሎቹ ጊዜያዊ ምሽግ አሻቅበው ስለተኮሱ ዙሪያቸውን የተከበቡ መሆናቸውንና ማምለጫም እንደሌላቸው እስራኤሎቹ ስለአወቁ ደነገጡ ። በመካከላቸው ከፍተኛ የሆነ የመረበሽ መንፈስ ተፈጠረ ። በዚያ በኩል ሾልከን እንሔዳለን ብለው ከነበሩት ውስጥ ጥቂቶቹ ማልቀስ ጀመሩ ።

ሀማዲ የደጀን ተቆጣጣሪ ከነበረው መኰንን ከአል - በክር የራ ዲዮ ጥሪ ደረሰው ። " ሀማዲ ነኝ ። ምን ? እርሱ ማነው ? ማንነቱን ማወቅ አለብህ ። ንግግሩን ጨርሷል ? የባግዳድ ስልከኛ መጨረሱን አረጋግጧል ? ምን እየተናገረ ነበር ? አዎን ፤ እብራይስጥ እንደማትና ገር አውቃለሁ ። እርግጠኛ ነኝ ። አረብኛ ይናገራል ? አንድ ዓይኑን ስታወጣው ሁሉንም ነገር ጐልጉሎ ይነግርሃል ። የምታገኘውን ውጤት እንድትነግረኝ " ብሎ ስልኩን መልሶ ለስልከኛው ከሰጠው በኋላ ወደ ሪሽ ተመልክቶ " አህመድ " አለው ።

በአቧራው ውሽንፍር ውስጥ ቀስ ብለው ወደፊት እየተራመዱ ሪሽ ወደ ሀማዲ ዞሮ " ገብቶኛል ፤ ዋጋ የለውም " አለው ።

" ከ - ጋር ተገናኝቶስ እንደሆን ? "

" ዋጋ የለውም ። "

ሀማዲ በሃሳብና በጭንቀት ተዋጠ ። ዕድላቸው በየጊዜው እየ ጨለመ የመጣ መሆኑ ተሰማው ። ሪሽን ትቶ ወደ ጨለማው ዞሮ ከሔደ በፔርሻ ላይ የምትወጣውን ፀሐይ ለማየት ዕድል ይኖረዋል ። ይህን ማድረግ ካልቻለ ግን ለመኖር የነበረው ምርጫ ሪሽን መግደል ነበር ።

* * *

ጆን መክለር ከአሽባሎቹ እየተተኮሱ በቀበሮ ጉድጓዶቻቸው አጠገብ የሚያርፉትን ጥይቶች እየተመለከተ " በዚህ ዓይነት መቀ ጠል አንችልም " ብሎ የቀሩትን ሁለት ጥይቶች በሽጉጡ ውስጥ አስገባ ። ቀጥሎም " ኰሎኔል ፣ ወደ አሜሪካ አምባሳደር ውሰዱኝ ብለህ ለመናገር እስከ አሁን አልተማርክም ? " ብሎ ጠየቀው ።

ሪቻርድሰን የሰማያዊ ኮቱን አዝራሮች ቀልፎ " በሚቀጥሉት ደቂቃዎች ውስጥ በጣም መጠንቀቅ አለብን ፤ መክለር ። ሕይወታ ችን በትንሽ ስህተት አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል " አለው ።

መክለር ሽጉጡን አቀባብሎ " የአደረከው ለምንድን ነው ፣ ቶም ? " ብሎ ጠየቀው ።

ሪቻርድስን ከረባቱን አስተካክሎ ከትከሻው ላይ ጥቂት አቧራ አራገፈ ።

" የአደረከው ለምንድን ነው ብየ ነው የጠየኩህ ? "

ሪቻርድስን በትንሹ የቀበሮ ጉድጓድ አሻግሮ መክለርን እየተ መለከተ " ምኑን ? " ብሎ ጠየቀው ።

መክለር ሽጉጡን አጉርሶ አስጠበቀው ።

ሪቻርድስን ቆቡን አንስቶ አሸዋውን እያራገፈ አቆልቁሎ ሰፌ ውን የሽጉጥ አፈሙዝ እየተመለከተ " ለገንዘብ - ውድ ለሆነ ነገር ድክመት አለብኝ " አለው ።

" ምን ያህል ገንዘብ ቶም ? "

" ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ የአሜሪካ ብር ። "

መክለር አፏጭቶ " መጥፎ አይደለም " አለው ።

" አይደለም ፤ በስዊዘርላንድ በባንክ ገቢ የተደረገ መሆኑንም ልነግርህ እወዳለሁ ። በመጨረሻም ሌላ አንድ ሚሊዮን እንደሚጨ መርልኝ ቃል ተገብቶልኛል ። አሁን ግን አይመስለኝም ። "

" ምናልባት አሁን አቋርጠው ይመጡ ይሆናል ፡ ቶም ። እነእርሱ ሰዎች ብዙ ገንዘብ አላቸው ። "

" ልክነህ ጆን ፤ እነእርሱ ሰዎች በምን ላይ ለማዋል የማያውቁት ብዙ የነዳጅ ሽያጭ የአሜሪካ ብር አላቸው ። የምዕራቡ አገር ለዘይት የሚያፈሰው የደለበ የገንዘብ ክምችት አለው ። "

" የሚያስገርም የአባባል ዘይቤ ነው ፡ ቶም ። ነገር ግን እየተ ነጋገርን ያለነው ስለዚያ ወይም ስለእስራኤል አይደለም ። እየተነጋገ ርን ያለነው ስለአንተ - ቶም - በአሜሪካ አየር ኃይል ውስጥ ኰሎ ኔል - ለውጭ ኃይል ምሥጢር እየሸጥህ ስለአለኸው ነው ። ይህ ደግሞ ከሕግ ውጭ ነው - በአሜሪካ ውስጥ እንኳን ቢሆን " አለው ።

ሪቻርድስን ቆቡን በራሱ ላይ አስተካክሎ ካደረገ በኋላ " በአገሬ ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ስለአልነበርኩ ይህን ላብራራልህ አልችልም ፡ ጆን። የአሜሪካንን የጦር ጋዜጦች ለማሳተም ችግር አልነበረም ። ለውጭ ኃይል መሸጡ ሕገ ወጥ ለመሆኑ አሁንም እርግጠኛ ነህ ? " ብሎ ጠየ ቀው ።

" አታድበስብስ ቶም ። "

" መልካም ፡ እንግዲህ ወደ አገሬ ስመለስ ቅጣቴን አገኛለሁ ። ስለማልፈረጥጥ ሽጉጥህን እንድታስቀምጠው እለምንሃለሁ ። "

“ ሰዎች የመሣሪያ አፈሙዝ በሚያዩበት ጊዜ የተሻለ ይናገራሉ ፣ ቶም ” ብሎ መከለር በጥርሶቹ መካከል ይዞት የነበረውን የክብሪት እንጨት ተፋው ። “ እነዚህን ሕዝቦች ትወዳቸዋለህ ብየ ገምቼ ነበር ። ”

“ በአሁኑ ጊዜ የሴማዊ ተቃዋሚ መስሎ መታየት ጊዜው ያለፈበት ፈሊጥ ነው ። ”

“ አሁን ገባኝ ። ”

በሪቻርድሰን ፊት ላይ ጉልህ ለውጥ ታየ ። አፉ ተያያዘ ፤ ዓይኖቹ ጉረጉዱ ። “ በ1967 በትራቪ ከአሰለጠንኳቸው የእስራኤል በራሪዎች ጋር ወደ መኰንኖች ክበብ ሔጀ ጠጣሁ ። በ1973 በደረሰው ጥፋት አብሬአቸው አዝኛለሁ ። ከዚያ በኋላ የማውቀው ነገር ቢኖር አንድ ሰው ስለእኔ ጥሩ ስለተናገረ በዚህ ልመደብ መቻሌን ነው ። በዚህ ተመድቤ ሥራውን ባገኘሁ ጊዜ ተንገሸገሸኩ ። ”

መከለር መልስ አልሰጠውም ።

ከብዙ ሴኮንዶች በኋላ ሪቻርድሰን ቀና ብሎ ወደ መከለር እየተመለከተ “ ለማንኛውም በማንም ሰው ላይ ጉዳት ሊደርስ አይገባም” አለው በለሰለሰ አንደበት ።

“ ስለ እነእርሱ እየተነጋገርን አይደለንም ፣ ቶም ። እኔም አልወዳቸውም ይሆናል ። በሥቃይ ላይ ብንሆን እንኳን አሳልፌ አልሰጣቸውም ። ለምን እንደሆነ ታውቃለህ ፣ ቶም ? ምክንያቱም አጐቴ የነገረኝ እንደዚህ እንዳደርግ ነው ። የሚከፈለኝም ለዚሁ ነው . . . ቶም”

ሪቻርድሰን አባባሉን ችላ አለው ። ፊቱ እንደገና ተዝናና ። ፈካም አለ ። “ ይህ ጉዳይ አንድ ነገር አስታወሰኝ ፣ ጃን ” ብሎ ፈገግ ካለ በኋላ “ በገንዘብ ልንስማማ እንችላለን ? አንድ መቶ ሺህ ብሰጥህ ?

“ አዝናለሁ ። ”

“ እንግዲያው ግማሹን ? ”

“ አይሆንም ። ” መከለር የመጨረሻውን የክብሪት እንጨት ከኪሱ ውስጥ በርብሮ አገኘ ።

“ በተጨማሪ ለሁለተኛ ጊዜ የሚሰጠኝን በሙሉ ? ”

መከለር የሰማው አልመሰለም ። የክብሪቱን እንጨት እያኘከ “ ማንም ሰው መጐዳት የለበትም አልከኝ ። ግን ብዙ ሰዎች በእርግጥ ተጐድተዋል ” አለው ።

" አውቃለሁ ፤ ስለሆነው ሁሉ አዝናለሁ ፤ ጆን ። ይህ ሁሉ ይሆናል ብሎ የገመተ አልነበረም ። በዚያ ጊዜ ይህን አርቆ ሊያይ የሚችል ማን ነበር ? በእውነት የሚቆጨኝ ይህ ነው ። ይህ ሁሉ ጉዳት " ብሎ ወደ አቧራው ተመለከተ ።

" አንድም ሰው እንዲጐዳ ካልፈለግህ በ02 ለመሳፈር ለምን መረጥክ ፣ ቶም ? "

ሪቻርድሰን የደረቁ ከንፈሮቹን ከላሰ በኋላ " መልካም . . . እሺ ፤ አደጋ የሚያጋጥም ከሆነ 01 መሆን ስለነበረበት . . . ችግር የሚፈጠር ከሆነ የሚመጣው ከአቪዳር እንጂ ከቤከር እንዳልነበረ ስለአወቅን ነው " አለው ።

መከለር አጭር ሳቅ ሳቀ ። " አውቀሃል ? እነዚህን ነገሮች እንዴት ልታውቃቸው ቻልክ ? ለምሳሌ እኛ ስለተፈጥሮና ስለመሳሰሉት ከምናውቀው ውጭ ቤከር ለማስረዳት ቢሞክርና አቪዳር ደግሞ የእርሱን አባባል ቢያስተጋባ ምን ይመስልሃል ? ይህ ማለት ሁለት ሺህ ሜትር ወደ ሰማይ ከፍ ብለህ የሩጫ እሽቅድድም እንደማድረግ ያስቆጥራል ፤ የእኔ ወንድም ። "

" በሚገባ ታስቦ የተደረገ ባወጣ ያውጣው ነው ፣ ጆን ። በሕይወቴም ላይ ፈርጃለሁ ። ፈሪም አይደለሁም " ብሎት ወደ አቧራው ውስጥ ተመለከተ ። " ድምጽ ይሰማኛል ። ወጥተን እጃችንን እንስጥ ወይስ እዚህ እስኪመጡ ተቀምጠን እንጠብቃቸው ? "

"አንተ አምላክ የረገመህ ሰው ፣ ለእነዚህ ምሕረት ለሌላቸው ወጣቶች እጅህን አሳልፈህ ለመስጠት ጓጉተሃል ፣ ቶም ። ጅግና ነህ ብለው የሚቀበሉህ ይመስልሃል ፣ ሪቻርድሰን ? አንተ የማትረባ ደደብ ይገድሉሃል ። ስለአንተም ማንም ሰው የሚያውቅ አይኖርም ፤ እኔንም ይገድሉኛል ። "

ሪቻርድሰን በአሉታ ራሱን ነቅንቆ ፈገግ አለ ። " ውሸት ነው ፤ እኔን አይገድሉኝም ። ሪሽ አለቃ አለው ። አለቃውና እኔ ስለሕይወቴ ደህንነት ዋስትና ተነጋግረናል ። ከሪሽ ጋር ስለሚኖረው ችግር አስቀድመን ተወያይተናል ። እኔ ብገደል በኤምባሲው ባለው ካዝና ውስጥ በእስራኤል ውስጥ ያሉትን የአረብ ሽብር ፈጣሪዎች ወኪሎችና ራሴ የምገናኛቸውና ሌሎችም የሚገናኙአቸው ሰዎች የስም ዝርዝር የተጻፈበት ደብዳቤ አለ ። እኔ ስለሚሆነው ነገር አስቀድሜ አስባለሁ ፣ ጆን " ብሎት ለትንሽ ጊዜ ንግግሩን ቆም ካደረገ በኋላ " በአንተም ላይ አደጋ እንዲያደርሱ አልፈቅድላቸውም " አለው ።

" አመሰግናለሁ ፣ ቶም ። ከአሜሪካ ቆንስላ አንተ የተሻልክ ነህ። መልካም ፣ ሪሽ እነዚህን ሰዎች ይቆጣጠራቸው እንደሆን ፤ ራሱንም ለመቆጣጠር ይችል እንደሆን እደነቃለሁ ። እንደማስበው ጠብሰው ሊበሉህ አዘጋጅተውሃል . . . ምናልባትም አያደርጉትም ይሆናል።" በሃሳብ ላይ የወደቀ መሰለ ። " እንደምታውቀው ቶም ፣ የአሜሪካ ፍርድ በእነዚህ ቀኖች ውስጥ ልል ነው ። ወደ አገራችን ይገፉህ ብመለስ ግድ የሌለህ ለዚህ ነው ። በብዙ አገሮች ውስጥ እንደሚደረገው ቢሆን ግን በጨለማ ውስጥ ግብጣህን ብለው ወደ አልታወቀ ቦታ ይጥሉህ ነበር ። ቀድሞ የነበረው የአሜሪካ የጦር ፍርድ ቤት ከአስር እስከ ሃያ ዓመት እስራት ያከናንብህ ነበር ። ከዚያም ከስድስት ወይም ባነሰ ዓመት ጊዜ ውስጥ ትፈታ ነበር ። ከዚያ በኋላ ወደ ስዊዘርላንድ ትሔዳለህ ። አሜሪካም አሳልፎ ለእስራኤል አይሰጥህም ። ምክንያቱም እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የተቃውሞ ጩኸት ያስነሳበታል።"

"ሕጉቹን እኔ አልሠራኋቸውም" ብሎ በጥርጣሬ ተመለከተው።

" አንተ አትሠራቸውም ። ነገር ግን አልፎ አልፎ ሥልጣን ሲሰጠኝ እኔ እሠራቸዋለሁ " ካለው በኋላ ለትንሽ ጊዜ ንግግሩን ቆም አደረገ ። ቀጥሎም " ብትሞት የሽብር ፈጣሪዎቹ ምሥጢር ይገለጣል አልክ ? " ብሎ ጠየቀው ።

" ቆይ ፣ ስለዚያ መነጋገሩ አይጠቅምም ፣ ጆን ፤ እዚህ ብዙ የምንመካከርባቸው ነገሮች አሉ ። "

" አዎን ፣ አሉ ፤ በቂ ጊዜ ቢኖረን ኖሮ ሌላም እንነጋገር ነበር። ነገር ግን የአጋጣሚ ነገር ሆኖ ምንም ጊዜ የለንም ። "

" ተው ! " ብሎ ሪቻርድሰን እጆቹን በቅጽበት በፊቱ ላይ አደረገ ። " ለሕይወትህ ደህንነት ዋስትና ልሰጥህ እችላለሁ ። እነዚህ ሰዎች " ብሎ ሳይጨርስ መክለር በሽጉጡ ተኩሶ በመሃል ግንባሩ ላይ ስለመታው በጥይቱ ኃይል ራሱ ወደኋላ ተገፍትሮ ከቀበሮው ጉድጓድ ግድግዳ ጋር ተጋጨ ። መለዮውም ከራሱ ላይ ወልቆ በነፋሱ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ተወሰደ ።

* * *

ዴቪድ ቤከር ከአውሮፕላኑ ላይ ወርዶ ሚሪያም የጻፈችውን በፕላስቲክ ጠቅልሎ በቆርቆሮ ውስጥ አድርጎ ትንሽ ጉድጓድ ቆፍሮ ቀበረው ። ሚሪያም በጀግንነት ለመሞት የተዘጋጀችና ለዚህም ፍርሃት ያልተሰማት መስላለች ። ይህን ጽሑፍ ቀብሮ ለማስቀመጥ ያላት ሃሳብ በመጠኑም ቢሆን መሠረተ ቢስ ቢመስልም ያለችውን ተቀብሏታል ። በፍጥነት ጉድጓዱን አፈር መልሶ ሸፈነው ። የጽሑፉን ዋና ኮፒ በአውሮፕላኑ ውስጥ በአንድ ቦታ አስቀመጠው ።

ከአጐነበሰበት ተነስቶ እጆቹን ሲጠራርግ ከ200 ሜትር እርቀት አካባቢ በአቧራማው ነፋስ ውስጥ ሁለት አረቦች እርስ በእርሳቸው ሲጯጯኹ ሰማቸው ። ይህን የሰማ አንድ እስራኤላዊ ስለተኮሰባቸው ከሁለት አንዱ የሕመም ጩኸት አሰማ ። እዚህ በሚደርሱበት ጊዜ በቀላሉ እንደማይለቁአቸው ቤከር ገብቶታል ። እርሱም ሆነ ሌሎቹ እስከ መጨረሻው የደም ጠብታ ለመዋጋት በተወሰደው ውሳኔ ላይ የተጸጸተ አልነበረም ።

በፊት ጉማው ሥር ተንጋሎ የረዳት ኃይል ማመንጫውን በመጠገን ላይ ወደነበረው ወደ ካን ሔዶ " ተነሳ ፒተር ፣ ከአሁን በኋላ ምንም ማድረግ አትችልም ። ተነሳና ወደ አውሮፕላኑ ውስጥ ግባ " አለው።

ካን ከራሱ ቀና ብሎ " ለምን ? " ብሎ ከጠየቀው በኋላ " ስማ እዚህ በሚመጡበት ጊዜ የኃይል ማመንጫውን ለመጠገን በመልፋት ላይ ያለውን ፒተር ካንን እንዲያዩት እፈልጋለሁ ። ምናልባትም ድካ ሜን አይተው በማዘን ወደ ሎድ የምሳፈርበት ትኬት ይሰጡኝ ይሆ ናል " ብሎ አቧለተበት ።

ቤከር በአነጋገሩ ፈገግ ብሎ " እሺ . . . እኔ . . . በአካባቢው አይ ሃለሁ " አለው ።

ካን ከተመለከተው በኋላ " እሺ ፣ በአካባቢው እኔም አይሃለሁ ካፒቴን " ብሎ መለሰለት ።

ቤከር ተመልሶ በቀስታ በመሰላሉ ላይ ወደ አውሮፕላኑ ሲወጣ በአካባቢው ባለው አየር ውስጥ ጥይቶች ያፏጩ ነበር ።

በክንፉ በኩል አድርጐ ቁስለኞቹ በነበሩበት አልፎ ወደ ነጂው ክፍል ገባ ።

በነጂው ክፍል ከሚሪያም ጐን ተቀምጠ " ያልሽውን ፈጽሜ አለሁ " አላት ።

" አመሰግናለሁ ። "

ከረጅም ጊዜ ዝምታ በኋላ በመጨረሻ ቤከር " በዚህ ዓይነት ነገር እንደምሞት አውቃለሁ " አላት ።

ሚሪያም እጅዋን ዘርግታ ክንዱን በመያዝ " በሕይወቴ ዘመን ከአየኋቸው ውስጥ አንተ እጅግ በጣም ጐበዝ ሰው ነህ " አለችው ።

ቤከር ጐንበስ ብሎ የመቆጣጠሪያ መሣሪያውን ተመለከተ ።የፈ ለገው ነገር ቢፈጠር ከአውሮፕላኑ ነጂ ክፍል ውስጥ እንዳይወጣ ሆስ

ነር ባያዘው ኖሮ አንድ ነገር ለማድረግ በስሜት ተገፋፍቷል ። ራዲዮ ኑን ክፍቶ መስመር መፈለግ ጀመረ ። ይህን አንድ ሰው በጀርባው ላይ በጥይት መትቶ እስኪያሳርፈው ድረስ ይቀጥላል ። ስለሚሪያም - ከሴቶቹ ሁሉ - ሐዘን ተሰማው ። አሸባሎቹ እነእርሱን እንደሚፈል ጓቸው እርግጠኛ ነበር ።"እዚህ መቆየት ትፈልጊያለሽ? ማለቴ . . ."

" እኔም ታዝግባለሁ " ብላው ፈገግ አለች ።

በመስኮቱ መሃል ተመልክቶ " በእረኛው ጐጆ አጠገብ ሰዎች እየተሰበሰቡ ናቸው ። እንደማስበው - ሊያደርጉ ነው ። "

" አዎን ፥ እኔም አይቻቸዋለሁ ። የማላስቸግርህ ከሆነ ከአንተ ጋር እዚሁ እቆያለሁ ። "

ካቅማማ በኋላ እጅዋን ይዞ ጭብጥ አደረጋት ።

ራሳቸውን በራሳቸው ለማጥፋት የፈለጉት እስራኤሎች ቁስለ ኞቹ ከለቀቁ በኋላ በደም በጨቀየው ጐጆ ውስጥ ተሰበሰቡ ።

አረቦች አብዛኛውን ጊዜ ራሳቸውን በግድያ አያጠፉም ። ነገር ግን አብዱል ማጂድ ጃባሪና ኢብራሂም አሪፍ ሲገቡ በጐጆው ውስጥ ከነበሩት አንድም የተደነቀ ሰው አልነበረም ። ምክንያቱም እነዚህ ሁለቱ ቢሞቱ በጣም ይሻላቸው እንደነበረ የማያውቅ ሰው ስላልነ በረ ነው ።

ጐጆው ፍጹም ጨለማ ስለነበረ ለእያንዳንዳቸው የጭንቀታቸ ውን ሁኔታ አቅልሎላቸዋል ። ሰው ሲገባ የሚሰማው ሹክሹክታ ብቻ ነበር ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሌላ ሰው እንደማይመጣ ግልጽ ሆነ ። ስለሚቀጥለው እርምጃ ማንም የሚያውቅ ስለሌለ ጸጥታ ሰፈነ ። በጐ ጆው ውስጥ አሥር ወንዶችና ሴቶች በየማዕዘኑ በትናንሽ ቡድን በመ ከፋፈል ተቀምጠዋል ። ከቡድኖቹ በአንዱ ውስጥ ራስን በራስ ስለ መግደል አስፈላጊነት ዋና አነሳሽ የነበረው ጀሹዋ ሩቢን ነበር ። ይጋ ል ቴኮ በአቅራቢያው ተጋድሟል ። ቴኮ አሸባሎቹ በመቃረብ ላይ መሆናቸውን ለወገኖቹ ለመንገር ከምሽጉ ወጥቶ ሲሮጥ በነበረበት ጊዜ በተመታው ጥይት ባለመሞቱ ተናዷል ። አሁን እንደገና ሞትን መቋቋም አለበት ። ከሩቢንና ከቴኮ ጋር አራት ወጣቶች - ሁለት ሴቶ ችና ሁለት ወንዶች- የምክር ቤት ረዳቶችና ሁሉም የሕቡዕ መከላ ከያ ማህበር አባሎች የሆኑ ነበሩ ።

በሌላው ጥግ ከተቀመጡት ቡድኖች ውስጥ ያአኮቭ ሌይበር ፣ ቤተ አብራምስና ራሄል ባኡም ነበሩ ። ቤተ አብራምስ ላለፉት ሁለት ቀናት ቁስለኞቹን ትንከባከብ ስለነበረ ሥቃያቸውን በቅርብ ሆና ስለአየች በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከደስተኛነት ወደ ሀዘንተኛ ነት ተለውጣለች ። ራሄል ባኡም በሌይበርና በአብራምስ መካከል በወለሉ ላይ ተጋድማለች ። እራስዋም እንደ ቴኮ ከቁስለኞቹ ጋር ወደ ኮንኮርዱ መወሰድን እምቢ ብላለች ። ሥቃይዋ በጣም የከፋ ስለነበረ ለበለጠ ሥቃይ በኮንኮርዱ ውስጥ መቆየት አልፈለገችም ። ካፕላንን አከማዋለች ። በኋላም ጩኸቱን ሰምታዋለች ። የዚያ ዓይነት አሰቃቂ ሞት አስፈርቷታል ።

ያአኮቭ ሌይበር ውሳኔ ከመውሰዱ በፊት ስለሦስት ልጆቿ በሃ ሳብ ተወጠረ ። ነገር ግን አሸባሪዎቹ በሕይወት አንድም ሰው እንደማይ ተው ሩቢን አሳምኖታል ። በተጨማሪ ሁለተኛ ሃሳብ በአዕምሮው ውስጥ ተጸነሰበት ፤ ይኸውም ሁለቱ የሴት አስተናጋጆች በጣም እንደ ሚፈልጉት አወቀ ። ይህን ጉዳይ በለሰለሰ አንደበት በጨለማው ውስጥ ሲነግራቸው ቤተ አብራምስ ተንሰቅስቃ አለቀሰች ። ራሄል ባኡም ግን ጸጥ አለች ። በአጠገቧ ተንበርክኮ እጅዋን ያዘ ። ቤተ አብራምስም ተንበርክካ የሁለቱን እጆች ያዘች ።

በሦስተኛው ምድብ ውስጥ አብደል ጃባሪና ኢብራሂም አሪፍ ነበሩ ። ከእስራኤሎቹ ጋር ብቸኛ ሆነው ለአለፉት 30 ዓመቶች ኖረ ዋል ። አሁንም ከእነእርሱ መሃል ሆነው ለብቻቸው ለመሞት ተዘ ጋጅተዋል ።

ጃባሪ የመጨረሻ ሲጋራውን አቀጣጥሎ “ ታውቃለህ ኢብራ ሂም ፤ በእግዚአብሔር እጅ እንደ ማልሞት ሁልጊዜም ቢሆን አውቅ ነበር ” ብሎ አንሾካሾከለት ።

አሪፍ ሰውነቱ ተለዋውጦ ተንቀጠቀጠ ። እርሱም በጨለማው ክፍል ውስጥ ሲጋራውን አቀጣጥሎ በኃይል ማገው ። “ በልብ ሕመም እሞት ይሆናል ” ብሎ ለመቀለድ ከሞከረ በኋላ እንደገና በኃይል ስቦ “ይህን ነገር እንዴት ልንፈጽመው እንችላለን ? ” ብሎ ጠየቀው ።

“ እንደሚመስለኝ ሁለት ወይም ሦስት ሽጉጦች ስለአሉ ለእያ ንዳንዳችን ያስተላልፉልናል ። ”

የአሪፍ እጅ በጣም ስለተንቀጠቀጠ ሲጋራውን እንኳን መያዝ አልቻለም ። ሽጉጡን እንዴት አድርጐ ሊይዘው እንደሚችል አላወ ቀም ። “ የማደርገው መስሎ አልታየኝም ፤ አብደል ” ብሎት ከተ ቀመጠበት ተነሳ ።

ጀባሪ በኃይል ይዞ ተመልሶ እንዲቀመጥ ወደታች ጐተተው ። " ቂል አትሁን ፤ በሞሺ ኳፕላን ላይ የፈጸሙትን አልሰማህም ? በአንተ ላይ የሚፈጽሙት ምን እንደሚሆን አይታይህም ? ከዚያ እስከፈሥቃይ ራስህን አድን ፤ ውድ ወዳጄ " ብሎ ሹክ አለው ።

አሪፍ ማልቀስ ስለጀመረ ጃባሪ አጽናናው ። ጃባሪ ሀዘን የተሰማው ሚሪያምን ደህና ሁኚ አለማለቱ ብቻ ነበር ። ከያዕቆብ ሆስነር ጋር በፍቅር ወድቃለች ብሎ ተጠራጥሯል ። ምርጫዋ ያ በመሆኑ ከንክኖታል። አፍቅሯትም ስለነበረ መጠነኛ ቅናት አድሮበታል ። በቁራን ውስጥ በግልጽ እንደተጻፈው ገነት የሚባል ቦታ እንዳለ አምኗል ። ገነት እንደሚገባም አምኗል ። ነገር ግን ሚሪያም በርንስቴይን ወደዚያ ገነት አትገባም ብሎ ሊያምን አልቻለም ። " አይዞህ አሪፍ ፤ ራስህን አጽናና ። የወዲያኛው ዓለም ከዚህኛው በጣም የተሻለ ነው ። ግሩም መዓዛ ያላቸው የአትክልት ቦታዎች ፤ የማያቋርጡ ምንጮች ፤ ወይን የሚፈስበትና ድንግሎች የሚኖሩበት ነው ። ታዲያ ያ ለማልቀስ ምክንያት ነው ? "

አረቦችን የማይወደውና በሰላሙ ድርድር ውስጥም አባል እንዳይሆኑ ይቃወም የነበረው ይጋል ቴኮ እንኳን በለሰለሰ ድምጽ " አብደልና ኢብራሂም አይዟችሁ ፤ ተበራቱ " አላቸው ።

" ደህና ነን ፣ ይጋል ፣ እናመሰግናለን " ብሎ ጃባሪ መልስ ሰጠው ። ጃባሪ አሁንም ከመሞቱ በፊት ሚሪያምን ሊያያት ባለመቻሉ ተቆጭቷል ። እርስዋን ለመፈለግ ከጐጆው ወጥቶ ለመሔድ ዳዳው ። ግን አሪፍን ብቻውን ትቶት መሔድ አልፈለገም ። አሸባሎቹ እየተቃረቡ መጡ ። ሪሽን ያታለለው መሆኑን ለማሳወቅ ፈለገ ። ግን መቆየቱ ለሁሉም አይበጅም ። በመጨረሻም ራሳቸውን ለማጥፋት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው በመናገሩ የነበረውን ዝምታ አደፈረሰው ። ይሁን እንጂ መልስ የሰጠው አልነበረም ።

የጥይቱ ተኩስ እየቀረበ በመጣ ቁጥር አጸፋ የሚሰጡት እስራኤሎች ወደ ጐጆው እየተጠጉ መጡ ። የጐጆውን ግድግዳ በሩምታ የተተኮሱ ጥይቶች መቱት ። ይህ ሁኔታ እርምጃ እንዲወስዱ ስለገፋፋቸው ሩቢን ወደ ወለሉ መካከል መጥቶ ጉሮሮውን በማፍታታት " እርምጃ በአስቸኳይ መውሰድ አለብን " ካላቸው በኋላ ለትንሽ ጊዜ ንግግሩን አቆመ ። ቀጥሎም " የሚቀል መስሎ ከታያችሁ ሁለት ሽጉጦች ስለአሉኝ ስለእናንተ እኔ አደርገዋለሁ " አላቸው ።

ጀባሪ ከተቀመጠበት በፍጥነት ተነስቶ ወደ መሃል ብመምጣት " እባክህ ቶሎ አድርገው " አለው ።

ሩቢን መልስ ሳያስጥ ሽጉጡን አንስቶ ጃባሪን በግንባሩ ላይ ተኩሶ በአንድ ጥይት መታው ። ሩቢን የተፈናጠቀበትን ደም ከፊቱና ከሽጉጡ ላይ ሲጠርግ ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ ። መናገርም ነ ቃተው ። በሚቀጥ ለው ምን ማድረግ እንደሚችል አላወቀም ። ሽጉጡን ወደራሱ ልብ አዞሮ ምላጩን ስለሳበው በአራቱ ረዳቶች አጠገብ በጀርባው ተዘረረ ። ከሴቶቹ አንድዋ ጮሀ ተስለመለመች ። ሌሎቹ ሦስቱ ግን በወለሉ ላይ ነ ስተካከለው አጋደሙት ። ሁለቱ ወጣት ወንዶች ሽጉጦቹን አነሱ ። እርስ በእርሳቸው በችኮላ ከአንሾካሾኩ በኋላ ሌይበር ፣ አብራምስና ባኡም ወዳሉበት ጥግ ሔዱ ። የሲጋራ ማቀጣጠያ አብርተው ወደ ሰዎቹ ከአነጣጠሩ በኋላ አጥፍተው ምላጩንመሳብ ሲጀምሩ ኢብራምስ አለ ቀሰት ። ሌይበር ሰውነቱን በሁለቱ ሴቶችናወንዶች መካከል ወረወረው ። አንደኛው ተኮሰ ፤ ግን የመታው አልነበረም ። ሌላው ወጣት ሰው ለማ ነጣጠር የሲጋራ ማቀጣጠያውን እንደገና አበራ ።

ቄስ ሌቪን ዘሎ ወደ ጐጆው ገባ ። ለማየት የሚፈልገውን የሲጋራ ማቀጣጠያው ከመጥፋቱ በፊት አየ ። የሁለቱን ሰዎች አንገትጌዎች አፈፍ አድርጐ ወደ ወለሉ ከገፈተራቸው በኋላ በጨለማው ውስጥ በእርግጫና በጥፊ ሲመታቸው እየጮኸና እየማለ ነበር ። "እናንተ እኔን ለማሸነፍ የምትችሉ ይመስላችኋል ? አገኘኋችሁ ! ምን እንደሆ ናችሁ አውቃለሁ፤ከዚህ ውጡ! ውጡ! ውጡ!" ብሎ በጨለማው ውስጥ በዳበሳ ወዲያና ወዲህ ተሯሯጠ ። የኡሪ ሩቢንና የአብደል ጃባሪ ሰው ነት ለብዙ ጊዜ አደናቀፈው ። የሁለቱን ሰዎች መሞት እስኪያውቅ ድረስ ደጋግሞ ሰውነታቸውን እረገጠው ። " ውጡ ! ውጡ ! ከዚህ ውጡ ! እንደዚህ ማድረግ እንዴት ደፈራችሁ ። ቁስለኞቹን ወደ ኮንኮ ርዱ ውሰዱ ! ውጡ ! "

ቄስ ሌቪን ወደጐጆው እንደገባና በውስጥ እንደተገኘ በክፍሉ ውስጥ የነበረውን ጭንቀት አስወገደው ። እያንዳንዱ መሔድ የሚችል ከጐጆው ውስጥ እየወጣ ሔደ ።

ቄሱ በጐጆው ውስጥ ብቻውን በወለሉ መሃል ቆሞ ሰውነቱ ይን ቀጠቀጥ ነበር ። በፊቱ ላይ እንባው እንደምንጭ ውሃ ፈሰሰ ። በበኩሉ ማድረግ የሚገባውን አደረገ ። ነገር ግን እርሱ ትክክለኛ ለመሆኑ ወይም እነእርሱ ስህተተኞች ለመሆናቸው የሚያረጋግጥበት መንገድ አልነ በረውም ። የሁለቱን ሰዎች ሬሳ በሚቀረው አጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት ሊቀብር እንደሚችል አሰበ ። የሞቱት ግን እነማን እንደነበሩ ገና ለይቶ አላወቀም ።

* * *

የወጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ኦሪኤል ዌይዝማን በምዕራብ ቁልቁለት በኩል በነበረው ክልል ከመከለር የቀበሮ ጉድጓድ አጠገብ መጠነኛ

ትጥቅ የነበራቸውን ጥቂት ሰዎች ሰበሰበ ። ዌይዝማን በጉድጓዱ ውስጥ ሰማያዊ ዩኒፎርሙ አሸዋ በመልበስ ላይ የነበረውን የሪቻርድሰንን ሬሳ ተጋድሞ አየ ። መከለር በሌለበት ምክንያቱን ለመናገር ወይም ለመመ ርመር ጊዜ አልነበረውም ።

አሪኤል ዌይዝማን ያሉትን ሰዎች እየመራ ወደ ወንዙ በመውረድ ዶብኪን እንደ አደረገው ለማድረግ ቆርጧል ። ከቁስለኞቹ በስተቀር ለመሔድ ይቻላሉ ብሎ አምኖአል ። ቢጫ ቀለም ያለውን የሕይወት ማዳኛ ጃኬት የለበሱትን ሴቶችና ወንዶች በመስመር አሰለፋቸው ።እንደ እሩዋጭ ተንበርክኮ ሁሉም እንደ እርሱ እንዲያደርጉ መመሪያ ሰጣ ቸው ። “ ከአንድ እስከ ሦስት ስቆጥር ትሔዳላችሁ ። አሁን እስከቆ ጥር ጠብቁ ። ”

ጥቂት ትዕዛዞች ከዋናው የጦር እዝ ማዕከል መምጣት እየጀመሩ ነበር ። እስከ አሁን ያለማቋረጥ መልዕክት የሚያመላልሱት ሯጮች ለሆስነርና ለበርግ የሚያመረቃ ዜና ን ላመጡም ። ሲመለሱም ከሚያ በረታታ ሃሳብ በስተቀር መደረግ የሚገባው ትዕዛዝ ይዘው አልተመ ለሱም ።

ሆስነርና በርግ እጅግ በጣም ጥሩ የነበሩ ትዕዛዞች ፤ ትዕዛዞች እን ዳይሆኑ የሚያስገድድ ጊዜ እንደመጣ ተማመኑ ። በመሆኑም ሰዎቻ ቸው ሕይወታቸውን ለማዳን ተፈጥሮአቸው የሚያዛቸውን እንዲያ ደርጉ ፈቀዱላቸው ።

ሆስነር ወደ በርግ ዞሮ “ ሙሉ በሙሉ ኃላፊ ሆነህ ለመሥራት ትፈልጋለህ፣ይስሐቅ?“እኔ ሥልጣኔን ለመልቀቅ ዝግጁ ነኝ ” አለው ።

በርግ የተኮሳተረ ፈገግታ እያሳየና ራሱን በአሉታ እያነቃነቀ “ አልችልም ፤ አመሰግናለሁ ” አለው ።

“ ማድረግ የሚገባኝን አላደረገም ብለህ የምታምነው ምን ነገር አለህ ? ”

በርግ ለትንሽ ጊዜ ካሰበ በኋላ “ የለኝም ፤ እውነቱን ለመናገር እጅግ በጣም ጥሩ ሥራ ሠርተሃል ። ትንሽ የማግባባት ዘዴ ብትጨም ርበት ኖሮ የበለጠ ይሆን ነበር . . . ምናልባትም ላይሆን ይችላል ” ብሎ ነገረው ። እየተቃረበ የመጣውን ተኩስ ስለሰማ ሰዎቻችንም አስ ደናቂና ግሩም ናቸው ” አለው ።

“ አዎን ፤ ናቸው ። ”

የሆስነር የመጨረሻ ሁለት ሰዎች ማርከስና አልፐርን ወደ ትዕ ዛዝ መስጫው ጣቢያ መጡ ። ማርከስ “ ምን ማድረግ ይገባናል ፣ አለቃዬ ?” ብሎ ጠየቀው ።

ሆስነር ምን እንደሚነግረው አላወቀም ። “ የሚቻልህን ያህል ብዙ ሰዎች ከአንተ ጋር ይዘህ ሒድ ” ካለው በኋላ ለትንሽ ጊዜ ንግግሩን ቆም አደረገ ። ቀጥሎም “ አመሰግንሃለሁ ። የዚህ የመከላከያ የጀርባ አጥንትና ዋና አንቀሳቃሽ ነበርክ ። እዚህ እጅግ ድንቅ ሥራ ሠርተሃል ። ከዚህ ሁሉ በሕይወት የሚተርፍ ሰው አይረሳህም ” አለው

ሁለቱ ሰዎች ራሳቸውን በአዎንታ ነቅንቀው ወደጨለማ ገቡ ።

በርግ እጁን በሆስነር ትከሻ ላይ አስቀምጦ “ ከመቋረጥህ በፊት ወደ ኮንኮርዱ ብትሔድ በጣም የተሻለ ይሆናል ብየ እገምታለሁ ።ቃል ገብተህላታል ። እርስዋም እየጠበቀችህ ናት ። እኔ እዚሁ ሆኜ ለማድረግ የምችለውን እሞክራለሁ ” አለው ።

ሆስነር በአሉታ ራሱን እያነቃነቀ “ አልሔድም ። እርስዋ በእኔ ላይ ሊያደርጉ የሚፈልጉትን ለማየት እንደማትፈልግ ሁሉ እኔም በእርስዋ ላይ የሚፈጽሙትን ማየት አልፈልግም ። ይህን ስለምታውቅ ይመጣል ብላ አትጠብቀኝም ” አለው ።

“ የምትለው ገባኝ ። አንተም — ልታደርግ ነው ። ”

“ አላደርግም ፤ የዚያ ዓይነት ሰው አይደለሁም ። ከመሔዴ በፊት ለአህመድ ሪሽ የምነግረው ጥቂት ነገሮች አሉኝ ። ”

በርግ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። በፊቱም ላይ መጥፎ ፈገግታ ታየበት ። “ ግሩም ሠርተናል ፤ አልሠራንም ? ”

“ አዎን ፤ የምንችለውን ሁሉ አድርገናል . . . አድምጥ ! ”

“ ምን ? ”

“ ሰማህ ? ”

“ አዎን ፤ አዎን ። ”

ሆስነር አንጋጦ ተመለከተ ። በሰማዩ ላይ ድንገተኛ የብርሃን ብልጭታ ያየ መሰለው ። ከሩቅ የጄት ሞተር ጩኸት ሰማ ። “ አገኙን፤ ይስሐቅ ! አገኙን ይስሐቅ ! ” ብሎ ጮኸ ።

“ እዚህ ! እዚህ ነን ” እያለ በርግ እጁን ማወዛወዝ ጀመረ ።

ሆስነር ራሱን አስገድዶ ፈገግ አለ ። “እኛን ለመርዳት በጣም ዘግይተዋል ። ግን ሪሽንና ሰዎቹን ለማውደም በጣም አልዘገዩም ።” ወደ በርግ ዞሮ በእስራኤል ወታደራዊ ጸጥታ ላይ ያለኝ እምነት የተጠበቀ ነው ” አለው ።

በርግ በጣም ንጉቶ ስለነበረ ሆስነር የሚናገረው በደንብ አልገባ ውም ። በኋላ ግን ገባው ። የአየር ኃይል ደረሰ — የእስራኤል ወይም የኢ ራቅ — ግን በጣም ዘግይተዋል ። በርግ ከጉጉቱ እየበረደ ስለመጣ ሰው ነቱ ተንቀጠቀጠ ። ራሱንም በአዎንታ አነቃንቀ ። " ዶብኪን እንዳ ደረገው ተስፋ አለኝ " የሚል ብቻ ነበር ማሰብ የቻለው ።

ሆስነርና በርግ አንጋጠው ሲመለከቱ የሚያስፈሩ ሚሳይሎች በሰ ማይ ላይ እየሰነጠቁ ሲወረወሩ የብርሃን ብልጭታቸውን አዩ ።

## — 33 —

ላስኮቭ በመጀመሪያ የወሰደው እርምጃ ለቤከር በመጨረሻ የገ ባለትን ቃል ከዳን ነበር ። ሌየሩን በራዳሩ በመመልከት 160 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ በፎኒክስ ሚሳይል አነጣጥሮ በኢላማው ውስጥ አደረገው ።

የሌየሩ አብራሪ በእንቅልፍ ኃይል ተሸንፎ እያፋሸገ በመስኮቱ ወደ ውጭ ተመለከተ ። አብራሪው ወደ ላይ የሚወጣ መስሎት በመዘናጋት ሌ የሩን ወደ ምዕራብ ወንዝ ዳርቻ አበረረው ። ከበታች ያለው መሬት ጥቅ ጥቅ ባለው አቧራ ጨልሟል ። ከላይ ግን ንጹህ ሰማይና የጨረቃ ብርሃን ነበር ። የንጋት ውጋጋን ከፔርሺያ በኩል እየዘለቀ ስለነበረ ቀኑ ለበረራ ተመቺ መስሏል ። የጦር ሠፈራቸው ወደ አለበት ሻሚያ በረሃ ሔዶ ነዳጅ ሞልቶ በቶሎ ለመመለስ አቅዷል ። እንደገና እዛጋ ።

በግራ መስኮቱ በኩል ሲመለከት በሰማዩ ላይ ብርሃን ያለው ነበ ልባል ሲውዘገዘግ አየ ። ከአንድ ሴኮንድ በኋላ ሚሳይሉ ወደ እርሱ እየመጣ እንደነበረ ስለአወቀ ተገረመ ። አጠገቡ የተኛውን አብራሪ መታ አድርጐ ከቀሰቀሰው በኋላ አቅጣጫቸውን ለውጠው በክብ ለመ ብረር ቢሞክሩም ሚሳይሉ ተከተላቸው ። አብራሪው ነገሩ ምን እንደሆነ በትክክል ካወቀ በኋላ የሚያስፈራ ጩኸት አሰማ ። የፎኒክሱ ሚሳ ይል እየተንበለበለ ከክፍላቸው ውጭ መጥቶ የቆመና ዓይኑን እየጨ ነቆረ የሚመለከታቸው መሰላቸው ። በቅጽበት እንደ አልነበሩ አድ ርጐ በመበታተን በሰማይ ላይ አዘራቸው ።

ላስኮቭ ተዋጊ አውሮፕላኖቹን በራዳር እየተከታተለ መመሪያ ይሰጣቸው ነበር ። አብራሪዎቹ በጨለማው ውስጥ በዮርዳኖስና በኢ ራቅ ራዳሮች እንዳይታዩ ዝቅ ብለው አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር ለመብረር ከአርባ አምስት ደቂቃ ያነሰ ፈጀባቸው ። የላስኮቭ አውሮፕላን ሁለት የፎኒክስ ሚሳይሎች የተሸከመ ሲሆን የቀሩት ተዋጊ አውሮፕላኖች ከአየር ወደ መሬት የሚተኮሱ መሣሪያዎች ይዘዋል ።

ሌየሩ ከራዳሩ እይታ እንደጠፋ ላስኮቭ በመናገሪያው " ኮንኮ ርድ 02 ፣ ይህ ገብርኤል 32 ነው ፤ ትሰማኛለህ ? " ብሎ ጠየቀው ።

ሚሪያም በበራሪው ክፍል ውስጥ ተቀምጣ ከወደሰማይ የፈንዳ ነገር ሰማች ። ምን እንደሆነ ግን ልትገምት አልቻለችም ። ለማንኛ ውም ቢሆን አልተጨነቀችም ።

" ኮንኮርድ 02 ፣ ይህ ገብርኤል ነው ፣ ትሰማኛለህ ? " ሚሪያም ከሩቅ ድምጽ የሰማች መሰላት ። በተጨማሪም ድምጹን በመጠኑም ቢሆን የምታውቀው መሰላት። "ኮንኮርድ 02 ፣ ትሰማኛለህ ? " ከአሁን በፊት ፈጽማ እንዳላየች ሆና ራዲዮኑን ጉንበስ ብላ ተመለከተች ።

" ኮንኮርድ 02 ፣ ይህ ገብርኤል 32 ነው ፤ ትሰማኛለህ ? እባክህ መልስ ስጠኝ ። "

እንዴት እንደሚሠራ በትክክል ባታውቅም መናገሪያውንና የራዲዮኑን መስመር እየነካካች " ቴዲ ! ቴዲ ! እሰማሃ ለሁ ! " ብላ ጮኸች ። ተበሳጭታ መናገሪያውን በመጣል በቁስለኞች ወደ ተሞላው ክፍል በሩጫ ሔዳ " መጥተዋል ! አየር ኃይላችን ! " ብላ ጮኸች ። ክፍሉ በድምጽ ተሞላ ። እጅግ በጣም በመደነቅ ለአንድ ሴኮንድ ያህል በዚያ በቆመችበት ጊዜ ከኋላዋ የቴዲ ላስኮቭ ድምጽ እንደሕልም ሆኖ " ኮንኮርድ 02 ፣ ይህ ገብርኤል 32 ነው ፤ ትሰማኛ ለህ ? " ሲል ስለተሰማት ወደ ክንፉ ሮጣ በመውጣት " ዴቪድ ! ካፒ ቴን ቤከር ! " ብላ ጠራችው ።

ቤከር ረዳት የኃይል ማመንጫውን ጥገና ትቶ ወደ አውሮፕላኑ ውስጥ እንዲመጣ ካፕላንን ቀደም ብሎ ጠይቆት እምቢ ቢለውም ለመ ጨረሻ ጊዜ ለመጠየቅና አሻፈረኝ ቢልም ለመሰናበት ወጥቶ ወደ ካፕላን ሄዷል ። የሮኬቱን ድምጽና ፍንዳታ ስለሰማ ምን እየተካሄደ እንደነበረ ገባው ። ሚሪያም በጠራችው ጊዜ ተመልሶ በመሰላሉ አጋማሽ ላይ ደርሶ ነበር ። ገፍቷት በማለፍ በቁስለኞቹ መካከል እየሮጠ ወደ ነጂው ክፍል ገባ ።

" ኮንኮርድ 02 ፣ ይህ ገብርኤል 32 ነው ፣ ኮንኮርድ 02 ፣ ኮንኮርድ 02 ፣ እባክህ መልስ ስጠኝ ። "

ቤከር እየተንቀጠቀጠ የድምጽ ማጉያውን በአንድ እጁ በሌላው ደግሞ ራዲዮኑን እያስተካከለ " በግልጽ ይሰማል ፣ ገብርኤል ፣ ገብር ኤል ! በግልጽ ይሰማል ! በአስጊ ሁኔታ ላይ ነን ፣ አረቦቹ በክልላችን ውስጥ ገብተዋል ፣ ሰምተኸኛል ፣ ገብርኤል ? "

ላስኮቭ ከመቀመጫው እንደመነሳት ብሎ " በግልጽ ይሰማል ! በግልጽ ይሰማል ! በአስጊ ሁኔታ ላይ መሆናችሁ ገብቶኛል ፣ 02 !

ጠብቀኝ ! ጠብቀኝ ! ቻርሊ ኮማንዶዎች ይዞ በመንገድ ላይ ነው ። ልት ጠብቀኝ ትችላለህ ? ”

የቤከር ድምጽ እየተንቀጠቀጠ “ አዎን ፣ እንጃ ፣ አላውቅም ፣ እርዳታ ልታደርግልን ትችላለህ ? ” አለው ።

“ በአሁኑ ጊዜ ያለሁት ራቅ ብየ ነው ። በአራት ደቂቃ ውስጥ እደ ርሳለሁ ። የት ቦታ እንዳላችሁ የሚያሳይ የብርሃን ምልክት መስጠት ትችላለህ ? ”

“ አዎን ፣ የማረፊያ መብራቴን ምልክት አበራዋለሁ ። ”

“ ሮጀር በአንተስ በኩል ? ”

“አዎን ፣ አዎን ፣ ያለንበትን ወሰን የሚያሳይ ብርሃን የሚረጭ ፈ ንጂ እወረውራለሁ ። የእነርሱ ወደ ውስጥ የሚገቡት ከባድ ምልክቶች የእኛ ደግሞ ወደውጭ የሚወጡት ቀላል ምልክቶች ስለሆኑ ምልክቶ ቹን በጥንቃቄ መመልከት አለብህ ገብርኤል ። ”

ብዙ የቆሰሉ ወንዶችና ሴቶች ከቤከር ኋላ መጥተው ክፍሉን ሞሉት ። የሆስነር ሰው የነበረው ጃፍ በክፍሉ ውስጥ አልፎ በክንፉ ላይ በመውጣት በነፋሱ ውስጥ ጮኸ “ አየር ኃይላችን እየመጣ ነው ! አየር ኃይላችን እየመጣ ነው ። አካባቢያችንን ጋዝ እያበራችሁ አሳዩ ። ሆስነርና በርግ የት ናቸው ? ጠብቁ እየመጡ ናቸው ” ብሎ አካባቢ ውን በጩኸት አናጋው ።

ኤሸር አሮንሰን ጃፍን አልፋ በመሮጥና ዘላ በመውረድ እየወደ ደቀችና እየተነሳች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩና የእርሱ ቡድኖች ለማም ለጥ እንዳይሄዱ ለመንገር ወደ ምዕራብ ቁልቁለት ገሰገሰች ።

በደቂቃ ውስጥ አሽባሎቹና እስራኤሎቹ ምን እየተፈጠረ እንደ ነበረ ስለአወቁ በተራራው ላይ ብዙ መጯጯኽ ሆነ ።

ሪሽና ሀማዲ የቀሩት ወታደሮቻቸው ወደፊት እንዲገፉ አደረጉ ። እስራኤሎቹም ወደ ኮንኮርዱ እያፈገፈጉ የቀሩአቸውን ጥቂት ሰው ሠራሽ ፈንጂዎች ወደጠላት ወረወሩ ። እስራኤሎቹ ከጠላት ጋር ፊት ለፊት በሚጋጠሙበት ጊዜ ለመጨረሻ ውጊያ ያስቀመጡአቸውን ጥይቶች ስለተጠቀሙባቸው ተኩሱ ጨመረ ።

አሽባሎቹ ከፍተኛ የሞትና የመቁሰል አደጋ ቢደርስባቸውም እያ ንገራገሩ ወደፊት መግፋታቸውን አልተውም ። እያንዳንዱ የቆሰለ አሸ ባል ማልቀስና መራገም ጀመረ ። ደፍረው በመዋጋት እስራኤሎቹን ለመጨረስና የተመኙትን ሁሉ ለማድረግ ወይም ከቦ በመጠበቅ በመ

ጨረሻ እጃቸውን እንዲሰጡ ለማድረግ በሚያስችል ሃሳብ ላይ እንዳሉ የእስራኤል አየር ኃይል በድንገት መምጣት ሁኔታውን ለወጠው ። አሸባሎቹ ለመደራደሪያ የሚሆኑአቸው ጥቂት እስራኤሎች በሕይ ወት መማረክ አማራጭ የሌለው ሆኖ አገኙት ።

የኮንኮርዱን የማቆሚያ መብራት በመመልከት አሸባሎቹ ወደ አውሮፕላኑ መተኮስ ጀመሩ ። ሪሽ ኮንኮርዱ ከፈነዳ እስራኤሎቹ በሙሉ በለሚሞቱ ወደነጂው ክፍል ብቻ እንዲተኩሱ አዘዛቸው ። ለመንጋት በነበረው ውጋጋን ምክንያት ነፋሱ አልፎ አልፎ ገለጥ ሲል ኮንኮርዱን በግልጽ ለማየት ቻሉ ።

ሌየሩ ስለፈነዳ ስብርባሪው ወደ መሬት ሲያርፍ አሸባሎቹ ስለ አዩ የነበራቸው ጊዜ ጥቂት እንደነበረ አወቁ ። ከአሁን በኋላ ለደህ ንነታቸው ጥሩው ቦታ ወደ እስራኤሎቹ መጠጋት እንደነበረ ተገነዘቡ ። ከተቻለም እስራኤሎቹን ምርኮኞች አድርገው በኮንኮርዱ ውስጥ መቀመጡ በበለጠ የተሻለ እንደሚሆን አመኑ ። ውጊያውን የሚያካ ሂዱት በጨበጣ ስለሚሆን በተወሰኑ ደቂቃዎች ውስጥ አሸናፊው ማን እንደሚሆን ይለያል ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከሰዎቹ ጋር ሆኖ የአሜሪካ-አየር ኃይል ባልደረባ የነበረውን የኮሎኔል ቶማስ ሪቻርድሰንን ሬሳ ተሸክመው ወደ ኮንኮርዱ ተመለሱ ። መክለር ወዴት እንደሄደ አልታወቀም ፤ በጉጆው ውስጥ ስለደረሰው ሁኔታ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከቄስ ሌቪን ጋር ተነጋግሮአል ። በጉጆው ውስጥ የነበሩት ወንዶችና ሴቶች እንደዚሁም ሰባት ቁስለኞች ሌይበርም ጭምር በአውሮፕላኑ ዕቃ መጫኛ ክፍል ውስጥ እንዲቆዩ ተወስኖአል ።

የሕቡዕ መከላከያ ድርጅት ማህበር አባል በሆኑት ሁለት ሰዎች የኡሪ ሩቢን አስከሬን ለመቃብር እንዲሆን ወደተቆፈረው ቦይ ተወ ሰዱል ።

ኢብራሂም አሪፍ በሸከሙ ክብደት እየተንገዳገደና እያለቀሰ አንድም ሰው ሳያስነካ የአብደል ጃባሪን በድን ተሸክሞ መጣ ። እን ዳይቀበርም ከለከለ ።

ሚሪያም በርንስቴይን በኮንኮርዱ ክንፍ ላይ ሆና የወዳጅዋን ሬሳ በአሪፍ ክንድ ላይ ተዝለፍልፎ አየች ። ዓይኖቿ በእንባ ተሞሉ ። ሌሎች ሰዎች ስለአስከሬኑ በሚነጋገሩበት ጊዜ “ አሪፍ ” ብላ ጮኸች ።

ትልቁ ሰው ድምጿን ሲሰማ ቀና ብሎ ተመለከታት ። “ አሪፍ አንተ እንደምታፈቅረው እኔም አፈቅረዋለሁ ። ነገር ግን ስለሞቱ

በመሬት ላይ ማረፍ አለበት ። የሁለታችንም ሃይማኖቶች ደህን ያዛሉ ። ሁኔታው እንዲገባህ ያስፈልጋል ። ጊዜው እየሮጠ ነው ። እባክህ ሰዎቹ እንደሚሉት አድርግ ። ”

አሪፍ ቀና ብሎ ለመናገር ቢሞክርም ድምጹ እምቢ አለው ፣ በፍ ጥነት ዞሮ የሚችለውን ያህል እየሮጠ ሄዶ ወደ መቅበሪያው ቦታ ሲደርስ ከታች የኡሪ ሩቢን በድን ተጋድሞ አየው ። የጃባሪን የተ ገለጡ ዓይኖች ተመለከታቸው ። “ ደህና ሁን የጥንት ወዳጄ ” ብሎ ቀስ አድርጐ በማንሸራተት በኡሪ ሩቢን ሰውነት ላይ አጋድሞ በሁለቱም ላይ ጥቂት አፈር መለሰባቸው ። ወደዚያው ሁለት ጠመንጃ የያዙ እስራ ኤሎች ዘለው በጉድጓዱ ውስጥ እንደገቡ በእግሮቻቸው ስር አስከሬ ኖቹን ቢያዩም በዚያ አካባቢ የነበረው አመቺ መከላከያ ያ ብቻ ስለነበረ ትተው መሄድ አልፈለጉም ። ቀጥለውም ወደ አቧራው ውስጥ መተኮስ ጀመሩ ። አንደኛው ወደ አሪፍ ዞሮ “ መሳሪያ ከሌለህ ተመልሰህ ብት ሄድ ይሻልሃል ። እየተቃረቡ ናቸው ” አለው ። አሪፍ በአዎንታ ራሱን ነቅንቆ ወደ ኮንኮርዱ ተመለሰ ። ሕይወት ከደደብነት ፣ ከምጸትና ከመ ጨነቅ መሳ ለመሳ የተፈጠሩ አስመስሎ አሪፍ በሃሳቡ ነጸብራቅ ተመለ ከታቸው ። አብዱል ቢሞትም ነፍሱ ያረፈችበት ቦታ ግሩም መዐዛ ያላቸው አትክልቶች ያሉበት ፣ ወይን የሚፈስበትና ድንግሎች የሚኖ ሩበት ነው ብሎ ስለአመነ የቅናት ስሜት አደረበት ።

የላስኮቭ ረዳት ዳኒ ሌቮን አካባቢውን ለማየት እንዲችሉ ለምል ክት የተቀጣጠለውን ብርሃን አየ ። የኮንኮርዱ የማረፊያ ምልክት መብ ራት በአለበት ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ማለትም ወደ ኮንኮርዱ እየተተ ኮሱ የሚሄዱትን አረንጓዴ ብርሃን ያላቸው ጥይቶች አየ። ወደ አሽባሎቹ የሚተኮሱት ጥቂት ጥይቶች ነበሩ ። አልፎ አልፎ አቧራው መብራቶቹን ይጋርዳቸው ነበር ። ሌቮን ከነበረበት ከፍታ ላይ ሆኖ ፀሐይዋ በዛግሮስ ተራራ ላይ ወጥታ ታየችው ። ጨረሩ ገና በባቢሎን ላይ በቀጥታ አልተ ረጨም ። ኃይለኛው የአቧራ ውሽንፍር ባይኖር ኖሮ በአሁኑ ጊዜ በባ ቢሎን ላይ መጠነኛ ብርሃን መታየት ነበረበት ።“ ወንዙን አልፈን በላ ያቸው ላይ ደርሰናል ” ብሎ በድምጽ ማጉሊያው ለላስኮቭ ነገረው ።

“ ሮጀር ፣ ገብቶኛል ። ” ላስኮቭ ተዋጊ አውሮፕላኖቹን ወደ ኢላማቸው እንዲጠጉ አዘዛቸው።

አሥራ ሁለቱ ኤፍ - 14 ተዋጊ ጀቶች ሁለት በሁለት እየሆኑ ምግብ እንደ አየ ጩልሌ ሽው እያሉ አዘቅዝቀው ወረዱ ። ከምዕራብ በረሃ በኩል በጣም ዝቅ ብለው እያስገመገሙ መጡ ። ላስኮቭ በመጀ መሪያ መጣ ። ጀቶቹ ስህተት እንዳይፈጥሩ ላስኮቭ በ20 ሜትር እርቀት ላይ ሆኖ በኮምፒዩተር ሁሉን ነገር አረጋገጠ ። አሥራ ሁለቱ

ኤፍ - 14 ተዋጊዎች ተከታትለው ሲመጡ ድምጻቸው አስፈሪና አደ ንቋሪ ነበር ። የረጋው አቧራ በኃይል ከመነሳቱም በላይ ከኮንኮርዱ ሥር ያለው መሬት ተንቀጠቀጠ ።

ኮምፒውተሩ የመሬቱን ሁኔታ በሚያሳያቸው ዓይነት እያንዳንዱ ተዋጊ አውሮፕላን ዝቅ ብሎ በረረ ። በተራራው ላይ የነበሩት ሰዎች ተፈጥሮአቸው በሚያስገድዳቸው መሠረት ጀቶቹ ሲበሩ በመሬቱ ላይ እንደሚተኙ አያጠራጥርም ።

ከአለፉ በኋላ ግማሾቹ ተዋጊ ጀቶቹ ወደ ደቡብ ሄደው ሲ - 130 ግዙፍ አውሮፕላኖቹን እንዲጠብቁና አስፈላጊ ከሆነም ለማረፊያ የታሰ በውን አካባቢ በጥይት እንዲያጠሩ ላስኮቭ አዘዛቸው ። አሸባሪዎቹ በዚያ ይኖራሉ ብሎ ባይገምትም ደንቡ መሟላት አለበት ።

ሆስነር በአንድ እግሩ ተንበርክኮ በርግን እንዲወጣ ረዳው ። “ ፒፓ ህን ከአፍህ ውስጥ ሊነጥቁህ ተቃርበው ነበር ፣ ይስሐቅ ። አብረን የም ናደርገውን ጉዞ የምናቆመው በዚህ ቦታ ስለሆነ ሂድና ኮንኮርዱንና በው ስጡ ያሉትን ተቆጣጠር ። አመራርም ስጣቸው ። እኔ ደግሞ በዚህ ዘግ ይቼ የሚመጣውን እቆጣጠራለሁ ” አለው ።

“ የምንከራከርበት ጊዜ ይኖረኛል ብየ ባስብ ኖሮ አደርገው ነበር። ደህና ሁን ያዕቆብ ፣ መልካም ዕድል ” ብሎት የሆስነርን ጀርባ መታ ከአደረገ በኋላ እየሮጠ ሔደ ።

አሸባሪዎቹ ከምሥራቅ በኩል እርሱ ወደነበረበት የእዝ ጣቢያ እየተቃረቡ እንደነበሩ ሆስነር አውቋል ። አሸባሪዎቹ እየተጠጉ ሲመጡ በደቡብ በኩል የሌሎች ሰዎች ድምጽ ስለሰማ ሽጉጡን አቀባብሎና ተንበርክኮ ጠበቃቸው ።

ከኃይለኛው አቧራማ ነፋስ ውስጥ ማርከስና አልፐርን ብቅ ስለ አሉና ሆስነርም ስለጠራቸው እየሮጡ መጡ ። “ አንድ ኤኬ-47 ጠመን ጃና ሙሉ ጥይታችሁን ስጡኝና እናንተ ወደ ኮንኮርዱ ሄዳችሁ ሰዎቻች ንን እያበረታታችሁ በማጠናከር ተከላከሉ። እኔ ደግሞ በዚህ ምሽግ ውስጥ ሆኜ የጠላትን ግስጋሴ ለማዘግየት እችላለሁ ። እናንተ በአሉአችሁ መሣሪያዎች ሁሉ ተጠቀሙ። በኮንኮርዱ አካባቢ የመከላከያ ቦዮች መቆ ፈር ነበረብን ። ሆኖም አሁን ስለዚያ ማሰቡ ዋጋ አይኖረውም ። ትዕዛዝ ከበርግ ትቀበላላችሁ ። መጨቃጨቅ አያስፈልግም ። ትዕዛዙን ተቀ በሉ እሺ ” አላቸው ።

አንድ ጠመንጃና ሁለት ( ሙሉ ያልሆኑ ) ካርታ ጥይቶች ሰ ጡት ። የቴል አቪቭ ስዕል የነበረበትን ጨርቅ ሆስነር ለአልፐርን ሰጠ ው ።

“ ማስታወሻ ሳም ፣ ለልጅ ልጆችህ ይህን ታሪክ በምትነግርበት ጊዜ ልበ ሰው ። አንተ ምን ዓይነት ሐቀኛ እንደነበርክ ያስባሉ ” አለው ።

አልፐርን ጨርቁን በደስታ ተቀበለው ። ሁለቱም የደህና ሁን ምል ክት ከሰጡት በኋላ ሄዱ ። ሆስነር በጉብታው ጀርባ ራሱን አስተካክሎ እንደተቀመጠ ለሙከራ ያህል ጥቂት ጥይቶች ተኮሰ ። ሌሎቹን ለሚ ሰጠው የተኩስ አጸፋ አስቀራቸው ።

ላስኮቭንና ኤፍ - 14 ተዋጊ ጄቶችን ሆስነር በማየቱ በሕይወቱ ሙሉ ከአየውና ከአጋጠመው ሁሉ በበለጠ ተደሰተ ። በእርግጥ የመ ጡት ዘግይተው ነበር ። ጃፍ ሲ - 130 ግዙፍ አውሮፕላኖች ኮማንዶ ዎች በመምጣት ላይ መሆናቸውን ነግሮታል ። ቢያርፉ እንኳን በጣም ዘግይተዋል ። በጭቃማ ሜዳው ላይ ከአረፉ በኋላ የኤፍራጥስን ወንዝ አቋርጠው መምጣት ይኖርባቸዋል ። ነገር ግን ኮንኮርዱ ሊያርፍ በነበረ ብት መንገድ ( ሜዳ ) ላይ ቢያርፍ ኖሮ እዚህ ለመድረስ የሚቀራቸው አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ነበር ። ይህም ሆኖ እስከ አሁን ባለአራት ሞተሩን አውሮፕላን ድምጽ አልሰማም ።

አየር ወለድ ወታደሮች ደርሰው ሊያድኑአቸው ይችሉ ይሆናል ። ነገር ግን በዚህ በጨለማና አቧራ ውስጥ የመሬቱ አቀማመጥ በግልጽ ስለማይታያቸው ማማሻቹ በውሃው ላይ ሊያርፉ ለለሚችሉ ራስን በራስ ማጥፋት ይሆናል ። ሁኔታውን ብዙ ሊለውጠው ባይችልም መም ጣታቸው ጥሩ የኃይል ምልክት ነበር ። በእርግጥ ሁኔታውን በጣም መጥፎ ሊያደርገው ይችላል ። አሸባሪዎቹ ቀደም ብሎ የነበራቸው ሃሳብ ለመ ጨረስ ስለነበረ የማንኛውንም ፍጻሜ ያቀርበው ነበር ። አሁን ግን ራሳቸውን እስራኤሎቹን በምርኮኝነት መያዝ አለባቸው ። ይህ ደግሞ ነገሩን ሁሉ እንደ አዲስ እንዲጀመር ያደርገዋል ። ሆስነር ይህን ሁሉ ላስኮቭ አስቀድሞ ያስብበታል ብሎ ተስፋ አድርጓል ። አሸባሪዎቹ መሸነፋቸውን ሲያውቁ ተራራውን በሙሉ ለማቃጠል እንደማያቅማሙ ያውቃል ። ይህ ከአልሆነ ግን ሁልጊዜም ተንኮል ከመሥራት ወደኋላ አይሉም ብሎ ሆስነር የሚያምንባቸው አህመድ ሪሽና ሳሌም ሀማዲ ይያዛሉ ።

ሆስነር በሃሳቡ ሚሪያምን ደህና ሁኝ አላት ። ወደ ኮንኮርዱ ሄዶ ይህን መልዕክት ላስተላልፍ ወይም በዚሁ ልቆይ በሚል ሃሳብ ተዋጠ ።

ፒተር ካን በፊት ጉማው ስር ሆኖ ረዳት የኃይል መስጫውን በሚ ጠግንበት ጊዜ የሆነውን ሁሉ አዳምጧል ። እየተንፏፏጡ ወደ አው ሮፕላኑ ውስጥ ሲገቡ የእግር ኮቴዎች ሰምቷል ። ጥቂት ሰዎች መሣሪያ

ሳይዙ ወደ ኮንኮርዱ ሲገቡ አይቷል ። ራቅ ብለው ተንበርክከው የሚ ተኩሱትን ከጠመንጃዎቻቸው በሚወጣው ብልጭታ አይቷቸዋል ። በእረኛው ጐጆ ግድግዳ ላይ ብዙ ጥይቶች ማረፋቸውን አያ ቷል ። ጥቂት ወንዶችና ሴቶች በአውሮፕላኑ መውጫ ት ጠገብ የመከላከያ ቦታቸውን መያዛቸውንና አንዲት ሴት ከእርሱ በስተኋላ በአለ ቦታ ላይ በመሆን ትጠብቅ እንደነበረ አጢኖአል ። በየትኛውም መንገድ ቢሆን ፍጻሜአ ቸው እየተቃረበ ነበር ። ካን ግን ተስፋ ሳይቆርጥ ጥገናውን ቀጥሏል ።

በድንገት ተንከባሎ ከጉማው መያዣ ሥር በመውጣት ጠመንጃ ወደዚያችው ሴት ሄዶ እጁንና ፊቱን ከጠረገ በኋላ ሮጦ በመሄድ ወደ ኮንኮርዱ ወጣ ። በክንፉ አጠገብ ሲደርስ ሚሪያም ክንዱን ይዛ “ ያዕቆብ ሆስነርን አላየህም ? ” ብላ ጠየቀችው ። “ አላየሁትም ፣ በር ንስቴይን ። እኔ የቆየሁት በፊት ጉማው ሥር ነበር ። በመሠረቱ እኔም የምፈልገው እርሱን ነበር ” አላት ። ለመከላከያ ሠርተዋቸው የነበ ሩትን መሣሪያዎች ሁሉ ወደ ኮንኮርዱ ሰብስበው ያመጡአቸው መሆ ኑን አየ ። እስከመጨረሻው ድረስ ያደረጉት ፍሬኢማ ሥራ በማየቱ ተደ ሰተ ። “ ስሚ ፣ በርንስቴይን ፣ እዚህ የምንታኮስበት ቦታ ስለሆነ ወደ ውስጥ ብትገቢ የተሻለ ነው ”ከአላት በኋላ ትቷት ኮከብ በአለበት በክ ንፉ መጫረሻ ወደ ቆመው ወደ በርግ ሄደ ። ስድስት ወንዶችና ሴቶች የሚሆኑ ወደ ጨለማው ውስጥ ይተኩሱ ነበር ። አሸባሎቹ ወደ ክንፉ ተኩሰው ለማፈንዳት እንዳላሰቡ ለበርግም ሆነ ለሌሎች ግልጽ ሆኖ አል ። በዚህ ምክንያት ክንፉ ለደህንነት የተመቸ ቦታ ሆኖ ተገኝ ቷል ።

“ ይቅርታ ” ብሎ ካን የበርግን ትከሻ ነካው ።

በርግ ዞሮ “ ሀሎ ካን ። የተበላሸውን ረዳት የኃይል ማመንጫ ለመጠገን መሞከርህ ጥሩ ነው ፣ የእኔ ልጅ ” አለው ።

“ ልክ ነህ ፣ ከአንተ . . . ወይም ከሆስነር ጋር ለመነጋገር የምፈ ልገው ስለዚሁ ጉዳይ ነው . . . ”

“ ሆስነር አሁንም ያለው በዚያ ስለሆነ ከእኔ ጋር ተነጋገር ” ብሎ በእጁ አመለከተው ፣

“ እሺ ፣ ለማንኛውም የጠገንኩት መሰለኝ ። ”

“ ተጠገነ . . . ? ” ብሎ በርግ ከቁጥጥሩ ውጭ የሆነ አሳሳቅ አሰማ ። “ ምን ዋጋ ይኖረዋል ። የኔ ልጅ ? በአውሮፕላኑ ውስጥ ገብተህ ራስህን ዝቅ አድርገህ ጠብቅ ። ”

ካን በፍጥነት ቆሞ “ የገባህ አልመሰለኝም ። በወቅቱ አይደርሱ ልንም ። እኛ — እንችላለን ” አለው ።

ኃይለኛ ፍንዳታ የቆሙበትን አውሮፕላን አንቀጠቀጠው ።አንድ ኤፍ-14 ጄት በላያቸው ላይ አለፈ። ሌላ ኤፍ-14 ጄት በባለ 20 ሚሊሜትር መድፍ እየተኮሰ ሄደ ። ሦስተኛው ከኤፍራጥስ በኩል መጥቶ ከአየር ወደ መሬት ሚሳይል ተኮሰ። ሌላ ኤፍ-14 የጣለው ቦምብ በምዕራብ ቁልቁለት በኩል ሲያርፍ አፈሩንና ድንጋዩን ሲበታትነው የተነሳው ናዳ ጥቂት አሸባሎቹን ወደ ወንዙ ዳርቻና ወደ ውሃው ይዟቸው ወረደ ። እንደዚሁም የተበታተነው አፈርና ድንጋይ በመቶ በሚቆጠሩ ሜትሮች ወደ ሰማይ ተወረወረ ። አካባቢው ሁሉ በእሳት ተያያዘ ። በተጨማሪም የሮኬት ብልጭታ በሰማዩ ላይ ታየ ።

በርግ በወደቀበት ላይ ሆኖ “ ምን ? ” ብሎ ጮኸ ።

“ እንደሚመስለኝ ረዳት የኃይል ማመንጫውን በመቀስቀስ ሞተ ሩን ማስነሳት እንች ላለን ” ብሎ ካን ጮኾ ነገረው ።

“ ምን ጥቅም ይኖረዋል ? ምን ልዩነት ያመጣል ? የአየር ማቀዝ ቀዣው እንዲሠራ አንፈልግም ፡ ካን ። ”

“ የፈለገው ይሁን ከዚህ መሄድ እንችላለን ። ”

“ አብደሃል እንዴ ? ”

አንድ ሮኬት በአጠገባቸው ስለአረፈ ፍንጣሪው በአውሮፕላኑ ላይ ተረጨ ። ካን ቀና ብሎ “ አላበድኩም ፤ ኮንኮርዱን ከዚህ ማስ ነሳት እንችላለን ” አለው ።

“ የምንወስደው ወዴት ነው ? ”

“ የትስ ቢሆን ምን አለበት ። ብቻ ከዚህ መሄድ አለብን ። ”

ሆስነርን ለማየት ተስፋ በማድረግ በርግ ወደ ኋላው ዞሮ ሲያይ በዚያ ቆማ ትመለከት የነበረችው ሚሪያም ብቻ ነበረች ። ጮኾ ሊነ ግራት ፈልጐ ነበር ። ግን ልትሰማው ስለማትችል ወደ ካን ተመልሶ “ ለካፒቴኑ ሞተሩን ለመቀስቀስ እንዲሞክር ንገረው ” አለው ።

በርግ ሌላ ተጨማሪ ትዕዛዝ ከመስጠቱ ወይም ሃሳቡን ከመለወጡ በፊት ካን ዘሎ ወደ አውሮፕላኑ ውስጥ ገብቶ በሰዎቹ መካከል እየተ ጋፋ አልፎ አብራሪው ክፍል ውስጥ ገብቶ “ ዴቪድ ! ” አለው ።

ቤከር ከላስኮቭ ጋር በራዲዮ እየተነጋገረ ስለነበረ ዝም እንዲል በእጁ ምልክት ሰጠው ።

“ ዴቪድ ! ”

ቤከር በአሜሪካ አየር ሥልጠና በወሰደበት ጊዜ በአየር ላይ ስለ ሚደረግ ጥቃት ፣ ማስተካከልና መነጋገር ተምሮ ስለነበረ አሁን ጠቅ ምታል ። ከነበረበት ክፍል ውስጥ ሆኖ ብዙ ባይታየውም ጥቅም ያለው ሥራ እያከናወነ ነበር ። ይህን ለማድረግ በቂ ጊዜ አገኝቷል ። " እሺ ፣ ገብርኤል ፡ የቀረ ጥይት ከአለህ የምትጠቀምበት ጊዜ አሁን ነው ። በተራራው ሥርና በወንዙ ዳርቻ የሳትነው እንዳለ ለማጠናቀቅ አንድ ዙር እናደርጋለን ። አካባቢውን ለማጽዳት በዚያ በኩል ለመብረር እሞክራለሁ። በቀኝ ፊት ለፊት እስከ 200 ሜትር እርቀት ድረስ ማድረግ ትችላለህ ። የበረራ ምልክት የሚሰጠውን መብራት ብልጭ ድርግም ማድረግ አሁን እጀምራለሁ ። "

የወንዙ ሮጀር ፣ 02 ከመስኮትህ ውጭ የሚታይ የለም ። በጣም ተጠግቷል ።

ካን የቤከርን ትከሻ ይዞ አርገፈገፈው ። በእንግሊዝኛ ጮኾ እየ ነገረው ነበር ። " የምነግርህን አትሰማም ? ረዳት የኃይል መስጫው ተጠግኖአል ። ይህን ትልቅ ወፍ አስነስተህ ከዚህ እንሂድ " አለው ።

ለሴኮንድ ያህል ቤከር መናገር አልቻለም ። " ተጠገነ ? "

" አዎን ፣ አዎን ፣ " ምናልባት ይሆናል ብሎ ካን አሰበ ።

የቤከር ጣቶች የረዳት ኃይል ማመንጫውን ማስነሻ ነኩ ። ይህን ሞተር ሊቀሰቅስ የሚችል በቂ የባትሪ ኃይል ይኖራል ብሎ አላመነም። ማብሪያውን ነክቶ ወደ መሣሪያዎቹ ተመለከተ ። በመስኮቱ መካከል በኃይለኛው ነፋስ ውስጥ የሚመጣውን ድምጽ አዳመጠ ። የኃ ይል መስጫው ሞተር መዞር ጀመረ ። ነገር ግን ሊቀጣጠል አልቻለም። ቤከር የአውሮፕላኑን መብራቶች ጨርሶ አጠፋቸው ። ረዳት የኃይል መስጫው ሞተር ነዳጁ እስኪቀጣጠል ድረስ ሞተሩን ሊቀሰቅስ የሚ ችል ቀሪ የባትሪ ኃይል ይኖር ይሆን ? ያለምንም መነጋገር ሁለቱም የረዳት ኃይል መስጫውን ሙቀት መለኪያ ተመለከቱ ። ሁለቱም የሙ ቀት ምልክት የሚሰጠው መርፌ — ሞተሩ የሚነሳ መሆኑን የሚያሳየ ውን — ይነቃነቅ እንደሆነ ትኩር አድርገው ተመለከቱት ። ነጩ አመል ካች መርፌ ሳይንቀሳቀስ በመለኪያው ላይ ተቀምጧል ። ቤከር ሁልጊዜም እንደሚለው " ይህን ብቻ አምላኬ ፣ ይህን ብቻ " አምላኬ ይህን ብቻ " አለ ። ነገር ግን ምንም ለውጥ አልታየም ።

# — 34 —

ሁለቱ ሲ-130 ግዙፍ አውሮፕላኖች በምዕራብ በረሃ ላይ ዝቅ ብለው መጡ ። ከኤፍ - 14 ተዋጊ ጄቶች ቀደም ብለው ከእስራኤል ቢነሱም በሰዓት የሚበሩት 585 ኪሎ ሜትር ስለነበረ ወደ ሁለት ሰዓት ያህል ፈጀባቸው ።

የዮርዳኖስ ንጉሥ በኢራቅ ድንበር በኩል በሰሜን ዮርዳኖስ እንዲበሩ ያለምንም ጊዜ መፍጀት ፈቀደ ። የኢራቅ መንግሥት ፈቃድ ከመስጠቱ ቀደም ብሎ ኤፍ-14 ተዋጊ አውሮፕላኖች በኢራቅ ግዛት ውስጥ የደረሱ ሲሆን ሲ - 130ዎቹም እየተቃረቡ ነበሩ ። ይህ የተወሰደው እርምጃ ያወጣ ያውጣው ተብሎ የተደረገ ሲሆን ቢበዛ ሊሆን የሚችለው ሲ - 130ዎቹ እንዳይገቡ ማድረግ ፤ የገቡትም ኤፍ-14ቶቹ እንዲወጡ ማዘዝ ነበር ። ይሁን እንጂ ያለፈቃድ ወደ መሃል ኢራቅ ጠልቀው ስለ መግባታቸው የሚደረገው ገለጻ ሀፍረትን የሚያከናንብ ይሆን ነበር ።

ከብዙ ውይይት በኋላ ባግዳድ ከኢየሩሳሌም ጋር ተባብሮ ለመሥራትና በመጨረሻም የእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትርና የኢራቁ ፕሬዚዳንት ጋዜጣዊ መግለጫ በጋራ ለመስጠት ተስማሙ ። ይህን የጋዜጣ መግለጫ ተግባራዊ መሆን ለማረጋገጥ ሲል የኢራቅ መንግሥት በሻሚያ ብረሃ ከሚገኘው የጦር ሠፈር ከባሕር ኃይል የተውጣጣ አንድ ትንሽ ቡድን ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ ላከ ። በተጨማሪም የኢራቅ መንግሥት የሂላ ጦር በተጠንቀቅ ላይ እንዲጠብቅ አዘዘ ። ነገር ግን ሁለቱም መንግሥታት ያ የጦር ኃይል ትዕዛዙን ተቀብሎ ተግባራዊ እንደማያደርግ አውቀዋል ። ምክንያቱም ከወታደሮቹ ብዙዎቹ የሚከፈሉት በአህመድ ሪሽ ስለነበረ የኢራቅ መኰንኖችዓይ ኖቻቸውን በእነ እርሱ ላይ ጥለው ከመመልከት በስተቀር ሌላ ማድረግ አይችሉም ። ሁለቱም መንግሥታት ከሻሚያ ተነስቶ እርምጃ ለመውሰድ በጊዜው እንደማይደርስ ቢያውቁም ዋናው ቁም ነገር በጐ ፈቃደኛ መሆኑ ነበር።

ከሂላ ሌሎች መኰንኖች ፤ ከየአካባቢው የተውጣጡ የመንግሥት ሠራተኞችና ሌሎችም ሰዎች ከሂላ አየር ማረፊያ በመኪናዎች ተሳፍረው በሰሜን በኩል ወደ ባቢሎን አቅጣጫ ሄዱ ። በመጀመሪያ ኮንኮርዱ መሬት ሲነካ ባረሰው በሂላ - ባግዳድ መንገድ ላይ ደርሰው በመንገዱ (በሜዳው) ዙሪያ መብራት የሚሰጡ ምልክቶች አደረጉ ። ሌላው የጦር ክፍል ደግሞ በሞተር ጀልባ የኤፍራጥስን ወንዝ አቋርጦ በመሻገር በጭቃማው ሜዳ ላይ ለአውሮፕላን ማረፊያ ምልክት እንዲሆን ብልጭ ድርግም የሚል መብራት አስቀመጠ ። የተሠሩት ምልክቶች ሁሉ ሲ

130 አውሮፕላኖችን ለማሳረፍ ፍጹም አስፈላጊ ባይሆኑም ሊደርሱ የሚችሉ መጠነኛ አደጋዎችን መቀነስ የሚያስችሉ ነበሩ ።

ከሁለቱ አንዱ የሆነው በመጀመሪያ የመጣው የሲ - 130 ግዙፍ አውሮፕላን አብራሪዎች ኢሽማኤል ብሎሽና የመቶ አለቃ ኤፍሬም ሄርዝል በሂላ መንገድ ላይ የተደረገውን የመብራት ምልክት ስለአዩ ኃይላቸውን ባመቀነስ ወደ ግራ ታጠፉ ። ሦስት ኤፍ-14 ተዋጊ ጀቶች የዚህን አውሮፕላን ደህንነት እንዲጠብቁ ስለተመደቡ ቀድመው ዝቅ ብለው በረሩ ።

ግዙፉ አውሮፕላን በጦርነት ጊዜ እንደሚደረገው በፍጥነት ዝቅ አለ ። በውስጡ የነበሩት አምሳ ኮማንዶዎች በሚያርፍበት ጊዜ በሚያ ደርገው ንቅናቄ እንዳይጐዱ ቀበቶዎቻቸውን አጥብቀው አሠሩ ። በው ስጡ ሁለት ጂፖች በአንደኛው ላይ ባለ 106 ሚሊ ሜትር አውቶማ ቲክ ጠመንጃ በሌላው ላይ ደግሞ ጥንድ ባለ 50 ካሊበር የተደገኑ ስለ ነበሩ እንደገና አጥብቀው አሠሩአቸው ።

ዶክተሮቹና ነርሶቹ በተንቀሳቃሽ የሕክምና መሣሪያው ውስጥ ያስ ቀመጣቸውን የቀዶ ጥገና ዕቃዎችንና ሌሎቹንም አንድ በአንድ ፈተሹ ።

ካፒቴን ብሎሽ አሁንም እንደገና የበረራውን ኃይል በመቀነስ ፍጥነት የሚያሳየውን መርፌ ተመለከተ ። ብሎሽ አውሮፕላኑን በተ ደረጉት ምልክቶች መካከል ለማቆም ሲሞክር የነበረው ኃይለኛ ነፋስ ወደ ግራ ስለገፋው መስመሩን ለመከተል በጣም አስቸገረው ።

ሔርዝል ዓይኖቹን በመሣሪያዎቹ ላይ እንደጣለ “ በዚህ ቦታ ላይ ማረፍ ከፍተኛ ፈተና መሆኑን አውቀሃል ” አለው ።

ብሎሽ ኃይል እንደገና ሰጥቶ ከፍ ብሎ በመብረር ዞሮ ለመምጣት በሚዘጋጅበት ጊዜ ነፋሱ ለጥቂት ሴኮንዶች ጋብ ስለአለ አውሮፕላኑን አስተካክሎ በፍጥነት ወደታች ዝቅ ብሎ መጣ ።

ጉማው መሬት ሲነካ ድንጋዮቹ እየተበታተኑ በኃይል ተፈና ጠሩ ። አሁንም ኃይለኛው ነፋስ ወደ ግራ ሊገፋው ቢሞክርም ካፒ ቴኑ በአደረገው ጥረት ሞተሮቹን አጥፍቶ ፍሬኑን በኃይል ይዞ ስለአቆ መው ጩኸቱ ጆሮ ይበጥስ ስለነበረ በውስጡ የነበሩት ወንዶችና ሴቶች ጣቶቻቸውን በጆሮቻቸው ውስጥ አስገብተው ያዙ ።

ሔርዝል በመስኮቱ መካከል ተመልክቶ “ በቀላሉ ለመነሳት እን ዲችል ከፊቱ ትንሽ ቦታ ተው ” አለው ።

“ ሥራችንን ከፈጸምን በኋላ ወደ ባግዳድ እንበራለን ። ”

ለማረፊያ ምልክት በነበሩት መብራቶች አማካይነት አልፎ አልፎ ብእርቀት የቆሙ የኢራቅ መኪናዎች እዩ ። ሲ - 130 አውሮፕላን ሲቆም እጃቸውን ስለአውለበለቡ ብሎሽና ሄርዝል አጸፋውን ሰጡአቸው ። “ የአገሩ ተወላጆች የሚያዩን በወዳጅነት መልክ ነው ? ” ብሎ ሔር ዝል ጠየቀው ።

ግዙፉ አውሮፕላን ቀድሞ ኮንኮርዱ መሬት በነካበት ቦታ አቅራ ቢያ ለመቆም እያዘገመ መጣ ። ብሎሽ በማረፊያ መብራቶች አማካይ ነት ኮንኮርዱ እንደገና ተነስቶ የሄደበትን ቦታ ተመለከተ ። ሲ - 130 አውሮፕላን በዚያ ዓይነት በተሠራ ማረፊያ ላይ ለማረፍ ችግር የለበ ትም ። የኮንኮርዱ ማረፊያ ግን በጣም የለሰለሰ መሆን አለበት ። የኮ ንኮርዱን አብራሪ አደነቀው ። ቀጥሎም የባቢሎንን ተራራዎች በሩቅ ተመለከተ ።

ሔርዝል በመስኮቱ ተመልክቶ “ ባቢሎን … ባቢሎን ” አለው ።

አውሮፕላኑ ሙሉ በሙሉ ከመቆሙ በፊት የኋላ መዝጊያ ስለተ ከፈተ ኮማንዶዎቹ እየዘለሉ በመውጣት በግራና በቀኝ ቦታቸውን ያዙ ። የኢራቅ መኮንኖችና የመንግሥት ሠራተኞች የካኪ ዓይነት ቀለም በተቀቡ መኪናዎች ላይ ሆነው በጉጉት ተመለከቷቸው ። ሁለቱም ወገኖች ተሸብረዋል ። ሁለቱም ወገኖች እጆቻቸውን በማወ ዛወዝ የወዳጅነት ምልክት ተሰጣጡ ።

ሁለቱ ጅፖች እንዲወርዱ ተደረጉ ። አንድ ኮማንዶ ቡድን አው ሮፕላኑን እንዲጠብቅ ተደረገ ። የሕክምና ባለሙያዎች ለቁስለኞቹ የሚያደርጉትን የእንክብካቤ ዝግጅት አቀነባበሩ ።

ሦስት ቡድን ኮማንዶዎች እያንዳንዳቸው በመቶ አለቃ የሚታ ዘዙ በአጠቃላይ ግን በሻለቃ ሴት አሮን የሚመሩ ሁለቱን ጅፖች በጐ ንና በጐን ሆነው አጀቡ ። የመጀመሪያ ግባቸውን ለመፈጸም ወደ ኢሽ ታር በር አካባቢ ፣ እንግዳ መቀበያው ቤትና ቤተ መዘክሩ ሄዱ ።

ካፒቴን ብሎሽ በአውሮፕላኑ ነጂ ክፍል ውስጥ ሆኖ በመስኮቱ እየተመለከተ “ ወታደር መሆን ቀላል ሥራ አይደለም ” አለው ።

የመቶ አለቃ ሔርዝል ቀና ብሎ “ ከዚያ እዚህ እስኪደርሱ ድረስ ተኝተዋል ። ከሥራቸው ሲመለሱ ደግሞ ይተኛሉ ። ይልቅስ ለረዳት አብራሪህ እዘንለት ” ብሎ መለሰለት ።

ካፒቴን ብሎሽ የብርቱካን ፣ ቢጫ ፣ ቀይና ነጭ ቀለሞች ያሉት እሳት በመበልበል ላይ ወደ አለው ሰሜን ምሽግ ተመለከተ ። ጩኸቱ ከባቢሎን አውሮፕላኑ አረፈበት ድረስ ይሰማ ነበር ። እዚያ ላሉት ምስ ኪኖች አዝናለሁ ። እንደምታውቀው ኤፍሬም ፣ አርብ ከሰዓት በኋላ ይኸ ሁሉ ወጭ ተደርጎ ሰላም የሚል ቁራጭ ወረቀት ለማምጣት

እስከቻሉ ድረስ ወደ ኒውዮርክ ለመሄድ ሲነሱ መልካም እድል እንዲ ገጥማቸው ተመኝቼላቸው ነበር ” ብሎ አሜወተው ።

ሔርዝል በመስኮቱ ገልመጥ ብሎ ሲመለከት በተራራው ላይ ብልጭ ብልጭ የሚል እሳት ስለአየ “ እኔም በበኩሌ የሰላም ተደራዳሪ መሆን ቀላል እንደአልሆነ እገምታለሁ ” አለው ።

ካፒቴን ባሩሽ ጌይስና የመቶ አለቃ ዮሴፍ ስተርን ለማረፍ እንዲ ቻል አራቆቹ ያስቀመጡአቸውን ብልጭ ድርግም የሚሉ መብራቶ ችም ሆነ እንዲመሩአቸው የተመደቡላቸውን ሦስት ኤፍ - 14 ጄቶች ማየት አልቻሉም ። ጌይስ ፀሐይ እስክትወጣ ድረስ በተራራው ላይ ለመቆየት ቢያስብብም ራዲዩኑን ከፍቶ ዴቪድ ቤከርና ጄኔራል ላስ ኮቭ ሲነጋገሩ ስለአደመጣቸው ነገሩ ለትንሽ ጊዜ እንኳን ፋታ የማይ ሰጥ መሆኑን ተረዳ ። አሁንም ቢሆን የዘገየ መስሎ ቢሰማውም በበኩሉ የተላከበትን ተግባራዊ ለማድረግ ቆረጠ ።

ካፒቴን ጌይስ ጦርነቱ በሚካሄድበት ተራራ በጠመንጃ ተተኩሶ ሊመታው በማይችል እርቀት ላይ ለመጠጋት ስለአሰበ የማረፊያ ምል ክቶቹን መፈለጉን ትቶ በካርታው ላይ ኡማ ተብሎ ወደ ተመለከተው አንድ ኪሎ ሜትር ወደ ደቡብ ሄደ ። ጌይስ ለሦስቱ ኤፍ - 14 ተዋጊዎች መሪ አብራሪ በራዲዮ “ ኡማ በሚለው አካባቢ ለማረፍ ስለምፈልግ የብርሃን ምልክት ትሰጡኛላችሁ ? ” ብሎ ጠየቀው ። አረብኛ እንደ እብራይስጥ ነበር፥የሚያስደንቅ ብሎ ጌይስ አሰበ ። ኡማ —ሕብረተሰብ።

የተዋጊው ጄት አብራሪ የመቶ አለቃ ሔርማን ሻፍራን መልስ ሰጠው ።

“ ሮጀር ፥ ለማረፍ የሚያስችልህ ብርሃን ይሰጥሃል ። ”

ኤፍ - 14 ተዋጊ ጄት ከምዕራባዊ ምሥራቅ በኩል መጥቶ 750.000 የሻማ ኃይል ያለው በፓራሹት ውስጥ ሲወረወር ቡግ ቡግ የሚል ስለ ወረወረ ሰማዩና መሬቱ በሰው ሠራሽ ብርሃን ተሞላ ።

ጌይስ የአውሮፕላኑን አፍንጫ በቀጥታ ወደታች አድርጎና የበ ረራውን ኃይል ቀንሶ በኃይለኛው ነፋስ ውስጥ ሲወርድ በፊት ለፊቱ በኡማ የሚያርፍበትን ቦታ አየ ። አውሮፕላኑን በመንደሩ በስተግራ በኩል ለማሳረፍ በሚሞክርበት ጊዜ የኃይለኛው ነፋስ ግፊት ከፍ ስለ አደረገው በጭቃው ሜዳ ላይ የሚንሳፈፍ አስመሰለው ።

የመቶ አለቃ ስተርን በቀኝ በኩል በመስኮቱ መካከል ሲመለከት በኡማ ባሉት ቤቶች ውስጥ እሳት ጭልጭል ሲል አየ ። ነፋሱ ብርሃን የሚሰጠውን ከእነፓራሹቱ ወደ ሰሜን እያወዛወዘ ስለወሰደውና በተ

ፈለገበት ቦታ ሊቆይ ባለመቻሉ አብራሪው የሚያርፍበትን ስፍራ በግልጽ ማየት አልቻለም ። ኤፍ - 14 በወንዙ ላይ ሌላ ብርሃን ሰጭ በፓራሹት ስለወረወረ እንጌይስ ወደ አሉበት ወደ ምዕራብ መንሳፈፍ ጀመረ ።

በውስጡ የነበሩት አምሳ ኮማንዶዎች የነፋሱንና የአውሮፕላኑን ከፍተኛ የሆነ ቀጭን ድምጽ ሰሙ ። በጂፖቹ ፋንታ 12 በሞተር የሚን ቀሳቀሱ ታንኳዎች ነበሩ ። በተሳፋሪዎቹ ክፍል ውስጥ የነበሩት ሰዎች አውሮፕላኑ በአየር ላይ የተንጠለጠለ ፤ የተንሳፈፉና ወደፊት የማይ ሄድ መስሎ ስለተሰማቸው ድንጋጤ አደረባቸው ። የተወረወረው የብ ርሃን ፍንጣቂ በመስኮቱ መካከል በመግባቱ በሰዎቹ የዓይን ቅንድ ቦችና ከንፈሮች ላይ የላብ ችፍታ ይታይ ነበር ።

ካፒቴን ጌይስ አውሮፕላኑን ሊያሳርፍ የሚችለውን መሳሪያ በኃ ይል ስለገፋውና ጐማዎቹ መሬት ስለነኩ እጅግ በጣም ብዛት ያለው ጭቃ ተበትኖ ቢያለብሰውም መንደሮቹ ወደ አሉበት አቅጣጫ አመ ራ ። በሰማይ ላይ ተወርውረው የነበሩት ሰው ሠራሽ የፓራሹት መብ ራቶች ስለጠፉ መሬቱ እንደገና ጨለማ ሆነ ።

ከጭቃ በተሠሩት ቤቶች ውስጥ የነበረው እሳት ጭል ጭል ሲል ይታይ ነበር ። ከኡማ ባሻገር ጌይስ የኤፍራጥስን ወንዝ አየ ። ፍሬኑን ስለያዘው አውሮፕላኑ በጣም ቅርብ ከነበረው ጉጆ 100 ሜትር ያህል እርቆ ቆመ ።

የኋላ በሩ ስለተከፈተ ሦስት ቡድን ኮማንዶዎች ወጥተው ወደ መንደሩ ሄዱ ። አራተኛው ቡድን በ100 ሜትር ክልል ውስጥ ሆኖ አውሮፕላኑን ለመጠበቅ ከበበ ። ወደዚያውም የቀበሮ ጉድጓዶች መቆፈር ጀመረ ። ሻለቃ ሳሙኤል ባርቶክ በኡዚው አከታትሎ ወደ ሰማይ ቢተኩስም የአጸፋ ተኩስ አልነበረም ። ከወንዙ ባሻገር በሰሜን በኩል የጦርነት ተኩስ ከመስማቱም በላይ ብልጭታው ይታይ ነበር ። ባርቶክ ካርታውን ተመለከተ ። በዚህ መንደር ውስጥ የሚቃ ወማቸው ከሌለ ወንዙን አቋርጠው ተራራውን በመውጣት ጦርነት በሚካሄድበት ቦታ ደርሰው ከአረቦቹ ጋር ጦርነት ለመግጠም 20 ደቂቃ ይፈጅባቸዋል ። ነገር ግን ከኋላ መጥተው ከኮማንዶዎቹ ጋር ጦርነት ቢገጥሙ ወደ ኮንኮርዱ እርምጃቸውን እንዳይቀጥሉ ለማ ድረግ የሚያስችል ዋስትና መስጠት አይችልም ። ምን ያህል ፍልስ ጥኤማውያን ነበሩ ? እንደ ኮንኮርድ አብራሪው አነጋገር ከሆነ ከ150 ወታደሮቻቸው ውስጥ የቀሩት ከሶስት አሥራ ሁለቶች አይበል ጡም ። በዚህ ዓይነት የሰላሙ መልእክተኞች የሠሩት ከፍተኛ ጀብዱ ሊታመን የማይችል ያመስላል ። ሻለቃ ባርቶክ በመገረም ፈገግ አለ ። አይሆንም - ያን ለማመን የማይቻል ነው በማለት ለማመን

አመነታ ። ለማንኛውም ለሚኖረው የኃይል ብዛት በበኩሉ መዘጋ ጀት አለበት ።

ኮማንዶዎቹ መንደሩን ከበቡ ። በሰሜን በኩል የእስራኤል ቡድን ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ ደረሰ ። የመጀመሪያው ሰው በኤፍራጥስ ወንዝ ዳርቻ የደረሰው ፕራይቬት ኤርቪንግ ፊልድ ሽንቱን በውሃው ላይ ሸና ።

ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ ሦስተኛው ቡድን በመንደሩ ደቡባዊ በኩል ወደ ኤፍራጥስ መድረሱን በራዲዮ አስተላለፈ ።

በሻለቃ ባርቶክ የሚመራው ሁለተኛው ቡድን በመሃል በኩል ወደ መጀመሪያዎቹ ጐጆዎች ሄደ ።

አንድ ሽማግሌ ሰው በአንድ ትንሽ መንገድ ወደ እነእርሱ እያ ዘገመ መጣ ። በኮማንዶዎቹ ራሶች በላይ አሻግሮ ሲመለከት በጭቃው ላይ በአረፈው አውሮፕላን ጅራት ላይ በተሳለው የዳዊት ኮከብ የመ ጀመሪያው የፀሐይ ፍንጣቂ ሲያብረቀርቅ አየው ። ቀኝ እጁን ወደ ላይ አንስቶ ” ሰላም ለእናንተ ይሁን ” አላቸው ።

ሻለቃ ባርቶክ በአረብኛ “ ሰላም ለአንተ ይሁን ” አለው ።

ሽማግሌው ጠንከር ባለ አነጋገር “ ሰላም ” አላቸው ።

ሻለቃ ባርቶክ ብቻ በነገሩ ተገረመ ። በባቢሎን አቅራቢያ የይ ሁዳ ሰዎች አሉ ማለትን ሰምቷል ። ጊዜ ቢኖረው ኖሮ ከሽማግሌው ጋር መነጋገር ይወድ ነበር ። ነገር ግን አንድ ደቂቃ እንኳን ስለአልነ በረው “ ሰላም ለአንተ ይሁን ” ብሎት እጁን አወዛወዘለት ። የቤ ቶቹን ቁጥር አይቶ የነዋሪዎቹን ብዛት ሲገምት ከ50 እንደማይበልጡ ገመተ ። ራዲዮ ለሚያስተላልፈው ሰው “ የአይሁዶች መንደር የአገ ኘን መሆናችንን ለኢየሩሳሌም አስተላልፍ ” ብሎት ካርታውን ከተ መለከተ በኋላ “ የመንደሩ ስም ኡማ ይባላል ። ወደ ኢየሩሳሌም ልናመ ጣቸው እንችል እንደሆነ ጠይቃቸው ። ወደ ኮንኮርዱ በወቅቱ ባን ደርስም ቢያንስ ይህን ተግባራዊ እናደርጋለን ” ብሎ ከትከሻው በመዞር ጮኾ ነገረው ።

በሲ-130 ግዙፍ አውሮፕላን ውስጥ የነበረው ካፒቴን ጌይስ መልዕክቱን ከራዲዮ ኦፕሬተሩ ተቀብሎ ለኢየሩሳሌም አስተላለፈ።

ካፒቴን ጌይስ በራዲዮ መልዕክቱን ሲያስተላልፍ ጠቅላይ ሚኒ ስትሩ ሰማው ። በአምንታ ራሱን ነቀነቀ ። የባቢሎን አይሁዶች - ነገር ግን የኢራቅ ዜጐች ናቸው ። የኢራቅ ዜጐች የሆኑ ሰዎችን አፍኖ ማም

ጣት የወዳጅነት ምልክት አያሆንም “ መስማማቱን በራዲዮ ሲያስ ስተላልፍ ባጭሩ ሊሰማው ስለሚችል የደከሙበት ሁሉ በአደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል ። ነ ሁንም ቢሆን ስለመመለስ በተጻፈው ሕግ ማንኛውም ወደ እስራኤል ለመመለስ የሚፈልግ አይሁዳዊ መመለስ እንደሚችል ተገልጿል ። አልፎ አልፎ ወደዚያ ለመምጣት መጠነኛ እርዳታ ይፈልጋሉ ። ለዚህም ተመሳሳይ ሁኔታዎች ነበሩ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በከፍሉ ውስጥ ወደነበሩት ሰዎች ሲመለከት ጥቂት ወንዶችና ሴቶች በአፅንኦት ራሳቸውን ነቀነቁ ። ጥቂቶቹ በአሉታ ራሳ ቸውን ወዲያና ወዲህ ኦሉ። ብዙ ሰዎች ደግሞ በፊታቸው ላይ ጭንቀት ይታይባቸው ነበር ። በዚህ ጉዳይ ላይ ውይይት ከፍቶ ለመከራከር ጊዜ ስለአልነበረ ውሳኔው የሚጠበቀው ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ነበር ። በድ ምጽ ማጉሊያው “ በቂ ቦታ አለህ ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ካፒቴን ጌይስ ፈገግ ብሎ “ ለእነእርሱ ቦታ እንዴት አይኖ ረንም ? አለው ።

“ መልካም . . . መልካም ፤ መምጣት ከፈለጉ . . . ወደ ቤታ ቸው መመለስ ከፈለጉ ይምጡ ” ከአለው በኋላ በወንበሩ ላይ ወደ ኋላው ለጠጥ ብሎ ተቀመጠ ። ታሪክ ለመሥራት — ምናልባት ጥፋት ለመሥራት—የሚያስከትለውን ውጤት ወይም ወደፊት የሚከተለውን ወቀሳ ችላ በማለት ውሳኔውን ሰጥቷል ። ኃይለኛውን ወይም አጨቃ ጫቂውን ውሳኔ ከወሰድህ በኋላ ሌላው ሁሉ ቀላል ይሆናል ። ጠቅ ላይ ሚኒስትሩ ተጨማሪ ቡና እንዲሰጡት አዘዘ ።

## — 35 —

ላስኮቭ ፀሐይዋ የመጀመሪያ ጨረርዋን በተራራዎቹና በሥራ ቸው ባሉት ሜዳዎች ላይ ስትረጭ አየ ። በሚያልፍበት ጊዜ ባቢሉንን በጨረፍታ አይቶ በውስጡ ምን ይኖር ይሆን ብሎ አሰበ ። በግብጽ ፒራሚዶች ላይ በር በነበረበት ጊዜ በዚያ መሬት ላይ ምን እንደነበረ እንደዚህ እንደ አሁኑ የማወቅ ፍላጐት አድሮበት ነበር ። ነገር ግን በአውሮፕላን ውስጥ ከቆዳ በተሠራ ወንበር ላይ ሆኖ ዓለምን እንዲ መለከት እጣ እድሉ ሆኖአል ። ብዙ ጊዜውን ያሳለፈው በዚህ ዓይነት ነበር ። ከዚህ ከአሁኑ ተልዕኮው በኋላ ግን በመሬት ላይ ከሕዝብዋ ጋር አብሮ እየተርመሰመሰ መኖር ይፈልጋል ።

ለሁለቱ ሲ - 130 ግዙፍ አውሮፕላኖች ከለላ ለሚሰጡት ጀቶች መልዕክት አስተላለፈ ። “ ሮጀር ፤ ከወታደሮችህ ጥቂቶቹ በተራራው

ላይ ወርደው እንዲያርፉ አድርግ ። መጠንቀቀ አለብህ።"ለመተኮስ እን ዲያመቸው ዝቅ ብሎ መጣ ። ፀሐይዋም ደማቅ ሆናለች ። ነገር ግን የአ ቧራው ውሽንፍር ባለመልቀቁ በጥቂት መቶ ሜትሮች እርቀት ላይ ሆኖ እንኳን መሬቱን በግልጽ ለማየት አልቻለም ።

ከምሥራቅ ቁልቁለት ከከተማው ክልል ውጭ ጀምሮ ከምሥ ራቅ ወደ ምዕራብ የነበረውን ቦታ በባለ 20 ሚሊ ሜትር መድፍ አረ ሰው ። እሥራኤሎቹ በጊዜያዊ ምሽግነት ሲጠቀሙባቸው ቆይተው የተዋቸውን ሁሉ ደበደባቸው ። አሁንም ቢሆን መሬቱ በአቧራ ውሽን ፍር ስለተጋረደ የሚፈልገውን እየመረጠ ለመምታት አስቸገረው ። በዚህ ምክንያት ወደፊት የሚገሰግሱትን አሸባሎች መርጦ ለመምታት አልሆነለትም ። በዚህ ዓይነት በሚደረግ ጦርነት በራስ ሰዎችም ላይ አደጋ ሊደርስ ይችላል ።

በድንገት ከፊት ለፊቱ ኮንኮርዱን አየው ። በዚያ አንድ ሴኮ ንድ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ አንዲት ሴት በኮንኮርዱ ክንፍ ላይ ስለአየ ሚሪያም ትሆናለች ብሎ አሰበ ። አንድ ሰው በመጣራት ላይ የነበረች ትመስላለች ። የኤፍራጥስን ወንዝ በሚያቋርጥበት ጊዜ ታጥፎ ከስድ ስት ኤፍ - 14 ተዋጊ ጄቶቹ ጋር ሆኖ ከሌሎቹ ተዋጊ ጄቶቹ ጋር የሥራ ልውውጥ ለማድረግ ወደ ደቡብ በረረ ። በአሁኑ ጊዜ ጄቶቹ ተሸከመ ውት የነበረውን ክብደት ለማቃለል ዕድል አጋጥሞአቸዋል ። የነዳጅ ምልክት ማሳያውን ተመለከተ ። እየተገለባበጠ በኃይል ይበር ስለ ነበረ ብዙ ነዳጅ መጠቀሙን አወቀ ። ስለዚህ ለመመለሻ እንዲበቃቸው ነዳጅ ሁሉም መቆጠብ ስለሚኖርባቸው የድምጽ ማጉሊያውን አን ስቶ " በዚህ አካባቢ የነዳጅ መሙሊያ የለም ይሆን ? ብሎ ጠየቀው ።

" መልካም " ብሎ ዳኒ ሌቮን " ከዚህ ወደ ግራ ታጥፈህ አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር ከበረርክ በኋላ ከሎድ አውሮፕላን ማረፊያ ታገኛ ለህ " አለው ።

ላስኮቭ ይህን አባባል ሲሰማ ለራሱ ፈገግ አለ ። በጭቃማ ሜዳው ላይ ባረፈው ሲ - 130 አውሮፕላን በላይ በሮ ሲያልፍ በመንደሩ አጠ ገብ በወንዙ ዳር ኮማንዶዎቹ በውሃው ላይ ለመሻገር የሚያስችላቸ ውን ታንኳ ሲያዘጋጁ አያቸው ። ሰዓቱን ሲመለከት ሲ - 130 ከአረፈ ሰባት ደቂቃ ብቻ ስለአነበረ ፍጥነታቸው መጥፎ አልነበረም ። " ገብ ርኤል 32 ፣ ያለሁት ከአንተ በላይ ነው ። ጥሩ አስተራረፍ ነው ። አሁ ንም ለማረፊያ የሚያገለግሉትን መብራቶች ማየት አልቻልኩም።መጥፎ ነገር እንዳይደርስብህ ደጋግሜ ክትትል አደርጋለሁ " ብሎ ለካፒቴን ጌይስ ነገረው ።

“ ሮጀር 32 ፣ በባቢሎን ውስጥ ጥሩ የሆነ ቅልጥፍና ያለው ሥራ አሳይተሃል ። በመሬት ላይ ያሉት እንዴት ናቸው ? ”

“ ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ ነው ። ”

ከጄቶቹ አንዱ ሲ - 130ን ፤ ሁለቱ ደግሞ ታንኳዎቹን እየተ ዟዟሩ እንዲጠብቁ ተደረገ ።

ላስኮቭ አሁን በምሥራቃዊው ወንዝ ዳርቻ ላይ ነበር ። በሲ -130 በላይ ወደ ሂላ መንገድ በረረ ። ትልቁን አውሮፕላን ኃይለኛ ነፋስ እያ ወዛወዘው ስለነበረ ሚዛኑን ጠብቆ በመሬቱ ላይ ቆሞ እንዲቆይ አብራሪው ሞተሮቹን ያላጠፋቸው መሆኑን ላስኮቭ ተመለከተ ።

ላስኮቭ በእንግዳ መቀበያው ቤት ፣ በቤተ መዘክሩና በኢሽታርበር ባሉት ግዙፍ የዘብ መጠበቂያ ግንቦች ላይ በረረ ። በእንግዳ ቤቱ ላይ ቦምብ ለመጣል ውስጠ ሕሊናው ቢገፋፋውም ኢየሩሳሌም እንዳያደርግ ከልክሎታል ። ዶብኪን በእንግዳ መቀበያው ቤት ውስጥ በሕይወት ይኖራል የሚል ስሜት ነበራቸው ። ላስኮቭ ግን አባባሉን አልተቀበ ለውም ነበር ። እንደዚሁም ቤከር ከአስተላለፈውና ከዶብኪን ሪፖ ርት ለመረዳት እንደተቻለው አንዲት እስረኛ ሴት በሕይወት ሳትኖር አትቀርም ። ሁሉም ነገር በቅርብ ጊዜ ውስጥ ይታያል ። ኮማንዶዎቹና ጂፖቹ ወደ አካባቢው እየተቃረቡ እንደነበሩ ላስኮቭ አይቷቸዋል ። ላስኮብ ውጊያ ይኖራል ብሎ ተጠራጥሮአል ። ሆኖም ውጊያው ከአስር ደቂቃ የበለጠ ከፈጀና ኮማንዶዎቹም አሸንፈው ሊገቡ ከአልቻሉና አስፈላጊ ሆኖ ከአገኘው የእንግዳ መቀበያ ቤቱንና ቤተ መዘክሩን ለመምታት ፈቃድ አለው ። ምናልባት በቤቱ ውስጥ እስራኤላዊ እስረኞች ቢኖሩ ሁኔታው እንደሚገባቸው አምኖአል ። ዶብኪን ራሱ ወታደር ስለነበረ አመቺ ከአልሆነ የዚህ ዓይነት እርምጃ እንደ ሚወሰድ ያውቃል ።

* * *

ዴቪድ ቤከር እንደገና የረዳት ኃይል ማመንጫውን ቁልፍ ስለ ከፈተው ቀስ ብሎ ከቀድሞው ባነሰ መዞር ጀመረ ። ባትሪዎቹ በፍጥ ነት እየደከሙ መጡ ። ይሁን እንጂ መቀጣጠልም ሆነ የሙቀት መለ ኪያው እንቅስቃሴ አልነበረም ። ወደ ካን ዞሮ “ አዝናለሁ ፒተር ” አለው ።

ከውጭ የተተኮሰ ጥይት በክፍላቸው ውስጥ ስለአረፈ ሁለቱም ለጥ አሉ ። ቤከር የነዳጅ ሽታ አፍንጫውን ስለሰነፈጠው ከነዳጅ መያ ዣዎቹ ወይም ከማስተላለፊያዎቹ ጥቂቶቹ የተመቱ መሰለው ።

“ እንደገና ሞክር ፣ እንደገና ሞክር ፣ ዴቪድ የሚቀርብን ነገር የለም ” አለው ካን ።

ቤከር በኃይል ጮኾ “ ሁሉም ነገር እያበቃለት ነው ። የነዳጁ ሽታ አይሰማህም ? ” አለው ።

“ ከጋለ የመዳብ ሽቦ ሽታ በስተቀር ሌላ አይደለም ፣ ሞክር ። ”

“ የመጨረሻዎቹን ባትሪዎች ለራዲዮ ማስተላለፊያ እፈልጋቸዋለሁ ። ”

“ ስለእግዚአብሔር ብለህ እንደገና ሞክር ። ”

ቤከር እስከ አሁን ድረስ ስለካን የሚያውቀው ትሁትና ሥራው ሁሉ እጥር ምጥን ያለ መሆኑን ብቻ ስለነበረ አሁን ስለአሳየው ጠባይ ተደነቀ ። በመጀመሪያ ወደ ረዳት ኃይል መስጫው ሞተር ማብሪያና ማጥፊያ ቀጥሎም ብትንትኑ በወጣው መስታወት መካከል ወደ ውጭ ተመለከተ ። ሦስት ወይም አራት አሽባሎቹ ከአንድ መቶ ሜትር ባነሰ እርቀት ላይ ከጉብታው በኩል ሲመጡ አያቸው ። አንድ ማርከስን የሚመስል ሰው በኤኬ - 47 ጠመንጃ ስለተኮሰባቸው ተንደባለው መደበቂያ ሲፈልጉ አያቸው ። በአሁኑ ጊዜ የፀሐዩ ጨረር የአሸዋውን ውሽንፍር እያለፈ ስለገባ በመጠኑም ቢሆን መታየት ጀምሯል ። አቧራ በሞላው ግራጫና አቧራማ የጧት ወገግታ ውስጥ የሰው ጥላ ስለአየ እነማን እንደሆኑ ቤከር በአድናቆት ተመለከታቸው ።

አንድ ኤፍ - 14 ዝቅ ብሎ መጥቶ በአጠገባቸው ስለበረረ ኮን ኮርዱ እንዲንቀጠቀጥ ከማድረጉም በላይ በአቧራ ሸፈነው ። ቤከር ሳያስበው የረዳት ኃይል መስጫ ሞተሩን ማብሪያ ነካው ። ወደ ካን ዞሮ “ አንድ ነገር እየሰማሁ ነው ? ” ብሎ ጠየቀው ።

ካን የሰማው ነገር ባይኖርም የተቀመጠበት ወንበር ሲንቀጠቀጥ ሰማው ። በኃይል ጮኾ “ ሞተሩ ተነሳ ! ጠግኜዋለሁ ! ” አለው ።

ከአሁን በኋላ ስለሚወስደው እርምጃ ካን ግድ እንደሌለው ቤከር ተሰምቶታል ። በእርሱ በኩል ያለመሰልቸት በአደረገው ያልተቋረጠ ጥረት ሥራውን ፈጽሟል ። ከአሁን በኋላ የሚቀረው የቤከር ሥራ ነው ። ረዳት የኃይል መስጫው ሞተር ለአንድ ደቂቃ ያህል እን ዲሠራ አደረገው ። ረዳት የኃይል ማመንጫው ባትሪዎቹን ሁሉ ስለ ሞላቸው የከፍሎቹ መብራቶች የበለጠ ብርሃን ሰጡ ። መለኪያዎችና ሌሎችም መሣሪያዎች እንደቀድሞአቸው ተስተካክለው መሥራት ጀመሩ ።

ቤከር ፊቱን ጠርጕና እጆቹን በሸሚዙ ላይ አሽቶ የአውሮፕላኑን የውጭ ቀኝ ሞተሩን ሲቀሰቅሰው ከኤል አል ጋራጅ አሁን ጥገና ተደርጐለት እንደወጣ ዓይነት ያለምንም ችግር ሠራ ። ወደ ካን መልከት ሲል ካን በአውራጣቱ የደስታ ምልክት ሰጠው ። ቤከር ነዳጅ የሚያሳየውን መሳሪያ ሲመለከት አመልካቾቹ አይንቀሳቀሱም ። በቀዩ መስመር ላይ ነበሩ ። አንዱ ሞተር የሌለውን ነዳጅ በብዛት ያቃጥል ነበር ። ቤከር ነገሩ አልገባውም ። አንድ ትክክል ያልሆነ ነገር መኖር አለበት ። በአውሮፕላኑ ውስጥ ከነበሩት አሥራ ሶስት የነዳጅ መያዣዎች አንዱ ውስጥ ዘይት የገባ መሆን አለበት ። የግራ ሞተሩን ቁልፍ ሲከፍተው በፍጥነት መዞር ጀመረ ። ከጭስ ማውጫው ውስጥ ነጭ ጭስ ከተፋ በኋላ ደህና የሚሠራ መሰለ ።

ካን ከተቀመጠበት ተነስቶ በረዳት አብራሪው መቀመጫ ፊት ለፊት ቆሞ ርዳታ ማድረግ ጀመረ ። መለኪያዎቹን ሲነካካቸው አይንቀሳቀሱም ። ኮንኮርድ 02 ከአሁን በኋላ እንደገና ተነስቶ ሊበር አይችልም የሚል ሃሳብ ቢያድርበትምና ቢገምትም በአጋጣሚ ይንቀሳቀስ ይሆናል - በማለት “ ተነሳ አንተ ሽማግሌ ጥንብ አንሳ ! ” አለው።

የውስጥ ሞተሩ ተነሳ ፤ ግን ድምጹ መጥፎ ነበር ። ቤከር በውጭ ያለውን አነስተኛ ሞተር ለማስነሳት ቢሞክርም ባትሪ እንደሌለው መኪና ዓይነት ምልክት እንኳን አልሰጠውም ።

“ወደ ሞተሩ የኤሌክትሪክ ኃይል አይደርስም ፤ ምናልባት ሽቦዎቹ ተበጥሰው ይሆናል ” አለው ካን ።

ቤከር ፍሬኑን አፍኖ ረግጦ የሚሠሩትን ሦስት ሞተሮች ቀሰቀሰ። በላያቸው ላይ የተከመረውና እየበነነ የገባው አሸዋ በአንድ ሴኮንድ ውስጥ ሞተሮቹን ሊያበላሻቸው ይችል ይሆናል ። ነዳጃቸውም በአልታሰበ ጊዜ ውስጥ ሊያልቅ ይችላል ። ቤከር በአንድ ጊዜ ፍሬኑን መልቀቅ አልፈለገም ። “ ሁሉም ወደ አውሮፕላኑ ውስጥ እንዲገቡ ንገራቸው ” ብሎ ለካን ነገረው ።

ካን ዘሎ ከነጂው ክፍል በመውጣት ወደ ተሳፋሪዎቹ ክፍል ሄደ ። በክፍሉ ውስጥ ቁስለኞቹ በወለሉ ላይ ተኝተዋል ። የሚችሉት ደግሞ ተቀምጠዋል ። ሴቶችና ወንዶች በተሰባበረው መስታዎት የጠመንጃ አፈሙዞቻቸውን አውጥተው ወደ አሸባሪዎቹ ለመተኮስ ይጠባበቃሉ ።

ካን ወደ ክንፉ ላይ ወጥቶ ሲመለከት አሥራ ሁለት የሚሆኑ ወንዶችና ሴቶች በጨለማው ውስጥ አሸባሪዎቹ ወደነበሩበት አቅጣጫ ያተኩሳሉ ። ጥቂት ሰዎች በመሬቱ ላይ ሆነው የሚተኩሱ አስመሰለው እንጣጥፈዋል ። የተኩስ ድምጽ የሚሰጠው ግን በካሬት ላይ ያቀዱት

ክር ነበር ። በዘዴ ለመጠቀሚያ ከሠሩአቸውና ከአዘጋጁአቸው ውስጥ የቀራቸው ይኸ ብቻ ነበር ። ካን በክንፉ መጨረሻ ላይ በርግን ስለ አየው እየሮጠ ሄዶ “ ልንቀሰቅሰው ነው ፣ ሁሉም ወደ ውስጥ እንዲ ገቡ አድርግ ” አለው ።

በርግ የሰማው መሆኑን በእጁ ምልክት ሰጠው ። እያንዳንዳ ቸው ተጠቃለው የመጡ መሆናቸውን ለማወቅ እየሞከረ ነበር ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ቡድኖች አሉ ። ራሳቸውን ለመግደል ሞክ ረው የነበሩት በዕቃ መጫኛው ክፍል ውስጥ አሉ ። የቆሰሉት በሙሉ ተሰብስበዋል ። የቀሩት በክንፉ ላይና በጉጆው አጠገብ በመከላከል ላይ እንደነበሩ እርግጠኛ ነበር ። ሆስነርንና ጆን መክለርን ለትንሽ ጊዜ ያያቸው የለም ። በርግ በክንፉ ላይ ሆኖ ጮኾ ተናገረ ። ሆኖም ምንም ያስጨነቀው ነገር አልነበረም ። ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ እያንዳንዱ ሰው አሸባሪቹም ጭምር በመሆን ላይ የነበረውን አውቀዋል ።

የመጨረሻዎቹ የታጠቁ ወንዶችና ሴቶች ከመሬት ወደ አውሮ ፕላኑ ላይ ወጥተው ግማሾቹ በክንፉ ላይ በተጠንቀቅ ቆሙ ። ግማ ሾቹ ደግሞ በጅራቱ አጠገብ ወጥተው የቆሙ ሲሆን ሌሎቹም ጠላ ትን ለማጥቃት በሚያመች ሁኔታ ቦታ ያዙ ። አልፐርን የማርከስን ሬሳ ተሸክሞ እየሮጠ መጣ ። ሌሎች አምስት ወንዶችና ሴቶች ተከ ትለው መጡ ። በርግ የስም ዝርዝራቸውን እንደገና ተመልክቶ ልክ መሆኑን አረጋገጠ ። ኮማንዶዎቹ ቆፍረው በማውጣት ሬሳዎችን ያመጡ ይሆናል ። የካፕላንንም አስከሬን እንደሚያገኙት እርግጠኛ ነበር ። ምናልባትም የደቦራ ጌዲዮንና የዶብኪንን ( ሞተው እንደሆን ) ያገኙ ይሆናል ። ከሆስነርና ከመክለር በስተቀር ሌሎቹ ተሰብስበው የመጡ ይመስላል ። ሆኖም ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ አልነበረም ። በማስታወሻው ላይ በፍጥነት ጽፎ ጫማውን አውልቆ በውስጡ ወረ ቀቱን ከአስቀመጠ በኋላ ጫማውን ከአውሮፕላኑ ውጭ ወረወረው ። ምናልባት ኮንኮርዱ ቢቃጠል ኮማንዶዎቹ ወደዚያ ሲደርሱ እንዲያ ገኙትና የሞቱትን ዝርዝር ለማወቅ የመንደርደሪያ ሃሳብ እንዲሰጣቸው ነበር ።

አልፐርን የማርከስን አስከሬን ተሸክሞ እመግቢያው ላይ እንደ ደረሰ በርግ እየሮጠ መጥቶ “ ሆስነርስ ? ” ብሎ ጠየቀው ። አልፐርን ትከሻውን ነቅነቅ አድርጎ “ እንደማይመጣ ታውቃለህ ” አለው ። በርግ በአዎንታ ራሱን ነቅንቆ የሚሪያም በርንስቴይንን ዓይን ሲመ ለከት አልፐርን የተናገረውን እንደሰማች ገባው ።



ADDIS ABABA ... HAILE LIBRARY

ወደ አውሮፕላኑ ጠርዝ ሮጣ መጥታ ለመዝለል ስትንቀሳቀስ በርግ ክንድዋን ይዞ ወደ ኋላ ጐተታት ። እየተንፈራገጠች ክንድዋን ለማስለቀቅ ብትሞክርም አጥብቆ ስለያዛት እንዲለቃት ጮኸችበት ። ከአንዲት ሴት ጋር ተባብረው በመያዝ ወደ መግቢያው አመጧት ።

የእስራኤሎቹ ኮማንዶዎች ከኋላቸው እየተጠጓቸው እንደሆነ አሸባሎቹ አውቀዋል ። የመጨረሻ የጉብዝና ችሎታቸውን ቢያሳዩም ከአቅማቸው ውጭ እየሆነባቸው መጥቷል ። በጣም ደክመው ስለነበረ ደንዝዘዋል ፣ ወደፊትም የሚያደርጉትም እርምጃ ሥቃይ ሆኖባቸዋል ። አፎቻቸው ፣ የአፍንጫዎቻቸው ቀዳዳዎችና ጆሮዎቻቸው በአቧራ ተሞልተዋል ። ዓይኖቻቸው በአሸዋ ታውረዋል ። ከፊታቸው ለአሉት እሥራኤሎች ሳይሆን ከኋላቸው ስለአሉት እሥራኤሎች ማሰብ ጀምረዋል ። ወደፊት መጓዛቸውን የቀጠሉት በሕይወት ለመኖር እስራ ራኤሎችን ማሸነፍ አውቀው ብቻ ሳይሆን አህመድ ሪሽና ሳሌም በሚያደርጉባቸው ጩኸትና ማስፈራራት ጭምር ነበር ። አሸባሎቹ አሁን በአሉበት ሁኔታ እንኳን በጣም አደገኞች ነበሩ ። እንደ ወን ዶና ሴቴ ነብሮች ነበሩ — የአንበሳ ግልገሎች ከመሆን አልፈዋል —

ሪሽ ሁለት እህትማማቾች ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ሲሄዱ አገኛ ቸው ። ከኋላ በተተኮሰው ፣ በድካም ፣ በአቧራውና በጨለማው ምክ ንያት ተደናግረው መሆናቸውን ቢያስረዱትም ሪሽ አስገድዶ በማንበ ርከክ ከኋላቸው በሽጉጥ ራስ ራሳቸውን መትቶ ገደላቸው ።

ሀማዲ በተደረገው የግፍ ድርጊት በጣም ተነካ ። የልፋት ዋጋም ይህ ዓይነት በመሆኑ ተገረመ ። ሪሽ ያደረገው ለጊዜው ሠርቶለታል። አሁን የቀሩት ሁለት አስራሁለቶች ወደሚያጉረመርመው ኮንኮርድ ፈጠን በአለ እርምጃ ቀጠሉ ። ሪሽ ሰዎች አመጽ ከማንሳታቸው በፊት አምባገነን ወንዶችና ሴቶች የሚወስዱትን ጨካኝ እርምጃ በመፈ ጸሙ ተደሰተ ።

* * *

ሆስነር የኮንኮርዱን መነሳት በመጀመሪያ ሲሰማ ተደነቀ ። ቀጥ ሎም ካን ደከመኝ ሳይልና ሳይሰለች የሠራውን ስለአስታወሰ ፈገግ አለ ። አፍንጫው መሬት ሰርጐዶ የገባውን ፣ ዋና ጐማዎቹ የፈነዱ ትንና ብዙ ብልሽቶች የደረሱበትን አውሮፕላን ቤከር ሊያንቀሳቅሰው ይችል ይሆን ? በማለት አሰላሰለ ። የፈለገው ይሁን ሙከራው አስደናቂ ነበር ። ኮማንዶዎቹ በፍጥነት እየተንቀሳቀሱ ቢሆንም ፍጥነታ ቸው በቂ አልነበረም ። ከኮንኮርዱ ጋር በምሥራቃዊ ቁልቁለት ቢገ ናኙ ትልቅ ልዩነት ይኖረዋል ። ይህ እያንዳንዳቸውንና ዴቪድ ቤከ ርንም ጭምር ያስደንቃቸው ነበር ብሎ ሆስነር ገመተ ። ካን ረዳት የኃ

ይል መስሚውን እንደሚጠግነውና ከዚያ ተንቀሳቅሰው እንደሚ ሄዱ ራሱ ካን አውቋል ።

ሆስነር ተንበርክኮ ከተኮሰ በኋላ እንደገና ወደኋላው አፈገፈገ ። ከኮንኮርዱ በኩል ተኩሱ ወደ እርሱ እየተጠጋ ቢመጣም ምንም ማድ ረግ አልቻለም ። ከእሥራኤሎቹ በኩል የሚተኮሰው እምነት የማይጣ ልበትና እየቀነሰም መምጣቱን አውቋል ። በድንገት የሞተሩን ከፍ ተኛ የሆነ ቀጭን ድምጽ ስለሰማ ቤከር ለማንቀሳቀስ ፍሬኑን እንደ ሚለቅ ገባው ። ገልመጥ ብሎ ሲመለከት የሞተሮቹን ቀይ ፍም መም ሰል አየ ። ወደ ኋላው ዞሮ ሲያይ አሽባሎቹ በአቧራው ውስጥ መስመር ይዘው እየሮጡና እየተወላከፉ ሲመጡ ተመለከታቸው ። ከኤፍ -14 ተዋጊ ጀቶች ፣ ከኤ-47 ጠመንጃዎችና ከሞተሮቹ ጩኸት በላይ አህመድ ሪሽ “ ፍጠኑ ! ፍጠኑ ! ይህ የመጨረሻ ጥረታችሁ ነው ! አሁን ከአልሆነ ምንጊዜም አይሆንም ! በርቱ የእኔ የነብር ግልገሎች ! ለጠላት ግድያ ተከተሉኝ ! ” ብሎ ሲናገር ሰማው ።

ሆስነር ወንዶችና ሴቶች አህመድ ሪሽን ለምን እንደተከተሉት ገብቶታል ። የድምጹ አጣጣል ከቀድሞው የተለወጠ አልነበረም ። ቋንቋው በአረብኛ ፈንታ ጀርመንኛ ቢናገር እንኳን ድምጹን ለመ ለየት ችግር አይኖርበትም ነበር ። ጥቂት ሰዎች በተፈጥሮአቸው የአዛ ዥነት ስጦታ አላቸው ። ነገር ግን አዕምሮአቸው ሲረበሽ የሚይዙ ትንና የሚጨብጡትን በማጣት ውጤታቸው ዋጋ ቢስ ይሆናል ።

ሆስነር ለመቃብር በተቆፈረው ቦይ ውስጥ ገባ ። እግሩ በሰዎቹ በድን ላይ ስለአረፈ የሞቱት እነማን ይሆኑ ብሎ አወጣ አወረደ ።ጠመ ንጃውን አቀባብሎ በጨለማው ውስጥ አህመድ ሪሽን መጠበቅ ጀመረ።

* * *

የመቶ አለቃ ጀሹዋ ጊደል ኮማንዶ ቡድን በቤተ መዘክሩ ኋላ እንዲቆይ የተደረገ ሲሆን የቀሩት ሁለት ቡድኖች ከአንዱ ጂፕ ጋር በኢሽታር በር በኩል አልፈው ሄዱ ።

የጊደል አስር ሰዎች ባለ 106 ሚሊ ሜትር አውቶማቲክ ጠመንጃ የተጠመደበትን ጂፕ በግራና በቀኝ አጅበው ቤተ መዘክሩንና የእን ግዳ መቀበያውን ቤት በሚለየው አቧራማ መንገድ መሄድ ጀምረዋል ። በጂፑ ውስጥ የመቶ አለቃ ጊደል ፣ ነጂው ፣ ሁለት ጠመንጃ የያዙና ዶክተር አል - ታኒ - የቤተ መዘክሩ ሃላፊ - ነበሩ ። የመቶ አለቃ ጊደል ዶክተር አል - ታኒን ያገኘው በጽሕፈት ቤቱ ውስጥ ነበር ። ዶክተር አል - ታኒ በጽሕፈት ቤቱ ውስጥ ሆኖ በውጭ ምንም እንዳልደረሰ ዓይነት አድርጐ ወደፊት ለጉብኝት የሚመጡትን ሰዎች ስም ዝርዝር አንድ በአንድ ይመለከት ነበር ።

የቤት መዘክሩ ሐላፊ ከጊደል ጋር ሆኖ ጊደል ወደሚፈልገው በጥቂት መቶ ሜትር እርቀት ላይ ወደሚገኘው ቦታ አብረው እየተጓዙ ነበሩ ። “ በእንግዳ መቀበያው ቤት ውስጥ ምን ያህል አሸባሎች ያሉ ይመስልሃል ? ” ብሎ ጊደል ጠየቀው ።

ዶክተር አል-ታኒ የእንግዳ መቀበያ ቤቱን ያውቀዋል ። “ ለእኔ አይነግሩኝም ፡ ወጣቱ ሰው ። ቢሆንም አምሳ ያህል ልዩ ልዩ የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸው ፡ ከአስር በላይ ረዳቶችና አንድ ዶክተር ፡ ጥቂት ዘብ ጠባቂዎችና ተረኛ መኰንኖች ይኖራሉ ብየ እገምታለሁ።”

“ በግንቡ ውስጥ የምድር ቤት አለ ? ”

“ የለም ። ”

“ በሙሉ ሕንጻ ነው ? ”

“ አዎን ። ”

“ እንግዳ ይኖር ይሆን ? ”

“ የለም ፡ የጉብኝቱ ወራት አልጀመረም ። ”

“ ሲቪል ወይም የጦር ሰው ያልሆነ ይኖር ይሆን ? ”

“ አንዳንድ ጊዜ ከመንደር የሚመጡ ጥቂት ሴቶች ። ”

“ ራዲዮ አለ ? ከመስክ ላይ ከአሉት አሸባሎች ጋር ይነጋገራሉ?”

“ አዎን ፡ በመተላለፊያው ተረኛ ሰው በሚቀመጥበት ክፍል ራዲዮ አለ ። ”

“ ቁስለኞቹ የራሳቸው መሳሪያዎች አሉአቸው ? ”

“ አዎን ። ”

“ ከባድ መሳሪያዎች ? የእጅ መትረየሶች ? የሮኬት መተኮሻ ዎች ? አዳፍኔዎች ? የእጅ ቦምቦች ? ”

“ የምትላቸውን ዓይነት አላየኹም ። ”

“ እስረኛ የሚያስቀምጡት የት ነው ? ”

“ በሥራ አስኪያጁ ጽሕፈት ቤት ውስጥ አንዲት ሴት እሥረኛ አለቻቸው ። ”

“ እስራኤላዊት ? ” ዶብኪን ለኢየሩሳሌም ከሰጠው ሪፖርት ጊደል ስለ እስረኛዋ አውቋል ።

“ ናት ብየ አምናለሁ ። ”

" ስለጄኔራሉስ ? " ጊደል ቀደም ብሎ ስለጄኔራሉ የሚያውቀውን ሁሉ ነግሮታል ። ነገር ግን አል-ታኒ የተባለውን አላመነም ። ምናልባትም በእርሱ ወዳጅነት የተነሳ እስራኤሎቹ ሊጠቀሙበት የፈለጉ መስሎ ታየው ። " ጄኔራሉን ግን አላየኸውም ? " ብሎ በድጋሚ ጊደል ጠየቀው ።

" የአላየሁት መሆኑን ነግሬሃለሁ ። "

" ስለጄኔራሉ የሰማኸው ምንም ነገር የለም ? "

" ቢኖር እነግርህ ነበር ። "

" በሌላ ቦታ እስረኛ ያስቀምጣሉ ? "

" አላውቅም ። ክፍሎቹ በቁስለኞች ተሞልተዋል ። ማድቤቱም ምግብ የሚዘጋጅበት ነው ። የሙዝናኛ ክፍሉንም ምግብ ቤት አድርገው ይጠቀሙበታል ። እንደማስበው የሥራ አስኪያጁን ጽሕፈት ቤት ለዚህ ዓይነት ነገር የሚጠቀሙበት መስሎ ይታየኛል ። ከእርሱ ጥሪ ደርሶህ ተነጋገርኩ ከአልክበት ጊዜ ወዲህ ወደ እንግዳ ቤቱ አልሄድኩም ። ስለዚህ ምናልባት ይኖር ይሆናል ። "

ጊደል ቀጥ ብሎ የእንግዳ መቀበያውን ቤት ሲቃኝ በመስኮቶቹ መካከል መብራቶች ስለአየ " የሥራ አስኪያጁ ጽሕፈት ቤት የት ነው ? " ብሎ ጠየቀው ።

" ወደ መተላለፊያው እንደገባህ ልክ ከፊት ለፊት ባለው መዝጊያ በስተግራ በኩል ያለው ክፍል ነው ። መስኮቶቹ በፊት ለፊቱ ናቸው ። "

" ሐላፊው ማነው ? "

" አል - ባከር የሚባል ሰው ነው ። "

" የሚግባባ ወይም ስምምነት የሚያደርግ ነው ? "

ዶክተር አል -ታኒ ይህን አነጋገር ሲሰማ በመጠኑ ሳቀ ።

" ማለቴ ቁስለኞቹ ውጊያ ከሚገጥሙ ይልቅ ወደ ስምምነት የሚያመራ ሰው ነው ብለህ ታስባለህ ? "

" አንተ ጠይቀው ። "

የመቶ አለቃ ጊደል ወደ ሕንጻው ተመለከተ ። በዚያ በኩል የሚያደርገውን እንቅስቃሴ አንድም ሰው አለማየቱ የማይታመን ነገር ነበር ። ኮማንዶዎቹ ከጂፑ ግራና ቀኝ ሆነው ወደፊት መሔዳቸውን ቀጥለዋል ። የእንግዳ መቀበያ ቤቱ በአሁኑ ጊዜ በግልጽ ይታ

ያል ። ጊደል በኮከብ ብርሃን የሚያሳየውን የመስክ መነጽሩን በዓይ ኖቹ ላይ አድርጎ ሲመለከት በሕንጻው ፊት ለፊት የተተከሉ ድንኳኖች አየ ። በቤቱ ዙሪያ የነበሩት ባሕር ዛፎች በረንዳው በግልጽ እንዳይ ታይ ከልለውታል ። በቤቱ በስተግራ በኩል ጥቂት መኪናዎች ቆመ ዋል ። በጥቂት መስኮቶች መካከል መብራቶች ጭልጭል ሲሉ ይታ ያሉ ። ከማድቤት የሚወጣው ጭስ ይታያል ። ምናልባትም ቁርስ እያ ዘጋጁ ይሆናሉ ። ጥቂት ሰዎች በየበረንዳዎቹ ላይ ተቀምጠዋል ። እስከ አሁን አንድም ሰው ያያቸው አልመሰለም ። ወደ አል - ታኒ ዞሮ "በቂ ምክንያት ይዘው ቢያነጋግሩት የሚቀበል ይመስልሃል ? ልታግባባው የምትችል ይመስልሃል ? " ብሎ ጠየቀው ።

" እኔ " ብሎ በአሉታ ራሱን ነቀነቀ ። " እኔ—ነኝ ወይም እስረ ኛቸው ነበርኩ ። ስለዚህ ነገር እንዳትሳሳት ። እኔ የእነዚህ ሰዎች ወገን አይደለሁም ። "

ጊደል ሃሳቡን አሰባስቦ ወደ እንግዳ መቀበያው ቤት ዞረ ።

ዶክተር አል - ታኒ በጥንቃቄ እጁን በመቶ አለቃው ትከሻ ላይ ጣል አድርጎ " አንተ ወጣት ሰው ፡ ወዳጄ ጄኔራል ዶብኪን በዚያ ውስጥ ታስሮ በሕይወት ያለ ከሆነ ከዚያ ውስጥ እርሱን ለማውጣት የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ ። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ከሌሎቹ ጋር ልዩነት ይኖራቸዋል ብየ የምናገረው የለኝም ። በሌላዋ ምርኮኛ ላይ የፈጸሙትን ተመልክቻለሁ ። ጄኔራል ዶብኪን እስረኛቸው ከሆነ በድብደባ ወይም በጥይት ገድለውታል ። ለዚህም እመነኝ ። በዚህ ላይ ጊዜህንም ሆነ ሰዎችህን አታጥፋ " አለው ።

የመቶ አለቃ ጊደል በመነጽሩ ሰዎች በበረንዳው ላይ ሆነው አተኩረው ሲመለከቱ አያቸው ። ነጭ ጨርቅ አሽርጠዋል ። አንዳን ዶቹም ፋሻ አስረዋል ። ድምጽና ብልጭታ ወደሚያዩበት ወደ ሰሜን የጦር ምሽግ ይመለከቱ ነበር ። እርሱን ያዩት አልመሰሉም ። በኋላ ግን በላይኛው በረንዳ ላይ የነበሩ ሰዎች ወደ እርሱ አቅጣጫ ሲመለ ከቱ አያቸው ። ወደ እነእርሱ እየተመለከተ እያለ ለዶክተር አል - ታኒ "አመሰግናለሁ ዶክተር፡ከእኛ ጋር መሄድ ከአልፈለግህ በስተቀር ከጂፑ ላይ ወርደህ መሄድ ትችላለህ " አለው ።

" ከእናንተ ጋር አልሄድም ፡ መልካም ዕድል ፡ አመሰግናለሁ" ብሎ በመሄድ ላይ ከነበረው ጂፕ ዘሎ ወረደ ።

የመቶ አለቃ ጊደል ብዙ ሰዎች እየሮጡ ወደቤቱ ውስጥ ሲገቡ ስለአያቸው " ፍጥነት ጨምር " አለው ። ጂፑ፡ ፍጥነቱን ስለጨመረ ኮማንዶዎቹ በሙራመድ ፋንታ መሮጥ ጀመሩ ። " አትርሰህ ለመተኮስ

ተዘጋጅ ። ” ባለ 106 ሚሊ. ሜትር አውቶማቲክ ጠመንጃ አገርሰው አነጣጠሩ ።

ከእንግዳው መቀበያ ቤት በድንገት የተተኮሱ ሁለት ጥይቶች በላያቸው ላይ ጥዝ ብለው አለፉ ።

የመቶ አለቃ ጊደል በስምምነት ለማድረግ የሚሞክረው ድርጊት እንደ አከተመለት አወቀ ። በተከታታይ የተተኮሱት ጥይቶች ጂፑን አልፈው በመሬቱ ላይ አረፉ ።

የጂፑ ነጂ ለመቶ አለቃ ጊደል የራዲዮ ስልክ ስለሰጠው “ ለአየር ክለላ ነው ” አለው ።

የመቶ አለቃ ጊደል ስልኩን ተቀብሎ “ ምሥራቅ ወንዝ ዳርቻ ፤ ሁለት - ስድስት ነኝ ” አለው ።

“ ሮጀር ፤ ይህ ገብርኤል 32 ነው ። ቤቱን መትቼ ድምጥማጡን ላጥፋላችሁ ? ”

“ አይሆንም ፤ ገብርኤል ። ምናልባት በውስጡ ወዳጆቻችን ሊኖሩ ስለሚችሉ እኛው እንጋፈጠዋለን ። ”

“ ሮጀር ፤ ሃሳብህን የምትለውጥ ከሆነ ንገረን ። ”

“ ሮጀር ፤ አመሰግናለሁ ። ” ጊደል ወደ ተኳሾቹ ዞሮ “ በግራ በኩል ያለውን ምድር ቤት ሳትነኩ ተኩስ ጀምሩ ” ብሎ አዘዛቸው ።

በባለ .50 ካሊበር የተተኮሰው ጥይት በሁለተኛው ፎቅ ላይ አረፈ ። በባለ 106 ሚሊ. ሜትር አውቶማቲክ ጠመንጃ አከታትለው ስለተኮሱ ጆሮ የሚበጥስ ፍንዳታ ተሰማ ። ሕንጻውም ብትንትኑ ወጣ ። መብራቶቹና መስኮቶቹ ተሰባበሩ ። ቤቱ በጭስ ተሞላ ። መብራቶች በሙሉ ጠፉ ። የመቶ አለቃ ጊደል ፍጥነት እንዲጨምር ለነጂው ነገረው ። ኮማንዶዎቹ በምብ የሚተኩሰውን ኤም - 79 መጣሪያ የእጅ መትረየሶችና ኤም - 16 አውቶማቲክ ጠመንጃዎች እየተጠቀሙ ወደ ፊት መገስገስ ጀመሩ ። ባለ 106 ሚሊ. ሜትር አውቶማቲክ ጠመንጃ እንደገና ስለተተኮሰ ጥይቱ መዝጊያውን ሰብሮ በመግባት በመተላለፊያው ላይ ፈነዳ ። ሁለት ኮማንዶዎች መሮጣቸውን አቁመው ፤ ኤም - 16 ቀላል አውቶማቲክ የእጅ መትረየሳቸውን አስተካክሉ ። በባለ 7.62 ሚሊ. ሜትር ጥይቶች እየተኮሱ ሕንጻውን ደበደቡት ።

ጂፑና ኮማንዶዎቹ ከሕንጻው በ200 ሜትር እርቀት ላይ ደረሱ ። አሸባሪዎቹ ባለ 106 ሚሊ. ሜትር አውቶማቲክ ጠመንጃ ከተተኮሰባቸው

በኋላ የአጸፋ ተኩስ መስጠት አቆሙ ። ለሦስተኛ ጊዜ የተተኮሰው 106 ሚሊ. ሜትር ጥይት ከፊት ለፊቱ መግቢያ በስተቀኝ በኩል በተሰ ባበረ መስኮት መካከል አልፎ በቤቱ ውስጥ ስለፈነዳ በቀኝ በኩል የነበረው ሕንጻ ግማሹ እየተናደ ወደቀ ። የእሳት ነበልባልና ጭስ በየ መስኮቶቹ ወጣ ። ከፊት ለፊት የነበሩት በረንዳዎች አንዱ በሌላው ላይ እየተሰባበሩ ተንኳኰቱ ። ነጭ ጨርቅ ያሸረጡ ወንዶችና ሴቶች በየ መስኮቱ እየዘለሉ በመውጣት ወደ መኪናዎች ሮጡ ። በኤም - 60 መትረየስ ወደ ቆሙት መኪናዎች በማከታተል ስለተተኮሰባቸውና ስለፈነዱ ወደዚያ ይሮጡ የነበሩት ሰዎች ወደ ጨለማው እየሸሹ ጠለቁ ።

የመቶ አለቃ ጊደል ቁስለኞች ያሉበትን ቤት በጥይት ለመምታት ምኞትም ሆነ ፍላጐት አልነበረውም ። ከዶክተር አል-ታኒ እንደተነገ ረውና ከጄኔራል ዶብኪን ሪፖርት እንደሰማው ከሆነ ጠቅላይ የጦር መምሪያው ጽሕፈት ቤትና እስረኞች የሚቀመጡበት አንድ ነበር ። በተጨማሪም በመጀመሪያ ጦርነት የከፈቱት አሸባሎቹ ነበሩ ። አሸ ባሎቹ የሕክምናና የወታደራዊ ድርጅቶችን አብረው ማድረጋቸው ከዓለም አቀፍ ሕግ ውጭ ነበር ። ሆኖም አሁን ዋጋቸውን እያገኙ ነበሩ ።

በ50 ሜትር እርቀት ላይ በባለ 106 ሚሊ. ሜትር አውቶማቲክ ጠመንጃ በፊት ለፊቱ በር መካከል ስለተተኮሰ ጥይቱ በመተላለፊያው ላይ ፈነዳ ። በዚህ ጊዜ የተተኮሰው ከሚያስለቅስ ጋዝ ጋር ስለነበረ ጭሱ ይወጣ ነበር።ድብልቅልቅ ያለ ጩኸትና ጫጫታ ከውስጥ ተሰማ።

ጂፑ ወደ ድንኳኖቹ ፣ ከዚያም ወደ ደረጃዎቹና ወደ በረንዳው ተጠጋ ። ነጅው የመኪናውን የፊት መብራቶች ስለአበራላቸው እያንዳ ንዱ ኮማንዶ በመስኮቱ መካከል ወደ ውስጥ እየዘለለ ገባ ። በቤቱ ውስጥ በሞቱና በመሞት ላይ በነበሩት ሰዎች ላይ የተንኮታኮተው ድንጋይና አቧራ በላያቸው ላይ ተከምሮባቸዋል ። ከመተላለፊያው በላይ የነበረው የፎቁ ወለልበመደርመሱ የሚቃጠሉ አልጋዎች ነበሩ። በጥግ በኩልም በሽተኞች ተጋድመው ነበር ። እስራኤሎቹ ፊታቸውን በጋዝ መከላከያ ሸፍነው በኮሪደሩ በኩል ባሉት በሮች የሚያስለ ቅስ ጋዝ ወደ ውስጥ ወረወሩ ። ሁለት ኮማንዶዎች በጣሪያው ቀዳዳ በመጠቀም የሚያስለቅስ ጋዝ ተኮሱ ። ሁለት ሌሎች ኮማንዶዎች በኋላ በር በኩል ወጥተው ሲመለከቱ አሥራ ሁለት ያህል ወንዶችና ሴቶች ጨርቅ ያሸረጡና ዩኒፎርም የለበሱ ውጋጋኑ አነስተኛ ወደ ሆነው ጨለማ ሲሄዱ የተቃወማቸው አልነበረም ።

በመተላለፊያውና በሮቹ ላይ የማቃሰትና የማልቀስ ድምጽ ይሰማ ነበር ። የተቃጠለና በደም የተበከለ የሌሊት ልብስ የለበሱና በድን ጋጤ የተርበተበቱ ወንዶችና ሴቶች እጆቻቸውን በራሶቻቸው ላይ አድርገው በጋዙ ምክንያት እየሳሉ ፡ እያስታወኩና እየተጨናበሱ በሰልፍ በደረጃው ላይ ወርደው መጡ ።

የመቶ አለቃ ጊዶል ዘሎ ወደ ሥራ አስኪያጁ ጽሕፈት ቤት ገባ ። ከመስነጣጠቁ በስተቀር ቤቱ አልፈረሰም ። አቧራው ከጣራያው ላይ እየበነነ በመውረድ ላይ ነበር ። ጊዶል በመጀመሪያ ልጅቱን አይቶ ወደ እርስዋ ሲሮጥ አንድ ነገር እግሩን ስለአደናቀፈው እንድ እጅና እግሩን የታሠረና በሆዱ ተደፍቶ የተኛ ሰው አየ ። በሰውነቱ ግዙፍነትና በእርገዝሙቱ ጀኔራል ዶብኪን መሆኑን አወቀው ። በጥንቃቄ ገለበጠው ። በፊቱ ላይ ደም ይፈልቅ ነበር ። አንድ ዓይኑ በዓይኑ ጅማት በጉንጩ ላይ ተንጠልጥሏል ። ጊዶል በጣም ስለዘገነነው ራሱን ለማጠናከር ለአንድ ሴኮንድ ያህል ዘወር አለ ። በኃይል ከተነፈሰ በኋላ ተመልሶ ተመለከተው ። በተሰበረው አፍንጫው አጠገብ ፍልቅ ፤ ፍልቅ የሚለውን ደምና የከንፈሮቹን እንቃንቅ እስከ አየ ድረስ ሰውየው ይሙት ወይም አይሙት መናገር አልቻለም ።

የሕክምና ባለሙያው ወደ ልጅቱ በቀጥታ ሄዶ ከአዳመጣት በኋላ “ ሕይወትዋ አለ ። ድንጋጤ ነው ” ብሎ ወደ ዶብኪን ዞሮ በመንበርከክ መረመረው ። “ ጀኔራሉ ተዳክሟል ” ብሎ በደም የተበከለውን ልብሱን ከአየ በኋላ “ ጉዳቱ እምኑ ላይ እንደሆነ እግዜር ያውቃል ። በጄቱ ወደ ሲ - 130 በአስቸኳይ መወሰድ አለባቸው ” አለው ።

“ እሺ ” ብሎ ጊዶል ነጂውን በመስኮቱ መካከል ጠርቶ “ ለሲ - 130 ሁለት ቁስለኞች - አንድዋ በድንጋጤ ሌላው ደግሞ በደም መፍሰስ - ይዘን ስለምንመጣ እንዲዘጋጁ ንገር ። ቀጥለህም ሁለቱን የባቢሉን ምርኮኞች በሕይወት ያገኘን መሆናችንን ለኢየሩሳሌም አስተላልፍ” አለው ። ወደ ሐኪሙ ዞሮ ሌሎቹ ከእነዚህ በተሻለ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ተስፋ አደርጋለሁ ” ከአለው በኋላ በውጭ በሚያሳዝን ሁኔታ በመሰለፍ ላይ ወደ ነበሩት ወንዶችና ሴቶች ተመለከተ ። እንደገና የጄቱን ነጂ ጠርቶ “ጥቂት ባቢሎናውያን እንዳሉን ንገር ” አለው ።

— 36 —

ሁለት በተራራው ግርጌና ጥግ ሆነው አካባቢውን የሚጠብቁ አሽባሎች የእስራኤሎቹ ኃይል በታንኳ በወንዙ ላይ ሲመጣ አዩ ። በታንኳዎቹ ተሳፍረው በመምጣት ላይ የነበሩት የእሥራኤሎቹ ብዛት ከሠላሳ በላይ ነበር ። ለአንድ የሰለጠነ እግረኛ ወታደር በእስራኤሎቹ ላይ አነጣጥሮ ለመምታት የሚያስቸግር ነገር አልነበረም ። አሽባሎቹ

የነበሩበትን ጉብታ ከለላ በማድረግ በአውቶማቲክ ጠመንጃዎች ተኮሱባቸው ። ውሃው በታንኳዎቹ ላይ በኃይል ተረጨባቸው ። ወደዚያው ሦስት ታንኳዎች ከመመታታቸውም በላይ ብዙ ሰዎች ቆሰሉ ። እስራኤሎቹ የአጸፋ ተኩስ ቢያደርጉም ለመከላከል እጅግ በጣም በሚያስቸግር ቦታ ላይ ስለነበሩ ሻለቃ ባርቶክ ወደ ምሥራቅ ዳርቻ እንዲመለሱ አዘዛቸው ።

የእስራኤሎቹ ኮማንዶዎች ወደ የብስ ወጥተው በወንዙ ዳርቻ መሄድ ጀመሩ ። ከተተኮሰባቸው ቦታ ለመድረስ ግማሽ ኪሎ ሜትር ያህል ይቀራቸዋል። አሁን የሚተኩሱባቸውን አሸባሎች ከአስር ደቂቃ ባነሰ ጊዜ ጊዜ ውስጥ አስለቅቆ ቦታውን ለመያዝ ሻለቃ ባርቶክ ተጠራጠረ ። ስለዚህ አቅጣጫውን በመለወጥ በደቡብ በኩል አሮጌውን ምሽግ አልፎ ወደ ተራራው መውጣት የተሻለ አማራጭ ሆኖ አገኘው ። በዚህ ዓይነት ምንም ነገር ሳያደናቅፈው ከሄደ በአሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ ኮንኮርዱን ለማየት ይችላል ። እሥራኤሎቹ መስመር ይዘው በሚጓዙበት ጊዜ ባርቶክ በጉናቸው እየሮጠ ከኦፐሬተሩ የራዲዮ መገናኛ ተቀብሎ ሻለቃ አሮንን ጠራ ። “ ምሥራቅ ዳርቻ 6 ፤ ይህ ምዕራብ ዳርቻ 6 ነው ። በዚያ በኩል እንዴት እየተካሄደ ነው ? ”

አሮን በሚናገርበት ጊዜ ስለአለከለከ በሩጫ ላይ እንደነበረ ባርቶክ ገባው ። “ የከተማውን ክልል አልፈን ገብተናል ። አንድ የእኛ ሰው የሆነ ተገድሎ አገኝተናል ። አሥራ ሦስት የጠላት ወታደሮች ደምስሰናል ። ወደ ምሥራቅ ቁልቁለት እያመራን ነው ። በተራራው ጫፍ ላይ ለመድረስ ግማሽ ኪሎ ሜትር ያህል ይቀረናል ። ቆይ እስቲ ” ብሎ ሻለቃ አሮን ንግግሩንና መሮጡን አቆመ ። ቀጥሎም “ የጄት ድምጽ የሚመስል እየሰማሁ ነው ። ኮንኮርዱን ለማስነሳት ይችሉ ይሆን?” አለው ።

“ አንድ ጊዜ ” ብሎ ባርቶክ መስመር ሲፈልግ ቤከርና ላስኮቭ በኤል አል መስመር ላይ ሲነጋገሩ ሰማቸው ። መስመሩን ወደ ቀድሞው መልሶ “ ሮጀር ፣ ኮንኮርዱ ተነሳ ይላሉ ። ምን እቅድ እንደ አላቸው አላውቅም ። ሆኖም ነቅተህ አድምጥ ” አለው ።

ላስኮቭ በኮንኮርዱ በላይ ከሚያበሩት አብራሪዎቹ ከአንዱ ጥሪ ደረሰው ። “ ኮንኮርድ 02 ፣ ምን እያደረግህ ነው ? ” ብሎ በቁጣ ጠየቀው ።

ቢከር ቆቡን አደረገ ፣ የተስማማውም መሰለው ። በድምጽ ማጉ ሊያው " ከዚህ ሲአል ከሆነ ቦታ ልንወጣ ነው " አለው ።

" ማድረግ የለብህም ! በሙሉ ታልቃላችሁ ! "

" አስደናቂው ኮምፒዩተር ስለዚህ ጉዳይ ጠይቄው የምፈልገ ውን እንዳደርግ ነግሮኛል ። ስለዚህ እርሱ የሰጠኝን ምክር መቀበል አለብኝ ። አዝናለሁ ገብርኤል ። "

" " አደሆንም ፣ በሙሉ ትጨርሳቸዋለሁ ! " ብሎ ላስኮቭ ሲነ ግረው ስውነቱን መቆጣጠር አቅቶት እየተንቀጠቀጠ ነበር ። ድምጹን ዝቅና ለዘብ አድርጐ " ዴቪድ . . . ስማኝ " ብሎ ሳይጨርሽ ቤከር ዘጋበት ።

የቤከር ድምጽ እንደገና መጣ ። " ለማንኛውም ሁላችንም የምትን ነን ። ይህ ሊገባህ አይችልም ? እኛን ለመርዳት በጣም ዘግይተሃል ። "

" ፈጽሞ ልክ አይደለህም " ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ እንደገና ተቋረጠበት ።

ቤከር በለሰለሰ አንደበት " አዝናለሁ ጄኔራል ፣ አስደናቂ ሥራ አከናውነሃል ፣ ይህም እውነት ነው ፣ መልካም ዕድል ተመኝልን " አለው ።

" መልካም ዕድል ይሁንላችሁ ። "

ዴቪድ ቤከር ፍሬኑን ለቆ ጠበቀ ። የሆነ ነገር የለም ። ሞተሩ መንቀሳቀሱን የሚያሳዩትን መሣሪያዎች ተመለከተ ። ከዚህ ውጭ ሊያደርግ የሚችለው ነገር የለም ። አውሮፕላኑ ወደፊት የመንቀሳ ሳቀስ ምልክት ሰጠ ። መንቀጥቀጥም ጀመረ ። ከትከሻው ዘወር ብሎ ወደ ካን ዓይኖቹን ወርወር አደረገ ።

ካን ተመልክቶ " እንዳትዘጋው ዴቪድ ፣ ትንሽ ጠብቅ " አለው።

ቤከር በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ ። በየትኛውም መንገድ ሆነ አውሮፕላኑ ተሰባብሮ መበታተኑ አይቀርም ። በሦስቱ ሞተሮች በመ ጠቀም ወደ ምሥራቅ ቁልቁለት ቢነዱት በዝቅዝቀቱ ላይ እንዳለ ወይም ደልዳላው መሬት ላይ ሲደርስ መንኮታኮቱ አይቀርም ። አሁን እንኳን ቆሞ የሚያደርገው መንቀጥቀጥ ብልሽቱ የበዛበትን አውሮ ፕላን አንድ ሴንቲ ሜትር ከመሄዳቸው በፊት ሊያበላሸው ይችላል ። እጅግ በጣም መጥፎ - ወይም ምናልባትም እጅግ በጣም ጥሩ - ሊሆን የሚችለው የሚፈሰው ነዳጅ ተቀጣጥሎ ሁሉንም ይጨርሳቸው ይሆ ናል ። ለማንኛውም ነዳጁ አይቀጣጠልም ወይም አይፈስም ይሆናል

ብሎ ተመኘ ። ከሁለት አንዱ ለምን እንዳልሆነ ግን ሊገባው አል ቻለም ።

ቤከር ወደ ውጭ ሲመለከት ወንዶችና ሴቶች የሚተኩሷቸው ጥይቶች ወደ ክፍሉ እየገቡ ነበር ። የኤሌክትሪክ ሽቦ ሲንጣጣ ስለ ሰማ የማስተላለፊያው መሳሪያ መስመር እንደተበጠሰ ገባው ።

ኮንኮርዱ አሁንም አልተንቀሳቀሰም ።

ካን በበረራ መሐንዲሱ መሳሪያዎች ላይ የነበሩትን መልዕክ ቶች ለማንበብ ቢሞክርም ብዙ ብልሽት ስለነበራቸው ስህተቱ በየ ትኛው ላይ እንደነበረ ለይቶ ማወቅ አልቻለም ።

ሁለቱ የውስጥ ሞተሮች ከፍተኛ የግፊት ኃይላቸውን ቢያመነ ጩም የውጭዎቹ የሚንቀሳቀሱት በግማሽ ኃይል ነበር ። ካን በተቻ ለው ሁሉ ሙሉ ኃይላቸውን ሊያገኙ የሚችሉበትን ዘዴ ሞከረ ። አንድ ቁስ በተቀመጠበት ቦታ ላይ ሳይንቀሳቀስ ከቆየ በዚያው እንዳለ ይቆ ያል ። አውሮፕላኑ አንድ ጊዜ መንቀሳቀስ ከጀመረ ችግሩ ይቃለላል ። አንድ ቁስ መንቀሳቀስ ከጀመረ ደግሞ እንቅስቃሴው ይቀጥላል ።እባ ክህ አንተ ግዙፍ ነገር ተንቀሳቀስ ። ካን በድንገት “ የውስጡን ሞተ ሮች ኃይል አጥፋው ” አለው ለቤከር ።

ቤከር ምን ማለቱ እንደሆነ ገባው ። አውሮፕላኑ ወደፊት የማይ ሄድ ከሆነ ምናልባት ወደ ግራ ሊያዞሩት ይችላሉ ። ለትንሹ ሞተር ነዳጅ ስለሰጠው በቀኝ በኩል ያሉት የውጭ ሞተሮች ቀጭን ድምጽ ሰጡ ። የቀኝ ክንፎቹ በመጀመሪያ በማይታይ ሁኔታ ፥ በኋላ ግን ወደፊት መንቀሳቀስ ጀመሩ ።

ኮንኮርዱ ወደ ግራ መዞር ጀመረ ። አፍንጫው በተቀበረበት ኦቧራ ውስጥ ተንቀሳቀስ ። የቀኝ ክንፉ ሲጠመዘዝ የእረኛውን ጎጆ ጣሪያ ገፈፈው ። በቀኝ በኩል ያለው ተሽካሚው ለመውጫና ለመ ውረጃ እንዲሆን ከድንጋይና ከጭቃ የሠሩትን መሰላል መትቶ ሰበ ረው ። አውሮፕላኑ ሊቆም ተቃረበ ። ግን ወደፊት የሚያደርገውን እንቅ ስቃሴ ቀጥሏል ።

አውሮፕላኑ ከቆመበት በመንቀሳቀሱ ቤከር አንዱን ችግር ስለ ተወጣ በግራ በኩል ያለውን ሞተር ሲያስነሳው ኮንኮርዱ ቀስ ብሎ ወደፊት ሄደ ። ይሁን እንጂ በሚሄድበት ጊዜ ወደግራ ማዘንበሉን ቀጠለ ። ቤከር ከመቅጽበት አቅጣጫውን የሚያስተካክልበትን መሳ ሪያ በመጫን የፊት ጎማዎቹን ለማዞር ሞከረ ። ነገር ግን አውሮፕላኑ የፊት ጎማዎችም ሆኑ ጅራት እንደሌለው አስታወሰ ።

ካን “ ልታደርገው ከቻልክ ጥሩ ሙከራ ነው ፥ ዴቪድ ” አለው።

" ማንቀሳቀሱን እቀጥላለሁ ። ወዴት እንደሚወስደንም እናያ ለን ። ስማ ፣ ምናልባት በኋላ ዕድል ከአላገኘሁ ፣ ስለሠራኸው አሁኑኑ የምሥራች ልልህ እፈልጋለሁ " ብሎት ራሱን አስገድዶ ፈገግ አለ ። " የሆነው ይሁን - " ብሎ ሳይጨርስ በትከሻው ላይ ወደኋላ አየ ት ሲያደርግ ከእነወንበሩ ወደ ፊት ተጣብቆ ነጭ ሸሚዙ በደም ተበከ ሎ ስለአየው " ያንት ያለህ ! " አለ ቤከር ።

* * *

ያዕቆብ ሆስነር እየተንፏቀቀ በሚሄደው አውሮፕላን አጠ ገብ በሞተሩ የተነሳውን አቧራ ከለላ በማድረግ እየተኮሰ ሮጠ ። በነ በረበት ቦይ ውስጥ ሆኖ ሪሽን ለማግኘት አልቻለም ። ሪሽ ቂል አልነ በረም ። ሪሽ የሚሄደው በሰባት ወይም በስምንት ሰዎች ተከቦ ስለነበረ ሆስነር በአጠገቡ እንዲያልፍ ቢያደርገው እንኳን ሪሽን ነጥሎ ለመያዝ ወይም ለመምታት አይችልም። ሀማዲን ግን ለይቶ ሊያ ወጣውና ሊገድለው ይችል ነበር ። ሆኖም ሆስነር በሁለተኛ ደረጃ ባለ ሰው ምክንያት በራሱ ላይ አደጋ መጋበዝ አልፈለገም ። ሆስነር መከላከያ ለመፈለግ ወደ ጐጆው ማፈግፈግ ነበረበት ። ያም ቢሆን ጐጆውን እንደከበቡት ያህል ይቆጠር ስለነበረ ለሕይወቱ አስጊ ሆኖ አገኘው ። ስለዚህ ኮንኮርዱን ከለላ በማድረግ ሄደ ። አህመድ ሪሽን እስኪያገኝ ድረስ የሚጠቀምበት መከላከያ ማግኘት ነበረበት ።

ኮንኮርዱ ኃይል አግኝቶ እየነጠረ መሄድ በጀመረበት ጊዜ አሥራ ሁለት የሚሆኑ ወንዶችና ሴቶች በክንፉ ላይ ሆነው ወደ አሸባሪዎቹ በአውሮፕላኑ በተነሳው ኃይለኛ አቧራ ውስጥ ተኮሱ ።

በክንፉ ላይ ከነበሩት ብዙ ሰዎች አውሮፕላኑ ፍጥነቱን ከመ ጨመሩ በፊት ሆስነርን ስለአዩት እንዲወጣ ቢጮኹም ሆስነር ሰምቶ እንዳልሰማ ሆነ ። ሊወጣ እንዲችል ሸሚዞቻቸውን ቀጣጥለው ቢሰ ዱለትም ለመውጣት ዝንባሌ ያሳየ አልመሰለም ።

ራሳቸውን በራሳቸው ለማጥፋት ሞክረው የነበሩት ወንዶችና ሴቶች አሁንም በዕቃ ማስቀመጫው ክፍል ውስጥ ተፋፍገው ተቀም ጠዋል ። ይህ የተደረገው ለቅጣት ሳይሆን የበለጠ አመች በመሆኑ ነበር ። ሚሪያም በርንስቴይን ብርክ ይዟት ስለነበረ ከእነእርሱ ጋር እንድትቆይ ስለተደረገች ቤተ አብራምስ በክንድዋ ላይ ታቅፋ አጽ ናናቻት ።

ኢብራሂም አሪፍ የተቀመጠው በጥግ ስለነበረ አውሮፕላኑ እየ ተንፏቀቀ ሲሄድ ከአውሮፕላኑ ኋላ በአቧራው ውስጥ አንድ ሰው ሲሮጥ አየው ። እነእርሱን እንዲጠብቅ ለታዘዘው ለሕዝቅኤል ራባት ጮኾ ነገረው ። ራባት በፍጥነት በተሠበረው መስታዎት ራሱን ከኤኬ - 47

ጠመንጃው ጋር ብቅ አድርጐ እንጣጥሮ ሊተኩስ ሲል ጫማ የሌለውንና አቧራ የለበሰውን ሰው ስለአወቀው “ ያዕቆብ ሆስነር ነው ! ” ብሎ ተናገረ ።

ሚሪያም በርንስቴይን ይህን ስትሰማ በሰዎቹ መካከል ሮጣ ስትሄድ አሪፍና ራባት ያዟት ። በማይታመን ፍጥነት ወደ አውሮፕ ላኑ በር ስትሄድ አንድ እግርዋን አሪፍ ፣ ሌላውን እግርዋን ደግሞ ራባት ጥርቅም አድርገው ያዟት ። ሁለቱን ነጥቃ ልትሄድ ስትሞክር ያእኮቭ ሌይበር ጉልበትዋን ያዘች ። ለሦስት ይዘው ወደ ውስጥ ጐተ ቷት ። ቤተ አብራምስ ከኋላቸው በኩል በላያቸው ላይ ወድቃ “ ትሂድ! ከፈለገች ተዋት ትሂድ ! ” ብላ ጮኸችባቸው ።

ቤተ አብራምስን ወደ ኋላ ሲጐትቷት ከፍተኛ ትርምስ ተፈጠረ ።

ሚሪያም በጅራቱ በኩል ቁጥር አስራ አንድ የነዳጅ መያዣን ተሸከሞ በነበረው የብረት ርብራቦሽ ውስጥ ራስዋን ወደ ውጭ ስታ ወጣ እግርዋን ጠፍረው ስለያዟት እንደ እብድ ሆና ጮኸች ። ወደ ውስጥ ጐትተው ሊያስገቡዋት አልቻሉም ። ወደ ውጭ መውጣትም አልቻለችም ።

የሚሪያም ፊት በእንባ እየታጠበ በጐረና ድምጽ “ ያዕቆብ ! ያዕ ቆብ ! ” ብላ ጮኸች ።

ኮንኮርዱ ፍጥነቱን እየጨመረ ስለሔደ ያዕቆብ ሆስነርም እየራቀ ሔደ ። በመቅረብ ላይ ወደ ነበረ አንድ አካል ላይ ለመተኮስ ሲዞር ሆስነር ወደቀ ። በአቧራው ላይ ተጋድሞ ሰማያዊውና ነጩ ኮንኮ ርድ በነፋስ በተቀላቀለው አቧራ መካከል ሲሰወር ተመለከተው ። እጁንም በማወላወል አውሮፕላኑን ተሰናበተው ። ሚሪያም በር ንስቴይን እንደአያት አምናለች ። እርስዋም “ያዕቆብ ! ያዕቆብ” ብላ እጅዋን በማውለብለብ መልስ ሰጥታዋለች ። እየተነፋረቀች ስሙን ደጋግማ ተጣራች ።

ቤከር የአውሮፕላኑን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ሞተሮቹን በማ ጥፋትና በማስነሳት የተለያዩ ሙከራዎች ቢያደርግም የአውሮፕላኑ ፍጥነት እየቀነሰ ስለመጣ ተጨማሪ የነዳጅ መስጫውን ከፈተ ። ይሁን እንጂ የኮንኮርዱ እንቅስቃሴ ወደ ግራ አዘነበለ ። በትከሻው ላይ ገልመጥ እያለ ወደ ካን ቢመለከትም የሕይወት መኖር ምልክት ሊያ ይበት አልቻለም ።

ቤከር ኮንኮርዱ እንዲሄድ የሚፈልገውን አቅጣጫ ትቶ ወደ ምዕራብ በቀስታ እየተሽከረከረ በሚሔድበት ጊዜ አንድ አረብ በአቧራው ውስጥ ብቅ ከአለ በኋላ ተሰወረበት ።

ቤከር በክፍሉ ውስጥ ከነበሩት ሰዎች ውስጥ ጥቂቶች በመላተም ሳይጐዱ እንዳልቀሩ አውቋል ። በዚህ ዓይነት አውሮፕላኑ በሚቆም በት ጊዜ ክፍሉ በሬሳ ሳይሞላ አይቀርም የሚል ስሜት አደረበት ። በአዕምሮው ውስጥ በአውሮፕላኑ ቀዳዳዎች የሰው ደም እንደ ውሃ ሲፈስ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች እየተንገዳገዱ ከአውሮፕላኑ ውስጥ ሲወርዱ እያንዳንዳቸው ዓይናቸው ወደ ውስጥ ገብቶና ሰውነታቸው በደም ተበክሎ ፣ አዕምሮአቸው ተበላሽቶ ታየው ። ከሃሳቡ ሲባንን ላቡ በአንገቱ ላይ ተንቆረቆረ ። እጆቹም ተንቀጠቀጡ ። በዚህ ምክ ንያት ይህን አስቀያሚ ነገር ከአንድ ነገር አስጠግቶ እንዲቆም ማድ ረግ አለበት ። ከዚህ ከአሁኑ ሁኔታ በአንድ ጉብታ ስር ተንከባሎ መሞት በጣም የተሻለ መስሎ ታየው ።

በግራ መስታወቱ መካከል የምዕራብ ቁልቁለት አፋፍ ታየው ። በዚያ ኃይለኛ ዘቅዛቃ ቦታ ላይ ወደ ወንዙ ቢወርድ ምን ያስከትልበት ይሆን ? በሚወርድበት ጊዜ ኮንኮርዱ ይሰባበር ይሆን ? በፍጥነት በው ሃው ውስጥ ይሰምጥና ሰዎቹ ያልቁ ይሆን ? ከዚህ ለማዳን አንድ መን ገድ ብቻ ነበር ። የውስጥና የውጭ ሞተሮቹን በየተራ በማጥፋትና በማስነሳት ፣ ነዳጅ በመጠኑና በብዛት በመስጠት ሁለቱም ክንፎች ሚዛናቸውን እንዲጠብቁ ስለአደረጋቸው ኮንኮርዱ በቀጥታ ወደ ቁል ቁለቱ አፋፍ እንዲያመራ ሆነ ። ሁለቱ ሞተሮች በኃይል አጓሩ ።

ኮንኮርዱ መክለርና ሪቻርድስን የቀበሮ ጉድጓዶች በቆፈሩባ ቸው ቁልቁለት አፋፍ ላይ ሊደርስ ጥቂት ሜትሮች ቀሩት ። በዚህ ጊዜ ቤከር “ በክፍሉ ውስጥ ያሉ ሁሉ ራሳቸውን ከግጭት አደጋ ሊያ ድኑ የሚችሉበትን እንዲያደርጉ ” ጮኾ ነገራቸው ።

በክንፉ ላይ የነበሩ ወንዶችና ሴቶች ወደ ውስጥ ገቡ ። በክፍሉ ውስጥ ያሉት ሁሉ ወደጅራቱ በመዞር በወለሉ ላይ ተጋደሙ ወይም ተቀመጡ ። ከአደጋው ለመከላከል በራሳቸው ላይ ትራሶችና ብርድ ልብሶች አስቀመጡ ። በተጨማሪም እያንዳንዳቸው ቁስለኞቹን አጥብቀው ለመያዝ ሞከሩ ።

ረጅሙና የተከሰከሰው የኮንኮርዱ አፍንጫ በቁልቁለቱ አፋፍ ላይ በደረሰ ጊዜ በሰማይ ላይ ለመብረር የተዘጋጀ መሰለ ።

ቤከር ለተበላሸው ሞተር ጭምር ነዳጅ በኃይል ሰጠ ። አውሮ ፕላኑ የተንጠለጠለ መሰለ ። በኮንኮርዱ አፍንጫ በኩል አቆልቁሎ ሲመለከት በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ የጧት ውጋጋን ረጭቷል ። የመቆ ጣጠሪያ መሳሪያዎቹን ሲመለከት የውጭ ሞተሩ እየቆመ ነበር ። ነዳጅ አልቆበት ይሆን ? ወይስ በገባበት አሸዋ ምክንያት ሞተሩ እየ

ቆመ ይሆን ? በግራ በኩል ያለው የውጭ ሞተር በድንገት የእሳት ምልክት ሰጠ ። የውስጡም ሞተር ኃይሉን በጣም በመቀነስ ጭስ መትፋት ጀመረ ። ኮንኮርዱ በአፋፉ ላይ ብቅ በማለት በከፊል በአየር ላይ የተንሳፈፈ መሰለ ።

ኮንኮርዱ እንደተመታ ወፍ በመሬቱ ላይ በሚንደረደርበት ጊዜ አህመድ ሪሽ እየጮኸ ከቀሩት አሸባሎች ጋር ሆኖ ተከተለው ። ከአውሮፕላኑ በኩል በአንድ ወይም በሁለት ቀዳዳዎች አነስተኛ ተኩስ ይተኮስ ነበር ። አንድ ሰው ግን በተሰባበረው የአውሮፕላኑ ጅራት ክፍል ውስጥ ሆኖ እያስተካከለ ተኮሰ ። ሪሽ ሁሉም ወደዚያ ሰው እንዲተኩሱ አዘዘ ። ሰውየው የተመታ ቢመስልም አከታትሎ መተኮሱን ቀጠለ ።

አሸባሎቹ ያለ ኃይላቸውን ሁሉ በመጠቀም በሳሌም ሀማዲ መሪነት ወደ ሚንገዳገደው ኮንኮርድ ተጠጉ ። አህመድ ሪሽ ከኋላቸው ሆኖ ወደፊት እንዲሮጡ ለማስፈራራት በአቧራው ላይ በሚተኩሰው ጥይት የሚፈናጠረው አሸዋ ጀርባቸውንና ቂጣቸውን ይመታቸው ነበር ። በአንድ ጨርሶ ሊያብድ ትንሽ በቀረው ሰው እየተመሩ እነዚያ ከሃያ የማይበልጡ ምስኪን አሸባሎች እየወደቁና እየተነሱ ሩጫቸውን ወደፊት ቀጠሉ ። ከእነዚያ 150 ያህል ከነበሩ ኩሩ ተዋጊ ወንዶችና ሴቶች ውስጥ የቀሩት ጥቂት ሰዎች በፍርሃት ፣ በውርደትና በስቃይ ላይ በመውደቅ ከነብር ልጅነት ይልቅ ወደ ተኩላነት የተለወጡ መሰሉ ።

ሪሽ አንድ በድካም ወድቆ መነሳት ያቃተው ሰው በጥይት ተኩሶ ገደለ ። ኮንኮርዱን ተከትሎ ሲሮጥ በመቃረብ ላይ የነበሩት የእሥራኤል ኮማንዶዎች የሚተኩሱት ጥይት ድምጽ ከኋላው ተሰማው ።

ላስኮቭ ከአየር ላይ ሆኖ ይመለከታቸው ነበር ። አልፎ አልፎ በግልጽ የታዩትን አሸባሎች ለመጨረስ ቢፈልግም ወደ ኮንኮርዱ በጣም ስለተጠጉ አልቻለም ። እየተቃረቡ ለመጡት ኮማንዶዎችም የተስተካከለ ትዕዛዝ ለመስጠት አልቻለም ። የኤፍ - 14 ጄት ፍጥነት ከፍተኛ በመሆኑ በጣም ተጠግቶ እርዳታ ለመስጠት አስቸጋሪ ሆነበት ። ኤፍ - 14 ጄቶች ለዚህ ሥራ የተመረጡት በፍጥነታቸው ምክንያት ነበር ። ነገር ግን በዚያ ወጣ ገባ በሆነ ተራራማ ላይ ፣ የንጋቱ ውጋጋን በኃይለኛ የአቧራ ውሽንፍር እንዲጨልም በሆነበትና በሰዓት በዝቅተኛ 196 ኪሎ ሜትር እየበረሩ ወገኖቻቸው ያሉበትን አካባቢ ለመምታት አይችሉም ። ኮማንዶዎቹ ወደ ኋላ እንዲያፈገፍጉ ለመጠየቅ ቢያስብም ሁኔታውን አጢኖ ሲመለከተው የተሻለ

ውጤት ለማግኘት የሚቻለው በኮማንዶዎች ሆኖ አገኘው ። እንደገና ዝቅ ብሎ በመብረር ከኮንኮርዱ በመራቅ አካባቢውን በጥይት መደ ብደብ ወይም በደቡብና በምሥራቅ እየተቃረቡ በመጡት ኮማንዶ ዎች አማካይነት እርምጃ መውሰዱን አመነበት ። ዝቅ ብሎ በመብረር የቀሩትን ባለ 20 ሚሊ ሜትር ጥይቶች ለመተኮስ ወሰነ ።

ሆስነር በአንድ ጉድባ ውስጥ ተቀምጦ አሸዋ በመልበስ የመ ድፉን ጥይት ፍንዳታ ሰማ ። አሸባሎቹ በዚያ ጉድጓድ ውስጥ ሆኖ አቧራ በመልበሱ ሳያዩት አለፉ ።

በተሸሸገበት ቦታ ውስጥ ሆኖ የአውሮፕላኑ ድምጽ ቀስበቀስ እየቀነሰ ሲመጣ ተሰማው ። በጥንቃቄ ቀና ብሎ ሲመለከት በቁል ቁለቱ አፋፍ ላይ ወደፊት ብቅ ብሎ ቆሟል ። በደካማው የንጋት ብር ሃን ሲመለከት በሞተሩ ላይ ብልጭ ድርግም የሚለው እሳት እየጠፋ ነበር ። አሸባሎቹም ወደ ኮንኮርዱ እየተጠጉ ነበሩ ። በምሥራቅ በኩል ኮማንዶዎቹ ቁልቁለቱን ሲወጡ አልፎ አልፎ የሚተኩሱትን የጥይት ድምጽ መስማት ችሏል ። በአንድ ጉልበቱ በርከክ ብሎ በኤኬ - 47 ጠመንጃው ለመጠቀም የሚችልበትን ዘዴ አመቻቸ ። በሚያጐርስ በት ጊዜ አካባቢውን ሲቃኝ ያ የነበሩበት ቦታ ከሚሪያም ጋር ግንኙ ነት ያደረጉበት እንደነበረ ስለአስታወሰ እንደ አልጋ የተጠቀሙበትን አሸዋማ ቦታ በእጁ ዳሰሰው ።

አጉርሶ እንደ አበቃ እንደገና ወደ ኮንኮርዱ ተመለከተ ። ሃሳቡ ቢሟላም ባይሟላም እንደሚሞት ቢያውቀውም አሁን የሚፈልገው ሪሽን ለመግደል ነበር ። አሁን ግን የኮንኮርዱን ሁኔታ ሲያየው እርሱ በሕይወት እንደሚኖርና ሌሎቹ እንደሚሞቱ አወቀ ። ምክንያቱም ሪሽ ሊደርስባቸው ፡ ሊጨፈጭፋቸው ወይም ምርኮኛ ሊያደርጋቸው አይችልም ። ይህ በቁልቁለቱ ላይ ተንሸራተው ወደ ወንዙ ለመውረድ የሚደረገው ሙከራ ያለጥርጥር ሁሉንም ይገድላቸዋል ። አሁን ሆስ ነር ማድረግ የሚችለው ኮማንዶዎቹ መጥተው ወደ ቤቱ እስኪወስ ዱት ድረስ መጠበቅ ነው ። ግን ይህን ማድረግ እንደማይቻል ራሱም ያውቀዋል ። ከዚያ ተነስቶ ኮንኮርዱ ወደ አለበት አቅጣጫ ሔደ ።

ቤከር በቁልቁለቱ ላይ ለመውረድ መወሰን አልቻለም ። ወን ዙን ለብዙ ጊዜ ባየው ቁጥር እየረዘመ ሔደበት ። ምርጫው ግን ምን ነበር ?

በርግ ወደ በረራ ክፍሉ መጥቶ ካንን ከተጣበቀበት አላቆ አስ ቀመጠው ። በደረቱ ላይ ከተመታው ቁስሉ ደሙ ይፈስ ስለነበረ ለመ ተንፈስ ተቸግሯል ። በርግ አካባቢውን ቃኝቶ አንድ ካርታ የተሳለበት

ወረቀት ስለአገኘ ጨባብጦ ደም የሚያፈሰውን ቀዳዳ ጠቅጥቆ ስለ ዘጋው ደሙ ፍልቅ ፍልቅ ሲል ይሰማ የነበረው ድምጽ ቆመ ።

ቤከር ለአንድ ሴኮንድ ያህል ከአሰበ በኋላ " አስራ ሁለት ሰዎች በፊት ወደአለው ክፍል ውስጥ እንዲመጡ ጥራልኝ " ብሎ ለበርግ ነገረው ።

በርግ ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ በመውጣት ጮኾ ሰዎቹ እን ዲመጡ አዘዘ ።

አስራ ሁለት ያልቆሰሉና ቆስለውም ለመራመድ የሚችሉ በፍ ጥነት መጥተው ወደፊት ባለው ትንሽ ክፍል ውስጥ ገብተው ቆሙ።

ኮንኮርዱ በሰዎቹ ክብደት ምክንያት በበለጠ አጋድሎ ወደፊት ተንሸራተተ ። በርግ ሮጦ ሄዶ በረዳት አብራሪው ወንበር ለይ ተቀመጠ።

ሳሊም ሀማዲ እየተንጠባጠቡ የመጡትን አሸባሎች እየመራ አፋፉ ላይ ሊደርስ ሁለት ሜትር ያህል ወደቀረው ኮንኮርድ መጥቶ ጨርሶ ሊንሸራተት አንድ ሴኮንድ ሲቀረው ጠመንጃውን በትከሻው ላይ አንግቶ ዘሎ ወጣ ።

ሀማዲ በክንፉ ላይ ወጥቶ የሚይዘው አጥቶ ሲፍጨረጨር እግሩ ጥይት በበሳው የአውሮፕላን ቀዳዳ ላይ ስለአረፈ እንደምንም ብሎ በአደጋ ጊዜ በሚወጣበት ክፍል በር ላይ ስለደረሰ ተንጠራርቶ የመግቢያውን ክፈፍ ጨምዶ ያዘ ። በዚያ ወቅት መዝጊያውንም ሆነ መስኮቱን የሚያይ አንድም ሰው ያለ አልመሰለም ። አሁንም ወደ ተከፈተው በር ተንፏቆ መጣ ።

አውሮፕላኑ የመንሸራተት ኃይሉ እየጨመረ ስለመጣ ከአፋፉ በቁልቁለቱ ላይ እየተንፏቀቀ ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ ወረደ ። በአየር ላይ ሆነው የጀቶቹ አብራሪዎች ሲመለከቱት ግርማ ሞገሱ ሌላ ነበር።

ሳሌም ሀማዲ በመግቢያው ላይ ሆኖ ከአደጋው ለመዳን ብርድ ልብስ ፡ ትራስና ሌሎችም ነገሮች በራሳቸው ላይ አድርገው በወ ለሉ ላይ የተጋደሙትን ተመለከተ ። ሀማዲ የመዝጊያውን ክፈፍ ለቆ ወደ ጨለማው ክፍል ውስጥ ገባ ። የአውሮፕላኑ መንቀጥቀጥ ወደ ነጂው መዝጊያ ወስዶ አላተመው ። በብረቱ መዝጊያ ላይ ጀርባውን አስጠግቶ ኮንኮርዱ እስኪጋጭ ድረስ ጠበቀ ። ሀማዲ የመስመጥ የመገደል ፡ የመማረክ ወይም የአካል ጉዶሎነት እድል ያጋጠመው እንደሆነ አስቀድሞ ማሰብ አልቻለም ። ነገር ግን የመጨረሻው የፍ ጻሜ ቀን ሲመጣ በአህመድ ሪሽ አካባቢ መቆየት አይፈልግም ።

ቤከር በሚወርድበት ጊዜ ቁጥጻጦዎቹን ተመለከተ ። የኮንኮርዱ ዋና ጉማ ስለተጨራመተ ኮንኮርዱ በሆዱ እየተንሸራተተ በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ ዘሎ ገባ ። ውሃው እስከ መስኮቱ ድረስ ስለመጣ በተሰባበረው መስታወት መካከል ወደ ቤከርና በርግ ፈሰሰ ። ከዚያ ቀጥሎ ሁሉም ነገር ተመሰቃቀለ ።

የጋሉት ሞተሮች ውሃው ስለነካቸው ከፍተኛ ጭስ ማውጣት ጀመሩ ። በአውሮፕላኑ ውስጥ ውሃ ስለገባ የሰዎች ድምጽ ተሰማ ። እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ውሃው ከገባ በኋላ ኮንኮርዱ መንሳፈፍ ስለ ጀመረ ተሳፋሪዎቹ ቀና ብለው መመልከት ጀመሩ ።

ሳሌም ሀማዲ በፍጥነት ተንሸራቶ መጠነኛ ብርሃን ወደአለበት ወደ በረራው ክፍል ሲገባ በበረራ መሐንዲሱ መቀመጫ ላይ ደሙ በኃይል የሚፈስና በውስጥ የነበረውን የውሃ ቀለም በደሙ የለወጠ አንድ ሰው ተቀምጧል ። ሌላ ሰው ደግሞ በአብራሪው ወንበር ላይ ተቀምጧል ። ከእርሱ ቀጥሎ በረዳት አብራሪው ወንበር ላይ የሲቪል ልብስ የለበሰና ራሱን የሳተ የሚመስል አንድ ሰው ተቀምጧል ። የተሰባበሩ መስታዎቶች በየአለበት ነበሩ ። በሚመለከትበት ጊዜ የመግሪያዎቹ መብራቶች መድከም ጀምረዋል ። በክፍሉ ውስጥ የነበሩት መብራቶችም ጠፉ ። ሀማዲ ጩቤውን መዝዞ የሲቪል ልብስ የለበሰው ሰው ዋናው መሆኑ ስለገባው በመጀመሪያ ወደ እርሱ ሄደ ።

## —37—

ያዕቆብ ሆስነር እራቅ ብሎ አሸባሪዎቹ ወደ ወንዙ እየተንደረደረ ወደሚወርደው ኮንኮርድ አቆልቁለው ሲተኩሱ ተመለከታቸው ። ሪሽን መርጦ ለመግደል ቢሞክርም ሁሉም አሸዋ በላያቸው ላይ ተነስንሶባቸው ስለነበረ ለመለየት አልቻለም ።

የላስኮብ ኤፍ - 14 በጭቃማ ሜዳው በኩል ባለው ሰማይ ላይ ያንዣብብ ስለነበረ በድንገት አሸባሪዎቹ ወደ ነበሩበት ተራራ አቅጣጫ መጣ ። የሻለቃ አሮን ኃይል ወደፊት መግፋቱን አቁሞ ትዕዛዝ እስኪደርሰው ድረስ ከለላ እንዲሰጥ ላስኮቭ መመሪያ ሰጠው ። የሻለቃ ባርቶክ ኃይል አቅጣጫውን ለውጦ ኮንኮርዱ ወደነበረበት በፍጥነት ተመለሰ ።

የንጋቱ ብርሃን እየጨመረ ከመምጣቱም በላይ ኃይለኛው ነፋስ ደግሞ እየቀነሰ መጣ ። አሸባሪዎቹ በአቧራውና በጨለማው ተከልለው ለብዙ ጊዜ ሲያጠቁ ከቆዩ በኋላ ብርሃኑ እየጨመረና ነፋሱም እየ

ቀነስ በመምጣቱ ልብሳቸውን ተገፈው እርቃናቸውን የቀሩ ዓይነት ሆነው ተሰማቸው ። ኤፍ - 14 ተዋጊ ጀት የቀሩትን አራት ሮኬቶች ስለተኮሰባቸው በተራራው ላይ የአሸባሎቹ መስመር በፍንዳታው የብርቱካን ቀለም ዓይነት በነበረው ነበልባል ተያያዘ ።

ፍንዳታው በአስከተለው የመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት ሆስነር ከወደቀበት ቦታ ቀና ብሎ ሲመለከት አህመድ ሬሽ ተረፍርፈው በመቃጠል ላይ የነበሩትን ወታደሮቹን ቆሞ ሲመለከት አየው ። የጸጉርና የሰውነት መቃጠል ቅርናት ነፋሱ እስኪወስደው ድረስ በተራራው ላይ ይሸት ነበር ።

ሆስነር ቆሞ አካባቢውን ሲመለከት በዚያ ተራራ ላይ የቀሩት ሬሽና እርሱ ብቻ እንደነበሩ አመነ ። ሬሽ ለማፈግፈግ በጣም ምቹ ቦታ ይሆናል ያለውን ይዟል ። ሆስነር ቀስ ብሎ ከኋላው ወደ እርሱ እየተራመደ ሔዶ “ ሀሎ ፡ አህመድ ! ” አለው።

ሬሽ ሳይዞር “ ሀሎ ፡ ያዕቆብ ሆስነር ” አለው ።

“ አሸነፍናችሁ ሬሽ ። ”

ሬሽ ራሱን በአሉታ ነቅንቆ “ ሀማዲ በአውሮፕላኑ ውስጥ ስለ ገባ ሙሉ በሙሉ አላሸነፋችሁንም ። ምናልባትም ይሰምጥ ይሆናል ። የሰላም ተልዕኮው ስብሰባ እንዳበቃለትም እርግጠኛ ነኝ ። የሞቱ ብህንና የቆሰሉብህንም አትርሳ ። እኩል ለእኩል ነን ብለን እንጥራው” አለው ።

ሆስነር የኤኬ - 47 ጠመንጃውን ምላጭ አጥብቆ ይዞ “ ጠመንጃህንና ሽጉጥህን ጣል ፡ ቀስ ብለህ ወደ እኔ ዞር ? አንተ ከይሲ ፣ እጆችህን በራስህ ላይ አድርግ ” ብሎ አዘዘው ።

ሬሽ የተባለውን ከአደረገ በኋላ ለሆስነር ፈገግታ በመስጠት “የተቆጣህ ትመስላለህ ። መጠጥ ትፈልጋለህ ? ” ብሎት በወገቡ ላይ በቀበቶው ወደ አንጠለጠለው ኮዳ ተመለከተ ።

“ ሰፊ አፍህን ዝጋ ” ሲለው የሆስነር እጆች እየተንቀጠቀጡ ነበሩ ። የጠመንጃውም አፈሙዝ የሚንቀሳቀስ መሰለ ። ቀጥሎ ስለሚወስደው እርምጃ መወሰን አልቻለም ።

ሬሽ አሁንም ለሆስነር ፈገግታ ሰጥቶ “ ይህ ሁሉ የአንተ ስህተት እንደሆነ ታውቃለህ ። የአንተ ድክመት ባይጨመርበት ኖሮ ይህ ሁሉ አይፈጸምም ነበር ። በአለፈው ዓመት ውስጥ ሆስነር ኮንኮርዱን ከአፍንጫው እስከ ጅራቱ ፍተሻ ያደረገ በመሰለኝ ቁጥር እያሳበኝ ከሕ

ልሜ የባነንኩባቸው ሌሊቶች ብዛት ምን ያህል እንደነበረ ልነግርህ አልችልም ። በስም ብቻ ዝነኛ የሆነውን የኤል አል የጸጥታ ተቆጣጣሪ የሆነውን ያዕቆብ ሆስነርን ከፍተኛ ግምት ሰጥተውት ነበር ። ጭን ቀትም አድርብን ነበር ” ብሎት ከሳቀ በኋላ “ ያዕቆብ ሆስነር ስም ብቻ መሆኑን የነገረን አልነበረም ። ትክክለኛው ያዕቆብ ሆስነር ግን ከግመል የተሻለ ማሰብ የሚችል አንጐል የለውም ” አለው ። ቀጥ ሎም በመሬቱ ላይ ምራቁን ጢቅ ከአደረገ በኋላ “ አንተ በሕይወት ትኖር ፤ እኔ ደግሞ እሞት ይሆናል ። ነገር ግን ከአንተ ጋር ቦታዎች አልለዋወጥም ” ብሎት እንደገና ሳቀ ።

ሆስነር ከአፉና ከዓይኖቹ ላይ አቧራውን ጠረገ ። የጠመንጃውን ምላጭ እንዲስብ ሪሽ እየገፋፋው ነበር ።

“ የምትናገረውን ጨረስህ ? ”

“ አዎን ፤ ልነግርህ ያሰብኩትን ነግሬሃለሁ ። አሁን ቶሎ ግደ ለኝ ። ”

“ በአዕምሮዬ ውስጥ ያለው ያ አልነበረም ። ” አሸዋ የለበሰው የሪሽ ፊት አመድ የለበሰ መሰለው ። “ ጄኔራል ደብኪንን ማርከሽ ዋል ? ከምሽጋችን የወሰዳችኋት ሴትስ የት ናት ? ሁለቱም በአንተ እጅ ውስጥ ናቸው ? እውነቱን ንገረኝ ፤ ሪሽ ። ከነገርከኝ በፍጥነት በግንባርህ ላይ ተኩሼ እገድልሃለሁ ። ከአልሆነ ግን . . . ”

ሪሽ ትከሻውን ከፍና ዝቅ ከአደረገ በኋላ “ አዎን ፤ ሁለቱንም ማርከናቸዋል ። በመጨረሻ ጊዜ ስለያቸው በሕይወት ነበሩ ። ይሁን እንጂ ከእንግዳ መቀበያው ቤት በራዲዮ በደረሰኝ መልዕክት መሠረት የአንተ ወታደሮች ቤቱን በቦምብ እንዳፈረሱትና ቁስለኞቹንም በጥ ይት እንደገደሉአቸው ለማወቅ ችያለሁ ” ከአለው በኋላ እንደገና ትከሻውን ነቅንቆ “ ስለዚህ እስከ አሁን በሕይወት ይኖራሉ የሚል ማን አለ ? ” አለው ።

“ ሆስፒታሎችና የጦር ዋና ጽሕፈት ቤት አብረው አይሆኑም ሪሽ ” ከአለው በኋላ ስሎ ከጉሮሮው ውስጥ የነበረ አቧራ ተፋ ።

“ ውሃ ትፈልጋለህ ? ”

“አፍህን ዝጋ ። ” ሪሽ የአንድ አስርተ ዓመት የጸጥታ መሸለሚያ ይሆን ነበር ። በሕይወት ይዞት ለመሄድ በቂ ምክንያት ነበረው ። የእ ስራኤልን መንግሥት ጸጥታ ለጥቂት ጊዜ አስቸግሮ ስለነበረው ጉዳይ ሪሽ ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች ብዙ መልሶች መስጠት ይችል ነበር ።

ሆስነር በተጨማሪ ጥቂት ነገሮች ለራሱ ማወቅ ፈለገ ። " ስለአውሮፕላኑ በረራ ምሥጢር ያስተላለፈልህ ማነው ? "

" ኰሎኔል ሪቻርድሰን ። "

ሆስነር ራሱን በአዎንታ ከነቀነቀ በኋላ " የሚሪያም በርንስቴይን ባለቤትና ሌሎቹስ ያሉት የት ነው ? " ብሎ በድንገት ጠየቀው ።

ሪሽ ፈገግ አለ ።

" መልስ ስጠኝ ፣ አንተ ከይሲ ። "

" እንደማስበው ይህን ጥያቄህን ወደ መቃብር ይዤው እወርዳለሁ እንጂ አልነግርህም ። "

የሆስነር ጣት ምላጩን ጫን አደረገ ። በሕይወት ከወሰደው በራ ምላ ወህኒ ቤት ውስጥ በሸቦ ቀዳዳ እየተመለከተ ሕይወቱን ሙሉ ይኖራል ። የሕይወት ሙሉ እስራት በራስ ላይ ተመትቶ ሞቶ ከመረሳት የበለጠ መጥፎ ነው ። ሆስነር ግን ዓይን ያወጣ ዓይኑ ይውጣ የሚለውን የጥንት ወይም ኋላ ቀር ሕግ መጠቀም ፈለገ ። ከጥላቻው ብዛት የተነሳ የሪሽን ደም ሲፈስ ማየት ፈለገ ። ሪሽ በሰው እንደበት ሊነገር የማይቻል ሰይጣን ስለሆነ በወህኒ ቤት ገብቶ ይቆያል ፣ አርፎ ይቀመጣል ለማለት አስተማማኝ የሆነ ዋስትና ማግኘት አይቻልም ።ሪሽ በሕይወት ሆኖ እስትንፋሱ እስከ አለ ድረስ አደገኛና አስፈሪ እንደሆነ ተላላፊ በሽታ ዓይነት ነው ።

" ፍቅረኛህን ገደልንብህ ፣ አልገደልንም ? በጣም የቅርብህ ስለነበረች ለአንተ ድርብ ሞት ነው ፣ አይደለም ? " በሪሽ ፊት ላይ የታየው ግልጽ ባይሆንም ነገሩ እውነት ነበር ።

ሪሽ መልስ አልሰጠውም ። የሰጠው አስፈሪና የበቀል ፈገግታ ግን የሆስነርን የጀርባ አጥንት ሰንጥቆ ገባ ። ሆስነር በፊቱ ልዩ ልዩ ነገሮች ታዩት ። መላ ሰውነቱ በድካምና በስሜት መንቀጥቀጥ ጀመረ። ጠመንጃውን አነጣጥሮ ተኮሰ ።

የሪሽ የጉልበት ሎሚ በጥይቱ ስለደቀቀ በአቧራው ላይ ወድቆ የሕመም ጩኸት አሰማ ። " ቃል በገባህልኝ መሠረት ቶሎ ግደለኝ ። "

ሆስነር የሪሽ ደም ሲፈስ ፣ አጥንቱ ሲበታተንና ሲጮኽ በማየቱ ተደሰተ ። ደምና ሕመም አይኖረውም ብሎ አስቦ ነበር ። ይህ ግን ትክክለኛ አስተሳሰብ አልነበረም ።

" ቃል ገብቶሃል ! "

“ ሁለታችን ቃል ከ.ዳናችንን የጠበቅንበት ጊዜ መቼ ነበር ? ” ብሎ እንደገና ተኩሶ ሌላውን የጉልበቱን ሎሚ አፈረሰው ።

ሪሽ እንደ እንበሳ እያጓሩረ በአፉ ተደፍቶ ደም እስኪተፋ ድረስ ተንፈራፈረ ። “ ለአላህ ፍቅር ብለህ ! ለእግዚአብሔር ፍቅር ብለህ! ሆስነር ! ” አለው ።

“ ቅድመ አያቶችህ የባቢሎን ሰዎች ነበሩ ፡ ሪሽ ? የእኔ የምርኮ ኛው ክፍል ነበሩ ? ከእነዚህ ሁሉ መቶ ዓመቶች በኋላ በእዚህ አፈራ ላይ ያለነው በዚያ ምክንያት ይሆን ? አላማህ ያ ነበር ? ሁለት ጥይ ቶች ተኩሶ የቀኝ የእጅ እንጓውንና የቀኝ ክርኑን መታው ።

ሪሽ በአሸዋው ላይ ኩርትምትም ብሎ ተንሰቀሰቀ ። “ ማረኝ ! ማረኝ ! እባክህ ! ”

“ ምሕረት ? እኛ ሴማውያን እርስ በእርሳችን ምሕረት አሳይተን አናውቅም ። ለሞሼ ካን ምሕረት አሳየኸው ? እርሱስ ለአንተ ምሕ ረት አሳየህ? ከኖህ ዘመን የውሃ ጥፋት ምናልባትም ከዚያ በፊት ጀምሮ ሰዎቻችን እርስ በእርሳቸው የአለ አንድ ምህረት ሲተራረዱ ቆይተዋል። በጤግሮስና በሜዲትራንያን መካከል ያለው መሬት በዚህ ዓለም ላይ እጅግ በጣም ትልቁ የመቃብር ቦታ እንዲሆን አድርገነዋል ። በፍ ርድ ቀን የሞቱት ከተነሱ የሚቆሙበት በቂ ቦታ አይኖራቸውም ” ብሎ በመተኮስ የቀኝ ክንዱን መትቶ በከፊል ጉዳው ።

ሪሽ ተዝለፈለፈ ። ሆስነር ወደ ሪሽ ተራምዶ ሌላ ጥይት ከአጐ ረሰ በኋላ ተኩሶ የሪሽን ራስ መታው ።

ሆስነር ሕይወት አልባ የሆነውን የሪሽን በድን በኃይል እረግጦ ስለገፋው በሸርታታው ቁልቁለት ላይ እየተንከባለለ ወርዶ በኤፍራ ጥስ ወንዝ ውስጥ ገባ ።

የሪሽ ሰውነት በውሃው ውስጥ ሲሰምጥ በሚመለከትበት ጊዜ ሁለት አሸባሎች ከታች በተራራው መነሻ ላይ ሆነው የሚንሳፈፈ ውን ኮንኮርድ እየተኮሱ ሲመቱት አያቸው ። ሆስነር ጠመንጃውን አስተካክሎ በኢላማው ውስጥ አስገባቸው ። በአንድ በኩል ሲመለ ከት ኤፍ-14 ተዋጊ ጄት በንጹሁ ሰማይ ላይ በቀጥታ ወደ እርሱ ሲመጣ አየው ። ጠመንጃውን ጥሎ እጁን በማወዛወዝ ምልክት ቢሰጥ አብራሪው አይመታኝም ብሎ በማሰብ ከአቅማማ በኋላ ወደ ሁለቱ አሸባሎች አቆልቁሎ ተኮሰ ።

ቴዲ ላስኮቭ ለአንድ ሴኮንድ ያህል ያዝ ከአደረገ በኋላ የመጨ ረሻ ሮኬቱን ተኮሰ ። የሆስነር ጥይት አለቀ ። ከቁልቁለቱ መነሻ ወደ

ኮንኮርዱ የሚተኩሰው ጥይት አቆመ ። ወደ እርሱ የሚመጣውን ሮኬት በትክሻው ላይ ተመለከተው ። ቀጥሎም ኤፍ-14 ተዋጊ ጄት በኤፍራጥስ ላይ ሲበር አየው ። ድርጊቶቹ በአለፉት ቀኖች ብቻ ሳይሆን በአለፉት ዓመቶች ሁሉ ራሱን በራሱ ማጥፊያ እንደ ነበሩ አወቀ ። እምላክ በጐ አድራጊ ብቻ ሳይሆን መጥፎ አድራጊም በመሆኑ ለእርሱ መጥፎ አድራጊ ነው ብሎ አሰበ ። ሆስነር ይህ እንደሚሆን አውቆ ስለነበር ለደረሰበት ችግር አላዘነም ፣ አልተጸጸተም ። የተሰማው ሀዘን ቢኖርም እንኳን ስለሚሪያም ነበር ።

በመጨረሻ ሆስነር ገብርኤል 32 የሚለውን የላስኮቭን ምልክት በብዥታ አየ ። ቀጥሎም የሚጋርድ ብርሃን ሸፈነው ። በወርቃማው ሙቀት ታፈነ ። ከሚሪያም ጋር ሆኖ ፀሐይ በፈነጠቀበት ክፍል ውስጥ ምግብ ሲበላ በአዕምሮው ውስጥ እንደ ሕልም ሆኖ ታየው ።

ላስኮቭ ዞሮ ሲመለከት የምዕራባዊው ተራራ በእሳት ተያይዞ አየው ።

* * *

ሳሌም ሀማዲ ወደፊት በፍጥነት አለፈ ። ከኋላው ረጅም ድጋፍ ያለው መቀመጫ እንደ ልብ ለማየት አያስችልም ። እንዴት አድርጎ ሥራውን እንደሚቀጥል ለጥቂት ጊዜ ከአሰበ በኋላ በበርግ ኋላ መጥቶ ስስ ፀጉሩን ይዞ ወደ ኋላ በመጐተት የበርግን ጉሮሮ አመቻቸው ።ሰውየውን እንዳየው የሚጠላው የሚቭትዛን ኤሎሂም ሐላፊ እንደነበረ አወቀው ። እጆቹ ተንቀጠቀጡ ። ለመግደል በወጥመድ ውስጥ የገባ ሰይጣን እንደ አገኘ ያህል አድርጎ ቆጠረው ። የበርግን ጉረሮ በጩቤው ሰነጠቀው ። ማንቁርቱንና መተንፈሻውን ለመጉመድ በተቃረበበት ጊዜ በግራው በኩል አንድ ሰው ሲንቀሳቀስ አየው ። ቤከር እየነቃ በመምጣት ላይ ነበር ። ቤከርን ሲመለከተው በዓይኖቹ ላይ ምሬትና ጥላቻ ከመታየቱም በላይ ትንሽ እንኳን ፍርሃት አልነበረውም ። የሀማዲ እጆች ፣ ዓይኖቹና ከንፈሮቹ መንቀጥቀጥ ጀመሩ ። አዘቅዝቆ ወደ በርግ ሲመለከት ይህን ሰው መግደሉ ምንም ጥቅም እንደማያስከትል ትውስ አለው ። አለመግደሉ ግን ለመኖር የሚያስችል ልዩነት ያመጣል ብሎ አሰበ ። በመሃል እጁ ውስጥ የገባ ጠላቱን አለመግደል የመጀመሪያ ጊዜው ነበር ። ለትንሽ ጊዜ ከአሰበ በኋላ ከበርግ አንገት ላይ ጩቤውን አነሳ ።

ቤከር ወደ ተሰባበረው መስኮት አመለከተው ።

ሀማዲ ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ "በእስራኤል ውስጥ ለአሉ ሰዎችህ ሀማዲ አንድ ሕይወት አዳነ ብለህ ንገራቸው ። ይስሐቅ በርግ ብድር እንዳለበት ንገረው" በማለት ረጋ ብለ እብራይስጥ ነገረው ። ማን

ያውቃል ፣ ምናልባት አሁን ያደረገውን ምሕረት ብድሩን አንድ ቀን ያገኝ ይሆናል ። ከሁለቱም በኩል ያሉ ወኪሎች ለሕይወታቸው ዋስ ትና እንዲሆናቸው የዚህ ዓይነት ደግ ነገር ያደርጋሉ ። ሳሌሜ ሀሚዲ አንድ የማይረሳ ውለታ አደረገ ። በቤከርና በበርግ መካከል ሀማዲ አልፎ በመሄድ በተሰባበረው መስታዎት መካከል ሾልኮ ወደ ውሃው ውስጥ ገብቶ ጠፋ ።

ቤከር አሁን ሙሉ በሙሉ ነፍሱን አውቋል ፣ ከበርግ አንገት ላይ የሚፈልቀውን ደም ስለ አየ ሕልም እንዳልሆነ አረጋገጠ ። ለማመን በጣም አስቸጋሪ ነገር ነበር ። አዲስ ክስተት በማያው ቁት አገር ብሎ አሰበ ። ሀማዲ - ሳሌም ሀማዲ - ይህን ምናልባት ወደ ኢየሩሳሌም እን ደገና ቢመለስ በሪፖርቱ ላይ ተርኮ ያቀርበዋል ።

ቤከር በትክሻው በኩል ዘወር ብሎ ጮኽ ተናገረ ። ወደ ካን ተመ ልክቶ ''ፒተር'' ብሎ ቢጠራውም መልስ አልሰጠውም ። በደረቱ ላይ ይፈስ የነበረውን ደም ሊያይ ስለአልቻለ የተመታው ቀዳዳ ተዘግቶ ይሆናል ፣ ወይም ሞቶ ይሆናል ብሎ አሰበ ።

ክንፎቹ ሰፊ ቦታ ስለያዙ ኮንኮርዱ በመንሳፈፍ ላይ ቢሆንም በዚህ ዓይነት ለብዙ ጊዜ እንደማይቀጥሉ ቤከር አውቋል ። በየሽን ቁሮቹ የሚገባው ውሃና በላዩ ላይ የሚያርፈው ማዕበል ኮንኮርዱን ወደ ውስጥ እየገፉት ነበር ። ከወደ ጅራቱ እየሰመጠ ከአፍንጫው ቀና እያለ መምጣቱን ቤከር አጢኖአል ።

ያኮቭ ሌይበር የክፍሉን ደጃፍ በኃይል ከፍቶ በመግባት ''ካፒ ቴን የዕቃ ማስቀመጫው'' ብሎ ተናግሮ ሳይጨርስ ካንና በርግ በወን በሮቻቸው ላይ ተዝለፍልፈው አያቸው ።

ሌይበር በአሁኑ ጊዜ ራሱን ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር ሥራውን በሚገባ በማከናወን ላይ እንደነበረ ቤከር አስተውሏል ።

'' የመጣህበትን ተናገር ።''

''በዕቃ ማስቀመጫው ክፍል ውስጥ ውሃ እያገዘ በመግባት ላይ ስለሆነ ራሳቸውን ሊያጠፉ የነበሩትን ሰዎች ወደ ሌላ ክፍል እንዲዛ ወሩ አድርጌአለሁ ። አልፐርን በጅራቱ ክፍል ውስጥ እንደነበረ ባው ቅም አሁን ላገኘው አልቻልኩም ።''

ቤከር ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ ''እሺ ቤተ አብራምስ ወደዚህ መጥታ ለካንና ለበርግ የሕክምና እርዳታ እንድታደርግላቸው ጥራት ። እስከ አሁን አላደረጉ እንደሆነ እያንዳንዳቸው ያለውን ሁሉ የሕይወት ማዳኛ ጃኬት እንዲለብሱ ትዕዛዝ ስጣቸው ። ከዚያ በኋላ ስለ ደረሰው ጉዳት ሙሉ ሪፖርት አቅርብልኝ '' አለው ።

"እሺ" ብሎ ሌይበር ሲሄድ ተሳፋሪዎቹ በጣም ከተጐዱት በስተቀር በስድስቱ በሮች ለመውጣት የተዘጋጁ መስለዋል ። ቤተ አብራምስን ከሚሪያም ጋር ተቀምጣ ስለ አገኛት በጀርዋ ሹክ ከአላት በኋላ አልፎ ለኤሼር አሮንስንና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ነገራቸው ።

ቤተ አብራምስ ፣ ኤሽር አሮንስንና አሪኤል ዌይዝማን በፍጥነት ወደ ነጂው ክፍል ሄዱ ። ሁለቱ ሴቶች በየተራ ካንና በርግን ወደ ተሳፋሪዎቹ ክፍል እየተሸከሙ ወሰዱአቸው ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በቤከር ትከሻ ላይ ዘመም ብሎ በእርጋታ " እየሰመጥን ነን ? " ብሎ ጠየቀው ።

ቤከር ሁለቱ ሴቶች በርግን ይዘው ከክፍሉ እስኪወጡ ድረስ ጠብቆ " አዎን ፣ እየሰመጥን ነው ። በድንገት ከሰመጥን ሁላችንም እናልቃለን ። አሁን እንዲወጡ ማዘዝ ትችላለህ " አለው ።

"ነገር ግን ቁስለኞቹ ።"

"የሕይወት ማዳኛ ጃኬት አልብሳቸው ። እዚህ መቆየት አይችሉም ።"

"ወደ የብሱ መድረስ አንችልም ?"

ቤከር በመስኮቶቹ መካከል ወደ ውጭ ተመለከተ ። በግራው በኩል የባቢሎንን ጉብታዎች አየ ። በመጨረሻ እደርስበታለሁ ብሎት የነበረውን የምሽግ ጉብታ ዞሮ ተመለከተ ። በጥጉና በወንዙ ዳርቻ ጥቂት ኮማንዶዎች እጃቸው ሲያወዛውዙ አያቸው ። ጥቂት ኮማንዶዎች በታንኳ ሆነው ሲከተሉአቸው አየ ። በምዕራብ ዳርቻ በኩል በእርቀት የአፈር ቁልልና አንድ ትንሽ መንደር አየ ። በዚያም ኮማንዶዎች ነበሩ ። በአካባቢያቸው እርዳታ ሊሰጡአቸው የሚችሉ ሰዎች እንዳሉ አየ ። በኢየሩሳሌም ውስጥም እንደዚሁ ይጠብቋቸው ይሆናል ። ከኤፍራጥስ ወንዝ መሃል ኮንኮርዱን ወደ ዳር እንዴት እንደሚወስደው ግራ ተጋብቷል ። ኮንኮርዱ መንሳፈፉን ከቀጠለ በራሱ ወደ ዳርቻው ይደርስ ይሆናል ። ነገር ግን አይመስልም ። " እስከ አሁን ድረስ መጥተን እዚህ ደርሰናል " አለው ።

"እየተቃረብን ነው ። ይህን ሁሉ የመጣነው በዚህ በተረገመ ወንዝ ውስጥ እንደ ዓይጦች ሰምጠን ለመቅረት አይደለም " ብሎ አሪኤል ዌይዝማን ከነገረው በኋላ የከበባቸውን በጭቃ የተሞላ ውሃ ተመለከተ ።

"ሆስነር ለመሳፈር ችሎ ይሆን ? " ብሎ ቤከር ጠየቀው ።

"አልተሳፈረም ፣ በዚያው ቀርቷል ።"

ቤከር ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ "ሚሪያም በርንስቴይን እንዴት ናት ? " በማለት ጠየቀው ።
ዌይዝማን ወደ እርሱ መልከት ብሎ " ምንም አትሆንም ፡ ካፒቴን" አለው ።

ፒተር ካንን ተሸክመው ወደሚወስዱት ሁለት ሴቶች ዞሮ ሲመለከት የአውሮፕላኑ አፍንጫ ቀና እያለ በሚሄድ ከደም ጋር የተቀላቀለው ውሃ ወደ ተሳፋሪዎቹ ክፍል ሲገባ አየው ። ዞሮ ከተቀመጠ በኋላ "ሳሌም ሀማዲ በዚህ ክፍል ውስጥ ነበር" አለ ።

"ምንድን?"

"ምንም አይደል ፣ እንዳው ሃሳብ ነው" ካለው በኋላ ወደ ዳርቻዎቹ ተመለከተ ። ውሃው በአውሮፕላኑ ውስጥ እየጨመረ በመሄዱ መንሳፈፉን በጣም ቀነሰ ። አንድ ሰው—ኮማንዶዎች ፣የተዋጊ ጄቶች አብራሪዎች ወይም እርሱ ራሱ - ሊወስደው ስለሚገባው ምርጫ በጣም በአስቸኳይ ማሰብ አለበት ።

ቤከር ዘቅዘቅ ብሎ መቀመጡን ተላምዶት ነበር ። አሁን ደግሞ ኮንኮርዱ ከአፍንጫው እየተቃና በመሄዱ ተንጋሎ ተቀመጠ ። እነዚህ ጥቃቅን ሁኔታዎች በችግር ጊዜ የባለጠ ፍርሃት ከመፍጠራቸውም በላይ ያበሳጫሉ ። ራዲዮኑን ሞከረ ። ነገር ግን ኤሌክትሪኩ ሥራውን ስለ አቆመ አይሠራም ። በረዳት አብራሪው ወንበር ላይ ለተቀመጠው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር " አንተ ለማዘዝ ከአልፈለግህ እኔ ካፒቴኑ ስለሆንኩ እንዲወጡ ትዕዛዝ ላስተላልፍ" አለው ።

አሪኤል ዌይዝማን ራሱንና ዓይኖቹን ወደፊት አድርጐ "በሚሰምጥበት ጊዜ ማስጠንቀቂያ የምንሰጥበት መሣሪያ አለን ? " ብሎ ጠየቀው ።

ቤከር ወደ ሚኒስትሩ ዞሮ " አሁን እኮ እየሰመጠ ነው ። ጥያቄው የአሰማመጡ ፍጥነት እንዴት ነው የሚለው ብቻ ነው ።የሚሰምጠው እንደዚህ ቀስ ብሎ ከሆነ ጥቂት መሄድ እንችላለን ። ነገር ግን በድንገት ከሰመጠ አለቀልን ማለት ነው ። "

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በእርቀት ላይ ወደ አለው ጉብታ ፣ ከዚያም በመቃረብ ላይ ወደ ነበሩት ታንኳዎች ተመልክቶ ከአቅማማ በኋላ "ትንሽ እንቆይ" አለው ።

"መልካም" ብሎ ቤከር በመስኮቱ መካከል ብሩሁን ቀን ተመለከተ ። በኮንኮርድ 02 ላይ የማይረሳ ስም ያለው ሥራ ሠርተዋል ።

አሁን ግን ዘዴውና ብልሃቱ ሁሉ እያከተመ የመጣ መሰለ ። ትልቅ የባሕር ወፍ የምትመስለው መንሳፈፍ አልቻለችም ።

ሚሪያም በርንስቴይን በቀዳዳው መካከል ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ ተመለከተች ። ሰው አልባ የሆነውን ምሥራቃዊ ቁልቁለት አየች። በእንባዋና በተሠባበረው መስታዋት ምክንያት የመሬቱ እይታ ግልጽ ባይሆንላትም ወደ ባቢሎን ትመለከት እንደ ነበረች አውቃለች ።አንድ መንደር በሩቅ አየች ። ሰዎችም በወንዙ ዳርቻ ይንቀሳቀሱ ነበር ።ብዙ ሰዎች በወንዙ ዳር ተሰብስበው አተኩረው ይመለከቱ ነበር ። የተሰ ባበረው መስታወት ጥቁር ጀለቢያ የለበሱትን ሰዎችና አሸዋ የተቀ ለለባቸውን ጐጆዎች ቀለማቸውን ቀስተ ደመና አስመስለው ። በባ ቢሎን ውስጥ እንዳለው ቀለሙ የተለወጠ ድንጋይ ዓይነት ነበር ።ምር ኮኞቹ አይሁዶች በገናቸውን በዛፉ ላይ ሰቅለው በወንዙ ዳርቻ ሲሠሩ በሃሳብዋ ታዩአት ። ተንፍሳ ግንባርዋን በመስታወቱ ላይ ስታስጠጋው እንባዋ በፊትዋ ላይ ፈሰሰ ። ሆስነር እንደሞተ አውቃለች ። ሆስነር ከአህመድ ሪሽ ወይም ከእርሱ መሰል ጋር በሆነው መንገድ የመገና ኘት የሕይወት ተልዕኮ ነበረው ። ያም ሆነ ይህ በመጨረሻው አንድ ዓይነት የመንፈስ ሰላም ሊያገኝ እንደሚችል ተስፋ አደረገች ።

ዳኒ ሌቮን በድምጽ ማጉሊያ መናገሪያው “ ነዳጅ ጄኔራል ” አለ ።

ላስኮቭ የነዳጅ መለኪያውን ተመለከተ ። በአካባቢያቸው ለጦር ነት ያረጉት እንቅስቃሴ ከአሰበው በላይ ነዳጅ ፈጅቶባቸዋል ። “ሮጀር ሁሉም ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ አዘዘ ።እኛ ለትንሽ ጊዜ በዚህ እያንዣበብን እንቆያለን ።”

“ሮጀር ። ” ሌቮን በራዲዮ ለሁሉም ትእዛዝ ስለ አስተላለፈ በላስኮቭ ፊት ለፊት በረሩ ። በወንዙ ላይ ዝቅ ከአሉ በኋላ ወደ ምዕ ራብ ዞረው ሄዱ ።

ላስኮቭ በመስኮቱ ከዓይኑ እስኪሰወሩ ድረስ ተመለከታቸው ። ፀሐይዋ በኢራን ላይ ደምቃ ስለወጣች ጨረርዋ በሜሶፖታሚያ ላይ በመረጨቱ ግራጫው መሬት ወደ ወርቃማነት ተለወጠ ። ነፋሱ ስላ ቆመ አልፎ አልፎ በየጉድጓዳው ተራራማ መሬት ላይ አቧራው ተከ ማችቶ እንደ ደመና ሆኖ አየው ። አቆልቁሎ ሁለቱን ሲ-130 ግዙፍ አውሮፕላኖችና በመጨስ ላይ የነበረውን የእንግዳ ማረፊያ ቤት ፣የባቢ ሎንን ፍርስራሾችና በመሃከል ያለውን የአረቦች መንደር ተመለከተ ። በሌላው ዳርቻ የአይሁዶቹን መንደርና ወደ እነእርሱ እየተንሳፈፈ የሚሄደውን ትልቅ ነጭ ኮንኮርድ ትኩር አድርጐ ከተመለከተ በኋላ

"ሊታመን የማይችል ነው" አለ በመናገሪያው ። "የማይታመን ነው" በማለት ዳኒ ሌቮን መስማቱን ገለጸለት ።

ላስኮቭ በኮንኮርዱ ውስጥ ትሆን ብሎ አሰበ ። እየሰመጠ ስለ ነበረ በመጠኑ የሚታየው ክንፉ ብቻ ነበር ። ለሁለት ደቂቃዎች እን ኳን ጊዜ መስጠት አልፈለገም ። በኤል ኤል መስመር "ኮንኮርድ 02፡ ይህ ገብርኤል 32 ነው ። ውጡ ፤ ትሰማኛለህ ?" መልስ የለም ። ላስ ኮቭ አምስት ታንኳዎች ወደ ኮንኮርዱ ሲቃረቡ አየ ። ቤከር በዚያ መኖ ራቸውን ያውቅ ይሆን ወይ ብሎ አሰበ ። ሁሉንም ባይዝ ቢያንስ ቢያ ንስ ቁስለኞቹ ሊሳፈሩባቸው ይችላሉ ። የቀሩት ሰዎች ሊዋኙ ፤ ወይም በሕይወት ማዳኛ ጃኬት ሊንሳፈፉ ይችላሉ ። ለምን አይወጡም ? ላስኮቭ በመሬት ላይ ላሉት ሁለት ኮማንዶዎችና ለሁለቱ ሲ-130 አብራሪዎች እነጋገራቸው ። እያንዳንዳቸው ሃሳብ ሊኖራቸው ይች ላል ። ግን አንድም ሰው በትክክል ለማድረግ የሚፈልገውን አላወቀም። ለሚያጋጥሙ አደጋዎች የሚሆኑ ዘዴዎች ተምረዋል ። በቴል አቪቭ ለዚህ ዓይነት ሥራ የተዘጋጁት እንኳን የአሁኑ ዓይነት ያጋጥማል ብሎ ያሰበ አልነበረም ። ሻለቃ ባርቶክ በታንኳዎቹ ላይ ስለ ነበረ ለማ ዳን እጅግ በጣም ቅርቡ እርሱ ይመስላል ። በኡማ የነበሩት ኮማንዶ ዎች ነዋሪዎቹ የነበራቸውን ኋላ ቀር መጓጓዣ ይዘው ወደ ኮንኮርዱ እንዲሄዱ ስለ ጠየቋቸው ጉዞ ጀምረዋል ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ "ጥቂት ሰዎች ይሞቱብን ይሆናል ።ግን ምን ማድረግ እንችላለን ?እንውጣ" አለው።

"አንድ ደቂቃ ጠብቅ" አለው ቤከር ። ላስኮቭን በወንዙ ላይ ሲበር አየው ። በመጀመሪያ በቀጥታ ወደ ታች ቀጥሎም በወንዙ የቀኝ ዳርቻ በረረ ። ቤከር ወደ ማይሠሩት መሣሪያዎች አጎንብሶ ተመል ክቶ የአስቸኳይ ኃይል መስጫውን ቁልፍ ከፈተ ። ግን አልሠራም ። ይህንም ቀደም ብሎ ቢያውቀውም የኤሌክትሪክ ኃይል ያስፈልገዋል። ሞተሮቹም ሆነ የኤሌክትሪክ ኃይላቸው ቆመዋል ። ባትሪዎቹ በውሃ ውስጥ ገብተዋል ። ሌሎቹም መሣሪያዎች ተበላሽተዋል ። ቀደም ብሎ ባያስታውሰውም ሌላ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት የሚችል መሣ ሪያ ነበር ። ወዲያው ከመቀመጫው ሥር የነበረውን በእጅ የሚንቀሳ ቀስ እጀታ በመሳብ ያለ ኤሌክትሪክ የሚንቀሳቀሰው የሃይድሮሊክ ፖምፕ እንዲንቀሳቀስ ሲያደርገው በኮንኮርዱ ሥር ያለችው ጠባብ መዝጊያ ተከፍታ የትንሹ ጄኔሬተር ተሽከርካሪ መዘውር ወደቀ ። ይህ የወደቀው መዘውር በውሃው ውስጥ ጄኔሬተሩን ሲያንቀሳቅስ ቤከር ተመለከተ ። በተጨማሪም ይህ መዘውር የአስቸኳይ ጊዜውን ሃይድ ሮሊክ ፖምፕ ስለ አንቀሳቀሰው በአንዳንድ መሣሪያዎች ውስጥ ተፈ



ADDIS ABABA
UNIVERSITY
HALL LIBRARY

ላጊው የአየር ግፊት እየጨመረ መጣ ። ይህ በመሆኑ ኮንኮርዱ በው ሃው ላይ ተሽከረከረ ።

በዚህ ወቅት ካን በበረራ መሐንዲሱ ቦታ ቢሆን ኖሮ ሁሉም ነገር በትክክል የሠራ ይመስለው ነበር - አለመኖሩ ያሳዝናል ።

ይህ የአስቸኳይ ጊዜ መሣሪያ በጥቂት ሴኮንድ ውስጥ በውሃው ለመበላሸት እንደሚችል ቤከር ተገነዘበ ። የኤሌክትሪክ መሣሪያዎቹም የብልሽት ምልክት ማሳየት ጀምረዋል ። ይሁን እንጂ የአየር ግፊቱ በተ ገቢው መጠን ነበር ። ቤከር መሪውን ሲያዞር የቀኝ ክንፉ ወደ ውሃው ውስጥ ሲሰምጥ የግራ ክንፉ ደግሞ ዞረ ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አይሆንም የማለት ምልክት በትከሻው ሰጠው ። "ዴቪድ ! እኔ - አልኩህ ። "

"ቆይ ! " ኮንኮርዱ እየተንቀሳቀሰ ወደ ቀኝ ማምራት ጀመረ ። በከፊል አቅጣጫውን ለወጠ ። በከፊል ደግሞ ወደ ምዕራብ ዳርቻ ግማሽ ጐኑ አዘመመ ። ቤከር በፊት ለፊቱ ከአፈር የተደለደለ ከወንዙ ጋር የተገናኘው ፣ የኡማ ኋላ ቀር ማጓጓዣዎች መቆሚያ የሆነውን ስለ አየ አውሮፕላኑ ወደዚያ ሄዶ እንዲቆም ፈለገ ።

ኮንኮርዱ በሚዞርበት ጊዜ የመስመጡም ፍጥነት ጨመረ ። አቅጣጫውን በሚለውጥበት ጊዜ በአደረገው መንዘፍዘፍ በውስጡ የነበረው ውሃ ስለወጣ ፍጥነቱን ጨመረ ። ቤከር መሪውን አጥብቆ የያዘበት እጁ ወደ ነጭነት ተለወጠ ። መሥራት ጀምረው የነበሩት ልዩ ልዩ የአውሮፕላኑ አካሎች እንደገና መንቀሳቀሳቸውን ማቆም ጀመሩ ። ተስተካክሎ አግድም በመሆን በውሃው ላይ ወደፊት መሄ ዱን ቀጠለ ። ቤከር እንደ አሰበው በተንቀሳቀሰበት ጊዜ ያገኘው የኃ ይል ግፊት እንዲሄድ አድርጐታል ። ኮንኮርዱ የሚሄደው ውሃው ወደሚወርድበት አቅጣጫ ስለ ነበረ ለመንቀሳቀስ የተሻለ ግፊት አደ ረገለት ። በዚህ ዓይነት ሄደው ከጭቃው ቁልል ጋር የሚጋጩ መስሎ ለቤከር ታየው ።

ቤከር በድንገት ከተሳፋሪዎቹ ክፍል የደስታ ሳቅና ጩኸት ስለ ሰማ ከትከሻው ዘወር ብሎ ሲመለከት ያአኮብ ሌይበር እየሮጠ ወደ እርሱ ሲመጣ አየው ። ቀጥሎም " ኮማንዶዎቹ ከታንኳዎቻቸው ጋር ወደ እኛ ደርሰዋል " ብሎ ነገረው ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዞሮ በመስኮቱ ተመልክቶ "ምናልባት ቁስለኞቹን ለማውጣት መሞከር አለብኝ " አለው ።

"አሁን የምንገኘው በአጉል ቦታ ላይ ስለሆነ ለጊዜው አንድም ሰው እንዳይንቀሳቀስ" አለው ቤከር ።

ሌይበር ወደ ተሳፋሪዎቹ ሄዶ የቤከርን ትዕዛዝ አስተላለፈ ።

ቤከር ወደ እርሱ አቅራቢያ የመጣውን ታንኳ አየ ። በውስጡ የነበረው ሻለቃ ባርቶክ ስለመውጣት ጮኾ አንድ ነገር ነገረው ። ቤከር ራሱን በአይሆንም እንቃንቆ ሁኔታውና የአውሮፕላኑ እኳኋን ለመውረድ አመቺ እንደ አልሆነ በእጁ አሳየው ።

ሻለቃ ባርቶክ የገባው መሆኑን በራሱ ምልክት ሰጠው ። ቀጥሎም አውራጣቱን ወደ ላይ በማድረግ ቤከር መጥፎ አብራሪ አለመሆኑን በምልክት አሳየው ።

ቤከር ፊቱን ከወደመስኮቱ መልሶ ወደ ወንዙ መመልከት ጀመረ። በጭቃው ክምር አጠገብ ሊደርሱ 150 ሜትር ይቀራቸዋል ። ይህም የኮንከርዱ እርዝመት ሁለት እጥፍ መሆኑ ነው ። የጥንት መጓጓዣዎቹ በአውሮፕላኑ ግራና ቀኝ ደርሰዋል ። ልዩ የሚመስሉትን አይሁዶች በመጓጓዣዎቹ ላይ አያቸው ። ቤከር ወደፊት ለፊቱ ሲመለከት ኮንኮርዱ የጭቃውን ቁልል እሁለት የሚከፍለው አልመሰለውም ። ምናልባትም ይከፍለው ይሆናል ። ከአሁን በኋላ የሚያደርጉት ሙከራ የማይኖር መሆኑ ተሰማው ። ከብዙ ጊዜ በኋላ የመዝናናት ስሜት ሰውነቱን ወረረው ። በሰባራው መስኮት መካከል ሲመለከት ጥሩው አየር በፊቱ ላይ አረፈ ። ከጭንቀቱም የተገላገለ መስሎ ተሰማው ። ሁኔታውን ሲከታተል ኮንኮርዱ ወደ ቀኝ የሚያዘንብል መሰለው ወይስ በውሃው ላይ ያረፈው የፀሐይ ብርሃን አንጸባርቆበት እይታውን ከልክሎት ይሆን? በቀጥታ ወደ ጭቃው ቁልል ቢሄዱ ኖሮ ኮንኮርዱን ማዞር ነበረበት ? ስለ ጄኔራል ላስኮቭ በኋላ መጠየቅ ይኖርበታል ።

የቀኝ ክንፉ በድንገት የውሃውን ዳርቻ አርሶ ወደ ላይ ሲወጣ ባጋጠመው ግፊት ምክንያት ኮንኮርዱ በበለጠ ወደቀኝ እንዲዞር አደረገው ። ዳርቻው ከፍ እያለ የሄደ ስለነበረ የቀኝ ክንፉም ከፍ እያለ ስለሄደ ሌላው ክንፉ ወደ ውሃው ውስጥ በበለጠ እንዲገባ ገፋው ።

በጭቃው ቁልል አጠገብ ደረሱ ። ኮማንዶዎቹና የመንደሩ ሰዎች ወደ ጐን ገለል ቢሉም አርቀው አልሄዱም ። አጐንብሶ የነበረው የኮንኮርዱ አፍንጫ ጥንት ከጭቃና ከጡብ በተሠራው ቁልል ውስጥ ስለገባ ጉብታው ተንቃነቀ ። ኮንኮርዱ ቀስ ብሎ በመስመጥ ላይ እንደ ነበረ ለቤከር ተሰማው ። ኮማንዶዎቹ ፣ የመንደሩ ሰዎችና በሕይወት የተረፉት ሰዎች ኮንኮርዱን አጥለቀለቁት ። በአውሮፕላኑ በውጭ ገላው ላይ ወጥተው ሲነጋገሩ ሰማቸው ፣ በግራ ክንፉ በኩል በውሃው ላይ እያቋረጡ ሲመጡና በኮንኮርዱ መግቢያዎች ወደ ውስጥ ሲገቡ

ሰማቸው ። ሰዎች ሲጮኹ ፣ ሲያለቅሱና ሲተቃቀፉ ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ ታወቀው ። ቀጥሎም የታየው በቁልሉ አፈር ላይ ቆሞ ኮንኮር ዱን ሰላምታ ሲሰጥ ነበር ። ከዚያም አንድ ሰው ይዞት ሄደ ።

## —38—

ሚሪያም በርንስቴይንና አሪኤል ዌይዝማን በቁልሉ አፈር ላይ ሻለቃ ባርቶክን አገኙት ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ራሱን ከእስተዋ ወቀ በኋላ ወደዚያው "የሰላሙ ስብሰባ እንዴት ሆነ ?" ብሎ ጠየቀው።

ሻለቃው ፈገግ ብሎና ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ " በኒውዮርክ የእስራኤልን መልዕክቶኞች እየጠበቁ ናቸው" አለው ።

አንድ የሲ-130 አውሮፕላን ሠራተኛ " የውሃ ችግር አላጋጠማ ችሁም ነበር ?" ብሎ ዴቪድ ቤከርን ጠየቀው ።

ያለ ጥርጥር ደርሶብናል ። እያንዳንዱ ሰው ምን ያህል ጠምቶት እንደነበር ማየት አትችልም ?" ብሎ ቤከር መለሰለት ።

ሠራተኛው "ገባኝ ። ።ነገር ግን ሰዎቹ ጢማቸውን ለምን እንደ ተላጩ አልገባኝም " አለው ። "ተላጭተዋል ? ብሎ ቤከር የራሱን ፊት ከዳበሰ በኋላ "እንድንላጭ አደረገን" አለው ። ቄስ ሌቪን በተ ራራው ላይ ወደ ነበረው ወደ ሻለቃ አሮን በታንኳ እንዲወስደውና የ ሞቱትንና የተቀበሩትን እንዲያሳየው ሻለቃ ባርቶክን ጠየቀው ። ሻለቃ ባርቶክ ግን የእርሱ ወደእዚያ መሄድ አስፈላጊ አለመሆኑን ነገረው ። ይሁን እንጂ ባርቶክ መሄድ አያስፈልግም ማለቱስ ህተት መሆኑን ቄሱ አስረዳው ። የኡማ መንደር ሰዎች በዚያ በጠባብ መንገዳቸው የተደረገ ውን የሰልፍ ዓይነት ከዚያ በፊት ፈጽመው ዓይተው እንደማያውቁና ወደፊትም ለማየት የሚኖራቸው ዕድል አጠራጣሪ እንደነበረ አው ቀዋል ። የመንደሩ ሰዎች ምግብና ወይን ለሚፈልጉት ሁሉ ሰጡ። የታመሙትን በወሳንሳ እየተሸከሙ ወሰዱ ። ለቅሶ ፡ ጩኸት ፡ ዘፈ ንና ዳንስ የተቀላቀለበት ፈንጠዝያ ተደረገ ። በኮንኮርዱ ውስጥ የነ በሩት ሰዎች ወደ ሲ-130 ሲዛወሩ ዋሽንቶች ተነፉ ። አንድ ሽማግሌ ለሚሪያም በርንስቴይን አንድ በገና ሰጣት ።

በሕይወት ለአሉት ሁሉም ነገር በጥድፊያ ተደረገላቸው ። እያ ንዳንዱ ሰው የሚጠይቃቸው ነገሮች ነበሩት ። ኮማንዶዎቹ የበለጠ በጠ የቁ ቁጥር የኮንኮርዱ ሰዎች የበለጡ ጥያቄዎች አቀረቡ ።

ሻለቃ ባርቶክ ራዲዮኑን አንስቶ በሲ- 130 አብራሪ ክፍል ውስጥ ለተቀመጠው ለካፒቴን ጌይስ " ለኢየሩሳሌም - - - ንገር ። ራሳቸውን

ከምርኮኝነት ነጻ አውጥተዋል ። ይዘናቸው እንመጣለን ። ስለደረሰው ጉዳት ወደፊት እንገልጻለን ብለህ ለኢያሩሳሌም ንገር'' ብሎ አዘዘው ።

''ሮጀር ፤ ብሎ ጌይስ የራዲዮ መልዕክቱን አስተላለፈ ።

የራዲዮ መልዕክቱ በድምጽ ማጉሊያው ውስጥ እንደ ተሰማ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመቀመጫው ላይ ቀጥ ብሎ በመቀመጥ ዓይኖቹን አሻሸ ። ስለራሳቸው እርግጠኛ እንዴት እንዳልነበሩና እንዴት እንደ ተጠራጠሩ አሰበ ። በመጨረሻ ግን ''ይሒዱ'' ብለው ወሰኑ - ከሁሉም በላይ የሆነው ተፈላጊ ነገር ይህ ነበር ። ማን በሕይወት እንዳለና ማን እንደሞተ በአዕምሮው ውስጥ አብሰለሰለ - የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በሕይወት ይኖር ይሆን ? የሰላም ተደራዳሪዎቹስ ? በርንስቴይን ? ቴኮ ? ታሚር ? ጃባሪ? አሪፍ ? በርግ እንዴት ይሆን ? ዶብኪንስ ? በሕይወት ይኖር ይሆን ? ሆስነር - ያ ታላቅ ምሥጢራዊና ችግር ፈጣሪ ። የትራንስፖርት ምክትል ሚኒስትሪት - በርንስቴይን - የትራንስፖርት ሚኒስትሩን ሳታበረው ታቆየው ይሆን ? በሕይወት ከአለ መልስ የሚሰጥባቸው ብዙ ጥያቄዎች አሉ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዓይኖቹን ገልጦ ዙሪያውን ተመለከተ ። ''ጀግኖች ፣ ሰማዕታት ፣ አታላዮችና ቦቅቧቆች— ማን ማን እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ ቢያንስ ቢያንስ አንድ ወር ያስፈልገናል ።

ካፒቴን ኢሽማኤል ብሎሽ ሲ-130 ግዙፍ አውሮፕላኑን በሂላ መንገድ ወደ ላይ አሽከረከረ ። በአውሮፕላኑ ውስጥ የሻለቃ አሮን ኮማንዶዎች በሙሉ ፣ በተራራው ላይ ተቀብረው የነበሩና ያልተቀበሩ የአልፐርን ጭምር አስራ አምስት አስከሬኖች ፣ በተጨማሪ በተራራው ግርጌ ተቆራርጦ የተገኘ በድን ነበሩ ። ኮማንዶዎቹ በውስጡ ማስታወሻ የተቀመጠበትን የበርግን ጫማ አገኝተዋል ። ማስታወሻውን ማግኘታቸው ይህን አስቀያሚ የሆነ ሥራ ለመጨረስ የተቃረቡ መሆናቸውን ለማወቅ አስችሏቸዋል ።

የአረብ ነው በማለት ሊተውት ተቃርበው የነበረ በፈንጂ በጣም የተጐዳና የተቃጠለ አንድ የሰው አካል አገኙ ። ነገር ግን አንድ አስተዋይ ወታደር በአንገቱ ላይ በወፍራም ሰንሰለት የተንጠለጠለ ከብረት የተሠራ የዳዊት ኮከብ አየ ። እንደዚሁም በአውሮፕላኑ ውስጥ ሠላሳ አምስት የቆሰሉ አሸባሎች ስድስት - በሽብር ፈጣሪነታቸው ይፈለጉ የነበሩ - ነበሩ ።አህመድ ሪሽና ሳሌም ሀማዲ በእነዚህ ውስጥ እንዳልነበሩ ታምኖአል ።

በኦፕራሲዮን ክፍል ውስጥ ጄኔራል ዶብኪንና ደቦራ ጌዲዮን በጠረጴዛዎች ላይ ተጋድመዋል።ሁለቱ የቀዶ ጥገና ሀኪሞች አውሮፕላኑ ተነስቶ እስኪበር ድረስ ሥራቸውን አቋርጠው ቆመው ይጠብቃሉ።

ቄስ ሌቪን ወደ ቀዶ ጥገናው ክፍል መጥቶ ሀኪሞቹን ተመለከተ ። ደቦራ ጌዲዮንን እያከመ የነበረው ሀኪም ቀና ብሎ በመመልከት በፍጥነት ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። ጄኔራል ዶብኪንን ታክም የነበረችው ሴት በአፍዋ ላይ የነበረውን ጨርቅ ዝቅ አድርጋ "የዚህ ዓይነት የጭካኔ ሥራ አይቼ አላውቅም ። ግን በሕይወት መኖር ይችላል ።አንተ አሁን በዚህ ቦታ አትፈለግም መምህር" ብላው አፏን መልሳ በጨርቁ ሸፈነች ፡

ቄስ ሌቪን ተመልሶ ከመቶ አለቃ ጊደል ጋር ስለሚቀርበው ምግብ ለመነጋገር ወደ አውሮፕላኑ የኋላ ክፍል ሄደ ።

ሲ-130 ግዙፍ አውሮፕላን ለመነሳት ብዙ ጊዜ ስለፈጀበት ካፒቴን ብሎሽ ትዕግሥቱ እያለቀ ስለመጣ "ወደ ባግዳድ መብረር እንደ ምንችል ነግሬህ ነበር" አለው ።

"ይህ የይለፍ ቀረጥ የሚከፈልበት መንገድ እንዳልሆነ ተስፋ አደርጋለሁ ።"

በመጨረሻ ግዙፉ አውሮፕላን ተነሳ ። ብሎሽ ወደ ግራ ታጥፎ በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ ከበታቹ የነበረውን ኮንኮርድ እያየ "ስማ ኤፍሬም ያን አውሮፕላን ያበረረውን ሰው ባገኘው እንዲያወጣው እነግረው ነበር" አለው ።

"ቤከር ነው ። በሥልጠና ጊዜ አብሬው በርሬ አለሁ ። ግሩም አብራሪ ነው ።" ብሎሽ ፈገግ ብሎ "ይህ በጣም አስቸጋሪ ሥራ ነበር፣አልነበረም ?" ሻለቃ ባርቶክ ሽማግሌው ሰው አህያ ጋልቦ በጭቃማው ሜዳ ላይ ሲመጣ አየው ። ሲ- 130 አውሮፕላን ጭነቱን እየጨረሰና ሞተሮቹም እየተሽከረከሩ ሲሆኑ ለሽማግሌው ሰው ትንሽ እንኳን ቁም ነገር የሰጡት አልመሰለም ። ባርቶክ በኋላ መግቢያው በኩል በትዕግሥት ቆሞ ጠበቀው ።

ሺር ጃሹብ ሆነ አህያው ትልቁ አውሮፕላን ያስፈራቸው አልመሰሉም ። ሽማግሌው ሰው አህያውን ጋልቦ እየነዳ ባርቶክ እቆመበት መውጫ አጠገብ ሲደርስ ቆመ ። እንደ ደረሰ ከአህያው ላይ ሳይወርድ 'ጄኔራል ዶብኪን የት ነው?' ብሎ ጠየቀው ።

"በዚያ አውሮፕላን ውስጥ ነው፣ ደህና ነው" ብሎ ወደ ሰማይ አመለከተው ። ሽማግሌው ሰው ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ "መልዕክት አድርስልኝ" አለው ።

"ያለጥርጥር።"

"በተጨማሪም የጥያቄህ መልስ ነው" ብሎ ሺር ጃሹብ በእህ ያው ጀርባ ላይ ቀጥ ብሎ በመቀመጥ "እኛ የኡማ ሰዎች ስላአቀረባች ሁሉን መልካም ጥያቄ እናመስግናለን ። ነገር ግን ከእናንተ ጋር ወደ እስራኤል አንሄድም" አለው ።

ሻለቃው በብስጭት ራሱን በአሉታ እያነቃነቀ "ለምን አትሄዱም? እዚህ የወደፊት የመኖር ዕድል የላችሁም" አለው ።

"ወደፊት በዚህ ስለሚሆነው የሚያሳስብ ነገር የለም " አለው ሺር ጃሹብ እነጋገሩን ጠበቅ በማድረግ ።

"ወደ ቤትህ ወደ ኢየሩሳሌም ና መምህር ፡ ቦታ አለን ። አሁኑኑ ሁሉም ወደ አውሮፕላኑ እንዲመጡ አድርግ ። የሚያስፈራ ምንም ነገር የለም ። ሰዎችህን ሰብስብ ፡ ዕቃዎችህን አምጣ ፡ከአስፈለገም እን ስሳዎችህን ጭምር አምጣ። ሂደህ ሰዎችህን ሰብስበህ አምጣቸው ሺር ጃሹብ ። ምርኮኝነቱ አብቅቷል ። ተነሳ ከባቢሎን እንሂድ ።"

ሽማግሌው ሰው ቀረብ ብሎ ወደ አውሮፕላኑ ውስጥ ተመለከተ ። አስደናቂ መብራቶች አየ ። ድምጽም ሰማ ። በውስጡ አይሁዶች - እሥራኤሎች - ሲራመዱ ፡ ሲቀመጡ ፡ሲያለቅሱ ፡ሲስቁ ማየት ቻለ። ያ ሁሉ ለምን እንደነበረ አልገባውም ። ከኃይለኛ ሕዝብ የመጡ መሆ ናቸው ግን ገብቶታል ። ከዚያ ሀይለኛ ሕዝብ ጋር የኡማ ሕዝብ እንዲ ቀላቀልና የኡማ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ከዚህ ሕዝብ ጋር ማደግና መኖር እንደሚችሉ አውቋል ። "ብዙ ወዳጆችና ዘመዶች በሂላና በባ ግዳድ አሉን ። ወደ ኡማ መጥተው ሲያጡን ምን ይላሉ ? በዚህ ዓይነት መሄድ አንችልም ።"

ባርቶክ የብስጭት መወራጨት እያሳየ " እዚህ መኖር ትፈልጋለህ ብየ አላምንም ። ይህ በጣም አስፈሪ ቦታ ነው" አለው ።

"ይህ ቦታችን ነው ። ለጄኔራል የነገርኩትን ለአንተም መልሼ ልንገርህ ። ሁልጊዜም በስተኋላ ቀሪ መኖር አለበት ። እኛ በእያንዳንዱ ሕዝብ ውስጥ ሁልጊዜም በዓለም ላይ ከተሰደድነው ውስጥ መኖር አለ ብን ። ኢየሩሳሌምን በመውሰድ ሊጨርሱን አይችሉም ። የምነግርህ ገብቶሃል ?"

ሻለቃ ባርቶክ በመጀመሪያ ሜዳውን ቀጥሎም ወደ ሽማግሌው ሰው ተመልክቶ " አዎን ፡ ያልከው ገብቶኛል ። ግን ይህ መሬት ልዩ ነው ። ስለዚህ ቦታ አንድ መጥፎ የሆነ ነገር አለ።እናንተ በዚህ ያላችሁ ወደ ዚህ የመጣችሁት በባርነት ነው ። አሁንም የምታስቡት ባሪያ እንደ ሆናችሁ ዓይነት ነው" አለው ። የትም ቦታ እንደማይሄድ ስለገባው

ፈገግ አለ ። የመጨረሻው ቁስለኛ ተሳፈረ ። ከአሁን በኋላ እንደማይ ጠብቀው አወቀ ። ራሱን አስገድዶ ፈገግ በማለት ‘‘መምህር ፣ ይህን አስታውስ - አሁን እያንዳንዱ ሰው የሚደክምለት ሰላም በደህና ከተ ከናወነ የዚህ መሬት አይሁዶች ከፈለጉ ወደ እሥራኤል መምጣት ይችላሉ ። በሂላና በባግዳድ ለሚኖሩትም እየጠበቅናቸው መሆናችንን ንገራቸው ። ለኡማ - - - እና ለሺር ጃሹብ እየጠበቅን ነን ።

‘‘አስታውሳለሁ ።’’

ሻለቃ ባርቶክ በአዎንታ ራሱን ነቅንቆ ‘‘ አንተን ለማሳመን የሚ ችሉ ቃላት ባገኝ ኖሮ እደሰት ነበር ። ምናልባት ጄኔራል ቢኖር ኖሮ - - - ደህና ሁን ሺር ጃሹብ ። ወደ ኢየሩሳሌም - - - መሄድ አለብን’’ አለው ።

ሽማግሌው ሰው በከተማው ስም ፈገግ ብሎ ‘‘በአሁኑ ጊዜ ጠን ካራና ኃይለኛ ከተማ ነው’’ አለው ።

‘‘አዎን ።’’

‘‘ደህና ሁን’’ ብሎት በዛቡ አህያውን አዙሮ እየጋለበ ሄደ ።

ሻለቃ ባርቶክ ለጥቂት ሴኮንዶች ከተመለከተው በኋላ ለሠራተ ኞቹ አለቃ ምልክት ሰጠው ። ሻለቃው ወደ ውስጥ ገባ ። መዝጊያውም ተዘጋ ። ወደ ሠራተኞቹ አለቃ ዞሮ’’ ወደ ቤታችን ለመመለስ ተዘጋ ጅተናል ብለህ ለአብራሪዎቹ ንገራቸው’’ አለው ።

በክፍሉ ውስጥ አንድ ቡድን ከኤርሚያስ የሚከተለውን ሲያነብ ሰማው - - - ታላቅ ጉባኤ ወደዚህ ይመለሳሉ ፤ በለቅሶ ይመጣሉ - - -

# ቅጥያ

*እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና ። በያዕቆብ ደስታ ደስ ይበላችሁ ፤*
*በአሕዛብም አለቃ እልል በሉ ።*
*ድምጻችሁን ከፍ አድርጉ አመስግኑም ፤*
*በሉም አቤቱ ሕዝብህን አድን ፤*
*የእስራኤልን ቅሬታ ።*
*እነሆ ከመስዕ ምድር አወጣቸዋለሁ*
*ከምድር ዳርም አስባስባቸዋለሁ ፤*
*በመካከላቸውም እውርና አንካሳ ይኖራሉ ፤*
*ያረገዘችና የወለደችም ባንድ ፤*
*ታላቅ ጉባኤ ወደዚህ ይመለሳሉ ።*
*በልቅሶ ይመጣሉ ፤*
*በምሕረትም እመራቸዋለሁ ።*
*በፈሳሽ ውሃ አጠገብ አመጣቸዋለሁ ፤*

በቀና መንገድ አይሰናከሉበትም ....
የእግዚአብሔርን ነገር ስሙ እላንተ የአሕዛብ ወገን

በሩቅም ደሴት ወሬ ንገሩ ። በሉም ፤
እሥራኤልን የበተነ ይሰበስበዋል ፤

በግ ጠባቂም መንጋውን እንደሚያሰማራ ያሰማራዋል ። እግዚአብሔር ያዕቆብን ያድነዋል ፤

ከርሱም ከሚበረታ እጅ አዳነው ።

ኤርምያስ 31፡ 7—11

ሁለቱ ሲ- 130 ግዙፍ አውሮፕላኖች ተከታትለው በኢራቅ ምድረ በዳ ላይ ወደ ምዕራብ በረሩ ።

ይስሐቅ በርግ በሸራ ወንበር ላይ ተቀምጦ ስለ ተወሰዱት እር ምጃዎች ሪፖርት በመጻፍ ላይ ከነበረው ከሻለቃ ባርቶክ ጋር ቀስ ብሎ ተነጋገረ ። የበርግ እጆችና የተቆረጡ ሰውነቶቹ አይዮዲን ተቀብተ ዋል ። በአንገቱ ላይ የታሰረውን ፋሻ እየነካካ ጥያቄውን ቀጠለ ። ለባርቶክ ጥያቄዎች በርግ የሰጣቸውን መልሶች ባለማመን ባርቶክ ራሱን ነቀነቀ ። የሰላም ተልዕኮው ቡድን በሚገባ የሰለጠነውን ወታ ደር ከእነሙሉ ትጥቁ እንዴት ሊያሸንፍ እንደቻለ ወታደሩ ባርቶክ ለማወቅ ፈለገ ። በሙያውና በግል ፍላጐቱ በወታደር ዓለም ውስጥ ተአምር ሊያሳዩ የቻሉበትን ምሥጢር ለማወቅ ጥረት አደረገ ። “ምና ልባትም ጥቂት የሰላም መልዕክተኞች የያዙ ባታሊዎኖች በጦር ኃይሉ ውስጥ ቢኖሩ ይጠቅሙ ይሆናል ” አለው ።

በርግ ፈገግ አለ ። “እኔ እንደማስበው በሰላሙ ውይይት በጣም ስለ አመኑና ይህን የሰላም ውይይት ሌላ ሰው በመቃወሙ ከቁጣቸው የተነሳ ግልገልዋን ለማዳን እንደምትከላከል አራስ ነብር ሆኑ ። አነ ጋገሩ ቀልድ ቢመስልም ትክክለኛ ነበር ። ነገር ግን ስለ ሁኔታው ለመ ግለጽ እጅግ በጣም የተሻለው መንገድ ይህ ነው ብዬ አምናለሁ ። ”

“ጥሩ አባባል ነው” አለው ሻለቃ ባርቶክ ። “ነገር ግን የአመራር፣ ለመከላከል አመቺ የሆነ አካባቢና ብልህ ተከላካዮች የተቀነባበሩበት ነበር ብዬ እጽፋለሁ ።”

“ጥሩ አቀራረብ ይመስላል ” አለው በርግ ።

በርግ ከአውሮፕላኑ አስተናጋጅ ሌላ ቡና ተቀብሎ ተደላድሎ ተቀ መጠ ። በረራው አጭር ቢሆንም በሕይወቱ ሙሉ ከተጓዘው እጅግ በጣም ረጅሙ ሆነበት ።

ሻለቃ ባርቶክ በጦርነት የሞቱ ፣ በጦርነት ላይ የቆሰሉና በጦርነት ላይ የጠፉ ብሎ በሦስት በመከፋፈል የጻፈውን ደግሞ ማንበብ ጀመረ ።

በርግ ሰፊውን የመንገደኞች መቀመጫ ክፍል ዙሪያውን ሲመለከት ሞተው በአረንጓዴ ፕላስቲክ ተሸፍነው በሌላው አውሮፕላን ከተወሰዱት ሌላ በዚህኛው ውስጥ መገኘት የነበረባቸውን ብዙዎቹን ማየት አልቻለም ።

"የጸጥታ ሰዎችህ ድንቅ ሥራ ሠርተዋል " አለው ባርቶክ ።

በርግ ራሱን በአዎንታ ነቅንቆ " ከስድስቱ የጸጥታ ሰዎች ውስጥ አምስቱ ሞተዋል - ብሪን ፤ ካፕላን ፣ ሩቢን ፣ አልፐርንና ማርክስ - ጃፍ ብቻ በሕይወት ቢኖርም ቆስሏል ። የሆስነር ቤተመንግሥት ተከላካዮች እነእርሱ ለእርሱ ፣ እርሱ ለእነእርሱ ታማኞች ነበሩ ። ሰዎች ከዚህ የበለጠ አንዱ ከአንዱ ሌላ ምን ሊጠይቁ ይችላሉ ? እነ እርሱ የሰለጠኑ ባለሙያዎች ነበሩ ። የሰለጠኑ ባለሙያዎች ደግሞ ሁልጊዜም ቢሆን ተመጣጣኝ ያልሆነ ጉዳት ይደርስባቸዋል ። መሆንም ያለበት እንደ ዚያ ነው ።

የኤል አል ሠራተኞች እንደዚሁ ባለሙያዎች የሆኑ ተመጣጣኝ ያልሆነ ሥቃይ ደርሶባቸዋል ። በሎድ ሆነ በባቢሎን የእነርሱ አውሮፕላን ስለነበረ ለተሳፋሪዎቹ ሙሉ ኃላፊነት እንደነበረባቸው ተሰምቷቸዋል ። ዳንኤል ጃኮቢና ራሄል ባኡም ክፉኛ ቆስለዋል ። በርግ በቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ እንደነበሩ አውቋል ። ይህ በአረንጓዴ ፕላስቲክ ተጠቅልለው በሬሳ ማስቀመጫ ክፍል ውስጥ ከመግባት በጣም የተሻለ ነበር ። ፒተር ካን ከቀዶ ጥገና ክፍል ወጥቷል ። ሐኪሙ ደሙ ጨርሶ እንዳይፈስ በርግ በካን የቁስል ቀዳዳ ውስጥ ወትፎት የነበረውን በደም የተበከለ ካርታ የተሳለበትን ወረቀት ለበርግ እያሳየው "ሕይወቱን አድንኸዋል ። ከሆስፒታል በሚወጣበት ጊዜ ለአንተ የሚከፍለው ብድር አለበት " ብሎ ከነገረው በኋላ ካርታውን ጨባብጦ በቆሻሻ ማስቀመጫ ውስጥ ጣለው ።

ከጸሐፊዎቹ ፣ ከአነጋጋሪዎቹና ከረዳቶቹ ውስጥ የሞቱ ነበሩ ። በጊዜያዊ የጦር ምሽጋቸው ውስጥ አራት ወንዶችና ሴቶች በጠላት ተገድለዋል ። እንደዚሁም ኢየሩሳሌም ከመድረሳቸው በፊት በአውሮፕላኑ ውስጥ የሚሞቱ ይኖራሉ ። በርግ ሁሉንም አያውቃቸውም ። ሀዘኑን አምቆ የሚይዝበት ልቡ ስለሞላ ስለአላወቃቸው ተደስቷል ።

የጠፉም ነበሩ ። ይህ ደግሞ ከሁሉም የበለጠ እጅግ በጣም አሰቃቂው ነበር ። ለሞታቸው ታዝናለህ ወይስ በአንድ ቦታ ወድቀው እዮ

ተሰቃዩ በሕይወት አሉ ብለህ ትስፋ ታደርጋለህ ? በአንድ አረብ ቁጥ ጥር ሥር እንዲቆዩ ትጸልያለህ ? ሚሪያም በርንስቴይን ከማንም የተ ሻለ መልስ ልትሰጥበት ትችላለች ። አሁን ልትጨነቅላቸው የሚገባት ሁለት አሉአት ።

ናእሚ ሀበር የት እንዳለች የሚያውቅ አንድም ሰው የለም ። ካፕላን ወደነበረበት ቦታ አድብታ በመሄድ ከሥቃዩ ለማዳን ገድላዋለች የሚል ሃሳብ እንድ ሰው ተንፍሷል ። ብዙ ሰዎች የጥይት ተኩስ ሰምተዋል ። ይህ ሲገመገም የካፕላን እሰቃዮች እንዲሞት በጥይት መቱት ለማ ለት አያስደፍርም ። ኮማንዶዎቹ ስለ አላገኙዋት ታዲያ አሁን ያለችው የት ነው ?

ጆን መክለር የት እንደገባ አይታወቅም ። ለእርሱ የትኛውም ዓለም ክፍት እንደነበረ በርግ አውቋል ። ከዚያ ዓይነቱ ቦታ መጥፋቱ ግን በመጠኑም ቢሆን ግራ የሚያጋባ ነበር ። ሪቻርድስንን የገደለው እርሱ ይሆን ? እንደገደለው በርግ ጥርጣሬ አድሮበታል ። ምክንያቱም ገብቶታል ። በሌላው ሲ-130 አውሮፕላን የተሳፈሩት ሐኪሞች ሪቻ ርድስን የተተኮሰበት ከቅርብ በመሆኑ ጥይቱ በስቶት ስለ ሄደ አለመ ገኘቱን አስታውቀዋል ።

ነገር ግን መክለር አሁን የት ነው ? ምናልባት በአሁኑ ጊዜ ባግ ዳድ ውስጥ ወደ አለው የአሜሪካ አምባሲ ሄዷል ወይም ሂላ ውስጥ ባለው የጸጥታ ወኪላቸው አማካኝነት አገሩ ገብቷል ። አንድ ቀን በቤ ይሩት አሜሪካ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ሁልጊዜም እንደሚያደርጉት ታሪኩን መዝግቦ ይገኝ ይሆናል ።

በርግ ደህና አድርጎ ያዕቆብ ሆስነርን ያውቀው እንደሆነ ሻለቃ ባርቶክ ለመረዳት ስለ ፈለገ “ እውነተኛው መሪ እርሱ ነበር?” ብሎ ጠየቀው ።

“በአብዛኛው እርሱ ነበር ። “ያዕቆብ ሆስነር የት ነው ? ምናል ባትም ሞቶ ይሆናል ። ምንጊዜም ቢሆን ሊያውቁት ይችሉ ይሆን ?”

ያዕቆብ ሆስነር አስቸጋሪና ምሥጢሩ የማይታወቅ ሰው ነበር ። አሁንም መጥፋቱ ወይም መሞቱ ውስብስብ ስሜትን አስከትሏል ። እዚያ የቀረው በአህመድ ሪሽ ላይ ያለውን የግል በቀል ለመወጣት ብቻ አልነበረም ። ከዚያ የበለጠ ነገር ነበር ። መሞት ፈልጓል ። መኖ ርም ፈልጓል ። ሆስነር ባለፉት ጊዜያትም ሆነ አሁን እስከ መጨረሻው አሸናፊ ነበር ። ወደ ኢየሩሳሌም ቢመለስ ግን እንደሆስነር ያለ ኩሩ ሰው ሊመልሳቸው ለማይፈልጋቸው ጥያቄዎች ይጋለጥ ነበር ።

ሚሪያም በርንስቴይን አገጭዋን በጉልበቶቿ ላይ አንተርሳ ተቀ ምጣለች ። ከእርስዋ ቀጥሎ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በሽራ ወንበር ላይ ተቀምጧል ። በአጠገቡዋ የተቀመጡ ጥቂት ሰዎች ያንጐላጁ ነበር ። ጥቂቶቹ ደግሞ እንቅልፍ ከአልወሰዳቸው ጋር ያለማቋረጥ ያወሩ ስለነበሩ ወሬውን ለመስማት ያልፈለጉ ወታደሮች ተነስተው ወደ ኋላ ሄዱ ። ክፍሉ በሙሉ በሰው ጠረንና በመድሀኒት ሽታ ተሞል ቷል ።

ከእርስዋ ራቅ ብሎ ወደ ተቀመጠው ዴቪድ ቤከር በምትመለ ከትበት ጊዜ ቢነቃም በሃሳብ የተዋጠ መስሎ ታያት ። ብዙ ጀግኖች ነበሩ ። ነገር ግን አንድ ብቸኛ ጀግና ቢኖር በእርግጥ ዴቪድ ቤከር ነበር ብላ አሰበች ። ካፒቴን ጊይዝና የመቶ አለቃ ስርተን ስለሙያው የሰ ጡትን አድናቆት የሞላበት አስተያየት ተቀብሏል ። የሚደነቅ ጀግና አብራሪ ነበር ። በመሆኑም በኢየሩሳሌም ውስጥ በከፍተኛ ከበሬታ ይቀ በሉታል ። ትኩር አድርጋ ስትመለከተው ብቸኛ መስሏል ።

ሚሪያም በርንስቴይንን ትኩር አድርጐ እየተመለከተ በነበረበት ጊዜ ከሃሳቡ በመባነን አሁን ወደ አለበት ሁኔታ እየተመለሰ ነበር ። ፈገግታ ሊሰጣት ሞከረ ። ይሁን እንጅ ፈገግታ መስጠቱ ስህተት እንደ ነበረ ስለተገነዘበ ጉሮሮውን አፍታቶ በለሰለሰ አንደበት “ የጻፍነው ማስታወሻ ጠፋ” አላት ።

ሚሪያም ፈገግታ ከአሳየችው በኋላ “ የእኔ ማስታወሻ ምናልባ ትም በቦምብ ጋይቶ ይሆናል ” አለችው ።

“በጣም ጥሩ ጸሐፊዎች አይደለንም ።”

“ቁም ነገሩ ሃሳቡ ነው ። ”

“አዎን” ብሏት ፈገግ ከአለ በኋላ ዓይኖቹን ጨፈነ ።

ሚሪያም እንቅልፍ እያሸለበው እንደ ነበረ አየችው ። እርስዋም ዓይኖቿን ጨፈነች ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ወደ እርስዋ ዘመም ብሎ ትከሻዋን ጉነጥ አደረጋት ። “ ስናርፍ የምንሰጠውን መግለጫ ማዘጋ ጀት አለብን ። በዚህ ያጋጠመንን ችግር ከሰላሙ ስብሰባ ጋር ለይተን ማየት አለብን ፡ ይህ ከመድረሱ በፊት የነበረውን ስሜትና ፍላጐት እንደገና ማነሳሳትና መገንባት አለብን ” ብሎ እጁን ከአወዛወዘ በኋላ “ ይህ ከመሆኑ በፊት - - - ” አላት ።

ሚሪያም በርንስቴይን ቀና ብላ ከተመለከተችው በኋላ “ ከአንተ ጋር ወደ ኒውዮርክ አልሄድም ” አለችው ።

ሚኒስትሩ በመገረም “ ለምን አትሄጅም ” አላት ።

"በስብሰባው አላምንበትም ።"

"ይህ አጉል መጃጃል ነው ።"

ትከሻዋን ከፍና ዝቅ አደረገች ። ያዕቆብ ሆስነር የመከራት ምን ነበር ? ሁልጊዜም ቢሆን እርሱ ስለስብሰባው ጥርጣሬ ነበረው ። ነገር ግን ሄዳ ኃይለኛ ተደራዳሪነቷን እንዲያውቁ እንድታደርጋቸው ሳይመከራት አልቀረም ። አረቦቹ ይህን እንደ ከባድ ድክመት አድርገው ቢቆጥሩት ደጋግመው ማሰብ ይኖርባቸዋል ።

"በአንድ ወይም በሁለት ቀን ውስጥ ልዩ ስሜት ያድርብሻል ሚሪያም ።"

"ምናልባት ይሆን ይሆናል ።" መከራከር አልፈለገችም ። ከወደ ኋላዋ በኩል ኤሸር አሮንስን ከኤርምያስ የሚከተለውን ስታነብ ድምጽዋን ሰማቻት "--- እኔ ከሩቅ አገር አድንሃለሁና ዘርሽንም ከተማረከበት አገር ። ያዕቆብም ይመለሳል ---" ዘር ? የእርሱ ዘር ? የእርሱ ዘር ከባቢሎን ውጭ ? ሳታውቀው በእጅዋ ሆድዋን ዳሰሰች ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ እንደገና እጁን ዘርግቶ ነካ ከአደረጋት በኋላ "እንደነገርኩሽ ወደ ኋላ ቀርቶ አሽባሎቹ ወደእኛ እንዳይመጡ መከላከል ማድረጉ ራሱን ወዳድ አለመሆኑንና እኛን ለማዳን ሲል ሕይወቱን አሳልፎ ለመስጠት ቆርጦ መነሳቱን ነው" አላት ።

ሚሪያም ራስዋን አስገድዳ ፈገግታ ከሰጠችው በኋላ "ለሌሎች ማሰብ ? ያዕቆብ ሆስነር የዚህን ቃል ትርጉም አያውቀውም ። ፍጹም ራሱን ወዳድ በመሆን ያደረገው መሆኑን አረጋግጥልሃለሁ ። ለምር መራ መቅረብ አልፈለገም - የቦምቦቹ በኮንኮርዶቹ ውስጥ መገኘት ብቻ ሳይሆን በአመራርም ጭምር - በእርሱ አዛዥነት ስለሞቱት ሁሉ ለሚቀርብለት ጥያቄ መልስ መስጠት አልፈለገም ። በፍርድ ቤት ውስጥ በተከሳሽ መቆሚያ ውስጥ ሆኖ መልስ ከሚሰጥ መሞቱን የሚመርጥ ይመስለኛል" ብላው እንደገና ፈገግ ለማለት ብትሞክርም እንባዋ በጉንጮቿ ላይ እየተንከባለለ ይወርድ ነበር ።

አሪኤል ዌይዝማን እንደገና ክንድዋን እየደባበሰ "ምናልባት አልሞተም ይሆናል" አላት ።

በዚህ ጊዜ ስለ ባልዋ አስታወሰች ። ስለባልዋ እንደዚህ ዓይነት እየነገሩዋት ቆይታለች ። በአውሮፓ ውስጥ ብዙ አይሁዳውያን ባሎቻቸውንና ሚስቶቻቸውን ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን ከዚህ ሁሉ ዓመታት በኋላ ለማግኘት በግልጽ ማስታወቂያዎች ላይ የሚያወጡ አሉ ። ወደ አሪኤል ዌይዝማን በተመለከተች ጊዜ ከምንጊዜውም የበ

ለጠ በፊትዋ ላይ የማይረሳው መለዋወጥ አየ ። ጥርሷን ገጥማ "ሞቷል፥ ሞቷል ፣ ራሱን ለአደጋ አጋልጦ በመስጠቱ ያሳዝናል " ብላ ፊትዋን በክንዶቿ መካከል አድርጋ አለቀሰች ።

ሁለቱም ሞተዋል ። እነእርሱም ሆኑ አባቷ ፣ እናቷ፥እህቷ ወይም እንጀራ አባቷ የተቀበሩበት ቦታ ባለመታወቁ እየሄደች መካነ መቃብራቸውን እንኳን መጐብኘት አልቻለችም ። ልትደርስበትና ልትዳስሰው የምትችለው ባለመኖሩ ሁኔታው እነዚህን ሰዎች ፈጽሞ በመሬት ላይ እንዳልኖሩ ዓይነት ሆኖአል ። ስለ እነእርሱ የሚዛመድ ነገር ቢኖር እንኳን እርስዋ ከምትኖርበት አገር ውጭ በአውሮፓና በባቢሎን ነበር ። አዕምሮዋ ሊረጋጋ አልቻለም ። በሃዘንም ተዋጠች ፣ ተለበለበችም ። ያዕቆብ ሆስነር እሪ በይ ፣ ጩኺ ፣ ሥቃይሽን ዓለም ይወቅልሽ ብሏት ነበር ። ይህን ብታደርግም እንኳን ሀዘንዋን ሊያነጥፍላት አይችልም ። ሆስነር እንደሚያፈቅራት ባይነግራት ኖሮ ስሜታዊ ወይም በራስ አለመተማመን ወይም ይህን መሰል ሁኔታን ለማሳየት ነበር በማለት ነገሩን ልታቀለው ትችል ነበር ።

አንድ ሰው በትከሻዋ ላይ ነካ ስለአደረጋት ቀና ብላ ስትመለከት አንድ ወጣት የአውሮፕላኑ ሠራተኛ ፈገግ ብሎ አቀልቁሎ እየተመለከታት አንድ የታጠፈ ወረቀት " የራዲዮ መልእክት" ብሎ ሰጣት ።

ለትንሽ ጊዜ ትኩር አድርጋ ከተመለከተችው በኋላ ከፍታ " አፈቅርሻለሁ ፣ ቴዲ " ተብሎ በእርሳስ የተጻፈውን አነበበች ።

ወጣቱ " መልስ አለው ? " ብሎ ጠየቃት ።

በእንባ የተሞሉ ዓይኖቿን በሁለት እጆቿ ጠርጋ ከአቅማማች በኋላ " መልስ አያስፈልገውም ፣ አመሰግናለሁ " አለችው ።

በነገሩ የተደነቀው ሠራተኛ ተመልሶ ሄደ ።

ሚሪያም ጽሑፉን እንደገና ከተመለከተች በኋላ በኪስዋ ውስጥ አስቀመጠችው ። ስለ ቴዲ ላስኮቭ ከማሰብዋ በፊት የያዕቆብን ዘር ማየት ይኖርባታል ።

ቴዲ ላስኮቭ በባቢሎን ላይ የመጨረሻ በረራ በአደረገበት ጊዜ ከነፋስ ፣ ከአሸዋና አንድ አህያ ጋልቦ ወደ ሰማይ እየተመለከተ ሜዳውን አቋርጦ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ከሚሄድ ሰው በስተቀር ሌላ ምንም ዝር የሚል አልነበረም ። በኡማ ከጭቃው ቁልል አጠገብ በመስመጥ ላይ የነበረውን ሰማያዊና ነጭ ቀለም ያለውን ትልቅ ኮንኮርድ አየ ። መንደሩና አውሮፕላኑ በ2500 ዓመት ውስጥ በተለያዩ አገሮች የተደረገውን ዕድገት በአንጻራዊ ሁኔታ የሚያንጸባርቁ ነበሩ ።

ላስኮቭ ዞሮ ወደ ምዕራብ በማምራት የሥልጣኔ ምንጭና የምር ኮኛ መሬት ከሆነው ከባቢሎን በሻሚያ በረሃ ላይ ወደ ኢየሩሳሌም በረረ ። ወደ ሰማይ እየመጠቀ ሲሄድ ለጦርነት እንዲያገለግሉት ተዘ ርግተው የነበሩት ክንፎች እንዲተጣጠፉ አደረጋቸው ።

በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ወደ ሁለቱ ሲ- 130 ግዙፍ አውሮፕ ላኖች ጐን መጣ ። ሚሪያም ስለ ፍቅሩ በግልጽ ለላከላት መልዕክት መልስ ባለመስጠቷ መጠነኛ ሀፍረት ተሰማው ። ይሁን እንጂ በአው ሮፕላኑ ውስጥ ለተሳፈሩት ሰዎች መልካም ስሜቱን ማሳየት እንደ ነበረና ለሞራልም ጥሩ መሆኑን አውቋል ። በሁለቱ አውሮፕላኖች መካከል ኃይሉን ቀንሶ በመብረርና በአካባቢያቸው በመዞር እጁን አወ ዛወዘላቸው ። በሲ-130 ውስጥ በየመስኮቶቹ አቅጣጫ የነበሩት ሁሉ እጃቸውን አውለበለቡለት ።

ሚሪያም በርንስቴይን ከአቅማማች በኋላ ከሌሎቹ ጋር ተነስታ በመስኮቶቹ መካከል እየተመለከተች ተዋጊው አውሮፕላን እንደገና ዞሮ በሄደበት ጊዜ ብትዘገይም እጅዋን አወዛወዘች ። ከተቀመጠችም በኋላ እንቅልፍ ስለ ወሰዳት ዴቪድ ቤከር ብርድ ልብስ አለበሳት ።

ላስኮቭ በግዙፎቹ አውሮፕላኖች አካባቢ መዞሩን አቁሞ ከፍ ብሎ በመብረር ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ ሄደ ። ቀድሞ በመድረስ ታጥ ቦና የሲቪል ልብሱን ለብሶ በባቢሎን አደራ የተበከሉትን ሰዎች በአ ውሮፕላን ማረፊያ እንደሚቀበላቸው ተስፋ አደረገ ። በዘመናዊው ዓለም ውስጥ የመለዋወጥ ፍጥነት መርከበኞች እየተመለከቱ አቅጣጫ ቸውን እንደሚያዩለት የሰሜን ኮከብ በአንድ ቦታ ተወስኖ የቆመ ሳይ ሆን በማይታመን ሁኔታ እየተለዋወጠ መጥቷል ። ሚሪያም በባቢሎን ውስጥ ተለውጣ እንደሆን በማለት አሰበ ። እርስዋ ግን የምትለወጥ አይደለችም ። ለአብዛኛው ነገር ግልጽና ሃሳበ ጽኑ ስለሆነች ለውጥ ላታሳይ ትችላለች ። ሁለት ፍቅረኞች ተለያይተው ሲገናኙ ሊሆን እንደ ሚችለው ሁሉ ያልተለመደና የቀዘቀዘ ስሜት ሊኖር ይችላል ።

የአረቦቹና የእሥራኤሎቹ መልዕክተኞች በተባበሩት መንግሥ ታት የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ በኒውዮርክ የሰዓት አቆጣጠር ከምሽቱ አራት ሰዓት ተሰብስበዋል ። በየአሥራ አምስት ደቂቃው ከባግዳድና ከኢየሩሳሌም መግለጫዎች ይሰጡ ነበር ። በመጨረሻ የደረሰው መግ ለጫ ለመልዕክተኞቹ የሚያበረታታ ዜና ነበር ።

ከመካከላቸው አንዱ አንድ ጠርሙስ መጠጥ ከፍቶ ለእያንዳን ዳቸው ቀድቶ አደለ ። በክፍሉ ውስጥ ብዙ ንግግር አልነበረም ። ነገር ግን ሁኔታዎች እየሰመሩ በመምጣታቸው በሁለቱ መልዕክተኞች

መካከል የነበረውን ሁኔታ እያለሰለሰው ስለመጣ በእያንዳንዳቸው ላይ የእምነትና የወዳጅ ነት መንፈስ እየጨመረ መጣ ። አንድ የአረብ መልዕክተኛ "የምሥራች !" ብሎ ጽዋውን ስለ አነሳ እያንዳንዱ መል ዕክተኛ ጽዋውን በማንሳትና ጣፋጩን የወይን ጠጅ በመጉንጨት ደስ ታውን ገለጸ ።

በተባበሩት መንግሥታት የእርቁ የእሥራኤል ቋሚ መልዕክተኛ ሳኦል ኤዘር የአሁኑ ቡድን በሕይወቱ በስብሰባ ላይ ከአየው ሁሉ የበለጠ አኩሪ የሰው ኃይል የተሰባሰበበት እንደነበረ ተገነዘበ ። በአደረጉት ጥረት ምክንያት የሚመጡት የአረብና የእሥራኤል መልዕክተኞች ሁሉ ነገር ስለተመቻቸላቸው አረንጓዴ ምንጣፍ ላይ እንደሚደርሱ አመነ ። ተነስቶ ወደ ሌላው ክፍል በመሄድ ለሚመጡት የእሥራኤል መልዕክተኞች በከተማው መሃል በሚገኝ ሆቴል የማረፊያ ቦታ እንዲ ያዝላቸው በስልክ አስመዘገበ ።

ሺር ጃሹቡ የአውሮፕላኑ እይታ ከዓይኑ እንደጠፋ አህያውን ወደ ምሥራቅ አዙሮ ሜዳውን አቋርጦ ወደ ኡማ ሔደ ። በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ በኤፍራጥስ ወንዝ ጊዜ የማይሽረውና የማይለውጠው እጹብ ድንቅ የሆነ ሁኔታ አየ ።

ከባቢሎን እንደገና ቀሪዎች ተመልሰው ሄዱ ። ቀሪዎች እንደገና በባቢሎን ውስጥ ለመቆየት መረጡ ። ሺር ጃሹብ በኢየሩሳሌም ውስጥ ትልቅ ደስታ እንደሚሆን ገመተ ። በኡማ ውስጥ ግን ያልተረጋገጠ ሁኔታ ነበር ። የኡማ መንደር ሰዎችበሕይወት ባይኖሩ በባግዳድና በሂላ ያሉ ወገኖቻቸው ይኖራሉ ። እግዚአብሔር አንድ ቀን የልጆቹን መፈ ታተን አቁሞ የተበታተኑት ሁሉ ተሰብስበው ከጽዮን ውጭ መኖሩ አስፈላጊ የማይሆንበት ጊዜ መጥቶ ወደ ሀገራቸው ይመለሳሉ ።

ፀሐይ በባቢሎን ተራራዎች ላይ ወጣች ። በዚህ ጊዜ ሺር ጃሹብ የኤፍራጥስን ወንዝ ተሻግሮ የሚሄድና በባቢሎን ፍራሾች ላይ በግልጽ ሊሰማ የሚችል የሚከተለውን መዝሙር አሰማ - "እኔም ከመንጋዬ የቀሩትን ከአወጣኋቸው አገር ሁሉ አሰበስባለሁ ። ወደ እርሻቸውም እመልሳቸዋለሁ ፤ ያፈራሉም ፤ይበዛሉም ። ጠበቆችም አስነሳላቸዋ ለሁ ። ይጠብቋቸዋልም ። ደግሞም አይደነግጡም ፤ አይፈሩምም ። ከእርሳቸውም አንድ አይጐልም ይላል እግዚአብሔር ።"

ተፈጸመ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ዓመተ ምሕረቶች
እንደ አውሮፓዊያን አቈጣጠር ናቸው ።